አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ
የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ  ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት

በ

ደነቁ አበረ

ሰኔ፣ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሐ ግብር


# የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት፡በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት

ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ


በ

ደነቀ አበረ

ለ

ዓለሙ ካሣዬ (ዶ/ር)

የኔዓለም አረዶ (ዶ/ር)


ሰኔ 2017 ዓ.ም

አዲስ አበባ

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የትምህርት እና ቋንቋዎች ጥናት ኮሌጅ

የአማርኛ ሥነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር

# የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት

ለአማርኛ ሥነ ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

በፎክሎር ለፍልስፍና ዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ የቀረበ

በ

ደነቁ አበረ

የፈተና ቦርድ አባላት

<u>የአማካሪዎች</u>

ስም________________________ ፊርማ______________ ቀን__________

ስም________________________ ፊርማ______________ ቀን__________

የውጭ ፈታኝ ስም______________ ፊርማ______________ ቀን__________

የውስጥ ፈታኝ ስም______________ ፊርማ______________ ቀን__________

# መታሰቢያነቱ

ይህ የዶክትሬት ዲግሪ ጥናት፣ በድንገት በሞት ላጣኋት ለውድ እህቴ፣ ለብርቱካን አበረ (እሙዬ) መታሰቢያ ይሁን ። እህቴ፣ በዚህ የትምህርት ጉዞ ከጅምሩ አንስቶ በሀሳብና በእንክብካቤ ሳትለየኝ፣ የድካሜና የጭንቀቴ ተጋሪ ሆና የስኬቴን ቀን ለማየት በታላቅ ጉጉት ትጠባበቅ ነበር። ፍጻሜውን ባታይም፣ ላደረገችልኝ ነገር ሁሉ ይህ ሥራ የዘላለም ምስክሬ ነው።

# አጠቃሎ


ይህ ጥናት “የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት” በሚል ርዕስ ተካሂዷል፡፡ ዐቢይ ዓላማው የወላይታን ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት መተንተን ነው፡፡ በብሔረሰቡ በዓይነትና በአገልግሎት በርካታ የቤት ዓይነቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት ለሰዎች መኖሪያነት የሚያገለግሉ የባህላዊ ቤቶች አሠራር ተተኳሪ ተደርገዋል ፡፡ ጥናቱ ዓይነታዊ የምርምር ዘዴን የተከተለ ሲሆን፣ መረጃዎችም በወላይታ ዞን ከሚገኙ አምስት ወረዳዎች ውስጥ ከአሥር ቀበሌዎች በዓላማ ተኮር ናሙና እና በጠቋሚ ናሙና ከተመረጡ ሰባ መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል፡፡ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችም ምልከታ፣ ቃለመጠይቅና የቡድን ውይይት ሲሆኑ፣የተገኙት መረጃዎችም በማህበራዊ ትምህርት፣ በመዋቅራዊ ተግባራዊነት፣በሥነ ትእምርትና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳቦችሃሳቦች ታግዘው በገላጭ መንገድ ተተንትነዋል፡፡ የጥናቱ ውጤት እንደሚያሳየው የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ዙፋ፣ሜሹዋ፣ ጉላንታናቡራሪያ በመባል በአራት አይነት ይከፈላሉ፡፡ ቤቶቹ ከውጭ ሲታዩ ተመሳሳይነት የሚታይባቸው ቢሆኑም ውስጣዊ አሰራራቸው የተለያየ ነው፡፡ በተለይ ‘ጉላንታ’ የተሰኘው ቤት አሰራሩ የዘጠኙን ፕላኔቶች አቀማመጥ መከተሉ ልዩ ያደርገዋል፡፡ የቤት አሰራር ሂደት ከቦታና ከግንባታ ቀናት መረጣ (የጨረቃን ዑደት ጨምሮ) ጀምሮ በብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ፈቃድና ቡራኬ የሚከናወን፣ ከፍተኛ ማኅበራዊ ተሳትፎ የሚታይበትና በሥርዓት የሚመራ ነው፡፡ የቤቱ ክብ ቅርጽ ‘ሙሉነትን’፣ ለጌጥነት የሚያገለግሉት ቀለማት ደግሞ የብሔረሰቡን ማንነትን የሚወክሉ ሲሆን፣ በተለይ ዋናው ምሰሶ ከማኅበራዊ ክብር፣ ከመንጻት፣ከእምነትና ከሥርዓተ ጾታ ጋር የተያያዙ ጥልቅ ትርጉሞችን ይዟል፡፡ በተጨማሪም የግንባታው ሂደት በባህላዊ ዘፈኖች፣ በምሳሌያዊ ንግግሮችና በምርቃቶች የታጀበ ነው፡፡ በብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ወቅት የብሔረሰቡ ተጠሪዎች፣አባቶች፣እናቶች፣ወጣቶች፣የቤተሰቡ አባላት፣ጎረቤቶች፣ ዘመዶችና የአካባቢው ህዝብ ቀደም ሲል በተሰጣቸው የሥራ ድርሻ መሰረት የተለያዩ ስራዎችን በመከወን የቤቱን ባለቤቶች ያግዛሉ፡፡ ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት የምሰሶውን ጫፍ ለሚጠርቡ ባለሙያዎች፤የበር ጉበንና መግቢያውን ለሚያስውቡ ግድግዳ ለሚሰሩ፣ጣሪያ ለሚሰሩ ባለሙያዎች የተለያዩ ምግቦች የሚቀርቡ ሲሆን ይህም ግድግዳ ሲሰሩ ከአደንጓሬና ከበቆሎ ንፍሮ ይዘጋጃል፣ጣሪያ የሚሰሩ ሰዎች በሙያው እውቀት (ልምድ) የገበዩ ሰዎች ስለሆኑ ባጭራ፣ፋጫታ የሚባሉ የተለዩ በወላይታ ባህል መሰረት የክብር ምግቦች ይዘጋጅላቸዋል፡፡ ለምግቡ ማቅረቢያ አንድ ወጥ የሆነ እርጥብ ኮባ በተቀመጡት ሰዎች ፊት ለፊት ወለሉ ላይ ይነጠፋል፤ ምግቡም የሚቀርበው በዚሁ ኮባ ላይ ሲሆን የኮባው እርጥብ መሆን ትርጓሜም ነገር ሁሉ መልካም ይሁን፣ሁሉም እርጥብ ይሁን እንደ ማለት ነው፡፡ የቤት አሰራር እውቀት ተስተላልፎን በተመለከተ አባቶች ልጆችን አስከትለው በመሄድ ቀለል ያሉ ስራዎችን እንዲሰሩ በማድረግና በማሳየት እውቀቱን እንዲለምዱ ያደርጓቸዋል፡፡

ምንም እንኳ በአሁኑ ወቅት ባህላዊ የሳር ቤቶች ቁጥር እየቀነሰ ቢመጣም፣ በምትካቸው የሚሰሩ ዘመናዊ ቤቶች የድሮዎቹን ውስጣዊ አቀማመጥና አንዳንድ ቁሶች ይዘው ተገኝተዋል ፡፡ በተጨማሪም ቆርቆሮ ቤቶቹ ሳር ቤቶቹ ውስጥ ያሉ ቁሶችን ይዘው የቀጠሉ ሲሆን ሳር ቤቶቹ ባህላዊውን አሰራር ተከትለው የተሰሩ ቢሆንም ቆርቆሮ ቤቶች ውስጥ የሚገኙ ቁሶችን በመያዛቸው ሳር ቤቶቹ ላይ የቀጠለውንና የተለወጠውን ከጥናቱ መረዳት ተችሏል፡፡ በዚህ መሰረት የወላይታ ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ ከመኖሪያነት ባለፈ ከሥነ ፈለክ (ከፕላኔቶችና ከጨረቃ)፣ ከማኅበራዊ አደረጃጀትና ከፍልስፍና ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው መሆኑን ጥናቱ አሳይቷል ፡፡ በመሆኑም ይህ ከሥነ ፈለክ ጋር ያለው መስተጋብር በሌሎች ተመራማሪዎችና ተቋማት ሰፊ ጥናት እንዲደረግበት ይመከራል ፡፡

# ምስጋና

በቅድሚያ፣ ይህ ጥናት እንዲጀመርና ለፍጻሜ እንዲበቃ በሁሉም አስቸጋሪ ጊዜያት ከፊት እየቀደመ ከጎኔ ያልተለየውን የድንግል ማርያም ልጅ ኢየሱስ ክርስቶስን ከልብ አመሰግናለሁ ።

ይህ ጥናት ተጀምሮ እስኪጠናቀቅና ለዚህ ደረጃ እንዲበቃ ውድ ጊዜያቸውንና እውቀታቸውን ሰውተው፣ አቅጣጫ እያሳዩና የጎደለውን እያሟሉ ላገዙኝ ለውድ አማካሪዎቼ ዶ/ር ዓለሙ ካሣዬ እና ዶ/ር የኔዓለም አረዶ ያለኝ ልባዊ ምስጋና ላቅ ያለ ነው ።

የዚህ ጥናት ዋልታና ማገር የሆኑትን የመስክ መረጃዎችን ያለ መሰልቸትና ያለመሰሰት በቅንነት በማቅረብ፣ እንዲሁም ሌሎች ቁልፍ መረጃ አቀባዮችን በመጠቆም ላገዝከኝ አቶ እያሱ ገጃቦ ምስጋናዬ ከፍ ያለ ነው ። የብሔረሰቡን ጥልቅ እውቀትና ፍልስፍና የሚመለከቱ ለጥናቱ የሚሆኑ መረጃዎችን በቅንነት ያለ መሰልቸትና ያለመሰሰት በማካፈል በእጅጉ ላገዝከኝ ቀሲስ ወልደማርያም ልሳኑ፣ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ። በመቀጠል የብሔረሰቡን ጥልቅ እውቀት በማካፈል ለጥናቱ መሠረት የሆናችሁኝ ቁልፍ መረጃ አቀባዮቼ ፦ አቶ ሃይሌ ሀርጎ፣ አቶ ዲዳዬ ቃልቶሬ፣ አቶ ኦልኬ ታንቱ፣ አቶ ታደሰ ኮይራ፣ አቶ ኡኩሌ ጥላሁን፣ አቶ መለሰ ያያ፣ አቶ አማኑኤል አይዴ፣ አቶ ባሞሬ አንጁሎ፣ አቶ ኤርሚያስ ጎበና፣ ዲ/ን ሲሳይ ኩማ እና መምህር መቶሳል ላበረከታችሁልኝ ዝርዝር መረጃና ትብብር ምስጋናዬ ከልብ የመነጨ ሲሆን እንዲሁም ተጨማሪ መረጃዎችን በመስጠት የረዳችሁኝ አጋዥ መረጃ ሰጪዎቼም ምስጋናዬ ይድረሳችሁ!

የባህልና ቱሪዝም ቢሮ እና የቅርስ ጥናት ቢሮ ሰራተኞች ላደረጋችሁልኝ ትብብር አመሰግናለሁ በተለይ ደግሞ ከወላይታ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ አቶ ሲሳይ መጻሕፍትን በማዋስ፣ ከቅርስ ጥናት ቢሮ አቶ እዩኤል መጻሕፍትን በማዋስ እና መረጃዎችን በመስጠት ላደረጋችሁልኝ እገዛ አመሰግናለሁ ።

የባህልና ቱሪዝም ቢሮ ከሀሳብ በዘለለ መጻህፍትን በማዋስ በተለይ አቶ ሲሳይ ላደረጋችሁልኝ አስተዋጽኦ ምስጋናዬ ከልብ ነው ። ከቅርስ ጥናት ቢሮ አቶ እዩኤል ለሰጠኸኝ መረጃዎችና ገንቢ አስተያየቶች በጣም አመሰግናለሁ ።

ለትልመ ጥናት ፈተና ወቅት የጥናቱን አራት ምዕራፎች አንብበህ ገንቢ አስተያየት ስለሰጠኸኝ ዶ/ር የወንዶሰን አውላቸው አመሰግናለሁ! በመቀጠል ለትልመ ጥናት ፈተና ወቅት የጥናቱን አራት ምዕራፎች አንብበህ ገንቢ አስተያየት በመስጠት፤አስፈላጊ መጻህፍትን በማዋስ፤ከምርምሩ ስራ ጋር ተያይዞ ግራ የገቡኝን ጥያቄዎች በጠየቅኩህ ቁጥር ያለመሰልቸት በቅንነት ሥራዬ እንዲጠራና ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን ላደረግክልኝ ሙያዊ ድጋፍ ዶ/ር ጥላሁን ተሲላ በጣም አመሰግናለሁ እግዚአብሔር ይስጥልኝ!

የጥናቱን ሰባት ምእራፎች አንብበሽ ለሰጠሽኝ እውቀት፣ገንቢና ምሁራዊ አስተያየት ዶ/ር ፍሬህይወት ባዩ አመሰግናለሁ ።

ዶ/ር ዘላለም ተፈራ ለደረጃ ማበልፀጊያ ፈተና ወቅት በተለያዩ የጥናቱ ምዕራፎች ላይ ምሁራዊ አስተያየቶችና ገንቢ ሂሶች በማቅረብ አቅጣጫ በመጠቆም፤ከምርምሩ ስራ ጋር ተያይዞ ግራ የገቡኝን ጥያቄዎች በመመለስና በማበረታታት ሥራዬ  ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን እና እዚህ እንዲደርስ ላደረጋግክልኝ  ሙያዊ ድጋፍ ምስጋናዬ የላቀ ነው ፡፡

በሀሳብ ከማበረታታት ጀምሮ አስፈላጊውን መረጃ በመስጠት ያገዛችሁኝ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ስነጽሑፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል መምህራን(መምህሮቼ) ምስጋናዬ ይድረሳችሁ ከደረጃ ማበልፀጊያ ፈተና በኋላ ለተነሱ አስተያየቶችና ጥያቄዎች አስፈላጊ መረጃዎችን ከመስጠት ባሻገር ገንቢ አስተያየቶችን በመስጠት በቅንነት ያበረታቸኸኝ የሥራ ባልደረባዬ መስፍን መኩሪያ እጅግ አድርጌ አመሰግንሃለሁ ፡፡

ዶ/ር ተመስገን በየነ ውድ ጊዜህን ሰውተህ የጥናቱን ሰባት ምዕራፎች በማንበብ ሙያዊ እውቀትህን በማካፈል ላደረግክልኝ አስተዋጽኦ ከልቤ አመሰግናለሁ! አቶ እሸቱ ማቴዎስ ለትምህርት የሚዋሰኝን ሰው አጥቼ ተስፋ በቆረጥኩ በመጨረሻዋ ሰዓት ደርሰህልኝ በቅንነት ዋስ ሆነህልኝ እንድማር  ላደረግክልኝ አስተዋጽኦ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ፡፡

አቶ ቸኮል ወርቁ ጸሐፊና የኮምፒውተር ባለሙያ በአርትኦት እና በፕሪንት ስራ ያለመሰልቸት በማገዝ ውጤታማ እንድሆን ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ስላደረግክልኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

ለጥናቱ መሳካት የገንዘብና የትምህርት እድል ድጋፍ ላደረጉልኝ ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ እና አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ምስጋናዬን አቀርባለሁ ፡፡

የወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የወላይትኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍና ትምህርት ክፍል መምህራን ቀሲስ ወልደማርያም ልሳኑ፣አቶ አለማየሁ ዋሩ፣አቶ አድማሱ ቱማቶ፣ወ/ሮ አየለች ተ/ማርያም፣ ወ/ሮ አሪፉ ኮራ፣ወ/ሮ አልማዝ አንጁሎ መረጃ ከመስጠት ባሻገር አስቸጋሪ የትርጉም ስራዎችን በመፍታት ስላገዛችሁኝ ከልቤ አመሰግናችኋለሁ ፡፡ እንዲሁም በስም ያልጠቀስኳችሁ፤ በሀሳብ ከጎኔ ላልተለያቸሁኝ የወላይትኛ ቋንቋና ሥነ ጽሑፍና ትምህርት ክፍል መምህራንና ጸሐፊ አመሰግናለሁ !

ሜሮን ዓለማየሁ (ሜሪዬ) እና ባለቤቷ ዶ/ር ባሳዝን ፋንታሁን የመስክ ስራዬን ጨርሼ አዲስ አበባ በቆየሁባቸው ጊዜያት ውስጥ በፈለግኩ ሰዓት ሁሉ ቤታችሁን ከፍታችሁ ሥራዬን በአግባቡ እንድሠራ ስላገዛችሁኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ! በተለይ ሜሪ ጓደኛዬ ዘወትር በመጠየቅ አይዞሽ በርቺ በማለት በሀሳብ ከመደገፍ ባሻገር በአርትኦት ስራ በማገዝ ለሰጠሽኝ ገንቢ አስተያየቶች እጅግ አድርጌ ከልቤ አመሰግንሻለሁ !

በዚህ ረጅም የምርምር ጉዞ ውስጥ የቤተሰቦቼ ድጋፍ ልዩ ነበር ፡፡ እናቴ እቴቴ ቸርነት፣ ሁሌም ስለሥራዬ መጨረሻ በመጨነቅና በመጸለይ ለሰጠሽኝ እናታዊ ፍቅርና እንክብካቤ ረጅም እድሜና ጤና እመኝልሻለሁ ፡፡ ወንድሞቼ አብዮት፣ ስንታየሁ፣ ፍጹም፣ ሀፍታሙ፣እንዲሁም ከሀሳብና

ከሞራል ባሻገር በአርትኦት ሥራ ላገዘከኝ ካሳሁን (ቀሲስ)፤ እህቶቼ ምህረት (ውሮ) እንዲሁም ዓለምፀሐይ(እኑ) የመስክ ሥራዬን ጨርሼ አዲስ አበባ በቆየሁባቸው ጊዜያት ቤትሽን እንደቤቴ ክፍት አድርገሽ ለሥራዬ በሚመች ሁኔታ በማሰናዳት ስላገዝሽኝ፤ላሳያችሁኝ ሞራላዊና ቁሳዊ ድጋፍ አመሰግናለሁ ። እህቴ ብርቱካን አበረ (እሙዬ)፣ የዚህን ጥናት ጅማሬ እንጂ ፍጻሜውን ለማየት ባትታደይም፣ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ ስጨነቅ አብረሽኝ ስትጨነቂ፣ ሳምሽ አብረሽኝ ስታምሺና ስትንከባከቢኝ የነበረውን ውለታሽን አልረሳውም ። ለዚህ ሥራ መሳካት ያደረግሽው አስተዋጽኦ በልቤ ውስጥ ህያው ነው፤ ሁሌም ሳነሳሽና ሳመሰግንሽ እኖራለሁ ።

ጓደኛዬ ዳጊ (ዶ/ር ደግሰው ጥላሁን) በትምህርታዊ ውይይታችን እንዲሁም አይዞሽ ባይነትሽ ሁሌም ከጎኔ ስለሆንሽ እጅግ አመሰግናለሁ ! ጓደኛዬ አልማዝ ፈረደ(አልሚ) ይሄን ትምህርት ከጀመርኩበት ጊዜ ጀምሮ ሁሌም አይዞሽ በርቺ ከማለት ባሻገር ከመስክ መልስ አዲስ አበባ በቆየሁባቸው ጊዜያት ቤትሽ መስራት(ማንበብ) በፈለግኩ ቀናት ለምርምር ስራው በሚመቸኝ መንገድ ቤትሽን ለኔ ክፍት በማድረግ ስላገዝሽኝ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ ። እንዲሁም ማኪዳ(ማኩ) አብድረህማን በዚህ ረጅም የትምህርት ጊዜ በርቺ በማለት በሀሳብ ስለደገፍሽኝ ከልብ አመሰግናለሁ!

የክፍል ጓደኞቼ ፣እየሩሳሌም ነጋና ታዲዮስ ቦቢሮ ስለአብሮነታችሁና ስለድጋፋችሁ አመሰግናለሁ!በተለይ ሙሉፀሐይ ገነቱ ከሀሳብ በዘለለ ባደረግናቸው ሙያዊ ውይይቶች፣መማማሮች ፤ የመረጃ ልውውጦች፤እንዲሁም ለነበረን መልካም ግንኙነቶች፣የክፍል ቆይታ እጅግ አድርጌ አመሰግናለሁ!

የጂአይኤስ ባለሙያ ዶ/ር ጳውሎስ እና የስነ ህዝብ ቢሮ ሰራተኛ የሆንከው አቶ ደስታ በቅንነት ለሰጣችሁኝ መረጃ ከልቤ አመሰግናለሁ!

ይህን ጥናት በማከናውንበት ወቅት አጋዥ መጻህፍትንና የምርምር ስራዎችን ፈልገው በመስጠት ፤በአግባቡ እንዳነብ ለረዱኝ ትሁቶቹ የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የኢትዮጵያ ጥናት እና ምርምር ተቋም ቤተ መጽሐፍት ሠራተኞች (አይኤስ) ላደረጋችሁልኝ ትብብር ምስጋናዬ ከልብ ነው ።

በአጠቃላይ ስማችሁን ያልጠቀስኳችሁ በዚህ የምርምር ሥራ ወቅት በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ለዚህ ጥናት አስተዋጽኦ ያደረጋችሁ ወዳጆቼና ጓደኞቼ ምስጋናዬ ይድረሳችሁ!

# ማውጫ

ይዘት ገጽ


አጠቃሎ ..... I

ምስጋና..... II

ማውጫ..... V

የሰንጠረዥ ዝርዝር ..... VIII

የፎቶግራፎች ዝርዝር ..... VIII

የወላይትኛ ቃላት አቻ አማርኛ ትርጉም..... VI

ምዕራፍ አንድ..... 1

1.መግቢያ..... 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ..... 1
1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች ..... 8
1.3. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች ..... 10
1.4. የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች..... 10
1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት ..... 11
1.6. የጥናቱ ወሰን ..... 11
1.7. የጥናቱ ውስንነት..... 12
1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች..... 13
1.9. የጥናቱ አደረጃጀት..... 15

ምዕራፍ ሁለት..... 16

ክለሳ ድርሣናት ..... 16

2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ ..... 16
*2.1. 1. የቁሳዊ ባህል ምንነትና ምድብ በፎክሎር..... 16*
*2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች..... 18*
*2.1.3. የቁሳዊ ባህል ጥናት አድማስ እና አስፈላጊነት ..... 18*
*2.1.4. የቁሳዊ ባህል አጥኚዎች የትኩረት ነጥቦች ..... 19*
*2.1.5. የሀገረሰባዊ ምህንድስና ምንነት..... 21*
*2.1.6. የቤት ምንነት..... 22*
*2.1.7. የባህላዊ ቤት ምንነት..... 23*
*2.1.8. ባህላዊ ቤትና ቅርጽ..... 24*
2.1.8.1. ባህላዊ ቤት..... 24
2.1.8.2. የባህላዊ ቤት ቅርጽ ..... 25
*2.1.9. ለውጥ እና ቀጣይነት..... 25*
2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ ..... 30
*2.2. 1. የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ..... 30*
*2.2.2. የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ..... 34*
*2.2.3. የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ..... 36*
*2.2.4. የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ..... 38*
*2.2.5. የንድፈ ሀሳቦች ትስስር ..... 38*
2.3. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት (ክለሳ)..... 39

2.3.1. የባህላዊ ቤት አሰራር፣ አይነቶች እና የመስሪያ ግብአቶች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች.... 40
2.3.2. ባህላዊ የቤት አሰራርን ከስነ ቃል ጋር አያይዘው ያጠኑ ...................................... 52
2.3.3. ባህላዊ ቤትን ከእደ ጥበብ ጋር በማጣመር የተጠኑ ጥናቶች.................................. 52
2.3.4. ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብን በተመለከተ በአፍሪካ እና በተለያዩ የውጭ ሀገራት የተሰሩ ጥናቶች ........................................................................................................ 56

ምዕራፍ ሦስት.................................................................................................................... 65

ጥናቱ ሥነ ዘዴ.................................................................................................................... 65

3.1. የጥናቱ ዓይነት........................................................................................................... 65
3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ...................................................... 66
3.2.1. ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ....................................................................................... 66
3.2.2. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች.......................................................................................... 66
3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ...................................................................................... 67
3.3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሮች እና መቼቶች............................................................ 72
3.3.2. የተጠኚ አካባቢዎች እና የተጠኚዎች የናሙና አመራረጥ........................................... 72
3.3.3. የመረጃ አደረጃጀት.................................................................................................. 73
3.3.4. የአጋዥ መሳሪያዎች አጠቃቀም ............................................................................... 74
3.3.5. የምርምር ሥነ ምግባር.............................................................................................. 75
3.4. የመስክ ተሞክሮና መረጃ የተሰበሰበባቸው ጊዜያት ...................................................... 76
3.5. የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች............................................................................... 78
3.6. የምዕራፎች አደረጃጀት .............................................................................................. 80

ምዕራፍ አራት.................................................................................................................... 83

4.1. የጥናቱ አካባቢ እና የወላይታ ብሔረሰብ አውዳዊ ዳራ.................................................. 83
4.2. የአካባቢው ስያሜ ..................................................................................................... 83
4.3. የወላይታ ህዝብ አሰፋፈር............................................................................................ 86
4.4.የወላይታ ህዝብ እና ስርጭት ....................................................................................... 89
4.5. የወላይታ ዞን መልክአምድራዊ አቀማመጥ ................................................................. 89
4.6. የህዝቡ ቋንቋ እና ኃይማኖት....................................................................................... 90
4.6.1. የህዝቡ ቋንቋ........................................................................................................... 90
4.6.2. የህዝቡ ኃይማኖት..................................................................................................... 91
4.7.የህዝቡ መተዳደሪያ፣ መሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎት .................................... 92
4.8. የወላይታ ብሔረሰብ ታሪካዊ ቅርስ፣ ቱሪዝምና ባህላዊ ተቋማት ..................................... 92
4.9. የወላይታ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት............................................................................ 92
ምዕራፍ አምስት................................................................................................................. 95
የወላይታ ብሔረሰብ ቤት ውክልና እና ባህላዊ የቤት አይነቶች ......................................... 95
5.1. የቤት ምንነትና ውክልና በወላይታ ብሔረሰብ............................................................... 95
5.2. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አይነቶች................................................................. 97
5.2.1. ዙፋ (Zuufaa)...................................................................................................... 101
5.2.2. ሜሾ ቤት (Meeshsho keettaa) ......................................................................... 103
5.2 .3. ጉላንታ (Gulantta)........................................................................................... 105
5.2.4. ቡራሪያ ቤት (Buraariyaa keettaa).................................................................. 108

ምዕራፍ ስድስት................................................................................................................ 110

6.1. የቤት ሥራ ሰበብ እና ቅድመ ቤት ስራ ...................................................................... 111
6.2. ለቤት መስሪያ የሚውል የአፈር አይነት ...................................................................... 114
6.3.የወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት የመሬት መለኪያ አይነቶች ..................................... 124

6.4. በወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት ግንባታ የምሰሶ ሥራ ............................................ 132
6.5.የምሰሶ ውክልናና በስራው ላይ የሚቀርቡ ዘፈኖች ..................................................... 136
6.6. ምሰሶ የሚቆምበት ጉድጓድ ውስጥ የሚጨመሩ ነገሮች ትዕምርት ............................. 151
6.7. የበር መቃን ሥራ............................................................................................... 157
6.8. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት የክዳን ሥራ.......................................................... 162
6.9. በወላይታ ብሔረሰብ ቤት የሚሰራባቸው እለታትና ወራት ትርጓሜዎች...................... 163
6.10. የወላይታ ባህላዊ ቤት አሰራርና የጨረቃ ኡደት ..................................................... 166
6.11. በወላይታ የቤት አሰራር ውስጥ የህዝቡ የሥራ ድርሻዎች ....................................... 171
6.12. ከቤት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምርቃቶች፤ባህላዊ ዘፈኖችናምሳሌያዊ አነጋገሮች፤ ..... 183
6.13. የወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት ሙያተኞች እና የቤት አሰራር እውቀት ተስተላልፎ193
6.14. ድህረ ቤት ሥራ ክዋኔዎች .................................................................................. 196

ምዕራፍ ሰባት ........................................................................................................... 201

7.1. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ቅርጽ ...................................................... 201
7.2. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ቅርጽና ትርጓሜ...................................... 203
7.3. የወላይታ ብሔረሰብ የቤት ቅርጽ ክብነትና ትርጓሜ................................................... 206
7.4.የወላይታ ባህላዊ ቤት መገንቢያ ግብዓቶች ............................................................... 213
7.5. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ................................. 223
7.6. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ማስዋቢያ ግብአቶች............................................... 224
7.7. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ጉልላት(ጉምቦ) ሥራና ትርጓሜው ......................... 231
7.8. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት የቀለም ምርጫና ትርጓሜ ...................................... 234

ምዕራፍ ስምንት .......................................................................................................... 240

በወላይታ ባህላዊ የቤት አሰራር ውስጥ የታዩ የለውጥና የቀጣይነት ገጽታዎች ................. 240

ምእራፍ ዘጠኝ ............................................................................................................. 260

ማጠቃለያ ግኝትና ይሁንታ ....................................................................................... 260

9.1. ማጠቃለያ ........................................................................................................... 260
9.2.ግኝቶች ................................................................................................................ 261
9.3. ይሁንታ ............................................................................................................. 269

ዋቢ ጽሑፎች ............................................................................................................... 271

አባሪዎች .................................................................................................................... 283

## የሰንጠረዥ ዝርዝር

ሰንጠረዥ1፡- የህገረሰባዊ አምልኮ ስያሜዎች ........ 91
ሰንጠረዠ2 ፡- ለጉላንታ ባህላዊ ቤት ሥራ የሚሆኑ ቁሳቁሶች ........ 118

### የ ፎቶግራፎች ዝርዝር

ፎቶ1፡- የኢትዮጵያን፣የወላይታ ዞንን እና ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎችን የሚያሳዩ ካርታዎች ........ 84
ፎቶ2፡- አዲሱ የደቡብ ኢት/ያ ክልሎችን የሚያሳይ ካርታ ........ 85
ፎቶ3፡- የኢትዮጵያ ክልሎችን የያዘ ካርታ ........ 88
ፎቶ4፡- ቃለመጠይቅ ከመረጃ አቀባይ ጋር ........ 100
ፎቶ5፡- የዙፋ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ ........ 102
ፎቶ6፡- ሜሹዋ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ገጽታ ........ 104
ፎቶ7፡- የወላይታ ሜሹዋ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ ........ 104
ፎቶ8፡- የወላይታ ጉላንታ ቤት ውጫዊ ገጽታ ........ 107
ፎቶ9፡- የጣሪያ ስራው ጅማሬ መሬት በእንጨቶች ላይ ........ 125
ፎቶ10፡- ባለሙያዎች የጣሪያ ስራ በመስራት ላይ ሆነው የሚያሳይ ፎቶግራፍ ........ 126
ፎቶ11፡- ያለቀ የጣሪያ ሥራ ........ 129
ፎቶ12፡- ባህር ዛፍ በጣሪያው ሲቀለበስ ........ 130
ፎቶ13፡- ባህርዛፍ ከተቀለበሰ በኋላ የተጠናቀቀ ጣሪያ ........ 131
ፎቶ14፡- ምሰሶውን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሲያዘጋጁ የሚያሳይ ........ 138
ፎቶ15 ፡- ምሰሶ ተቆርጦ ተቀምጦ የሚያሳይ ........ 142
ፎቶ16፡- ምሰሶውን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሲያዘጋጁ የሚያሳይ ........ 142
ፎቶ17፡- ምሰሶውን የማቆም ሂደትን የሚያሳይ ........ 143
ፎቶ18፡- ምሰሶውን የማቆም ሂደትን የሚያሳይ ........ 145
ፎቶ19፡- በአግድም መዝጊያውን ለመቆለፍ የሚያገለግለው ኮልቢያ (Kolbbiyaa) ........ 158
ፎቶ20፡- ቋሚና አግዳሚ መዝጊያ እንጨቶችን ማስገቢያ ሂራቁዋ (Hiraquwaa) ........ 158
ፎቶ21፡- የበር መቃን ሥራ ........ 159
ፎቶ22፡- ባለሙያዎች በመቃንና በጉበን ሥራ ላይ ........ 161
ፎቶ23፡- ሙቾ (Muchchuwa) ባህላዊ ምግብ ........ 178
ፎቶ24፡- ተቀቅለው የቀረቡ ቦዬ፣ስኳር ድንችናድቡልቡል ድንች ........ 179
ፎቶ25፡- ለመስተንግዶ የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጥ ........ 180
ፎቶ26፡- የቡና ቅጠል መድሐኒት ........ 196
ፎቶ27፡- በቤቱ ጓሮ፣ከጎንና ከፊት ለፊት የሚተከሉ አትክልቶች ........ 197
ፎቶ28፡- ቡና እና እንሰት ........ 199
ፎቶ29፡- በመሰራት ላይ ያለ የወላይታ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ቅርጽ ........ 202
ፎቶ30፡- ያለቀ የወላይታ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ገጽታ በምስል ........ 202
ፎቶ31፡- የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ገጽታ ምስል ........ 203
ፎቶ32፡- ለክብነት አስረጂ የሆኑ የወላይታ ባህላዊ የቤት ቁሶች ........ 209
ፎቶ33፡- ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣መቀመጫዎችና ባህላዊ የገበጣ መጫወቻዎች ቅርጽ ከቤቱ ክብነት ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ ለማሳየት አስረጂ ........ 210
ፎቶ34 ፡- ለአጨዳ የደረሰ ሰንበሌጥ ........ 216
ፎቶ35፡- ከውጭ በኩል ለጌጥ የሚደረግ ........ 217
ፎቶ36፡- የወላይታ ባህላዊ ቤቶች መገንቢያ ሀማካ በፎቶ ........ 218
ፎቶ37፡- የማገሮቹ ማሰሪያዎች ወፍቾ በፎቶ ........ 218

ፎቶ38፡- ተገምዶ ቀለም የተነከረ ቃጫ ........................................................................................ 219
ፎቶ39፡- ለቤት ሥራ የሚውሉ መሣሪያዎች ................................................................................. 220
ፎቶ40፡- ለቤት መስሪያ የሚውሉ ቁሳቁሶች ................................................................................ 223
ፎቶ41፡- ሳሎንና ጓዳ የሚለይበት ሳጠራው ጥግና በሳጠራው አናት ላይ ለውበትና ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶች የሚያሳይ ........................................... 227
ፎቶ42፡- የፈረሶችና የበቅሎዎች ማደሪያ ሲሆን ለቤቱ ውበት አስረጂነት የቀረበ ................. 228
ፎቶ43፡- የፈረሶችና የበቅሎዎች ማደሪያ ሲሆን ለቤቱ ውበት አስረጂነት የቀረበ ................. 230
ፎቶ44፡- ከእንጨት ተጠርቦ የተሰራ ጉልላት ፎቶ ........................................................................ 233
ፎቶ45፡- የወላይታ ህዝብ የሚጠቀማቸው ቀለሞች.......................................................................... 236
ፎቶ46፡- ወላይታ የሀዴ አይነቶች ..................................................................................................... 239
ፎቶ47፡- ቆርቆሮ ቤት ሆኖ በከፊል ባህላዊ ቁሶችን ያያዘ.................................................................. 244
ፎቶ48፡- የወላይታ ዙፋ ቤት ውጫዊ ገጽታ ...................................................................................... 245
ፎቶ49፡- ባህላዊ የስጋ መስቀያ ኮጫ...................................................................................................... 247
ፎቶ50፡- የጭቃ ምርግ የተደረገበት ባህላዊ ቤት.............................................................................. 248
ፎቶ51፡- ለዚህም አስረጂ የጉላታ ባህላዊ ቤት ቀጥሎ ቀርቧል ፡፡ ......................................... 249
ፎቶ52፡- የመሰረት ስራ እና በጅምር ያለ ቤት.................................................................................... 254
ፎቶ53፡- ያለቀ የጉላንታ ቤት ፎቶ ውጫዊ ......................................................................................... 255
ፎቶ54፡- በባህላዊና በዘመናዊ ግብዓቶች የተሰራ ቤት ..................................................................... 255
ፎቶ55፡- ባህላዊ ቤቱ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኂላ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች በጋራ ሲመገቡ........................................................................................................................................ 258
ፎቶ56፡- የምረቃ ስነስርዓት ላይ የሀገር ሽማግሌዎች ባህላዊ ልብስ ሀዴ ለብሰው ንፍሮ በመመገብ ባህላዊ መጠጥ በጋራ ቦርዴ እየጠጡ................................................................................ 259

# የወላይትኛ ቃላት አቻ አማርኛ ትርጉም

| የወላይትኛው ቃል | የአማርኛው አጠራር/አነባበብ/ | የአማርኛው ትርጉም |
|---|---|---|
| Arssa | አርሳ | መኘታ |
| Boniyaa | ቦኒያ | በጋ |
| Baraataa | ባራታ | በረከት |
| Cociya | ጮጪያ | የእሳት ምድጃ |
| Debushsha | ድቡሻ | የህብረተሰብ ተጠሪዎች |
| Eqa Gallassa Gallassa | ኤቃ ጋላሳ | ገደ ቢስ እለት |
| Giffaatta | ጊፋታ | የዘመን መለወጫ |
| Gumbbuwa | ጉምቡዋ | ጉልላት |
| Goccillaa | ጎጪላ | መርገጪያ |
| Ichchashiyaa | ኢቻሺያ | ጥር |
| Ifittaa | ኢፊታ | መዝጊያ በር |
| Kaaraa | ካራ | ጣሪያ |
| Madabaa | ማዳባ | መቀመጫ |
| Mehiyaa zazaluwa | ሜሂያ ጋጣታ | የከብቶች በረት |
| Para gaxatta | ፓራ ጋጣታ | የፈረስ በረት |
| Pouwa | ፖኡዋ | ብርሀን |
| Quruxuwaa | ቁሩጡዋ | ጓዳና ሳሎን መክፈያ |
| Qolluwa | ቆልሉዋ | ጓዳ |
| Qoriya | ቆሪያ | የበር ጉበን |
| Qosilettaa | ቆስሌታ | የበር መቃን |
| Shidhdhaa | ሺዳ | ዋልታ |
| Sussaa | ሱሳ | ወፍቾ |
| Shaagaa gallassaa | ሻጋ ጋላሳ | ገዳም እለታት |
| Tuussaa | ቱሳ | ምሰሶ |
| Wiygiyaa | ዊይጊያ | ሳሎን |
| Xettaa | ጤታ | መቶ |
| Xuumma | ጡማ | ጨለማ |
| Zazaluwaa | ዛዛሉዋ | የላሞች በረት |
| Zanddiidaa | ዛንዲዳ | ቀጫጭንማገር |

# ምዕራፍ አንድ

# 1. መግቢያ

ይህ ጥናት የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራርን በመመርመር፤የቤት ምንነቱንና ውክልናውን፤ ባህላዊ የቤት አይነቶችን፤የቤት አሰራር ሂደቱን፤ የቤቱን ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጽ የቤት መገንቢያ ግብዓቶችን፤ማህበረ-ባህላዊ ተዛምዶን ተንትኖ አቅርቧል ። በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱ ወሰን፣ የጥናቱ ውስንነት፣ የጥናቱ አስፈላጊነት፣ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ተካተዋል ። የጥናቱ ዳራ ቀጥሎ ቀርቧል ።

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

ለሰው ልጆች አስፈላጊና መሰረታዊ ፍላጎቶች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የመኖሪያ ቤት ነው ። ኢትዮጵያ የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ህዝቦች አገር ናት ። እነዚህም ህዝቦች የራሳቸው የሆነ የማንነታቸው መገለጫ የሆኑ እሴቶች ያላቸው ሲሆን ይህም እንደየአካባቢው ብሔረሰብ ባህል በዕለታዊ ኑሮ የሚገለገሉባቸውና ማህበራዊ ኑሯቸውን የሚያቀኑባቸው ናቸው ። ከነዚህ መካከል ባህላዊ የቤት አሰራር አንዱ ሲሆን ይህም እንደየአካባቢው የተለያየ ነው ።

በኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል በተዘጋጀው መዝገበ ቃል ውስጥ ‹‹ቤት ከእንጨት፣ ከድንጋይ ወይም ከጡብ……የሚሰራና ለተለያየ አገልግሎት ለሰው፣ለእንስሳት መኖሪያ፣ለዕቃ ማስቀመጫ የሚውል ዙሪያው በግድግዳ ላዩ በጣሪያ የተከለለ መጠለያ፣ጎጆ፣ሳርቤት፣ ቆርቆሮ ቤት፣ ህንጻ…. የሚይዝ ነው ›› (የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማዕከል ፣1993፣ ገ. 241) ።

ከቀረበው ማብራሪያ ለቤት የተሰጠው ብያኔ ከመስሪያ ቁሶች ወይም ግብአቶች ዓይነትና ቤቶች ከሚሰጡት ልዩ ልዩ ተግባር አንጻር የተቃኘ ነው ። ለሰው ልጆች መሰረታዊ ፍላጎቶች ከሚባሉት ውስጥ አንዱ የሆነው የመኖሪያ ቤት የራሱ የሆነ የአጀማመር ታሪክ አለው ።

(Adedeji, 2011) እንዳብራራው ‹‹የሰዎች አኗኗር ተመዝግቦና ተሰንዶ ከመቀመጡ በፊት (Pre-history period) የሰዎች አሰፋፈር የማህበረሰቡን ምቾት ከማስጠበቅ፤ፍላጎታቸውን ከማሟላት አኳያ ሳይሆን ከሚመጣው ጠላት እና አውሬ እራሳቸውን ከመከላከል አንጻር የሚመሰረት ነበር›› (p. 3) ።

የጥንታዊ ሰዎች የአሰፋፈር ሁኔታ ላይ የተለያዩ ምክንያቶች ቢገለጹም በዋናነት ሰዎች በእለት ተለት አኗኗራቸው ውሃን በቀላሉ ለማግኘት ፤ ከውሃው ዳርቻ የሚገኘውን በንጥረ ነገር የዳበረ ጭቃ ወይም

ደለል ለመጠቀም ፤ ውሃውን ለመስኖ ተጠቅመው ሰብል ለማምረት ሲሉ ኑሯቸውን በውሀ አካላት ዳርቻ መስርተው ይኖሩ እንደነበር መዛግብት ያሳያሉ ። ለማሳያ በኢንዱ ወንዝ አቅራቢያ የሞሂንጆ ዳሮ ሰፈራ ፤በኤፍራጥስ እና ጤግሮስ መካከል የሜሶፖታሚያ ስልጣኔ፤ እንዲሁም በናይል ወንዝ አቅራቢያ የግብጻውያን ስልጣኔ የሚጠቀስ ነው (Kennedy, 2019) .

መሬት በጥንታዊ ሰዎች የአሰፋፈርና የአስተራረስ ሁኔታ ላይ ሌላው አይነተኛ ገጽታ ነበር ። አርኪዎሎጂስቶች እሳተ ጎሞራ ባለባቸው አካባቢዎች ባደረጉት ጥናት ብዙ የጥንታዊ ሰዎች የአሰፋፈር ሁኔታዎችን የሚያሳዩ መረጃዎችን በማግኘታቸው ምክንያት ጥንታዊ ሰዎች እሳተ ገሞራ ወደሚበዛባቸው አካባቢ መስፈራቸው ለም የሆነ የእርሻ መሬትን ለማግኘት እንደሆነ ለማሳየት ሞክረዋል ። ስለሆነም ለጥንታዊ ሰዎች ከውሃ ቀጥሎ የመኖሪያ ስፍራን ለመምረጥ ለም አፈር ሁለተኛ መሰረታዊ ምክንያታቸው እንደነበር ተጠቁሟል (Tan et al., 2023).

Adriana (2001) እንደሚገልጸው፣የጫካ ወይም የደን መኖርም ለመስፈር አንዱ የጥንታዊ ሰዎች ምክንያት እንደነበር አርኪዎሎጂስቶች በነዚህ አካባቢዎች ያገኙትን የሰዎች ቅሪት አካል እንደ ማስረጃ አቅርበዋል። ጥንታዊ ሰዎች በጫካ አካባቢ በመኖር እንጨቱን ለቤት መስሪያነት፣የዱር እንስሳቱንና ፍራፍሬዎችን ለምግብነት፤የእንስሳቱን ቆዳ እንዲሁም የዛፍ ልጥ ለአልባሳትነት ይጠቀሙ እንደነበርም ጠቁመዋል ። እንደ አጠቃላይ ጥንታዊ ሰዎች ትክክለኛና ምቹ የመኖሪያ ስፍራን ለመምረጥ ከቦታ ቦታ ይዘዋወሩ የነበር ቢሆንም ይህ እንቅስቃሴያቸው በተፈጥሮአዊ ተግዳሮቶች ምክንያት ማለትም ሰፋፊ የውሀ አካላት፣የቦታዎች በረሃማነት፣እንዲሁም የተራሮች ሁኔታ እንቅስቃሴያቸውን ይገታ እንደነበርም ጠቅሰዋል ፡፡

በድንጋይ ዘመን፣ በግምት ከ2.5 ሚሊዮን ዓመታት በፊት፣ ጥንታዊ ሰዎች በዋሻ፣ በአነስተኛ ጎጆ እና በዛፍ ሥር ይኖሩ ነበር ። ምግባቸውንም በአደንና ፍራፍሬዎችን በመለቃቀም ያገኙ ነበር ። እነዚህም ሕዝቦች ከድንጋይና ከአጥንት የተሠሩ መሣሪያዎችን በመጠቀም አእዋፋትንና የዱር እንስሳትን ያድኑ ነበር (Kennedy, 2023, p. 2) ።

በኋለኛው የድንጋይ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ10,000 እስከ 8,000 ዓ.ዓ. ገደማ) የነበሩ ሰዎች፣ ትናንሽ የድንጋይ መሣሪያዎችን፣ አጥንትንና እንጨትን በማሾል የሠሯቸውን እንደ ጦርና ቀስት ያሉ መሣሪያዎችን ይጠቀሙ ነበር ። በመሆኑም፣ ሰዎች በወንዞችና በሌሎች የውሃ አካላት አቅራቢያ መጠለያ በመሥራት የዘላንነት ሕይወት ይኖሩ ነበር (Stanislawski, 1973) ።

በአዲሱ የድንጋይ ዘመን (ከክርስቶስ ልደት በፊት ከ8,000 እስከ 3,000 ዓ.ዓ. ገደማ) ጥንታዊ ሕዝቦች ከአደንና ፍራፍሬ ለቃሚነት ወደተረጋጋ ሕይወት ተሸጋገሩ ። ይህም የሆነው በእርሻ ላይ በመሰማራት ጥራጥሬ እህሎችን በማምረትና እንስሳትን በማርባት ነው ። ለዚህም እንደ መጥረቢያና ማረሻ ያሉ የተሻሻሉ መሣሪያዎችን ይጠቀሙ ነበር ። በዚህም ምክንያት በአስተራረስ ዘዴ፣ በመሣሪያ አሠራር፣ በቤት ግንባታ፣ እንዲሁም በልብስ አሠራርና በሸመና ጥበባቸው ላይ ከፍተኛ መሻሻል ታይቷል (Adriana, 2001)።

ጥንታዊ ሰዎች ውሃና ምግብ ፍለጋ ከቦታ ቦታ ይንቀሳቀሱ እንደነበር ቢታወቅም፣ ከዘላንነት ወደ ቋሚ የሰፈራ ሕይወት እንዴት እንደተሸጋገሩ የሚያሳይ በቂ ማስረጃ አልተገኘም ። ይሁንና አንዳንድ ተንታኞች የሰፈራ አቀማመጥ ምርጫቸው ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ጥቅሞችን ታሳቢ ያደረገ እንደሆነ ይገልጻሉ ።

የተጠኚው ብሔረሰብ የመጠለያ አሠራር ታሪካዊ ጅማሮ ከጥንታዊ ሰዎች የመጠለያ አሠራር ጋር እንደሚዛመድ ጥናቶች ያመለክታሉ (Kennedy, 2023, p. 2)። በተለይም ከወላይታ ሕዝብ ጋር በተያያዘ የሚከተለው መላምት ተቀምጧል ፡-

የወላይታ ሕዝብ በወንዞች ዙሪያ መስፈር የጀመሩት በአሮጌው፣ በመካከለኛው እና በአዲሱ የድንጋይ ዘመን አካባቢ ሳይሆን አይቀርም ። የወላይታ ሕዝብ ታሪካዊ መነሻው ኪንዶ ዲዳዬ አካባቢ ባሉት ዋሻዎች ሲሆን፣ በጦርነት እና በተለያዩ መንገዶች እየተስፋፉ ሄደዋል (ፋንጨ እና ኢዮብ, 2006, pp. 45-46)

ይህ የሰፈራ ሁኔታ ለሰው ልጆች ሥልጣኔ መሠረት ጥሏል ። ሰዎች በአንድ አካባቢ መኖር መጀመራቸው ከእንስሳት ጋር አብሮ የመሰደድ ልማዳቸውን አስቀርቶ፣ ለአዳዲስ ግኝቶች ትኩረት እንዲሰጡ አስችሏቸዋል ። በመሆኑም፣ በአንድ ቦታ ተወስኖ መኖር የሰው ልጅ የእድገት ደረጃ ቁልፍ ማሳያ ነው ። በጥንት ዘመን እርሻ ዋነኛ የመስፈሪያ ምክንያት የነበረ ሲሆን፣ በዘመናችን ግን እንደ ሃይማኖትና ባህል ያሉ ጉዳዮች ሰዎች በአንድ ቦታ እንዲሰፍሩ ከሚያደርጉ ዋነኛ ምክንያቶች መካከል ይጠቀሳሉ (Stanislawski, 1973)።

የማንኛውም ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር በአካባቢው ከሚገኙ የተፈጥሮ ሀብቶች ጋር የተቆራኘ ነው ። ይህም ማለት፣ ለግንባታ የሚያገለግሉ ቁሳቁሶችና የአሰራር ዘይቤዎች እንደየአካባቢው

ይለያያሉ ። ለምሳሌ፣ በደጋማ አካባቢ የሚኖር ማህበረሰብ የሚሰራው ቤት፣ በቆላማ ከሚገነባው ቤት በዓይነትም ሆነ በአሰራር ይለያል ። ስለዚህም ብሔረሰቡ በአካባቢው የሚገኙ ነገሮችን በመጠቀም ያንፃል፤ይገነባል ።

የቤት አሰራር በአካባቢ ብቻ ሳይሆን በጊዜ ሂደትም ለውጦችን ያስተናግዳል ። ምሁራን እንደሚገልጹት፣ የመጠለያ አይነቶች የራሳቸው የሆነ የአጀማመር ታሪክ ያላቸው ሲሆን፣ በየዘመኑም የተለያዩ የዕድገት ደረጃዎችን አልፈዋል ። ይህንንም ሂደት በሚከተለው መልኩ ያስረዳሉ።

የመጠለያ ታሪካዊ ለውጥ በበርካታ ደረጃዎች ውስጥ አልፏል ። እንደ Sherif and Sabry (2000) ገለጻ፣ የመጀመሪያው የተፈጥሮ መጠለያ ዛፎች ነበሩ ። የጥንት ሰዎች በዛፎች ላይ በመጠለል ከፀሐይ፣ ከዝናብና መሬት ላይ ካሉ አውሬዎች ከፊል ጥበቃ ያገኙ ነበር ። ቀጣዩ የተፈጥሮ መጠለያ የነበሩት ዋሻዎች ሲሆኑ ከከፋ የአየር ሁኔታ የተሻለ ከለላ ቢሰጡም ከዱር እንስሳት ጥቃት ሙሉ በሙሉ ለመከላከል አዳጋች ነበሩ ። በመሆኑም የሰው ልጅ ወደ ሦስተኛው ደረጃ ማለትም ወደ ሰው ሠራሽ መጠለያዎች ተሸጋገረ። መጀመሪያ ላይ እንደ ድንጋይና የዛፍ ቅርንጫፎች ያሉ ቀላል ቁሳቁሶችን በመጠቀም መሠረታዊ ግንባታዎችን ያከናውን ነበር ። ይህ ሂደት ሰዎች የተሻሉ ግንባታዎችን ለመስራት የሚያግዙ ቀላል መሣሪያዎችን እንዲፈጥሩና እንዲያውቁ አስችሏቸዋል ። ቀስ በቀስም እንደ ግዙፍ የድንጋይ ንጣፎች፣ የእንስሳት አጥንቶችና ቆዳዎች ያሉ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ይበልጥ የተራቀቁ መዋቅሮችን መገንባት ጀመሩ (Sherif and Sabry, 2000) ።

ከዚህ በኋላ በተለያዩ ሀገራት የተለያዩ የመጠለያ አይነቶችን መገንባት ተጀመረ ። ለአብነት ይህ የዕድገት ሂደት በጥንታዊ ስልጣኔዎች ውስጥ ይበልጥ ጎልቶ ይታያል ። Elattar (2009) ይህን ሂደት ሲያስረዳ

- የጥንት ግብፃውያን በፀሐይ የደረቁ ጡቦችን በመጠቀም ጠፍጣፋ ጣሪያ ያላቸው ቤቶችን ይገነቡ ነበር ።
- የጥንት ግሪኮች ደግሞ ዝናብና በረዶን በቀላሉ የሚያንሸራትቱ፣ በድንጋይ የተሰሩ ጣሪያ ያላቸው ቤቶችን ፈጥረዋል ።
- ሮማውያን የግሪኮችን ቴክኖሎጂ በማሻሻል፣ በቀዝቃዛ የአየር ንብረት ውስጥ ቤቶችን ለማሞቅ የሚያስችል ሥርዓት ዘርግተዋል ። ይኸውም በቤቱ ወለል እና በግድግዳ ውስጥ የሸክላ

ቱቦዎችን በማሳለፍ በውስጣቸው ሙቅ አየር ወይም ውሃ እንዲዘዋወር በማድረግ ነበር (Elattar, 2009)፡፡

በመካከለኛው ዘመን የአውሮፓ የቤት አሰራር ይበልጥ የተራቀቀ ሆነ ፡፡ Hendriks (2000) እንደሚገልጸው፣ ጀርመናውያን እና ስካንዲኔቪያውያን በከባድ የእንጨት ማዕቀፎች ላይ የተመሠረቱ ሕንፃዎችን ይገነቡ ነበር ፡፡ በዋና ዋናዎቹ የእንጨት ምሰሶዎች መካከል ያሉትን ክፍተቶች በሸክላ በመሙላት ጠንካራ ግድግዳዎችን ይፈጥሩ ነበር ፡፡ እነዚህ ሕንፃዎች ውስብስብና በርካታ አገልግሎቶችን የሚሰጡ ሲሆን፣ ለፈረሶች ማረፊያ፣ ለመሣሪያዎች ማከማቻ፣ ለማእድ ቤት፣ ለመመገቢያ አዳራሽ፣ አልፎ ተርፎም ለጦር እስረኞች ማቆያ ያገለግሉ ነበር (Hendriks, 2000) ፡፡ በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች አውሮፓውያን በድንጋይ ወይም በጡብ መሠረት ላይ በከፊል ከእንጨት የተሰሩ ቤቶችን መገንባት ጀመሩ ፡፡

ከኢንዱስትሪ አብዮት በኋላ የግንባታ ቴክኖሎጂ ከፍተኛ ለውጥ አስመዝግቧል ፡፡ በዚህም አውሮፓውያን ደግሞ በድንጋይ ወይም በጡብ መሠረት በግማሽ እንጨት የተሠሩ ቤቶችን መገንባት የጀመሩ ሲሆን የዛፍ ግንዶችን በቤቶቹ ጥግ ላይ በማስቀመጥ ቤቱን ለመደገፍ ጠንካራ የእንጨት ምሰሶዎች ጥቅም ላይ እንዲውሉ አድርገዋል ፡፡ የመጠለያ ግንባታ ቀስ በቀስ እንደ ሲሚንቶና ብረት ያሉ ዘመናዊ ቁሳቁሶችን መጠቀም ጀመረ ፡፡ በዚህም ሰማይ ጠቀስ ሕንፃዎችን መገንባት የተለመደ ሲሆን፣ ለመስታወት የተሰጠው ትኩረት ደግሞ ለህንፃዎች ዘመናዊ ገጽታ እንዲላበሱ አስችሏል (Hourigan and Morassut, 2017)፡፡

በሌላ በኩል የአፍሪካ ባህላዊ የቤት አሰራር ከአካባቢው ቁሳቁሶች ጋር የተቆራኘ ነበር ፡፡ *Ron* (*1999*)[1] እንዳብራራው፣ ቋሚ አጽዋት በሌሉባቸው አካባቢዎች ይኖሩ የነበሩ ዘላን ማህበረሰቦች ከእንስሳት ቆዳና ጸጉር የተሰሩ ድንኳኖችን ይጠቀሙ ነበር ፡፡ በሌሎች አካባቢዎች ደግሞ ከጭቃ የተሰሩ ክብ ቅርጽ ያላቸው ጎጆዎች የተለመዱ ነበሩ ፡፡ በኢትዮጵያም ተመሳሳይ ሁኔታ ይታይ ነበር፤ Gebremedhin (1971) በጥናታቸው እንደገለጹት፣ የጥንት ሰው ሠራሽ መጠለያዎች ከድንጋይና ከዛፍ ቅርንጫፎች የተሠሩ ሲሆን፣ ድንጋዮቹን ከስር በመደርደር የዛፍ ቅርንጫፎቹን ለማቆም ይጠቀሙባቸው ነበር (p. 24)፡፡

[1] .በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀሱት የዘመን አቆጣጠሮች ከአማርኛው ስም በኋላ ያለው በኢትዮጵያ ዘመን አቆጣጠር ሲሆን ከእንግሊዝኛው ስም በኋላ ያለው ደግሞ እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር ነው፡፡

የጥንት የሰው ልጅ መጠለያዎች ከጥቃት መከላከያነት ባለፈ ማኅበራዊ ትርጉም እንዳልነበራቸው Sadhana (2016) ይገልጻሉ ። ይሁንና ይህ የመጠለያ አሰራር በዘመናት ሂደት ውስጥ እየተለወጠና እየተሻሻለ መጥቷል ። የዚህ ለውጥ ተጨባጭ ማሳያ በወላይታ ብሔረሰብ የቤት አሰራር ታሪክ ውስጥ ይንጸባረቃል ።ዘብዴዎስ (2012) እንደሚገልጹት፣ የወላይታ ህዝብ መጀመሪያ ላይ በዋሻ ውስጥ ይኖር ነበር ። ከጊዜ በኋላ የህዝብ ቁጥር መጨመር እና ከሌሎች ነዋሪዎችና ከዱር አራዊት የሚሰነዘረው ጥቃት ሲበዛባቸው፣ ከዋሻ በመውጣት በአካባቢያቸው ከሚገኙ እንጨትና ሰንበሌጥ ቀላል ጎጆዎችን (ደሳሳ ጎጆ) ሰርተው መኖር ጀመሩ ። ይህንንም አሰራር አንዱ ከሌላው እየተማረና እያሻሻለ፣ ከዘመናት ልምድ በመነሳት "ደጎ" በተሰኘ የኅብረት ሥራ ምቹና ውብ ቤቶችን መገንባት ጀመሩ (ዘብዴዎስ፣ 2012፣ ገጽ 401-408) ።

የወላይታ ብሔረሰብን የቤት አሰራር ታሪክ ለመተንተን የቁሳዊ ባህል ጥናት ወሳኝ ነው ። ቁሳዊ ባህል የሰውን ልጅ በቅርሶችና በቁሶች አማካይነት የሚያጠና የትምህርት ዘርፍ ሲሆን፣ በውስጡ የሚመረመሩት ቁሶች ከዕለት ተዕለት ተግባራቸው የዘለለ ትርጉም ያላቸው ሲሆን በቁሶች አማካይነት በውስጣቸው ያለውን ስሜት ትርጉም እንዲኖረው ከማድረግ ባሻገር የአንድ ማህበረሰብ የእውቀትና የአስተሳሰብ መገለጫ ናቸው (Glassie, 1999, p. 42) ። Dorson (1972) እንደሚጠቁሙት፣ የአንድ ማህበረሰብ ቁሶች የባለቤቶቹን ልማድ፣ እምነትና ባህል ያንጸባርቃሉ ። ስለዚህ ቁሶቹን ከሰሪዎቻቸው ጋር አጣምሮ መመርመር የማህበረሰቡን ሁለንተናዊ ማንነት ለመረዳት ያስችላል (p.21) ።

በተመሳሳይ፣ *Glassie,* (1999) ሰዎች በቁሶች አማካይነት ውስጣዊ ስሜታቸውንና አስተሳሰባቸውን እንደሚገልጹ ያብራራሉ (P. 42) ። ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ ታሪክና እምነት አሻራ ይይዛሉ፤ የማህበረሰቡም የእውቀትና የክህሎት ውጤቶች ናቸው። ይህ እውቀትና የአሰራር ክህሎት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፈውም እንደ ማየት፣ ማስታወስና በተግባር መስራት ባሉ መደበኛ ባልሆኑ መንገዶች ነው (Glassie, 1999, P. 10 ) ። ስለዚህ ቤት፣ መሰረታዊ የመጠለያ ፍላጎትን ከማሟላት ባለፈ፣ የማንነት፣ የታሪክና የማኅበራዊ ትስስር ማዕከል የሆነ ቁሳዊ ባህል ነው።

ለዚህ ጥናት መነሻ የሆኑና በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ያተኮሩ ተዛማጅ ጥናቶች ተዳሰዋል ። እነዚህም በዓለም አቀፍ፣ በአፍሪካ እና በኢትዮጵያ የተከናወኑ ጥናቶችን ያካተቱ ሲሆን፣ የተመረጡ ሃያ ያህል ሥራዎች ተፈትሸዋል ።

በዓለም አቀፍ ደረጃ፣ በሰሜን ምስራቅ ህንድ (Chuki, Sarkar, & Kurar, n.d.) እና በቡድሂስት ማኀበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ላይ የተደረጉ ጥናቶች ተጠቃሽ ናቸው ። በአፍሪካ ደረጃ ደግሞ በናይጀሪያ የሀውሳ ማኀበረሰብ የቤት አሰራር ላይ የተሰራ ጥናት ተዳሷል ።

በሀገር አቀፍ ደረጃም በርካታ ጥናቶች ተከናውነዋል ። በተለይም በደቡብ ኢትዮጵያ የተለያዩ ብሔረሰቦች ላይ ትኩረት ያደረጉ ለምሳሌ፣ ግርማ ኪዳኔ(1994) በወላይታ ቤቶች፤ፍቃዱ ገዳሙ(2003) በጉራጌ ቤቶች፤ olmstead (1972 ) በዶርዜ ቤቶች ላይ፤ጋረደው መንገሻ (2015) በኮንሶ ባህላዊ ቤቶች፣እንዲሁም ሀብቴ መንግስቱ በጋሞ ባህላዊ ቤቶች ላይ ጥናቶች አድርገዋል ። በተመሳሳይ በአማራ ክልል፣ አስቴር ሙሉ(2000) በዘጌ ቤቶች፤ አስማማው እስተዚያ(2003) በደጋ ዳሞት ወረዳ የቤት አሰራር ላይ ጥናቶቻቸውን አቅርበዋል ። ከዚህ በተጨማሪ፣ማማዬ አያሌው (2002) በአፋር ክልል ፣ብሩክታዊት ብርሃኑ (2011) በባሶና ወረና፤ Dorothea (1982) በሐረር ቤቶች Shimizu, et al (2018) በትግራይ እንዲሁም አለማየሁ ደርጌ እና ዴናሞ አዲሴ በመላው በኢትዮጵያ በቀርከሃ ግብአቶች ስለሚሰሩ ባህላዊ ቤቶች ያጠኑ ተመራማሪዎች ናቸው ።

ከተጠቀሱት ጥናቶች መካከል ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡና ከዚህ ጥናት ጋር ቀጥተኛ ተዛማጅነት ያላቸው አራት የመመረቂያ ጽሑፎች ይገኛሉ። እነዚህም የማማዬ አያሌው (2002) የመጀመሪያ ዲግሪ፣እንዲሁም የአስቴር ሙሉ (2000)፣ የአስማማው እስተዚያ(2003) እና ብሩክታዊት ብርሃኑ (2011) የሁለተኛ ዲግሪ ዲግሪ ጥናቶች ናቸው ። ከእነዚህ ውስጥ ሁለቱ ጥናቶች ባህላዊ ቤትን ከእጅ ሥራ ጋር ሲያቆራኙ፣ አንዱ ደግሞ የቤት አሰራርን ከሥነ ቃልና ከሀገረሰባዊ ልማድ ጋር አጣምሮ አቅርቧል ። አራተኛው ጥናት በባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብ ላይ ብቻ ትኩረት አድርጓል ።

ምንም እንኳን ከላይ የተጠቀሱት ጥናቶች ጠቃሚ ግንዛቤዎችን ቢያስጨብጡም፣ ይህ ጥናት ከእነሱ የሚለይባቸው ነጥቦች አሉት ። በትኩረት አቅጣጫ፣በመጠነ ርዕይ፣ በጽንሰ ሀሳብ፣በንድፈ ሀሳባዊ ማዕቀፍ እና በጥናት አካባቢ ልዩነት አለው ። ከሁሉም በላይ ይህን ጥናት ከሌሎች ጥናቶች ልዩ የሚያደርገው በፎክሎር የትምህርት ዘርፍ ሀገረሰባዊ ምህንድስና(ቁሳዊ ባህል) ላይ ያተኮረ የመጀመሪያው የሶስተኛ ዲግሪ (PhD) ጥናት መሆኑ ነው ።

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች

ይህን ጥናት ለማከናወን ያነሳሱኝ ዋና ዋና ምክንያቶች ከግል ምልከታ(ገጠመኝ)፣ የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ጥሪ ወይም በብሔረሰቡ ውስጥ የታዘብኩትን የእውቀት ክፍተት እና በአካዳሚያዊ ቅኝት መርሃ ግብሩ ከወሰድኳቸው ኮርሶች የተረጋገጠውን የምርምር ክፍተት ያጣመሩ ናቸው ። እነዚህም እንደሚከተለው ተዋቅረዋል ።

**1. የግል ገጠመኝ እና ከብሔረሰቡ የባህል ጠብቆት/ተቆርቋዋሪነት/ ጥሪ**

የመጀመሪያውና ዋነኛው አነሳሽ ምክንያት በተደጋጋሚ ወደ ወላይታ አካባቢ ባደረግኳቸው የመስክ ምልከታዎችና ጉብኝቶች የተገኘ ነው ። በወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ የኦሞቲክ ጥናትና ምርምር ማዕከል እንዲሁም በማህበራዊ ሳይንስና ስነ-ሰብ ኮሌጅ አስተባባሪነት በተካሄዱ ታሪካዊ ቦታዎች ጉብኝቶች ላይ የብሔረሰቡን የቤት አሰራር ጥበብ በቅርበት የመታዘብ እድል አግኝቻለሁ ። በተጨማሪም፣ በቦዲቲ ከተማ አቅራቢያ በክቡር ዶ/ር ዘብዲዎስ ጫሞ የተገነባውን የግል ሙዚየም መጎብኘቴ ለጥናቱ ተጨማሪ ግፊት ፈጥሮብኛል ። ሙዚየሙ በዘመናዊና ባህላዊ አሰራር ተቀናጅቶ መገንባቱ፣ የውስጥ ክፍሎቹ የዘጠኙን ፕላኔቶች ምሳሌ ተከትለው መሰራታቸውና ሌሎችም ውስብስብ የጥበብ መገለጫዎች መኖራቸው፣ በጉዳዩ ላይ ጥልቅ ምርምር የማድረግ ፍላጎቴን አጠናክሮታል ። በነዚህ ምልከታዎች ወቅት ትኩረቴን የሳቡ ሁለት ዋና ዋና ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው ።

- **የሥነ-ሕንጻ ጥበብ ውስብስብነት ፡-** የወላይታ ባህላዊ ቤቶች በውጫዊ ገጽታቸው ተመሳሳይ መስለው ቢታዩም ፣ የውስጥ አቀማመጣቸው ፣ የምሰሶ አተካከልና የቅርጻቸው ትርጓሜ ከፍተኛ ልዩነት ያሳያል ። በተለይ የቤት አሰራሩ ከጨረቃ ኡደት ጋር ያለው መስተጋብር፣ የምሰሶ ትዕምርቶች እና ለጌጥነት የሚውሉ ቀለማት ያላቸው ተምሳሌታዊ ትርጉም በቀላሉ የማይታይ ጥልቅ እውቀት እንዳለ አመላክቶኛል ።
- **የብሔረሰቡ ሽማግሌዎች ጥሪ ፡-** በጉብኝቱ ወቅት መረጃ ይሰጡን የነበሩ የሀገር ሽማግሌዎች፣ ይህ የሥነ-ሕንጻ እውቀት በተተኪ ትውልድ እጦት ምክንያት ሊጠፋና ሊረሳ እንደሚችል በተደጋጋሚ በምሬት ገልጸዋል ። “ይህ እውቀት ሳይጠፋ በጥናት ተመዝግቦ እንዲቀመጥና ለትውልድ እንዲተላለፍ የበኩላችሁን ተወጡ ” በማለት ያቀረቡት ተደጋጋሚ ጥሪ ፣ ለጥናቱ ማኅበረሰባዊ ፋይዳ እንዳለው በማመን ኃላፊነት እንዲሰማኝ አድርጓል ።

## 2. አካዳሚያዊ

የግል ምልከታዎቼ በአካዳሚያዊ ቅኝት ሲደገፉ ይበልጥ ተጠናክረዋል ። በፒኤችዲ መርሃ ግብሩ የወሰድኳቸው ኮርሶች በተለይም Contemporary Issues in Ethiopian Folklore (Folk 806)፣ Issues in Popular Culture and Environmentalism (Folk 802) እና Advanced Seminar in Folklore and Development (Folk 804) በውይይቶችና በንባብ እንደተረዳሁት፣ በቁሳዊ ባህል ጥናት ዘርፍ ሰፊ ክፍተት መኖሩን እንድገነዘብ አስችለውኛል ።

- **የጥናቶች ውስንነትና ይዘት ፦** በኢትዮጵያ ቁሳዊ ባህል ላይ የተሰሩ ጥናቶች በቁጥር አናሳ ናቸው ። ያሉትም ጥናቶች በአብዛኛው ከመሆን አያልፉም። የቁሳቁሱን ዓይነት፣ አሰራርና አጠቃቀም ከመግለጽ ባለፈ ትዕምርታዊ (symbolic) እና ትርጓሜያዊ (interpretive) ትንታኔ አያቀርቡም ። በተጨማሪም ብዙዎቹ ጥናቶች ማህበራዊ ፋይዳዎች እና የእውቀት ሥርዓቶች በጥልቀት እንደማይመረምሩ በውይይቶች እና በአማካሪዎቼ በተሰጡኝ የቤት ስራዎች (Annotated Bibliography) አማካኝነት ለመገንዘብ መቻሌ በዚህ ጥናት ላይ እንዳተኩር አድርጎኛል ።
- **የሥነ-ዘዴ ክፍተት ፦** በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በተለያዩ የትምህርት መስኮች የተጠኑ ጥናቶች ቢኖሩም፣ የፎክሎር የጥናት ዘርፍ የሚከተላቸውን የሥነ-ዘዴ ማዕቀፎች ባለመጠቀማቸው ምክንያት የባህሉን ፍልስፍናና የማንነት መገለጫነት በጥልቀት አይዳስሱም ። ስለሆነም ይህንን ክፍተት ለመሙላትና ከገለጻ ባለፈ ትንታኔያዊ ይዘት ያለው ጥናት ለማቅረብ መነሳሳቴ የዚህ ምርምር ሁለተኛው ምክንያቴ ነው ።

## 3. የጥናቱ የመጀመሪያነት እና የምርምር መስኩ አስተዋጽኦ

በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል ውስጥ ባደረግኩት የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝት በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ ላይ ያተኮረ የመጀመሪያ፣ የሁለተኛም ሆነ የሶስተኛ ዲግሪ ጥናት እንዳልተሰራ ለማረጋገጥ ችያለሁ ። ይህም ጥናቱ በአይነቱ የመጀመሪያና በዘርፉ ያለውን የምርምር ክፍተት የሚሞላ መሆኑን አረጋግጦልኛል ። ስለሆነም ከግል ምልከታና ከብሔረሰቡ ጥሪ የተቀዳው፣ በአካዳሚያዊ ዳሰሳ የተረጋገጠው እና በጥናት የመጀመሪያነቱ የተደገፈው ይህ የጥናት ርዕስ፣ ጠቃሚና ወቅታዊ የምርምር ሥራ እንደሚሆን በማመን በጥናቱ ልገፋበት ችያለሁ ።

## 1.3. በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች ጥናቱ የሚመልሳቸው የምርምር ጥያቄዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

- በወላይታ ብሔረሰብ ባህል ውስጥ የቤት ምንነት፣ውክልናው እና የታወቁ የባህላዊ ቤት አይነቶች የትኞቹ ናቸው?
- የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደትና በግንባታው ወቅት የሚከወኑ የማህበራዊ ክዋኔዎች ተግባራት ምን ይመስላል?
- የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጾችየሚይዙት ምሳሌያዊና ባህላዊ ትርጓሜዎች ምንን ይወክላሉ?
- .በወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት አሰራር ጥበብ ላይ የታዩትን ለውጦችና ቀጣይነቶች እንዲሁም ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሁኔታዎች ምንድናቸው?

## 1.4. የጥናቱ ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች

### የጥናቱ ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራርን፣ ተያያዥ ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳዎቹን እና በዘመናት ውስጥ ያሳየውን ለውጥና ቀጣይነት በጥልቀት መመርመር ነው፡፡

### የጥናቱ ዝርዝር ዓላማዎች

ይህንን ዋና ዓላማ ከግብ ለማድረስ ጥናቱ የሚከተሉትን ዝርዝር ዓላማዎች አካቷል ፡፡

- በወላይታ ብሔረሰብ ባህል ውስጥ የቤት ምንነት፣ውክልናው እና የታወቁ የባህላዊ ቤት አይነቶችን መለየት፤
- የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ሂደትና በግንባታው ወቅት የሚከወኑ የማህበራዊ ክዋኔዎችን ተግባራት መፈተሽ፤
- የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጾች የሚይዙትን ምሳሌያዊና ባህላዊ ትርጓሜ መፈከር፤
- በወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት አሰራር ጥበብ ላይ የታዩትን ለውጦችና ቀጣይነቶች እንዲሁም ለዚህ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሁኔታዎችን መለየት፤

## 1.5. የጥናቱ አስፈላጊነት

የቁሳዊ ባህል ጥናት የሥነ-ሰብ፣የሥነ ቁፋሮ፣የማህበረሰብ፣የሥነ-ልቡና፣የአካባቢ ጥናት፣የታሪክ እና የጥበብ ታሪክ ተመራማሪዎችን የሚያጠቃልል ሁለገብ የትምህርት (የጥናት) መስክ ነው ። የቁሳዊ ባህል ጥናት በሰዎች እና በቁሶች መካከል ያለውን ውስብስብ መስተጋብር ያብራራል (Tauer, 2001)፡፡

ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፎች ውስጥ ሀገረሰባዊ ምህንድስና ላይ ትኩረት በማድረግ ከወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ትኩረት አድርጎ ተጠንቶና ተተንትኖ መቅረቡ በተለያየ መንገድ ለአካባቢው ህዝብ ጠቀሜታ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል ።

ከትውልድ ትውልድ በቃል፣በድርጊትና በተጨባጭ ሲተላለፍ የነበረውን የብሔረሰቡን ዕውቀትና ጥበብ በጽሁፍ እንደ አንድ መረጃ በማደራጀት ማስቀመጡ ለብሔረሰቡና ለቁሳዊ ጥናት ዘርፍ ፋይዳ ይኖረዋል ተብሎ ይታሰባል ።

በቁሳዊ ባህል ላይ በተለይ በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ምርምር ለሚያካሂዱ አጥኚዎች እና ከፎክሎር ትምህርት ክፍል ውጪ ሆነው ተያያዥነት ላላቸው ትምህርት ክፍሎች የመረጃ ምንጭ በመሆን ያገለግላል ።

ይህ ጥናት በአካባቢው ለሚገኙት ለባህል ቱሪዝምና ለቅርስ ጥበቃ ቤቶቹ ጨርሰው እንዳይጠፉና ተጠብቀው እንዲቆዩ እንዲያደርጉ በተወሰነ ደረጃ ግንዛቤ የሚሰጥ በመሆኑ ይህንንም መሰረት አድርገው ባህላዊ ቤቶቹ ተጠብቀው እንዲደራጁና ለጥናት የመረጃ ምንጭ እንዲሆኑ በማድረግ እገዛ ሊያደርግላቸው ይችላል ተብሎ ይታሰባል ።

እድሉን አግኝተው በተለያየ ምክንያትና ዓላማ ይህን ጥናት ለሚያነቡ ሰዎች የብሔረሰቡን ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ፤የመስሪያ ግብአቶች ከአካባቢው መገኘት፤ ቤቱን የሚሰሩ ባለሙያዎችን እውቀት፤ የብሔረሰቡን እምነት፤የቤቱ ቅርጽና አሰራር ከብሔረሰቡ ጋር ያለውን ትስስር ያስተዋውቃል ።

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

- ይህ ጥናት ከቁሳዊ ባህል ዘርፎች ውስጥ የሀገረሰባዊ ምህንድስና ክፍል በሆነው የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ትኩረት አድርጎ ቀርቧል ። ‹‹ቁሳዊ ባህል ሀገረሰባዊ እጅ ስራ፣ሀገረሰባዊ ስዕል፣ ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ሀገረሰባዊ ልብስ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራርን ይይዛል

(ፈቃደ፣1991) ፡፡ ስለሆነም ጥናቱ ርዕሰ ጉዳይን፣ ቦታን፣ የተጠኚ አካላትን መረጃ መሰረት በማድረግ ገደቡን ወስኖ ተሰርቷል ፡፡

- ጥናቱ በወላይታ ብሔረሰብ ከሚገኙ የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ውስጥ ባህላዊ የቤት አሰራርን መርምሮ ሂደቱን ተንትኖ  አቅርቧል ፡፡ በብሔረሰቡ በዓይነትና በአገልግሎት በርካታ የቤት ዓይነቶች ቢኖሩም በዚህ ጥናት ለሰዎች መኖሪያነት የሚያገለግሉ የባህላዊ ቤቶች አሠራር ተተኳሪ ተደርጓል ፡፡
- በጥናቱ ውስጥ የባህላዊ ቤቶች አይነቶች፣ አሰራራቸው፣ ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጻቸው፣ የግንባታ ግብዓቶቻቸው፣ ማህበረ-ባህላዊ ፋይዳቸው እንዲሁም በጊዜ ሂደት ያሳዩት ለውጥና ቀጣይነት በጥልቀት ተተንትነዋል ፡፡
- ከቦታ አንፃር፣ ጥናቱ በወላይታ ዞን ስር በሚገኙ አምስት ወረዳዎች (ኪንዶ ዲዳዬ፣ ሶዶ ዙሪያ፣ ኦፋ፣ ሁምቦ እና ካዎ ኮይሻ) እና በነዚሁ ወረዳዎች ስር በተመረጡ አስር ቀበሌዎች ላይ ተወስኗል ፡፡ እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡት የተለያየ መልክዓ ምድራዊ እና የአየር ንብረት አቀማመጥ ስላላቸው እንዲሁም ባህላዊ ቤቶችና ባለሙያዎች በተሻለ ሁኔታ ይገኙባቸዋል ተብሎ ስለታመነ ነው ፡፡
- በዚህም መሰረት፣ ጥናቱ ለሰው ልጆች መኖሪያነት በሚያገለግሉ ቤቶች ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን፣ ከቤት አሰራር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌላቸው ሌሎች የቁሳዊ ባህል ዘርፎች ከቤት ግንባታ ውጪ የሚነገሩ ሥነ-ቃሎች እና ለሌላ አገልግሎት የሚውሉ የቤት አይነቶች (እንደ ጎተራ ያሉ) በዚህ ጥናት አልተካተቱም፡፡

## 1.7. የጥናቱ ውስንነት

ይህ ጥናት፣ የተወሰኑ ውስንነቶች አሉት ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ ዋና ዋናዎቹ የሚከተሉት ናቸው፡-

- **ዘዴያዊ ውስንነት** ጥናቱ በአብዛኛው የተመሰረተው በመረጃ ሰጪዎች ትውስታ ላይ በመሆኑ፣ የማስታወስ ተፈጥሯዊ ውስንነት በመረጃዎቹ ጥራትና ምሉዕነት ላይ ተጽዕኖ ሊኖረው ይችላል ፡፡ በተጨማሪም፣ የአጥኚዋ ጾታ ሴት መሆን በወላይታ ባህል መሰረት አንዳንድ ሂደቶችን (ለምሳሌ ምሰሶ በሚተከልበት ወቅት የሚደረገውን ክዋኔ) በቅርበት ለመታዘብ እንቅፋት ፈጥሯል ፡፡ ይህ ሁኔታ የተወሰኑ የመስክ መረጃዎች በቀጥታ

ምልከታ ሳይሆን በቃለ መጠይቅ ብቻ እንዲሰበሰቡ በማድረጉ የጥናቱ ክፍተት ሊሆን ይችላል ፡፡

- **ንድፈ-ሀሳባዊ ውስንነት** ጥናቱ በመዋቅራዊ ተግባራዊነት፣ በሥነ-ትዕምርት፣ በማህበራዊ ትምህርት እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ-ሀሳቦች ላይ ቢመሰረትም፣ ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች አንፃር እንደ ፍካሬ-ልቦና እና እንስታዊነት ያሉ ንድፈ-ሀሳቦች ለተጨማሪ ትንተና ጠቃሚ መሆናቸውን ለመገንዘብ ተችሏል ፡፡ የእነዚህ ንድፈ-ሀሳቦች አለመካተት የትንተናውን ጥልቀት ውስን ያደርገዋል ፡፡
- **የትኩረት ውስንነት** ጥናቱ የባህላዊ ቤቶችን ለውጥና ቀጣይነት ለማሳየት በከፊል ዘመናዊ ግብዓቶችን ተጠቅመው የተሰሩ ቤቶችን አካቷል ፡፡ ነገር ግን ዋነኛ ትኩረቱ በባህላዊ ቤቶች ላይ በመሆኑ፣ የእነዚህ ሽግግር ላይ ያሉ ቤቶች አሰራርና ፋይዳ በጥልቀት አልተተነተነም ፡፡ ይህን ርዕሰ ጉዳይ ለብቻው በጥልቀት ማጥናት ያስፈልጋል ፡፡

## 1.8. በጥናቱ ወቅት ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር በጥናቱ ወቅት መረጃ በመሰብሰብ ሂደት ውስጥ ያጋጠሙ ችግሮችና መፍትሔዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

በዚህ ጥናት ካጋጠሙ ችግሮች መካከል የመጀመሪያው በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ በተዘዋወርኩባቸው ቀበሌዎች ከሚገኙ ባህላዊ ቤቶች መካከል መጀመሪያ ላይ የተመለከትኳቸው ዘመናዊውንና ባህላዊውን አሰራር የተከተሉ ናቸው ፡፡ እነዚህም ባህላዊውን ጥበብ ተከትለው ቦታውን መርጠው፤ደልድለው ፤ምሰሶ አቁመው፤ግድግዳ አቁመው፤ቀጫጭን ማገር ካደረጉ በኋላ በፌሮ ያስራሉ፤ቀጥለው ሳር፤አርማታ በማድረግ ሲሰሩ የተመለከትኩ ሲሆን በዚህም የተለወጡና የቀጠሉ ነገሮች መኖራቸውን ለመረዳት ችያለሁ ፡፡ ይሁንና ይህም ለጥናቴ አስፈላጊ ቢሆንም በዋናነት ባህላዊውን የአሰራር ጥበብ ተከትለው የተሰሩት የጥናቴ ትኩረት በመሆናቸው ፍለጋዬን ቀጠልኩ ፡፡

ሁለተኛው ለጥናቱ በተመረጡት ወረዳዎችና ቀበሌዎች ባህላዊ ቤቶችን የሚሰሩ ባለሙያዎች በቁጥር አነስተኛ መሆንና በተመረጡት ወረዳዎች መረጃ ሰጪዎችን እንደ ልብ ለማግኘት አለመቻል ሲሆን ለዚህም እንደ መፍትሄ የተወሰደው እነዚህ ባለሙያዎች ያሉበትን ተጨማሪ ወረዳዎች በጥቆማ በማግኘትና በማካተት ወደ ቦታው በመሄድ አስፈላጊ መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡

ሦስተኛው ከመረጃ ሰጪዎች ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም ባህላዊ ቤቶችን የሚሰሩ ባለሙያዎች መረጃ እንዲሰጡ ሲጠየቁ መረጃውን በስፋት ከመግለጽ መቆጠብ፣ ችግሮች ያጋጠሙ ሲሆን እንደ መፍትሔ

የተወሰደው የጥናቱን ዓላማ ደጋግሞ በማስረዳት፤ በተደጋጋሚ በመሄድና ወዳጅነትን በመፍጠር እንዲሁም ደግሞ ወዳጅነትና ዝምድና ባላቸው ሰዎች አማካይነት ቀረቤታን በመፍጠር መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተችሏል ።

ሰኞ እለት ከወላይታ ሶዶ በሌሊት ተነስቼ ወደ ካም ኮይሻ ጉዞዬን አደረኩ ከረፋዱ አምስት ሰዓት ላይ ካምኮይሻ አውቶቢስ ተራ ደረስኩ ። የመረጃ አቀባዬ ቤት ከከተማው ትንሽ ወጣ ያለ ቢሆንም በሌላ ጉዳይ ወደ ሴትየዋ ቤት ከሚሄድ ሰው ጋር ሆነን ደረስን ። ይሁንና መረጃውን የምትሰጠኝ ወ/ሮ ባሎሜ እቤት አልነበረችምና 2፡30 ያህል ከቆየች በኋላ ተመለሰች ። የምፈልገውን መረጃ ተቀብያት በድጋሚ እንደምመጣ ተነጋግረን ተሰናብቻያት ወጣሁ ።

ከሷ ቤት እንደወጣሁ ጉዞዬን ወደ ከተማ አደረግኩ ። ከተማ እንደደረስኩ የረሃብ ስሜት ስለተሰማኝ ሻይ በዳቦ ከተመገብኩ በኋላ ወደ አውቶቢስ ተራ ሄድኩ ። እዛም ስደርስ ወደ ኋላ ለመመለስ ሰው አልሞላም በጎዶሎ ከተመለስኩ አያዋጣኝምና ትንሽ ጠብቁ አለን ። እኔም እዛው ከነበሩ ሰዎች ጋር መጠበቅ ጀመርኩ ። በመጨረሻም የሚፈለገው የሰው ቁጥር ባለመገኘቱ መኪናው እንደማይሄድ ተነገረን ። እየመሸ በመሆኑ የማውቀው ሰው ባለመኖሩ በጣም ፈርቼ ግራ በተጋባሁ ሰዓት ሁለት ሰዎች ገሱባ(ኦፋ) እስከሚባለው ወረዳ ድረስ በሞተር እንሂድ ። ገሱባ ስንደርስ ሰኞ ቀን የኦፋ ወረዳ የገበያ ቀን በመሆኑ ወደ ወላይታ የሚሄድ መኪና አይጠፋም አሉኝና በሀሳባቸው ተስማምቼ ጉዞ ልንጀምር እነሱ የሚያወቋቸውን ሁለት ሞተረኞች አስጠርተው አስመጡ ከነሱም አንዱ ላይ ሁለቱ ሰዎች ቁጭ አሉ ።

ሁለተኛው ላይ እኔና ሌሎች ሁለት ሰዎች ሞተሩ ላይ ተቀመጥን ጉዞ ጀመርን ። በርግጥ ወላይታ ሶዶ ውስጥ ሞተር አንዱ የትራንስፖርት መገልገያ በመሆኑ ብዙ ጊዜ እገለገልበታለሁ ። ሆኖም ግን በዚህ መንገድ ሳይሆን አንድ ሞተረኛ የሚጭነው አንድ ሰው ነው ። እዚህ ቦታ ላይ ያየሁት በጣም አስፈሪ ነበር ይሁንና አማራጭ ስላልነበረኝ ከሌሎች ሁለት ሰዎች ጋር እየተንዠን ሳለ ሹፌሩ መንገድ ላይ አንድ በእድሜው አነስ ያለ ልጅ በመጨመር ለአራት ሆነን ጉዞ ቀጠልን ። ገሱባ ከተማ ለመድረስ 30 ደቂቃ ያህል እንደቀረን የኛ ሞተር ፍሬን ተበጥሶ በፈጣሪ ፍቃድ ከአደጋ ተረፍን ። በመሪ ብቻ ታግዞ ከተማው ጋር አደረሰን ከዛ በሌላ ሞተር ወደ አውቶቢስ ተራ ሄድኩኝ ። የወላይታ መኪና አግኝቼ ምሽት 3፡00 ሰዓት ላይ ወላይታ ሶዶ ገባሁኝ ። በሌላ ቀን ደግሞ የአካባቢው ነዋሪ የሆነች ሴት በሰዎች አማካይነት አግኝቼ ውዬ አድሬ መረጃውን በድጋሚ አጠናክሬ ለመሰብሰብ ችያለሁ ።

### 1.9. የጥናቱ አደረጃጀት

ይህ ጥናት ዘጠኝ ምዕራፎችን አካቷል ፡፡ እነዚህ ምዕራፎች ተደራጅተው የቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው ምዕራፍ የጥናቱን መግቢያ የያዘ ሆኖ ጥናቱን በማስተዋወቅ ሂደቱን የሚገልጽ ሲሆን በስሩ የጥናቱ ዳራ፣ የጥናቱ አነሳሽ ምክንያቶች፣የጥናቱ ጥያቄዎች፣ የጥናቱን ዋናና ዝርዝር ዓላማዎች፣ የጥናቱን ወሰን፣ የጥናቱን ውስንነት፣የጥናቱን አስፈላጊነት፣የጥናቱን አደረጃጀት፣ በጥናቱ ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ መፍትሔዎች ተካተዋል ፡፡

በሁለተኛው ምዕራፍ የፅንሰ ሀሳባዊ ማሕቀፍ፣የንድፈ ሀሳብ ማሕቀፍና የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት ቀርበዋል ፡፡

በሦስተኛው ምዕራፍ የመረጃ ምንጮች እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣የአጋዥ መሳሪያዎች አጠቃቀም፣የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች፣የመረጃመሰብሰቢያ አንጻሮች፣የናሙና አመራረጥ፣የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎችና የምርምር ሥነ ምግባሮችን ይዟል ፡፡

በምዕራፍ አራት ደግሞ የህዝቡ አውዳዊ ዳራ፣ አሰፋፈርና የህዝብ ብዛት፣መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ፣ኢኮኖሚና መሰረተ ልማት፣ማህበራዊ አገልግሎት፣የአካባቢው ስያሜና ቋንቋ፣የሕዝቡ ሐይማኖትንና የጋብቻ ሁኔታን የሚያስተዋውቁ መረጃዎች ቀርበዋል ፡፡

ከምዕራፍ አምስት እስከ ስምንት ያሉ ይዘቶች የምርምሩን ትንታኔ ክፍል የሚሸፍኑ ሆነው ትንታኔዎቹ፤ የጥናቱን ዓላማዎች መነሻ በማድረግ ተደራጅተው ቀርበዋል ፡፡ በምእራፍ ዘጠኝ ማጠቃለያ፣ግኝትና ይሁንታ ተካተዋል ፡፡ የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው፣ በዓይነት እና በይዘት ተለይተው፤ ከጽንሰ ሃሳብ፣ ከንድፈ ሃሳብና ከመተንተኛ ሞዴሎች ጋር ተገናዝበው፤ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

# ምዕራፍ ሁለት

# ክለሳ ድርሣናት

በዚህ ምዕራፍ በዋናነት ሦስት ጉዳዮች የቀረቡ ሲሆን የመጀመሪያው ፅንሰ ሀሳባዊ ማሕቀፍ፣ ሁለተኛው ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ ሲሆን ሦስተኛው ደግሞ የተዛማጅ ስራዎችን ቅኝት ይዟል እነዚህም ርዕሰ ጉዳዮች እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

## 2.1. ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራ

በዚህ ርዕስ ስር የቁሳዊ ባህል ምንነት ፤ የቁሳዊ ባህል ዘርፎች፤ የቁሳዊ ባህል ጥናት አድማስ እና አስፈላጊነት፤ የሀገረሰባዊ ምህንድስና ምንነት፣ የቤት ምንነት፣የባህላዊ ቤት ምንነት፣ ቀጥሎ ቀርበዋል

### 2.1. 1. የቁሳዊ ባህል ምንነትና ምድብ በፎክሎር

ቁሳዊ ባህል በሥነ ሰብ፣በማህበረሰብ፣ በሥነ ቁፋሮ፣በፎክሎር ወዘተ ሊጠና ይችላል ፡፡ ይህ ጥናት ቁሳዊ ባህልን ከፎክሎር የጥናት ስልት አንጻር ትኩረት አድርጎ የተጠና ነው ፡፡ የቁሳዊ ባህል ብያኔ በምሁራን በተለያየ መንገድ የተገለጸ ሲሆን ይኸውም ከፊሎች ቁሳዊ ባህልን  የቁሶች ስብስብ ብለው ሲያብራሩት ሌሎች ደግሞ ቁሶች የሚጠኑበት የጥናት ዘርፍ እንደሆነ ይገልፃሉ ፡፡ ይህም ቀጥሎ ቀርቧል፡-

ቁሳዊ ባህል የቁሶች ስብስብ ብለው የሚያብራሩ እንዳሉ ሁሉ ቁሶች የሚጠኑበት የጥናት ዘርፍ እንደሆነም ይገልፃሉ ፡፡ ፈቃደ ስለቁሳዊ ባህል ምንነት የሚከተለውን ገልጸዋል፡-

> ቁሳዊ ባህል በአይን የሚታየውን በእጅ የሚዳሰሰውን ከዘመናዊ ኢንዱስትሪ በፊት ጀምሮ የሰው ልጅ ፈጥሮ የተገለገለባቸውን ቁሳቁሶች፣እነዚህ ቁሳቁሶች የተሰሩበትን ዘዴ ወይም ቴክኒክ የልዩ ልዩ ምግቦችን አሰራር፣ የቅመም አቀማመም ብልሃትን፣ የልብስ፣ የቤት፣ የአጥር ወዘተ. አሰራርን ሰዎች ልዩ ልዩ ስራዎችን የሚያከናውኑባቸው መሳሪያዎችንና ሌሎችን ተመሳሳይ ጉዳዮች ያጠናል ማለት ነው (ፈቃደ፣1991ገ.15) ፡፡

ፈቃደ የቁሳዊ ባህልን ምንነት ከመግለፅ በተጨማሪ በስሩ የሚካተቱ ዘርፎች *ሀገረሰባዊ እጅ ስራ* (Folk Crafts) ፣ ***ሀገረሰባዊ ስዕል*** (Folk Art) ፣ ***ሀገረሰባዊ ምህንድስና*** (Folk Architecture) ፣ ***ሀገረሰባዊ ልብስ*** (Folk Costume) **እና** ***ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራር*** (Folk Cookery) **በማለት አስቀምጠዋል** ፡፡

Glassie **ደግሞ ቁሳዊ ባህልን እንደሚከተለው በይነውታል** ‹‹Material culture is the culture made material; it is the inner wit at work in the world. Beginning necessarily with things, but not ending wtith

them, the study of material culture uses objects to approach human thought and action›› (Glassie, 1999, p.41) ፡፡

ከፈቃደ ብያኔ ቁሳዊ ባህል የቁሶችን ምንነትና የተሰሩበትን ዘዴ የሚመረምር መሆኑን ለመረዳት ሲቻል ከGlassie ብያኔ ደግሞ ፅንሰ ሀሳቡ የቁሶቹ ባለቤት የሆነውን የሰው ልጅን አስተሳሰብ እና ፍልስፍና በቁሶች አማካይነት መመርመር እንደሚቻል መረዳት ይቻላል ፡፡

ከቀረቡት ብያኔዎች መገንዘብ እንደሚቻለው ቁሳዊ ባህል ሰዎች ቁሳዊና መንፈሳዊ ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት ባህላዊ እሴቶቻቸውን፣እምነታቸውን፣ለስነ-ውበት ያላቸውን አመለካከት የፈጠራ ችሎታቸውን ለማሳየት ሲሉ የሚሰሯቸውን ቁሳዊ ነገሮች የሚያካትት ፅንሰ ሀሳብ ነው ፡፡ በዚህ መሰረት ቁሳዊ ባህል የሰው ልጅ ቁሳዊ እና መንፈሳዊ ፍላጎቶቹን ለማሟላት ወደ ባህላዊ ስፍራነት እና ወደ ባህላዊ ቁስነት የተለወጡ ወይም የሚለወጡ ተፈጥሮአዊ ስራዎችንና ተፈጥሯዊ ቁሳዊ ነገሮችን ያካትታል ማለት ነው ፡፡ ባጠቃላይ ቁሳዊ ባህልን ማጥናት ማለት በቁሳዊ ነገሮች አማካይነት የሰው ልጅን አዕምሮ ማጥናት ነው ፡፡

ሰለሞን Glassie (1968, p.10) ጠቅሶ እንደገለጸው "ባህላዊ ቁሶች የማህበረሰቡን ፍልስፍና፣ታሪክ፣እምነት፣ሐይማኖት፣ባህል ወዘተ.መሰረት በማድረግ የማህበረሰቡን የዘመን ተመክሮ አሻራዎች የሚያሳዩ ጥበባዊ ውጤቶች ናቸው" (2007፣ገጽ248) ፡፡

እንደ (Prown, **1982, p. 1)** **ገለጻ** «Material culture is study of through artifacts of the beliefs, values, ideas, attitudes and assumption of a particular community or society at a given time». ቁሳዊ ባህል በቁሶቹ አማካኝነት የአንድን ማህበረሰብ እምነት፣ወግ ፣ ልማድ ፣ አመለካከት ለማጥናት የሚያስችል ዘርፍ ሆኖ በተሰሩበት ዘመን ሰዎች ሊዘጋጅ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ Prown አክለውም የቁሳዊ ባህል ተቀዳሚው ትኩረቱ በማህበረሰቡና በቁሱ መካከል ያለውን የጋራ ግንኙነት በመመርመር ቁሶቹ ለማህበረሰቡ የሚሰጡት አገልግሎት ምንድን ነው? የሚሉትን ጥያቄዎች መርምሮ የሚገልጽ መሆኑን ገልጸዋል ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ እንደ (ሰለሞን፣2007፣ገጽ248) "ቁሳዊ ባህል (Material culture) አንዱ የፎክሎር ዘውግ ነው ፡፡ በዚህ ዘርፍ ውስጥም የሚካተቱት በዐይን የሚታዩ፣በእጅ የሚዳሰሱና በምላስ የሚቀመሱ ተጨባጭ የፎክሎር አይነቶች ናቸው ፡፡ እነዚህ የፎክሎር አይነቶች ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚያገኛቸውን ግብአቶች ፣ በራሱ እውቀት የፈጠራቸውን የማምረቻ መሳሪያዎች፣የራሱን የአሰራር ስልትንና ዕውቀትን መሰረት በማድረግ የሚሰራቸው ቁሶች ናቸው" በማለት ገልጸዋል ፡፡

(ሰለሞን፣2007፣ገጽ248) አክለውም ቁሳዊ ባህሎች ያላቸው ቅርጽ የቁሱን ገጽታና የማህበረሰቡን ማንነት የሚገልጹ ናቸው ። ምክንያቱም በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ የሚገኙ ተመሳሳይ ባህላዊ ቁሶች የተለያየ ቅርጽ አላቸው ማለት ማህበረሰቦቹ የተለያየ ባህል፣ፍልስፍና፣ርዕዮተ ዓለም፣የዓለም እይታ ወዘተ. አላቸው ማለት ነው ።

### 2.1.2. የቁሳዊ ባህል ዘርፎች

ቁሳዊ ባህልን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን የየራሳቸውን ምደባ አስቀምጠዋል ። ለምሳሌ (Dorson) እንደሚገልጹት፣ቁሳዊ ባህል ሀገረሰባዊ የእጅ ሥራ፣ሀገረሰባዊ ሥዕል፣ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ሀገረሰባዊ ልብስ እና ሀገረሰባዊ የምግብ አሰራርን ያካትታል (Dorson, 1972, P. 233) ። በተመሳሳይ (Walls) ይህንኑ ሀሳብ በማጠናከር ቁሳዊ ባህልን (Walls, 1990, P.107) ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ባህላዊ ጥበብ፣ዕደ-ጥበብ፣ምግብ እና አለባበስ በሚል እንደሚከፋፈል ያስረዳሉ (Walls, 1990, p. 107) ።

ፈቃደም በበኩላቸው፣ ቁሳዊ ባህል የልዩ ልዩ ምግቦች አዘገጃጀት፣ የቅመማ ቅመም አጠቃቀም ብልሃት፣ የአልባሳት፣ የቤትና የአጥር አሰራር እንዲሁም ሰዎች ለተለያዩ ሥራዎች የሚጠቀሙባቸውን መሣሪያዎች እንደሚያካትት ይገልጻሉ (ፈቃደ, 1991, p. 15) ። በተጨማሪም Prown ጥበብ፣ ጊዜ ማሳለፊያዎች፣ መደነቂያዎች፣ የመሬት አቀማመጥ ማሻሻሎች፣ተግባራዊ ጥበቦችና መሳሪያዎች በማለት ያስቀምጧቸዋል (Prown, 1982, p. 3) ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ቁሳዊ ባህል በዓይን የሚታይና በእጅ የሚዳሰስ ሆኖ በስሩ የተለያዩ ክፍሎች አሉት ። እነዚህም ሀገረሰባዊ ምህንድስና፣ ባህላዊ ጥበብ፣ዕደ-ጥበብ፣ ምግብ፣ አለባበስ፣የቤት ግንባታን የሚያካትት ሲሆን የዚህ ጥናት አከፋፈል ትኩረትም የፈቃደን አከፋፈል የተከተለ ነው ።

### 2.1.3. የቁሳዊ ባህል ጥናት አድማስ እና አስፈላጊነት

ከአንድ ማህበረሰብ አመለካከት፣እምነትና ማንነት ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያላቸው ባህላዊ ቁሶች ከፎክሎር አንጻር መጠናታቸው ፋይዳቸው ላቅ ያለ ነው ። የቁሳዊ ባህል ጥናት አስፈላጊነትን በተመለከተ Prown እና Mayo እንደሚከተለው አቅርበዋል ።

ቁሶች ከነበራቸው አገልግሎት ባሻገር የተለየ እሴት የሚገለጽባቸው ሆነው እሴቶቹም ተፈጥሯዊ ወይም በሰዎች ሊሰሩ እንደሚችሉ Prown ገልጸው በማያያዝም ‹‹ Surviving Historical events Objects created in the past are the only historical occurrences that continue to exist in the present.›› ፡፡ ጥቅሱም በጥንት ጊዜ የተፈጠሩ ቁሶች በአሁኑ ጊዜ የሚቀጥሉ ብቸኛ ታሪካዊ ክስተቶች ሆነው ባለፈ

ዘመን የተከናወነን ድርጊት እንድንገነዘብ የሚረዱ እንደሆኑ የሚያስረዳ ነው ። በማስከተልም Prown ‹‹ More Representative. They offer the possibility of a way to understand the mind of the great majority of non literate people, past and present, who remain otherwise in accessible except through impersonal records and the distorting view of a contemporary literary elite ›› ቁሳዊ ባህል ጥንትም ሆነ ዛሬ የተማሩና ያልተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በቁሶቹ አማካይነት ባህላቸውንና እምነታቸውን እንደሚገልጹበት የሚያሳይ ነው ። በተጨማሪ Prown ‹‹The fundamental purpose of the study of material culture is the quest for cultural belief systems, the patternts of belief of a particular group of people in acertain time and place. ›› ብለዋል ። ይኸውም የቁሳዊ ባህል መሰረታዊ ዓላማ በባህሉ ውስጥ ያሉ የእምነት ስርዓቶችን መፈለግ፣ የአንድ የተወሰነ የሰዎች ቡድን በአንድ በተወሰነ ቦታና ጊዜ ውስጥ የነበረን እምነት፣ባህል፣ታሪክና አመለካከታቸውን መመርመር መሆኑን ያስገነዝበናል (1982, p. 2-3)፡፡

በሌላ በኩል የቁሳዊ ባህል መጠናት አስፈላጊነትን በተመለከተ Mayo (1984, p. 3) ‹‹Artifacts are symbols and can explain much about society, religious beliefs, forms of government, manual dexterity, level of intelligence, artistic comprehension, available natural materials, structure of commerce, and scientific and emotional of the producing society›› በማለት ገልጸዋል ። ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው ቁሶች ትዕምርት ያላቸውና ስለ ማህበረሰቡ ሀይማኖታዊ እምነቶች፤የመንግስት አስተዳደራዊ መዋቅር፤ የእውቀትን ደረጃ፤ጥበባዊ ግንዛቤ፣ውስብስብ የሆኑ የአምራቹን ማህበረሰብ ሳይንሳዊና ስሜታዊ ሁነቶችን መግለፅ ወይም ማብራራት የሚችል መሆኑን የሚጠቁም ነው።

ባህላዊ ቁሶች ከእለት ተእለት ተግባሮቻቸው በተጨማሪ የሰው ልጅ ለመኖር ከተፈጥሮ ጋር ሲያደርግ የነበረውን ትግልና አሸናፊ ለመሆን ተፈጥሮን ለመግለጽ የሄደበትን ዘዴ መያዛቸውን ይህ ደግሞ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ታሪክና ጥበብ አንድ ላይ መምጣታቸው ቁሳዊ ባህልን እንዲጠና ያደርገዋል (Glassie, 1999)፡፡

በፎክሎር ጥናት ውስጥ የከተማው ባህል በሀገረሰባዊው ላይ እንዲሁም ሀገረሰባዊው በዘመናዊው ላይ የሚያመጣው ለውጥ መጠናት አለበት የሚል ሀሳብ ለመግለጽ ነው (ፍቃደ፣1991) ።

### 2.1.4. የቁሳዊ ባህል አጥኚዎች የትኩረት ነጥቦች

የቁሳዊ ባህል አጥኚዎች በቁሳዊ ባህል ላይ ጥናት ሲያደርጉ በምርቱ ወይም ቁሳዊው ነገር (Product) በምርቱ ሂደት (process) እና ህዝብ (people) በሦስት መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ሊያደርጉ ይገባል። ምርቱ የፎኩ የፈጠራ ሂደት ውስጥ በተጨባጭነት የሚገለጽ ውጤት ሲሆን ሂደቱ ደግሞ

የምርቱን የፈጠራ እና የግንባታ ሁኔታ ይገልጻል ። የመስራት ፍላጎቱ (ተነሳሽነቱን)፣ ዕቅዱን፣በተጨባጭ የስራውን ጊዜ፣ግምገማ(የሰሪው፣የሌላው)ይይዛል ። ህዝብ የሚለው ደግሞ ጥበበኛውን (ባለሙያ)፣የዕውቀቱ መገኛ (መማሪያ)፣የዕውቀቱ ተስተላልፎና ተጠቃሚውን የሚመለከት ነው (Shomeker,1990)፡፡

አውድ ማን፣ ምን፣ መቼ፣የት፣ ምን፣ ለምን እና እንዴት ከሚሉ ጥያቄያዊ ጉዳዮች ያለፈ ነው። የሚመለከታቸውን ሰዎች፣ ምርትና ሂደት ጠንቅቆ ለመግለጽ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ታሪካዊ፣ ሥነ-ልቡናዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ኢኮሎጂካል፣ ርዕዮት የተለያዩ ገጽታዎች መታሰብ ይኖርባቸዋል ። ምርምር የሚደረግበት ዓላማ የሚከተሉትን ሦስት የትኩረት ነጥቦች መመልከትን ይመለከታል።

1. በቅርብ አውድ ፡- የግለሰቡን ፈጠራ እና በእንቅስቃሴያቸው ላይ የተፅዕኖ መስፋፋትን የሚያመጡት የግል ሕይወት፤ቤተሰብ፣ማህበረሰብ ፣ክልል እና ህብረተሰብ የግል ተነሳሽነታቸው፤የእነሱ ሰብዕና እሴቶቻቸው፤ህይወታቸውን እንዴት ያሳውቃሉ? የግል ዝንባሌያቸው ባሕርያቸው ለሕይወታቸው ምን ያህል ነው? ችሎታቸውን የተማሩት እንዴት ነው?በምርጫዎች ወይም ተመሳሳይ ነገር በማድረግ ላይ ተጽዕኖ የሚያሳድሩት ነገሮች ምንድን ናቸው? ዘመናዊው የብዙኃኑ ባሕል በአስተሳሰባቸው ላይ ምን ተጽዕኖ ያሳድራል?

2. በታሪካዊ አውድ ለውጥና ቀጣይነት በጊዜ ሂደት ያለውን ሁኔታ የሚታይ ነው ። በቁሱና በማህበራዊ አገባቡ ላይ ለውጥ የፈጠሩ ትግበራዎች ምንድን ናቸው? አንዳንድ ነገሮች ለምን ሳይለወጡ ይቀራሉ? በማህበራዊ አውድ ለለውጥ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች እንዴት ለውጥ ላይከሰት ቻለ? ለለውጡ የግለሰቦች ተጽዕኖ ምን ይመስላል? ማህበረ ባህላዊ ለውጦች በቤተሰብ፣በማህበረሰብ፣ በአካባቢና በአገር ደረጃ ምን ይመስላሉ? የሚሉ ጉዳዮች ከዚህ ጋር በተያያዘ የሚታዩ ናቸው ።

3. ፎክሎሪስቶች ወይም ማንኛውም ሰው ለምን በዚህ በቁሳዊ ወይም ባህላዊ ወግ ልዩ ገጽታ ላይ ፍላጎት ይኖረዋል? ይህ ወግ ለእኛ ምን ትርጉም አለው? በከተማ የተሠራውን ከፍ አድርገን የምንመለከተው ለምንድን ነው? (Shomeker,1990,P.109) ።

ከላይ የቀረበው ጽሁፍ እንደሚያስረዳው አውድ አንድን ጉዳይ በአግባቡ ለመረዳት የሚጠቅም ነው። ከዚህ በተጨማሪ በፎክሎር ጥናት አስፈላጊና መሰረታዊ ጉዳይ ነው ።

### 2.1.5. የሀገረሰባዊ ምህንድስና ምንነት

ሀገረሰባዊ ምህንድስና የማህበረሰቡን ባህል፣የአኗኗር ሥርዓት እና መልክአምድራዊ ጉዳዮችን መነሻ በማድረግ የሚሰሩ ቤቶችን ያካትታል ።

ሀገረሰባዊ ምህንድስና ባህላዊ የሕንፃ ጥበብ የሚባል ሲሆን ሁሉንም ባህላዊ የሕንፃ ገጽታዎችን የሚመለከት ሆኖ የመኖሪያ ቤትና የተለያዩ ሕንፃዎችን ቅርጽ፣የግንባታዎችን አይነት፣መጠን፣ ለስራው የሚመረጠውን ቦታ፣በተመረጠው ቦታ የግንባታዎችን አቀማመጥ፣የመስሪያ ቁሳቁሶችን፣የግንባታ መሳሪያዎች እና ቴክኒኮች የሚያካትት ሲሆን እያንዳንዱ ክፍልና የክፍሎቹ ጥቅም በሀገረሰባዊ ምህንድስና ስር የሚተኮርባቸው ነጥቦች ናቸው (Dorson, 1972, P. 28) ፡፡

በአጠቃላይ ሀገረሰባዊ ምህንድስና የማህበረሰቡን ባህል፣ የአኗኗር ሥርዓት እና መልክአምድራዊ ጉዳዮችን መሰረት ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን በዚህም የግንባታው አይነት፣ቅርጽ፣መጠን፣የመስሪያ ግብዓቶች፣የአሰራር ዘዴዎች፣ለስራው የሚመረጠው ቦታ፣ወዘተ በሀገረሰባዊ ምህንድስና ስር ትኩረት እንደሚገባቸው የሚገልጽ ነው ።

ሀገረሰባዊ ምህንድስና በህንጻ ውስጥ ያሉ ቅርፆችንና ተግባሮቻቸውን ባህላዊ ገጽታ የሚያካትት ሲሆን ለቤቱ መስሪያ የሚሆኑ ቁሳቁሶችም ከአካባቢው ይገኛሉ ። ሌላው ቅርጻቸው እና አቀማመጣቸው ባህላዊ ትውፊት ላይ የተመሠረቱ ሆነው የግንባታ ቴክኒካቸው በመልክአ ምድራቸው የተገደቡ እንደሆኑም ተገልጿል (Walls, 1990) ፡፡

"ሀገረሰባዊ ምህንድስና (Folk Architecture) የማህበረሰቡን ባህል፣ የአኗኗር ስርአት፣ መልክዓምድራዊ ሁኔታና ሌሎች ጉዳዮችን መሰረት በማድረግ የሚሰሩ መኖሪያ ቤቶችን፣ቤተክርስቲያኖችን፣ መስጊዶችን፣ገዳሞችንህውልቶችንየጋራ መሰብሰቢያ ስፍራዎችን የእንስሳት ማደሪያዎችን ግድቦችን፣ ድልድዮችን፣ እርከኖችን፣ ጎተራዎችን ወዘተ ያካትታል"(ሰለሞን፣2007 ገጽ 271)።

ሰለሞን አክለው እነዚህን የምህንድስና አይነቶች ለመስራት የሚያገለግሉ ግብአቶች አዘገጃጀት፣የግብዐቶቹ አጠቃቀም፣የምህንድስናው የአሰራር ስልት፣የአሰራር ዘዴ፣መጠን፣ቅርጽ፣አገልግሎት፣ለምህንድስናው የሚሆን ቦታ አመራረጥ፣የምህንድስናው ቅርጽና ይዘት ያለው ማህበራዊ ትዕምርት ወዘተ በሀገረሰባዊ የምህንድስና ዘርፍ ውስጥ ተካተው የሚጠኑ ርዕሰ ጉዳዮች እንደሆኑ አመላክተዋል (ሰለሞን፣2007፣ገጽ271)።

### 2.1.6. የቤት ምንነት

I, ባህላዊ ቤት በአካባቢው ሰዎችና በአካባቢው ግብአቶች ማለትም ከድንጋይ ፣ ከእንጨት፣ ከጭቃ፣ከአፈር ፣ከጭድ፣ ከሰንበሌጥ፣ ከቆርቆሮ ወዘተ... የሚሰራ ሆኖ ለሰዎች፣ለእንስሳት መኖሪያነት እና ለተለያየ አገልግሎት የሚውል ነው ፡፡

II, ደስታ (1962፣ገጽ219) ስለ ቤት ምንነት ሲገልጹ ቤት ማለት በቁሙ ማደሪያ፣ መኖሪያ፣ በድንጋይና በጡብ፣ በጠርብ፣ በጨፈቃ፣ በኖራ፣ በጭቃ፣ በጭድ፣ በሰንበሌጥ፣ በቆርቆሮ፣ በሳንቃ፣ የተሰራ ጣራ ሆኖ ውስጠ ክፍት፣ ቦታ፣ዕቃ፣ዋሻ፣ ፍርኮታ፣ጎሬ፣ጉድጓድ ለሰው ጥቅም የሚሆን ነገር ሁሉ ተሰርቶ የሚገኝበትና የሚቀመጥበት እንደሆነ ነው ፡፡

III, “ቤት ከእንጨት፣ከድንጋይ ወይም ከጡብ......የሚሰራና ለተለያየ አገልግሎት፣ ለሰው ወይም ለእንስሳት መኖሪያ፣ለዕቃ ማስቀመጫ የሚውል ዙሪያው በግድግዳ፤ ላዩ በጣሪያ የተከለለ መጠለያ፣ጎጆ፣ሳር ቤት፣ቆርቆሮ ቤት፤ ህንጻ.... የሚይዝ ነው” (የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣1993፣ ገጽ241) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቤት  በጭቃ፣ በጭድ፣ በሰንበሌጥ፣  ሳር ወዘተ. የሚሰራ ሆኖ ለሰውና ለእንስሳት መኖሪያ የሚያገለግል ነው ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ  በአብዛኛው የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች እንደየግንባታ  ጥራት ደረጃቸው ፤ እንደ  የግንባታ  ቁሳቁስ  ዓይነታቸው፤ እንደ ኢኮኖሚ ደረጃቸው የተለያዩ እንደሆኑ ተገልጿል፡፡

IV, ተመራማሪዎቹ "ቤት" የሚለውን ጽንሰ-ሐሳብ በተለያየ መንገድ አብራርተዋል ፡፡ ለምሳሌ Melnikas (1998) መኖሪያ ቤት ደህንነት እና ሙቀት እንዲሁም የማረፊያ ቦታን ከሚሰጡ በጣም አስፈላጊ የህይወት ክፍሎች ውስጥ አንዱ ሲሆን  ቤት የተለየ በአንጻራዊነት የተገደበ፣ በአካል፣ በባዮሎጂያዊ፣ በማህበራዊ ቅርበት ሰዎች በቡድን አገልግሎቶችን በመቀበል የቤት ውስጥ ሥራዎችን እና ሌሎች ማህበራዊ እንቅስቃሴዎችን የሚያከናውኑበት ነው በማለት ይገለጻል፡፡

V. Smith (1776) የመኖሪያ ቤት እንደ ሸቀጥ እንደሆነ ሲገልጽ Ricardo (1817) እና Jevons (1871) ደግሞ ቤት ማለት ተጨባጭ ንብረት ወይም ቋሚ መኖሪያ ነው በማለት ይገልጻሉ ፡፡ ሌላው Grimes & Orville (1976)  በጥንት ጊዜ “መኖሪያ ቤት” የሚለው ጽንሰ-ሐሳብ ከአካላዊ ክስተት ጋር የተቆራኘ ሆኖ እንደየ አገሩ ከግንባታ ወጪዎችና  ቁሳቁሶች ዓይነት ጋር የተያያዙ በመሆናቸው  መኖሪያ ቤቶቹ ሊለያዩ ይችላሉ ይላል ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው አጥኚዎች ቤትን የማረፊያ ቦታ የተለያዩ ስራዎች የሚሰሩበት፣ሰዎች በቡድን የሚኖሩበትና ተጨባጭ ንብረት እንደሆነ ገልጸዋል ፡፡

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች ባሻገር ቤት (Home) በባህልና በማህበረሰብ ጥናቶች ውስጥ ሰፊ ትርጉም ያለው ጽንሰ-ሀሳብ ነው ፡፡ ትርጓሜው ከአካላዊ መጠለያነት አልፎ ማህበራዊ፣ ባህላዊ፣ ስነ-ልቦናዊ እና መንፈሳዊ ገጽታዎችን የሚያካትት ሆኖ የማህበረሰቡ መሰረት እና የማንነት መገለጫና ባህላዊ ማዕከል ነው ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ስለቤት

**ሀ. ቤት እንደ ቁሳዊ መጠለያ ፡-** በመሰረታዊ ደረጃ ቤት ሰዎችን ከፀሐይ፣ ከዝናብ፣ ከብርድ፣ ከዱር አራዊት እና ከሌሎች ውጫዊ አደጋዎች የሚከላለል አካላዊ ግንባታ ነው ፡፡ ይህ ግንባታ እንደየአካባቢው አየር ንብረት፣ ባህል እና የሚገኙ የግንባታ ቁሳቁሶች (ለምሳሌ ፡- እንጨት፣ ጭቃ፣ ድንጋይ፣ ሳር) ሊለያይ ይችላል (Fasil, 2007)። የቤቱ አሰራር እና አወቃቀር የማህበረሰቡን ቴክኖሎጂ እና ከአካባቢው ጋር ያለውን መስተጋብር ያሳያል፡፡

**ለ. የቤተሰብ ማዕከል ፡-** የቤተሰብ አባላት የሚገናኙበት፣ የሚወያዩበት፣ የሚተሳሰቡበት እና ትውልድ የሚተካበት ዋና ስፍራ ሆኖ የዕለት ተዕለት ኑሮ፣ ምግብ የሚዘጋጅበት እና ማህበራዊ መስተጋብር የሚከናወንበት ነው ፡፡

**ሐ. የማንነት መገለጫ ፡-** የቤቱ አሰራር፣ የውስጥ ቁሳቁሶች አደራደር፣ ጌጦች እና አጠቃላይ ይዘቱ የባለቤቶቹን እና የማህበረሰቡን ማንነት፣ እምነት እና ማህበራዊ ደረጃ ያንጸባርቃል ፡፡ ለምሳሌ፣ የሀረሪ ባህላዊ ቤት የውስጥ አቀማመጥ የቤተሰቡን ማህበራዊ ህይወት እና እንግዳ አቀባበል ባህል በግልጽ ያሳያል ፧

**መ. የደህንነትና የመረጋጋት ስፍራ ፡-** አካላዊ ጥበቃ ብቻ ሳይሆን ስነ-ልቦናዊ ደህንነትንና የመረጋጋት ስሜትን ይሰጣል ፡፡ "እንደ ቤት የለም" የሚለው ብሂል ይህንን ስሜት ይገልጻል

**ሠ. የትውስታ እና ቅርስ ማከማቻ ፡-** የቤተሰብ ታሪክ፣ ትውስታዎች እና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ቅርሶች (ቁሳዊ እና መንፈሳዊ) የሚከማቹበት ህያው ሙዚየም ነው (Unesco , 2006)።

### 2.1.7. የባህላዊ ቤት ምንነት

ባህላዊ ማለት ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፍ ሆኖ ግብአቶቹ ቁስ አካላዊ የሆኑ እና ቁስ አካላዊ ያልሆኑ ገጽታዎች የሚታይበት መሆን አለበት ይላሉ (Hamka, & Winarni, 2021)፡፡ በሌላ መልኩ (Hosseini, & Shahedi, 2012) ባህላዊ ቤቶች በኀብረተሰቡ ሕይወት ውስጥ ጉልህ የሆኑ ክስተቶችን ያቀፉ ሆነው በአካባቢው በተለመዱና ተቀባይነት ባላቸው ቅርጽ ይሰራሉ ፡፡ በተጨማሪም ባህላዊ

ቤቶች የህብረተሰቡን የዕለት ተዕለት ፍላጎቶች ለማሟላት ባሕላዊ በሆነ መንገድ፤በአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች፤በባህላዊ መሣሪያ በመታገዝ የሚገነቡ ቤቶችን የሚይዝ ነው ፡፡

ሌላው ባህላዊ የህንጻ ጥበብ (Vernacular architecture) በአካባቢው በሚገኙ ቁሳቁሶች ሙያዊ አርክቴክቶች ወይም መሐንዲሶች ሳይጠቀሙ በአካባቢው ሰዎች የተገነቡ ሕንፃዎችን እና መኖሪያ ቤቶችን የሚመለከት ሆኖ ከአካባቢው ባህል እና አየር ሁኔታ ጋር የተጣጣመ ባህላዊ ኪነ-ህንፃን ለመግለጽ የሚያገለግል ነው (Lawrence, 2013, p. 19)።

### 2.1.8. ባህላዊ ቤትና ቅርጽ

#### 2.1.8.1. ባህላዊ ቤት

የተለያየ ባህል ያላቸው ሰዎች የተለያየ ቤት እንዳላቸው ብዙ ሙግቶች ይቀርባሉ ፡፡

I, የቤት ቅርጽ እና ባህል ሁልጊዜ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው ፡፡ በብዙ አጋጣሚዎች ቅርጹ የህብረተሰቡ ባህላዊ አውድ መለኪያ ሆኖ ይታያል (Rapaport, 1991) ፡ ፡

II, ቤት የባህል አንዱ ክፍል ሆኖ በቅርጹ እና በቦታ አቀማመጡ ባህላዊ እምነቶችን እና ልማዶችን የሚያንፀባርቅ ነው (Homoud, 2009) ፡ ፡ ሌላው (Rapoport, 1991) ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች የመኖሪያ ቦታቸውን ቅርጽ የሚነድፉት ከማህበራዊና ባህላዊ ፍላጎቶቻቸው ጋር በሚስማማ መልኩ እንደሆነ ሲገልጹ (Aryani, Mulyadi, & Wahyuningsih, 2015) ደግሞ የማንኛውንም የቤት ቅርጽ ጥራት ከማህበራዊ ባህል ፍላጎቶች አንጻር ሊገመገም ይችላል ይላሉ ፡፡

III, ቤት የሚገነባው እንደ ነዋሪዎቻቸው ፍላጎት ነው (Alitajer, & Nojoumi, 2016) ። አካላዊ ቅርፁ፣ማህበራዊ እና የቦታ አደረጃጀቱም በብዙ ምክንያቶች ባህላዊ ተጽእኖ ይደረግበታል (Hashim Ali, & Abu Samah, 2009) ፡ ፡ በቦታ አደረጃጀት ውስጥ ያለው ተዋረድ እንደ አካባቢ እና ማህበረ ባህላዊ ሁኔታዎች ሊቀረጽ ይችላል (Shirazi, 2005) ፡ ፡ የማንኛውም ቤት ቅርጽ እንደየተገነባው አካባቢ፣ የሰውን ልጅ ባህሪ የባህል እና ትውፊታዊ እምነቶችን ያንጸባርቃል (Samadi, 2013)።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ቅርጽ በባሕላዊ ቤቶች ውስጥ ከሰዎች እምነት፣ ባህላዊ ልማዶች እና ከአኗኗራቸው የሚስማማ ሆኖ ከብሄረሰቡ ጋር የተያያዘ ነው ፡፡ የቤት ቅርጽ እና ባህል ሁልጊዜ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው ፡፡ በብዙ አጋጣሚዎች ቅርጹ የህብረተሰቡ ባህላዊ አውድ መለኪያ ሆኖ ይታያል፡፡ የየትኛውም ሀገር ስልጣኔ የሚለካው በባህል ነው ፡፡ የቤት ቅርጽ በሚነድፍበት ጊዜ በቤቱ ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች ህይወታቸውን እንዴት እንደሚቀርጹ ይታሰባል ፡፡

በውጤቱም  ቅርጹ  በባህል አማካኝነት የጋራ ልምዶቻችንን የሚቀርጹ ባህሪያትን ያመነጫሉ ፡፡ ሰዎች የሚኖሩበት  ቤት፣ከተሞች፣እቃዎች፣ የሚነደፉ ነገሮች ሁሉ በአዲስ መልክ እንደሚቀርጹ መገንዘብ ይቻላል ፡፡

### 2.1.8.2. የባህላዊ ቤት ቅርጽ

- **የቅርጽ ምንነት**

ቅርጽ ማለት "ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከነሐስ የተሰራ የአንድ ነገር ምስል፤የአንድ ነገር ውጫዊ ገጽታ፤መልክ ገጽ" ነው (አማርኛ መዝገበ ቃላት፣1993፣ገ.170) ፡፡ ሌላው የጋራ አስተሳሰብ እና ቅርፅ ማዕከላዊ አቀማመጥ በባህላዊ ጽንሰ ሀሳብ ላይ የተመሰረተ ነው ፡፡ ሌላው ቅርፅ ከመስመሮች ወይም ቀለሞችና ሌሎች ጋር የሚገናኝ ሆኖ እንደ አራት ማእዘን፣ሶስት ማእዘን እና ክብ ያሉ የጥበብ ስራዎችን  የሚይዝ ነው (Hosseini, Mursib, Nafida, and Shahedi, 2012) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ቅርጽ ከድንጋይና ሌሎች ነገሮች የሚሰራ ምስል ሆኖ ሶስት፣አራትና ክብ ቅርጽን ያካትታል ፡፡

### 2.1.9. ለውጥ እና ቀጣይነት

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር የለውጥ እና ቀጣይነት ብያኔ እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡ እንደ (Smith et al., 1982, P. 127) ‹‹ቀጣይነት የሚለው ቃል የሚያመለክተው ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን የአንድነት ሂደትን ከመጠበቅ ወይም ከባህላዊነት በጣም የተለየ ነው"፡፡ የጥንካሬ ማንነት አዲስ መገለጫን የሚጨምር መላመድ እና ለውጥ ነው ፡፡

ለውጥ በጊዜ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ባለው ማንነት ውስጥ ያለ ልዩነት ሲሆን ለውጥ ሲከሰት የሚታይ ልዩነት አለ፤ ከሚታየው ልዩነት ጋር በለውጥ ውስጥ ያለው ርዕሰ ጉዳይ ማንነት ይቀጥላል ሆኖም ቀጣይነት እና ለውጥ በባህላዊ ሽግግር አውድ ውስጥ የሚተገበሩ ተለዋዋጭ ጥንዶች ናቸው (*Nisbet*, P.197) ሌላው ለውጥ (change) የሚለው ቃል የመጠን ወይም የአይነት ቅየራ (መቀየር)ን የሚይዝ ሆኖ  ለውጥ እንደ ጊዜና እንደ ቦታ ሌላው የቁስ አካል የህልውና ገጽታ ነው ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት እንደተቻለው ለውጥ በጊዜ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ባለው ማንነት ውስጥ ያለ ልዩነት የሚል ትርጉሙን የሚገልጽ ሲሆን በዚህም ልማድ የሚነሳ ሆኖ በልማድ ተደጋጋሚነት ስር ቀጣይነት የሚገለጽ ነው ፡፡ ምክንያቱም አንድን ነገር ልምድ ሆነ ሲባል እየተደጋገመና እየቀጠለ መሄዱን ያሳያል ፡፡

በዚህ ጥናትም እነዚህ እሳቤዎች መሰረት ተደርገው የብሔረሰቡ ባህላዊ የቤት አሰራር ዕውቀት ከለውጥና ቀጣይነት ጋር ተያያዥ የሆኑ እሳቤዎች ተመርምረውና ተጠንተው ቀርበዋል ፡፡

ለውጥን "በአሮጌ ነገር ምትክ አዲስ እና ጥቅም ላይ የዋለ አዲስ ነገር" (Logman Dictionary of English, 1986 P.19) በማለት ይገልፃል ፡፡

‹‹ለውጥ አዲስ ሁኔታ፣ የተለየ ነገር፣ ልዩነት›› ሲል ይበይነዋል (አማርኛ መዝገበቃላት፣ 1993፣ ገ.21)

‹‹ለውጥ ማንኛውንም አካልና ክስተት እንዲሁም የእንቅስቃሴ መስተጋብርን አቅፎ በተለያዩ ቅርጾች፣ይዘቶች፣ስርዓቶች ወዘተ…ውስጥና መሀከል ባለው መስተጋብር አማካይነት ይከናወናል›› (ማርክሲዝም ሌኒኒዝም፣ 1978፣ ገ.33) ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በተለያዩ ምሁራን ከቀረቡት ብያኔዎች መረዳት እንደተቻለው ለውጥ በጊዜ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ባለው የሰው ልጅ(ማንነት) ውስጥ ያለ ልዩነት የሚል ትርጉምን የሚገልጽ ሆኖ በልማድ ተደጋጋሚነት ስር የሚገለጽ ቀጣይነት ነው ፡፡ ምክንያቱም አንድን ነገር ልምድ ሆነ ሲባል እየተደጋገመና እየቀጠለ መሄዱን ያሳያል ፡፡ በዚህ ጥናትም እነዚህ እሳቤዎች መሰረት ተደርገው የብሔረሰቡ ባህላዊ የቤት አሰራር ዕውቀት ለውጥና ቀጣይነት እንዲሁም ተያያዥ የሆኑ እሳቤዎች ተመርምረውና ተጠንተው ቀርበዋል ፡፡

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች በተጨማሪ ለባህላዊ ቤቶች መለወጥ ምክንያት የሚሆኑ ጉዳዮች ቀጥሎ ተገልጸዋል ፡፡

- **ባህላዊ ቤቶች ላይ የሚደርሱ ተጽእኖዎች**

ባህላዊ ቤቶች እንዲለወጡ ምክንያቶቹ ብዙ ቢሆኑም ዋና ዋናዎቹ ሦስት ናቸው ፡፡ እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል፦

ሀ. **የመስሪያ ቁሳቁስ ፡-** እንደ እንጨት እና ድንጋይ የመሳሰሉ ባህላዊ የቤት መስሪያ ቁሳቁሶች በኮንክሪት በመስታወት እና በብረት ተተክተዋል፡፡

**ለ.ቴክኖሎጂ ፡-** የዓለም በአንድ መንደር ስር መሆን፣የውጪው ዓለም የቤት አሰራር እንዲሁም የከተማ ልማት እንቅስቃሴዎች በባህላዊ ቤት መሰረት አጣጣል እና ቅርጽ ላይ አይነተኛ ተጽእኖ

ፈጥረዋል ፡፡ ሌላው በአሁን ወቅት ባህላዊ ቤቶች እንደ ኤሌትሪክ ዝርጋታ፣ የውሃና ፍሳሽ እንዲሁም የኢንተርኔት ዝርጋታዎች አካተው እየተገነቡ ነው፡፡

**ሐ.አገልግሎትና የአኗኗር ሁኔታ ፡-** የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘዴ ከመለወጡ አንጻር ባህላዊ ቤቶች ዘመናዊ ክፍሎችን እና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ስፍራዎችን አካተው እየተገነቡ ነው ፡፡ ሌላው ከአንድ በላይ ክፍል መያዛቸው፤ በቤት ውስጥ የስራ መስሪያ ክፍል ወይም ቢሮ እንዲሁም በቤት ውስጥ እና ከቤት ውጪ የሚኖሩ ክፍት ቦታዎች ውስጥ ሰዎች እንዴት እንደሚኖሩና ስራቸውን እንዴት እንደሚያከናውኑ ማሳያ ነው (Rapoport, 1969 and Oliver, 1997) ፡፡

እንደ (Oliver, 2006) ቀጣይነት በባህላዊ ቤት አሰራር ውስጥ ሦስት ዋና ዋና ነጥቦችን በስሩ የያዘ ሲሆን ይህም ቀጥሎ ቀርቧል ፡፡

**ሀ.ባህላዊ ማንነት ፡-** ባህላዊ ቤቶች የማህበረሰቡን ባህላዊ ወግ ፣ እሴት እና ልማድ በመግለጽ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ፡፡ ይህንንም ብዙ የማህበረሰብ አባላት ጠብቀው እያኖሩት ያለ ክዋኔ ነው፡፡

**ለ.የቤት መስሪያ ቁሳቁስና የአሰራር ዘዴዎች ፡-** በተወሰኑ አካባቢዎች አገር በቀል (ባህላዊ) የግንባታ ቁሳቁስ እንዲሁም ባህላዊ የቤት አሰራር ዘዴዎች ተጠብቀው ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው ፡፡

**ሐ. ወካይነት ፡-** እንደ የቤት መሰረት አጣጣል ፤የግድግዳ ስራ እና ክብ ቅርጽ አሰራር እንዲሁም ቀለም አመራረጥ ያሉ ጉዳዮች ማህበረሰባዊና ሀይማኖታዊ ትርጉም እንዲሰጡ ተደርገው የመስራታቸው ሁኔታ እንደቀጠለ ነው ፡፡ የቀረበው መረጃ በአንዳንድ አካባቢዎች ቀጣይነት በቤት አሰራር ውስጥ የብሔረሰቡን ባህል፣ ልማድ፣የቤት አሰራር ስልቱንና የመስሪያ ቁሶች ተጠብቀው መዝለቃቸውን የሚያሳይ ነው ፡፡

- **ለውጥና ቀጣይነት በባህላዊ ቤት አሰራር ላይ**

ባህላዊ ቤቶች የብሔረሰቡን አካባቢያዊ ምንነት፤ እሴት እና ባህል የሚገልጹ ቢሆንም በጊዜ ሂደት የተወሰኑት የአሰራር ሁኔታዎች ቀጣይነት ሲኖራቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በመተው ላይ ናቸው ፡፡

**ቀጣይነት ፡-** ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት  የብሔረሰቡን ባህል እና እምነት የሚያንጸባርቁ ተምሳሌታዊ የሆኑ የማስዋብ ስራዎች በመስራት፤ የቤት አቀማመጥ ምርጫ ሁኔታ እንዲሁም አካባቢያዊ እና አገርበቀል የሆኑ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ቀጣይነትን እያረጋገጠ ነው ። ለውጥ ደግሞ ምንም እንኳን በባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት ላይ ባህሉን ጠብቆ እንዲሰራ ጥረት ቢደረግም የዓለም አንድ መንደር መሆን፤ ዘመናዊነት እንዲሁም ከተማ በባህላዊ የቤት በአሰራር ሂደት ላይ ተጽእኖ ፈጥረዋል ። ስለሆነም አብዛኛዎቹ ባህላዊ ቤቶች ዘመናዊ የቤት መስሪያ ቁሳቁስ፤ቴክኖሎጂዎችን እንዲሁም የውጪው ዓለም የቤት አሰራር እየተገበሩ ይገኛል ። ይህም የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘይቤ እና የምጣኔ ሀብት ለውጦች ውጤት መሆኑን ያመለክታል  Preston (2016)፡፡

አገር በቀል የቤት አሰራር ጥበብ በየወቅቱ ነባር የአሰራር ልምዶችን በማስቀጠል፤ከተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦችን ፤ሽግግሮሽን በመቀበል እንዲሁም ልምምድን በማካተት የማህበረሰቡን ወቅታዊ ፍላጎት ከግምት ውስጥ አስገብቶ በእድገት ውስጥ ይገኛል Rapoport (1969) and Rudofsky (1964)፡፡

ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ ቀጣይነት ከቦታ፣ከጊዜ እና ቁሳዊ ሁኔታ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሲሆን ከቅርጽ፣ከአገልግሎት፣ከማህበረሰባዊ ጉዳዮች አንጻር የተለያየ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል (Philokyprou, 2015)፡፡

እንደ (Qian, 2021) ለገጠር አካባቢ ልማት የማህበረሰባዊና ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦች ፤ የተቀናጀ የገጠርና የከተማ ልማት መኖር አይነተኛ ምክንያቶች ናቸው ። እነዚህም ለመኖሪያ ቤቶች ቅርጽና አቀማመጥ ለውጥ መኖር፤ የአኗኗር ዘይቤ መቀየር፤እንዲሁም የከተማና የገጠር ትስስር ሂደት አይነተኛ ማሳያ ናቸው ። በተጨማሪም  እንደ Qian (ibid) ሀሳብ የዘመኑ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንዳስቀመጡት በኢትዮጵያ ዘመናዊነት ከመስፈኑ በፊት በርካታ ባህላዊ የቤት አሰራር ስልቶች እንደነበሩ ያስቀምጣሉ ። ይህም ባህላዊ ቤቶች ተምሳሌትነታቸው ከትውልድ ትውልድ ቀጣይነት እንዳይኖረው ተጽእኖ ፈጥሯል ። ቢሆንም የዓለም የቤት አሰራር ስልት በብዙ የእድገት እርከን ውስጥ ማለፉ እሙን ነው ። በተጨማሪም  ይህ እሳቤ በጥናቱ ዳራ ሲቃኝ Sheriff and Sabry (2000) እንደገለጹት ጥንታዊ ሰዎች በዛፍ ስር ፤በዋሻ እና የተለያየ ቅርጽ ባላቸው አለቶች ውስጥ ይኖሩ ነበር እንዲሁም Sherif and Sabry (ibid) ስለ ግብጾች፣ጀርመኖች፣እስካንዲኒቪያኖች እንዲሁም አጠቃላይ ስለ አውሮፓ የቤት አሰራር ስልት አስቀምጠዋል። ጎንለጎን የአንድ ቦታ ወይም አካባቢ የቤት አሰራር ስልት ቀጣይነት ከቦታ እና ከጊዜ ጋር ፣ከአሰራር ቅርጽ ጋር፣ ቤቶችን ከአገር በቀልነትና ባህላዊነት አንጻር ከመመደብ አንጻር፤ ከሚሰጡት አገልግሎትእንዲሁም ከማህበረሰብ ማንነት ጋር ትስስር

እንዳለውም ገልጸዋል ። ጉዳዩ ሰፊ ንባብ እና ትርጉምም እንደሚያስፈልገው ምልከታውን አስቀምጧል (Philokyprou, 2015)፡፡

አጠር ባለ ምልከታ በIron Age and the Etruscan period ወቅት በግንባታ ቁሳቁሶች እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ይሰጥ የነበረው አጽንኦት በቅሪት አካል ጥናት ግኝት አተረጓገም ላይ አይነተኛ ተጽእኖ አሳድሯል ። እንዲሁም በባህላዊ የቤት አሰራር ልምምድ ቀጣይነት ላይ ጥላውን አጥልቷል። ይህም በቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ከታየው ለውጥ ይልቅ በቤት መስሪያ ግብአቶች ላይ የታየው ለውጥ በቤት ግንባታ ጥበብ ላይ እንዲኖር ያረገው አይነተኛ ለውጥ ዋና ምክንያት ሆኖ ተጠቅሷል Pallottino (1975)፡፡

ነገር ግን የግንባታ ስልት ቀጣይነትን ከተለያዩ የግንባታ ግብአቶች አንጻር ማየት በቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ላይ የሚኖረውን አረዳድ  ያጠነክራል ።

ከመነሻው እንደ Pallottino (1975) ያሉ ምሁራን የEtruscan የቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ሽግግር የግሪክና የምስራቃዊያን ተጽእኖ ውጤት እንደሆነ አሳይተዋል ። አክለውም የዘመናዊ ቤት መስሪያ ቁሳቁሶች በእነዚህ አገራት መመረት Etruscan የቤት አሰራር ስልት ላይ ለውጥ አምጥቷል ። ከአስር ዓመታት በኋላ Torelli (1985) የተለየ ምልከታ አስቀምጦ ነበር ። ይህም ከሌሎች አገሮች  ተጽእኖ ይልቅ በአገሪቱ ውስጥ በነበሩት ተጽእኖ ፈጣሪ ማህበረሰብ ተጽእኖ ምክንያት የመጣ ለውጥ መሆኑን ገልጿል። በአገሪቱ ውስጥ የነበሩት ተጽእኖ ፈጣሪ ማህበረሰቦች ያላቸውን ሀብት ለማሳየት ከነዚያ አገራት የሚገቡትን የቤት መስሪያ ቁሳቁስ ይጠቀሙ እንደነበርም እንደ ማሳያ አቅርቧል ። በተቃራኒው ቅርብ በሆነ የIzzet (2007) እና  Rohner (1996), ምልከታ  አዳዲስ የሆኑ የግንባታ ቁሶችን መጠቀምን ከከተማዊነት ጋር አያይዞ አቅርቧል ። ይህም በግንባታ ቁሶች እና በግንባታ ስልት ላይ የሚታዩ ለውጦች አዳዲስ የከተማ አሰራር ልምዶችን ወደ ራስ ለማምጣት ከመነጨ የማህበረሰቡ ፍላጎት አንጻር እንደሆነ አትቷል  ይህም ምልከታውን የለውጡ ምክንያት ከግንባታ ቁሶች ለውጥና ከቴክኖሎጂ ለውጥ ይልቅ የአገነባብ ስልት ላይ አጽንኦት መሰጠት እንዳለበት ትኩረት ሰጥቶ አልፏል ስለሆነም ምሁራኖች ለውጡ በማህበረሰቡ የባህርይ ለውጥ  ማምጣትና ባህልን ከማደስ አንጻር እንደሆነ ትኩረት እንዲያረጉ አድርገል ። ይህም የአመለካከት ለውጥ የቴክኖሎጂ ሽግግር  ላይ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ የቤት አሰራር ጠባያት መለያየት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ጥቆማ ሰጥቷል ።

## 2.2. ንድፈ ሀሳባዊ ማሕቀፍ

በዚህ ጥናት የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፣የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ ፣ የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ እና የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡ የንድፈ ሀሳቦቹ በጥናቱ ውስጥ ያላቸው አቀማመጥ ወይም ቅደም ተከተል ታሪካዊ አመጣጣቸውን (አፈጣጠራቸውን) መሰረት አድርገው ስራ ላይ የዋሉ ሲሆን እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡

1. **የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ፡-** (Structural Functionalism Theory (Late 19th to early 20th century)
2. **የሥነ ትእምርት ንድፈ ሀሳብ ፡-** (Semiotics Theory Early to mid 20th century)
3. **የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሃሳብ ፡-** (Social Learning Theory (1950s–1970s)
4. **የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ፡-** (Social Constructivism Theory (1960s–1980s)

### 2.2. 1. የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ

የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሐሳብ መሠረቶች በ19ኛው ክፍለ ዘመን በታላላቅ ምሁራን እንደ (Auguste Comte)፣ (Herbert Spencer) እና (Emile Durkheim) አማካኝነት ተጥለዋል ፡፡ በ20ኛው ክፍለ ዘመንም እንደ (Bronislaw Malinowski) (A.R. Radcliffe-Brown) ያሉ አንትሮፖሎጂስቶች ከፍተኛ አስተዋጽኦ አበርክተዋል (Parsons & Bales, 1955 )። ቀደምት የተግባራዊነት ባለሙያዎች፣ ኅብረተሰቦች በእድገት ደረጃዎች ውስጥ እንዴት እንደሚያልፉና አንዳንድ ኅብረተሰቦች ከሌሎቹ በበለጠ ፍጥነት ለምን እንደሚያድጉ ለመረዳት ይጥሩ ነበር ፡፡ ተቋማትና ማኅበራዊ ሚናዎች ተዋህደው ወጥ የሆነና ሊተነበይ የሚችል ማኅበራዊ ሥርዓት ይፈጥራሉ ከሚል መነሻ፣ኅብረተሰቦች ማኅበራዊ መረጋጋትንና ትስስርን እንዴት እንደሚያሳዩ መርምረዋል (Sean, 2005)።

እንግሊዛዊው ፈላስፋ Herbert Spencer "የሶሺዮሎጂ መርሆች" (Principles of Sociology) በተሰኘ መጽሐፋቸው፣ በኅብረተሰብ ውስጥ "የበረታው የሚቀጥልበትንና የደከመው የሚጠፋበትን" (survival of the fittest) ሐሳብ በማራመድ ይታወቃሉ (Spencer, 1896) ። Spencer ዋነኛ ትኩረት ማኅበራዊ ሚዛን (social equilibrium) ላይ ነበር ፡፡ እርሳቸው እንደሚሉት፣ ኅብረተሰብ በተፈጥሮው ወደ ሚዛናዊነት የማዘንበል ባህሪ አለው፤ ማኅበራዊ ለውጥ በሚከሰትበት ጊዜ መዋቅሩ ራሱን አስተካክሎ ወደ ነበረበት ሚዛን ይመለሳል ፡፡ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ዋና መሠረት የተጣለዉ በፈረንሳዊው የማህበረሰብ አጥኚ Emile Durkheim ነው ፡፡ Durkheim በመጀመሪያ ማህበራዊ ተቋማትን ማብራራት

የፈለገው በህብረተሰቡ ውስጥ ያሉ ግለሰቦች የራሳቸውን ባዮሎጂያዊ ፍላጎቶች የሚያሟሉበት የጋራ መንገድ ነው ። ለአጠቃላይ ህብረተሰብ እና ለህይወት አሠራር ያላቸውን አስተዋፅኦ በማብራራት የባህላዊ እና ማህበራዊ ባህሪያትን ዋጋ ለመረዳት ፈለገ ።

የንድፈ ሐሳቡ ዋነኛ መሠረት የተጣለው ግን በፈረንሳዊው የሶሺዮሎጂ አባት Emile Durkheim ነው። Durkheim ማኅበራዊ ተቋማትን ሲያብራራ፣ ግለሰቦች ሥነ-ሕይወታዊ ፍላጎቶቻቸውን በጋራ የሚያሟሉበት መንገድ እንደሆነ ከመግለጽ ባለፈ፣ተቋማቱ ለአጠቃላይ ማህበረሰብ ህልውና የሚያበረክቱትን አስተዋጽኦ ለመረዳት ፈልጓል ። Emile Durkheim Durkheim በአራት ቁልፍ ጉዳዮች ላይ ያተኩር ነበር ፡- (1) የኅብረተሰብ አፈጣጠርና አንድነት፣ (2) የሃይማኖት ሚና፣ (3) ራስን የማጥፋት ማኅበራዊ መንስኤዎች (4) ማኅበራዊ መተላለፍና ወንጀል ።

Durkheim የመጀመሪያውን ትኩረቱን "በማህበረሰቡ ውስጥ የሥራ ክፍፍል" በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ ተናግሯል Durkheim የስራ ክፍፍል በሁሉም ማህበረሰቦች ላይ በግልጽ እንደሚታይ አስተዋለ ይህም ለምን እንደሆነ ለማወቅ ፈለገ Durkheim ለዚህ ጥያቄ የሰጠው መልስ በ"አንድነት" እሳቤ ውስጥ ሊገኝ ይችላል ። በጥንት ዘመን ቀደምት የማህበረሰቦች እርስ በርስ ትብብር ሁሉንም ሰው በአንድነት እንዲይዝ አድርጓል ። አንድነት እዚህ ላይ ሁሉም ሰው በአንጻራዊ ሁኔታ ተመሳሳይ ስራዎችን ሲሰራ ያሳያል ። ለምሳሌ፣ በአዳኝ ማህበረሰብ ውስጥ ጉልህ የሆነ የስራ ክፍፍል አልነበረም፤ ሰዎች ተሰብስበው ያድኑ ነበር ። Durkheim የጋራ እሴቶች፣ የጋራ ምልክቶች እና የልውውጥ ሥርዓቶች በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የመተሳሰሪያ መሳሪያዎች ሆነው ይሠሩ እንደነበር በንድፈ ሀሳብ አስቀምጧል ። ዘመናዊ እና ውስብስብ በሆኑ ማህበረሰቦች ውስጥ ግለሰቦች በጣም የተለያዩ በመሆናቸው ተመሳሳይ ተግባራትን አይፈጽሙም ። ሆኖም ልዩነቱ ወደ ተለየ የአብሮነት በልዩነት ቅርፅ ይመራል ። Durkheim ይህንን ተፈጥሯዊ መተባበር ሲል ጠርቶታል ። ለምሳሌ አንድ የግንባታ ሠራተኛ ለሰዎች ቤት መገንባት ቢችልም፣ በሥራው ላይ ጉዳት ከደረሰበት ለሕክምና ወደ ሐኪም ቤት ይሄዳል (ምናልባትም አሠሪውን ለመክሰስ ጠበቃ ይሆናል) ። በኅብረተሰቡ ውስጥ ያለው የሥራ ክፍፍል ልዩ ችሎታን ይጠይቃል ። ውጤቱም ተፈጥሯዊ ወይም አንድነት ነው (Stanley , 1984) ፡፡

Radcliffe Brown እና Malinowski ለግለሰብ ስነ ህይወታዊ ፍላጎት ሳይሆን ለማህበራዊ መዋቅር ትኩረት ይሰጣሉ ። እንደ Malinowski አንድ ሰው ለመኖር ሊሟሉለት የሚገቡ አራት ማህበራዊ ተቋማት ምጣኔ ሀብት፣ ማህበራዊ ደንብ፣ ትምህርት እና ፖለቲካዊ ተቋማት ሲሆኑ እነሱን

ለማግኘት በባህሉ ውስጥ የሚተገበሩ ትዕምርታዊ ሥርዓቶች (እንደ ሃይማኖት፣ እምነት እና እሴቶች) ሚናቸውን ይወጣሉ ። እነዚህም የማህበረሰቡ ህልውና እንዲቀጥል የማድረግ ተግባር አላቸው ይላሉ የባህልን ማህበራዊ ፋይዳ በማሳየት ሂደት፣ ማህበራዊ ሁኔታ ስነ ልቡናዊ እና ስነ ህይወታዊ ፍላጎቶች ማሟያ ሳይሆን እነሱን በበላይነት የሚገዛ ነው ይላሉ ። ትዕምርቶች አንድን ደንብ መግለጫ መሳሪያ መንገድ ናቸው ። ሌላው Malinowski ባህላዊ ልምምዶች የፊዚዮሎጂያዊ እና ስነ ልቦናዊ ተግባራት እንደ ምኞትና እርካታ እንደነበሩ ተከራክረዋል ። የRadcliffe-Brown መዋቅራዊ ተግባራዊነት በማህበራዊ መዋቅር ላይ ያተኮረ ነው ። Radcliffe Brown እንደ Malinowski ለግለሰብ ስነ ህይወታዊ ፍላጎት ሳይሆን ለማህበራዊ መዋቅር ትኩረት ይሰጣሉ ። Malinowski ከላይ የገለጿቸው አራት ማህበራዊ ተቋማት ምጣኔ ሀብት፤ማህበራዊ ደንብ፤ትምህርት እና ፖለቲካዊ ተቋማት የማህበረሰቡ ህልውና እንዲቀጥል የማድረግ ተግባር እንዳላቸው ያስረዳሉ ። Radcliffe-Brown የማህበራዊ ክስተቶች ማብራሪያዎች በማህበራዊ ደረጃ መገንባት እንዳለባቸው ተከራክረዋል ። ለRadcliffe-Brown ግለሰቦች በህብረተሰቡ ውስጥ ባለው የማህበራዊ ሚናዎች አጠቃላይ መዋቅር ውስጥ ያላቸውን አቋም በተመለከተ ብቻ ጉልህ ነበሩ (Parsons, 1951)፡፡

አንድ ማህበራዊ ሁኔታ የሚገለጸው ከሌላ ማህበራዊ ሁኔታ አንጻር እንጂ ከስነ ልቦናዊ ፍላጎት አንጻር ሊሆን አይገባም የሚል አቋም አላቸው ። በተጨማሪም የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በማህበራዊ መዋቅሩ ስር ነው ። በዚህ ውስጥም ባህሉ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ተግባር የሚቆጣጠሩ ህግና ደንቦች አሉ ። ከግለሰባዊ ፍላጎት ይልቅ ለማህበረሰቡ ህልውና ቅድሚያ ይሰጣል የማህበረሰቡ ማህበራዊ የመዋቅር ሥርዓት ቀጣይነት የሚኖረው በማህበራዊ ህይወቱ ሂደት ነው ።

ቀደምት መዋቅራዊ ተግባራዊ ባለሙያዎች በተለያዩ መንገዶች ማህበረሰቦች በእድገት ደረጃዎች ውስጥ እንዴት እንደሚያልፉ አንዳንድ ማህበረሰቦች ከሌሎች በበለጠ ፍጥነት እንዴት እንደሚያድጉ እና በባህሎች ውስጥ የማህበራዊ ለውጦችን ተመሳሳይነት ለመረዳት ፍላጎት ነበራቸው ። ተቋማት እና ማህበራዊ ሚናዎች አንድ ላይ ተጣምረው ንድፍ ያላቸው እና ሊገመቱ የሚችሉ ማህበራዊ ዝግጅቶችን ይመሰርታሉ ብለው ገምተው የነበረ ሲሆን በዚህም ማህበረሰቦች የማህበራዊ እኩልነት እና የመተሳሰር ዝንባሌን የሚያሳዩባቸውን መንገዶች መርምረዋል (Sean, 2005) ።

20ኛው ክፍለ ዘመን እየገፋ ሲሄድ በተግባራዊ አስተሳሰብ በርካታ ጠቃሚ አስተዋጽኦዎች ታዩ መዋቅራዊ ተግባራዊነት ከ1850ዎቹ ጀምሮ አንትሮፖሎጂ ውስጥ በሚያስደንቅ ስኬት ተግባራዊነቱም በአሜሪካ በአንትሮፖሎጂ፣በሶሺዮሎጂ ከነበረው በበለጠ ፍጥነት እያደገ መጥቷል ። Parsons ያነሱት ዋናው ጥያቄ የማህበራዊ ስርዓቱን ህልውና እና ጥገና ለማረጋገጥ ግለሰቦች እንዴት የአንድ

ማህበረሰብ አባል የሚሆኑባቸውን ሂደቶች የሚመለከት ነው (Parsons, and Bales, 1951) ፡፡ እንደ Parsons ገለጻ ማህበረሰብ ዓለም አቀፋዊ የማህበራዊ ስርዓት ሲሆን በተቀናጀ የእሴት ስርዓት ላይ የተመሰረተ ነው ።

ግለሰቡ በማህበራዊ ሥርዓቱ ውስጥ የሚሳተፈው በስርአቱ ውስጥ ባለው ልዩ ልዩ ሚናዎች እና የስራ ቦታዎች መሰረት ከሌሎች ጋር በመገናኘት ሲሆን በተለይ ቤተሰብ ትልቅ ሚና ይጫወታል (Parsons, and Bales, 1951) ። Freud's Psychoanalysis ንድፈ ሀሳብ ላይ በጥልቀት በመሳል Parsons ወንድ እና ሴት ልጆችን በመለየት ወደ ተወሰኑ ወንድ እና ሴት ሚናዎች ከስርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዘ ተግባር-ተኮር ሚናዎች የወንዶች እና የሴቶች ተለይተው ይታወቃሉ ። እነዚህ ጾታ-ተኮር ተደጋጋፊ ሚናዎች የቤተሰብን ስርዓት እንዲሁም ደግሞ የህብረተሰቡን አጠቃላይ ስርዓት ሚዛን ይጠብቃሉ ።

በተለያዩ የዓለም ክፍሎች በሚኖሩ የሶሺዮሎጂስቶች እገዛ የተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ከጊዜ ወደ ጊዜ ቀስ በቀስ ዳበረ ። ለዚህ ፅንሰ-ሀሳብ የመጀመሪያ እድገት በጣም ጉልህ አስተዋፅኦ ያበረከቱት Emile Durkheim እና A.R. Radcliffe-Brown ናቸው ። ይሁን እንጂ Herbert Spencer የማህበረሰቡን የተፈጥሮ ምርጫ ይደግፉ ነበር ። Spencer በማህበረሰብ ውስጥ ሚዛናዊ የመሆን ተፈጥሯዊ ዝንባሌ እንዳለ ተከራክረዋል ። ስለዚህ የማህበረሰብ ሁኔታ ሲቀየር በማህበራዊ መዋቅሩ ላይ የሚፈጠሩ ለውጦች ሚዛናዊ ይሆናሉ ይላሉ ።

Parsons ለግለሰቦች ሚና ከመመደብ ይልቅ በተለያዩ የማህበረሰቡ ክፍሎች ውስጥ እንዴት እንደሚስማሙ በራሳቸው ማግኘት እንዳለባቸው ሲገልጹ አያይዘውም አንዱ ሌላውን በመጨመር በባህል ከተዋቀሩ የጋራ ስርዓት አንፃር ይገለጻል ። ግለሰቡ ከማህበረሰቡ ጋር የሚያቆራኘውን ደንቦች እና እሴቶች በየጊዜው ያስታውሰዋል ። ስለዚህ ግለሰቡ በባህላዊ ስርዓታቸው የተገለጹ ግላዊ ግቦች ላይ ለመድረስ ይነሳሳል ። በተመሳሳይ ጊዜ እነዚህ ግቦች አጠቃላይ ማህበረሰቡን ይጠቅማሉ ። እ.ኤ.አ. በ19 60 ዎቹ ውስጥ የተግባራዊነት ተፅእኖ ማሽቆልቆል ሲጀምር ፣ የቋንቋ እና የባህል ለውጦች በማህበራዊ ሳይንስ ውስጥ እጅግ በጣም ብዙ አዳዲስ እንቅስቃሴዎችን አስከትለዋል ። ይህ የሶስተኛው ትውልድ የማህበራዊ ንድፈ ሃሳብ ተነሳሽነት ያላቸው አቀራረቦችን፣ ወሳኝ ንድፈ ሃሳቦችን፤ስነ -ሥርዓተ-ፆታን፤ተምሳሌታዊ መስተጋብርን፤መዋቅራዊነትን፤ ድኅረ መዋቅራዊነትን እና ንድፈ ሐሳቦችን ያጠቃልላል (Kingsley, 1959) ፡፡

በዚህ ጥናት የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ በአካባቢው ቤቶቹ ሲሰሩ ከብሔረሰቡ እርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነት፣ እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ቡድን በቤቱ ስራ ወቅት የሚኖራቸው የስራ ድርሻ እንዲሁም በማህበረሰቡ በቤቱ ስራ ወቅት የሴትና የወንድ ሚናን፤ለውጥና ቀጣይነትን ለመተንተን

ጥቅም ላይ የዋለ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ይህ ንድፈ ሀሳብ  የምሰሶና ጸታን ግንኙነት ለመግለጽ ተግባራዊ ሆኗል ፡፡

በዚህ ጥናት የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሃሳብን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ሀሳቦች ተጠቅሰዋል ፡፡ ይሁንና ከዚህ ሥራ ጋር የበለጠ ቅርበት ያላቸውና ለጥናቱ የተጠቀምኳቸው የRadcliffe Brown, Malinowski, Emile Durkheim እንዲሁም የParsons and Bales (1951) ሥራዎች ናቸው ፡፡

### 2.2.2. የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ

ሥነ ትዕምርት የምልክቶች እና የትርጓሜ ጥናት አጠቃቀምና ትንተና ነው ፡፡ የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ የምልክቶችን ሚና ከማህበራዊ እና ባህላዊ ደረጃ አንጻር ያጠናል ፡፡

የሥነ-ትዕምርት ንድፈ ሃሳብ የፍቺ አሰጣጥ ጥቆማን፣ የፍንጭአሰጣጥ ሂደትን፣ የአሰያየም አይነትን የተመሳስሎ ባህሪን፣ የምስያ ንፅፅርን ፣የዘይቤ አጠቃቀምን(metaphors)ትዕምርታዊ ውክልናን (symbolism) የማመላከትተግባርን (signification) እና የተግባቦት (Communication) ሂደቶች ይመለከታል (Danesi, 2004) ፡፡

የሥነ ፍቺ ንድፈ ሀሳብ መስራቾች Ferdinand de Saussure እና Charles S. Peirce ናቸው ፡፡ ሀሳባቸውም ሥነ ፍቺ ምልክቶችን ለመግለፅ እና ለመከፋፈል መሰረታዊ ጉዳይ እንደሆነ ነው (Danesi, 2004) ፡፡

“Semiotics” የሚለው የእንግሊዝኛ ቃል የመጣው “semeion” ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ፍቺውም “ትእምርት” ወይም “sign” ማለት ነው፡፡ “semiotics” ወይም “semiology” ትእምርቶች በኅብረተሰቦች አኗኗር ውስጥ ያላቸውን ትርጉም የሚያጠና ሳይንስ ነው Berger (2010, P.4) ፡፡

በአጠቃላይ አሁን ላይ የሚደገፈው ዘመናዊ semiotics የተጀመረው በሁለት ፀሐፊዎች በGeneva ዩኒቨርሲቲ የቋንቋ ፕሮፌሰር Ferdinande de Saussure (1857–1913) አቀራረብ “semiology” እና በHarvard ዩኒቨርሲቲ ፈላስፋ Charles S. Peirce (1839–1914) “semiotics” ሳይንስ ነው (Berger,2010,P.4) ፡፡

“ምልክቶች ውስብስብ ጉዳይ ናቸው ፡፡ ምልክቶች ሙሉ በሙሉ የዘፈቀደ አይደሉም ብሎ ያምን ነበር፡፡ ይህም ብዙውን ጊዜ በመካከላቸው አንድ ዓይነት ግላዊ-ዘፈቀደ ወይም መሠረታዊ ትስስር

እንዳለ ይጠቁማል ። ለነገሮች የተሰጡ ተምሳሌታዊ ጠቋሚዎች ለነገሮች ትርጉም ያስገኛሉ" (Berger, 2010, P.14)፡፡

ምልክቶች ጠቃሚ የሆነ ታሪካዊ እና ባህላዊ ትርጉሞች ያላቸው ነገሮች ናቸው ። የዳዊት ኮከብ ለአይሁዶች ፤የአሜሪካ ባንዲራ ከአሜሪካውያን ጋር የሚገናኙ ሲሆኑ እነዚህ ምልክቶች ከታሪክ እና ከባህል ጋር የተሳሰሩ ናቸው ። በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ጠቃሚ ሚናዎች አላቸው (Clifford, 1973, P.45) ።

Peirce የማንኛውም ትእምርት ፍቺዎች መሰረት የትእምርቱ አካል በሆኑ ሦስት የትእምርት አላባውያን ነው ይላል Peirce ውክልና (Representamen) ቁሱ የሚያመለክተውን ምስልና ሀሳብ ይመለከታል ። ቁስ (Object) ደግሞ ቁሱና ውክልናውን ይዞ የሚገኝ ለትርጓሜ መነሻ የሆነውን ቁስ የሚመለከት ነው ። ፍካሬ የውክልናውን ሁነት፣ ድርጊት፣ እንቅስቃሴ መርምሮ በአዕምሯችን የሚፈጥርብን ምስል ተጨማሪ የሆኑ ፍቺ መስጠትን የሚገልጽ ነው (Chandler, 2002) ።




የስነ-ፍቺ ንድፈ ሃሳብ፤ የሥነልሳናዊ ቋንቋ ትዕምርትን፣ ቁስን፣ ሁነትን፣ ድርጊትን፣ ባህሪን፣ ጠባይን፣ ሥነልሳናዊ ያልሆኑ መግባቢያዎችን፣ አካላዊ እንቅስቃሴዎችን፣ ወዘተ. እንደ ትዕምርት አካቶ የሚያጠና ሳይንስ ነው። ባህላዊ ቁሶችንም ከቁስነታቸው ባለፈ አካባቢያዊና ባህላዊ ስምምነት ያላቸውን ፍቺ ይመረምራል፤ይተረጉማል (Posner, 2004, p. 56-58)፡፡

የስነፍቺ ንድፈ ሀሳብ መሠረት፤ በቁስ አካል፣ በአዕምሮ እና በባህል መሀል በሚካሄድ የእርስ በእርስ መስተጋብር ውስጥ ነው። ቁስ አካል የተለያዩ ትዕምርቶች የሚመነጩበት ተጨባጩ አካል ነው። አዕምሮ ደግሞ የሰው ልጅ ውጪያዊ ዓለምን ከውስጣዊ እሳቤ ጋር በማገናኘት አካባቢውንና ዓለምን ይገነዘባል። የፎክሎር ባለሙያዎችም በማህበረሰቡ የተወከሉ ባህላዊ ተግባራትንና ቁሶችን በማጤን የትዕምርቶችን ምንነት፣ትርጓሜ እና ፍካሬ ይመረምራሉ። የሚጠናው ትዕምርት ምን ምን ፍቺዎችን ይዞ ይገኛል? ፍቺዎቹ ለምን ተግባር ተመረጡ? የሚሉትን ጥያቄዎች ይመለከታል (Danesi, 2004, P.18)፡፡

በዚህ ጥናት የሥነ-ትዕምርት ንድፈ ሃሳብን በተመለከተ የተለያዩ ምሁራን ሀሳቦች ቀርበዋል ። ይሁንና ለዚህ ጥናት የበለጠ የረዱኝና ለሥራው የተጠቀምኩት (Danesi,2004, P.18)፤ (Clifford,1973, P. 45)፤ Charles S. Peirce እና Chandler, 2002 ሥራዎች ናቸው ::

በመሆኑም ይህ ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ የሆነው በብሔረሰቡ በሚሰሩ ቤቶች ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚታዩ ምልክቶች፣ ፎቶዎች፣ስዕሎች፣ የባህላዊ ቤቱ የአሰራር ቅርጽ፤ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታው፤ የቤቱ መጠን፤ የመስሪያ ግብአቶች በማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ትርጓሜዎች የሚገለጹ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ከቤቱ ጋር ተያይዘው የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ባህላዊ ዘፈኖች እንዲሁም ደግሞ ከቤቱ ስራ ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች ትርጓሜ ተሰጥቷቸው ተተንትነዋል ።

### 2.2.3. የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ

የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሃሳብ እንደ ህግ ትምህርት፣ ፖለቲካ፣ ሶሺዮሎጂ እና ሳይኮሎጂ ካሉ ብዙ ዘርፎች ሊወሰዱ ይችላሉ ። ለየብቻ እያንዳንዱ የትምህርት ዘርፍ የሰውን ጸባይ በተማረበት መስክ ለማብራራት ይሞክራል ። ነገር ግን አንድ ሰው እንደ ማህበራዊ ሰራተኛ አንድን የተለየ ባህሪ ማብራራት መቻሉን ለማረጋገጥ ዋናው ዲሲፐሊን ምንም ይሁን ምን ተገቢውን ፅንሰ-ሀሳብ ወይም ጥምር ማግኘቱ አስፈላጊ ነው ።

የማኅበራዊ ትምህርት ጽንሰ-ሐሳብ ከሥነ-ልቦና የመጣ ቢሆንም የእሱ ጽንሰ-ሐሳቦች ለማህበራዊ ስራ ጥናት በጣም ጠቃሚ ናቸው ። ይህ የማህበራዊ ትምህርት ፅንሰ-ሀሳብ መግቢያ መሰረቱን አስፈላጊነታቸውን ፣ ጥንካሬዎችን እና ድክመቶቹን በማህበራዊ ስራ ውስጥ ያለውን አተገባበር ያመላክታል ።

የማህበራዊ ትምህርት ጽንሰ-ሀሳብ እንደሚያሳየው ማህበራዊ ባህሪ መማር የሚቻለው የሌሎችን ባህሪ በመመልከት እና በመኮረጅ ነው ። ሳይኮሎጂስቱ Albert Bandura የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሃሳብን በባህሪነት ላይ ባለው ተጽእኖ ከሚታወቀው የቀድሞ የስነ-ልቦና ባለሙያ B. F. Skinner ስራ ይልቅ እንደ አማራጭ አዘጋጀ ።

የመማሪያ ንድፈ ሐሳቦች አካባቢን በልማት ውስጥ እንደ ዋና ኃይል ይመለከቱታል Hoffman (1993) ምሁራኑ የመማር ንድፈ ሐሳቦችን እንደ ባህሪ፣ ማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ እና ማህበራዊ የእውቀት ትምህርት በማለት ፈርጀዋቸዋል ። በጥናት አውድ ውስጥ Albert Bandura በጣም ታዋቂ የስነ-ልቦና ባለሙያ ነው በጥናት አውድ ውስጥ Albert Bandura በጣም ታዋቂ የስነ-ልቦና ባለሙያ

ነው ። የእሱ የማህበራዊ ግንዛቤ ጽንሰ-ሀሳብ በብዙ ዘርፎች እንደ ትምህርት ፣ ጤና፣ ሳይንስ ማህበራዊ ፖሊሲ እና የስነ-ልቦና ሕክምና ላይ ኩረጃዎች የታየባቸው ሆነው እነዚህ ላይ ተጽዕኖ አሳድሯል (Bandura,1977) ፡፡

የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ ምናልባት በጣም ተደማጭነት ያለው የመማር እና የእድገት ንድፈ ሃሳብ ሊሆን ይችላል ። ንድፈ ሀሳቡ በብዙዎቹ የባህላዊ ትምህርት መሰረታዊ ፅንሰ-ሀሳቦች ላይ የተመሠረተ ሲሆን ትኩረትን፣ ትውስታን እና መነሳሳትን ስለሚያካትት በባህሪያዊ የመማር ንድፈ ሃሳቦች እና የግንዛቤ ትምህርት ንድፈ ሃሳቦች መካከል ድልድይ ተብሎ ይጠራል (Muro & Jeffrey, 2008) ፡፡

የማህበራዊ ትምህርት መርሆዎች በህይወት ውስጥ በተመሳሳይ መንገድ እንደሚሰሩ ይታሰባል። በምልከታ የመማር ትምህርት በማንኛውም ዕድሜ ላይ ሊከናወን ይችላል ። እንደ ማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ እውነታ ከሆነ ሰዎች እርስ በርሳቸው በምልከታ እና በማስመሰል ሊማሩ ይችላሉ ። በእነዚህ አጠቃላይ መርሆች መሰረት የባህሪ ለውጥ ሳይደረግ መማር ሊከሰት ይችላል ። በሌላ አገላለጽ የባህርይ ባለሙያዎች እንደሚሉት መማር በባህሪው ዘላቂ ለውጥ መወከል አለበት ። በተቃራኒው የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳባዊያን እንደሚናገሩት ሰዎች በመመልከት ብቻ መማር ስለሚችሉ ትምህርታቸው በብቃታቸው ላይ ላይታይ ይችላል (Bandura, 1965) ፡፡

የማህበራዊ ትምህርት ጽንሰ-ሀሳብ በበርካታ ቁልፍ መላምቶች የተመሰረተ ሲሆን ይህም ሰዎች የሚማሩት በመመልከት ነው ። ተማሪዎች ሞዴልን በመመልከት አዲስ ባህሪ እና እውቀት ማግኘት ይችላሉ (Ashford, & LeCroy, 2012) ፡፡

በማህበራዊ ግንባታ ንድፈሃሳብ እንደተገለጸው ሥርዓተ-ፆታዊ ግንዛቤ ከስነህይወታዊ ይልቅ ማህበራዊ ፍችና ስምምነቶች ላይ ስለሚያተኩር ማህበራዊ ህገ ደንብ አለው ። ከዚህ የተነሳ ሰዎች ወንድነትንና ሴትነትን ሲማሩና ሲቀበሉ በዛ ህግ እየታረሙ እንደሆነ ተገልጿል ። እንደዚሁ ሁሉ የማህበራዊ አስተምህሮ ንድፈ ሃሳብ /Social Learning theory/ም የፆታዊ ልዩነት ምንጩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ፆታ ለይ ተግባራትና ህገደንቦች ናቸው ብሎ ያምናል ። ይኸውም ማበረታቻዎችና ቅጣቶች ልጆችን ወደ ሚመስላቸው ፆታዊ ምድብ እንዲሄዱ ይገፋፋቸዋል ። ከዚህም ባለፈ እያዩትና እየተገበሩት የሚማሩበት ወኪል/ሞዴልም ይቀርብላቸዋል። በመሆኑም ሥርዓተ-ፆታዊ ግንዛቤን በማህበረሰቡ ውስጥ በሚያደርጉት ምልከታ ይማሩታል ከዚህ ማህበራዊ አስተምህሮም ማህበራዊ የሆነው ፆታዊ ግንዛቤ ይገነባል (Bandura, 2006) ፡፡

Bandura (ibid) አክለው በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ ውስጥ ሶስት ፅንሰ-ሀሳቦች አሉ ። በመጀመሪያ ሰዎች በመመልከት መማር ይችላሉ ። ይህም የእይታ ትምህርት በመባል ይታወቃል። በሁለተኛ ደረጃ የአዕምሮ ሁኔታዎች ለመማር አስፈላጊ ነገሮች ሲሆኑ እሱም እንደ ውስጣዊ ማጠናከሪያ ተብሎም ይጠራል ብለዋል ። ይህ ንድፈ ሀሳብ ከቤት ስራው ለመዳ ጋር የተያያዙ እሳቤዎችን ለመተንተን ጥቅም ላይ ውሏል ።

### 2.2.4. የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ

የማህበራዊ ዘርፍ ተመራማሪ የሆኑት Berger and luck man እንደ አውሮፓዊያን አቆጣጠር በ1966 "የማህበራዊ ግንባታ" በተባለ መጽሀፋቸው ውስጥ ማህበረሰቡን የፈጠረው የሰው ልጆች የሚያደርጉት መስተጋብር ነው በማለት ይከራከራሉ። ሌላው የእነሱ ማዕከላዊ ጽንሰ ሐሳብ ሰዎችና ቡድኖች በማኅበራዊ ሥርዓት ውስጥ እርስ በርሳቸው ያላቸው ግንኙነት ምንድነው? ማህበረሰቡ በአካባቢው የሚከናወኑ ድርጊቶችን እንዴት ይገልጻል? ይለምዳል ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ በመስጠት በጊዜ ሂደት የአእምሮ ውክልናን እንዲፈጥሩ በማድረግ ትርጉሙ በማኅበረሰቡ ውስጥ ተቀርጾ እንዲታይ ያደርጋል

እውቀት በግለሰብ ደረጃ የሚመሰረት ሆኖ ከግለሰብ ግለሰብ፣ ከማኅበረሰብ ማኅበረሰብ፣ተግባርና እና አደረጃጀት አንጻር የሚለያይ በመሆኑ ዕውቀት ተፈጥሯዊ ሳይሆን ማኅበራዊ ውቅር ነው። እውቀት በማህበረሰብ መስተጋብር የሚፈጠር ሆኖ በግለሰቦች አመለካከት ላይ የተመሰረተ ነው (Berger, and luck man, 2001) ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው እውቀት የሰው ልጅ ማህበራዊና ባህላዊ ግንባታ ውጤት ነው ግለሰቦች ትርጉም የሚፈጥሩት እርስ በርስ ከሚኖሩበት አካባቢ ጋር በመወዳደር ነው ። ሌላው የእውቀት መሰረቱ የማህበረሰቡ ፍላጎት ሲሆን የንድፈ ሀሳብ መሰረት ባህሉ ከአውዱ ከማህበረሰቡና ከሚገነባው እውቀት ላይ ነው ።

በዚህ ጥናት ማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ግለሰቦች (ማህበረሰቦች) የቤት አሰራር እውቀቱን እንዴት አዳበሩት? የአሰራር እውቀቱ ቡድናዊ(ማህበራዊ) ስልትን ይከተላል?በቤት ስራው ውስጥ ማህበረሰቡ እርስ በርስ ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል ።

### 2.2.5. የንድፈ ሀሳቦች ትስስር

በዚህ ጥናት የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ-ሀሳብ ከእውቀት ለመዳ ጋር ተያያዥ የሆኑ ነገሮች የሚቀርቡበት ሲሆን ይህም የብሔረሰቡ አባላት እውቀቱን እንዴት ለመዱት? ለሚል ጥያቄ መልስ

ይሰጣል ። የእውቀት ሽግግሩም አባቶች ቤት ወደሚሰራበት ቦታ ሲሄዱ ልጆቻቸውን ይዘው ይሄዳሉ ። ልጆቹም ቀለል ያሉ እንደወፍቾ ያሉ ነገሮችን በማቀበልና በመመልከት ይለምዳሉ ። በዚህ ሂደት መሰረት እውቀቱ ከአባቶች ወደ ልጆች ይተላለፋሉ ።

የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ (Structural-Functional) በአካባቢው ቤቶቹ ሲሰሩ የብሔረሰቡ እርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነት ምን እንደሚመስል እያንዳንዱ ግለሰብ ወይም ቡድን በቤቱ ስራ ወቅት የሚኖራቸው የስራ ድርሻ ምን እንደሚመስል እንዲሁም በብሔረሰቡ በቤቱ ስራ ወቅት የሴትና የወንድ ሚናን ለመተንተን ተግባር ላይ ውሏል ። በተቋም ውስጥ በሚኖሩ ግንኙነቶችና የስራ ድርሻዎች በአንድነት በብሔረሰቡ ለሚመሰረትበት ዓላማ ስለሚጠቅም አንዱ ለሌላው ቀጣይ ህልውና አስፈላጊ ናቸው ። በዚህም በማህበራዊ ህይወትና በቤቶቹ ውስጥ የታዩ የለውጥ ሂደቶችም በዚህ ንድፈ ሀሳብ መታገገያነት ተቃኝተዋል ።

የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ (Semiotics) በብሔረሰቡ በሚሰሩ ቤቶች ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚታዩ ምልክቶች በብሔረሰቡ የሚሰጣቸው ትርጓሜዎች የሚገለጹ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የእንጨቱ አይነት፣የእንጨቱ መጠን፣ የእንጨቱ የቆይታ ጊዜ፣የእንጨቱ የአቆራረጥ ልማድና ሰዓት የሚሰጣቸው ትዕምርትና ልማዶች የተተነተኑበት ሲሆን ሌሎች ከቤቱ አሰራር ጋር የተያያዙ ነገሮች ሁሉ ትርጓሜ ተሰጥቷቸው ተተንትነዋል ።

የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ (Social Constructivism) በዚህ ጥናት የማኅበራዊ ግንባታ ንድፈ ሃሳብ እንዴት ተተገበረ? ሲባል የባህላዊ ቤት ባለሙያዎች የቤት አሰራር እውቀቱን እንዴት አዳበሩት? የቤቱ አሰራር ሂደት ምን ይመስላል?ወዘተ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ የተሰጠበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ የባህላዊ ቤት አሰራሩ ዕውቀት እና ቤቶቹ ላይ የታዩ ለውጦችም በዚሁ ንድፈ ሀሳብ ትንታኔ ተደርገውባቸዋል።

## 2.3. የተዛማጅ ስራዎች ቅኝት (ክለሳ)

በዚህ ርዕስ ስር ተዛማጅ የሆኑ ቀደምት ጥናቶች ሂሳዊ በሆነ መንገድ ተቃኝተው የቀረቡ ሲሆን ለጥናቱ የተመረጠው ርዕሰ ጉዳይ ምን ላይ አተኮረ? ምን ውጤትስ ተገኘ? ምን አይነት ክፍተት አለ? በሚሉ ጥያቄዎች ማተኮሪያነት ተቃኝተዋል። እንዲሁም ከሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ጋር ያላቸዉ ዝምድና እና ልዩነት በንፅፅር ተብራርቶ ቀርቧል።

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ከባህላዊ የቤት አሰራር ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ጥናቶች ከጭብጥና ከይዘት አንጻር ዳሰሳ የተደረገባቸው ሲሆን በዚህም የጥናቶቹ ዐቢይ ዓላማዎች፣የትኩረት አቅጣጫዎች፣መጠነ

ርዕይ፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችና ግኝቶች ላይ ትኩረት ተደርጎ የክለሳ ሂደቱ ተከናውኗል ፡፡ ጥናቶቹ ባላቸው ጭብጥ፣ርዕሰ ጉዳይና ይዘት መሰረት ባህላዊ የቤት አሰራር፣ አይነቶች እና የመስሪያ ግብአታቸው ላይ ያተኮሩ ጥናቶች ፤ባህላዊ የቤት አሰራርን ከስነ ቃል ጋር በማጣመር ለመጀመሪያ ዲግሪ የቀረበ ጥናት፤ባህላዊ ቤትን ከእጅ ስራ ቁሶች ጋር በማድረግ ለሁለተኛ ዲግሪ የተሰሩ ጥናቶች፤ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብን መሰረት አድርገው የተሰሩ ጥናቶች፤ ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብን መሰረት አድርገው በአፍሪካ እና በተለያዩ የውጭ ሀገራት የተሰሩ ጥናቶች በሚሉ አምስት ክፍሎች ተለይተው ቀርበዋል ፡፡

በባህላዊ የቤት አሰራር ዕውቀት ላይ የተሰሩ ጥናቶች ሃያ ሁለት (22) ናቸው ፡፡ ከነዚህም መካከል ሁለቱ ከኢትዮጵያ ውጭ በአፍሪካ በናይጀሪያ የቤት አሰራር ላይ እና በሰሜን ምስራቅ ህንድ ላይ ያተኮሩ ናቸው ፡፡

በኢትዮጵያ ከተሰሩት ጥናቶች ደግሞ አምስቱ በደቡብ ክልል፤Olmstead, Judith የዶርዜ ቤቶች ጋረደው መንገሻ በኮንሶ ባህላዊ ቤቶች፤አለማየሁ ደርጌ በሲዳማ ባህላዊ ቤቶች ላይ፤ ግርማ ኪዳኔ በወላይታ ቤቶች፣ፍቃዱ ገዳሙ በጉራጌ ቤቶች ያካሄዷቸውን ጥናቶች አቅርበዋል፡፡ በአማራ ክልል ሆኖ ሁለቱ በምዕራብ ጎጃም አስቴር ሙሉ ፣ በዘጌ ቤቶች ላይ፤አስማማው እስተዚያ የደጋ ዳሞት ቤቶችን ያጠኑ ሲሆን ማማዬ አያሌው በአፋር ክልል ፤ Elisabeth Dorothea የሀረር ቤቶች ላይ፤ ሰርተዋል፡፡ ሌላው በአፍሪካ የናይጀሪያ ሀውሳ ቤቶች፣ በአሳም በሰሜን ምስራቅ ህንድ አንድ፣ ለቴክኖሎጂ ተቋም አንድ፣ ለቅርስና አካባቢ ተቋም አንድ፣ ለሥነ ምህንድስና ተቋም አንድ፣ ለሥነ ህንጻ ጆርናል ደግሞ አንድ በጠቅላላው ሃያ ጥናቶች ቀርበዋል ፡፡

### 2.3.1. የባህላዊ ቤት አሰራር፣ አይነቶች እና የመስሪያ ግብአቶች ላይ ያተኮሩ ጥናቶች

በዚህ ርዕስ ዙሪያ የቀረቡ ጥናቶች አምስት ሲሆኑ እነዚህም በሚከተለው መንገድ ቀርበዋል ፡፡

Olmstead, Judith. (1972) “The Dorze house: a bambo Basket” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርቧል ፡፡ ይህ ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ በጋሞ ከፍተኛ ቦታዎች በሚገኙት የዶርዜ ቤቶች ላይ ያተኮረ ሲሆን አጥኚው በአካባቢው ለሁለት ዓመት ያህል ለአንትሮፖሎጂ የመስክ ስራ መቆየቱን ገልጾ በአካባቢው ቤቶቹ የሚሰሩትና የሚከፋፈሉት ከቀርከሃ እንደሆኑና ቤቶቹም ለሰዎች መኖሪያ፣ ለእንስሳት መኖሪያ፣ ለጠላ ማስቀመጫ፣ተብለው ተከፋፍለው እንደሚሰሩ ተገልጿል ፡፡ ሌላው ቤቶቹ ተሰርተው ካለቁ በኋላ በእንጨት ተገፍተው የሚቆሙ ሲሆን ይህም በማህበረሰቡ እርኩስ መንፈስን ይከላከላል ተብሎ የሚታመን እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

በማህበረሰቡ ቤቶቹ ሲሰሩ መጠናቸው ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ሲሆኑ ይህም ከኢኮኖሚያቸው ጋር የተያያዘ እንደሆነ ተገልጿል ፡፡ ትንሽ ቤት የፈለገ ሰው የሚከፍለውም ገንዘብ እንደ ቤቱ መጠን ዝቅ ያለ ሲሆን ትልቅ ቤት የፈለገ ሰውም እንደ ቤቱ መጠን ከፍ ያለ ገንዘብ እንደሚከፍል በጥናቱ ተጠቅሷል ፡፡

ዓላማው በአግባቡ ተደራጅቶ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ንድፈ ሀሳቦች፣ጽንሰ ሀሳቦችና ሥነ ዘዴዎች በአግባቡ ያለመቅረባቸው በጥናቱ እንደ ክፍተት ታይቷል ፡፡ የJudith olmsteade ጥናት በደቡብ ኢትዮጵያ በዶርዜ ባህላዊ ቤቶች ላይ የተጠና ጥናት በመሆኑ ከቦታ አንጻር ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት አለው ፡፡ ይሁን እንጂ የዘዬ፣የቋንቋና የባህል ልዩነት አላቸው ፤ ሌላው በትኩረት አቅጣጫ ተቀራራቢነት አላቸው ፡፡ ይህ ጥናት የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት በሚል ርዕስ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ ከJudith olmsteade ጥናት ይለያል ፡፡ ከይዘት አንጻር ደግሞ የJudith olmsteade ጥናት ለjournal of Ethiopian Studies ታስቦ በጥቂት ገጽ የተዘጋጀ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ሦስተኛ ዲግሪ ለማግኘት ታስቦ የተከናወነ መሆኑ በስፋት የተለየ ያደርገዋል ፡፡

Hecht, E. D. (1982). *The city of Harar and the traditional Harar house*. **በሚል ርዕስ ጥናት አቅርባለች** የሀረር ቤቶቹ የተሰሩት ከሸክላ አፈርና ከድንጋይ እንደሆነ ይህንንም ግብዓት የሚያገኙት ሀኪም ከተባለ ተራራ መሆኑንም ጭምር የገለጸች ሲሆን የቤቶቹን አቀማመጥ በተመለከተ ሳሎኑ ሰፊ ሆኖ የማህበረሰቡን ባህል መሰረት አድርጎ ምንጣፎች የተነጠፉበት ሲሆን በቤቶቹ ውስጥ ስለሚደረጉ አንዳንድ ባህላዊ ድርጊቶች ለአብነት እንደጫት መቃምና ስለመሳሰሉት ጉዳዮች በቤቱ በየትኛው ክፍል እንደሚደረጉና ስለቤቶቹ የቀለም አቀባብ ቅርጽ ተምሳሌታዊ ትርጉም ተገልጿል፡፡ ግድግዳዎቹ ላይም ለዳቦ ወይም ለኬክ ማቅረቢያ የሚሆኑ የተለያዩ ስፌቶች እንደሚሰቀሉ የተጠቀሰ ሲሆን እነዚህም የሚሰሩት በሴቶች እንደሆኑ ተጠቅሷል፡፡ ከዚህ ጋር አያይዛ በዓልን መሰረት አድርገው ቤቶቹ ነጭ ቀለም እንደሚቀቡ የገለጸች ሲሆን በተጨማሪም በአንድ አካባቢ በአንድ አጥር ውስጥ በርካታ ቤቶች እንዳሉና በአንድ ማዕድ ቤት እንደሚጠቀሙም ገልጻለች ፡፡ በመጨረሻም ሀረሪዎች ከቤታቸው ጋር እጅግ የጠበቀ ቁርኝት እንዳላቸውና እጅግ ከባድ ችግር እስካልገጠማቸው ድረስ ቤታቸውን እንደማይለቁና እንደማይሸጡ በጥናቱ ተገልጿል ፡፡ የElisabeth Dorothea ጥናት ትንታኔ ተደራጅቶ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን በንድፈ ሀሳቦችና ሥነ ዘዴዎች ተጠናክሮ ባለመቅረቡ ክፍተት ያለበት ሲሆን በባህላዊ ቤቶች ላይ የተሰራ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት አለው፡፡ ይሁን እንጂ ከዚህ ጥናት ጋር በትኩረት አቅጣጫና በመጠነ ርዕይ ሰፊ ልዩነት አለው፡፡

Garedew, M. (2015). *Transformation of Konso vernacular houses*. **በሚል ርዕስ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ለኢትዮጵያ የስነምህንድስና ህንጻ ግንባታ እና ከተማ ልማት ኢንስቲትዩት ጥናት አቅርቧል የጥናቱ ዐቢይ ዓላማ ባህላዊ የኮንሶ ቤቶች ባህሪያትን እና ለውጦችን መተንተን ሲሆን በጥናቱም የኮንሶ ቤቶችን የለውጥ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው? በኮንሶ አገር አቀፍ ቤቶች ላይ እየታዩ ያሉት የለውጥ ዓይነቶች ምንድናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናታቸው ምላሽ ሰጥተዋል ፡፡ ይህንንም ከግብ ለማድረስ መረጃዎች በቃለ መጠይቅ፣በግል ምልከታና በቡድን ውይይት ተግባር ላይ ውለዋል ፡፡**

**በውጤቱም መሰረት በኮንሶ አምስት ባህላዊ ቤቶች እንዳሉ የተገለጸ ሲሆን በመጨረሻም የኮንሶ ባህላዊ ቤቶች በከፊል መለወጣቸውን በጥናቱ እንደተረጋገጠ ተገልጿል ፡፡ የጋረደው መንገሻ ጥናት በዓላማውና በጥናቱ የሚመለሱ ጥያቄዎችን ባግባቡ ማቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎኖች ሲሆኑ የጥናቱ ንድፈ ሀሳብ፣ጽንሰ ሀሳብ በአግባቡ አለመጠቀሱ የጥናቱ ደካማ ጎን ነው ፡፡ የጋረደው መንገሻ ጥናት በደቡብ ባህላዊ ቤቶች ላይ የተሰራ በመሆኑ የተወሰነ መቀራረብ የሚኖረው ሲሆን በሌላ ጎኑ ደግሞ ከጥናቱ ንድፈ ሀሳብ ፣ከጥናቱ ቦታና የትኩረት አቅጣጫ ጋር በተያያዘ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አለው ፡፡**

Enrico Castelli's (2003) study, "Konso Architecture," published in the *Proceedings of the Sixth International Conference on the History of Ethiopian Art*, offers an in-depth analysis of the architectural practices of the Konso people in southern Ethiopia. **በ6ኛው የኢትዮጵያ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ ከገጽ 440 እስከ 456 ድረስ "የኮንሶ ኪነ-ሕንፃ ጥበብ" በሚል ርዕስ የቀረበው የ**Enrico Castelli's (2003) **ጥናታዊ ጽሑፍ ትኩረት ያደረገው በደቡባዊ ኢትዮጵያ ስለሚገኘው እውቁ የኮንሶ ሰዎች የቤት አሰራር ጥበብ ላይ ጥልቅ ትንታኔ መስጠት ነው ፡፡ ሌላው ይህ ጥናት ውስብስብ የሆነው የኮንሶ ህንጻ ግንባታ ሥራ የሚከናወንባቸው አከባቢዎች ከኮንሶ ማህበራዊ፣ ባህላዊ እና አካባቢያዊ መስተጋብሮች ጋር ትስስር እንዳላቸው የሚያሳይ ነው** Enrico Castelli's በ2003 **በኮንሶ ቤቶች ላይ ባደረገው ጥናት ውስጥ ያነሳቸው መሰረተ ሀሳቦች ቀጥሎ የቀረቡት ናቸው ፡፡**

**1.አንድን አከባቢ ተላምዶ ስለመኖር ፦ በዚህ ስር በባህሉ የእርከን ሥራ የሚጠቀስ ሲሆን ይህም ኮንሶዎች የአፈር መሸርሸርንና የለም አፈር መራቆትን ለመከላከል ብሎም የከርሰ-ምድር ውሃ ሀብት ለመያዝ በሚያደርጉት ምርምር-ተኮር የአኗኗር ስልት ደረቅ የሆነ የጎርፍ መከላከያ እርከን** (terracing) **ሥራ ጥበብ ባለቤት ሆነዋል ፡፡ እነዚህ የእርከን ስራዎችም የኮንሶ አርሶ-አደሮች ከእርሻ ስራ ጋር**

ምን ያህል እንደተቆራኙና ቀጣይነት ያለውን የአፈር ለምነት መከላከያ መንገዶች ምን ያህል በጥልቀት እንደተለማመዱ የሚያሳይ ነው ።

2. ተራራ ላይ ሠፈራዎች (Paletas) ፦ ተራራ ጫፎች ላይ ስልታዊ የሆነ አሰፋፈር ለማካሄድ ደረቅ ከሆኑ ድንጋያማ ግድግዳዎች ቤት መስራትና መትከል ብሎም ለራስ ቤተሰብ መከላከልና ለማህበራዊ ጉዳዮች ግልጋሎት ማዋል ላይ ያተኮረ ነው ።

3. ባህላዊ ክንዋኔዎችን ማከናወኛ ቦታዎች (moras) ፦ በእነዚህ ሠፈራዎች የባህላዊ ክንዋኔ ማከናወኛ ጣቢያዎች ለማህበረሰቡ እንደ መሰብሰቢያ ስፍራ ስለሚያገለግሉ ለኮንሶዎች ለባህላዊና ማህበራዊ ክንውኖች መሰረታዊ ሚና ይጫወታሉ ማለት ነው ።

4.የትውልድ ቀጣይነትን የሚያመለክቱ ድንጋዮች (Daga-Hela) ፦ እነዚህ ድንጋዮች አንድን ወሰነ-መንግሥት ወደ ቀጣይ ትውልድ ሥርወ-ምንግሥት ለማሸጋገር እንደ ምልክት ቆመው ሲያገለግሉ የኮንሶን ባህላዊ ሥነ-ሥርዓት ወደ ቀጣይ ትውልድ ለማሸጋገር ከፍተኛ ሚና አላቸው ።

5. የመቃብር ሥፍራ ጠቋሚ የእንጨት ምልክቶች (Waka) ፦ ከአንድ የኮንሶ ማኅበረሰብ አንድ የተከበረ ትልቅ ሰው ሲሞት እነዚህ ዋካ የሚባሉት ቆልመም ያሉ የእንጨት ምልክቶች መቃብሮቹ ላይ ስለሚቀመጡ የኮንሶን ቱባ ባህላዊ የቀብር ሥነ-ሥርዓቶችን ያመላክታሉ።

በአጠቃላይ የCastelli's ጥናት ስለኮንሶ ኪነ-ህንጻ ጥበብ ጥንካሬ የሚገልጽ ነው ። ሌላው ህዝቡ ከራሱ መልክዓ ምድርና ባህል ጋር እንዴት ተቆራኝቶ እንደሚኖር እንዲሁም ደግሞ የኮንሶ ማህበረሰብ በህንፃ ጥበባቸው እንዴት አድርገው ሌሎችንም እምቅ ሀብቶችን ይዘው እንደሚኖሩ ተብራርቷል።

ዓላማው፣ስነዘዴውና ትንታኔው በአግባቡ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው ። ኮንሶ በደቡብ ኢት/ያ ስር የሚገኝ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት ያለው ሲሆን በመጠነ ርዕይና በጥናት አቅጣጫ ይለያያሉ ።

D.R. Buxton (1964) Ethiopian medieval architecture.The present state of studies journal of semetic studies vol, 9, issue 1 pp.239-244.

የBuxton ጥናት በይበልጥ ትኩረት ያደረገው በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የኢትዮጵያ ልዩ የህንፃ ጥበብ ላይ ሆኖ በተለይም አጽንኦት የሰጠው በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ነው ።

ሌላው የኢትዮጵያ የስነ-ህንጻ ሥራ ላይ በጊዜው የነበረውን የምርምር ውጤትና አረዳደድ ላይ ነው ። በዚህም ስለ ስነ-ህንፃ ምን ያህል እንደተጠና? ሳይጠኑ የቀሩ ርዕሰ-ጉዳዮችን እና ለወደ ፊት ምን ምን መጠናት እንዳለባቸው ነው ፡፡ በተጨማሪ የBuxton ጥናት በኢትዮጵያ ጥንተ-ታሪክና ስነ-ህንፃ ጥበብ ላይ ሆኖ ትኩረቱም በመካከለኛው ክፍለ ዘመን አቢያተክርስቲያናት ላይና በስነ-ጽሑፍ ውጤቶች ላይ ሲሆን እነዚህ ሥራዎችም ፈር የያዙት በሰለጠኑ ባለሙያዎች ሳይሆን በጀማሪ አሳሾች ጥረት እንደተጀመረ ነው ።

ከአውሮፓ ርቀውና ወጣ ብለው እንደሚገኙ ክልሎች ኢትዮጵያ ውስጥ ሁሉንም ቦታ በጥናት ማድረስ ከባድ በመሆኑ ብዙም ዘመናዊ ትምህርት ባልተማሩ ግን ለትምህርት ጉዳይ ብቻ በሚንቀሳቀሱ አጥኚ ሰዎች ነበር የተገለጹት ። እነዚህ ጀማሪ ግን ለማወቅ ብቻ ተነሳሽነት ያላቸው ጥናታዊ ጽሑፍ አቅራቢዎች የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ለአውሮፓዊያን ጥናቶች በር ከፋች እንድትሆን አግዘዋል ።

በሥልጣኔ ማማ ላይ የወጡ ዘመናዊ አጥኚዎችም ከጥንት ዘመን ስነ-ጽሑፍ ስራዎች ጋር እንደሚቆዩ የቋንቋ አጥኚዎችና ጥንተ መልክአምድር አጥኚዎች መዝገበ-ታሪክ ባለመቀመጡ ከኋላ ቀር ጽሑፎችና ድርሳናት ጋር ሲታገሉ ቆይተዋል ። በድሮ ጊዜ የነበሩ ስነ-ጽሑፎች የተጻፉት ለባህልና ትምህርት ትኩረት ባልሰጡ ወታደራዊ ዘመቻዎች ሳቢያ ነበር ። ከዚህም የተነሳ በጣም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ሳይጠኑ ተከድነው እንደቀሩ የሚገልጽ ነው ።

የቋንቋ አጥኚዎችና ጥንተ-መልክአ ምድር አጥኚዎች በድሮ ጊዜ የነበሩ ስነ-ጽሑፎች የተጻፉት ለባህልና ትምህርት ትኩረት ባልሰጡ ወታደራዊ ዘመቻዎች ሳቢያ ነበር፡፡ ስለሆነም በጣም ጠቃሚ የሆኑ ነገሮች ሳይጠኑ ተሸፍነው ቀርተዋል የሚል ነው ።

በሌላ መንገድ በመካከለኛው ዘመን በኢትዮጵያ ከድንጋይ ተቀርጸው ተራራዎች አከባቢ የተሠሩ ቤተ-እምነቶች መሰረታቸው የተጣለው በሰለጠኑ ባለሙያዎች እንደሆነ ሲገለጽ ቆይቷል ። ይሁን እንጂ ስለእነዚህ አካባቢዎች ዛሬ ላይ ያገኙናቸው የምርምር ውጤቶች ባልሰለጠኑ ጀማሪ አጥኚዎች በእነ Monti della Corte, Frau Irmgard Bidder እና በፀሐፊው በራሱ የተጀመሩ ሥራዎች ሆነው ተገኝተዋል፡፡ Buxton የድሮ ሰዎች የዕውቀትና የሥልጠና እጥረት እንዳላቸው የገለጸ ቢሆንም እነዚህ ቤት ሰሪዎች Buxton በዚህ ዘመን ሰለጠኑ የተባሉ ሰዎች እንኳን ያላበረከቱትን አስተዋጽኦ ማበርከታቸውን ገልጿል ።

በሌላ ጎን ደግሞ የዚህ ጥናት አቅራቢ የተፈጠሩ ስህተቶችን ሳይጠቅስ አላለፈም። እነዚህ ስህተቶችም ባልተገመተ ሁኔታ ኢትዮጵያ ውስጥ በመቅረታቸው እና ከአውሮፓዊያን መሰረተ-ትምህርት እይታ ወጭ ለሆኑ የጥንት ኢጣሊያ ምርምር ውጤቶች ቦታ አለመስጠት እንደሆነ ነው ። እነዚህ አይነት ስህተቶች እስከ ዛሬም ድረስ በደንብ ባልተማሩ ሰዎች አከባቢ የሚታዩ ሆነው ግን ሰለጠኑ የተባሉት ተመሳሳይ ስህተቶችን ሰርተዋል ማለት ነው ። በመጨረሻም Buxton እንደገና መፈተሽ የሚፈልገው ከ17 ዓመት በፊት በኢትዮጵያ ስነ ህንጻ የደረሰባቸውን ግምታዊ ድምዳሜዎች መሰረት አድርጎ ዛሬ ያሉበትን ደረጃ ለማወቅ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ።

ይህ ጥናት በመካከለኛው ክፍለ ዘመን በነበረው የኢትዮጵያ ልዩ የህንፃ ጥበብ ላይ አጽንኦት ሰጥቶ ትኩረቱ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ያተኮረ ነው ። ሌላው የስነ-ህንጻ ላይ የተጠኑት ጥናቶች ትኩረት፤አሁን የደረሱበት ደረጃ፤የጥናቱ ውጤት መሰረት ተብራርቶ ቀርቧል ። ዓላማው፣ስነዘዴውና ትንታኔው በአግባቡ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው ። በቤት ላይ ስለተሰራ ብቻ የሚቀራረብ ቢሆንም ከዚህ ጥናት ጋር ያለው ልዩነት ሰፊ ነው ። ይህም በመካከለኛው ክፍለ ዘመን የኢትዮጵያ ልዩ የህንፃ ጥበብ በተለይ በኢትዮጵያ የኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ላይ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ለሰው ልጆች ለመኖሪያነት በሚያገለግለው ቤት ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ ስለተሰራ ልዩነት አሳይቷል ።

Girma Kidane (1994) “The traditional ways of building houses with in wolayta society” **በሚል ርዕስ** ጥናት አቅርበዋል ። በዚህ ጥናት የወላይታ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር መንገዶች የቀረቡ ሲሆን አጥኚው እንደገለጹት ለጥናታቸው መነሻ የሆናቸው ምክንያት ወደ ወላይታ ባደረጉት ጉዞ የወላይታዎች ቤቶችና የቤት ቁሶች ውበት ስቧቸው እንደሆነ ገልጸዋል ። በባህሉም ማንኛውም የገንዘብ አቅም ያለውና እድሜው ጉርምስና ላይ የደረሰ ወንድ ቤት እንዲሰራ የሚፈቀድ ሲሆን ሴቶች ባል አግብተው ወደ ባላቸው ቤት መሄዳቸው ስለማይቀር ቤት ለመስራት እንደማይፈቀድላቸው ገልጸዋል ።

ሌላው በብሔረሰቡ ቤት ለመስራት የተወሰነ ጊዜ እንዳላቸውና ይህም በወላይታ ብሔረሰቡ ቤት የሚሰራው ከህዳር እስከ ጥር ባለው የበጋ ወር እንደሆነ በክረምት ወንዞች ስለሚሞሉ የመስሪያ ቁሶችን ማግኘት ከባድ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ።

በግርማ ኪዳኔ ጥናት አነሳሽ ምክንያትና ዓላማ በአግባቡ መቅረባቸው የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ድክመቱ ደግሞ በጽንሰ ሀሳቦች፣ንድፈ ሀሳቦች፣በሥነ ዘዴዎችና ትንተናዎች በግልጽ ያለመቅረባቸው የጥናቱ ክፍተት ነው ።

የግርማ ኪዳኔ ጥናት ቀደም ሲል ከተሰሩት የጥናት ወረቀቶች በተሻለ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት አለው ። ይህም ሁለቱም ከቁሳዊ ባህል ዘርፎች ሥነ ምህንድስና (ባህላዊ የቤት አሰራር) ላይ የቀረቡ በመሆናቸው ተመሳሳይነት አላቸው ። ሌላው ከቦታ አንጻር ሁለቱም የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ያተኮሩ ናቸው ። ልዩነቶቹ ደግሞ ይህ ጥናት የባህላዊ ቤቶቹ የአሰራር ሂደት፤የቤቶቹ ቅርጾች ተምሳሌት እንዲሁም ቤቶቹ በሚሰሩበት ወቅት የሚታዩ፤የሚቀርቡ ስነቃሎች፤የእምነት ስርአቶች፤የተለያዩ የፎክሎር ጉዳዮች የዚህ ጥናት አካል ሲሆኑ በግርማ ጥናት ውስጥ ግን የቤቶቹ አሰራር በገለጻ መልክ ከመቅረብ ባሻገር ከብሔረሰቡ ባህል ጋር የተያያዙ ጉዳዮች ያልተካተቱና ትኩረት ያልተሰጣቸው በመሆኑ ይህ ጥናት ከግርማ ኪዳኔ የተለየ ያደርገዋል ።

Fekadu Gedamu. (2003) “The Gurage House; Its construction and socio-economic significance **በሚል** ርዕስ ለ6ኛው ዓለም አቀፍ የኢትዮጵያ የኪነ ጥበብ ታሪክ ኮንፍረንስ” ጥናት አቅርበዋል ። ይህ ጥናት በጉራጌ ባህላዊ ቤቶች ላይ አተኩሮ የጉራጌ ቤቶች የሚሰሩበት ግብአቶች ምን ምን ናቸው? የምግብ ዋስትናቸውን ለማረጋገጥ የሚያመርቱት ምርት ምንድነው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል ። የጉራጌ ቤቶች የሚሰሩባቸው ግብአቶች (ጥሬ ዕቃዎች) ዕድ፣ወይራ፣ዘንባባ፣ሳርና እንሰት እንደሆኑ በጥናቱ ተገልጿል ።

ሌላው ጉራጌዎች አራት ቤቶችን እንደሚሰሩ እና ይህንንም ሴቶችና ወንዶች በትብብርና በህብረት እንደሚሰሩት እና በቤቱ ስራ ወቅትም ቤቱን ማስዋብ የሚባሉ ደረጃዎች እንዳሉ በጥናቱ ቀርቧል ። ከዚህ በተጨማሪ ማህበረሰቡ ለቤት ውበት ከፍተኛ ግምት እንደሚሰጡ በጥናቱ ተገልጿል ።

በመጨረሻም በአሁኑ ሰዓት የጉራጌ ባህላዊ ቤቶች እየተለወጡ መሆናቸውን ይህም ቀደም ሲል በሳር ይከደኑ የነበሩት አሁን ግን ወደ ቆርቆሮ ክዳን መለወጣቸው በጥናቱ ተገልጿል ።

በፍቃዱ ጥናት ዓላማ፣ግኝትና ትንታኔ በአግባቡ ተደራጅተው መቅረባቸው የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ንድፈ ሀሳቦች፣ጽንሰ ሀሳቦችና ሥነ ዘዴዎች፣ በግልጽ ያለመቀመጣቸው ደግሞ የጥናቱ ደካማ ጎን ነው ።

የፍቃዱ ጥናት በባህላዊ ቤቶች ላይ የተሰራ በመሆኑ እና ከቦታ አንጻርም በደቡብ ላይ ስላተኮረ ተቀራራቢነት ያለው ቢሆንም የኔ ጥናት  በወላይታ ብሔረሰብ ላይ መሆኑ ደግሞ ልዩ ያደርገዋል ። ሌላው በተጠኚው ማህበረሰብ ቤቶች ላይ ለውጥ መኖሩን ማሳየቱ ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል ።

Habte Mengistu. Gamo  Society Vernacular House Typologies and Their Science, Southern Ethiopia **(**2013) in the *American Scientific Research Journal for Engineering, Technology, and Sciences* (ASRJETS), Volume 3, Issue 1. **በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል ።**

**የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በደቡብ ኢትዮጵያ የጋሞ ማህበረሰብን የቤት አይነት እና ሳይንሳቸውን መለየት ሲሆን በጥናቱ ስለ ህብረተሰቡ ቤቶች እውነታዎች የቀረበ ሆኖ የሥነ ሕንፃ ግንባታዎች ጌጣጌጦች ፣ የግንባታ ቁሳቁሶች፣ የግንባታን ቴክኒኮች ሳይመለከቱ ተለይተዋል ። የቤት ውስጥ አይነቶችን ለመወሰን በአጠቃላይ የቤቱ ዋና ወይም ዋና ክፍል ብቻ ከግምት ውስጥ ይገባል ። ትናንሽ የጎን ክንፎች፤ የኋላ አገልግሎት (ወይም ቅጥያዎች) በኋላ ላይ ተጨማሪዎች እና የተያያዙት ግንባታዎች ብዙውን ጊዜ ከግምት ውስጥ አይገቡም ።**

**ጥናቱ የተካሄደው** 57 **የአገሬው ቤቶችን በመውሰድ ነው ። ጥናቱ አይነታዊ የጥናት ዘዴን የተከተለ ሲሆን መረጃዎች የተሰበሰቡት በምልከታ ፣ በቪዲዮና ምስልን በመጠቀም ነው ። በጥናቱ ውጤትም በጋሞ ማህበረሰብ ውስጥ ዋጄ፣ካራ እና ያራ የተባሉ ሶስት ዋና ዋና የአገሬው ቤቶች እንዳሉ የተገለጸ ሲሆን እነዚህም በቅርጻቸው፤ በተግባራቸውና በአሰራራቸው እና በተጠቀሙበት የግንባታ ቁሳቁስ እንደተለዩ በጥናቱ ተገልጿል ። ሌላው የጥናቱ ውጤት  የጋሞ ብሔረሰብ ከመኖሪያ ቤታቸው ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን የሚያሳይ ነው ። ሁለቱም ጥናቶች በደቡብ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው የሚቀራረቡ ሲሆን ልዩነታቸው በጋሞ ላይ የተጠናው የቤት አይነቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ ከአይነቶቹ ባሻገር የቤቱ ቅርጽ ከቤት አሰራሩ ጋር የተገናኙ ጉዳዮች የቤቶቹ አሰራር ተምሳሌቶች፣ቤቶቹ ሲሰሩ የሚቀርቡ ዘፈኖችና ምግቦች ላይ ያተኮረ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል ።**

Alemayehu Darge Dalbiso & Denamo Addissie Nuramo (2019)“Ethiopian Vernacular Bamboo Architecture and Its Potentials for Adaptation in Modern Urban Housing: A case Study” **በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል ። በዚህ ጥናት ኢትዮጵያ ግዙፍ የቀርከሃ ሃብት የተጎናጸፈች ብቻ ሳትሆን እጅግ የበለጸገ ባህላዊ የቀርከሃ ቤት ግንባታ ቴክኒኮች ያላት ሀገር እንደሆነች የተገለጸ ሲሆን ይህም ከሺህ አመታት በላይ እንደቆየ በጥናቱ ተገልጿል ። እነዚህ የግንባታ ልማዶች በገጠር ለሚኖሩ በሚሊዮን ለሚቆጠሩ ሰዎች ቤቶችን በርካሽ ዋጋ ማቅረብ የስራ እድል መፍጠር፤ ለመኖሪያ ቤት ግንባታ የተፈጥሮ ደኖችን ሽክም መቀነስ እና የገቢ ማስገኛን ጨምሮ በርካታ ጥቅሞች እንዳሉት በጥናቱ ተገልጿል ።**

**ኢትዮጵያ ውስጥ ሁለት አይነት የቀርከሃ ዝርያዎች እንዳሉና እነሱም** Oxytentra abyssinica lowland bam-boo and Yushania alpine highland bamboo **ኦክሲቴንትራ አቢሲኒካ በተለምዶ ቆላ ቀርከሃ እና**

ዩሻኒያ አልፓይን የደጋ ቀርከሃ በመባል እንደሚታወቁ በጥናቱ ተገልጿል ። ሁለቱም ዝርያዎች በደቡብ ኢትዮጵያ የሚገኘውን የሲዳማ ቤትን ጨምሮ ለበርካታ ባህላዊ የመኖሪያ ቤቶች ግንባታ ያገለግላሉ ። ይህ ጥናት የቀርከሃ ግንባታ ቴክኒኮች በኢትዮጵያ የቀርከሃ አብቃይ በሆኑ አካባቢዎች የመኖሪያ ቤት አቅርቦት ላይ አተኩሯል ። መረጃዎች በምልከታ እና በግላዊ ቃለ መጠይቅ አማካይነት የማሰባሰብ ስራ በክልሉ ተካሂዷል ። አይነታዊ እና መጠናዊ ዘዴዎችን በመጠቀም የግንባታ ቴክኒኮችን እና አጠቃላይ ሂደቱ ተለይቷል ።

የሲዳማ ቤት ቅርጽ እና መዋቅር በዋናነት ጥቅም ላይ የዋለው ቁሳቁስ ውጤት ነው ። የሽንኩርት ቅርጽ እና ክብ ቅርጽ የሚፈጠረው በቀርከሃ ተክል ተለዋዋጭነት ነው ። አብዛኛውን የግንባታ ስራ በቡድን መስራት ይመርጣሉ ።

በቻይና ውስጥ ያሉ ሰዎች ከ2-8 ሳምንታት የሚፈጀውን አጠቃላይ የግንባታ ሂደት ለመከታተል 'ሙርቻ ' የሚባል መሪ እንደሚመርጡ በጥናቱ ተገልጿል ። አጠቃላይ የግንባታ ሂደት ለመከታተል የማይተባበሩ አባላት ከቡድኑ የተገለሉ እንደሚሆኑ በጥናቱ ተመላክቷል ። በአሁኑ ጊዜ እጅግ የላቀው ባህላዊ የግንባታ ክህሎት በዘር የሚተላለፍ እና በቤተሰብ ውስጥ ከአባቶች ወደ ልጅና ወደ ልጅ ልጆች ብቻ የሚተላለፍ እንደሆነም በጥናቱ ቀርቧል ። ስለዚህ የኢትዮጵያ መንግስት እና የቀርከሃ ዘርፍ ከሀገር ውስጥ ገንቢዎች ጋር በቅርበት በመስራት ባህላዊ ስነምህንድስናን ማሻሻል አስፈላጊ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ። ይህ ደግሞ በገጠር ክላስተር መንደር ሰፈራ መርሃ ግብር አማካይነት በኢትዮጵያ የገጠር ድሃ መኖሪያ ቤቶችን በሰብአዊ ፕሮግራሞች ለማሻሻል እድል እንደሚሰጥ በጥናቱ ተጠቁሟል ። ሁለቱም ጥናቶች በደቡብ ላይ የተሰሩ በመሆናቸው በተወሰነ ደረጃ የሚቀራረቡ ሲሆን ልዩነታቸው በሲዳማ ላይ የተጠናው ከቀርከሃ የሚሰሩ ቤቶች ላይ ብቻ ያተኮረ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የቤት አይነቶች፣የቤቶቹ አሰራርና ትእምርቶች፣ቤቶቹ ሲሰሩ የሚቀርቡ የስነቃል ዘርፎች ላይ ያተኮረ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል ።

Nobuhiro Shimizu, Ephrem Telele, Alula Tesfay and Riichi Miyake "Fundamentals of Hidmo in Inderta: A Traditional House Type in Tigray Region Ethiopia"(2019) በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል ይህ ጥናት Hidmo ስለተባለውና በኢትዮጵያ በትግራይ ክልል በሚታየው ባህላዊ የቤት አይነት እና ከኤርትራ ደጋማ ቦታዎች ጋር ተያይዞ በዋናነት ግንቦች፣ግድግዳዎች፣ የእንጨት ጣሪያዎች እና የአፈር ጣሪያዎችን ያቀፈ ነው ። ጥናቱ ያተኮረው በቀድሞው የኢንደርታ ጠቅላይ ግዛት በአሁኑ የትግራይ ክልል ደቡብ ምስራቃዊ ዞን በሚገኘው የቤት አይነት ላይ ነው ። ዓላማውም በአካባቢያዊ የግንባታ እቃዎች መሰረታዊ እውቀት ላይ በመመርኮዝ የተለመደውን የእሸግ አቀማመጥ Hidmo ቤት

የቦታ እና የግንባታ አካላትን ግልጽ ማድረግ ሲሆን በዚህ መሰረት የእያንዳንዱ ህንጻ መዝገበ ቃላት ማዘጋጀት እና በእሸጉ ውስጥ ያለው  እያንዳንዱ ቦታ በHidmo ቤት ውስጥ የግንባታ አካሉን ለመረዳት ይረዳል ፡፡

በዚሁ ጥናት የተለመደው የእሸግ አቀማመጥ የተለመደው ቤት የቦታ ክፍሎች እና የመደበኛ ቤት የግንባታ አካላት ተፈትሸዋል ፡፡ በእያንዳንዱ እሸግ ውስጥ ሰዎች ለመኝታ ፣ ለመብላት፣ሌሎችን እንዲጎበኙ ለመጋበዝ ፣ እህል እና ቁሳቁሶችን ለማከማቸት ፣ ምግብ ለማብሰል፣የቤት እንስሳትን ለመጠበቅ እና ሌሎች የዕለት ተዕለት ተግባራትን ለማከናወን ህንፃዎችን እና ቦታዎችን እንደሰሩ በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

አብዛኛዎቹ የዕለት ተዕለት የቤት ውስጥ እንቅስቃሴዎች በዋናው ቤት ውስጥ ይከናወናሉ ፡፡ በጥናቱ እንደተገለጸው ሚድራ-ቤት የመግቢያ በር ያለው የዋናው ቤት ማዕከላዊ ቦታ ነው ፡፡ በተጨማሪም የእህል ማከማቻ እና ትናንሽ የቤት እንስሳትን ለማኖር ባለ ሁለት ፎቅ ክፍል ለመኝታ እና ለማከማቸት አንድ ፎቅ ክፍል ብዙውን ጊዜ ተያይዟል ፡፡ በተወሰኑ ክፍት ቦታዎች ምክንያት የክፍሉ ውስጠኛው ክፍል በደንብ አይሰራም ፡፡  ይሁን እንጂ ወፍራም ግድግዳዎች እና ጣሪያው ለቤት ውስጥ  ጥንካሬ አስተዋፅኦ ያደርጋሉ ፡፡ ምንም እንኳን እያንዳንዱ የቦታ ክፍል እና የግንባታ አካል አንድ ዓይነት ስም ቢኖረውም ብዙውን ጊዜ እንደ ግንበኞቹ የአሰራር መንገድ ይለያያል ፡፡

የHidmo ቤት ዋና ቁሳቁሶች ድንጋዮች እና እንጨቶች ናቸው ፡፡ የድንጋይ ቁሳቁሶች ለግድግዳዎች ጥቅም ላይ ሲውሉ እንጨት ለጣሪያ እንደሚውል ቀርቧል ፡፡ የድንጋይ ቁሳቁሶች ከጎረቤት ወይም በአቅራቢያ ካሉ ቦታዎች ይሰበሰባሉ ፡፡ በኢንደርታ ውስጥ እንደ ኖራ ድንጋይ ያሉ ደለል ቋጥኞች በብዙ ቦታዎች ይገኛሉ ፡፡ በሌላ በኩል እንጨት እምብዛም የማይገኝ ቁሳቁስ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ፡፡ ስለዚህ ተጨማሪ የእንጨት ቁሳቁሶችን መጠቀም የቤቱን ክብር እንደሚጨምርም በጥናቱ ሰፍሯል ፡፡ ይህ ማለት የግንባታ ዘዴ እና መጠን ላይ ብቻ ሳይሆን የተተገበረው የግንባታ ቁሳቁስ የቤቱን ቦታ በአካባቢያዊ አውድ ውስጥ በተዋረድ ውስጥ ለመወሰን አንድ ምክንያት እንደነበር በጥናቱ ቀርቧል ፡፡

በዚህ ጥናት ውስጥ የባህላዊው Hidmo ቤት መሠረታዊ ነገሮች ተብራርተዋል ፡፡ የአካባቢውን የግንባታ ባህል ቅርስ እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል እና ለወደፊቱ ተፈላጊ የመኖሪያ አካባቢዎችን እንዴት ዲዛይን ማድረግ እንደሚቻል ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን መሰረታዊ እውቀት እንደገና መገምገም እንዳለበት በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

በትግራይ ክልል ባህላዊ ቤት ላይ የተሰራው ጥናት በአካባቢያዊ የግንባታ እቃዎች መሰረታዊ እውቀት ላይ በመመርኮዝ የHidmo ቤት የቦታ እና የግንባታ አካላትን ግልጽ ማድረግ የሚል ሲሆን የቤት አይነቶችና የግንባታ ግብአቶችን በማንሳቱ በተወሰነ የሚቀራረብ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የቤቶቹ አሰራርና ትእምርቶች፣ቤቶቹ ሲሰሩ የሚቀርቡ የስነቃል ዘርፎች ላይ ያተኮረ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል

Philip, LeBel. (1969) " On Guragé Architecture" ለ*Journal of Ethiopian Studies,* በሚል ርእስ ጥናት አቅርበዋል ። የLeBel, ጥናት መሰረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች መዋቅራዊ ቅርጽ ባህላዊ ጠቀሜታዎችና ንጽጽራዊ ትንታኔዎች ሲሆኑ በመዋቅራዊ ቅርጽ ስር የLeBel, ጥናት መሰረታዊ ሀሳብ ስለጉራጌ ሕዝብ አኗኗር፤ ስለህንፃ ግንባታ ዕውቀታቸው፤ ስለአሰፋፈራቸው እና ለግንባታው ስለሚጠቀሙት ግብአቶች በሰፊው አስቀምጧል ።

በባህላዊ ጠቀሜታዎች ደግሞ በLeBel, ጥናት መልዕክቱ የጉራጌ ሕንፃ ቅርጾች ስለባህላቸው፣ ማህበራዊ ትስስራቸው እና ከአካባቢያቸው ጋር ተላምዶ የመኖር ጥበባቸውን አትቷል ። በመጨረሻም ንጽጽራዊ ትንታኔ LeBel, ጥናት የጉራጌን የሕንጻ ጥበብ በሰፊው የኢትዮጵያ እና የአፍሪካ ኪነ-ህንፃ ጥበባት ባህልና ሥነምህዳራዊ ተጽእኖና እይታ ውስጥ አካቶ በንጽጽር አስቀምጧል ። በዚህ ጥናት የጉራጌ ቤት ግንባታ ጥንቃቄ የተሞላበት እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን ይህ ደግሞ ለቤቶቹ ከፍተኛ ጥራት እና የቆይታ ጊዜያቸውን እንደሚያመለክት በጥናቱ ተገልጿል ። በዚህም ብዙ ቤቶች በበቂ መጠን በቀይ እንጨት ከተሠሩ የምስጥ ድግሱን ለመከላከል አስፈላጊ ነው ። ብዙ የጉራጌ ቤቶች ለሃምሳ ዓመታት ወይም ከዚያ በላይ የሚቆዩ ሲሆን በየአሥር እና አሥራ አምስት ዓመቱ ብቻ አዲስ ጣራ እንደሚያስፈልጋቸው በጥናቱ ተገልጿል ። ቤቶቹ በቀን ቀዝቃዛ ሲሆኑ በሌሊት ደግሞ ይሞቃሉ ። በጥናቱ እንደተጠቀሰው ከፍተኛው ግድግዳ እና ጣሪያው ጭስ በጣራው ላይ በፍጥነት እንዲወጣ ስለሚያደርግ የአየር ማራዘሚያ በጭራሽ ችግር የለበትም ። ሆኖም እነዚህ ቤቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የመጥፋት አደጋ የተጋረጠባቸው ሲሆን ለዚህም ዋናው ምክንያት ለመገንባት የሚያስፈልገው ወጪ አድካሚ እና ጥረት የሚጠይቅ መሆኑ ነው ።

አሁን ባለው ዋጋ የሳር ቤት ለመገንባት አስቸጋሪ ነው ። ሌላው ችግር ደግሞ የአካባቢው ደህንነት ሲበላሽ ባለቤቱ በቀጥታ ገንዘብ እንዲያቀርብ ግፊት ስለሚደረግበት የሳር ቤት ግንባታ ዋጋ ሊጨምር መቻሉ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ የሳር ቤት ለእሳት አደጋ የመጋለጥ እድል አለው ። ይህን የመሰለ ከባድ መዋዕለ ንዋይ በማፍሰስ ጥሩ soeur bét በመገንባት ላይ የሚያጋጥሙት አደጋዎች ከጊዜ ወደ ጊዜ እየመረመረ እንደሆነ በጥናቱ የተገለጸ ሲሆን soeur bét እነዚህ ሁሉ ችግሮች ቢኖሩትም ይህን

የመሰለ ጥሩ ባህል ከኢትዮጵያ እየጠፋ ነው ። ምክንያቱም አኩሪ ባህል የሀገሪቱ ጥንታዊ ቅርሶች ዋነኛ መገለጫ እንደሆነ ጥናቱ ያትታል ።

በደቡብ ምዕራብ ሸዋ ከሚኖሩ የጉራጌ ህዝቦች መካከል ጥራት ያለው የቤት ውስጥ አርክቴክቸር ባህል እንዳለና እሱንም The Guragé tuqul or soeur bét ጉራጌ ቱኩል ወይም ሶውር ቤት ብለው ሊጠሩት እንደመረጡና ይህም የገጠር መለያ እንደሆነ በጥናቱ ቀርቧል ። እነዚህን ቤቶች በ1955 ዓ.ም በአዲስ አበባ በተካሄደው ሀገር አቀፍ የቤቶች ኤግዚቢሽን ላይ ያቀረበው የጉራጌ ኤግዚቢሽን ኮሚቴ በላቀ ግንባታ እንደተሸለመ በጥናቱ ተገልጿል።

የጉራጌ Soeur bét ከብዙ የአገሪቱ አካባቢዎች የሚለያቸው የዝግጅት አቀማመጥ እና የግንባታ ዘዴዎች ሲሆን ይህም በጉራጌ soeur bét የኢትዮጵያን ሕዝቦች የሚያለሙ ብዙ የእንሰት ተክሎችና መኖሪያ ቤቶች በመንደር ውስጥ በሥርዓት ተደርድረው መገኘታቸው ነው ። የጉራጌ መንደር ሰፈር qaya ቀያ በመባል ይታወቃል ።

ሰፈራዎች ቀጣይነት ባለው መስመር (jäfwärä) የሚገኙ ሲሆን ይህም የአካባቢው አውራ ጎዳና ይሉታል። ሰፈራ በየመንደሩ፣ በየቤቱ yä at säb bét፣ አንድ፣ ሁለት ወይም ሶስት ቤቶችን ሊያካትት ይችላል። በሰፈራ ንድፍ ውስጥ በጥንቃቄ የተደረደሩ በእያንዳንዱ መኖሪያ ቤት ዙሪያ የ äsät ወይም Ensete ventricosum ረድፎች እንደሆኑ በጥናቱ ቀርቧል። እንሰቱም በጉራጌዎች ዘንድ ለምግብነት እና ለsoeur béts ግንባታ በጣም አስፈላጊ ነው ። የ äsät (የእንሰት) ማሳዎች በቤቶቹ ዙሪያ በጥንቃቄ የተደረደሩ ሲሆን ወፍራም አረንጓዴ ቅጠሎቻቸው ደግሞ የእሳት መስፋፋትን ለመከላከል ይረዳሉ ። ከእያንዳንዱ ቤት እስከ jäfwärä ድረስ ጋይካታ በመባል የሚታወቁት ወፍራም አረንጓዴ ሣር ያላቸው የእግረኛ መንገዶች ይገኛሉ ። እነዚህ የእግር መንገዶች ኤማ፣ከመንደሩ ውጭ ዉር ኤማ ተብሎ በሚጠራዉ jäfwärä ላይ ተጨማሪ የመንደር ጉዞ ይደረጋል ። በእያንዳንዱ ቤተሰብ ውስጥ ከፍተኛው የቤቶች ብዛት ሦስት ሲሆን በጣም ትልቅ እና መካከለኛ መጠን ያላቸው ቤቶች ይገኛሉ ። እንደ ቅደም ተከተላቸው gweä ፣ xärar እና zägär በጉራጌ የቤት ህይወት ውስጥ ለሚኖሩ የተለያዩ እንቅስቃሴዎች መነሻዎች ናቸው ። የእነዚህ ቤቶች ዲያሜትሮች ከአራት እስከ አስር ሜትር ቁመታቸውም በእኩል መጠን የሚሰራ ነው ። ሌላው gweä እንስሳትን ለመጠበቅ ሸቀጦችን ለማከማቸት አልፎ አልፎ እንደሚያገለግል በጥናቱ ተገልጿል ።

በጥናቱ እንደተገለጸው xärarን ለመጠበቅ በዋናው የመኖሪያ ክፍሎች ውስጥ ምንም አይነት መጨናነቅ እንዳይፈጠር በgweä ውስጥ ምግብ ሁል ጊዜ ይበስላል ። zägär ቤት ለዳቦ እና አረቂ ያሉ መጠጦችን ለማዘጋጀት የሚያገለግል ሲሆን ሌላው የአካባቢው ሴቶች ወተት፣ ቅቤ ወይም ሌላ ለማጠራቀም እንደ

ጊዜያዊ መሰብሰቢያ ያገለግላል ። በተጨማሪ ለትልቅ በዓል ዝግጅት፤ አልፎ አልፎ ሌሎች ክፍሎች ሲጎድሉ፣ zägär ቤት ሊያገለግል እንደሚችል በጥናቱ ተገልጿል በጉራጌ ቤቶች ላይ የተሰራው ጥናት በሳር ቤት ላይ ያተኮረ ሆኖ ይህም ለእሳት አደጋ የመጋለጥ እድል አለው ። ሌላው እነዚህ ቤቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የመጥፋት አደጋ እንደተጋረጠባቸው የሚያሳይ እንደሆነ በጥናቱ ተብራርቷል ። ሁለቱም ጥናቶች በደቡብ ላይ የተሰሩና ባህላዊ ቤት ላይ ማትኮራቸው ሲያቀራርባቸው ልዩነታቸው የጉራጌ ቤት ላይ የተጠናው የቤቶቹ አሰራር ፤ቤቶቹ የመጥፋት አደጋ እንደተጋረጠባቸው መግለጹ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የቤቶቹ አሰራርና ትእምርቶች፤የቤቶቹ ቅርጽና ተምሳሌት ቤቶቹ ሲሰሩ የሚቀርቡ የስነቃል ዘርፎች ላይ ያተኮረ መሆኑ የተለየ ያደርገዋል ።

### 2.3.2. ባህላዊ የቤት አሰራርን ከስነ ቃል ጋር አያይዘው ያጠኑ

ማማዬ አያሌው፤ (2002) "በአፋር ክልል የቤት አሰራር ሂደትና በሂደቱ የሚነገሩ ስነ ቃሎች ይዘት ትንተና" በሚል ርዕስ ለመጀመሪያ ዲግሪ ጥናት አቅርባለች።የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የአፋር ክልል የቤት አሰራር ሂደትና በሂደቱም የሚነገሩ ስነ ቃሎች ምን እንደሚመስሉ መግለጽ ሆኖ የአፋር ድንኳን መሰል ባህላዊ ቤት አድአሪ ወይም አሪ በመባል እንደሚታወቅ እና የሚሰራውም ጠንከር ካሉ ቀጫጭን እንጨቶች ተዋቅሮ ጣራው በሳር እና በፊላ እንደሚሸፈን በጥናቱ ተገልጿል። በአፋር ቤት የሚሰሩት ሴቶች እንደሆኑ እና ቤቶቹም ከሚያዝያ ወር በኋላ የሚሰሩ እንደሆነ ቀርቧል። የማማዬ ጥናት በቀረበበት ደረጃ ዓላማውና ትንታኔው በአግባቡ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው። የማማዬ ጥናት እንደቀረበበት ደረጃ በዓላማ፣በጽንሰ ሀሳቦች፣ንድፈ ሃሳቦችና ሥነ ዘዴዎች ክፍተት ታይቶበታል።

የማማዬ ጥናት ባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ያተኮረ የፎክሎር ጥናት በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሲሆን ልዩነቱ ደግሞ በቦታና በቀረበበት ደረጃ ከዚህ ጥናት የተለየ ነው።

### 2.3.3. ባህላዊ ቤትን ከእደ ጥበብ ጋር በማጣመር የተጠኑ ጥናቶች

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ለአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡት ጥናቶች ሁለት ሲሆኑ እነዚህም እንደሚከተለው ቀርበዋል ።

አስቴር ሙሉ (2000) "ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች በዘጌ ባህረ ሰላጤ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ አጠናን መንገድ መግለጽ፣መቅረስ፣መሰነድና ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ

የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም ነው፡፡ ጥናቱ የዘጌ ባህረ ሰላጤ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች አይነታቸውና አገልግሎታቸው ምን ይመስላል? በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች አሰራር ምን ምን ገጽታዎች አሏቸው? በዘጌ ባህረ ሰላጤ ውስጥ የሚገኙ ቤቶች ከሀገረሰባዊ ምህንድስና አንጻር ምን ልዩ ሁኔታ ይታይባቸዋል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ መረጃዎች በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴ ተሰብስበዋል ፡፡ ቁሶቹ ማህበረሰቡ ቅርጻቸውን ተከትሎ ለመለያ ሲል በተሰጣቸው ስያሜ መሰረት ከተግባራቸው አንጻር መዋገናቸው በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

ይህ ጥናት በዘጌ ባህረ ሰላጤ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶችንና ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶችን በሳይንሳዊ የአጠናን መንገድ ከመግለጽ፣ ከመቅረስና ከመሰነድ በተጨማሪ ለማህበረሰቡ ጠቀሜታ የሚያበረክቱበት መንገድን መጠቆም በሚል የቀረበ ነው ፡፡ ሌላው የቤት ዓይነቶችን፣ የአሰራር ሂደት ደረጃዎችን፣ ማህበራዊ መስተጋብሮችን፣ የቤቶቹን መጠንና ቅርጽ ይህን ተከትሎም የባለቤቶቹን የኑሮና የክብር ደረጃ ለማሳየት የተቻለ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ የእጅ ስራ ቁሶችንም በተመሳሳይ መልኩ መግለጽና መተንተን የተቻለ ሲሆን የሀገረሰባዊ ቤቶችም ሆኑ የእጅ ስራ ቁሶቹ በመጥፋት ላይ መሆንና ለዚህ ደረጃ መድረስ ተፅእኖ ፈጣሪዎችን በጥናቱ ለማመልከት ተሞክሯል ፡፡ የጥናቱ ግኝትም ሀገረሰባዊ ቤቶቹም ሆኑ የእጅ ስራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆናቸውን በመግለጽ ይደመድማል ፡፡

የአስቴር ጥናት በአነሳሽ ምክንያት፣በዓላማና በሥነ ዘዴ በአግባቡ ተደራጅቶ የቀረበ መሆኑ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ንድፈ ሀሳብን በተመለከተ በጥናቱ የተነሳ ሀሳብ አለመኖሩና በትንታኔው ግልጽነት ያለመኖር ችግር የጥናቱ ደካማ ጎን ነው ፡፡

የአስቴር ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም በፎክሎር የጥናት መስክ በቁሳዊ ባህል ላይ ያተኮሩ መሆናቸው፤ ሲሆን ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር የአስቴር ጥናት በከፊል ባህላዊ ቤትን በማንሳቱ የተወሰነ መቀራረብ አለው፡፡ ልዩነቱ ከጥናት ቦታ አንጻር ሲሆን የአስቴር ጥናት በአማራ ክልል ሆኖ በምዕራብ ጎጃም ላይ ትኩረት ያደረገ ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ በደቡብ ክልል ሆኖ በወላይታ ዞን በሚገኙ በተመረጡ ወረዳዎችና የከተማ አስተዳደሮች ላይ ትኩረት አድርጓል፡፡

አስማማው እስተዚያ (2003) "በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች በደጋ ዳሞት ወረዳ" በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል ፡፡ የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በደጋ ዳሞት ወረዳ በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች አሰራር ብሎም በምን ተጽእኖና እንዴት እየጠፉ እንዳሉ በመግለጽ ማሳየት ላይ ያተኮረ ነው ፡፡ ጥናቱም በወረዳዋ በመጥፋት ላይ ያሉትን ሀገረሰባዊ ቤቶችና

የእጅ ስራ ቁሶች መለየት፣ የሀገረሰባዊ ቤቶቹና የእጅ ስራ ቁሶቹ በመጥፋት ላይ ለመሆናቸው ተጽዕኖ ያሳደሩ ጉዳዮችን መጠቆም፣ የሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶችን የመስሪያ ቁሳቁስ የአሰራር ሂደታቸውን፣አገልግሎታቸውንና ሰሪዎቻቸውን መግለጽ ለሚሉ ጥያቄዎች መልስ ሰጥቷል፡፡ በጥናቱ ቃለ መጠይቅና ምልከታ ዋነኛ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ሲሆኑ በአጋዥነት ወይም መረጃን በማሟያነት ደግሞ የፅሁፍ መጠይቅ፣ የናሙና ጥናትና የተተኳሪ ቡድን ውይይት ለመረጃ መሰብሰቢያነት ጥቅም ላይ ውለዋል ፡፡ በውጤቱም የሀገረሰባዊ ቤቶቹም ሆኑ የእጅ ሥራ ቁሶች በመጥፋት ላይ መሆንና ለዚህ ደረጃ መድረስ ተጽዕኖ የተመለከቱት የደን መጨፍጨፍ፣የኢንዱስትሪ ምርቶች በገፍ መመረት፣ባህላዊ ቁሶች የኋላ ቀር ምልክት ተደርገው መወሰድ እንደሆኑ በጥናቱ ተጠቁሟል ፡፡ የአስማማው ጥናት ዓላማ፣ሥነ ዘዴ እና የትንተናው ክፍሎች በአግባቡ ተደራጅተው መቅረባቸው የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ደካማ ጎኑ ደግሞ የንድፈ ሀሳቦች በግልጽነት አለመቅረብ ነው ፡፡

የአስማማው ጥናት ስለሀገረሰባዊ ቤቶች በከፊል ስላጠና በተወሰነ መንገድ ከዚህ ጥናት ጋር የሚቀራረብ ሲሆን በተጨማሪም የሁለቱም የጥናት መስኮች ፎክሎር መሆናቸው ያመሳስላቸዋል ፡፡

ብሩክታዊት ብርሃኑ (2011) “የባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብ በባሶና ወረና ወረዳ” በሚል ጥናት አቅርባለች፡፡ የጥናቱ ዋና ዓላማ በባሶና ወረና ወረዳ የሚገኙ ባህላዊ ቤቶች ማህበራዊ ግንኙነትን ከማጠናከር እንዲሁም ሀገር በቀል እውቀት ላይ የተመሰረቱ ፍልስፍናዎችን ከማንጸባረቅ አንጻር ያላቸውን ሚና መመርመር ነው፡፡ በጥናቱ ሂደትም ለጥናቱ በተመረጠው ወረዳ ያሉ ባህላዊ የቤት ዓይነቶች ምን ምን ናቸው? ለባህላዊ ቤቶች በግብአትነት የሚውሉት ጥሬ እቃዎች ምን ምን ናቸው? ለቤቱ ግንባታ በተለየ ሁኔታ የሚመረጥ ቦታ እና ወቅት አለ? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናታቸው መልስ ሰጥተዋል ፡፡ እነዚህን የምርምር ጥያቄዎች ከግብ ለማድረስ ቃለ መጠይቅ እና ምልከታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል ፡፡

የተሰበሰበውን መረጃ ለመተንተን ገላጭ የመተንተኛ ዘዴ ተጠቅመዋል ፡፡ ጥናቱ በባሶና ወረና ወረዳ ውስጥ በሚገኙ ሦስት ቀበሌዎች ላይ የተደረገ ሲሆን የርዕሰ ጉዳይ ትኩረቱም የባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብ ላይ ብቻ እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል ፡፡ ሌላው በወረዳው የሚገኙ የማህበረሰቡ የግንባታ ጥበብ አሻራ ያረፈባቸው ቤቶች ላይ እንደመሆኑ በቅርጻቸው፣በሚሰሩበት ጥሬ እቃ እና በአሰራር ስልታቸው የተለያየ ስያሜ እንዳላቸው በጥናቱ ያስረዱ ሲሆን በዚህም እልፍኝ (ቤተ ንጉስ)፣አዳራሽ (መአዘን)፣ ዳስ እና ችግሬ ቤት የሚባሉ ሲሆኑ ከሚሰሩበት ጥሬ እቃ አኳያ ደግሞ የግንብ እና የግድግዳ ቤት ናቸው ፡፡

በጥናቱ ከቤቶቹ ዓይነት እና የግንባታ ጥሬ እቃ ባሻገር የባህላዊ ቤቶቹ አጠቃላይ (የውስጥና የውጪ) መዋቅር በቤት አሰራሩ ከግንባታው በፊት ከግምት ውስጥ የሚገቡ ጉዳዮች፣የተፈጥሮና የባህል ትስስር እንዲሁም ቤቶቹ ለማህበራዊ ግንኙነት ያላቸው አስተዋጽኦ የሚሉት ርዕሰ ጉዳዮች ትኩረት ተደርጎባቸዋል ፡፡

በሌላ በኩል የቤቶቹ ቅርጽ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተቀየረ ለመምጣቱ ዋና ዋና የተባሉት ምክንያቶች በጥናቱ የተካተቱ ሲሆን እነሱም የሳር ቤቶች ለእሳት አደጋ የተጋለጡ ናቸው ፡፡ ሌላው ከሳር ቤቶች ይልቅ አሁን የመጡት የቆርቆሮ ቤቶች ለአሰራር ምቹ መሆናቸው ሲሆን በተቃራኒው ደግሞ የሳር ቤቶች በሚሰሩበት ወቅት በጣም አድካሚ እንደሆኑ እና ቶሎ ቶሎ መታደስ የሚፈልጉ መሆናቸው ነው ፡፡ ሌላው የቆርቆሮ ቤቶች በአንጻራዊነት የተሻለ እድሜ እንዳላቸው በጥናቱ ተገልጿል ፡፡ ከእነዚህ ሀገረሰባዊ ቤቶች መመናመን ጋር ተያይዞ በግንባታ ጥበቡ ላይ እየመጣ ያለው ለውጥ እና ቀጣይነት ሌላኛው የጥናቱ ትኩረት ነው ፡፡ በመሆኑም የግንባታ ጥሬ እቃዎች መለወጥ፤በግንባታ ወቅት የነበረው የደቦ ሥርዓት መቀዛቀዝ፤ እንዲሁም ለግንባታ የሚመረጠው ወቅት ከለውጡ ጋር የሚመደቡ ሲሆኑ ቀጣይነቱን የሚያሳዩት ደግሞ በቆርቆሮ ቤት ውስጣዊ ክፍል የመደብ መኖር(መገንባት)፤ ለወለሉና ለግድግዳ ማስዋቢያ አዛባ መጠቀም እና አንዱ ቤት ከሌላው ቤት ጋር ያለው ርቀት በቀደመው መንገድ መሆን በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

የብሩክታዊት ጥናት በባሶና ወረና ወረዳ የባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብን በተመለከተ በስነ ዘዴ፣በንድፈ ሀሳብ፣ክለሳ ድርሳን እና የትንተናው ክፍል በአግባቡ የተደራጁና የተገለጹ መሆናቸው የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን በጥናቱ ምን ያህል መረጃ ሰጪዎች ተመረጡ? የተመረጡበት ምክንያት ምንድነው? የቡድን ተኮር ውይይት መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ለምን እንዳልተመረጠ? የተገለጸ ነገር ካለመኖሩ ባሻገር በምልከታና በቃለ መጠይቅ ምን አይነት መረጃዎች እንደተሰበሰቡ? የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች ለምን አልተካተቱም? ለሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ ምላሽ አልተሰጠም፡፡ በመሆኑም ጥናቱ የስነ ዘዴ ክፍተት አለው ፡፡

የብሩክታዊት ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር የሚያመሳስለው ሁለቱም በባህላዊ ቤት ላይ ያተኮሩ መሆናቸው ሲሆን በተጨማሪም የንድፈ ሀሳብ፣የሥነ ዘዴ ወዘተ… በተወሰነ መንገድ ተቀራራቢነት አላቸው ፡፡ ከትኩረት አቅጣጫ አንጻር የብሩክታዊት ጥናት የባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብ በባሶና ወረና ወረዳ የሚል ሲሆን ይህ ጥናት ደግሞ የወላይታ ማህበረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር እውቀት ላይ ትኩረት ተደርጎ የተሰራ በመሆኑ ልዩነት አሳይቷል ፡፡

### 2.3.4. ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብን በተመለከተ በአፍሪካ እና በተለያዩ የውጭ ሀገራት የተሰሩ ጥናቶች

Oluwagbemiga Paul Agboola and Modi sule Zango (2014) “Development of Traditional Architecture in Nigeria: study of HAUSA House Form” **በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል ። የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ በናይጀሪያ ውስጥ የባህላዊ ምህንድስና እድገት በሀውሳ ቤት ማሳያነት የሚል ሲሆን የሀውሳ ቤት ጥናት ባህላዊ የህንጻ ጥበብ እድገት አስተዋጽኦ ያደረገው ምንድነው? እውቀቱ የሚከናወነው በየትኛው ግብአት ነው? የአሰራር ስልቱና አቀማመጡ ምን ይመስላል? አካባቢያዊ እና ባህላዊ ምክንያቶቹ ምንድናቸው? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሰጠ ሲሆን በውጤቱም የሀውሳ ባህላዊ የህንጻ ጥበብ እድገት አስተዋጽኦ ዕውቀቱ የሚከናወነው ወይም የሚሰራው በአገር ውስጥ ግብአቶች አሰራር ስልቱ፣አቀያየሱ (አቀማመጡ)፣ማህበራዊነቱ እንዲሁም ባህላዊ እና አካባቢያዊ ምክንያቶቹ ከሌላው እንዲለይ እንዳደረገው በጥናቱ ቀርቧል። በናይጀሪያ ባህላዊ ህንጻዎች ከዳር እስከ ዳር መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ ያላቸው ሲሆን ይህም የአየር ንብረት ማሳያ ውጤት መሆኑ በዚህም የአገር ውስጥ ቴክኖሎጂ ማህበራዊ ኢኮኖሚን መፍጠሩም በጥናቱ ተገልጿል ።**

**ሌላው በናይጄሪያ የኮሎኒያሊዝም መምጣት የባህላዊ ህይወት ልምዱ እና የናይጄሪያ ባህል እንዲለወጥ ያደረገ መሆኑ ይህም በባህላዊ ምህንድስና (የህንጻ ጥበብ) እና በዘመናዊ የህንፃ ጥበብ መካከል ደካማ የሆነ ግንኙነት እንዲኖር እድሉን እንደ ፈጠረ በጥናቱ ተገልጿል። በአብዛኛው በናይጄሪያ ውስጥ በቅርቡ የተገነቡት ህንፃዎች ከውጭ አገር በመጡ (በሚገቡ) የመስሪያ ግብአቶች እና ቴክኒኮች እንደሆኑ በጥናቱ ቀርቧል ። በመጨረሻም የሀውሳ ባህላዊ የህንጻ ጥበብ እንዲለወጥ ተጽዕኖ ካሳደሩት መካከል ዘመናዊ ግብአቶችና ቴክኖሎጂ፣ የገጽታ ለውጥ፣የአሰራር ለውጥ፣ባህላዊውን አስወግዶ በዘመናዊ ቀለም ማስዋብ፣ጣሪያው የሳር ክዳን የነበረውን በቆርቆሮ መለወጥ፣ ክርባዊ (ጎባጣ) የነበረውን በሱ ፋንታ ቀጥተኛ መስመር እንዲይዙ ተደርጎ መሰራቱ ለለውጡ ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል። ዓላማውና ትንታኔው ተደራጅተው መቅረባቸው የጥናቱ ጠንካራ ጎን ነው ። በባህላዊ ቤቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ጋር ተቀራራቢነት አለው ። በአጠናን ዘዴ፣ በትኩረት አቅጣጫና በመጠነ ርዕይ ከዚህ ጥናት ልዩነት አለው ።**

**Navanita Das, Shulanki Pal, Spondan Sapon Bora** (2014). **“study of Traditional Houses in Assam” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል። ይህ ጥናት በሰሜን ምስራቅ ህንድ የባህላዊ ቤቶች የአሰራር ስልቶች ላይ የሚከሰቱ አደጋዎች ላይ ትኩረት ያደረገ ነው ። በጥናቱ ውጤትም በጥናት አካባቢው የሚሰሩ ባህላዊ ቤቶች የአሰራር ስልቶች ችግር ያለባቸውና ለአደጋዎች የሚያጋልጡ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን በአብዛኛው ለእንደዚህ አይነት አደጋ የሚጋለጡ ቤቶች የሚሰሩት ቀለል ካለ ሽምበቆ በመሆኑ**

እንደሆነ ተገልጿል። በአሳም የተለያዩ የቤት አይነቶች እንዳሉና ቤቶቹ ጥንታዊ ጥበብን ተከትለው በመሰራታቸው ዘመናዊ ግንባታን በአንድ ላይ እንደያዙ በጥናቱ ቀርቧል። በአሳም ላይ የቀረበው ጥናት ትንታኔዎች ተደራጅተው መቅረባቸው የጥናቱን ጠንካራ ጎን የሚያሳይ ሲሆን ዓላማ፣ጽንሰ ሀሳብና ንድፈ ሀሳብ ላይ ክፍተት ታይቶባቸዋል።

Sonam Chuki, Raju Sarkar and Ritesh Kurar. (2017). “A Review on Traditional Architecture Houses in Buddhist Culture” በሚል ርዕስ ለአሜሪካ ጆርናል ሲቪል ምህንድስና ጥናት አቅርበዋል ።

የዚህ ጥናት ዐቢይ ዓላማ የቡድሂስት ባህል ያላቸው ቡታን፣ ቻይና፣ ጃፓን፣ ላኦስ፣ ማያንማር፣ ኔፓል፣ ታይላንድ እና ቬትናም የተባሉት አገሮች ባህላዊ መኖሪያ ቤቶች የሕንፃ ገጽታቸው፤አሰራር፤ቅርጻቸውና የግንባታ ቁሳቁሳቸው ምን ምን እንደሆኑ ተንትኖ መግለጽ ነው ። በጥናቱ ውጤት የእነዚህ ሀገሮች ተወላጆች የህንጻ ገጽታዎች፣የቦታዎች አደረጃጀትና የግንባታ እቃዎች ጥቅም ላይ እንደዋሉ በጥናቱ ቀርቧል ። በባሕላዊ የቡታኒዝ ቤቶች ፊት ላይ ከሚታዩት ሥዕሎች አንስቶ እስከ የታይላንድ ፎቅ ድረስ ያሉት የቡድሂስት ሕዝቦች ባህላዊ እና ሐይማኖታዊ እምነቶች በሥነ ሕንፃው ውስጥ በከፍተኛ ሁኔታ የተንጸባረቁ መሆናቸው በጥናቱ ተገልጿል ።

ለጥናቱ የተመረጡት ሁሉም አገሮች በተወሰነ ደረጃ ተመሳሳይ በሆነ ሐይማኖት እና ባህል ምክንያት በባህላዊ መኖሪያቸው ውስጥ ተመሳሳይ የስነ-ህንፃ ባህሪያትን እንደ ከፍ ያለ ወለል ፣ ከፍ ያለ ጣሪያ የግንባታ ቁሳቁስ ምርጫ ፣ተንቀሳቃሽ ውጫዊ የእንጨት ደረጃዎች ፣ የአራት ማዕዘን ቅርጾች፣የሚጠቀሙ እንደሆነ ተገልጿል ።

በተጨማሪም የክልሉ የአየር ንብረት በባህላዊ መኖሪያ ቤቶች ባህሪያት ውስጥ ትልቅ ሚና እንደሚጫወት፤ እንዲሁም ደግሞ ተመሳሳይ ባህል እና ሐይማኖት ያላቸው ሀገሮች ጥቂት ተመሳሳይ የሥነ ህንጻ ባህሪያት እንዳላቸው፤ሃይማኖትና ባህል የአንድን ሀገር የሕንፃ ጥበብ በመቅረጽ በኩል ትልቅ ሚና እንዳላቸው በጥናቱ ተገልጿል። ትንታኔው በአግባቡ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን ሥነ ዘዴው በግልጽነት ያለመቅረቡ የጥናቱ ክፍተት ነው። ሁለቱም ጥናቶች ባህላዊ ቤት ላይ ማትኮራቸው ያመሳስላቸዋል።

V R Vitasurya, G Hardiman, S R Sari. (2018) “Transformation of traditional houses in the development of sustainable rural tourism, case study of Brayut Tourism Village in Yogyakarta” በሚል ርዕስ ለ4ኛው ዓለም አቀፍ የከተማ ልማት ፕሮግራም አቅርበዋል ። የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ የ Brayut መንደር ነዋሪዎች ባህላዊውን ቤት እንደ መኖሪያ ቤት ህልውና ለመጠበቅ የሚጠቀሙባቸውን የአካባቢውን እሴቶች ለማሳየት ያለመ ነው። የባህላዊ ቤቶች ለውጥ ከነዋሪዎች ፍላጎት ጋር በተያያዘ

ውስጣዊ  እና ውጫዊ ገጽታዎች ላይ በመንግስት ከክልላዊ ልማት ጋር በተያያዙ ተጽዕኖ እንደሚያሳድር በጥናቱ ተገልጿል ፡፡

ዘመናዊነት የአካባቢውን ነዋሪዎች ፍላጎት ስለሚነካ እና የመንግስት የልማት ፕሮግራም ለቱሪዝም መንደር የለውጥ ጥያቄዎች ላይ ተጽእኖ አሳድሯል፡፡ ሌላው Brayut ቱሪዝም መንደር በባህላዊ የቱሪዝም መስህብነት ላይ የተመሰረተ መንደር እንደሆነ በጥናቱ የተገለጸ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ ለውጡ በቱሪዝም ላይ የሚያሳድረው ተጽዕኖ ላይ ትኩረት እንዳደረገ በጥናቱ ተገልጿል፡፡ በተገኘው ውጤት መሰረት ሦስቱ የጃቫን ባህላዊ ቤቶች ለውጥና ዘመናዊነት ላይ ትኩረት ያደረጉ ናቸው፡፡

ትንታኔው ተደራጅቶ መቅረቡ የጥናቱ ጠንካራ ጎን ሲሆን በቦታና በጥናቱ መስክ ልዩነት  የታየባቸው ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በንድፈ ሀሳብ፣በጽንሰ ሀሳብና በትኩረት አቅጣጫ ሰፊ ልዩነት አለው ፡፡

Mazdak,Irani.(2014) “TraditionalHousinginSustainable Architecture” በሚል ርዕስ ጥናት አቅርበዋል፡፡ የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በኢራን ባህላዊ ቤቶች ከጂኦግራፊ እና ከአየር ንብረት ሁኔታዎች ጋር ግንኙነት እንዳላቸው የሚገልጽ ሆኖ ቤቶቹ የተገነቡት በኢራን ያሉ አራቱን የአየር ንብረቶች መሰረት አድርገው እንደሆነ የቀረበ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የቤቶቹ አሰራር ከኢኮኖሚያቸው ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚገልጽ ጥናት ነው፡፡ ሌላው በኢራን ውስጥ እንደ ሞቃታማ እና እርጥብ፣ ሙቅ እና ደረቅ ፣መለስተኛ ፣ እርጥብ እና ቅዝቃዜ ያሉ አራት የተለያዩ የአየር ንብረት ሁኔታዎች ከአየር ንብረት ጋር ተቀናጅተው የተለያዩ ሕንጻዎችን በተለይም በባህላዊ የመኖሪያ ቤቶች ዲዛይን እንዲቋቋሙ ምክንያት እንደሆነ በጥናቱ ተገልጿል:: ይህ ጥናት በባህላዊ ቤቶች ላይ ያተኮረ በመሆኑ ከዚህ ጥናት ተቀራራቢነት አለው፡፡ በጽንሰ ሀሳብ፣በቦታ፣በባህልና በትኩረት አቅጣጫ ከዚህ ጥናት ጋር ልዩነት አሳይቷል ፡፡

ከላይ ከተጠቀሱት መካከል በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ተጠንተው ለአማርኛ ቋንቋ ሥነ-ጽሁፍ እና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የቀረቡት ጥናቶች አራት ሲሆኑ ከእነዚህም መካከል ባህላዊ ቤትን ከእጅ ስራ ቁሶች ጋር በማድረግ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የተሰሩት ስራዎች ሁለት ናቸው ፡፡ እነዚህም የእጅ ስራ ቁሶችን ከቤት አሰራር ጋር የያዙ እና በመጥፋት ላይ ያሉ ሀገረሰባዊ ቤቶችና የእጅ ስራ ቁሶች የሚመለከቱ ሆነው ቀሪው አንዱ ደግሞ የባህላዊ ቤቶች የግንባታ ጥበብን በማየቱ የትኩረት አቅጣጫ ልዩነት አላቸው ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ከዚህ ጥናት ጋር የተጠኚ ማህበረሰብ ቦታ እና የመተንተኛ መንገድ ልዩነት አላቸው አራተኛው በአፋር ክልል የቤት አሰራር ሂደትና በሂደቱ የሚነገሩ ስነ ቃሎች ላይ ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ስራ ሲሆን ይህ ጥናት የአፋር ክልል የቤት አሰራር ሂደትና በሂደቱም የሚነገሩ ስነ

ቃሎች ምን እንደሚመስሉ የሚገልጽ ሲሆን ከእኔ ጥናት ጋር በቦታ፤በንድፈ ሀሳብ፤ጽንሰ ሀሳብ እና መሰል የምርምር ዕሳቤዎች የተለየ ነው ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ በውጭ ሀገር ባህላዊ ቤቶች ላይ የቀረቡት ጥናቶች የባህል፣የኢኮኖሚ ደረጃ፣የመስሪያ ግብአቶች፣የጥናት ዘዴዎች፣የንድፈ ሀሳቦች፣ጽንሰ ሀሳቦች፣የሥነ ዘዴዎችና የትኩረት አቅጣጫ ሰፊ ልዩነት አላቸው ፡፡

ከዚህ ቀጥሎ የሁለቱ ክለሳ ድርሳናት ማለትም የንድፈ-ሀሳባዊና የተዛማጅ ጥናቶች ያሳዩትን አበርክቶ ፤የተገኘው የእውቀት ክፍተት ፤ ክፍተቶቹን ለመሙላት የሚሆኑ የመፍትሄ ሀሳቦች ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡ ከላይ የተዳሰሱት ጥናቶች ተመርምረው ጥናቶቹ ያልመለሷቸው ወይም ትኩረት ያልሰጧቸው ጉዳዮች ምንድን ናቸው? ለሚለው የተገኙት ክፍተቶች የጥናቱ ትኩረት ናቸው ፡፡

በዚህ ጥናት የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች አበርክቶ የእውቀት ክፍተትና የክፍተቶቹ መፍትሔዎች ቀጥለው ቀርበዋል ፡፡ ይህ ጥናት የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት በሚል ርዕስ የቀረበ ሲሆን በዚህም ስር የቤት ምንነትና ውክልና፤የቤት አይነቶች፣አሰራር፣ውጫዊና ውስጣዊ ቅርጽ እንዲሁም ለውጥና ቀጣይነት በንድፈ ሀሳቦችና ሞዴሎች ተተንትኖ ቀርቧል ፡፡ የወላይታ ቤቶች አይነቶችና አሰራራቸው ኢኮኖሚ፣የአየር ንብረትና ማህበራዊ ደረጃ ላይ መሰረት አድርገው ይሰራሉ ፡፡ ቤቶቹ የተገነቡት የአየር ንብረቶች መሰረት አድርገው እንደሆነ የቀረበ ሲሆን ከዚህ ጋር ተያይዞ የቤቶቹ አሰራር ከኢኮኖሚያቸው ጋር የተያያዘ እንደሆነ የሚገልጽ ጥናት ነው ፡፡

የተዛማጅ ጥናቶች እና ንድፈ ሀሳቦች ለዚህ ጥናት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ ያደረጉ ሲሆን በተዛማጅ ጥናቶች የተለያዩ ሀገሮች የቤት አይነቶች፤ባህላዊ የቤት አሰራር እውቀት ፤የመስሪያ ግብአቶች፤ከቤቱ ጋር የተያያዙ ነገሮች ተምሳሌት ለዚህ ጥናት እገዛ አድርጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በውጭ ሀገር ባህላዊ ቤቶች ላይ የቀረቡት ጥናቶች የባህል፣የኢኮኖሚ ፣የመስሪያ ግብአቶች፣የጥናት ዘዴዎች፣የንድፈ ሀሳቦች፣ጽንሰ ሀሳቦች፣የሥነ ዘዴዎችና የትኩረት አቅጣጫ ሰፊ ቢኖራቸውም ለዚህ ጥናት አስተዋጽኦ አድርገዋል ፡፡ ሌላው በጥናቱ የቀረቡት ንድፈ ሀሳቦች ለትንተና አስተዋጽኦ አድርገዋል ፡፡

በተዛማጅ ጥናቶች እና ንድፈ ሀሳቦች ከተገኙት የእውቀት ክፍተቶች መካከል አነሳሽ ምክንያቶች ጽንሰ ሀሳቦችና ሥነ ዘዴዎች በአግባቡ ያለመቅረባቸው ይጠቀሳሉ ፡፡ ሌላው የተወሰኑት ባህላዊ ቤቶች በከፊል እየተለወጡ መሆናቸው፤ ከቤቱና ከአሰራሩ ጋር የተያያዙ ጥናቶች ዝርዝር አሰራራቸው ብቻ

መጠናቱ ፤ ሌላው እነዚህ ቤቶች በቅርብ ጊዜ ውስጥ የመጥፋት አደጋ እንደተጋረጠባቸው እንዲሁም ደግሞ ለእሳት አደጋ የመጋለጥ እድል እንዳላቸው  በጥናቱ ተብራርቷል ፡፡

ክፍተቶቹን ለመሙላት በሳይንሳዊ አጠናን መንገድ ተጠቅሞ መግለጽ፣መቅረስ፣መሰነድና ለብሔረሰቡ ጠቀሜታ የሚያበረክቱበትን መንገድ መጠቆም ሲሆን የአካባቢውን የግንባታ ባህል ቅርስ እንዴት መጠበቅ እንደሚቻል እና ለወደፊቱ ተፈላጊ የመኖሪያ አካባቢዎችን ቅርጽ እንዴት ማውጣት እንደሚቻል ግምት ውስጥ በማስገባት ይህን መሰረታዊ እውቀት እንደገና መገምገም ፡፡

ሌላው ህዝቡ ከራሱ መልክዓ ምድርና ባህል ጋር እንዴት ተቆራኝቶ እንደሚኖር እንዲሁም ደግሞ የኮንሶ ማህበረሰብ በህንፃ ጥበባቸው እንዴት አድርገው ሌሎችንም እምቅ ሀብቶችን ይዘው መኖራቸውን መረዳት ፋይዳው ላቅ ያለ ነው ፡፡ በተጨማሪም የኮንሶዎች የእርከን ሥራ  የአፈር መሸርሸርንና የለም አፈር መራቆትን ለመከላከል ብሎም የከርሰ-ምድር ውሃ ሀብት ለመያዝ በሚያደርጉት ምርምር-ተኮር የአኗኗር ስልት ደረቅ የሆነ የጎርፍ መከላከያ እርከን (terracing) ሥራ ጥበብ ባለቤት መሆናቸውን መገንዘብ ጥሩ ተሞክሮ ነው ፡፡ በተጨማሪ  የእርከን ስራዎችም የኮንሶ አርሶ-አደሮች ከእርሻ ስራ ጋር ምን ያህል እንደተቆራኙና ቀጣይነት ያለውን የአፈር ለምነት መከላከያ መንገዶች ምን ያህል በጥልቀት እንደተለማመዱ የሚያሳይ ነው ፡፡ ይህም ከላይ እንደቀረቡት መረጃዎች ጠቀሜታው የጎላ ነው ፡፡

በውጭ ሀገር ባህላዊ ቤቶች ላይ የቀረቡት ጥናቶች የባህል፣የኢኮኖሚ ደረጃ፣የመስሪያ ግብአቶች፣የጥናት ዘዴዎች፣የንድፈ ሀሳቦች፣ጽንሰ ሀሳቦች፣የሥነ ዘዴዎችና የትኩረት አቅጣጫ ሰፊ ልዩነት አላቸው ፡፡

በሀገር ውስጥ ባህላዊ ቤቶች ላይ ከቀረቡት ጥናቶች መካከል አብዛኛዎቹ ትኩረት ያደረጉት የቤቶቹን የአሰራር ሂደት መዘርዘር ላይ ነው ፡፡ ሌላው ቤቶቹን ከብሔረሰቡ ማንነት ጋር በማዛመድ ትእምርቱን ጠለቅ ብለው ያሳዩት እምብዛም አይደሉም ፡፡

➢ ከላይ በዝርዝር የተገለጹት የእውቀት ክፍተቶች ጠቅለል ሲደረጉ እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

- አብዛኞቹ ጥናቶች የኢትዮጵያን ባህላዊ ቤቶች በጠቅላላው ሲዳስሱ፣ በተለይ የወላይታ ብሔረሰብ ቤት አሰራር ያለውን ልዩ ሂደት፣ ምልክታዊ ትርጉም እና ከማህበራዊ ህይወት ጋር ያለውን መስተጋብር በጥልቀት አላጠኑም ፡፡

- የወላይታ ቤት አሰራር ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ የቆየው እውቀት በዘመናዊነት ተጽዕኖ እየተሸረሸረ መሆኑ ቢታወቅም፣ የዚህ እውቀት ስልታዊ ሰነዳ አልተሰራም ::
- የባህላዊው ቤት አሰራር አካባቢያዊና ኢኮኖሚያዊ ዘላቂነት ከዘመናዊ የሲሚንቶ ቤቶች ጋር ሲነጻጸር ያለውን ጠቀሜታ ያሳየ ጥናት የለም ።

የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ የብሔረሰቡ እርስ በርስ ማህበራዊ ግንኙነት፣  በቤቱ ስራ ወቅት የሴትና የወንድ ሚናን፤ለውጥና ቀጣይነትን የምሰሶና ጾታን ግንኙነት ለመተንተን ተግባራዊ ሆኗል ። የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ ከውስጥም ሆነ ከውጭ የሚታዩ ምልክቶች፣ ፎቶዎች፣ ስዕሎች፣የቤቱ ቅርጽ፤ ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታው፤ የቤቱ መጠን፤ የመስሪያ ግብአቶች  በማህበረሰቡ የሚሰጣቸው ትርጓሜዎች ከዚህ በተጨማሪ ከቤቱ ጋር ተያይዘው የቀረቡ ምሳሌያዊ ንግግሮች፣ባህላዊ ዘፈኖች እንዲሁም ደግሞ ከቤቱ ስራ ጋር ተያይዘው የሚከወኑ ሀገረሰባዊ ልማዶች፣ባህላዊ ምግቦችና መጠጦች ትርጓሜ ተሰጥቷቸው ተተንትነዋል ። በተጨማሪ ግለሰቦች (ማህበረሰቦች) የቤት አሰራር እውቀቱን እንዴት አዳበሩት? የአሰራር እውቀቱ ቡድናዊ(ማህበራዊ) ስልትን ይከተላል?በቤት ስራው ውስጥ ማህበረሰቡ እርስ በርስ ያለው ግንኙነት ምን ይመስላል? ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ተሰጥቷል።

- **የንድፈ ሀሳብና የተዛማጅ ጥናቶች አበርክቶ፤የእውቀት ክፍተትና የክፍተቶቹ መፍትሔዎች**




**ምንጭ፦ በአጥኚዋ የተዘጋጀ ህዳር 2017 ዓ.ም**


ንድፈ ሀሳቦች




ምንጭ፡- በአጥኚዋ የተዘጋጀ ህዳር 2017 ዓ.ም

# ምዕራፍ ሦስት

# ጥናቱ ሥነ ዘዴ

በዚህ ምዕራፍ ስር የጥናቱ ዓይነት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ምንጮች ፣የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች፣ የናሙና አመራረጥ ስልት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ አንፃር፣ የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴል፣ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

## 3.1. የጥናቱ ዓይነት

ይህ ጥናት አይነታዊ (qualitative) የምርምር ዘዴን ተከትሏል፡፡ ይህ የምርምር ስልት፣ ተመራማሪው በተሳታፊዎች ተፈጥሯዊ መቼት ውስጥ በመገኘት መረጃዎችን የሚሰበስብበት፣ ከዝርዝር መረጃዎች በመነሳት አጠቃላይ ጭብጦችን የሚገነባበትና ትርጓሜ የሚሰጥበት አካሄድ ነው (Creswell, 2007) ፡፡ እንደ Dawson (2009) ገለጻም፣ "አይነታዊ ምርምር ማህበራዊ ክስተቶችን በጥልቀት ለመመርመር፣ ለመረዳት እና ለመተርጎም የሚረዳ ነው" (p. 16) ፡፡

በዚህ ጥናት አይነታዊ የምርምር ዘዴ ተግባራዊ የሆነው ዓይነታዊ የምርምር ዘዴ ባህሪን፣ አመለካከትን ልምድን የሚመረምር በመሆኑና ምን? የት? መቼ? ብቻ ሳይሆን ለምንና እንዴት? የሚሉ ጥያቄዎችን ስለሚያካትት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በማህበረሰቡ እውቀት፣ አመለካከትና አስተሳሰብ ላይ ስለሚያጠነጥን ቤቶቹ እንዴት እንደሚሰሩ የአሰራር ልምዳቸው ሁሉ በዚህ ስልት መሰረት ተገልጿል፤ተተርጉሟል፤ ተተንትኗል ፡፡

በዚህ ጥናት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ጥልቅ ቃለ መጠይቅ፣ተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ፣የመስክ ማስታዎሻዎች እና ቡድን ተኮር ውይይት ተግባር ላይ ውለዋል ፡፡

አይነታዊ ምርምር ልምድን መሰረት ስለሚያደርግ የኢትኖግራፊክ የአጠናን ስልትን ተከትሏል ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በብሔረሰቡ ላይ ያተኮረ በመሆኑ ሲሆን ይህንንም ልምድ ለማግኘት በተደጋጋሚ ወደ መስክ በመሄድ እና ከብሔረሰቡ ጋር በቦታው ለተወሰኑ ወራት(ዓመት) በመቆየት መረጃዎች የተሰበሰቡ በመሆናቸው እንዲሁም የብሔረሰቡን አመለካከት፣ልምድ እና ከባህሉ ጋር የተገናኙ አስተሳሰቦች ስለሚገለጹ ሲሆን ይህ ጥናት ከላይ በተገለጸው መንገድ ተጠንቶ ቀርቧል ፡፡

### 3.2. የመረጃ ምንጮች እና የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

በዚህ ርዕስ ስር ለጥናቱ ጥያቄዎች መመለስ የሚበጁ መረጃዎች የሚገኙባቸው ምንጮች ምንነት፣ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን እና የመረጃ አቀባዮችን መምረጫ የናሙና ዘዴዎች እንዲሁም የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተካተዋል ፡፡

ለዚህ ጥናት አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከካልአይ እና ከቀዳማይ ምንጮች ተሰብስበዋል ፡፡ በመረጃ አሰባሰብ ሂደትም በቅድመ መስክ ወቅት ጥናቱ ስለሚጠናበት ቦታና ብሔረሰብ እንዲሁም ስለሚጠናው ጉዳይ አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከማዕከላዊ እስታትስቲክስ ቢሮዎች እና ከደን ጥበቃ ቢሮዎች ተሰብስበዋል ፡፡ ከመስክ መረጃዎች በምልከታ፣ በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት በሶስት መንገድ ይሰበሰባሉ (ፈቃደ 1991፣ ገ.90) ፤ (Goldstine, 1964, P. 77) በዚህ ጥናትም በዋናነት ከላይ የተጠቀሱት ሶስቱ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተግባራዊ ተደርገዋል ፡፡

#### 3.2.1. ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች

ቀዳማይ ምንጮች የሚባሉት ከዚህ በፊት ያልታተሙ ወይም ያልተተነተኑ የመጀመሪያ ደረጃ ምንጮች ናቸው ፡፡ ይህ የመረጃ ቅርጽ በምልከታ፣ በልምድ እና መስክን መሰረት በማድረግ እውነታን ለማግኘት የሚሰበሰብ ነው (Walliman, 2006 , P.84) ለጥናቱ በመረጃ ሰጪነት የተመረጡ ግለሰቦች እና ቡድኖች፣ የተለያዩ አውዶች፣ ሁነቶች፣የእምነት ሥርዓቶችና ክዋኔዎች ዋነኛ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ናቸው ፡፡

የዚህ ጥናት ቀዳማይ የመረጃ ምንጭ መስክ በመሆኑ ወደ ተጠኘው አካባቢ በመሄድ ከመስክ መረጃዎች በዋናነት በቃለመጠይቅ፣በምልከታና በቡድን ተኮር ውይይት መንገድ ተሰብስበዋል ፡፡ ለጥናቱ በመረጃ ሰጪነት የተመረጡ ግለሰቦች እና ቡድኖች፣ የተለያዩ አውዶች፣ ሁነቶች፣ የእምነት ሥርዓቶችና ክዋኔዎች ዋነኛ ቀዳማይ የመረጃ ምንጮች ሆነው መረጃዎች ተሰብስበውና ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

#### 3.2.2. ካልዓይ የመረጃ ምንጮች

ካልዓይ የመረጃ ምንጮች የሚባሉት ከቤተ መጻህፍት፣ከአርካይቭ፣ ከሙዚየም፣ከመዛግብት ታዋቂና ታማኝ ድረ ገፆች የሚሰበሰቡ መረጃዎች ናቸው ፡፡ ይህ ጥናት ካልዓይ የመረጃ ምንጮችን መሰረት በማድረግ ጽንሰ ሀሳቦች፣ንድፈ ሀሳቦችና ሥነ ዘዴዎች የሚገኙበት ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ ስለሚጠናው ብሔረሰብ አጠቃላይ መረጃ መልክአምድራዊ ሁኔታ፤ስለቦታው ስያሜ፤መተዳደሪያ

ኢኮኖሚ፤ስለ ህዝቡ ቁጥር፤ ስለ አየር ንብረት፤ስለቱሪስት መስህቦች፤ ስለህዝቡ እምነት፤ መሰል እና ተያያዥ ጉዳዮች ከላይ በተጠቀሱት ዘዴዎች ተሰብስበው ቀርበዋል ፡፡ ሌላው ቀደም ሲል በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ የተጠኑ ጥናቶችና ሌሎች አስፈላጊ የሆኑ መረጃዎች ከካልዓይ የመረጃ ምንጮች ተሰብስበው ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

### 3.3. የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች

ሁሉም የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎች የራሳቸው የሆነ ጠንካራ እና ደካማ ጎኖች አላቸው ፡፡ ስለሆነም ታማኝና ትክክለኛ መረጃዎችን ለማግኘት ለጥናቱ አዋጭ የሆኑ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን ተጠቅሞ ምርምሩን ማከናወን ተመራጭ ዘዴ ነው ፡፡ ለዚህም ወሳኙ የተለያዩ ዘዴዎችን እያሰባጠሩ መጠቀም የተሻለ መንገድ ነው ፡፡ ይህ ጥናትም ከላይ የተጠቀሱትን መንገዶች መሰረት አድርጎ ተከናውኗል ፡፡ ጥናቱም በመስክ ላይ ትኩረት የሚያደርግ በመሆኑ በዋናነት መረጃዎች በምልከታ፣በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ተኮር ውይይት መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበውና ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

#### I, ምልከታ

በፎክሎር ጥናት ምልከታ አንድን ጉዳይ፣ ድርጊት፣ ክዋኔ (ሁነት) በአካል ተገኝቶ በሁሉም የስሜት ሕዋሳት አማካይነት ተረድቶ መረጃ መሰብሰብ ማለት ነው ፡፡ በመሆኑም ‹‹ምልከታ አንድን ድርጊት ማየት ብቻ ሳይሆን “መቅመስ፣ መዳሰስ፣ መስማትና ማሽተትን ሁሉ ይጨምራል›› (Goldstein, 1964, P. 77) ፡፡ ምልከታ እንደሚጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዓይነት በጊዜ ሊወሰን የሚችል ቢሆንም እንኳን አጥኚው ለሚካሄደው ጥናት የሚያስፈልገውን መረጃ በአካል ተገኝቶ ከአውዱ በአምስቱም የስሜት ህዋሳት አማካይነት በትኩረት ለመሰብሰብ የሚያስችል የመረጃ ማሰባሰቢያ ዘዴ ነው (Dawsen, 2009, P.90) ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ያለው “የምልከታ ዘዴ መረጃ ሰብሳቢው ሰው መረጃ ለመሰብሰብ ከሚፈልግባቸው ተጠኝዎች ጋር ወይም አካባቢ በመሆን የሚያደርጉትንና የሚናገሩትን ነገር በቅርበት ሆኖ እያየና እየሰማ በመመዝገብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ነው” (2004፣ ገ.182-183) በማለት ገልጸውታል ፡፡

አንድ የፎክሎር አጥኚ በምልከታ ከመስክ መረጃ በሚሰበስብበት ጊዜ እንደ ርዕሰ ጉዳዩ ባህርይ በሁለት ዓይነት መንገድ ማለትም በተሳትፏዊና ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ መሰብሰብ ይችላል (Kothari, 1990, P. 96) ፡፡

**ተሳትፏዊ ምልከታ ፡-** ተሳትፏዊ ምልከታ አጥኚው ክዋኔውን ከከዋኞቹ ጋር አብሮ እየከወነ መረጃ የሚሰበስብበት የመረጃ አሰባሰብ ስልት ነው ፡፡ ይህ አጥኚ በተሳትፏዊ ምልከታ መረጃ ለመሰብሰብ ሶስት መሰረታዊ ጉዳዮችን ማለትም መረጃው የሚገኝበትን ቦታ መምረጥን፣ በክዋኔው የሚሳተፍበትን አጋጣሚ መፍጠርና የምርምር ስነምግባሮችን መከተልን መዘንጋት እንደሌለበት (Dawsen, 2009, p.105-109) ይገልጻሉ ፡፡

**ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ ፡-** ኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ አጥኚው ክዋኔው በሚቀርብበት ጊዜ ከዳር ሆኖ መረጃ የሚሰበስብበት መንገድ ነው ፡፡ በዚህን ጊዜ አጥኚው ማስታወሻ በመያዝ የተለያዩ መቅረጸ ድምጾችን በመጠቀም ከተጠኚው ማህበረሰብ የሚፈልገውን መረጃ መሰብሰብ ይችላል ፡፡

በዚህ ጥናትም እንደአስፈላጊነቱ ሁለቱን የምልከታ መንገዶች መነሻ በማድረግ መረጃዎች ተሰብስበዋል

በኢ-ተሳትፏዊ ምልከታ የቤቱ አገነባብ ሂደት፣የቤት አይነቶችና የአሰራራቸው አጀማመርና አጨራረስ ሂደት በአሠራሩ ሂደት የመለያ ባህርያቶቻቸው የተሳታፊዎቹ ሚና፣የመሥሪያ ቁሳቁሶች፣ቴክኒኮች፣ የውስጥ አከፋፈልና መሥፈርት ፣የተገነቡ ቤቶች አገልግሎት፣የቤቱ አከፋፈል ምህንድስናና አቢይ አገልግሎታቸው፣ማህበራዊ ፋይዳ፣ባህላዊና ኢኮኖሚያዊ ፋይዳዎችን የሚመለከቱ መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡

ሌላው ከቤቱ አሰራር ጋር በተገናኘ የሚቀርቡ ዘፈኖች፣ጭፈራዎች፣ ልማዶች፣እምነቶች፣ እንዲሁም የባህል ምግቦችና መጠጦች በተሳትፏዊ ምልከታ የተሰበሰቡ ሲሆን ይህም ከሚያዝያ 16/2014 እስከ ጳጉሜ አራት 2016 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ በሦስት ዙር ተከፋፍሎ ተካሂዷል ፡፡ ባህላዊ ቤቱ እየተሰራ ባለው ኦፋ ወረዳ አምስት ዙር ምልከታ የተደረገ ሲሆን በወላይታ ዩኒቨርሲቲ የሚገኘው ባህላዊ ቤት በምሰራበት ተቋም ውስጥ መሆኑና ቅርብ ቦታ ላይ መገኘቱ ከሌሎች የበለጠ ስምንት ጊዜ የመመልከት እድል ተመቻችቶልኛል ፡፡ እንዲሁም ካዎ ኮይሻ ወረዳ የሚገኘው ባህላዊ ቤት በሁለት ዙር ምልከታ ተደርጓል ፡፡

### II, ቃለ መጠይቅ

‹‹ቃለ መጠይቅ በቃል የሚደረግ ሆኖ በመላሹና ቃለ መጠይቅ በሚያካሂደው ሰው መካከል የፊት ለፊት የቃላት ምልልስ ያለበት ነው፡፡ በዚህም ጠያቂው ይጠይቃል፤ ተጠያቂው ደግሞ ያብራራል ፡፡ ቃለ መጠይቅ ፊት ለፊት ብቻ ሳይሆን በስልክ መልእክትም ይደረጋል›› (ያለው፣ 2009፣ገ.181፤ Kothari, 1990, P. 97) ፡፡

ቃለመጠይቅ ተመራማሪው ለመረጃ አቀባዮቹ በቃል ጥያቄ በማቅረብ መረጃ የሚሰበስብበት ዘዴ ሲሆን ዘዴው የራሱ የሆነ ጠንካራና ደካማ ጎኖች አሉት፡፡ ከጠንካራ ጎኖቹ መካከል አንዱ ቃለመጠይቅ በምልከታ ሊገኙ የማይችሉ መረጃዎችን ማስገኘት ማስቻሉ ነው (Creswell, 2014) ለምሳሌ ከጊዜ አንፃር ወደ ኋላ በመመለስ ታሪካዊ ሁነቶችና ስርዓቶችን የሚመለከቱ መረጃዎች ማግኘት የሚቻለው በቃለ መጠይቅ አማካኝነት ከሚሰበሰቡ መረጃዎች ነው ፡፡

ከቦታ አንፃርም በአካል መገኘት ሳያስፈልግ ተገቢውን ጥንቃቄ በማድረግ አንድን ድርጊት ጠይቆ መረዳት ይቻላል፡፡ እንዲሁም በአይን መታየት፣ በእጅ መዳሰስ የማይችሉ ረቂቅ ጉዳዮች፣ ትዕምርታዊና ተምሳሌታዊ ሁነቶች፣ ትርጓሜያቸው ተተንትኖ ሊብራራ የሚችለው በባህሉ ባለቤቶች አማካኝነት ሲሆን በሌላ በኩል ግን በቃለ መጠይቅ ዘዴ ሊሸፈኑ የማይችሉ ክፍተቶች ሊያጋጥሙ ይችላሉ፡፡ ከክፍተቶቹ አንዱ በቃለ መጠይቅ ዘዴ መረጃ ከተፈጥሯዊ አውዱ ውጭ እንዲሰበሰብ መፍቀዱ ነው፡፡ በዚህም መረጃ አቀባዩም ሆነ ተመራማሪው መረጃዎችን የሚረዱት ከራሳቸው ፍላጎትና ስሜት አንፃር ብቻ የሚሆንበት አጋጣሚ ይፈጠራል ፡፡ በመሆኑም ሌሎች እውነተኛ መረጃዎች ተደብቀው በምትኩ የተሳሳቱ መረጃዎች ሊሰበሰቡ ይችላሉ (ያለው፣2009) ፡፡

በዚህ ጥናት የቃለ መጠይቁ ተሳታፊዎች ያታቸውን፣ ዕድሜያቸውን፣ የሚኖሩበትን አካባቢ ተጨባጭ ሁኔታ (ከተማና ገጠርነት፣ ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸውን፣ ወዘተ መሰረት በማድረግ ተመርጠው መሳተፍ ያለባቸው የምህንድስናው ዕውቀት ባለቤቶች/ባለሙያዎች (እንዴት ያቅዳሉ?መቼ ይሰራሉ?የዕውቀቱ ተስተላልፎ ምን ይመስላል?የቤቱ አሰሪዎች/ተጠቃሚዎች፣እቅድ፣ዲዛይን፣በግንባታ ሂደቱ ያላቸው ድርሻ፣በቤቱ የውስጥ አከፋፈልና ምክንያት የሚሉ ታሳቢ ተደርገው ተከናውነዋል ፡፡ በዚህ ጥናት ከዚህ በላይ የተጠቀሱትን መሠረታዊ ጽንሰ ሀሳቦች ታሳቢ በማድረግ ከቃለመጠይቅ ዓይነቶች፤ ውስን ቃለመጠይቅ (Structured interview)፡ ከፊል ነፃ ቃለመጠይቅ (Semi-structured Interview) እና ነፃ ቃለመጠይቅ (Unstructured Interview) ይዘቶች ቀርበው የመስክ መረጃዎች ተሰብስበው ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡ እነዚህን፣እንደ አስፈላጊነታቸው እያፈራረቁ መጠቀም ጠቀሜታ አለው (ያለው፣2004፣ገ.183-184) ፡፡ እነዚህም ለዚህ ጥናት ግብዓት የሚሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ተግባራዊ ተደርገዋል ፡፡

በጥናቱ ሂደትም ከሠላሳ (30) በዕድሜ የገፉ ወንዶች፣ ከሃያ (20) በዕድሜ የገፉ ሴቶች እና ከሃያ (20) ወጣቶችና በመካከለኛ እድሜ ላይ ከሚገኙ በድምሩ ከሰባ (70) ሰዎች መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡ በአጠቃላይ ከሠላሳ ቁልፍ እና ከአርባ አጋዥ መረጃ አቀባዮች ተሰብስበዋል ፡፡

## III, ቡድን ተኮር ውይይት

‹‹ቡድን ተኮር ውይይት የአይነታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ስልት ሲሆን የቡድን ውይይት አቀማመጥ ያለው፤ በተወሰኑ ጉዳዮች የሚወያዩ ከ6-12 የሚደርሱ ተሳታፊዎችን የያዘ ውይይት ነው›› (Neuman, 2007, p. 338-339) ይላሉ ፡፡ ሌላኛው ብያኔ በያለው እንዳወቀ (2009፣ገ.191) የቀረበ ሲሆን ‹‹ቡድን ተኮር ውይይት በችግሩ ዙሪያ በቂ መረጃ ይኖራቸዋል ተብሎ የሚታሰቡ ሰዎችን በመውሰድ በሚነሳው ጥያቄ ዙሪያ በቡድን ተወያይተው ምላሽ እንዲሰጡ የሚደረግበት ዘዴ ነው ፡፡ ተሳታፊዎቹም እስከ 12 ሊደርሱ ይችላሉ ፡፡ ይህ ዘዴ የቡድን ቃለ መጠይቅ ነው ማለት ይቻላል ነገርግን ከቃለመጠይቅ የሚለየው በርካታ ሰዎችን በአንድ ጊዜ ማሳተፍ መቻሉ ነው›› በማለት ገልጸዋል ፡፡

አቀራረቡ በአጠቃላይ ቡድን ተኮር ውይይት አንድ የጋራ ጉዳይ ያላቸው የተወሰኑ ሰዎች በጠያቂው (አወያዩ) ምክንያት ተገናኝተው በምርምሩ ርእሰ ጉዳይ ስር በሚነሱ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አድርገው ከግላዊ ልምዳቸው አንጻር ሃሳብ የሚያቀርቡበት ዘዴ ሲሆን በተተኳሪ ጉዳዩ ዙሪያ ያላቸውን አስተያየት፣ አቋም እና አመለካከት ለመረዳት የሚያስችል ዘዴ ነው ፡፡

እንደ Neuman (2007, P. 338-339፤ያለው፣2009፣ገ.191) ገለጻ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴዎች ማግኘት ያልቻልነውን መረጃዎች በተለያየ መንገድ ለመግለጽ እንዲሁም በምልከታና በቃለ መጠይቅ ያገኘነውን መረጃዎች ተዓማኒነት ለማረጋገጥ፤ ቡድን ተኮር ውይይት ተግባር ላይ ይውላል ፡፡ ቡድን ተኮር ውይይት የዓይነታዊ መረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ ሆኖ በተወሰኑ ጉዳዮች የሚወያዩ ከ6-12 የሚደርሱ ተሳታፊዎችን የያዘ ውይይት ነው ፡፡

የቡድን ተኮር ውይይት የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴ በምልከታና በቃለ መጠይቅ ዘዴዎች ለማግኘት አዳጋች የሆኑ መረጃዎችን ለመሰብሰብ እንዲሁም ደግሞ በሁለቱ የተገኘውን መረጃ ተዓማኒነት ለማረጋገጥ በዚህ ጥናት ተግባራዊ ሆኗል ፡፡ በጥናቱም በሁለት ቡድኖች የመስክ ውይይት ተካሂዷል በቡድኑ ውስጥ ከአምስት እስከ ሰባት የሚደርሱ አባላት የተሳተፉ ሲሆን ቡድን አንድ በኪንዶ ዲዳዬ፤ቡድን ሁለት ሶዶ ዙሪያ ውስጥ በሚገኙ በባህላዊ ቤት ስራ ውስጥ የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው ባለሙያዎች፣በሳር ቤቱ ውስጥ የሚኖሩ አባቶች፣ቤቱ ሲሰራ የተለያየ የስራ ድርሻ ያላቸው እናቶች ፣ወጣት ሴቶችና ወንዶች ጋር ውይይት ተካሂዷል ፡፡

## IV, ንጥል ጥናት

የንጥል ጥናት (Case study) ጥልቅ መረጃን ለመዳሰስ የሚያገለግል የዓይነታዊ ዘዴ አይነት ሲሆን በእውነተኛ ህይወት አውድ ውስጥ ያሉ ውስብስብ ጉዳዮችን ተንትኖ ያስረዳል (Thomas, 2011)፡፡ የንጥል ጥናት በእውነተኛ ህይወት ውስጥ ያሉ ክስተቶችን እንድንገነዘብ የሚረዳን የምርምር ስትራቴጂ ሲሆን ስልቱም በተለያዩ ዘርፎች ማለትም በስነ-ልቦና፣ በሶሺዮሎጂ፣ በፖለቲካል ሳይንስ እና በማህበራዊ ሳይንስ ውስጥ የተለመደ ነው (Yin, 2003)። የሚጠናው ጉዳይ በተፈጥሮ ያሉ የመረጃ ምንጮችን እንደ ሰዎች እና በጉዳዩ ወሰን ውስጥ በሰዎች መካከል ያለውን መስተጋብር ስለሚጠቀም በጣም አስፈላጊ የምርምር ስትራቴጂ ነው (Hyett, Kenny & Dickson-Swift, 2014)፡፡

ሌላው ንጥል ጥናት የሚባለው አንድን ሰው፣ቡድን፣ማህበረሰብ ወይም ተቋም ከሌሎች ነጥሎ በመውሰድ በጥልቀት ከተለያዩ መስፈርቶች አንጻር ለማጥናት የሚያስችል የምርምር የንድፍ አይነት ነው ። ተመራማሪው በርካታ የመረጃ መሰብሰቢያ ዘዴዎችን አቀናጅቶ ለመጠቀም ይችላል ። መረጃዎቹንም ጥናቱ ከሚካሄድበት ሰው፤ቡድን፤ማህበረሰብ ወይም ተቋም በተጨማሪ ከሌሎች ሰዎች፣ቡድኖች፣ማህበረሰቦች ወይም ተቋማት ለመሰብሰብና ቀደም ሲል ከጥናቱ ተሳታፊ ያገኘውን መረጃ በበለጠ ሊያዳብርበት፤ሊያስተያይበት ሊያወዳድርበትና እውነተኛነቱን ሊያረጋግጥበት ይችላል ንጥል ጥናትን በአብዛኛው የሚጠቀሙት ዓይነታዊ ምርምር ዘዴን ተግባራዊ የሚያደርጉ ምሁራን ናቸው ። በዚህ የምርምር ንድፍ የሚገኘው መረጃ ዓይነታዊ ሲሆን የሚጠናውን ነገር እንዳለ በተፈጥሯዊ  መልኩ በስፋትና በጥልቀት ያቀርበዋል (ያለው፣2006) ።

በንጥል ጥናት (Case study) ሂደት ውስን ርዕሰ ጉዳይን ለይቶ እና ግለሰብን መርጦ ከተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች አንፃር በጥልቀትና በዝርዝር ለማጥናት ተገቢና አመቺ ስልት እንደሆነ (Blaxter, Hughes and Tight, 2006, 71-72)፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ የሚታወቁ አራት ዓይነት ባህላዊ የቤት አይነቶች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም ዙፋ፣ጉላንታ፣  ሜሹዋ እና ቡራሪያ ናቸው ። ከእነዚህ ውስጥ ለንጥል ጥናት የተመረጠው የጉላንታ ቤት ሲሆን ይህም በሶዶ ዙሪያ፣ኦፋና ኪንዶ ዲዳዬና ካዎ ኮይሻ በሚባሉ ወረዳዎች ውስጥ በሚገኙ ቤቱ የሚገኝባቸውን ቀበሌዎች መሰረት አድርጎ ተከናውኗል ።

### 3.3.1. የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሮች እና መቼቶች

በዚህ ርዕስ ስር የመረጃ መሰብሰቢያ አንጻሮች እና የመረጃ መሰብሰቢያ መቼቶች ቀጥሎ ቀርበዋል ። ውስጣዊ እይታ (emic perspective) ስለ ባህሉ ከባህሉ ባለቤቶች አንጻር ከሚሰጠው ትርጉም አንፃር እና ከውጫዊ አንጻር (etic perspective) የባህሉ ባለቤት ባልሆነው አጥኚ (ሠው) በሚሰጥ ትርጉም አማካይነት የሚከናወኑ ናቸው (Schoemaker, 1990) ፡፡ በዚህ ጥናት ውስጣዊ እይታ አንጻር ተግባራዊ የሆነው ከባህሉ ባለቤት የባህላዊ ቤት አሰራርን የሚመለከቱ በተጠኚው ብሔረሰብ እውቀት፣እምነትና አመለካከት መሰረት ተጠንቶ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን ከውጫዊ እይታ አንጻር ደግሞ ሳይንሳዊ የምርምር ዘዴዎችን በመከተል የብሔረሰቡን ዕውቀትና ጥበብ ሰብስቦ፣በይዘታቸው መድቦ በማደራጀት በጽንሰ ሀሳቦችና ንድፈ ሀሳቦች በማስተሳሰር ከርዕሰ ጉዳዩ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የተለያዩ ድርጊቶችንና ክዋኔዎችን በመተርጎም በሁለት የመረጃ  አንጻሮች ተተንትኖ ቀርቧል ።

‹‹የመረጃ መሰብሰቢያ መንገዶች ሶስት ሲሆኑ እነሱም ተፈጥሯዊ መቼት፣ ቅንብር ተፈጥሯዊ መቼት እና አርቴፊሻል (ሰው ሰራሽ) መቼት ይባላሉ›› (ፈቃደ፣1991፣ገ.122-123) ። በዚህ ጥናት ከሶስቱ መቼቶች ሁለቱ ተፈጥሯዊ መቼት እና አርቴፊሻል (ሰው ሰራሽ) መቼት ተግባራዊ ተደርገው መረጃዎች ተሰብስበዋል ። በተፈጥሯዊ መቼት ቤቱ ሲሰራ በመመልከት መረጃዎች የተሰበሰቡ ሲሆን በአርቴፊሻል መቼት ደግሞ ቀደም ሲል ቤቱ ሲሰራ ይነገሩ የነበሩ እና ዛሬ ላይ የሌሉትን ስነቃሎች በማስታወስ  መረጃ ለመሰብሰብ ተግባር ላይ ውሏል ። ከዚህ በተጨማሪ ከቤቱ ስራ ጋር ተያይዘው ቀደም ሲል የነበሩ ክዋኔዎች አሁን ግን በተለያዩ ምክንያቶች የማይከወኑትን በሚመለከት ከአውዱ ውጭ ሆኖ በመሰብሰብ ተግባራዊ ተደርጓል ።

### 3.3.2. የተጠኚ አካባቢዎች እና የተጠኚዎች የናሙና አመራረጥ

በዚህ ጥናት በዋናነት ዓላማ ተኮር ናሙና (Purposive sampling) እና ጠቋሚ ናሙና (Snow ball sampling) የተባሉት ጥቅም ላይ የዋሉ ሲሆን እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ።

በዚህ ጥናት ዓላማ ተኮር ናሙና (Purposive sampling) የመረጃ ሰጪዎችን የቀደመ ዕውቀትን መሰረት በማድረግ ለባህሉ ካላቸው ቀረቤታና በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ ያላቸው ዕውቀትና ልምዳቸው ግንዛቤ ውስጥ ገብቶ እነማን የሚፈለገው መረጃ ኖሯቸው ሊሰጡኝ ይችላሉ? የሚሉትን ጥያቄዎች መነሻ በማድረግ መረጃ ሰጪዎች የተመረጡ ሲሆን በዚህም በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ ልምድና ዕውቀት ያላቸውን መረጃ አቀባዮች በመምረጥ ተግባራዊ ሆኗል ። ሌላው ጠቋሚ ናሙና (Snowball/sampling) በሚባለው ደግሞ መረጃ ሰጪዎችን (ተጠኚዎችን) በጥቆማ የምናገኝበት የንሞና

ስልት በመሆኑ በጠቋሚ ንሞና ተመራማሪው በሚያጠናው ርዕሰ ጉዳይ ዙሪያ ዕውቀት ያለውን አንድ ሰው በማግኘት የተወሰነ መረጃ ተሰብስቧል ፡፡ በተጨማሪም እንደሱ በሚያጠናው ርዕስ ዙሪያ ተጨማሪ መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ ሌሎች ሰዎች ካሉ በመጠየቅ፤በጥቆማው መሰረት ሌሎች መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን በማግኘት መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡ በዚህም መሰረት ከባህላዊ ቤት አሰራር ጋር በተያያዘ ለጥናቱ መረጃ ሊያቀብሉ የሚችሉ አካላት እነማን ናቸው? የሚለውን ከተሳታፊዎች በሚገኝ ጥቆማ ዘዴ በመጠቀም መረጃዎች ተሰብስበዋል ፡፡ በዚህ ጥናት የመስክ መረጃዎች እድሜያቸው ከ30-85 የእድሜ ክልል ውስጥ የሚገኙ ሰዎች በመረጃ ሰጪነት ተሳትፈዋል ፡፡

በጥናቱ ሂደትም ሰላሳ (30) በዕድሜ የገፉ ወንዶች፤ሃያ (20) በዕድሜ የገፉ ሴቶች እና ሃያ 20) ወጣቶችና በመካከለኛ እድሜ ላይ የሚገኙ በድምሩ ሰባ (70) ሰዎች በመረጃ ሰጪነት ተመርጠው ተሳትፈዋል ፡፡ የሴቶቹ ቁጥር ከወንዶቹ ቁጥር ዝቅ ያለበትን ምክንያት በቅድመ መስክ ባገኘሁት መረጃ መሰረት በባህሉ ቤት የሚሰሩት ወንዶች ሲሆኑ ሴቶቹ ቤት ሲሰራ ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው በማቅረብ የተለያዩ ዕገዛዎችን ያደርጋሉ ፡፡ ሌላው በጥናቱ በዕድሜ የገፉ ሰዎች የተመረጡበት ምክንያት ከልምድ አንጻር የተሻለ ዕውቀት፣ልምድ እና ተአማኒነት ያለው መረጃ ይሰጣሉ ተብሎ ስለታመነበት ነው ፡፡

### 3.3.3. የመረጃ አደረጃጀት

በቃለ መጠይቅ በድምጽ የተገኙ መረጃዎች ወደ ጽሁፍ ተገልብጠዋል ፡፡ ጽሁፉ ደግሞ መረጃ ከተሰበሰበበት ወላይትኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ ተቀይሯል ፡፡

#### I) ትራንስክሪፕሽን

The two primary transcription styles are verbatim and non-verbatim, and each of these approaches may be appropriate within different contexts. Verbatim transcripts convey a word-for-word account of audio or video files. Instead, these transcripts include every audio element from the original recording. They're also the only option for certain use cases, such as deposition transcripts, where it's necessary to have a complete, accurate record (Lawrence, 1995) ሁለት አይነት ትራንስክሪፕሽን ዘዴዎች ያሉ ሲሆን በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆነው ቃል በቃል (verbatim) የተባለው ሲሆን በዚህም ከመስክ በመቅረጸ ድምፅ በቃል የተቀዱት መረጃዎች ከመተርጎማቸው በፊት ወደ ጽሁፍ ተቀይረዋል ፡፡ ይህም በድምጽ የተገለጹት መረጃዎች መልእክታቸው በትክክል እንዲተላለፍ በጥንቃቄ ደጋግሞ በማዳመጥ ቃል በቃል ለመግለጽ ጥረት ተደርጓል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በቤቱ ስራ ወቅት ከምሰሶ

ጉተታና ምሰሶ ከማቆም ሂደት ጋር ተያይዞ በድምጽ የተገለጹ ዘፈኖች ትርጉማቸው እንዳይሳሳት በጥንቃቄ ለመገልበጥ ተችሏል ፡፡

**II) አተረጓጎም**

Some of the methods mentioned by Peter New mark, in his 'A Textbook of Translalion ' and other scholars are: word-for-word translation, literal translation, faithful translation, communicative translation, semantic translation, adaptation and free translation (New mark, 1988,P.81). **ከላይ በ**Peter New mark ‹A Textbook of Translalion› **ከተጠቀሱት የትርጉም አይነቶች መካከል በዚህ ጥናት ተግባራዊ የሆኑት የቃል በቃል ወይም ቀጥተኛ ትርጉም** (word-for-word translation, literal translation) እና አውዳዊ ትርጉም ናቸው ፡፡ በዚህ ጥናት መረጃዎች ከባህሉ ባለቤቶች በአማርኛና በወላይትኛ ቋንቋዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበዋል ፡፡ እነዚህም በኪንዶ ዲዳዬ፣ካዎ ኮይሻ፣ኦፋና ሁምቦ ከሚገኙ ሰዎች መረጃዎች በወላይትኛ ቋንቋ የተሰበሰቡ ሲሆን በሶዶ ዙሪያ ከሚኖሩ መረጃ ሰጪዎች ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ተሰብስቧል ፡፡

መረጃዎችም ለዚህ ጥናት እንዲሆኑ የትርጉም ስራ የተከናወነ ሲሆን ይህም እንደ መረጃዎቹ አይነት ቀጥታ ትርጉምና አውዳዊ ትርጉም ስራ ላይ ውሏል ፡፡ የትርጉሙ ትክክለኛነት በቋንቋው ባለሙያዎች ታይቷል ፡፡ ስለዚህም መረጃው የተሰበሰበበት ወላይትኛ ቋንቋ ሀሳብ ሳይሸራረፍ የቀረበ ሲሆን አንዳንድ በአማርኛ አቻ ትርጉም የሌላቸው የወላይትኛ ቃላት በጥናቱ በመገኛ ቋንቋው እንደነበረ ተቀምጠዋል ፡፡ ሌላው በጥናቱ ቋንቋ (ስሜት)ትርጉም አይሰጡም የተባሉ ቃላት በባለሙያዎች እገዛ ስሜት እንዲሰጡ ተደርገው የቀረቡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በሙዳዬ ቃላት ማብራሪያ ቀርቧል ፡፡

### 3.3.4. የአጋዥ መሳሪያዎች አጠቃቀም

እንደ ፈቃደ (1991፡ገ.90-99) ገለጻ ‹‹የመስክ መረጃ መሰብሰቢያ መሳሪያዎች፣ፎቶ ካሜራ፣መቅረጸ-ድምጽ፣ ቪዲዮ ካሜራ እና ማስታወሻ ደብተር ናቸው ›› ፡፡

**ሀ. በመቅረጸ ድምፅ ፡-** አማካይነት በቃለ መጠይቅ ወቅት፤ ከመረጃ ሰጪዎች ፍቃድ የተገኘባቸው መረጃዎች ከመስክ በመቅረጸ ድምፅ የተሰበሰቡ ሲሆን እነዚህም መረጃዎች ከመቅረጸ ድምጽ ወደ ጽሁፍ ተቀይረዋል ::

**ለ. በቪዲዮ ካሜራ ፡-** በመስክ ከመረጃ ሰጪዎች በፍቃድ የተገኙ ከባህላዊ ቤት አሰራሩ ጋር የተገናኙ ገለጻዎች፣ማብራሪያዎችና ማስረጃዎች፣ የምስልና ድምፅ መቅረጫ መሳሪያዎች ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡

የእነዚህም ሂደቶች መስክ ላይ የተገኙ የቤት አይነቶችን፣ቁሶችን፤የጓሮ አትክልቶችን፤ የቤቱን ውስጣዊና ውጫዊ ገጽታ በምስልና በድምጽ በመሰብሰብ ተከናውኗል።

**ሐ. በፎቶ ካሜራ ፡-** ደግሞ በቃለ መጠይቅ እና በቡድን ውይይት ወቅት የመረጃ ሰጪዎችን ማንነት ለመግለፅ፤ባህላዊ ቤቶቹን ለማሳየት ፍቃድ የተገኘባቸው፤ባለሙያዎች ቤቱን ሲሰሩ፤የመስሪያ ግብአቶች፤የቤቱ ውስጣዊ ገጽታ፤ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቁሶች እና ከጥናቱ ጋር ተያያዥ የሆኑ እሳቤዎችን የተመለከቱ መረጃዎችን ለመቅረጽ ተግባራዊ ሆኗል።

**መ. በማስታወሻ ደብተር ፡-** ምስላቸው በፎቶ ግራፍ እንዲነሳ፣ ንግግራቸው በመቅረጸ ድምፅ እንዲያዝ፣ እንዲሁም ተግባራቸው በቪዲዮ እንዲቀረጽ ፍቃደኛ ያልሆኑ መረጃ ሰጪዎች ተግባርና ሃሳባቸው ደግሞ በማስታወሻ ደብተር በመጻፍ ተከናውነዋል ። እነዚህም በብሔረሰቡ ከቤት ጋር በተለይ ከምሰሶ እና ከህገረሰባዊ እምነቶች ጋር ተያያዥነት ያላቸው መረጃዎች ከመረጃ ሰጪዎች ተሰብስበው ተግባራዊ ሆነዋል ።

በዚህ ጥናት በመቅረጸ-ድምጽ ፣ በቪዲዮ ካሜራ፣ በፎቶ ካሜራ እና በማስታወሻ በመውሰድ መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል ።

### 3.3.5. የምርምር ሥነ ምግባር

በምርምር ወቅት መዘንጋት የሌለበት የምርምር ሥነምግባር ጉዳይ ሲሆን ይህም የመረጃ ጉዳይ፤ የመረጃ አቀባዮች ፍላጎትና ሌሎች አስፈላጊ ጉዳዮችን የሚመለከት ይሆናል ። ተመራማሪዎች በመረጃ ትንተናና ትርጓሜ ወቅት የሚፈጽሙት የማይገቡ ተግባራት በአራት መልኩ የሚታዩ ሲሆን እነዚህም መረጃ ፈጠራ (data forging)፣ መረጃ ሙረዳ (data cooking)፣ መረጃ ልወጣ (data trimming)፣መረጃ ስቅየታ (data torturing) (ያለው፣2009) ሌላው በመረጃ ትንተና ላይ አድሏዊነት እና ስሜታዊነትን ማስወገድ ተገቢ ነው ። ‹‹በመስክ ምርምር ወቅት የጥናቱን ዓላማ ባጭሩ ማስተዋወቅ፣የማህበረሰቡን ባህል ማክበር፣ ለመረጃ ሰጪዎች ተገቢውን ክብር መስጠት፣ የቀጠሮ ሰዓት ማክበር፣ መረጃ በመስጠት የተባበረን ሰው ማመስገን›› እንደሚገባ ተገልጿል (Dawson, 2009, P. 152-154 ፤ ፈቃደ፣ 1991፣ ገ.96-97)፡፡

በዚህ ጥናት የምርምር ሥነ ምግባር ተግባራዊ የተደረገው ከቀዳማይና ከካልዓይ ምንጮች የተገኙ መረጃዎች ሲሰበሰቡ፣ ሲደራጁ እና ሲተነተኑ የመረጃዎቹን ይዘት መሰረት በማድረግ፣የምርምር ሥነ ምግባር ደንብን መሰረት በማድረግ ተከናውኗል ። በተጨማሪም በመረጃ አሰባሰብ ወቅት የመረጃ አቀባዮች መብት መጠበቅ ጋር የተያያዙ ደንቦች ተግባራዊ የተደረጉ ሲሆን በዚህም የመረጃ አቀባዮችን

ስም ያለፍቃዳቸው አለማውጣት በምትኩ ምናባዊ ስም መስጠት፤ ያለፍላጎታቸው ቀረጻ አለማከናወን መረጃ አቀባዮች የሰጧቸውን መረጃዎች በአግባቡ ማስቀመጥና መተንተንም የስነ ምግባር ጉዳዮች በመሆናቸው መረጃዎች በአግባቡ ተደራጅተው ተተንትነዋል ። ከዚህ በተጨማሪ በቃለመጠይቅ ወቅት መረጃ የሚሰጡ ሰዎች ፍቃደኛ ሆነው በመምጣታቸው ከጥያቄዎቹ በፊት ለፍቃደኝነታቸው በማመስገን እንዲሁም ደግሞ ጥያቄዎቹ ካለቁ በኋላም መረጃ ሰጪዎችን በማመስገን መረጃዎች ተሰብስበዋል ።

### 3.4. የመስክ ተሞክሮና መረጃ የተሰበሰበባቸው ጊዜያት

ይህ ጥናት በወላይታ ስር ከሚገኙ ወረዳዎች መካከል በኪንዶ ዲዳዬ፣አፋ፣ካዎ ኮይሻ፣ሁምቦና ሶዶ ዙሪያ ውስጥ ከሚገኙ ቀበሌዎች መካከል በተመረጡት ተከናውኗል ። ጥናቱ በስምንት ዙር የመስክ ጉብኝት እንደሁኔታው እዛው በመቆየትና ደርሶ መልስ ጉዞ ነበረው ። የዚህ ጥናት መረጃ የተሰበሰበዉ ከሚያዝያ 16/2014 ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 4፣ 2016 ዓ.ም ባሉት ጊዜያት ውስጥ በስምንት ዙር ተከፋፍሎ ነው ።

ጥናቱ የተካሄደበት አካባቢ ተወልጄ ያደግኩበት እና መደበኛ ትምህርቴንም የተከታተልኩበት መሆኑ ለጥናቴ አመቺ ሁኔታዎችን ፈጥሮልኛል ። የመጀመሪያው ዙር ጉዞ ሚያዚያ 13፣2014 ዓ.ም ከአማርኛ ቋንቋ፣ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የትብብር ደብዳቤ በማጻፍ ሚያዚያ 15፣2014 ዓ.ም ከአዲስ አበባ ተነስቼ ወላይታ ሶዶ ከተማ ከቀኑ 8፡00 ሰዓት ደረስኩ ።

በነጋታው ሚያዚያ 16፣ 2014 ዓ.ም ከጠዋቱ 3፡00 በቅድሚያ ያመራሁት ወደ ዞኑ ባህልና ቱሪዝም የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮ ነበር። ለባህልና ቱሪዝም የመንግስት ኮሙኒኬሽን ቢሮው ሀላፊ ስለጥናቱ ዓላማ ካስረዳሁ በኋላ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ከአማርኛ ቋንቋ፣ሥነጽሁፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የተፃፈውን ደብዳቤ በመስጠት ለሚመለከታቸው አካላት ሁሉ የትብብር ደብዳቤ ተጻፈልኝ ።

በመቀጠል በሶዶ ከተማና አካባቢ ለጥናት በተመረጡት ወረዳዎች ውስጥ ካሉ ቀበሌዎች መካከል ቁልፍ የመረጃ አቀባዮች ያሉበትን ቦታ በሚያውቁ ሰዎች፣ በዘመዶቻቸውና፣ በጓደኞቻቸው አማካይነት አገኘሁ። ላገኘኋቸዉ መረጃ አቀባዮች የጥናቱን ዓላማ እያስረዳሁ ፍቃደኝነታቸውን ሲገልፁልኝ ለቃለ መጠይቅ ቀጠሮ እየያዝኩ ተመለስኩ። ስለአካባቢው አጠቃላይ ገፅታ ስለአካባቢው ዳራ ፣ማኅበራዊ፣ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮችን የሚገልጹ የመጽሔት፣የመጻህፍት መረጃዎች ከዞኑ ባህልና ቱሪዝም፣ የመንግስት ኮሙኒኬሽን መምሪያ፣ ስለአካባቢዉ ታሪክ ከሚያዉቁ የሀገር ሽማግሌዎች፣

ከማዕከላዊ እስታቲስቲክስ እና ከባህልና ቱሪዝም ቢሮዎች ማሰባሰብ ችያለሁ (ከሚያዝያ16-ግንቦት1/2014ዓ.ም) ።

በሁለተኛው ዙር የመስክ ጉዞ ከግንቦት 02/ እስከ ሰኔ28/2014 2014 ዓ.ም ጀምሮ የተካሄደ ሲሆን ይህም ወደ ዋናው የመስክ ስራ የገባሁበት ጊዜ ነበር ። ይህም ባህላዊ የቤት አይነቶች ላይ በቂ እውቀት ያላቸው በአካባቢው ብሔረሰብ እውቅና የተሰጣቸው ሰላሳ በዕድሜ የገፉ ወንዶች፤ሃያ በዕድሜ የገፉ ሴቶች እና ሃያ ወጣቶችና በመካከለኛ እድሜ ላይ የሚገኙ በድምሩ ከሰባ መረጃ አቀባዮች ጋር ቃለ መጠይቅ ተደርጓል። ለቃለ መጠይቅ ያዘጋጀኋቸውን ጥያቄዎች እያነሳሁ መረጃ አቀባዮች እንዲመልሱልኝ በማድረግ መደበኛ ጥያቄዎችን እና አንዳንዴም ለውይይት ይሆናሉ የምላቸውን ጥያቄዎች አንስቼአለሁ ።

በዚህም መጀመሪያ የሄድኩት በጥናቱ ወሰን ላይ እንደገለጽኩት ወደ ኦፋ(ገሱባ) ወረዳ ሲሆን ይህንንም ጉዞ ያደረግኩት ከባህላዊ ቤት አሰራር ጋር በተገናኘ ሰፋ ያለ እውቀት እንዳለው ከሚነገርለት አቶ ኢያሱ ገጃቦ ጋር ሲሆን በሱ አማካኝነት በኦፋ ወረዳ ሌሎች አምስት ሰዎችን አግኝቼ አምስት ቀን በመመላለስ መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ ።

በመቀጠል የሄድኩት የወላይታ መነሻ በሆነውና ትክክለኛ ባህሉም ይገኝበታል ተብሎ በአካባቢው ሰው ወደ ሚታመነው ኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ነበር ። እዛም እንደደረስኩ የአካባቢውን ሰዎች በመጠየቅ ወደ ባህልና ቱሪዝም ቢሮ ደረስኩና ለሀላፊው የመጣሁበትን ዓላማ አስረድቼ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የተሰጠኝን ደብዳቤ ለሀላፊው ሰጠሁ ። እሱም ካዳመጠኝና ወረቀቱን ካነበበ በኂላ ሁለት ሰዎችን ጠርቶ መረጃ የሚሰጡኝን ሰዎች ቤት እንዲያሳዩኝ ነገራቸው እነሱም ወደ ተባሉት ሰዎች ቤት ወሰደውኝ መረጃዎችን ሰበሰብኩ ። ሌላው እዛው ወረዳ ላይ የሚኖር ግለሰብን ቀደም ሲል ለዚህ ስራ መረጃዎችን ይሰጥሻል በሚል ወላይታ ላይ በሰዎች አማካይነት ተዋውቀው ስለነበር ስልክ ደውዬ አገኘሁት ። እሱም መረጃዎችን ከሰጠኝ በኂላ ሌሎች በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ እውቀት ያላቸው የተለያዩ ሰዎችን ጠቁሞኝ ከነሱ ጋርም እንድገናኝ አደረገ ። እነሱም የምፈልጋቸውን መረጃዎች ሰጡኝ ።

በሶዶ ከተማና ዙሪያ የሚገኙ ሰዎችን በማውቃቸው ሰዎች አማካይነት ወደሚገኙበት ቦታ በመሄድ እንዲሁም ደግሞ ካዎ ኮይሻና ሌሎች ተጨማሪ ወረዳዎች ላይ የሚገኙ መረጃ አቀባዮችንም በሚያውቋቸው ሰዎች በጥቆማ በማግኘት መረጃዎችን ለመሰብሰብ ችያለሁ ።

በሁለተኛው ጉዞዬ ደግሞ ሰዎች እየኖሩበት ያሉበትን ቤት ተመለከትኩ፤ ይህም ቤት ሙሉ በሙሉ ባህላዊውን አሰራር ተከትሎ የተሰራ ነው ። ይሁንና ቤት ውስጥ ያሉ ቁሶች ዘመናዊና ባህላዊ ሆነው

አግኝቻቸዋለሁ ፡፡ በሦስተኛው  የመስክ ጉብኝቴ ደግሞ የጥናቴ ትኩረት የሆነውን ባህላዊ ቤት ባህሉን ተከትለው የተሰሩና በውስጣቸው የሚገኙ ቁሶችም ባህላዊ መሆናቸውን ተመልክቻለሁ፡፡ በአጠቃላይ በአካባቢው ላይ አዳዲስ ቆርቆሮ ቤቶችን እየተመለከትኩ ባለሁበት ወቅት ከቆርቆሮና ከሳር ቤቱ ውስጥ በእድሜ የገፉ ሶስት አባቶችና በእድሜ የገፉ አንዲት እናት እኔ ወዳለሁበት በመምጣት ለምን እንደመጣሁ ቤቱን ለምን እንደፈለግኩ ጠየቁኝ እኔም የመጣሁበትን ዓላማ ሳስረዳቸው  በጣም ደስ እንዳላቸውና ይሄ የምንወደው ባህላዊ ቤታችን በቆርቆሮ ቤት እየተተካ በመሆኑ እንዳይጠፋብን አደራ ለመንግስት ባህሉ እንዲቀጥል አድርጉልን በማለት ስጋታቸውንና አደራቸውን ከምርቃት ጋር ሰጥተውኝ ተመለስኩ ፡፡

ሦስተኛው ዙር የመስክ ጥናት ከሐምሌ01/2014 ጀምሮ ለሠላሳ ቀናት ተካሂዷል ፡፡ በዚህም ወቅት በሁለቱ የመስክ ጉብኝት ወቅት የተዘለሉ፣ ያልተጠየቁ እና ያልተሟሉ ጉዳዮችን ማሟላት ችያለሁ ፡፡ አራተኛው የመስክ ጊዜ ከጳጉሜ 01/2014ዓ.ም እስከ ጳጉሜ 03/2014ዓ.ም በተለያየ በራሳቸው ጉዳይ መረጃ ለመስጠት ፍቃደኛ ያልነበሩ ሰዎች በዘመዶቻቸው አማካይነት ዓላማውን ደጋግሜ በመንገር፤በቅርብ ሰዎች በማስነገር፤በፍቃደኝነት እቤታቸው ሄጄ መረጃ እንድወስድ በቀጠሮ መረጃን ሰጥተውኛል ፡፡

ጳጉሜ04-05/2014ዓ.ም ላይ የመጀመሪያውን ረቂቅ ለአማካሪዎቼ የላኩበት ጊዜ ሲሆን እነሱም አንብበው ጥቅምት 28/2015 ዓ.ም ላይ መለሱልኝ ፡፡ በሰጡኝ አስተያየት መሰረት ለአምስተኛ ጊዜ ወደ መስክ በመሄድ የጎደሉና ማብራሪያ የሚፈልጉ ጥያቄዎችን አስተካከልኩ ፡፡

ህዳር 27/2016ዓ.ም የደረጃ ማበልጸጊያ ፈተና ወቅት ነበር ፡፡ በዚህም ከፈታኙ መምህር የተሰጡኝን አስተያየቶች፤የጎደሉ መረጃዎችን ለመሙላት፤ ለጥያቄዎች መልስ ለመስጠት ለስድስተኛ ጊዜ ወደ መስክ ጉዞ በአራት የደርሶ መልስ ጊዜ ጉዞዎችን በማድረግ የጎደሉና ጥያቄ የሚጭሩ ሀሳቦችን አስተካክዬ የካቲት መጨረሻ ላይ ለአማካሪዎቼ ላኩላቸው እነሱም ከ1ወር በኋላ ሚያዝያ 15/2016 መለሱልኝ ፡፡ ከነሱ የተነሱ አስተያየቶችንና ጥያቄዎችን ለማጥራት ለስምንተኛ ጊዜ ወደ መስክ በመጓዝ እዛም ቆይታ እያደረግኩ አምስት ጊዜ በመመላለስ  መስከረም 2017 ዓ.ም የመስክ ጉዞዬን አጠናቀቅኩ ፡፡

### 3.5. የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች

በዚህ ጥናት ቀጥሎ የቀረቡት የSchlereth የመተንተኛ ሞዴሎች ቁሳዊ ባህልን ለመመደቢያ እና ለመተንተኛነት ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

**ሀ. ታሪካዊ ጥበብ አመልካች** (Art Historical) :- ቁሶች በሚጠኑበት ጊዜ የሚሰጡት ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ማድረግ ሳይሆን በቁሶቹ ላይ ያለውን ጥበባዊ የምናሳይበት ነው ። ስለዚህም ጥበባዊ ውጤቶች ግንዛቤ ውስጥ ገብተው ቅርጽ፣ቀለምና ጥንካሬ በአግባቡ መግለጽ ታሪካዊ ጥበብ አመልካችነታቸውን ያሳያል ።

**ለ. ተምሳሌታዊ** (Symbolic) :- በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ቁሶቹ ዕለት ዕለት በማህበረሰቡ ከሚኖራቸው ተግባር ባሻገር ያለውን ጥበብ መመርመር እንደሚያስፈልግ ነው። ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዲሁም ደግሞ ምን ለመግለጽ እንደመጡ መመርመርና ተምሳሌታዊ ፋይዳቸው ምንድነው? ቁሶቹ የሚያሳዩት የህይወት ፍልስፍና ምንድነው?የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚገለጽበት ነው ።

**ሐ. ባህላዊነት** (Cultural) ፡- በቁሶቹና በማህበረሰቡ ባህል መካከል ያለውን ዝምድና የሚመረምር ነው፡ ሌላው የማህበረሰቡን የትኛውን የባህል አይነት ይወክላሉ? የሚሉ ጥያቄዎች ተመርምረው ምላሽ ለማግኘት የሚረዳ የመተንተኛ ሞዴል ነው ።

**መ.አካባቢያዊነት** (Environmental) :- የአንድ አካባቢ መልክአምድራዊ ገጽታና ቁሶቹ ያላቸው መስተጋብር ምን ይመስላል የሚል ጥያቄ የሚመረመርበት የሞዴል አይነት ነው።

**ሠ. መዋቅራዊ** (Structuralist) ፡- ቁሶቹ እንዴት እንደተሰሩ በአካል ውቅራቸውን የሚያሳይ ሆኖ ቁሶቹ ከምን ከምን ግብአቶች ተሰሩ? የአሰራር ቅደም ተከተላቸው ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት ነው ።

**ረ. ባህሪያዊ** (Behaviorist) :- ማህበረሰቡና ቁሶቹ ያላቸው ባህርያዊ መስተጋብር ምን ይመስላል? ማህበረሰቡ ቁሱን እንዴት ይረዳዋል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ ያገኙበታል ።

**ሸ.ማህበራዊነት** (Community) ፡- ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ትስስር የሚገልጽ ሆኖ ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ገጽታ በምን መንገድ ያሳያሉ? የቁሶቹ ተገልጋዮች ቁሶቹን ከምን አስተሳሰብ ይገለገሉባቸዋል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ተመርምረው ምላሽ ያገኙበታል ።

**ቀ.ማህበራዊ ታሪካዊነት** (Social Historical) ፡- የቁሶቹ የአመጣጥ ታሪክ ምን ይመስላል? ቁሶቹ የማህበረሰቡን ታሪክ በምን መልኩ ይገልጹታል? ቁሶቹን ማን ሰራቸው? ከየት ተገኙ? በየትኛው ዘመን ተገኙ ለሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚገኝበት የመተንተኛ ሞዴል ነው ። በዚህ ጥናት ከላይ

የቀረቡት ሞዴሎች መሰረት ተደርገው መረጃዎች ተሰብስበው ተተንትነዋል (Schlereth, 1985, p.24) ፡፡

**የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች በዳያግራም**




ምንጭ፡ - በአጥኚዋ የተዘጋጀ ህዳር 2017 ዓ.ም

## 3.6. የምዕራፎች አደረጃጀት

በዚህ ንዑስ ምእራፍ ስር የመስክ መረጃዎች እንዴት እንደተሰበሰቡ?መረጃዎች ከነማን ተሰበሰቡ? መረጃዎቹ በምን መንገድ ተደራጁ? በየምዕራፎቹ ከመስክ የተገኙት መረጃዎች ይዘታቸው ምን እንደሆኑ? መረጃዎቹ የተተነተኑበት ንድፈ ሀሳቦችና ሞዴሎች የትኞቹ ናቸው?የሚሉ ጥያቄዎች ምላሾች እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

ይህ ጥናት ዓይነታዊ ጥናት በመሆኑ በምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተሰበሰቡ መረጃዎች ከመተርጎማቸው በፊት በቃል የነበሩት ወደ ጽሁፍ ተቀይረው የትርጉም ስራ ተሰርቷል ፡፡ ሌላው የመስክ መረጃዎችን ለመተንተን ገላጭ እና የይዘት ትንተና ዘዴ ተግባር ላይ ውለዋል ፡፡ አደረጃጀቱም በቅደም ተከተልና ተመሳሳይ የሆኑትን ወደ አንድ በማምጣት ተከናውኗል ፡፡ ይህን

ጥናት ለመስራት አነሳሽ የሆኑ ምክንያቶች እና ዓላማ መሰረት ተደርገው ይዘቱን ለማሳየት የምርምሩ ትንታኔ ክፍል በአምስት ምዕራፎች ተደራጅቶ ቀርቧል ፡፡

በምዕራፍ አምስት ስር ቤት ምንነቱና ውክልናው በብሔረሰቡ፤ከቤት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፤የወላይታ ባህላዊ ቤት አይነቶች፤የጉላንታ ቤት ባህላዊ ተምሳሌቶች፤የመስክ መረጃዎች በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ ፣በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፤ በሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ (Schlereth, 1985, P. 24) የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች መሰረት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

በምዕራፍ ስድስት ስር በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ለመስራት የሚያነሳሱ ምክንያቶች፤ቅድመ ቤት ሥራ፤ቤት የሚሰራበት አፈር፤ የጣሪያ ስራ፤ጣሪያ የሚሰሩ ሰዎች የሚዘፍኑት ዘፈን፤ግድግዳና የበር መቃን አወቃቀር፤የክዳን ስራ፤የምሰሶ ስራ፤ምሰሶ ሲጎተት ፤ምሰሶ ተጎትቶ መጥቶ ሰፈር ሲደርስ ምሰሶ ሲቆም የሚዘፈኑ ዘፈኖች ፣ምሰሶና ማህበራዊ ክብር፤ምሰሶና ተምሳሌታዊ ፍቺዎች፤ምሰሶ የትውፊታዊ እምነት ማሳያ፤ምሰሶ እና መቆሚያው ጉርጓድ፤ምሰሶና ትውፊታዊ እምነት፤ምሰሶና ሥርዓተ ጾታ፤ቤት የሚሰራባቸው እለታትና ትርጓሚያቸው፤ቤት የሚሰራባቸው ወራት፤የባህላዊ ቤቶች አሰራርና የጨረቃ ኡደት፤የቤቱ አቅጣጫ የቤቶቹ የአሰራር ቅደም ተከተሎች፤የስራድርሻ፤የብሔረሰብ ተጠሪዎች፤ የሴቶች ፤የአካባቢው ወጣቶችና ጎልማሶች ፤የቤቱ ባለቤት በአካባቢው የቤት ቁሶችን የሚሰሩ ሰዎች፤ቤት በሚሰራበት ወቅት የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጦች፤ግድግዳ በሚዘጋጅበት ወቅት፤ግድግዳ በሚቆምበት ወቅት፤በጣሪያ ስራ ወቅት፤ምሰሶ በሚቆምበት ቀን፤ የተዘጋጀው ምግብና መጠጥ ለታዳሚው ሲቀርብ፤አዲስ ቤት ሲገባ የሚቀርቡ ምርቃቶች፤ድህረ ቤት ሥራ፤የአጥር መስሪያ ግብአቶችናትዕምርቶች፤በቤቱ ዙሪያ የሚተከሉና የማይተከሉ ተክሎች፤ እነዚህ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ይዘት በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፤ በሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ በፍካሬ ልቦና እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በ(Schlereth, 1985, 24) የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች መሰረት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

በምዕራፍ ሰባት የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤትውጫዊ ቅርጽ፤ውስጣዊ ቅርጽ፤የቤቱ ውስጣዊ ቅርጽና ትርጓሜ፤የሙሉነት እሳቤ በብሔረሰቡ የቤት አሰራር፤የሙሉነትና የሙሉ ቁጥር እሳቤ የብሔረሰቡ የቤት አሰራር እውቀት መተላለፊያዎች፤ባህላዊ ቤትን የሚሰሩ ባለሙያዎች፤ቤት ማስዋብ፤የቤት ጉልላት ትርጓሚዎች፤ቀለምና ውክልናው፤ የተባሉ ይዘቶች በመዋቅራዊ ተግባራዊነት

ንድፈ ሀሳብ፤ በሥነ ትዕምርት ንድፈ፤በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ የሆኑ ሲሆን ከቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች ደግሞ የSchlereth ተግባራዊ ሆነው መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

በምዕራፍ ስምንት ለውጥና ቀጣይነት በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ውስጥ በሚል የቀረበ ሲሆን በምዕራፍ ዘጠኝ ደግሞ ማጠቃለያ ግኝት እና ይሁንታ ቀርበዋል ፡፡

እነዚህ ይዘቶች በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ ፣በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፤ በሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ መሰረት ተግባራዊ ሆነዋል ፡፡

# ምዕራፍ አራት

## 4.1. የጥናቱ አካባቢ እና የወላይታ ብሔረሰብ አውዳዊ ዳራ

በዚህ ምዕራፍ ስር የአካባቢው ስያሜ፣የወላይታ ህዝብ አሰፋፈር፣የወላይታ ህዝብ ብዛት እና ስርጭት፣የወላይታ ዞን መልክአ ምድራዊ አቀማመጥ፣የሕዝቡ ኃይማኖት፣ የወላይታ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት እና ቅድመ ጋብቻ፤ እንዲሁም አዲሱ የደቡብ ኢት/ያ ክልሎችን፤ የኢትዮጵያ ክልሎችን ፤ለጥናቱ የተመረጡ ወረዳዎችንና በስራቸው ያሉ ከተሞችን የሚያሳይ ካርታ ቀጥሎ ቀርበዋል ።

### 4.2. የአካባቢው ስያሜ

(Bender, 1986) እንደገለጸው፣ ወላይታ (Wolayta) እና ወላይታቱዋ (Wolaittattuwa) ለቋንቋው መጠሪያነት የሚያገለግሉ የተለመዱ ስሞች ናቸው ። በተመሳሳይ፣ ዘብዲዮስ ጩሞ (2012, ገ. 25) ወላይታ የሚለው ስያሜ "የተባበረ ሕዝብ" የሚል ትርጉም እንዳለውና ከተለያዩ አካባቢዎች የመጡ ሕዝቦች ከነባር የወላይታ ነገዶች ጋር ተቀላቅለው መኖራቸውን እንደሚያመለክት አስረድተዋል ።

የወላይታ ህዝብ ቋንቋውንም ሆነ አካባቢውን "ወላይታ" በሚል ስያሜ ይጠራዋል፤ ትርጉሙም የእድሜ ባለፀጎች እንደገለፁት ወላይታ ማለት "የአገር እና የህዝብ ስም" ነው ። ከዚህም ጋር በማያያዝ አንዳንድ የብሔረሰቡ ክፍሎች ቃሉ በወላይትኛ "ወላሄታ" (የተቀላቀለ) ከሚል ቃል እንደመጣ እና ይህም ስያሜ ከተለያዩ ቦታዎች በተለያየ አጋጣሚ የተሰበሰቡ ጎሳዎች በህብረት የሚኖሩበት አካባቢ መሆኑን የሚያመለክት ትርጉም እንደሆነ ይገለፃል (ቃለ መጠይቅ፣ መሸሻ ፋንታ፣ ፋንታ አላሮ ሰኔ /2014) ።

ፎቶ1፡-  የኢትዮጵያን፣የወላይታ ዞንን እና ለጥናት የተመረጡ ወረዳዎችን  የሚያሳዩ ካርታዎች




**ምንጭ፡- Geo information Institute of Ethiopia 2022.**

ፎቶ 2፡- አዲሱ የደቡብ ኢት/ያ ክልሎችን የሚያሳይ ካርታ




ምንጭ፡ሥነ-ህዝብ ቢሮ ሰኔ2016 ዓ.ም

### 4.3. የወላይታ ህዝብ አሰፋፈር

በአካባቢው ለረዥም ጊዜ ከቆዩ የሀገር ሽማግሌዎችና የታሪክ አዋቂዎች በቃለ መጠይቅ ባገኘሁት መረጃዎች መሰረት የወላይታ ህዝብ[2] ከተለያዩ ቦታዎች መጥተው ከሰፈሩ 113 የተለያዩ ጎሳዎች የተመሰረተ ነው ። እነዚህ የተለያዩ ጎሳዎች በወላይታ ምድር ለረዥም ዘመን ቆይተው ከተዋሀዱ በኋላ በሁለት አቢይ ነገዶች ተከፈሉ ። እነዚህም ሁለት አቢይ ነገዶች ማላና ዶጋላ በመባል የሚታወቁ ሲሆን በማላ ነገድ ስር 12 ጎሳዎች ይገኛሉ ። በዶጋላ ነገድ ስር ደግሞ 101 ጎሳዎች አሉ (ቃለ መጠይቅ፣ በዛብህ፣ መሸሻ፣ ጥቅምት 2፣ 2014) ።

"የዎላይታ ህዝብ[3] በወንዞች ዙሪያ መስፈር የጀመሩት በአሮጌው በመካከለኛው እና ከአዲሱ የድንጋይ ዘመን አካባቢ ሳይሆን አይቀርም የሚል መላምት አለ። የወላይታ ህዝብ ታሪካዊ መነሻው ኪንዶ ዲዳዬ አካባቢ ባሉት ዋሻዎች ሲሆን በጦርነት እና የተለያዩ መንገዶች እየተስፋፉ ሄደዋል" ፋንጩ እና ኢዮብ (1966፣ገ.45-46) ።

በሌላ አንጻር አዳዲስ መላምቶች አርኪኦሎጂካል ጥናቶችን መሰረት በማድረግ ከ58 000-70 000 ምዕተ ዓመት በፊት በሞቼና ቦራጎ ዋሻ ውስጥ እና በአካባቢው የሰፈሩት የተለያዩ የዎላይታ ጎሳዎች በግብርና እና ከብት እርባታ በሚተዳደሩበት ጊዜ የስልጣኔ ደረጃቸው እየጨመረ በመምጣቱ ከግብርና ውጤት ባሻገር ሰዎች ጦርነት ሲጀምሩ ወደ ኦሞ ወንዝ ዳርና ኪንዶ ዲዳዬ እንደተንቀሳቀሱ ጥናቶች ያስረዳሉ ፋንጩ እና ኢዮብ (1966፡45-46) ።

በወላይታ ዞን ከ58,000 ዓመታት በፊት የሰው ዘር ይኖርበት እንደነበረ በሶዶ ዙሪያ በሚገኘው እና ሞቼበራጎ በተባለው ዋሻ ላይ የተደረገው የአርኪዎሎጂ ምርምር ያስረዳል። ከዚህ ዋሻ ውስጥ በቁፋሮ የተገኙት ቅሪቶች የብሔረሰቡን የሺህ ዓመታት የእርሻ፣ የሽመና፣ የቆዳ፣ የብረታብረት እና ዕደ

---

[3] . እንደ ባይለየኝ ጣሰው ገለጻ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ሕዝብ ማለት ሰፋ ያለ የጋራ ጠባይ የሚያንጸባርቅ ባሕል ወይም ተመሳሳይ ልምዶች ያላቸው፣ሊግባቡበት የሚችሉበት የጋራ ቋንቋ ያላቸው፣የጋራ ወይም የተዛመደ ሕልውና አለን ብለው የሚያምኑ፣የሥነ ልቦና አንድነት ያላቸውና በተያያዘ መልክዓ ምድር የሚኖሩ ናቸው ። ከዚህ በተጨማሪ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ሕዝብ የተባሉት የሚያመለክቱት ባሕርያት፣መጠንና ደረጃዎች በሶስቱም አሟልተው ይገኛሉ (ዜና ልሳን፣ገ.18፣2015) ። በዚህ ጥናት ውስጥ ብሔር፣ብሔረሰብ፣ሕዝብ የተባሉት እሳቤዎች ተመሳሳይ ሀሳብ ስላላቸው በማፈራረቅ ተግባር ላይ ውለዋል ።

ጥበብ  ክህሎት የሚያሳዩ ናቸው ፡፡ በዛሬዋ ወላይታ ዞን በኦፋ ወረዳ ጣዳ ጋርቤ ውስጥ በአክርሳ ዋሻዎች በተደረጉት የአርኪዎሎጂ ጥናቶችና ምርምሮች መሰረት በዋሻዎቹ ውስጥ የተሳሉት ስዕሎች ከ6000 ዓመታት በፊት በስፍራዎቹ እንስሳትና እፅዋት የማላመድ ተግባራት መገለጫ የሆኑ ነገሮች እንደተጀመሩ ምርምሩ ፍንጭ ይሰጣል (የወላይታ ብሔር ባህላዊ ተምሳሌቶች ፕሮፋይል 2010ዓ.ም፣ገ.170) ፡፡

በወላይታ ውስጥ ግዛትን በመከላከልና በማስፋት በተለያዩ ሥፍራዎች ከ1500 ዓመታት በፊት ጀምሮ ከአንድ ወጥ አለት በባህላዊ ምህንድስና ተጠርበው በወንድ ሰው ተምሳሌት ተቀርፀው የተተከሉ በተለምዶ "የአሩጂያ ትክል ድንጋዮች" በመባል የሚጠሩት ትክል ድንጋዮች የማህበረሰቡን ጥንታዊነትና ስልጣኔ አመላካች ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ መሸሻ ፋንታ፣ ሚያዝያ 17፣ 2003) ፡፡

"የዎላይታ ህዝብ በወንዞች ዙሪያ መስፈር የጀመሩት በአሮጌው በመካከለኛው እና ከአዲሱ የድንጋይ ዘመን አካባቢ ሳይሆን አይቀርም የሚል መላምት አለ፡፡ የወላይታ ህዝብ ታሪካዊ መነሻው ኪንዶ ዲዳዬ አካባቢ ባሉት ዋሻዎች ሲሆን በጦርነት እና የተለያዩ መንገዶች እየተስፋፉ ሄደዋል" (ፋንጨ እና ኢዮብ 1966፣ገ.45-46) ፡፡

ፎቶ3፡- የኢትዮጵያ ክልሎችን የያዘ ካርታ




ምንጭ፡- ሥነ ህዝብ ቢሮ 2016ዓ.ም

### 4.4.የወላይታ ህዝብ እና ስርጭት

የዎላይታ ህዝብ ብዛት፣የቦታውን ስፋት፣ በኢትዮጵያ ውስጥ በአብዛኛው የሚኖሩበትን ክልልና የዞኑ ዋና ከተማ ከአዲስ አበባ ያለውን ርቀት በተመለከተ (Lamberti and Sottile, 1997) እንደሚከተለው አቅርበዋል ፡፡

እ.ኤ.አ. በ2007[4] የኢትዮጵያ የሕዝብና ቤት ቆጠራ መሠረት የወላይታ ሕዝብ ብዛት 1, 707, 079 እንደ ነበር ተገልጿል ፡፡ አብዛኛዎቹ የዎላይታ ቋንቋ ተናጋሪዎች የሚኖሩት በደቡብ ብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልል ውስጥ እንደሆነ ጠቁመዋል ፡፡ በተጨማሪም ሕዝቡ የሚኖርበትም አካባቢ 'ወላይታ' በሚለው ስም ይታወቃል ፡፡ የዞኑ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 3500 ኪ.ሜ. አካባቢ እንደሆነ ጠቁመዋል ፡፡ ሌላው ግብርናና ንግድ የህዝቡ መሰረታዊ ተግባራት ሲሆኑ ዞኑ በውስጥም ሆነ በውጪ በቀላሉ ለመግባባት የሚያስችል የተደራጀ መሰረተ ልማት አለው ፡፡ አክለውም የዞኑ ዋና ከተማ ሶዶ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 330 ኪ.ሜ ርቀት ላይ እንደምትገኝ ገልጸዋል ፡፡

የዞኑ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 4,208 ካሬ ኪሎ ሜትር ገደማ ሲሆን፣ የሕዝቡ ዋነኛ የኢኮኖሚ መሠረት ግብርናና ንግድ ነው ፡፡ በተጨማሪም ዞኑ ከሌሎች አካባቢዎች ጋር የሚያገናኝ የተደራጀ የመጓጓዣ መሠረተ ልማት ያለው ሲሆን፣ የዞኑ ዋና ከተማ ሶዶ ከአዲስ አበባ በስተደቡብ 330 ኪሎ ሜትር ርቀት ላይ ትገኛለች (የማዕከላዊ ስታቲስቲክስ ኤጀንሲ, 2008) ፡፡

### 4.5. የወላይታ ዞን መልክአምድራዊ አቀማመጥ

እንደ (Annual Statistical Abstract, 2012, p.2) ገለጻ ‹‹የወላይታ ዞን በደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ህዝቦች ክልል መንግስት ከሚገኙ ማእከላዊ ዞኖች አንዱ ሲሆን 6.29-7.10$^0$ ሰሜን ላቲትዩድ እና 37.13$^0$ -38.08$^0$ ምስራቅ ሎንግቲዩድ ላይ ይገኛል›› ፡፡

---

[4] Wolayta has 1, 707, 079 native speakers according to the 2007 population and housing census of Ethiopia. The majority of Wolayta speakers reside in the Southern Nations, Nationalities and People's Regional State of Ethiopia. Wolayta speakers also use the name Wolayta in order to refer to the land they live in. Its total area is about 3500sq. km. Farming and trade are basic activities for the people. Wolayta is an independent administrative zone. The zone has a well-organized infrastructure to communicate easily internally as well as externally. The main town of the zone is Soddo, which is located about 330km south of Addis Ababa. (1997,P,15)

የወላይታ ዞን በሰሜን የከምባታ ጠምባሮ እና የሀዲያ ዞን፣ በምስራቅ ሲዳማ ክልል፣ በደቡብ ጋሞ እና ጎፋ ዞን፣ በምዕራብ ዳውሮ ዞን እና በሰሜን ምስራቅ ከኦሮሚያ ክልል ጋር ይዋሰናል (ፋንጮ እና ኢዮብ፣2006፣ገ.198) ፡፡

የወላይታ ዞን መሬት አቀማመጥ በአብዛኛው ሜዳማ፣ አልፎ አልፎ ግን ጉብታዎችና ተራሮች ያሉበት ነው ፡፡ ወላይታ ሶስት የአየር ንብረቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ በመባል የሚታወቁ ናቸው ፡፡ የዞኑ አብዛኛው ክፍል ወይና ደጋ ሲሆን በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ደግሞ ቆላማ ሲሆኑ በከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙት ደጋማ ናቸው (Annual Statistical Abstract, 2012) ፡፡

የዞኑ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 451,170 ሄክታር ወይም 4511.7km2 ነው ፡፡ ዞኑ በ16 ወረዳዎችና 6 ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ሲሆን በአጠቃላይ 377 ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 289 የገጠር እና 79 የከተማ ቀበሌዎች ናቸው (Annual Statistical Abstract, 2012, p. 1-2 ) ፡፡

የወላይታ ዞን በ $7^0$ ሰሜን እና $37^0$ 45 ምስራቅ ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው ፡፡ የወላይታ ዞን መሬት አቀማመጥ በአብዛኛው ሜዳማ፣ አልፎ አልፎ ግን ጉብታዎችና ተራሮች ያሉበት ነው ፡፡ ወላይታ ሶስት የአየር ንብረቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ በመባል የሚታወቁ ናቸው ፡፡ የዞኑ አብዛኛው ክፍል ወይና ደጋ ሲሆን በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ደግሞ ቆላማ ሲሆኑ በከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙት ደግሞ ደጋማ ናቸው ፡፡ ሌላው የዞኑ አጠቃላይ የቆዳ ስፋት 451,170 ሄክታር ወይም 4511.7km2 ነው ፡፡ ዞኑ በ16 ወረዳዎችና 6 ከተማ አስተዳደሮች የተዋቀረ ሲሆን በአጠቃላይ 377 ቀበሌዎች ያሉት ሲሆን ከነዚህም ውስጥ 289 የገጠር እና 79 የከተማ ቀበሌዎች ናቸው (Annual Statistical Abstract, 2012, p. 1-2 ) ፡፡

## 4.6. የህዝቡ ቋንቋ እና ኃይማኖት

### 4.6.1. የህዝቡ ቋንቋ

የብሔረሰቡ ቋንቋ ዎላይታቷ *(Wolayttattuwaa)* ተብሎ የሚጠራ ሲሆን ከኦሟዊ ቤተሰብ ስር ይመደባል ፡፡ በአሁኑ ሰዓት የወላይታቷ ቋንቋ የፅሑፍ ቋንቋ ሆኖ እያገለገለ ይገኛል ፡፡ የወላይታ ሶዶ ትምህርት በሬዲዮ ማሰራጫ ጣቢያ ከ1965 ዓ.ም ጀምሮ እስከ 1980ዎቹ መጀመሪያ ድረስ ባሉት ዓመታት ውስጥ የተወሰኑ ትምህርታዊ ፕሮግራሞችን እንደ የእርሻ እና የጤና ትምህርት የመሳሰሉትን ለወላይታ እና ለአጎራባች ህዝቦች በወላይታቷ ቋንቋ ያሰራጭ ነበር ፡፡ በተጨማሪም

ቀደም ሲል በአገሪቱ ውስጥ መሰረተ ትምህርት ይሰጥ በነበረበት ወቅት በወላይታቷ ቋንቋ ትምህርት ሲሰጥ እንደነበረ ከቃለ መጠይቁ የተገኙ መረጃዎች ይጠቁማሉ :: በአሁኑ ጊዜ በወላይታ ዞን የሚኖሩ ህፃናት አፋቸውን በፈቱበት ወላይታቷ ቋንቋ በመማር ላይ የሚገኙ ሲሆን የላቲን ፊደላትን በመጠቀም የወላይታቷ ቋንቋ መፃህፍት ታትመው አገልግሎት ላይ ውለዋል :: የአንደኛ ደረጃ የመጀመሪያ ሳይክል ሙሉ በሙሉ በወላይታቷ የሚሰጥ ሲሆን በ2ኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ምላይታቷ እንደ አንድ የትምህርት አይነት ይሰጣል ። የዞኑ የስራ ቋንቋም ሆኖ እያገለገለ ይገኛል (የደቡብ ብሄሮች ብሄረሰቦችና ህዝቦች ፕሮፋይል፣169) ።

### 4.6.2. የህዝቡ ኃይማኖት

"በጥንታዊው የኦሪት ዘመንና ከዚያም በፊት የነበረው የእምነት አይነት በወላይታ ነበር፤የዚያ አይነት እምነት አሁንም ራቅ ራቅ በሚሉ ዘመናዊ ሥልጣኔ ባልተዳረሰበት አካባቢ ይንጸባረቃል" (ዘብዴዮስ፣2012፣ገ.427) ። በወላይታ ውስጥ ከሚገኙት ጎሳዎች መካከል አንዳንዶቹ የሀገረሰባዊ አምልኮ ተከታዮች የነበሩ ሲሆን ይህም በሰንጠረዥ ቀጥሎ ቀርቧል ።

ሰንጠረዥ 1 የሀገረሰባዊ አምልኮ ስያሜዎች

| ተ.ቁ | የጎሳዎቹ ስም | የሀገረሰባዊ እምነት |
|---|---|---|
| 1 | ወምግራ | ሀምዛ |
| 2 | ቡቡላ | ሙሉ ጉሾ |
| 3 | ዛምባቻ | ሀውዙሎ |
| 4 | ወሺሻ | ኢንግላላ |
| 5 | ዛቷ | አቦርዴ |
| 6 | ኦዶ | ደዳ (መብረቅ) |
| 7 | ቃሊቻ | አሼዋሳ ሳጋኖ |
| 8 | ዶንጋ | ቃይዳራ |
| 9 | ዛምኔ | ገመነ |
| 10 | ቦሮዳ | ዋሊለ |

(ዘብዲዮስ፣ 2012፣ገ.25)

### 4.7.የህዝቡ መተዳደሪያ፣ መሰረተ ልማት እና ማህበራዊ አገልግሎት

የወላይታ ማህበረሰብ ኢኮኖሚ የተመሰረተው በጥምር ግብርና ሲሆን እንደ አገዳ ተክሎች፣ ስራስሮች፣ ጥራጥሬዎች፣ አትክልት፣ ፍራፍሬ፣ ጥጥ፣ የቅባት እህሎች፣ ቡና፣ቅመማቅመም እና የእንሰት ተክሎች በወላይታ ዞን ውስጥ በቋሚነት ይተከላሉ ። የእንስሳት ግብዓትን በሚመለከት ማህበረሰቡ የዳልጋ ከብቶች፣ ትናንሽ የቤት እንስሳትን እና ዶሮ ያረባሉ:: በወላይታ ዞን ውስጥ የተለያዩ የመሰረተ ልማት አውታሮች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም የአውቶማቲክ ስልክ፣ የፖስታ፣ የባንክ፣ የፋይናንስ፣ ብድር እና ቁጠባ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት በከተሞች አካባቢ ይገኛሉ (የሰሜን ኦሞ ህዝቦች ታሪክ፣11) ።

### 4.8. የወላይታ ብሔረሰብ ታሪካዊ ቅርስ፣ ቱሪዝምና ባህላዊ ተቋማት

የወላይታ ሕዝብ የበርካታ ታሪካዊ እሴቶች የሰው ሰራሽና ተፈጥሯዊ ቅርሶች ባለቤት ነው ። ከነዚህም መካከል የጥንት ሰው መኖሪያ የሆኑት የሞቼና ቦራጎ ዋሻ፤ የአሩጂያ ዋሻ ትክል ድንጋዮችና የተፈጥሮ ፏፏቴዎች በስሩ ይገኛሉ ። በተጨማሪም ባህላዊ የዳኝነት፣የአለባበስ፣የአመጋገብ፣ሥርዓቶች ባለቤት ሲሆን ዓመቱን ሙሉ የሚፈሱ ወንዞች፤ የመዝናኛ ቦታዎች፤ፍል ውሃዎች፤ ይገኙበታል (የወላይታ ብሔር ባህላዊ ተምሳሌቶች ፕሮፋይል፣ገ.2፣2010 ዓ.ም) ።

በወላይታ ዞን ለቱሪስት መስህብ የሆኑ ቦታዎች ሞቾና ቦራጎ (Mochena Borago) ፣የሃሩና ዋሻ (Cave, Harurona) የአሩጂያ ዋሻ (Cave, Arujiya) ፣ የአጀራ ፏፏቴ፣የዳሞት ተራራ፣ ኦሞ ሰው ሰራሽ (Monastry), ሶዶ ሙዚየም (Abera,& Gobeze,2020 P,8-21) : :

“የወላይታ ብሔረሰብ ሲመራባቸውና ለዘመናት ጠብቆ ያቆያቸው ባህላዊ ተቋማት፤ እሴቶች እና የእምነት ሥርዓቶች ያሉት ሲሆን ከነዚህም መካከል ለአብነት ባህላዊ አስተዳደር፣የግጭት አፈታት፣ባህላዊ የቤት አሰራር፣የሙዚቃ መሳሪያዎች፣ባህላዊ አለባበስና አጊያጌጥ፣የዘመን አቆጣጠር ቀመር፣የዘመን መለወጫ፣የለቅሶ ሥርአት፣ባህላዊ የከብት ቆጠራ ሥነ ስርአት የሚጠቀሱ ናቸው” (የወላይታ ብሔር ባህላዊ ተምሳሌቶች ፕሮፋይል 2010ዓ.ም፣ገ.2) ።

### 4.9. የወላይታ ብሔረሰብ የጋብቻ ሥርዓት

እንደየብሔረሰቡ ባህልና ሐይማኖት ሥርዓት ይለያይ እንጂ ጋብቻ የተፈጥሮ ህግ በመሆኑ በማንኛውም ማህበረሰብ የሚፈጸም ተግባር ነው ። ቀደም ሲል በወላይታ ብሔረሰብ ጋብቻ በስድስት ዓይነት መንገድ ይፈጸማል ። እነዚህም ፓራ ፣ላታ፣ ላባ፣ ዳፋ፣ ሚሸቹዋ፣ አካንቷ ሰርግ (ቡላቻ) በመባል ይታወቃሉ (ቃለመጠይቅ፣ ኢዩኤል ፣ህዳር14/2015) ።

ጥንት በወላይታ ብሔረሰብ ለጋብቻ የደረሰው ወንድ ልጅ ቤተሰብም ሆነ ወንዱ ልጅ ለጋብቻ የምትሆነውን ልጃገረድ ካገኙ በኋላ በመጀመሪያ የልጅቷ ቤተሰብ ለጋብቻ የሚመጥኑ መሆናቸውን በጎሳ በእናትም ሆነ በአባት በኩል እስከ ሰባት ትውልድ ተቆጥሮ ዝምድና የሌላቸው መሆኑ ይረጋገጣል ። ቀጥሎ ሽማግሌዎች ከሦስት ሳምንት እስከ አንድ ወር ድረስ በተከታታይ ለሦስት ጊዜ ማክሰኞ እለትን ጠብቀው ይሄዳሉ ። በዚህም የራሱ ቅደም ተከተል አለው ። የልጅቷ ቤተሰብ ሽማግሌዎችን ወደ ቤት አስገብተው በሚቀበሉበት ቀን ከልጅቷ ዘመዶች የተለያዩ ጥያቄዎች ለልጁ ዘመዶች የሚቀርቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የልጁ መተዳደሪያና የራሱ ቤት አለው የሚሉት ዋነኞቹ ናቸው (ቃለመጠይቅ ኢዩኤል፣ህዳር14/2015)

- **ቅድመ ጋብቻ**

በባህሉ አንድ ሰው ቤት ለመስራት እንዲነሳሳ መነሻ የሚሆኑ የተለያዩ ምክንያቶች ያሉ ሲሆን ከነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በኋላ ትዳር መስርቼ በራሴ ቤት መኖር አለብኝ ብሎ ሲወስን በባህሉ መለስተኛ የተባለውን ቡራሪያ ቤት ይሰራል (ቃለመጠይቅ ኢዩኤል ሔራሞ፣ህዳር14/2015 ዓ.ም) ።

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሲሳይ ደግሞ በብሔረሰቡ ቤትን የሚሰሩት በጾታ ደረጃ ሲታይ ወንዶች ሲሆኑ ቤት ለመስራት አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ መጀመሪያ ቤት ለመስራት ይወስናል፤ይህንንም ቤት ልጁ እራሱ ይህ ካልሆነ ደግሞ አባቱ ብቻውን ወይም አባትና ልጅ ተባብረው ይሰራሉ (ቃለ መጠይቅ፣ህዳር12/2015 ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት እንደተቻለው ጋብቻ ከቤት ስራ ጋር የሚገናኝ ሲሆን ይህም በብሔረሰቡ አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በኋላ ትዳር ለመመስረት ሲያስብ በመጀመሪያ ቤት መስራት አለበት ። ለዚህ ምክንያቱ ልጃችሁን ለልጃችን በማለት ለመጠየቅ ለሄዱ ሽማግሌዎች ከልጅቷ ዘመዶች የተለያዩ ጥያቄዎች ለልጁ ዘመዶች የሚቀርቡ ሲሆን ከነዚህም መካከል የመጀመሪያዎቹ የራሱ የሆነ ቤት አለው ? መተዳደሪያው ምንድነው ? የሚሉት ዋነኞቹ እንደሆኑ ነው የተገለጸው ።

በወላይታ ብሔረሰብ አንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሚስት ለማግባት ሲያስብ በመጀመሪያ ቤት መስራት አለበት ፡፡ በባህሉ መሰረት ለትዳር የደረሰች ሴት ልጅን ለማግባት የሚፈልግ ሰው ሲመጣ የልጅቷ ወላጆች የሚያገባት ልጅ የራሱ ቤት ከሌለው በጋብቻው አይስማሙም (ቃለ መጠይቅ፣ማተቤ፣ህዳር18/2015ዓ.ም) ፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ ከሚካሄዱ ስድስት የጋብቻ አይነቶች መካከል ልጃችሁን ለልጃችን በማለት ለመጠየቅ ለሄዱ ሽማግሌዎች ከልጅቷ ዘመዶች የተለያዩ ጥያቄዎች ማለትም እንደ የራሱ የሆነ ቤት አለው ? የሚል ጥያቄ የሚቀርብባቸው ጋብቻዎች ፓራ፣ሚሽቹዋ እና አካንቷ የተባሉ የጋብቻ ዓይነቶች ሲሆኑ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በእነዚህ ሥርአቶች የተጋቢዎቹ ቤተሰቦች ከተስማሙ በኂላ የሽማግሌ መላክ ሥነ ስርአት ስላለበት በዛውም የተለያዩ ጥያቄዎች ስለሚነሱ ነው ፡፡

## ምዕራፍ አምስት

# የወላይታ ብሔረሰብ ቤት ውክልና እና ባህላዊ የቤት አይነቶች

በዚህ ምዕራፍ ስር ቤት ምንነቱና ውክልናው፤ከቤት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፤የወላይታ ባህላዊ ቤት አይነቶች፤የጉላንታ ቤት ባህላዊ ተምሳሌቶች፤የመስክ መረጃዎች የጥናቱን ዓላማዎች፣ጽንሰ ሀሳቦች መሰረት አድርገው በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ፤ በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፤ በሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብ፤እንዲሁም በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ተግባራዊ ሆነው እንደሚከተለው የቀረቡ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ በSchlereth (1985, p. 24) የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች መሰረት መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

### 5.1. የቤት ምንነትና ውክልና በወላይታ ብሔረሰብ

የአንድ ህዝብ ማንነቱ (ህይወቱ) የሚመሰረተው እና ሀብቱ የሚደራጀው  በቤቱ ላይ በመሆኑ ለወላይታ ብሔረሰብ ቤት ማንነቱና መለያው  ነው፤‹‹እገሌን አይታችኋል ሳይሆን›› የእገሌን ቤት አያችሁ››ነው የሚባለው ፡፡ ብሔረሰቡ ለቤት ያለው አመለካከት ከፍ ያለ በመሆኑ “ለወፍ እንኳን ጎጆ አለው”፤ “አይጥ እንኳን በድንጋይ ክምሮች ውስጥ ቤት አላት” ይላሉ ፡፡ ቤት ለወላይታ ብሔረሰብ የሚከበርበትና የሚወደስበት የኑሮው መሰረት ነው ፡፡

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ አየለ በወላይታ ብሔረሰብ ቤትና ህይወት(ኑሮ) የማይነጣጣሉ መሆናቸውን ሲገልጹ በወላይታ ባህል ቤትና ህይወት  የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ ህዝቡ ቤትን እንደ ሁሉ ነገሩ ነው የሚያየው ፡፡ ወላይታዎች ሁሉም ነገር ከቤት ቀጥሎ ነው ብለው ስለሚያምኑ መጀመሪያ የሚሰሩት ቤት ነው ፡፡  ወንዶች ቤት ሳይሰሩ ለትዳር ሚስት አያጩም ፡፡ ኑሮ የሚመሰረተው ቤት ሲኖር ነው ፡፡ አንድ ሰው ኑሮ አለው ሲባል ቤት አለው ነው የሚባለው ፡፡ በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ማለት ትልቅ ትርጓሜ ያለው ሆኖ ከህዝቡ ማንነትና ኑሮው ጋር የተገናኘ ነው[5] ፡፡

[5] ቃለ መጠይቅ ሲሳይ፣ሶዶ ዙሪያ፣ህዳር 12፣2015ዓ.ም ፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ማለት ትልቅ ትርጓሜ ያለው ሲሆን በዚህም የህዝቡ ማንነት መገለጫ ተደርጎ ይታያል ። ሌላው ቤት ማለት በወላይታ ህዝብ ትልቅ ክብር የሚሰጠው የግለሰቡ መገለጫና መወደሻው እንደሆነ ነው ።

በተመሳሳይ መልኩ በወላይታ ብሔረሰብ ቤትና ኑሮ የማይነጣጣሉ መሆናቸውን ሲያስረዱ በባህሉ ቅድሚያ የሚሰጠው ቤት በመሆኑ መጀመሪያ ቤት መሰራት አለበት ። ሁሉም ነገር ከቤት ቀጥሎ ነው መከናወን ያለበት ብለው ያምናሉ ። ከዚህ የተነሳ ወንዶች ቤት ሳይሰሩ ለትዳር ሚስት አያጩም አባትም ልጄን ልድረው ስላሰብኩ ቤት እየሰራሁ ነው በማለት ቤት ከሁሉም ነገሮች መቅደም እንዳለበት ያስረዳል ። ኑሮ የሚመሰረተው ቤት ሲኖር ነው፤አንድ ሰው ኑሮ አለው ሲባል ቤት አለው ነው[6] ።

ቤት ማለት ለወላይታ ሁሉ ነገሩ ሲሆን ይህም ቤት ለህዝቡ ኑሮው፣ትዳሩ፣ማንነቱ ነው። ሌላው በባህሉ ቤት ቅድሚያ የሚሰጠው በመሆኑ የወላይታ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ደርሶ ሚስት ለማጨት ቤት መስራት አለበት ተብሎ ይታሰባል፤ሌላው አባት ልጁን መዳር ሲፈልግ አስቀድሞ ለልጁ ቤት ይሰራል ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ ቤት ከአካላዊ መጠለያነት ባሻገር፣ የማህበረሰቡ መሰረት እና የማንነት መገለጫ ሲሆን የማህበራዊና ባህላዊ ማዕከል ነው ። የቤተሰብ ማዕከል ፦ የቤተሰብ አባላት የሚገናኙበት፣ የሚወያዩበት፣ የሚተሳሰቡበት እና ትውልድ የሚተካበት ዋና ስፍራ ሆኖ የዕለት ተዕለት ኑሮ፣ ምግብ የሚዘጋጅበት እና ማህበራዊ መስተጋብር የሚከናወንበት ነው ። የማንነት መገለጫ ፦የቤቱ አሰራር፣ የውስጥ ቁሳቁሶች አደራደር፣ ጌጦች እና አጠቃላይ ይዘቱ የባለቤቶቹን እና የማህበረሰቡን ማንነት፣ እምነት እና ማህበራዊ ደረጃ ያንጸባርቃል ። ለምሳሌ፣ የሀረሪ ባህላዊ ቤት የውስጥ አቀማመጥ የቤተሰቡን ማህበራዊ ህይወት እና እንግዳ አቀባበል ባህል በግልጽ ያሳያል ፤የደህንነትና የመረጋጋት ስፍራ ፦ አካላዊ ጥበቃ ብቻ ሳይሆን ስነ-ልቦናዊ ደህንነትንና የመረጋጋት ስሜትን ይሰጣል ። "እንደ ቤት የለም" የሚለው ብሂል ይህንን ስሜት ይገልጻል ፤የትውስታ እና ቅርስ ማከማቻ ፦ የቤተሰብ ታሪክ፣ ትውስታዎች እና ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚተላለፉ ቅርሶች (ቁሳዊ እና መንፈሳዊ) የሚከማቹበት ህያው ሙዚየም ነው (Unesco, 2006) ::

የቀረበው መረጃ በሞዴል ሲቃኝ ጠቀሜታዊነት (Functionalist) ቁሶቹ ለምን ለምን ተግባራት ይውላሉ? የቁሶቹ ተጠቃሚዎች ለቁሶቹ ያላቸው አስተሳሰብና ጠቀሜታ እንዲሁም የቁሶቹ አገልግሎት

---

[6]. ቃለ መጠይቅ፣ዳውሎስ አሳሮ 15/09/2014ዓ.ም እና ታደሰ ኦይራ ኦፋ፤06/09/2014ዓ.ም፣ቃለ መጠይቅ

የማህበረሰቡን የህይወት ፍልስፍና እንዴት ይገልጻሉ የሚሉ ጥያቄዎች ይመረመርበታል (Schlereth, 1985, p. 24) ፡፡

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሲሳይ ኩማ ቤትና ጋብቻን በሚመለከት ሲገልጹ በወላይታ ባህል አንድ ሰው ቤት(ጎጆ) አቆመ፤ጎጆ ወጣ፤ቤት ኖረው ሲባል ትዳር መስርቶ እራሱን ችሎ ኖረ ማለት ሲሆን አንድ ወንድ ልጅ ቤት የሚሰራው ትዳር ለመመስረት ነው፤ስለዚህም ቤትና ጋብቻ በባህሉ አቻ የሆነ ትርጓሜ አላቸው፤ቤት ለህዝቡ የሰውነትን ቁመና ያሳያል ተብሎ ይታሰባል፤ ሲነገር እንኳን በቤቱ ያደረ ሰው ነው ይባላል፤ አንድ በሰራው በራሱ ቤት የሚኖር ወጣት ሲያልፍ ከሱ በእድሜ የሚበልጡ ሰዎች እንኳን ብድግ ብለው ይቀበሉታል፤ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በቤቱ፣ያደረ፣በርስቱ የሚኖርና እራሱን የሚያስተዳድር ነው በሚል ክብር ይሰጠዋል፤በጥሩ እንዲታይ ያደርገዋል ፡፡ ቤት በብሔረሰቡ ጥሩ ከበሬታንና ጥሩ ሰብእናን የሚያሰጥ ነው[7]፡፡

## 5.2. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አይነቶች

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አይነቶች፤ ዙፋ(Zuufaa)፣ ሜሹዋ (Meeshshuwa)የሜሹዋ ቤት ውጫዊ ገጽታ፤የሜሹዋ ቤት ውስጣዊ ገጽታ፤ ቡራሪያ (Buraariyaa ጉላንታ(Gulantta) የጉላንታ ባህላዊ የቤት አሠራርና በውስጡ የሚካተቱ ነገሮች፤የጉላንታ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ፤የጉላንታ ቤት ውጫዊ ገጽታ እንዲሁም ቦታ መረጣ፤ ግርግዳ ሥራ፤የጣሪያ ሥራ፤የባህላዊ ቤት ምሰሶና ጣሪያው፤ የበር መቃን ሥራ፤የቤት ክዳን ሥራ፤የቤት ውስጥ ክፍፍል ቀርበዋል ፡፡ በተጨማሪም የወላይታ ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት የሚቀርቡ ምግቦች፤የአመጋገብና የአጠጣጥ ስርዓቶች፤የወላይታ ጉላንታ ባህላዊ ቤት ተምሳሌቶች፤ከቤት ምንነትና ስራ ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምሳሌያዊ አነጋገሮች፤የወላይታ ባህላዊ ቤት ሙያተኞች እና የእውቀት ሽግግር፤የወላይታ ብሔረሰብ የቤት አሰራር እውቀት ተስተላልፎ እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

ሌላው በዚህ ጥናት የቀረቡትና ትንታኔ የተሰጠባቸው የቤት አይነቶች አራት ናቸው ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ይህ ጥናት ሰፊ ስለሆነና ከብዛታቸው የተነሳ የተለየ መረጃ ያመጡ ይሆናል ከሚል እምነት ነው ፡፡ እነዚህም የመስክ መረጃዎች በተመረጡት ንድፈ ሀሳቦችና ሞዴሎች ተግባራዊ ሆነው መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አይነቶችን በተመለከተ የተለያዩ አተያዮች እንዳሉ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ያመለክታሉ ፡፡ በባህሉ ቁጥራቸው ከፍ ያሉ መረጃ ሰጪዎች አራት አይነት ቤቶች እንዳሉ

---

[7] . ቃለ መጠይቅ፣ህዳር12፣2015ዓ.ም፣

ሲገልጹ የተወሰኑት ደግሞ አምስት አይነት ቤቶች መኖራቸውን ጠቁመዋል ። ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል ።

የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት አይነት መሆናቸውን፤ስለአሰራራቸው፤ስለሚሰሩበት ግብአትና ቦታ በተመለከተ አቶ ኢያሱ ሲገልጹ የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት አይነት ሲሆኑ እነዚህም ዙፋ፣ሜሹዋ ጉላንታ እና ቡራሪያ ተብለው ይጠራሉ ። አራቱም የቤት አይነቶች ከውጪ አከዳደናቸው ተመሳሳይ ሆኖ ውስጣቸው ይለያያል ። ሜሹዋ ሁለት አይነት ሲሆን ዲሌማ ሜሹዋኔ እና ሌጋማ ሜሹዋ ተብለው ይጠራሉ ዲሌማ ሜሹዋ ከመሬት እስከ ጣሪያ ድረስ ምንም አይነት ክፍተት ሳይኖረው ግጥምና ችምችም ተደርጎ ይሰራል ። ዙፋ ቤት ቆላማ አካባቢ የሚሰራ ሆኖ አመጋገሩ በግማሽ ጨረቃ መልክ ነው ። ምክንያቱም ለቤቱ አመጋገር የሚመቹ እንጨቶች የሚገኙት በቆላማ አካባቢ በመሆናቸው ነው ። ለዙፋ ቤት የሚሆኑ ለማገር ወሳኝ የሆኑት ሀማካ፣ ሻቺንቹዋ በተባሉ እንጨቶች ለማገር አገልግሎት መዋላቸውና መገኘታቸው ቤቱ እንዲመረጥ ያደርገዋል ። ሌጋማ ሜሹዋ በቆላና በደጋ አካባቢ ሊሰራ የሚችል ሆኖ ከጣሪያ ወረድ ብሎ አንድ ክፍተት አለው ። ለዚህ ምክንያቱ ቤቱ ውበት እንዲኖረውና የአሰራር ደንቡ እንደሆነ ከመስክ መረጃዎች መረዳት ተችሏል ። ጉላንታ ወይናደጋ አካባቢ የሚሰራ ሲሆን ዘጠኝ ክፍተት ያለው ቤት ነው ። ዘጠኝ ክፍተቶች የኖሩበት ምክንያት አንደኛው ለውበት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ እቤት ውስጥ የገባ ሰው ቤቱን በሚያይበት ጊዜ ልክ መሬት የምትዞር እንዲመስል ታስቦ ነው ። ወደ ጣሪያው ሲታይ ከዋክብቶች እዛ ቦታ ላይ ችፍ ብለው የተቀመጡ ይመስላሉ ። ቡራሪያ የሚባለው ቤት አቅም የሌላቸውና ወጣቶች የሚሰሩት ቤት ሲሆን ማገሩ ዘርዘር ተደርጎ ነው የሚሰራው (ቃለ መጠይቅ፣ጥር15፣2014.ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው መረጃ ጋር በተመሳሳይ ሁኔታ እንደ አቶ አማኑኤል አይዴ ገለጻ ደግሞ የወላይታ ብሔረሰብ የቤት አሰራር አይነቶች አራት ናቸው ። የመጀመሪያው ሜሾ ጋቾ ቤት የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ድግሞ ጉላንታ ጋቾ ቤት ይባላል ። የጉላንታና የሜሾ ሁለት የቤት አይነቶች አንድ ወንድ ሚስት አግብቶ ሁለት፣ሦስትና አራት ልጆች ከወለደ በኋላ በቂ ዝግጅት አድርጎ የሚሰራቸው ናቸው ። ሦስተኛው የቤት አይነት ደግሞ ዙፋ ተብሎ ይጠራል ። አራተኛው ቡራሬ ጋቾ ቤት የሚባለው ሲሆን ይህም አቅም ያለው ሰው ሚስት ሳያገባ አስቀድሞ ሊሰራ የሚችለው የቤት አይነት ነው ። እነዚህ አራቱ የቤት አሰራር አይነቶች በጊዜ እርዝማኔ፤በስፋትና በአሰራራቸው የሚለያዩ ሲሆን ይህም ለቤቱ አሰራር በሚሰጠው ጊዜ፣ ስፋትና ብዛት ይወሰናል ። ከዚህ በተጨማሪ በመስሪያ ግብአቶችም ይለያያሉ ። ለአብነት ቡራሪያ የቤት አይነት በተገኙት የእንጨት አይነቶችና ሽምበቆ ሊሰራ የሚችል ሲሆን ዙፋ ቤት ሀማካና ሻቺንቹዋ በተባሉ እንጨቶች ለማገር አገልግሎት በመጠቀም

ይሰራሉ ፡፡ የቦታ አቀማመጣቸውም ይለያያል፤አራቱም የቤት አይነቶች የተለያየ የቤት አሰራር ስልት አላቸው (ቃለ መጠይቅ፣ጥር 20፣ 2014ዓ.ም) ፡፡

አቶ ኤርሚያስ ጎበና እንደነገሩኝ የወላይታ ብሔረሰብ የቤት አይነቶች አራት ሲሆኑ እነሱም ዙፋ፣ሜሾ፣ጉላንታና ቡራሪያ ተብለው ይጠራሉ ፡፡ እነዚህ ቤቶች ከውጭ ሲታዩ ተመሳሳይ ሆነው ውስጣዊ አሰራራቸው የተለያየ ነው ፡፡ ሌላው የመስሪያ ግብአታቸውም የተለያየ ነው (ቃለ መጠይቅ፣የካቲት5፣2014ዓ.ም) ፡፡

ከላይ የቀረቡት መረጃዎች በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኙ ቤት የባህል አንዱ ክፍል ሆኖ በቅርጹ እና በቦታ አቀማመጡ ባህላዊ እምነቶችን እና ልማዶችን የሚያንፀባርቅ ነው (Homoud, 2009) ፡፡ ሌላው (Rapoport, 1991) ከተለያዩ ባህሎች የመጡ ሰዎች የመኖሪያ ቦታቸውን ቅርጽ የሚነድፉት ከማህበራዊና ባህላዊ ፍላጎቶቻቸው ጋር በሚስማማ መልኩ እንደሆነ ገልጸዋል፡፡ የቤቶቹ በቁጥር የተለያየ መሆን ደግሞ የማንኛውንም የቤት ቅርጽ ጥራት ከማህበራዊ ባህል ፍላጎቶች አንጻር ሊገመገም ይችላል ይላሉ ፡፡ የወላይታ ብሔረሰብ የቤት አይነቶች ቁጥር በብሔረሰቡ የኢኮኖሚ ደረጃ ማህበራዊና ባህላዊ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ እንደሆነ መረዳት ተችሏል ፡፡

ከስር በፎቶ ላይ የሚታዩት አቶ ኦልኬ ታንቱ እንደነገሩኝ "በወላይታ ነባር የሆኑና በባህላዊ እውቀት የሚሰሩ አምስት አይነት ቤቶች ያሉ ሲሆን እነሱም፡- "Zuffa"ዙፋ፣"Dilima-Meshuwa"ዲሊማሜሹዋ፣ "Legama-meshuwa"ሌጋማሜሹዋ "Gulanta" ጉላንታ፣ "Buraria" ቡራሪያ ተብለው ይጠራሉ" (ቃለ መጠይቅ፣2014 ዓ.ም) ፡፡

በተመሳሳይ ወ/ሮ ባሎሜ አንጁሎ እንዳስረዱኝ በወላይታ ብሔረሰብ ዙፋ፣ዲሊማ ሜሹዋ፣ሌጋማ ሜሹዋ፣ጉላንታና ቡራሪያ ተብለው የሚታወቁ አምስት የቤት አይነቶች ይገኛሉ ፣ቃለ መጠይቅ፣2014 ዓ.ም) ፡፡

**ፎቶ 4፡- ቃለመጠይቅ ከመረጃ አቀባይ ጋር**



**ምንጭ፡-ኪንዶ ዲዳዬ፣ በአጋዥ ፎቶ አንሺ በ2014ዓ.ም የተነሳ**

የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አምስት አይነት ሲሆኑ እነሱም ዲሊማሹዋ፣ሌጋማሜሹዋ፣ዙፋ፣ጉላንታና ቡራሪያ ተብለው በአምስት የሚከፈሉ ሲሆን አሰራራቸውም ኢኮኖሚንና የአየር ንብረትን መሰረት ያደረጉ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ሸዋዬ፣የካቲት 10፣2014ዓ.ም) ፡፡

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በመስክ ቆይታ ወቅት ቃለ መጠይቅ ካደረግኩላቸውና በቤቶቹ አይነቶች ዙሪያ መረጃ ከሰጡኝ ሰዎች መካከል ብዙዎቹ የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት እንደሆኑ የገለጹ ቢሆንም የተወሰኑ ግለሰቦች ደግሞ ዙፋ (Zuffa)፤ዲሊማ ሜሹዋ (Dilima-Meshuwa) ሌጋማ ሜሹዋ (Legama-meshuwa)፤ጉላንታ (Gulanta) እና ቡራሪያ (Buraria) ተብለው በአምስት እንደሚከፈሉ መረጃ የሰጡ ቢሆንም አራት ናቸው ያሉት ኢያሱ ጋጃቦ፣ አማኑኤል አይዴ እና አቶ ኤርሚያስ ሁለቱ የሜሹዋ አይነቶች በሜሹዋ ውሰጥ ስለሚካተቱ እንደ አንድ ይቆጠራሉ በማለት ሲገልጹ አምስት ናቸው የሚሉት ደግሞ በሜሹዋ ቤት ውስጥ የተካተቱትን ሁለቱን ለየብቻ በመቁጠር ነው ፡፡ የቡድን ሁለት ተወያይ የሆኑት አቶ ኢያሱ ገጃቦና አቶ ታደሰ

ኮይራ የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት አይነት ሆነው ከውጭ ሲታዩ ተመሳሳይ ቢሆኑም ውስጣዊ አሰራራቸው የተለያየ እንደሆነ ገልጸዋል ።

በዚህ ንዑስ ምዕራፍ ስር የቀረቡት የቤት አይነቶች ቅደም ተከተላቸውም ውበትን፣ ኢኮኖሚን፣ የአየርን ንብረትንና ፍላጎትን መሰረት ያደረጉ ናቸው ።

ቤት የሚገነባው እንደ ነዋሪዎቻቸው ፍላጎት ነው (Alitajer & Nojoumi, 2016) ። አካላዊ ቅርፁ፣ማህበራዊ እና የቦታ አደረጃጀቱም በብዙ ምክንያቶች ባህላዊ ተጽእኖ ይደረግበታል (Hashim, Ali, & Abu Samah, 2009) ። በቦታ አደረጃጀት ውስጥ ያለው ተዋረድ እንደ አካባቢ እና ማህበረ ባህላዊ ሁኔታዎች ሊቀረጽ ይችላል (Shirazi, 2005) ፡፡ ባህላዊ ቤት በአየር ንብረት፣ በአካባቢያዊ ቁሳቁሶች፣በኢኮኖሚ ደረጃ፤ በማህበረ ባህላዊ ባህሪያት እና በባህላዊ ቴክኖሎጂ ተቀርጾ በአካባቢው ሰዎች ተግባራዊ የሚደረግ የባህላዊ ምህንድስና ክፍል ነው (Upadhyay, Yoshida, and Rijal, 2006)፡፡

በምዕራፍ አራት እንደተገለጸው የወላይታ ዞን በ 7$^0$ ሰሜን እና 37$^0$ 45 ምስራቅ ላይ የሚገኝ አካባቢ ነው። የወላይታ ዞን መሬት አቀማመጥ በአብዛኛው ሜዳማ፣ አልፎ አልፎ ግን ጉብታዎችና ተራሮች ያሉበት ነው ። ወላይታ ሶስት የአየር ንብረቶች ያሉት ሲሆን እነዚህም ደጋ፣ ወይና ደጋና ቆላ በመባል የሚታወቁ ናቸው ። የዞኑ አብዛኛው ክፍል ወይና ደጋ ሲሆን በስምጥ ሸለቆ ውስጥ የሚገኙ ቦታዎች ደግሞ ቆላማ ሲሆኑ በከፍተኛ ቦታዎች የሚገኙት ደግሞ ደጋማ ናቸው የወላይታ ብሔር ባህላዊ ተምሳሌቶች ፕሮፋይል(2010) ። ሌላው በምዕራፍ ሁለት በጽንሰ ሀሳብ ስር እንደተገለጸው "ቤት ከእንጨት ወይም ከድንጋይ ወይም ከጡብ……የሚሰራና ለተለያየ አገልግሎት፣ ለሰው ወይም ለእንስሳት መኖሪያ፣ለዕቃ ማስቀመጫ የሚውል ዙሪያው በግድግዳ፤ ላዩ በጣሪያ የተከለለ መጠለያ፣ጎጆ፣ሳር ቤት፣ቆርቆሮ ቤት፤ ህንጻ…. የሚይዝ ነው" (የአማርኛ መዝገበ ቃላት፣1993፡ገ.241) ። ይህ ደግሞ የኢኮኖሚ ደረጃን መሰረት ያደረገ መሆኑን ያሳያል ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው ቤት በጭቃ፣ በጭድ፣ በሰንበሌጥ፣ ሳር ወዘተ. የሚሰራ ሆኖ ለሰውና ለእንስሳት መኖሪያ የሚያገለግል ነው ። ከዚህ በተጨማሪ በአብዛኛው የተለያዩ መኖሪያ ቤቶች እንደየግንባታ ጥራት ደረጃቸው ፤ እንደ የግንባታ ቁሳቁስ ዓይነታቸው፤ እንደ ኢኮኖሚ ደረጃቸው የተለያዩ እንደሆኑ ተገልጿል ። አክለውም በሶዶ ዙሪያ የቡድን አንድ ተወያይ የነበሩት አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት አይነት መሆናቸውን ነው ።

### 5.2.1. ዙፋ (Zuufaa)

**ዙፋ ቤት (Zuufa keettaa) :-** የመጀመሪያው የወላይታ ባህላዊ ቤት ዙፋ ይባላል ። ይህ ቤት በውበቱ በብሔረሰቡ ዘንድ ተመራጭ ነው ። ውስጣዊ አሠራሩ በግማሽ ጨረቃ ቅርጽ ሆኖ ከታች ከወለሉ ጀምሮ እስከ ላይ ጣሪያ ማዋቀሪያው ድረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ይማገራል ። የዙፋ ቤት በአብዛኛው የማገሩ ማሠሪያ ሀረግ ነው። ቤቱ ቆላማ የአየር ንብረት ባላቸው አካባቢዎች ይሰራል ። ሌላው በጥራት የሚሠራ ከመሆኑም ባሻገር ለረዥም ጊዜ ይቆያል[8] ።

የዙፋ ባህላዊ ቤት በብሔረሰቡ ዘንድ ተወዳጅ የሆነ የቤት አይነት ነው ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቤቱ ከአሰራሩ ጀምሮ ውበት እንዲኖረው ታስቦ ስለሚሰራ ቤቱ በጣም ያማረ ነው ። ሌላው በባህሉ ቤቶች ሲሰሩ ውበትን ፤የአየር ንብረትን፤ የኢኮኖሚ ደረጃንና ፍላጎትን መሰረት አድርገው ስለሆነ ቤቱ በሰሪዎቹ ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ነው።

**ፎቶ 5፡- የዙፋ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ**



[8]. ቃለ መጠይቅ፣ ኢያሱ፣06/09/2014 ዓ.ም፤ቃለ መጠይቅ፣ ኢሳያስ፣06/09/2014 ዓ.ም

ምንጭ፡-ሶዶ ዙሪያ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣11/11/2014

### 5.2.2. ሜሾ ቤት (Meeshsho keettaa)

ሁለተኛው የወላይታ ባህላዊ ቤት ሜሹዋ ይባላል ፡፡ ይህ ቤት በውበት፣በጥራትና በጥንካሬ በሁለተኛ ደረጃ የሚመደብ የቤት ዓይነት ነው ፡፡ የቤቱ ውስጣዊ አመጋገር ከታች እስከ ላይ ጣሪያ (Kaaraa) ድረስ ጥቅጥቅ ብሎ የሚሰራ ነው ፡፡ ግድግዳው ከወይራ ፍልጥና ጉጋንታ(Guuganttaa) ከሚባል ጠንካራ የበረሃ እንጨት ይሰራል ፡፡ ይህ ቤት ሌጋማ ካራ(leegaama kaaraa) በተባለው የጣሪያ ዓይነት የሚሰራ ሆኖ የውስጥ ማገሮቹ ሰንሰለትና ዛጎል (maccamiya yelelluwaa) አስተሳሰር ቅርጽ ያለው ሆኖ ከላይ እስከ ታች መሬት ድረስ በቀጥታ መስመር ይወርዳል ፡፡[9]

ሜሾ ቤት በቆላና በደጋ አካባቢ ሊሰራ የሚችል ሆኖ ከጣሪያው ወረድ ብሎ አንድ ክፍተት አለው፡፡ አመጋገሩም ከታች እስከ ላይ ጣሪያው (kaaraa) ውቅር ድረስ ጥቅጥቅ ተደርጎ የሚሠራ ነው፡፡ ግድግዳው ከወፍራም ፍልጥ ወይም (Guganttaa) ከሚባል ጠንካራ የበረሃ እንጨት እና ቀጫጭን ወራጅ (Pariyaa) የሚሠራ ነው ፡፡ ይህ ቤት (hegaama kaaraa)በተባለ የጣሪያ ዓይነት የሚሠራ ሆኖ (meshuwaa keettaa) ውስጥ አመጋገሩ ሰንሰለታማ ዛጎል (maccamiyaa yelelluwaa) አስተሳሰር ስልት በመከተል ከላይ እስከ ታች መሬት ድረስ በቀጥታ መስመር ይወርዳል ፡፡ ጠንካራና ውበት ያለው ቤት ነው ፡፡

የኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ ሲገልጹ የሜሾ ባህላዊ ቤት በቆላና ደጋ የአየር ንብረት የሚሰራ ሆኖ አሰራሩም ጥቅጥቅ ያለ ነው ፡፡ ግድግዳው ከወፍራም ፍልጥ፣ ጠንካራ የበረሃ እንጨት እና ቀጫጭን ወራጅ (Pariyaa) የሚሠራ ሆኖ አመጋገሩም ሰንሰለታማ የዛጎል ቅርጽ አስተሳሰር ያለው ነው ፡፡

**የወላይታ  ሜሹዋ ቤት ውጫዊ ገጽታ**

ቀጥሎ የቀረበው  ፎቶግራፍ የሜሹዋ  ባህላዊ ቤት ውጫዊ ገጽታን የሚያሳይ ነው ፡፡

---

[9] ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣አፋ፣06/09/2014 ፡፡

ፎቶ 6፡- ሜሹዋ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ገጽታ



ምንጭ፡-ሶዶ ዙሪያ፣በጋሸ ዘብዲዮስ አማካይነትየተሰራ ቤት፣በአጥኚዋ የተነሳ፣11/11/2014/ዓ.ም

ፎቶ 7 ፡- የወላይታ ሜሹዋ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ



**ምንጭ፡-ሶዶ ዙሪያ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣11/11/2014ዓ.ም**

### 5.2 .3. ጉላንታ (Gulantta)

**ጉላንታ ቤት (Gulanttaa Keettaa) :-** ሦስተኛው የወላይታ ባህላዊ ቤት ጉላንታ የሚባል ሲሆን ከውስጥ በኩል አመጋገሩ ከላይ እስከ ታች በ9 ዙር ክፍተት እና በ12 ክንድ ልኬት የሚሠራ ነው ፡፡ እያንዳንዱ መዋቅር ከ20-25 ዙር ጥቅጥቅ ያለ ማገር ይዞ ይወርዳል ፡፡ ከየጉላንታው መሀል 15 ሳ.ሜ የሚደርስ ክፍተት ያለው ሲሆን የውስጡ ማገር በእጅ ከሚገመድ የቃጫ ሲባጎና ከነጭ የእንሰት ወፍቾ (bootta sussa) ወይም ሰንሰለት አምባር ዛጎል በተሰኙ የአስተሳሰር ስልቶች የሚሰራ ነው ፡፡ ቤቱ በተለያየ የኑሮ ደረጃ ውስጥ በሚገኙ የብሔረሰቡ ክፍሎች ለኑሮ የሚመረጥ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከፕላኔት ጋር ተያይዞ የሚነገር ታሪክና ውበት የሚሰጠው በመሆኑ ነው ፡፡ ውስጣዊ ቅርጹ ዘጠኝ ረድፍ ያለው ሆኖ አሰራሩ የፕላኔት አቀማመጥ ተምሳሌትን መሰረት ያደረገ ነው[10]፡፡

የጉላንታ ባህላዊ ቤት በውበቱና በጥንካሬው ተመራጭ የሆነ ቤት ሲሆን አሰራሩም በአሰራ ሁለት ክንድ ተለክቶ ይዘጋጃል ፡፡ ቅርጹም የፕላኔት አቀማመጥ ተምሳሌትን መሰረት ያደረገ ሆኖ ማቶት (ሽልአ) በተባለውና በእንዝርት መልክ በቆመው ምሰሶ ጫፍ ላይና ምጨፍልያ በተሰኘ ተሸካሚ ላይ

---

[10] . ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣ማተቤ 2014 ዓ.ም ፡፡

የፀሐይን ቅርጽ ይዞ ይታያል ። የወላይታ ብሔረሰብ ከጥንት ጀምሮ የጉላንታ ባህላዊ ቤት ዓለምን የሚያዩበት መነጽር አድርገው ያስባሉ [11]።

## I, የጉላንታ ባህላዊ የቤት አሠራርና በውስጡ የሚካተቱ ነገሮች

የወላይታ ህዝብ ከጥንታዊ የዋሻ ውስጥ ኑሮ ተላቆ በራሱ ጥበብ መጠለያ መሥራት የጀመረው ከብዙ ዓመታት በፊት ነው ። የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አሠራር የብሔረሰቡን አቅምና ደረጃ ጠብቀው የሚሠሩ ሆነው ሁሉም ቤቶች የራሳቸው የሆነ የአሰራር መንገድ አላቸው ። ቤቶቹም ከውጭ ሲታዩ ተመሳሳይ ሆነው ውስጣዊ ጥበባቸው የተለያየ ነው ።

## II, የወላይታ ጉላንታ ባህላዊ ቤት ተምሳሌቶች

ከአራቱ የቤት አይነቶች አንዱ የሆነው የወላይታ ጉላንታ ቤት በብሔረሰቡ ለኑሮ የሚመረጥ ነው ። ለዚህም ምክንያቱ ቤቱ ከፕላኔት ጋር ተያይዞ የሚነገር ታሪክ፣ውበትና ክብር የሚሰጠው ቤት ሆኖ በዘጠኝ ቦታ ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ የሚሰራ ነው ። እነዚህ ክፍተቶች ለቤቱ ውበትን ይሰጣሉ ። በወላይታ ባህል የቤት ሥራ፣ የቀን ቆጠራና የልጆች ግርዛት ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ነው ። የጉላንታ ባህላዊ ቤት በጣም ሰፋ ተደርጎ በአስራ ሁለት ክንድ መሰራት የሚችልና ለመኖሪያነት የሚያገለግል ነው።[12] የጉላንታ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ ዘጠኝ ረድፍ ያለው ሆኖ አሰራሩ የፕላኔት አቀማመጥ የተከተለ ነው ። ይህም ማቶት (ሸልአ) የተባለ በእንዝርት መልክ በቆመው ምሰሶ ጫፍ ላይ ምጨፍልያ በተሰኘ ተሸካሚ ላይ ሆኖ የፀሐይን ቅርጽ ይዞ ይታያል ። ሌሎቹ ዘጠኝ የሚደርሱ በምህዋር ላይ የሚሽከረከሩ የፕላኔት ተምሳሌት የሚሆኑ ጉላንታዎች አሉ።[13]

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው ብሔረሰቡ ቤቱ ዓለምን የሚያይበት መነጽር እንደሆነ አድርጎ ስለሚያስብ ዓለምን ወካይ በሆነው ፕላኔት ቅርጽ ቤታቸውን እንደሚሰሩ የሚገልጽ ነው

የወላይታ ጉላንታ ቤት ከመሬት እስከ ጣሪያ ድረስ ባለው ቦታ ላይ ያሉት ዘጠኝ ክፍተቶች የተለያዩ ጌጣጌጦች ሲደረጉበት ዝም ብሎ ወደ ጣሪያው ለተመለከተ ሰው አመጋገሩ እራሱ የከዋክብትን አቀማመጥ ይመስላል ። ሌላው ክፍተቱ ውበትን ይሰጣል፣ በዓለም ላይ ያሉ ፕላኔቶች ዘጠኝ ናቸው።

---

[11]. ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣ኢሳያስ፣ሸዋዬ 2014 ዓ.ም ።

[12]. ቃለ መጠይቅ፣አማኑኤል፣06/09/2014 ዓ.ም ።

[13]. ቃለ መጠይቅ፣ኢሳያስ፣15/09/2014 ።

ፎቶ8- የወላይታ ጉላንታ ቤት ውጫዊ ገጽታ



**ምንጭ፡- በወላይታ ባህልና ቱሪዝም ጊቢ የሚገኘው ባህላዊ ቤት ጳጉሜ1/2014ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ**

ከላይ የቀረቡት የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አይነቶች በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኙ፡- ኢትዮጵያ በብዝሃነቷ ልክ በርካታ የቤት አሰራር አይነቶች አሏት። ከእነዚህም መካከል በስፋት ከሚታወቁት መካከል ጥቂቶቹ የሚከተሉት ናቸው።

### 5.2.4. ቡራሪያ ቤት (Buraariyaa keettaa)

አራተኛው የወላይታ ባህላዊ ቤት ቡራሪያ የሚባል ሲሆን ማንኛውም ሰው ሊሰራው የሚችለውና ቀለል ያለ ነው ። ይህ ቤት በተገኘው የግድግዳ እንጨት፣ከቀርከሃ፣ከሸምበቆና ከአገዳ ሊሰራ ይችላል የውስጥ አመጋገሩ ከወለሉ እስከ ግድግዳው ጫፍ ድረስ ሀመካ (Hamakkaa) በተባለው እንጨት ወይም ከሸምበቆ አገዳ እና ከማሽላ አገዳ ሽብ ሽብ እየተደረገ ይማገራል ።

ይህ የጎጆ ቤት ዓይነት አቅም የሌላቸውና ወጣቶች የሚሰሩት ቤት ሲሆን ማገሩ ዘርዘር ተደርጎ ይሰራል ። በማንኛውም የግድግዳ፤ወራጅ አጠና ፤ ከቀርከሃ፣ ከሸምበቆ፣ እንጨቶች ሊሰራ የሚችል የቤት አይነት ነው። የውስጥ አመጋገሩ ከወለሉ እስከ ግድግዳው ጫፍ ድረስ በሸምበቆ ወይም ቀጫጭን ማገር (Hamakkaa) ሽብ ሽብ ተደርጎ የሚሰራ ሆኖ ከግድግዳው በላይ እስከጣሪያው ድረስ በዛንዲዳ (zanddidaa) ዘርዘር ተደርጎ ይታሠራል[14] ።

ስለ ቡራሪያ የቤት አይነት አቶ ኢሳያስ ሲገልጹ የገንዘብ አቅማቸው ዝቅ ያሉ ሰዎች የሚሰሩት የቤት አይነት ሆኖ ከሸምበቆና በማንኛውም የግድግዳ እንጨት ሊሰራ የሚችል ነው ። ሌላው የወላይታ ባህላዊ ቤት በግለሰቡ የአቅም ደረጃ የሚወሰን እንደሆነ ነው ።

ከላይ ከቀረበው ፎቶና የጽሑፍ ይዘት መረዳት የተቻለው የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ከውጭ ሲታዩ ተመሳሳይ ቢሆኑም ውስጣዊ አሰራራቸው የተለያየ እንደሆነ የተገለጸ ሲሆን ልዩነታቸውም በግብአት፣ በአመጋገር፣በጣሪያ አሰራር፣በወፍቾ አስተሳሰር ነው ።

**ሀ. የጎጆ ቤት ፡-** በዋናነት በኢትዮጵያ ከፍተኛ ቦታዎች እና ማዕከላዊ አካባቢዎች የሚሰራ ክብ ቅርጽ ያለው ቤት ነው። ግድግዳው ከእንጨት እና ከጭቃ (ጭቃ ቤት) የሚሰራ ሲሆን፣ ጣሪያው ደግሞ በሳር ይከደናል። በአብዛኛው አንድ ክፍል ብቻ ያለው ሲሆን፣ አንዳንዴ ለእንስሳት ማደሪያ የሚሆን አነስተኛ ቦታ በውስጡ ይኖረዋል (Pankhurst, 1990)

---

[14] ቃለ መጠይቅ፣06/09/2014 ።

**ለ. የዶርዜ ቤት ፡-** በደቡብ ኢትዮጵያ በዶርዜ ማህበረሰብ የሚሰራ፣ የንብ ቀፎ ወይም የዝሆን ቅርጽ ያለው ልዩ የቤት አሰራር ነው፡፡ ከቀርከሃ እና ከእንሰት (የኮባ) ቅጠል የሚሰራ ሲሆን፣ እስከ 12 ሜትር የሚደርስ ከፍታ ሊኖረው ይችላል፡፡ ይህ ቤት ከጊዜ በኋላ በመሬት ውስጥ ያሉ ተባዮች ሲበሉት ቁመቱ እያጠረ ይሄዳል፤ ነገር ግን አሁንም ለብዙ አመታት ያገለግላል፡፡ ሌላው አስደናቂ ባህሪው፣ ቤቱ በአዲስ ቦታ ላይ እንደገና እንዲተከል በማድረግ ማንቀሳቀስ መቻሉ ነው (Fasil, 2007)።

**ሐ. የሀረሪ ባህላዊ ቤት ፡-** በሀረር ከተማ የሚገኝ፣ አራት ማዕዘን ቅርጽ ያለው እና ልዩ የውስጥ አቀማመጥ ያለው ቤት ነው፡፡ የቤቱ ውስጠኛ ክፍል "ጊዲር ጋር" (ዋና ክፍል) ተብሎ የሚጠራ ሲሆን፣ በግድግዳው ዙሪያ እንግዶችና የቤተሰብ አባላት የሚቀመጡባቸው ከፍታ ያላቸው መድረኮች (ነደባ) አሉት፡፡ ግድግዳዎቹ በልዩ ልዩ ቀለም በተነከሩ ቅርጫቶች እና በሌሎች ጌጣጌጦች ያጌጡ ናቸው፡፡ ይህ ቤት ለማህበራዊ ክዋኔዎች (እንደ ሰርግ እና በዓላት) ትልቅ ቦታ አለው (Unesco, 2006)፡፡

**መ. የኮንሶ ባህላዊ ቤት ፡-** የኮንሶ ማህበረሰብ ቤቶች በድንጋይ የታጠሩ እና በመከላከያነት የተደራጁ መንደሮች ውስጥ ይገኛሉ፡፡ ቤቶቹ እራሳቸው ክብ ቅርጽ ያላቸው ሲሆኑ፣ ግድግዳቸው ከእንጨትና ከጭቃ፣ ጣሪያቸው ደግሞ በሳር ይሰራል፡፡ የኮንሶ መንደሮች የእርከን ስራ (terracing) እና "ሞራ" ተብሎ የሚጠራ የማህበረሰብ መሰባሰቢያ ቤት መኖሩ ልዩ ያደርጋቸዋል ((Unesco, 2011)

# ምዕራፍ ስድስት

## የወላይታ ባህላዊ ቤት አሰራር ሂደትና ተያያዥ ማህበራዊ ክዋኔዎች

ይህ ምዕራፍ በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት ላይ ትኩረት አድርጎ ተከናውኗል ። በተለይም ምሰሶ ከመጎተት ጀምሮ እስከሚተከልበት እና ጣሪያ እስከሚሰራበት ጊዜ ድረስ በተለያዩ የሥራ ደረጃዎች የሚዜሙ ባህላዊ ዘፈኖችን መርምሯል ። ከዚህም ባሻገር፣ የምሰሶ ማህበራዊ ክብር፣ የመቆሚያ ጉርጓዱ ዝግጅት እና ሌሎች ተያያዥ ጉዳዮች ላይ ጥልቀት ያለው ትንታኔ አቅርቧል ። በተጨማሪም፣ የቤት ሥራው የሚከናወንባቸው ዕለታትና ወራት እንዲሁም ከጨረቃ ኡደት ጋር ያላቸው ትስስርና ትርጓሜ ተብራርቷል ። በሂደቱ ውስጥ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (Debbushsha fogiya asata)፣ የሴቶች፣ የወጣቶችና የጎልማሶች የሥራ ድርሻ ምን እንደሚመስል ተዘርዝሯል ። በመጨረሻም፣ ከቤት ሥራ በኋላ የሚከናወኑ እንደ አጥር ዝግጅትና በቤቱ ዙሪያ የሚተከሉ ዕፅዋት ያላቸው ተምሳሌታዊ ትርጉም ተካቷል ።

እነዚህ ከመስክ የተሰበሰቡ መረጃዎች በማህበራዊ ትምህርት፣ በመዋቅራዊ ተግባራዊነት፣ በሥነ-ትዕምርት እና በማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳቦች ተተንትነዋል ። ትንታኔው የ(Schlereth, 1985) የቁሳዊ ባህል ጥናት ሞዴልንም እንደ ዋነኛ ማዕቀፍ ተጠቅሟል ።

## 6.1. የቤት ሥራ ሰበብ እና ቅድመ ቤት ስራ

በባህሉ አንድ ሰው ቤት ለመስራት እንዲነሳሳ መነሻ የሚሆኑ የተለያዩ ምክንያቶችን በተመለከተ የተለያዩ ሰዎች መረጃ የሰጡ ሲሆን ከነዚህም ውስጥ ከባሎሜ አንጁሎ፣ካዎ ኮይሻ፣ጥቅምት 29/2015 እና ከሲሳይ ኩማ፣ህዳር12/2015ዓ.ም በቃለ መጠይቅ የተሰበሰቡ መረጃዎች ቀጥሎ ቀርቧል ፦

በብሔረሰቡ አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስና ትዳር መስርቼ እራሴን አስተዳድራለሁ፤ ከእናትና አባቴ ጉያ ወጥቼ በራሴ ቤት መኖር እፈልጋለሁ፤ አባቴ በህይወት እያለ ንብረት (ቅሪት) (xee'uwa) እሰበስባለሁ፤"በባህሉ ቅሪት መሰብሰብ የሚባል ስርዓት" አለ፤ጥሪቴ ከአባቴ ወይም ከሌሎች ጋር አይቀላቀልብኝ ብሎ ካመነና የተለያዩ ሌሎች ጥሪቶችን ለመሰብሰብ እንዲመቸው ሲያስብ መጀመሪያ ቤት ይሰራል ።

ከዚህ በላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በባህሉ ቤት ለመስራት መነሻ የሚሆኑ የተለያዩ  ምክንያቶች አሉ ። እነዚህም አንድ ወንድ ልጅ ትዳር ለመመስረት ሲፈልግ፣ጥሪት ለመሰብሰብ እንዲመቸው ለብቻዬ መኖር አለብኝ ብሎ ሲወስን የሚሉት ናቸው ።

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢዩኤል ከላይ ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይና ተጨማሪ መረጃ ሲገልጹ በብሔረሰቡ አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስና ትዳር መስርቼ እራሴን አስተዳድራለሁ፤ አባቴ በህይወት እያለ ንብረት (ቅሪት) (xee'uwa) እሰበስባለሁ ብሎ ካመነ እንዲሁም ንብረቴ ከሌሎች ጋር አይቀላቀልብኝ ብሎ ሲያስብ (ሲወስን) በመጀመሪያ ቤት ይሰራል ።

በባህሉ ቤት በተለያየ ምክንያት ሊሰራ ይችላል ። ይህንኑ በተመለከተ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሲሳይ ሲገልጹ ቃለ መጠይቅ፣ህዳር20/2015፣ አንድ ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ከደረሰ በኂላ፤ ለማግባት ብቁ ነኝ ሲል ቤት ይሰራል፤ሌላው ቤት የተቃጠለበት ሰው ፤ቤቱ ያረጀበት ሰው ፤ አንዳንድ ዳገታማ አካባቢዎች ላይ የሚኖሩ ሰዎች ናዳ ሲያስቸግራቸው፤ወንዝ ሲያስቸግራቸው፣ በንጉስ አማካይነት ቦታ ሲሰጣቸው በዚያ ቦታ ላይ ቤት ይሰራሉ ።

የቀረበው መረጃ በሞዴል ሲቃኝ ማህበራዊ ታሪካዊነት ቁሶቹ የማህበረሰቡን ታሪክ በምን መልኩ ይገልጹታል? ቁሶቹን ማን ሰራቸው? ከየት ተገኙ? በየትኛው ዘመን ተገኙ በዚህ ጥናት ይህ ሞዴል መረጃዎችን ለመተንተን ተግባር ላይ ውሏል (Schlereth, 1985፡ p.24) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት እንደተቻለው በባህሉ ቤት የሚሰራው ወንድ ልጅ ለአቅመ አዳም ሲደርስ፣ቤት የተቃጠለበት ሰው፣ቤቱ ያረጀበት ሰው፣ናዳ ያለበት አካባቢ ያሉ ሰዎች ቤት ሊሰሩ እንደሚችሉ የሚገልጽ ነው ፡፡

ቤት ለመስራት ከሚያነሳሱ ምክንያቶች ጋር በተያያዘ ከቀረበው በተጨማሪ የካዎ ኮይሻ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ባሞሬ አንጁሎ ቤት የመስራት ሃሳብ አመንጪ ግለሰብን በተመለከተ ሲገልጹ ቤት የመስራት ሀሳብ ከባለቤቱ፣ከባለቤቱዘመዶች፣ከልጁ እናትና አባት እና እንጀራ እናት(ጣውንት) ሊመነጭ ይችላል ለአቅመ አዳም የደረሰ ወንድ ልጅ ያጫትን ሴት ለማግባት ሽማግሌ ሲልክ ልጁ ቤት አለው? በማለት የልጅቷ ቤተሰቦች ይጠይቃሉ? ያጫት ልጅ የምትሰጠውን ሀሳብ ተቀብሎ ቀደም ሲል የነበረውን ቤት አሻሽሎ ሊሰራ ይችላል ፡፡ እናትና አባት በተለይ አባት ያረጀ ከሆነ ሳልሞት ለልጄ ቤት መስራት አለብኝ ይላል፤ በዚህም ሀሳብ እናት ትስማማለች ሌላው እንጀራ እናት (ጣውንት) ካለች ልጁ ከቤቴ መውጣት አለበት የምትል ከሆነ ልጁ ወጥቶ ቤት ይሰራል ፡፡[15]

በቀረበው መረጃ መሰረት ቤት የመስራት ሀሳብ የሚመነጨው ከባለቤቱ፣ከባለቤቱ ዘመዶች፣ከልጁ እናትና አባት፣ ከልጁ አማቾች እና እንጀራ እናት(ጣውንት) ሊመነጭ ይችላል ፡፡ ለአብነት ያህል የልጁ አማቾች ቤት እንዳለው የሚጠይቁት ልጃቸውን በሚገባ ማስተዳደር ይችላል ወይ የሚለውን በተዘዋዋሪ ለማረጋገጥና ልጃቸው ሳትንከራተት እንድትኖርና ሀብት እንዲኖራት ነው ፡፡ የልጁ ቤተሰቦች ደግሞ በተለይ አባት ለልጁ ቤት ሰርቶ መስጠት እንዳለበት በባህሉ ስለሚታመን ነው ፡፡

በባህሉ ቤት ለመስራት የተለያዩ ቅድመ ሁኔታዎች አሉ ፡፡ አንድ ሰው ቤት ለመስራት ሲያስብ መጀመሪያ ሀሳቡን የሚነግረው ወይም ጥያቄ የሚያቀርበው ለአባቱ ሲሆን ይህንንም ቤት ለመስራት እፈልጋለሁና ለቤት መስሪያ የሚሆን ቦታ ስጠኝ ብሎ አባቱን ያማክራል፤አባትም ለባለቤቱ ልጃችን ትዳር ለመያዝ ደርሷል፤ ቤት ለመስራትም ይፈልጋል ፡፡ ስለዚህ ምን እናድርግ በማለት ያማክራል ሁለቱም በቤታቸው ይመካከራሉ ፡፡ ቦታ ይመረጣል ቀጥሎ ቤት የመስሪያ ቀን ይቆረጣል፤ለምሰሶ የሚሆን እንጨት ይመረጣል፤ጋታ የሚባል ሳር ይመረጣል፤ለግድግዳ የሚሆኑ የጽድ እንጨቶችና

---

[15]. ቃለ መጠይቅ፣ጥቅምት 30/2015 ዓ.ም ፡፡

ማገሮች ይመረጣሉ፤ ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ከተለያየ አቅጣጫ ተሰብስበው በስርአት እንዲቀመጡ ይደረጋል ።[16]

በወላይታ ብሔረሰብ ሴት ልጅ አግብታ ወደ ሌላ ቦታ ሄዳ ትኖራለች። ወንድ ልጅ ግን አግብቶ ሚስቱን ይዞ ወደ ቤት ስለሚመጣ ቤት መስራት ያለበት በአባቱ(በቤተሰቡ ይዞታ) ላይ ነው ተብሎ ይታሰባል ። ከዚህም የተነሳ ለቤት መስሪያ የሚሆን ቦታ ይሰጠዋል ። በዚህም መሰረት አንድ ወንድ ልጅ ቤት መስራት ሲፈልግ በመጀመሪያ ለአባቱ ያማክራል ፤አባቱም ከባለቤቱና ከሌሎች የቤተሰቡ አካላት ጋር በመሆን ተመካክሮ የሚሰራበትን ቦታ መርጦ ከሰጠው በኂላ ቤቱ የሚሰራበትን ቀን ይወስናሉ ። ቀጥሎ ግብአቶችን ወደ ማሰባሰብ ሥራ ይገባሉ ።

ቤት ለመስራት የተለያዩ ቅድመ ቤት ስራ ሁኔታዎች አሉ ። እነዚህም መጀመሪያ ለአባት ሀሳብን ማማከር ሲሆን አባትም ከእናት ጋር ተመካክሮ የመስሪያ ቦታ ከተሰጠ በኂላ ቤቱ የሚሰራበትን ቀን መወሰን፣ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶችን መሰብሰብ፣ቦታ መምረጥ እያለ ወደ ስራው ይገባል ። መጀመሪያ ለአባት የሚነገርበት ምክንያት በባህሉ አባት ለልጁ ቤት መስራት አለበት ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ሌላው አባት እንደ ምሰሶ ስለሚቆጠርና ትልቅ ክብር ስለሚሰጠው ነው ።

በባህሉ ቤት ሲሰራ ስለሚደረጉ ቅድመ ዝግጅቶች ሲገልጹ አዕምሮአዊና ቁሳዊ ዝግጅት ይደረጋል ። ለወዳጅ ለዘመድ ይነገራል፤ ቤት ሰሪው ወጣት ከሆነ ለመሰል ጓደኞቹ ይነግራል፤በወላይታ ባህል ጫቻ የሚባል ባህል አለ ። ይህም ቤት ሰሪው ነገ የሚከፍለው ዛሬ ላይ ሌሎች የሚውሉለት ውለታ ሆኖ ይሄን አክል አምጣልኝ በማለት የሚፈልገውን ግብአት በጣም ቅርብ ለሆነ ጓደኛው ይነግራል ። ይህም ሁለት አይነት የወዳጅነት ትዕዛዝ ላይ የተመሰረተ ሲሆን የመጀመሪያው ቤት ልሰራ ነው ተብሎ ለወዳጅ ዘመድ ይነገራል፤ሁለተኛው ደግሞ ይሄን አምጣልኝ ይባላል ።ለምሳሌ በዘመናዊው ሁለት ቆርቆሮ አምጣልኝ ወዘተ… እንደሚባለው አይነት ለማለት ነው ።

ከላይኛው ሀሳብ ጋር በተያያዘ የካዎ ኮይሻ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ባሎሜ የነገሩኝ አንድ ሰው ቤት ለመስራት የተለያዩ ቅድመ ዝግጅቶችን የሚያደርግ ሲሆን መጀመሪያ አዕምሮአዊና ቁሳዊ ዝግጅት ያደርጋል ። በዚህም በወላይታ ባህል ጫቻ የሚባል ባህል አለ ። ይህም ማለት አንድ ሰው ቤት ሲሰራ፣ቤት ሲያስመርቅና ሰርግ ሲሰርግ በጣም ለሚቀርባቸው ወዳጆቹ፣ ዘመዶቹ፣ ሳር፣ወፍቾ፣ የምሰሶ እንጨትና ማገሮች ይሄን ያክል አምጣልኝ በማለት የሚፈልገውን የሚጠይቅበት ሲሆን በባህሉ ይህን ውለታ አሁን በተለያየ መንገድ ያገዙት ሰዎች ነገ እነሱም አግዘን ብለው ሲጠይቁ የመክፈል ግዴታ አለበት ።

---

[16].ቃለ መጠይቅ፣ሲሳይ፣ህዳር 12/2015ዓ.ም፣ሶዶ ዙሪያ ።

ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት ቤት ሲሰራ የተለያዩ ዝግጅቶች የሚደረጉ ሲሆን ከነዚህም የመጀመሪያዎቹ አዕምሮአዊና ቁሳዊ ዝግጅቶች ናቸው ። አዕምሮአዊ ዝግጅት የሚባለው ቤት ለመስራት ከማሰብ፣ከመፈለግና ከመወሰን ጋር የተያያዘ ሲሆን ቁሳዊ ዝግጅት የሚባለው ደግሞ ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶችን በተለያዩ መንገዶች ማለትም በባህሉ እንደሚደረገው ለወዳጅ፣ለዘመድ ይሄን ግዙልኝ(አምጡልኝ) ብሎ በመንገርና ቀሪውን ደግሞ በራስ ከማዘጋጀት ጋር የተያያዘ እንደሆነ ነው ።

## 6.2. ለቤት መስሪያ የሚውል የአፈር አይነት

የቤት መስሪያ አፈርን በተመለከተም ዝግጅትና ጥንቃቄ ያስፈልጋል ። ይህንን ሁኔታ በሚመለከት አቶ መቶሳላ እንደነገሩኝ የወላይታ ህዝብ ቤት የሚሰራው ለእርሻ በሚሆን አፈር ላይ ነው ። ይህም ቀይ የአፈር አይነት ሲሆን በባህሉ ይህንኑ የአፈር አይነት ለቤት መስሪያ እና ለእርሻ ስራ ይገለገሉበታል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የምግብ ጭስና የከብቶች አዛባ የከብቶች ማደሪያ ከሆነው ጓዳ እስከ እንሰት ስር ድረስ ተቆፍሮ በተቀመጠው ቀዳዳ ወደ ጓሮ ይሄዳል ። ይህ ደግሞ ለተክሎች እድገት በጣም አስፈላጊ ሲሆን እንሰት ደግሞ በውፍረትም ሆነ በቁመት ብዛት ያለው ሆኖ እንሰቱ ወደ ቤቱ እየተጠጋ ሲሄድ ከበፊቱ በበለጠ ውፍረቱ፣እርዝመቱና መልኩ ያማረ ይሆናል ። ምክንያቱም ከቤቱ የሚወጣውን አዛባ (ማዳበሪያ) እንሰቱ በቀጥታ ስለሚያገኝ ነው ። አቶ መቶሳላ አክለውም ለእንሰቱ ማማር ከአዛባው ይልቅ ጭስ ነው የሚያስፈልገው፤ጪስ የማያገኝ ከሆነ አይወፍርም ከዚህ የተነሳ ጪስና አዛባ ሁለቱም በጣም ያስፈልጋሉ ። ሰፊ ማሳ እና ብዙ እንሰት ካላቸው በብዛት ሰው ወዳለበት አካባቢ ሄደው ቤት መስራት ይፈልጋሉ ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ እንሰቱንም ሆነ ሌሎች ተክሎችን ያሳድጋሉ የሚል እምነት ስላላቸው ነው (ቃለ መጠይቅ ፣መቶሳላ፣ታህሳስ 6፣2015ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው የወላይታ ህዝብ ቤት ለመስራት የሚመርጠው ለእርሻ የሚሆን መሬትን ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቤቱ ውስጥ ምግብ ሲሰራ የሚነደው እሳት ጭስ ጓሮ ውስጥ ለተተከለው እንሰትና ሌሎች ተክሎች ጠቃሚ ስለሆነ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ ከቤት ውስጥ የሚወጣው የከብቶች አዛባ ለመሬቱም ሆነ ለከብቶች ያለው ጥቅም ላቅ ያለ ነው ።

ሌላው በባህሉ ለቤት መስሪያ የሚሆነው የአፈር አይነት ውሀ የማያስገባ ቢሆን ይመረጣል[17] ፡፡ ምክንያቱም ውሀ የሚበዛበት ከሆነ ቤት ለመስራት አይሆንም (ዴንበዟ) ነው ይላሉ ፡፡ ጨፌያማ ሆኖ ውሀ የሚይዝ ከሆነ ከታች መሰረቱን ካብ እያደረጉ መሬቱ ከፍ እስከሚል ድረስ ይደለድላሉ ፡፡ በተጨማሪም ቤት ለመስራት የሚያገለግለው አፈር ውሀ ያለበትን ቦታ ለመደልደል፤መደብ ለመስራት፤ቤቱ ውስጥ ያልተስተካከለና ከፍ ዝቅ ያለ ቦታ ካለ ደልድሎ እኩል ለማድረግ ያገለግላል

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ለቤት መስሪያ የሚሆነው አፈር ውሃ የማይበዛበትና ውሃ የማይገባበት ቢሆን ይመረጣል ፡፡ ጨፌያማ ሆኖ ውሃ የሚይዝ መሬት ከሆነ ከስር ካብ እያደረጉ መሬቱ ከፍ እስከሚል በመደልደል ይሰራል ፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ለመስራት ሲታሰብ በመጀመሪያ በብሔረሰቡ የተመረጡ በባህሉ የብሔረሰቡ መሪዎች ድቡሻ ፎጊያጌታ (Debbushsha fogiyageta) የሚባሉ ሰዎች ፍቃድ ይጠየቃል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሰዎች ሁሉም ሥራ ላይ የመወሰን ስልጣን ስላላቸው ከቦታ መረጣ ፣ግብአቶች ከሚሰበሰቡበትና ከሚቆረጡበት ቀን ጋር በተያያዘ ቀናቱን ይወስናሉ ፡፡ በቅደም ተከተል የሚሰሩ ቤቶችን ከገለጹ በኋላ ቤቶቹ የእርሻ ስራ በማይበዛበት ሁኔታ እንዲሰሩ ቅደም ተከተሉን በማያዛባ መንገድ ያደራጃሉ ፡፡ ቀጥለውም እያንዳንዱ ሰው በደቦ እንዲሰራ መመሪያ ይሰጣሉ ፡፡ ከዚያም ቤት በሚሰራበት ሰዓት መመሪያ የሚሰጡ በባህላዊ የቤት አሰራር ላይ እውቀት ላላቸው ሽማግሌዎች መመሪያ የሚሰጡት የማህበረሰቡ ተጠሪዎች ሲሆኑ ሁሉም ነገር በነሱ ቡራኬ ስር ይሰራል[18] ፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ የትኛውንም ነገር ለመስራት ሁሉም ሥራ ላይ የመወሰን ስልጣን ያላቸው ድቡሻ ፎጊያጌታ (Debbushsha fogiyageta) የሚባሉ ሰዎች ፍቃድ ይጠየቃል ፡፡ እነዚህም ሰዎች በቤት ሥራ ወቅት ከቦታ መረጣ ጀምሮ የመወሰን ስልጣን አላቸው ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቤቱ በሚሰራበት ወቅት ለሽማግሌዎች መመሪያ ይሰጣሉ፤በቤቱ ስራ ወቅት የተለያዩ ስራዎችን ለሚያግዙ የአካባቢው ሰዎች መመሪያ ይሰጣሉ ፡፡

ከላይ በቀረበው መረጃ የወላይታ ህዝብ ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት የተመረጡ የህዝቡ ተጠሪዎች(ዱቡሻ ፎጊያ)[19] የሚባሉ ሰዎች ፍቃድ ይጠየቃል፤እነዚህ ተጠሪዎችም ከቤቱ ጋር ለተያያዙ

---

[17].ቃለ መጠይቅ፣አልኬ ታንቱ፣09/05/2015 ዓ.ም ፡፡

[18]. ቃለ መጠየቅ፣ታደሰ ኮይራ፣ ኦፋ፣06/05/2015 ዓ.ም ፡፡

[19] . ዱቡሻ ፎጊያ የሚባሉ ሰዎች የብሔረሰቡ ታላቆች ናቸው ፡፡ እነዚህ ሰዎች የብሔረሰቡ ተጠሪዎች ሆነው የትኛውንም ስራ ለመስራት በብሔረሰቡ የተመረጡ ሲሆኑ ከእነሱ ምክር ሀሳብ ውጪ የሆነ ነገር ማንም ሰው በራሱ መስራት

ማናቸውም ነገሮች ፍቃድ ይሰጣሉ፤መቅደም ላለበትና መከተል ያለበትን ጉዳይ አስመልክተው መመሪያ የሚሰጡ ናቸው ። በተጨማሪ በወላይታ የሚሰሩ ቤቶች የራሳቸው የሆነ ቅደም ተከተል አላቸው። ይህንንም ሂደት ለማስፈጸም የተመረጡ የማህበረሰብ ተጠሪዎች ቅደም ተከተሉን ጠብቀው እንደሚያስፈጽሙ ከአምስቱ ወረዳዎች ከተመረጡ መረጃ ሰጪዎች ማረጋገጥ ተችላዋል ።

ቀደም ሲል እንደተገለጸው በወላይታ የሚታወቁ ቤቶች አራት ሲሆኑ የእነዚህም የአሰራር ቅደም ተከተል በተወሰነ ደረጃ የመመሳሰል ነገር ይታይባቸዋል ። ይሁንና ከተጠቀሱት የቤት አይነቶች ውስጥ በአሰራሩና በትርጓሜው ለየት የሚለው የጉላታ ቤት ነው ። ይህ የጉላንታ ቤት አሠራር በንጥል ጥናት ዘዴ መሰረት እንደሚከተለው ቀርቧል፡-

**ንጥል ዘዴ አንድ፡-**

ከደረጃ ማበልጸጊያ በኋላ ከአቶ ኢሳያስ ጋር ኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ሰኞ እለት ጠዋት 3፡00 ላይ በመኪና ጉዞ ጀመርን 5፡00 ላይ አውቶቢስ ተራ ደረስን ከዚያም ቤት ለመስራት በዝግጅት ላይ ወደ ሚገኘው አቶ ጳውሎስ ቤት አመራን ። እንደደረስንም ጥሩ አቀባበል አደረገልን ዓላማዬን አስረድቼ ወደ ጥያቄዬ ገባሁ እሱም ከ3 ወራት በኋላ የጉላንታ ቤት ለመስራት እንዳቀደና አሁን ላይ ለመስሪያ የመረጠውን

---

አይችልም ። ድቡሻ ፎጊያጌታ የሚባሉት በብሔረሰቡ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆኑ ህዝቡም ተቀብሎ ሲመርቁ አሜን ብሎ ሲረግሙ ይቅርታ ጠይቆ የሚያሳዩትን መመሪያ ተከትሎ ይኖራል ። ምክንያቱም ብሔረሰቡ በእነዚህ መሪዎች ሀሳብ ለመገዛት አምኖ የሾማቸው ሰዎች ሆነው ሲሞቱ ብቻ ወዲያው የሚተኩ ሰዎች ናቸው ። ምክንያቱም የሚመረጠው የቤቱ ታላቅ ሳይሆን የብሔረሰቡ ታላቅ ስለሆነ ጎሳ ውስጥ የጎሳ መሪ እንደ ማለት ሀሳብ አለው ። በወላይታ ውስጥ ከሚገኙ ጎሳዎች መካከል አንድ ጎሳ ይመረጥና ከተመረጠው ጎሳ ውስጥ የብሔረሰብ ተጠሪ ይመረጣል ። ለምሳሌ በወላይታ ማላ ውስጥ ሁለት ጎሳዎች አሩጂያ ዘርና ትግሬ ማላ ዘር የሚገኙ ሲሆን በነዚህ ስር ደግሞ ዝርጎ ማላ፣ዶጎ ማላ ተብለው የሚጠሩ ይገኛሉ ። ከነዚህ ውስጥ ዱቡሻ ፎጊያጌታ የሚባሉት ይመረጣሉ ። ሌላው ለአብነት በወላይታ ውስጥ ኦውምሚጊራ የሚባል ጎሳ አለ ። የዚህ ጎሳ አባል በቤተሰቡ የተለየ አምላክ እንዳለው ተደርጎ የሚታመን ሲሆን ይህም አምባዛ ተብሎ የሚጠራ ሆኖ የመለኮታዊ ስልጣን እንዳለው በማመን የሚማጸኑት አምላክ ነው ። በተጨማሪ ቡቡላ የሚባል ጎሳ ያለ ሲሆን የሚያምኑት ሙሉጉሻ የሚባል የቤተሰብ አምላክ ነው ። ከላይ ከተጠቀሱት ጎሳዎች የሚመረጡ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች በአባቶቻቸው አማልክት ህዝቡን መርቀው የማድረስ ስልጣን ያለቸው ናቸው ተብሎ ይታሰባል ። ሌላው ጥንት እነዚህ ሰዎች ተጠሪነታቸው ለነገስታቱ ስለሆነ በወቅቱ የነገስታቱን ትዕዛዝ ቀጥታ ወደ ህዝቡ የማድረስ የህዝቡን የኑሮ ጥያቄዎች ቀጥታ ወደ ንጉስ የማቅረብ ምላሽ የማግኘት አይነት የአማላጅነት አይነት አገልግሎት ጭምር የሚሰጡ ሰዎች ናቸው (ቃለ መጠይቅ ወልደማርያም እና ታደሰ ኮይራ 2014 ዓ.ም )።

ቦታ ተመለከትኩ እንዲሁም የተወሰኑ የቤት መስሪያ ቁሳቁሶችን እንደ የግድግዳ እንጨቶች፣ቀጫጭን ማገሮችን መሰብሰቡን ተመለከትኩ፡፡[20]

የጉላንታ ባህላዊ ቤት ለመሥራት ያቀደ ሰው ከመጀመሪያ ጀምሮ ከፍተኛ ዝግጅት የሚያደርግ ሲሆን ቤቱ የሚሠራበትን ቦታ በመፈለግ መረጣ በማድረግ፤ ለቤት ሥራ የሚውሉ የግንባታ ቁሳቁሶችንና ለመስተንግዶ የሚሆኑ ነገሮችን በመሰብሰብ ዝግጅት እንደሚያደርግ ከመስክ ካገኘሁት መረጃዎች መረዳት ችያለሁ ፡፡

**ንጥል ዘዴ ሁለት ፡-** እንደ አጋጣሚ ከአቶ ጳውሎስ በቅርብ ርቀት በሚገኝ ቦታ ቤት እየተሰራ እንደሆነ አቶ ኢሳያስ ነግሮን ከሚያሳየን አንድ ሰው ጋር ወደቦታው ላኩን ስንደርስ በከፍተኛ ትብብር ቤቱን ሳር እያለበሱ ነበር የደረስነው ፡፡ በዚህም የብሔረሰቡን የመረዳዳት ባህል የተመለከትኩ ሲሆን በዚህም ባህላዊ ቤቱ በተሳትፎና በትብብር እንደሚሰራ ተረድችያለሁ ፡፡ የወላይታ ባህላዊ ቤት ማህበራዊ ፋይዳው ከፍተኛ ነው ፡፡ ምክንያቱም በወላይታ ብሔረሰብ የህዝቡ ማህበራዊ ተሳትፎ ጎልቶ ከሚታይባቸው ተግባራት አንዱና ዋንኛው በባህላዊ ቤት አሠራር ላይ የሚደረገው ተሳትፎ ነው ፡፡ በዚህ መሠረት ከቤቱ መሥሪያ ቦታ መረጣ ጀምሮ የግድግዳ፤ የማገር፤ የምሰሶ መረጣና ቆረጣ፤ የማሠሪያ ወፍቾ ቅድመ ዝግጅት እንዲሁም ቤቱ በሚሠራበት ወቅት ምሰሶ መትተትና ማቆም፤ የጣሪያ ሥራ፤ ሰንበሌጥ ማሰባሰብና ማልበስ፤ በዕለቱ ከአካባቢው እናቶች የሚደረግ የምግብ ዝግጅትና ተሳትፎ /Yaganowaa/ በህብረት ወይም በደቦ የሚፈፀሙ ሲሆኑ ሥራዎቹ በፆታና በዕድሜ ተከፋፍለው እንደሚከናወኑ ከመስክ በምልከታና በቃለመጠይቅ ያገኘሁት መረጃ ያመለክታል፡፡

በወላይታ ባህል በተለያዩ ስራዎች ሰዎች እርስ በርስ የሚረዳዱበት ባህል አለ ፡፡ ብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ወቅት ባህሉን ተከትለው እየተጋገዙ ይሰራሉ ፡፡ ይህንን በተመለከተ አቶ ኢያሱ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

በወላይታ ለእርሻም ሆነ ለሌሎች ስራዎች በባህሉ ሦስት አይነት የመረዳዳት ባህሎች አሉ፤ቤት ሲሰራ ግብአቶቹን የመሰብሰብ እና የመረዳዳት ባህል ያለ ሲሆን እነዚህ ሦስት የመረዳዳት ባህሎች ሀሺያ ፣ ዘይያና ዳጓ ተብለው ይጠራሉ ፡፡

**ሀ.ሀሺያ ፡-** የሚባለው ከ2-5 ሰዎች በጋራ በመሆን የመተጋገዝ ባህልን ይገልጻል፤ይህም በሬ በማረስ፣ ስኳር ድንችና ድቡልቡል ድንች ሲተከል፣እንሰት ሲተከል ሀሺያ የሚባል ሲሆን በዚህም ዛሬ በኔ ጓሮ ተክለው፣ነገ ባንቺ ጓሮ ተክለው እንደዛ እያሉ በየተራ የመስራት ባህል ሀሺያ ተብሎ ይጠራል ፡፡

---

[20]. ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣ጥር2016 ዓ.ም ፡፡

**ለ.ዘይያ ፡-** የሚባለው ደግሞ ከ5-10 ሰዎች የሚሳተፉበት ሆኖ እንደ ስራው ስፋትና መጠን የሚወሰን ሲሆን እንጨት በሚሰበሰብበትና ሰንበሌጥ በሚታጨድበት ጊዜ በዘይያ መልክ ያሰራሉ ፡፡

**ሐ. ዳን ፡-** የሚባለው አጠቃላይ የቤቱ ስራ ህዝቡ በሙሉ ስለሚነሳ ዳን ጠቅላላ ህዝብን አነሳስቶ መስራት ማለት ነው ፡፡[21]

የኪንዶ ዲዳዬ ወረዳ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ማተቤ ከላይ ከቀረበው የመረዳዳት ባህል ጋር በተያያዘ ሲገልጹ በወላይታ ባህል ሀሺያ፣ ዘይያና ዳን የተባሉ ሦስት አይነት የመረዳዳት ባህሎች ይገኛሉ ብሔረሰቡም የተጠቀሱትን ባህሎች ለቤት ስራ፤ለምሰሶ ቆረጣ፤ለሰንበሌጥ አጨዳ፤በእርሻ ወቅት እንሰትና ሌሎች ተክሎችን ለመትከል ይገለገሉበታል (ቃለ መጠይቅ፣መጋቢት 2014 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ቤት ሲሰራ ህዝቡ የሚረዳዳበት ሀሺያ፣ዘዬና ደን የተባሉ ሦስት አይነት ባህል ያለ ሲሆን በዚህም ለቤት መስሪያ የሚሆኑ የማገር፣የምሰሶ እንጨቶችን ካሉበት ቦታ በእነዚህ የመረዳዳት ባህሎች በህብረት አምጥተው ቤቱንም በህብረት ይሰራሉ ፡፡

የወላይታ ባሕላዊ ቤት አሰራር የብሔረሰቡን ዕውቀትና ጥበብ የሚያሳይ ሲሆን ቤቶቹም ከተለያዩ የእንጨት አይነቶች ከሣር እንዲሁም ለማሰሪያ ወፍቾ፤ቃጫ የመሳሰሉትን በመጠቀም ይገነባሉ ፡፡

**ንጥል ዘዴ ሁለት ፡-** በድጋሚ ወደ ኦፋ (ገሱባ) ባደረግኩት ጉዞ ቀደም ሲል መረጃ ለመሰብሰብ ደጋግሜ በሄድኩባቸው አጋጣሚዎች መረጃ ከመስጠት ባሻገር ሌሎች መረጃ የሚሰጡ ሰዎችን ባገናኘኝ አቶ ኢያሱ ገጃቦ አማካይነት የጉላንታ ቤት ለመስራት የሚያስፈልጉ ግብአቶችን በሰበሰቡበት ተመለከትኩ ፡፡ እነዚህ ቀጥሎ በሰንጠረዥ 2 ቀርበዋል ፡፡

ሰንጠረዠ 2 ፡- ለጉላንታ ባህላዊ ቤት ሥራ የሚሆኑ ቁሳቁሶች

| **የቤቱ አካላት** | **የሚያስፈልጉ ቁሳቁሶች** |
|---|---|
| ለግድግዳ | ዎጋራ፤ ጉጋንታ፤ ጋርጋሩዋ፤ ዎላይታ ጢዳ፤ ዳቺያ፤ አምቢያ፤ ወዘተ |
| ለማገር | ዎይሻ፤ ሃማካ፤ ሻትንታ፤ካሬታ ጉሩቼዋ፤ ወዘተ |
| ለማሰሪያ | ሱሳ /ወፍቾ/፤ ፖሹዋ፤ ጎላ /ቃጫ/ ወዘተ |
| ለቤት ክዳን | ጋታ /ሰንበሌጥ/ |

---

[21] . ቃለ መጠይቅ፣ታህሳስ 08/04/2016 ዓ.ም. ፡፡

| | |
|---|---|
| ለጣሪያ ሥራ | ጣንቃርሣ፤ ጌሹዋ፤ ጵይያ፤ ሃማካ፤ ኅባ፤ ሱሳ ወዘተ |
| ለምሶሶ | ጋርቢያ፤ ሞቆታ፤ ኦቻ፤ ኀሎልኡዋ፤ ወዘተ |
| ለበር መዝጊያ | ኢፍታ ለመሥራት ሃማካ፤ ዎይሻ፤ ወዘተ |

የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤቶች በብሔረሰቡ እውቀት ላይ ተመስርተው ፤በአካባቢው በሚገኙ ግብአቶች በአካባቢው በሚገኙ ባህላዊ የመስሪያ መሳሪያዎች ፤ ይሰራሉ ። በገሱባ፣ኪንዶ ዲዳዬና ዞዶ ዙሪያ የተመለከትኳቸው መሳሪያዎች በአጥኚዋና በረዳት ፎቶ አንሺ የተነሱ ሆነው እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ።

**ንጥል ዘዴ ሦስት ፡-** በኪንዶ ዲዳዬ ቆይታዬ አቶ አንጁሎ የተባሉ ግለሰብ የጉላንታ ቤት ለመስራት ቅድመ ዝግጅት ጨርሰው ወደስራው እንደገቡና አሁን ላይ የማጠናቀቅ ስራ ላይ እንደደረሱ በቃለመጠይቅና በምልከታ ለማረጋገጥ ችያለሁ ። በዚህም በመጀመሪያ ሜዳማ የሆነና ውሃ ልኩን የጠበቀ ቦታ ይመረጣል። ቀጥሎ የግለሰቡን የኢኮኖሚ ደረጃ መሰረት አድርጎ ስፋቱ ይወሰናል፤ወደስራው ሲገባ አመጋገሩ በዘጠኝ ዙር ምህዋር ከላይ እስከ ታች የሚሰራ ሆኖ እያንዳንዱ ምህዋር በሃያ ዙር ተጠቅጥቆ በየጉላንታው መሃል አሰራ አምስት ሳ.ሜ የሚደርስ ክፍተት አለው ።

የጉላንታ ባህላዊ ቤት ለመሥራት ቦታ ሲመረጥ ሜዳማ የሆነ፤ ጨፌ ያልሆነ መሬት፤ ውኃ ልክ ጠብቆ ለመስራት አስቸጋሪ ያልሆነ ቦታ ይመረጣል ። ምቹ ቦታ ካልተገኘ ውኃ ልክ እስከሚመጣ ድረስ ደልድለው ያስተካክላሉ ። የቤቱ ስፋት የሚወሰነው እንደግለሰቡ ኢኮኖሚ ሁኔታ ሲሆን 8 ክንድ፣ 10 ክንድ፤ 12 ክንድ፤ 13 ክንድ እየተባለ ስፋቱን እንደ ግለሰቡ አቅም እየወሰኑ ይሠራሉ[22] ።

የጉላንታ ቤት ከውስጥ በኩል አመጋገሩ በዘጠኝ ዙር ምህዋር ከላይ እስከ ታች የሚሰራ ነው ። እያንዳንዱ ምህዋር ከ20-25 ዙር ጥቅጥቅ ያለ ማገር ይይዛል ከየጉላንታው መሀል አስራ አምስት ሳ.ሜ የሚደርስ ክፍተት አለው ። የጉላንታ ቤት የውስጥ ማገር በእጅ ከሚገመድ የቃጫ ሲባጎና ከነጭ የእንሰት ወፍቾ (bootta sussa) ወይም ሰንሰለት አምባር ዛጎል በተሰኙ የአስተሳሰር ስልቶች የሚሰራ ነው[23] ። ሌላው አሰራሩም የፕላኔት አቀማመጥ ቅርጽ ያለው ሲሆን ማቶት (ሽልአ) የተባለ

[22] ጥላሁን ኡኩሌ፣ኦፋ፣06/04/2016ዓ.ም ።

[23] ቃለ መጠይቅ፣ኢሳያስ፣12/04/2016ዓ.ም።

በእንዝርት መልክ በቆመው ምሰሶ ጫፍ ላይ ምጨፍልያ በተሰኘ ተሸካሚ ላይ ሆኖ የሚታይ ሲሆን ሌሎቹ ዘጠኝ የሚደርሱ በምህዋር ላይ የሚሽከረከሩ የፕላኔት ተምሳሌት የሚሆኑ ጉላንታዎች አሉ[24]

ከላይ የቀረበውን አስረጂ በተመለከተ የሚከተለው የጉላንታ ቤት ፎቶ ከፊል ውስጣዊ ቅርጽ የሚያሳይ ነው ።

ከዚህ በተጨማሪ ለቤት መስሪያ የሚውሉ መሳሪያዎችን ተመለከትኩና ፎቶ አነሳኋቸው እነዚህም በፎቶግራፍ ቁጥር 12 ስር ቀርበዋል ።

የመጀመሪያ ቤት ከሆነ በትንሹ ነው የሚሰራው ልጆች አቅም እስኪያወጡ ድረስ ለጎጆ መውጪያ ከ20-50 ሜትር ባለው ርቀት ላይ ባህላዊ የአሰራር መንገዱን ተከትለው አባታቸውን ከበው ዙሪያው ላይ እንዲሰሩ ይፈቀዳል ። ቀጥሎም ግብአት መሰብሰብ ይጀምራሉ ። የሚሰበሰቡ ግብአቶች በተዋሲያን ነፍሳት እንዳይበሉ የሚቆረጡበት ጊዜ በጣም ወሳኝ እንደሆነ በባህሉ ስለሚታወቅ አስፈላጊው ጥንቃቄ ይደረጋል ። ከዚህ የተነሳ ግብአቶቹ ባህላዊ አስትሮኖመሮች የሚባሉት ባዘዙባቸው ቀናት ይቆረጣሉ ። የምሰሶ እንጨት፤ከቤት መስሪያ ግብአቶች መካከል የመጀመሪያውና ረጅም እድሜ እንዲኖረው የሚፈለገው የግድግዳ እንጨት(Goda)ሲሆን የግድግዳ እንጨት(Goda) የሚባለው በአብዛኛው የወላይታ ፅድ (wolaita tiidda) የሚባል እሾክ ያለበት ፅድ (ትላልቅ የሚባሉ ሰዎች ቤታቸውን የሚሰሩት የፅድ አይነት) እነዚህ ጽዶች ባህር ዛፍ ከመምጣቱ በፊት ለቤት መስሪያ የሚያገለግሉ ነበሩ፤የቤት አሰራሩ የቆየ የብሔረሰቡን አንድነት በጠበቀ መንገድ ይከናወናል[25] ።

የወላይታ ባህላዊ የቤት አሰራርን በተመለከተ በሶዶ ዙሪያ የቡድን ሁለት ተወያይ የሆኑት አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ በቅድሚያ በባህሉ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች ዱቡሻ ፎጊያ አሳቲ (Debbushsha fogiya asati) የሚባሉ ሰዎች የቤት ስራው ከመጀመሩ በፊትም ሆነ ከተጀመረ በኋላ መመሪያና ፍቃድ ይሰጣሉ ። የብሔረሰቡ ተጠሪዎች የሚባሉ ሰዎች ለቤቱ ስራ የሚሆነውን የአፈሩን ሁኔታ አይተው ያ ቦታ ለረጅም ጊዜ ባለቤቱን ይሸከማል ወይስ አይሸከምም? የሚለውን የመተንበይ አቅም አላቸው ።

[24] ቃለ መጠይቅ፣አማኑኤል፣20/04/2016 ዓ.ም።

[25].ቃለ መጠይቅ፣03/07/2016 ዓ.ም ።

ሌላው ለቤት መስሪያ የተመረጠውን ቦታ አይተው ይሆናል አይሆንም የሚለውን ይወስናሉ ። የብሔረሰቡ ተጠሪዎች በባህሉ የቦታውን የጥራት ሁኔታ፣አይነቱን፣ ቦታው ላይ ያለውን የራሳቸውን መንፈሳዊ ግምት መሰረት አድርገው መመሪያ ይሰጣሉ ። በዚህም ይሄ ግራ ነው፤ ይሄ ቀኝ ነው፤ይሄ ለፀሀይ ትይዩ ነው በማለት ከመረመሩ በኋላ ከዚህ ወደዚህ ቀይር ብለው ቦታን የመምረጥ ጉዳይንም ያከናውናሉ:: የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (Debbushsha fogiya asati) የቦታ መረጣውን ከጨረሱ በኋላ በዚህ ቦታ ላይ ቤት እንዲሰራ የሚለውን ይወስናሉ ። በሁለተኛ ደረጃ የተመረጠው ቦታ የተለያዩ ባእድ ቁሶች ተነስተው ቦታው ድንጋያማ አለመሆኑ ታይቶ መሬቱ በጥልቀት ይቆፈርና ይደመደማል፤ይደለደላል፤በሦስተኛ ደረጃ የቤቱ መሰረት(Baso) የኖራ ድንጋይ በአህያ ተጭኖ መጥቶ እየተጠቀጠቀ፣እየተደመደመ ይቆይና ባእድ አፈር አምጥቶ ከነባሩ አፈር ጋር ይቀላቀላል ይህም መዋሀዱ ሲረጋገጥ ለምሰሶና ለግድግዳ ቁፋሮ ይጀመራል፤ቀጥሎ መሰረቱ መጠንከሩና የሚፈለግበት ደረጃ ላይ መድረሱ ሲታወቅ ስራው ይጀመራል (የቡድን ውይይት፣26/11/2014 ዓ.ም) ።

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (Debbushsha fogiya asati) የቤቱ ባለቤት ረጅም እድሜና ከበሬታ ኖሮት በብሔረሰቡ ውስጥ ወልዶ፣ከብዶ፣ዘርቶ፣ሰብስቦ ይኖራል ወይስ አይኖርም የሚለውን የማወቅ አቅም ያላቸው ሰዎች እንደሆኑ የሚገልጽ ነው ። ሌላው ለቤት መስሪያ የተመረጠው ቦታ ይሆናል አይሆንም የሚለውን መርምረው ያሳውቃሉ ፡ በመጨረሻም በተመረጠው ቦታ ላይ ቤት እንዲሰራ ይወስናሉ ።

የቤት አሰራር ሂደትን ቅደም ተከተልን በተመለከተ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ አየለ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

የወላይታ ባህላዊ ቤት ለመስራት በመጀመሪያ ቦታ መምረጥ፣በሁለተኛ ደረጃ ቦታውን መደልደልና መቀየስ ሲሆን በሦስተኛ ደረጃ የሚቀየሰው የምሰሶ ቦታ ሆኖ የምሰሶው ቦታ መሀል ላይ ችካል ይቸከልና በችካሉ ላይ ወፍቾ ይታሰራል ። በአራተኛ ደረጃ ገመድ ይይዙና ክቡ ትክክል እንዲመጣ ጫፉ ሹል በሆነ ብረት ዙሪያውን የጭረት ምልክት እያደረጉ ዙሪያውን ይዞራሉ፤ በዚህም በትክክል ክብ መሆኑን ለማረጋገጥ ሃማካ የተባለ እንጨት ቆርጠው ያመጡና ከምሰሶ ችካል ወደታች ፣ወደፊት እያደረጉ ያዩና የግርግዳ ጉድጓድ የሚቆፈር ሲሆን በአምስተኛ ደረጃ ግድግዳው ዙሪያውን ይቆማል። ግድግዳው ቀጥ ብሎ እንዲቆም ካፒሲያ በሚባል አስተሳሰር ሦስት ዙር ማገር ያስራሉ። ይህም ግድግዳው ወጣ ገባ እንዳይኖረው ያደርጋል።[26]

[26] የቡድን ውይይት፣ 02/08/2016/ዓ.ም ።

የቀረበው መረጃ በSchlereth የቁሳዊ ባህል መተንተኛ ሞዴሎች ሲቃኝ መዋቅራዊ ቁሶቹ እንዴት እንደተሰሩ በአካል ውቅራቸውን የሚያሳይ ሆኖ ቁሶቹ ከምን ከምን ግብአቶች ተሰሩ? የአሰራር ቅደም ተከተላቸው ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ምላሽ የሚያገኙበት ነው ፡፡

ማህበራዊነት ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ትስስር የሚገልጽ ሆኖ ቁሶቹ የማህበረሰቡን የህይወት ገጽታ በምን መንገድ ያሳያሉ? የቁሶቹ ተገልጋዮች ቁሶቹን ከምን አስተሳሰብ ይገለገሉባቸዋል? ማህበረሰቡ ለቁሶቹ ያለው አመለካከት ምን ይመስላል? የሚሉ ጥያቄዎች ተመርምረው ምላሽ አግኝተውበታል

ከላይ የቀረበው መረጃ የወላይታ ህዝብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት ውስጥ ቀዳሚው ቦታ መምረጥ፣ ቦታ መደልደልና መቀየስ የሚባሉ ተግባሮች ሲሆኑ ከነዚህ ስራዎች በኋላ ቀጥሎ የሚመጣው የምሰሶ ቦታ ሲሆን ለምሰሶው የተመረጠው ቦታ መሀል ላይ ችካል ይቸከላል፤በችካሉ ላይ ወፍቾ ይታሰራል፤ቀጥሎ ገመድ ይያዝና ክቡ ትክክል እንዲመጣ ጫፉ ሹል በሆነ ብረት ዙሪያውን የጭረት ምልክት እየተደረገ ዙሪያውን በመዞር ይሰራሉ ፡፡ ከዚህ በኋላ ክብ መሆኑን ለማረጋገጥ ሃማካ የተባለ እንጨት ቆርጠው ካመጡ በኋላ ለምሰሶው ከተደረገው ችካል ወደታችና ወደፊት እያደረጉ በማየት ካረጋገጡ በኋላ የግርግዳ ጉድጓድ ይቆፈራል፤ግድግዳው ዙሪያውን ይቆማል ፡፡ ግድግዳው ቀጥ ብሎ በትክክል መቆሙን ለማረጋገጥ ደግሞ ሦስት ዙር ማገር ያስራሉ ፡፡ ይህም ግድግዳው ወጣ ገባ እንዳይኖረው ያደርጋል ፡፡

ከላይ በቀረበው መረጃ ላይ አቶ አማኑኤል ጎባና አክለው እንደነገሩኝ የቤቱ አሰራር ቅደም ተከተል በቅድሚያ ቦታ መምረጥ፣ ቦታ መደልደልና መቀየስ ፤ ቀጥሎ የምሰሶ ቦታ መቀየስ ሲሆን ይህም የምሰሶው ቦታ መሀል ላይ ችካል ይቸከልና በችካሉ ላይ ወፍቾ ይታሰራል ፡፡ በአራተኛ ገመድ ይዘው ጫፉ ሹል በሆነ ብረት ዙሪያውን የጭረት ምልክት እያደረጉ በማዞር ክቡ ትክክል እንዲመጣ ያደርጋሉ ፡፡ ቀጥሎ የግርግዳ ጉድጓድ ይቆፈርና ግድግዳው ይቆማል፡፡ ማገር ይማገራል ፡፡ ከዚያ ምሰሶ ይቆምና ጣሪያው በሱ ላይ ይደረጋል የሳር ክዳን ይለብሳል ፡፡ መቃንና ጉበኖቹ ይቸከሉና ቤቱ ሲጠናቀቅ መዝጊያ ይገባለታል ፡፡

ቀደም ሲል በዚሁ ምእራፍ በቅድመ ቤት ስራ ዝግጅት እንደተገለጸው በተለይ በግብአት መሰብሰብ ሂደት ጥንቃቄ ይፈልጋል ፡፡ ይህ ደግሞ ለአሰራር ሂደቱ ወሳኝ ነው የባህላዊ ቤቱ አሰራርን በተመለከተ ደረጃ በደረጃ ቢሆንም ሲቆይ ቤቱ እንዳይዛነፍ፤ እንዳይወድቅና ረዥም እድሜ እንዲኖረው እንጨቶቹ(ግብአቶቹ) ከቤቱ ስራ ቀድመው በጥንቃቄ ይመረጣሉ ፡፡ ይህም ቤቱን ለመስራት ከታቀደና ከተወሰነ በኋላ በባህሉ ለምሰሶ ይሆናሉ ከተባሉት መካከል የምሰሶ እንጨት

ይፈለጋል፤ለግድግዳ የሚሆኑ የእንጨት ዝርያዎች ጥንካሬያቸው ታይቶ የሚሰበሰቡ ሲሆን ለአብነት ጉጋንታ ጩጋ ፤ጋርጋሩዋ ጩጋ፤ ዎጋራ ጩጋ፤ ሜጋራ ጩጋ፤ ሙጫኩዋ ጩጋ፤ ኦንጋሬሪያ ጩጋ፤እነዚህ ሁሉም ለግድግዳ የሚቆረጡ የእንጨት ዝርያዎች ናቸው፡፡ ለማገር የሚሆኑ ደግሞ ፓሪያ፣ሀማካ፣የሚባሉ እንጨቶች ይሰበሰባሉ ፡፡ በመጀመሪያ ቦታ ይመረጣል ፤ ቦታ ይደለደልና ይቀየሳል በሁለተኛ የምሰሶ ቦታ ተለክቶ ይዘጋጃል፤ በሦስተኛው ግድግዳ ይቆማል፤በአራተኛው ማገር ይማገራል ፡፡ ከዚያ ምሰሶ ይቆምና ጣሪያው በሱ ላይ ይደረጋል ፡ በአምስተኛው ቤቱ እየተጠናቀቀ ሲመጣ የሳር ክዳን ይለብሳል ፡፡ በስድስተኛው መቃንና ጉበኖቹ ይቸከላሉ ፡፡ በመጨረሻም ቤቱ ሲጠናቀቅ ኢፊታ የተባለው መዝጊያ እንዲገባለት ይደረጋል ፡፡ ሌላው ሜሾ ቤት የሚባለው ከሆነ በሦስት ወራት ተሰርቶ የሚጠናቀቅ ሲሆን ሌሎቹ ቤቶች የጊዜ ፍጆታቸው እንደ ቤቱ ነው [27]፡፡

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው ወደ ቤቱ አሰራር ከመገባቱ ቀድሞ በግብአት መሰብሰብ ሂደት ላይ ጥንቃቄ እንደሚያስፈልግ ሲሆን ይህም በባህሉ ለቤት ስራ ይሆናሉ የተባሉ እንጨቶች በአግባቡ መመረጥ እንዳለባቸው የሚያስረዳና ለአሰራር ሂደቱ ወሳኝ መሆኑን ያሳያል ግብአቶቹ መመረጣቸው በቆይታ ቤቱ እንዳይዛነፍና ረጅም እድሜ እንዲኖረው ያገለግላል ፡፡ ከዚህ ቀጥሎ ወደ አሰራር ሂደቱ የሚገባ ሲሆን ይህም የራሱ የሆነ የአሰራር ቅደም ተከተል አለው ፡፡ ሌላው ቤቱ ተሰርቶ የሚያልቅበት ጊዜ የቤቱን አሰራር መሰረት ያደረገ እንደሆነ ነው ፡፡

I, **ቦታ መረጣ፣ቦታ ድልደላ** እነዚህ የአሰራር ቅደም ተከተሎች ቀጥለው ቀርበዋል ፡፡

በቡድን አንድ በኪንዶ ዲዳዬ በተደረገ የቡድን ተኮር ውይይት ከተወያዮች መካከል አቶ ኦልኬ ታናቱ የቤቶቹን የአሰራር ቅደም ተከተል በተመለከተ ቦታ መረጣ እና ቦታ ድልደላ ቀዳሚ ተግባሮች እንደሆኑ ሲገልጹ መጀመሪያ ቤቱን ለመስራት የሚሆነው ቦታ ይመረጣል፤ጎርበጥባጣ ከሆነ ይቆፈራል፤ቀጥሎ ጉድጓድ ይቆፈራል፤ጉድጓድ ሲቆፈር ሙሉ ክብ የሚዞረው በመጫሪያ ምሰሶ በሚቆምበት ቦታ ላይ ችካል ይቸክልና በሱ ላይ ዞሮ ሙሉ ክቡ ይቆፈራል፤ሳይሸራረፍ ክቡ ከተቆፈረ በኋላ የመሪ ማቆሚያው ቦታ በክቡ ውስጥ ይቆፈራል ፡፡ ከቦታ መረጣ በኋላ ሁለተኛው የቦታ ቅየሳ ሲሆን ይህንንም የወላይታ ባህላዊ የጎጆ ቤት እንደ መሬት ክብ ሲሆን ቤቱን ለመሥራት ከወሰነው ግለሰብ ጋር በመሆን ቅየሳው ቤቱ እንዴት ይሰራ? በሩ ወዴት አቅጣጫ ቢቆም ይሻላል? የሚለውን መነሻ አድርገው ቦታውን ይቀይሳሉ ፡፡ ግድግዳው ክብ ሆኖ እንዲቆም ተደርጎ እምብርቱ በጠንካራ ችካል ይቸከልና በችካሉ ላይ ሲባጎ ወይም ወፍቾ በማሰር በጫፉ ላይ ሾል ያለ ነገር አስሮ በመወጠር ዙሪያውን በጥንቃቄ ይጫራል ፡፡

---

[27] ቃለ መጠይቅ፣16/10/2016 ዓ.ም ፡፡

ከላይ የቀረበው ሀሳብ እንደሚያስረዳው ቀደም ብሎ ለምሰሶ የሚሆን እንጨት፤የግርግዳ እንጨት የፍልጥ እንጨት፤ተቆርጦ ይዘጋጃል፡፡ ለውስጥ ማገር ደግሞ እንደ ሀማካ ያሉ እንጨቶች፤ቋሚ የመሪ እና የወራጅ እንጨቶች ይሰበሰባሉ፡፡ ለቤት ክዳን የሚሆኑ የሳር አይነቶች ተመርጠውና ታጭደው የሚቀመጡ ሲሆን ለማሰሪያ የሚሆን ወፍቾም ይዘጋጃል፤እነዚህ ከተሰበሰቡ በኋላ ወደስራ የሚገባ ሲሆን የአሰራር ቅደም ተከተሉም ቦታ መረጣ ቀዳሚ ተግባር ሲሆን ከዚህ ቀጥሎ የተመረጠው ቦታ ይደለደልና ይስተካከላል ፡፡

**II, ቦታ ድልደላ፡-** ቦታውን መርጠው ካዘጋጁ በኋላ ቦታውን ይደለድላሉ፡፡ ውሃ ልኩ ትክክል መሆኑን የሚለኩት በእህል ሙቀጫ ሲሆን ይህም ከታች ዳር ሆነው ወደ ላይ ሲያንከባልሉ ሙቀጫው ቀጥ ብሎ ከታች ወደ ላይ ከሄደ ውሃ ልኩ ልክ ነው ብለው ለጥ ያለ ሜዳ መሆኑን ያረጋግጣሉ ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የቤቱን መሰረት ማስተካከል ከአካባቢ አካባቢ የሚለያይ ሲሆን ይህም በተዳፋት አካባቢ ያሉ ሰዎች ለቤቱ መሰረት ስራ ትኩረት ሰጥተው በጥንቃቄ ይሰራሉ ፡፡ ምክንያቱም ተዳፋት አካባቢ ለምሳሌ እንደ ኪንዶ ዲዳዬ፣ባይራ ኮይሻ፣ዳሞት አካባቢ ያሉ ሰዎች የመሰረት ስራው ተደምድሞ መክረሙን ሲያረጋግጡ ቀጥለው ደግሞ እያስተካከሉ ውሃ ልኩ እስኪጠብቅ ድረስ ይቀጥላሉ ፡፡ በሌላ በኩል ሜዳማ አካባቢ የሚኖሩ ሰዎች ብዙም ሳይቸገሩ ውሃ ልኩን ማግኘት ስለሚችሉ ለመሰረት ስራ አይጨነቁም ፡፡ ቀጣዩ ተግባር ላይ የሚመጣው የጣሪያ ስራ ሲሆን ይህም እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡

### 6.3.የወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት የመሬት መለኪያ አይነቶች

በወላይታ ባህል ቤት ሲሰራ ከቦታ ቅየሳ ጋር ተያይዞ የመሬቱን ልኬት ለማወቅ የተለያዩ የመለኪያ አይነቶች ተግባር ላይ ይውላሉ ፡፡ ይህንኑ በተመለከተ አቶ አድማሱ ቱማቶ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፡-

እርምጃ (ታንጓ) ፡- ይህ የልኬት አይነት አንድ ሰው የቻለውን ያህል ለመራመድ እግሩን የሚያነሳበት ልኬት ሲሆን አንድ ታንጓ አንድ ሜትር እንደ ማለት ነው ፡፡ ጭብጦ (ቡቡጡዋ)፡- በክንድ በመለካት ሂደት ውስጥ ጣቶቹን ጨብጦ በመቀነስ የሚካሄድ ልኬት ሆኖ ቡቡጡዋ ማለት አንድ ሜትር እንደ ማለት ነው ፡፡ ስንዝር (ታካሯዋ) ፡- ይህ ደግሞ ከአውራ ጣት ጫፍ መሬት ላይ (ወይም) በሚለካው ነገር ላይ አቁሞ እስከ ሌባ ጣት ጫፍ የሚዘረጋ ልኬት ሲሆን ታካሯዋም አንድ ሜትር እንደ ማለት ነው (ቃለ መጠይቅ፣01/11/2015 ዓ.ም) ፡፡

አቶ አድማሱ አክለውም የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ሲሰሩ ከላይ በተጠቀሱት የመለኪያ አይነቶች አማካይነት እንደሆነ ገልጸዋል ፡፡

ቀጣዩ ደረጃ ላይ የሚመጣው ደግሞ ቦታ ድልደላ ነው ፡፡ ስለዚህ ጉዳይም አቶ ኤርሚያስ ጎባና እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

III, **የጣሪያ ስራ** ፡- ለቤቱ ምሰሶ እንዲቆም ቀጠሮ ተይዞ ሳምንት ሲቀረው የጣሪያ ስራ ይጀመራል፤ለጣሪያ ስራ ቤቱ ከሚሰራበት ቦታ ፈቅ ብሎ ለጥ ያለ መሬት የሚመረጥ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ መዛነፍ እንዳይኖር ስለሚያደርግ ነው ፡፡ ለዚህም አራት ጠንካራ ባለባላ እንጨቶች ይተከሉና ባለባላዎቹ ላይ አራት አግዳሚ እንጨቶች ተጋድመው በላዩ ላይ የጣሪያ ሥራ ይጀምራል ፡፡ የጣሪያ ስራውም ሦስት ክፍሎች ያሉት ሲሆን እነዚህም ማቶት፣ጣሪያ እና ደንገሪጢያ የሚባሉ ናቸው ፡፡ ማቶት (shidhdha) የተባለ ዙሪያውን ክብ የሆነ መቀመጫ መሳይ ነገር ቀጠን ካለ(Hamakka) ከሚባል ጭራሮ እና ወፍቾ (Sussaa) ይሰራል ፡፡ ዋናው ጣሪያ ከማቶቱ ዙሪያ ላይ ጀምሮ ከ20 እስከ 22 ዙር እንደ ቤቱ ስፋትና ጥበት ታይቶ ሊሰራ ይችላል፡፡ የመጨረሻው ዙር ግን የሚዘጋው በአምባር (Mogaa) ነው ፡፡ ዳንጊሪጢያ (Dangerexxiyaa) የሚባለው ደግሞ ከጣሪያው በተወሰነ ርቀት በአምባር ወይም ሞጋ ተጀምሮ በግምት 11ዙር ያህል ይሰራና ያበቃል ፡፡ (ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዶ፣26/12/2015ዓ.ም) ፡፡

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ አድማሱ እንደነገሩኝ የጣሪያ ሥራ ከበድ ያለና ጥንቃቄን የሚጠይቅ ነው ፡፡ ከሌሎቹ በተለየ ሙያን የሚጠይቅ በመሆኑ የሚሰሩ ባለሙያዎችም የተለዩ ናቸው ፡፡ አሰራሩም ለጥ ያለ መሬት ላይ አራት ጠንካራ ባለባላ እንጨቶች ይተከሉና በላያቸው ላይ አራት አግዳሚ እንጨቶችን አጋድሞ በማስቀመጥ የጣሪያው ሥራ ይጀምራል (ቃለ መጠይቅ፣2014 ዓ.ም)

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች ጋር በተዛመደ መንገድ በባህሉ ከጣሪያ ስራ ጋር ተያይዞ ከሚነገሩ ምሳሌያዊ ንግግሮች ለአብነት "Ketta karra gala dadettes ፡ youwa karra qammi dadettes" የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር ቀጥተኛ ትርጉም የቤት ጣሪያ ቀን የሚሰራ ሲሆን የነገር ጣሪያ ለሊት ሲገመድ ያድራል ማለት ነው  ነገርን ማታ ላይ ሲያወሩ ወይም ለጥል ሲያዘጋጁ እንደሚያድሩና ይህም ቀላል እንደሆነ የሚገልጽ ሲሆን የጣሪያ ስራ ግን ጥንቃቄን የሚፈልግ በመሆኑ በቀን መሰራት እንዳለበት የሚገልጽ ነው (ቃለ መጠይቅ፣አለማየሁ፣2014 ዓ.ም) ፡፡ የወላይታ ቤትን ለመስራት ቦታ መረጣ፣ቦታ ቅየሳ፣ቦታ ድልደላና የጣሪያ ስራ ቀዳሚ ተግባራት እንደሆኑ ነው ፡፡

**ፎቶ 9- የጣሪያ ስራው ጅማሬ መሬት በእንጨቶች ላይ**




**ምንጭ፡- በወላይታ ዞን በኦፋ ወረዳ የተሰራው ባህላዊ ቤት ጅምር የጣሪያ ስራ፣ግንቦት2/09/2014 ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ**

**ፎቶ 10፡- ባለሙያዎች የጣሪያ ስራ በመስራት ላይ ሆነው የሚያሳይ ፎቶግራፍ**



ምንጭ፡- ኦፋ ፤በአጥኚዋ የተነሳ፤2014 ዓ.ም




ምንጭ፡- ኦፋ ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣2014 ዓ.ም

ፎቶ 11፦ ያለቀ የጣሪያ ሥራ




ኣፋ ወረዳ፣በአጥ ፈዋ የተነሳ 2014ዓ.ም

**ፎቶ 12፡- ባህር ዛፍ በጣሪያው ሲቀለበስ**




**ምንጭ፡- ኦፋ ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣2014 ዓ.ም**

ፎቶ 13፡- ባህርዛፍ ከተቀለበሰ በኋላ የተጠናቀቀ ጣሪያ



ምንጭ፡- ኦፋ ወረዳ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣ 2014ዓ.ም

### 6.4. በወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት ግንባታ የምሰሶ ሥራ

የምሰሶ ሥራ ከጣሪያ ስራ ቀጥሎ የሚመጣ ሲሆን መጀመሪያ ላይ የምሰሶ መረጣ ይካሄዳል፤ ይህንንም የሚያከናውነው የቤቱ ባለቤት በመሆኑ በባህሉ ‹‹ምሰሶንና ሚስትን የሚያገኘው ባለቤቱ ነው›› ይባላል፤ይህንን በተመለከተ የኦፋ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኡኩሌ ጥላሁን እንደሚከተለው አስረድተዋል ።

የቤቱ ባለቤት ለምሰሶ የሚሆን እንጨት በራሱ ጓሮ ከሌለ ፍለጋውን ከጎረቤት ይጀምራል፤ እንጨቱን እንዳገኘም "የኔ ልጅ ምሰሶ ሁን ብሎ ልብስ ያለብሳል" ለጎረቤቱም በጓሮህ ምሰሶውን ልብስ አልብሻለሁ ይላል ። ጎረቤቱም የቱን ነው ያለበስከው ሲለው አታየውም ጽድ፣ ዝግባ ሞቆታ ወይም ኦቻ የተባለውን እንጨት አለበስኩ ይላል ። እንኳን አለበስከው"በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ፤ልጅህም ይልበስ"በማለት ይመርቀዋል።[28]

በባህሉ ቤት የሚሰራ ሰው ለምሰሶ የሚሆን እንጨት በጓሮው ከሌለ አጠገቡ ካሉ ወዳጆቹ ማሳ ጀምሮ ይፈልጋል ። የሚሆነውን እንጨት እንዳገኘ ከአብራኩ እንደወለደው ልጅ በማሰብ «ልጄ ምሰሶ ሁን» በማለት ይመርቃል ። የእንጨቱ ባለቤትም ያለበሰውን ካየ በኋላ በደስታ «በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ» በማለት ይመርቀዋል ። ሌላው ምሰሶ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ ምሰሶ ሁን ማለት ክበር እንደ ማለት ነው ።

[28].ቃለመጠይቅ፣ 18/09/2015 ዓ.ም ።

ከላይ ለምሰሶ የተመረጠው እንጨት ከሚለብሰው ልብስ ጋር በተገናኘ የቀረበው ምርቃት በብሔረሰቡ  የተለያዩ ትርጓሜዎች ያሉት ሲሆን ይህም ቀጥሎ ቀርቧል፡-

"በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ፤ ልጅህም ይልበስ"

እንጨቱን የሰጠው አባወራ የተከልኩትን ስለወደድክልኝ በቤቴ የጸደቀ ዛፍ ላንተ ቤት ከሆነ በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ፤ልጅህም ይልበስ፤ብሎ ይመርቃል!  የኔ ቤት እንጨት ለዚህ ክብር ከተመረጠ በማለት ነው የሚመርቀው እንጨቱን ይመርጣል፤ የመረጠው እንጨት ላይ ሸማ ወስዶ ያለብሰዋል ። በባህሉ ድሮ ሸማ ዛፍ ላይ የሚወጣው ለሁለት ነገር ነው ። አንደኛው ለምሰሶ የተመረጠውን እንጨት ለማልበስ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ሀዘን እክል ካለ አላፊ አግዳሚ እንዲያየው እንጨቱ ጫፍ ላይ ሸማ ይታሰራል(ቃለ መጠይቅ ፣አድማሱ 2014 ዓ.ም)

ምሰሶ በባህሉ ብዙ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ የሚመረጠው  እንጨት የማይነቅዝና ምስጥ የማይበላው  ነው ። ሌላው በብሔረሰቡ ምሰሶውን የሰጠውም ሆነ የተቀበለው ሰው ክብርና ሙገሳን የሚያገኙ ሲሆን ይህም ዝምድናን መመስረቻ ነው። ከዚህ የተነሳ እነዚህ ሰዎች አንዱ ባንዱ ላይ ግፍ አይሰራብትም ። ምክንያቱም የቤቱን ምሰሶ ከሱ ቤት ስለወሰደ ግፍ ቢሰራብት ይደርስበታል ተብሎ ይታመናል

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ብሔረሰብ ምሰሶ ትልቅ ክብር የሚሰጠው በመሆኑ በባህሉ የምሰሶ እንጨት የተመረጠ በመሆኑ ነቀዝና ምስጥ የማይበላው ነው ። በተጨማሪ ምሰሶውን በሰጠው ሰውና በተቀበለው ሰው መሃከል የጠበቀ ወዳጅነትና ዝምድና ይመሰረታል ። ከዚህም የተነሳ አንዱ ባንዱ ላይ በክፋት አይነሱም ወይም አይበዳደሉም ። ምክንያቱም በምሰሶ መስጠትና መቀበል ስለሆነ ግፍ ከተደረገ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል ። ሌላው ምሰሶውን የሰጠው ሰውና የተቀበለው ሰው በብሔረሰቡ ትልቅ ክብርና ሙገሳን ያገኛሉ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ይሄ መልካም ትብብርና መረዳዳት ያመጣው ወዳጅነት ወደ ብሔረሰቡ እንዲወርድና እንዲሰርጽ ይፈለጋል ።

ምሰሶን ልብስ ከማልበስ ጋር በተገናኘ ተጨማሪ መረጃ የሰጡት የካዎ ኮይሻ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ ባሎሜ አንጁሎ ከላይ ምሰሶን ልብስ ከማልበስ ጋር በተገናኘ የሚከተለውን ሀሳብ አቅርበዋል፡-

በጎረቤቱ ያለውን ምሰሶ ልብስ ማልበሱ ጎረቤቱም ሀሳቡን በደስታ መቀበሉን  ብሔረሰቡ ነገሮችን በቅንነት እንዲያይ ያደርገዋል፤የተንከባከበው እንጨት ቢሸጥ ገንዘብ

ያወጣል፤በብሔረሰቡ ምሰሶ የሚከበር በመሆኑ እንጨቱን የሰጠውም ሆነ የወሰደው በህዝቡ ዘንድ ክብርና ሙገሳን ያገኛሉ ። ምሰሶውን የሰጠው ለዛ ቤት መሰረት እንደጣለና ቤት እንዳቆመለት ስለሚያምንና ስለሚያስብ ደስ እያለው ነው የሚሰጠው ። የሳር ቤቱ ፈርሶ ሌሎች ግብአቶች ለማገዶ ወይም ለቤት መስሪያ ሲሸጡ ምሰሶ ትልቅ ዝናና ክብር የሚሰጠው በመሆኑና የራስ ማንነት መገለጫ ተደርጎ ስለሚወሰድ ምሰሶ አይሸጥም ። ሌላው በንጉስ ቤት ሰው የሚለብሰው ሲሾም ስለሆነ ሹመት(አሰተዳዳሪ) ሁን ለማለት ነው ። በተጨማሪም ምርቃት ባንተ አያብቃ፤ ያንተ መልካምነትና ላንተ የሚሆኑ መልካም ነገሮች ለልጅ፣ ልጅ ይድረስ ይቀጥል እንደ ማለት ነው ።[29]

ከላይ የቀረበው የጽሁፍ ይዘት እንደሚያስረዳው በባህሉ አንድ ሰው ቤት ለመስራት ሲያስብ ቀደም ብሎ የምሰሶ እንጨት ይፈልጋል ። በዚህ ሂደት ውስጥም ለምሰሶ የሚሆነው እንጨት ከጎረቤት ማሳ ካገኘ ወዲያውኑ አዲስ የባህል ልብስ ያለብሰዋል፤ ለምሰሶ የሚሆነውን እንጨት የሰጠው ሰው ቤት የሚሰራውን ጎረቤቱን በኔ ማሳ የበቀለውን መርጠሃልና በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ በማለት ይመርቀዋል ። ምርቃቱም ወዳጅነትንና ዝምድናን መመስረቻ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ ከብሔረሰቡና ከቤቱ ባለቤት ቡራኬን የሚያስገኝ ስራ እንደሆነ ለመግለጽ ነው ።

የቤቱ ባለቤት ሙሉ የባህል ልብሱን ለብሶ በግራ እጁ በመጥረቢያ ምሰሶውን ከመታ በኋላ አጠገቡ ለቆመ ጎረምሳ ይሰጣል ፤ ከዛ ህዝቡ ምሰሶውን ይጥለዋል ። ባለቤቱ የባህሉን ልብስ ለብሶ ተዝናንቶ ምሰሶው ፊት ለፊት እየተረማመደ ይፎክራል፤ ይዘፍናል፤ ይጨፍራል። ዘመድ፣ ጓደኛ፣ ወዳጅ የሆነ ሁሉ በጭፈራው ይፎክራሉ፤ ይዘፍናሉ ። ምሰሶውን ይዘው ወደ ቤቱ ቀረብ ሲሉ ባለቤቱ ይድረስ ፤ መንፈስ ቅዱስ ይቅረብ፤ እግዚአብሔር ይቅረብ፤ እንግዳው ይድረስ ይላሉ[30]።

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው የቤቱ ባለቤት የወላይታን ባህላዊ ልብስ ለብሶ ምሰሶውን በያዘው መጥረቢያ ከመታ በኋላ አጠገቡ ላለ ጎረምሳ ይሰጣል፤ ቀጥሎም ህዝቡ ምሰሶውን ይጥለዋል፤ከዚያ በኋላ የቤቱ ባለቤት የባህል ልብሱን ለብሶ በኩራትና በመዝናናት ስሜት ወደዚያና ወደዚህ እየተረማመደ ይፎክራል ፤ይዘፍናል ፤ጨፍራል። የቤቱን ባለቤት የሚያወድስ ዘፈን እየዘፈኑና እየፎከሩ ምሰሶውን ወደ ቤቱ ያመጣሉ ።

---

[29] . ቃለ መጠይቅ ጥቅምት 22/02/2015 ዓ.ም ።

[30] . ኡኩሌጥላሁን፣አፋ፣16/09/2015/ዓ.ም ።

በባህሉ ምሰሶ በጣም የተከበረ ነገር ነው ፡፡ በባህሉ  አንድ ሰው ቤት ለመስራት ሲያስብ የምሰሶ እንጨት በራሱ ጓሮ ከሌለ  ፍለጋውን ከጎረቤቱ ቤት፤ ከዘመዱ ቤት ይጀምራል ፡፡ የምሰሶው እንጨት ከጎረቤት እርሻ ውስጥ ከተገኘ ሄዶ ጠይቆ መውሰድ ይችላል ፡፡ ገንዘብ አይከፈልም የፈለገ ትልቅ ዛፍ ቢሆን እንኳን ለምሰሶ ተብሎ ከተጠየቀ በነጻ ይሰጣል፤እኔ ቤት ልሰራ ነው ለምሰሶ የሚሆን እንጨት አንተ ዛፍ ውስጥ ስላገኘሁ ስጠኝ ተብሎ ሲጠየቅ የእንጨቱ ባለቤትም እግዚአብሔር ያድርስህ ውሰድ ይለዋል ፡፡ የሚመረጠው እንጨትም ወፍራምና ቀጥ ያለ መሆን አለበት ፡፡ ለምሰሶ የሚሆነው እንጨት ዋንዛ ወይም ጥንካሬ ያለው የዛፍ አይነት ነው ፡፡ የቤቱ ባለቤት ቤት በዚህ ቀን ምሰሶ አቆማለሁ ብሎ ይቀጥራል  አስራ አምስት ቀን (ወር ) ሲቀረው ለህዝቡ ቀጠሮ ይነገራል ፡፡ በቀኑ ህዝቡ ሌላ ቀጠሮ አይዝም ፡፡ በተነገረበት ቦታ በቀጠሮው ቀን (ምሰሶው በሚቆምበት ቀን) በዚሁ ቀበሌ ውስጥ እርሻ አይታረስም፤ በባህሉ ማንም ሰው ያንን የጎረቤቱን ቤት የመስራት ግዴታ አለበት ፡፡ አያምጣውና በአካባቢው ሰው ካልሞተ በስተቀር የምሰሶ ስራው በእለቱ አይቀርም ፡፡ ስለዚህ ሰው መጥቶ ነው የሚያቆመው ፡፡ [31]

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ብሔረሰብ የምሰሶ እንጨት ትልቅ ቦታ ይሰጠዋል ፡፡ ቤት ለመስራት የፈለገ ግለሰብ ለምሰሶ የሚሆን እንጨት በጓሮው ከሌለ  ከጎረቤት ወይም ከዘመድ ሊወስድ ይችላል ፡፡ ለወሰደው የምሰሶ እንጨት የሚከፈል ክፍያ የለም ፡፡ ምሰሶው በሚሰጠውና በሚቀበለው ሰው መሃከል ዝምድና እንዲፈጠር ያደርጋል ፡፡ ሌላው የምሰሶውን እንጨት ከማሳ  በጋራ አምጥተው በጋራ ያቆማሉ ይህ ደግሞ አንድነትንና መተባበርን ይገልጻል ፡፡ ምሰሶው የሚቆምበትን ቀን የቤቱ ባለቤት ይገልጻል ፡፡ በባህሉ ምሰሶ በሚቆም ቀን የአካባቢው ሰዎች እርሻና ሌሎች ስራዎችን አይሰሩም ፡፡ በባህሉ ባህላዊ ቤት ሲሰራ በትብብር እንደሆነ የሚያሳይ ነው ፡፡

ይሄ በብሔረሰቡ መካከል ያለ የመተባበር ባህል በንድፈ ሀሳብና በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ በምዕራፍ ሁለት በንድፈ ሀሳብ ክፍል በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ስር እንደተገለጸው Emile Durkheim እንደገለጸው በጥንት ዘመን ቀደምት የጥንት ማህበረሰቦች ትብብር ሁሉንም ሰው በአንድነት እንዲይዝ አድርጓል ፡፡ Durkheim የጋራ እሴቶች፣ የጋራ ምልክቶች እና የልውውጥ ሥርዓቶች በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የመተሳሰሪያ መሳሪያዎች ሆነው ይሠሩ እንደነበር በንድፈ ሀሳብ የገለጸ ሲሆን ይህንንም ተፈጥሯዊ መተባበር ሲል ጠርቶታል ፡፡ ሌላው አንድ ማህበራዊ ሁኔታ

[31] . ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዴ፣25/10/2015 ዓ.ም ፡፡

የሚገለጸው ከሌላ ማህበራዊ ሁኔታ አንጻር እንጂ ከስነ ልቡናዊ ፍላጎት አንጻር ሊሆን አይገባም የሚል አቋም የያዘ ሆኖ የአንድ ማህበረሰብ ሁለንተናዊ እንቅስቃሴ በማህበራዊ መዋቅሩ ስር ነው በዚህ ውስጥም ባህሉ ለማህበረሰቡ የሚሰጠውን ተግባር የሚቆጣጠሩ ህግና ደንቦች አሉ ይህም ከግለሰባዊ ፍላጎት ይልቅ ለማህበረሰቡ ህልውና ቅድሚያ ይሰጣል ። የማህበረሰቡ ማህበራዊ የመዋቅር ሥርዓት ቀጣይነት የሚኖረው በማህበራዊ ህይወቱ ሂደት ነው (Parsons and Bales፡ 1955)፡፡ ከዚህ በተጨማሪ Prown ‹‹ More Representative. They offer the possibility of a way to understand the mind of the great majority of Non literate people, past and present, who remain otherwise in accessible except through impersonal records and the distorting view of a contemporary literary elite ›› ቁሳዊ ባህል ጥንትም ሆነ ዛሬ የተማሩና ያልተማሩ የማህበረሰብ ክፍሎች በቁሶቹ አማካይነት ባህላቸውንና እምነታቸውን እንደሚገልጹበት የሚያሳይ ነው (Prown 1982፡ p.2-3)፡፡

### 6.5.የምሰሶ ውክልናና በስራው ላይ የሚቀርቡ ዘፈኖች

በወላይታ ባህላዊ ቤት ሲሰራ ምሰሶው ከተግባሩ ባለፈ ማህበራዊ ውክልና አለው ። ሌላው ከምሰሶ ስራ ጋር ተያይዘው የተለያዩ ዘፈኖች የማበረታቻና የሀይል ማሰባሰቢያ ዘፈኖች ይቀርባሉ ። እነዚህም ምሰሶው ከተቆረጠ በኋላ ቤቱ ወደሚሰራበት ቦታ እየጎተቱ ሲወስዱ፤ምሰሶ ተጎትቶ መጥቶ ሰፈር ሲደርስ፤ምሰሶ ሲቆም የሚዘፈኑት ዘፈኖች በቅብብሎሽ የሚቀርቡ ሲሆን እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ።

- **ምሰሶ ሲጎተት የሚዘፈን ዘፈን (Tuussaa Goocchiiddi yexxiyo yettaa)**

የምሰሶውን እንጨት ከፊት፣ ከኋላና መሃል ላይ በቁጥር በርካታ ሰዎች ተሸክመው ቤቱ ወዳለበት ሲሄዱ እነዚህን ዘፈኖች በቅብብሎሽ ይዘፍናሉ ፡፡

I). Hoollee hoo….ሆሌ ሆሆ (ህዝቡ)

Hoollee hoo hoo = ሆሌ ሆሆ (ህዝቡ

Tuussaa hoo hoo = ምሰሶ ሆሆ

Yayyaasa naawa yayyikke = ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

Asawu Yayyaasa naawa yayyikke = ሰዎች ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

Piriixuwa pinttenna Boojaa = በግልቢያ የማይሻገሩት ገደል

Durishin duuxxida dullee = በጭፈራ የደከመ መቀመጫ

Duufuwan keexxida qeesee hoo hoo = ቤተክርስቲያን ሚያድሩ ቄሶች

Yayyaasa naawa yayyikke = ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

Asawu Yayyaasa naawa yayyikke = ሰዎች ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

(ቃለመጠይቅ፣ደገፉ፣ሶዶዙሪያ፣11/12/2015፣ ዓ.ም)።

II). Ganamo Galttoori Ciggaa = ጪጋ የጋልቶሬ ጋናሞ ልጅ

Ciggenna citiki giigaa = በተፈጥሮ ውብ የሆንክ

Hardiido Haddachchi Bakee = ባኬ የሀዳቼ ሀርዲዶ ልጅ

Bakkeero Ololo Diimoo = ዲሞ የኦሎሎ ባኬሮ ልጅ

Ololo Ooyyato Dalggaa = ዳልጋ የኦዮቶ ኦሎሎ ልጅ

Yayyaasa naawa yayyikke = ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

Asawu Yayyaasa naawa yayyikke = ሰዎች ፈራችሁ አባቴ ይሙት አልፈራንም

Wajay Waalaana Albbeeshsho = ዋጃ ላይ ያለኸው አልቤሾ ዋላና

(ቃለመጠይቅ፣አድማሱ፣ሶዶዙሪያ፣11/12/2015፣ዓ.ም)።

ከላይ የቀረቡት  የዘፈን ግጥሞች ሁለት ፋይዳዎች ያላቸው ሲሆን የመጀመሪያው  ከምሰሶ ጉተታ ጋር የተያያዘ ሆኖ ሰዎች ሀይላቸውን አስተባብረው ምሰሶውን እንዲጎትቱ የሚያግዝ ነው ። ሁለተኛው በባህሉ  ለምሰሶው  በሚዘፈኑ ዘፈኖች ውስጥ በአካባቢው  ስመ ጥር የሆኑ ጀግኖችን ከነአካባቢያቸው በመጥራት ማወደስና ዝናቸውን ከፍ የማድረግ ተግባር ያለው ሲሆን ይህም በምሰሶው ስራ ላይ ያሉ ሰዎች በዘፈኑ የተጠቀሱ ጀግኖችን አርአያ እንዲከተሉ የሚያደርግ ተግባር ነው ። ለምሳሌ፡- ዋጃ ላይ ያለኸው አልቤሾ ዋላና Wajay Waalaana Albbeeshsho በማለት ሲሆን ይህም ዋጃ በሚባል አካባቢ ተወልደህ ጀግንነትህን፣ጉብዝናህን ያሳየኸው እንደ ማለት ሲሆን ቀደም ሲል የነበረ ጀግናን ለማወደስ ነው ።

ምሰሶውን እያረፉ በሚጎትቱበት ሰዓት ምሰሶው በጣም እየከበዳቸው ሲመጣ የሚከተለውን የማበረታቻ ዘፈን እየተቀባበሉ ያዜማሉ ።

Hayyaa maaddeesi (maaddees)-coray (ብዙሀኑ) እሰይ እረድቶናል

Goday maaddeesi (maaddees)-coray (ብዙሀኑ) ፈጣሪ አግዞናል

Nuna maaddeesi (maaddees)-coray (ብዙሀኑ) እኛን እረድቶናል

Wolqqaa immeesi (maaddees)-coray (ብዙሀኑ) ጉልበት ሰጥቶናል

የቀረበው የዘፈን ግጥም ሁለት መልዕክቶችን ይዟል ። የመጀመሪያው የፈጣሪን እገዛ መሰረት አድርገው እንደጨረሱ በማሰብና ተስፋ በማድረግ ሀይላቸውን አስተባብረው ምሰሶውን እንዲጎትቱ የሚያግዝ ነው ። ሁለተኛው ደግሞ በስሩ ፈጣሪ እንዲያግዛቸው ምልጃ ያለበት ሆኖ ጸሎታቸው እንደተሰማ የሚገልጽ ምስጋናና ደስታን ያዘለ ነው ።

**ፎቶ 14፡- ምሰሶውን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሲያዘጋጁ የሚያሳይ**



**ምንጭ፡- በወላይታ ዞን፣በኦፋ ወረዳ፣ግንቦት/15/2014 ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ**

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በባህሉ ምሰሶውን ሲጎትቱ በሚከብዳቸው ሰዓት በቀኝ በኩል የሚጎትቱት እሰይ እግዚአብሔር ይረዳናል ሲሉ በግራ በኩል ያሉት ደግሞ እሰይ ያግዘናል ይላሉ ። የሚዘፍኑት በህብረት እየተቀባበሉ ሲሆን ይህም አንድነትን ከማሳየት ባሻገር ከድካም ስሜት እንዲወጡና ጥንካሬ እንዲሰማቸው ያደርጋል ።

ምሰሶ ተጎትቶ መጥቶ ሰፈር ሲደርስ የሚዘፈን ዘፈን

Hoo hoo = **ሆሆ ሆሆ**

Tuussoo hoo = **ምሰሶ ሆሆ ሆሆ**

Haaya maadda xoossoo = **እሰይ እግዚአብሔር አግዘን**

Hoo ho sirinttaa sirimma = **ሆሆ ሆሆ አማስል ፣አሽከርክር፤**

Hoo keettaaway = **ሆሆ ሆሆ ባለቤቱ**

Keettaaway Imattay = **ባለቤቱ እንግዳው**

Hoo keettaaway = **ሆሆ ሆሆ ባለቤቱ**

Keettaaway Imattay = **ባለቤቱ እንግዳው**

Hayya nu gakkoos = **እሰይ እኛ ደርሰናል**

Hayya nu gakkoos = **እሰይ እኛ ደርሰናል**

ምሰሶው እንግዳው ይምጣልን በማለት ከበሮ እየመቱ በእልልታና በጭፈራ ደስታቸውን ይገልጻሉ (ቃለመጠይቅ፣ዲዳዮ ቃልቶሬ፣20/09/2014) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በባህሉ ለምሰሶ ከሚሰጠው ክብር የተነሳ የሚዘፈን ዘፈን ሲሆን ባለቤቱ ይድረስ እንግዳው ይድረስ በማለት ምሰሶውን፣የቤቱን ባለቤትና ቤቱን ያወድሳሉ ፡፡ ሌላው ምሰሶው ቶሎ እንዲደርስላቸው መፈለጋቸውን ከማሳየቱም ባሻገር ለትልቅ እንግዳ እንደሚደረገው አቀባበልና ክብር ለምሰሶም ክብር ይገባዋል እንደ ማለት ነው ፡፡

ምሰሶው በዘፈን ታጅቦ መጥቶ ሰፈር ሲደርስ የሰፈሩ ሴቶች በሙሉ ወጥተው በከበሮ፣በዘፈንና በእልልታ ያጅባሉ ፡፡ ቀጥሎ ምሰሶውን ወደ ቤት አስገብተው ያቆማሉ ፡፡ ከዚህ በኋላ ልክ እንደ ቤቱ ባለቤት ሁለት አይነት ዝግጅት ይደረጋል ፡፡ የመጀመሪያው ቤቱን ሌላ ቀን ለመስራት በቀጠሮ መለያየት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምሰሶውን አቁመው የመሄድ ቀጠሮ ነው ፡፡ ይህም የሚወሰነው በቤቱ ባለቤት ሲሆን እሱም ዛሬ ምሰሶ ታቆማላችሁ ፤ ሌላ ቀን ቤቱን ትሰራላችሁ በማለት እቅድ ሊያሲዝ ይችላል ፡፡[32]

---

[32] . ቃለ መጠይቅ፣አማኑኤል አይዴና ኤርሚያስ ጎባና፣24/09/2015 ዓ.ም ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ  በባህሉ ለቤት መስሪያ የተመረጠው የምሰሶ እንጨት የተከበረ በመሆኑ ወደ ቤቱ አካባቢ ሲደርስ የሰፈሩ ሴቶች ከየቤታቸው በመውጣት በከበሮ፣በዘፈንና በእልልታ ያጅባሉ ። እንደ ባለቤቱ ዝግጅትና ፍላጎት ምሰሶውን ባቆሙ ቀን የቀረው የቤት ስራ እንዲቀጥል ወይም  በቀጠሮ ሌላ ቀን እንዲሰራ መመሪያ እንደሚሰጥ የሚገልጽ ነው ።

ከዚህ በታች የቀረበው የዘፈን ግጥም ምሰሶውን እያቆሙ የሚዘፈን ሲሆን ይህም ስለምሰሶው ትልቅነት፣ክብደትና ክብር የሚገልጽ ነው ። በዘፈኑ ወቅትም ምሰሶውን ወደ ላይ፣ወደታች አሽከርክር፣ወደቤት አሽከርክር እያሉና እየተቀባበሉ በመዝፈን ሀይላቸውን ሰብስበው በትብብር እየዘፈኑ ምሰሶውን ያቆማሉ ። በዚህም ወንዶቹ ሲዘፍኑ እናቶችና ወጣቶች ምሰሶው በመቆሙ የተሰማቸውን ደስታ ከበሮ እየመቱ በእልልታ እየጨፈሩ ይገልጻሉ ። ከዚህ ቀጥሎ ዘፈኑም እንደሚከተለው ቀርቧል ።

Heello yaaho= **ሄሎ ያሆ**

Hayyo Hoyyo = **ሄሎ ያሆ**

Tussay Deexo = **ምሰሶ ከባድ (ክብር) ነው**

Deree bayra = **ህዝቡ ታላቅ ነው**

Daannay Daanna = **የሚኖረው ይኖራል**

Aaway aawa = **አባት አባት ነው**

Kaaray kaara = **ጣሪያ ጣሪያ ነው**

Dugekko sirimana = **ወደታች አሽከርክር**

Pudekko sirimana = **ወደላይ አሽከርክር**

Soxade sirimma = **ወደ ቤት በኩል አሽከርክር**

Soqommo sirimma = **ወደ ቤት ውስጥ አሽከርክር**

ምሰሶውን ወደ ሚሰራው ቤት አጠገብ ካመጡ በኋላ ቤቱ ውስጥ ሲገባ ቤቱን እንዳይጎዳው ከውጪ ሁለት ባላ እንጨቶች ከውስጥ ሁለት ባላ እንጨቶች ይደረጋል ። ቀጥሎ ዞንግልሳ የተባለ ምሰሶ የሚያርፍበት እንጨት ይቆማል ። በተጠቀሱት እንጨቶች እገዛ ምሰሶው የቤቱ ግድግዳ ሳይነካ በግድግዳው አናት ላይ ተደርጎ ወደ ቤት ይገባል ። በኋላም  ዛሮ ዛፊያ በተባሉ

ማገሮች ምሰሶው ከግድግዳ ጋር ታስሮ እያንዳንዱ የሚሰራበት ወፋፍራም ማገር በምሰሶው ጣሪያ ይመጣል ።

ቤቱን ከ20-30 በሚሆኑ ዛሮ ዛፊያ እያደረጉ ጣሪያና ዛሮ ዛፊያ አብረው እያገናኙ ቤቱን ይመልሳሉ[33] ። በሌላ መልኩ አቶ ታደሰ ኮይራ እንደነገሩኝ  ምሰሶ የግድግዳና የወራጅ እንጨቶችን፤የክዳን ሳርና ሌሎች ግብአቶችን ሰብስቦ ይይዛል ። አባወራም እንደ ምሰሶው ቤተሰቡን በሙሉ ሰብስቦ ያስተዳድራል፤በስሩ ያኖራል ። ምሰሶ ወፍራምና ጠንካራ እንጨት በመሆኑ ጥንካሬው ተጠብቆለት በቡድን ሆነው በቅብብሎሽ እየዘፈኑ ያመጣሉ ። ሌላው ምሰሶ ብዙ ነገሮችን የሚሸከም በመሆኑ ንቅናቄ ኖሮት የተዛባ እንዳይሆን በአራቱም ማዕዘን ወይም በቁጥር በርከት ብለው ባሉበት  አንዳንድ ወራጅ እንጨት በመያዝ የምሰሶው ጣሪያ ላይ ይወጣሉ ። ጣሪያው ላይ ሲያስሩ መመሪያ የሚሰጡት ተጠሪዎች እየዞሩ በመመልከት ወደ ምስራቅ፣ሰሜን፣ምዕራብ እንዳያዘነብል ሚዛኑ ሁሉ በትክክል እንዲጠበቅ መመሪያ ይሰጣሉ ። በመጨረሻም አፈሩን መልሱት ይባላል፤ አፈሩ ይመለሳል ። “ምሰሶው እንደ አባወራው ነው” ይላሉ ። ይህንንም ባለቤቱ ታታሪ፣ጎበዝና አቅም ያለው መሆኑን ለመግለጽ ነው [34]።

[33].ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ ገኛቦ፣15/10/2015 ዓ.ም ።

[34] . ቃለመጠይቅ፣10/10/2016.ዓ.ም ።

ፎቶ 15 ፡- ምሰሶ ተቆርጦ ተቀምጦ የሚያሳይ



ምንጭ ፡- ሶዶ ዙሪያ ፣ በረዳት ፎቶ አንሺ የተነሳ፣2014ዓ.ም

ፎቶ 16፡-ምሰሶውን ወደ ቤቱ ለመውሰድ ሲያዘጋጁ የሚያሳይ



ምንጭ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርስቲ ዋናው ጊቢ ግንቦት/10/2014 ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ

ፎቶ 17፡-ምሰሶውን የማቆም ሂደትን የሚያሳይ



ምንጭ፡- በወላይታ ዞን፣በኦፋ ወረዳ፣ግንቦት/15/2014 ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ

ምሰሶው እንደ ቆመ ወራጅ አጠና እንጨት /Zaaro zaafiyaa/ ከውጭ በኩል ዙሪያውን ተተክሎ አምስት ወይም ስድስት የሚሆኑ ጉልበት ያላቸው ወንድ ሞያተኞች ወራጅ ዛፉን በቆልማማ መያዣ /Hinggitaa/ እየሳቡ በጣሪያው ላይ በማሰር ይሰራሉ ።

የምሰሶና ጣሪያው ሲሰራ መጀመሪያ የምሰሶው መትከያ ጉድጓድ 3 ክንድ ይቆፈራል ። ከምሰሶው ጫፍ 3 ክንድ ተለክቶ በመሮ የጣሪያ ማንገቻ / ምጫፍሌ /ቀዳዳ ተበስቶ ምጫፍሌው ይሰካል ። የጣሪያ ማስገቢያ የምሰሶው ጫፍ ተድበልብሎ ይጠረባል ። ምሰሶውን አምጥተው ያስገባሉ ። ህዝብ በተጋደመው ምሶሶ ጣሪያ ለማምጣትና ለማስገባት በህብረት ይሄዳሉ ። ጣሪያው ሲመጣ ሴቶች በእልልታና በከበሮ እየጨፈሩ ሲቀበሉ ያመጡት ሰዎች በተጋደመው ምሰሶ ጫፍ ላይ ጣሪያውን ይሰካሉ ። ሕዝቡ በተቆፈረው ጉድጓድ ምሰሶውን በህብረት ያቆማሉ

**ሀ.ምሰሶና ማህበራዊ ክብር** ፡- በወላይታ ብሔረሰብ ምሰሶ በሚጎተትበት ወቅት ከጥንት ጀምሮ በባህሉ ደንብ ሆነው የተደነገጉ መመሪያዎች አሉ ። ከነዚህም አንዱ ማህበራዊ ክብር በመሆኑ በዚህ ላይ ጥንቃቄ ይደረጋል ። ይህን ጉዳይ አስመልክተው የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ወልደማሪያም ሲገልጹ በወላይታ ብሔረሰብ “ምሰሶን ማንኛውም ሰው እንዲጎትት አይፈቀድለትም” ይባላል ።

በብሔረሰቡ ምሰሶ እንዲነትቱ የሚፈቀድላቸው ማህበራዊ ክብር[35] ያላቸው ወንዶች ናቸው ። ብሔረሰቡን የሚመሩ ሰዎች ምሰሶ በሚነተት ቀን ማህበራዊ ክብር የሌላቸው ወንዶች ጉተታው ላይ እንዳይሳተፉ ክትትልና ጥንቃቄ ያደርጋሉ ። ከዚህ የተነሳ ምሰሶ ለመነተት ከመጡ ወንዶች መካከል ለማህበራዊ ክብር ያልበቁ የሚባሉ ያልተገረዙ ልጆች ከመጡ ያንን ምሰሶ እንዲነትቱ አይፈቀድም ። ይህም በባህሉ ያልተገረዙ ወንዶች ልጆች ለማህበራዊ ክብር አልበቁም ተብሎ ስለሚታመን ነው ። በባህሉ የሚገረዙትም ለማህበራዊ ክብር በቅተዋል ተብሎ ሲታሰብ ሲሆን አንድ ሰው ሙሉ ሰው ነው የሚባለው ለማህበራዊ ክብር በቅቷል በብሔረሰቡ በማህበራዊ ህይወት ውስጥ ተሳትፎ ማግባት ይችላል ። ቤት መስራት ይችላል፤የእድር አባል ሊሆን ይችላል ተብሎ በሚታሰብ ሰዓት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ ወልደ ማርያም ልሳኑ፣03/10/2015 ዓ.ም)።

በወላይታ ባህል ማህበራዊ ክብር ትልቅ ቦታ የሚሰጠው ሲሆን ይህም ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት ሁሉም ሰዎች ምሰሶውን እንዲነትቱ አይፈቀድም ። ምክንያቱም ምሰሶውን ለመነተት ከመጡ ሰዎች መካከል ያልተገረዙ ወጣቶች ምሰሶውን እንዲነትቱ ስለማይፈቀድ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች በዚህ ጉዳይ ጥንቃቄ ያደርጋሉ ።

ከላይ ከቀረበው የጽሁፍ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ባህል ምሰሶ እንዲነትቱ የሚፈቀድላቸው ለማህበራዊ ክብር የበቁ ወንዶች ናቸው፤በባህሉ ከማህበራዊ ክብር መገለጫዎች አንዱ ግርዛት ነው ። በዚህም የተነሳ ያልተገረዙ ወንዶች የምሰሶውን እንጨት መነተት በባህሉ አይፈቀድላቸውም ። በባህሉ ወንድ ልጅ የሚገረዘው ለማህበራዊ ክብር በቅቷል ተብሎ ሲታሰብ ነው ። ወንድ ልጅ የሚገረዘውም ለአቅመ አዳም ደርሷል፤ማግባት ይችላል ተብሎ ሲታሰብ ነው። ስለዚህም ምሰሶው ቤት ወደሚሰራበት ሲመጣ ማህበራዊ ክብር የሌላቸው ወንዶች እንዳይነትቱ የብሔረሰብ ተጠሪዎች ክትትልና መመሪያ ይሰጣሉ ። ሌላው ምሰሶ መነተት ባይፈቀድላቸውም በጭብጨባ አጅበው መምጣት ይችላሉ ።

---

[35] . በብሔረሰቡ ወንድ ለጋብቻ ደርሷል ተብሎ ሲታሰብ ነው የሚገረዘው፤በባህሉ በግርዛት ወቅት ላይ ፈረስ ጋልቦ፣አደን ሄዶ፤አውሬ አድኖ የግዳይ ምልክት የሆነውን አምጥቶ ከቤተሰብ ሽልማት(ዳጋ) ይወስዳል። በባህሉ ይህን የሚያሳልፍበት ዝግጅት አለ። ይህንን ሂደት ያለፈ ወንድ ምሰሶ መነተት ይፈቀድለታል። ግርዛት የማህበራዊ ክብር ሽግግር ነው። ይህንን የሽግግር ሥርዓት ያላደረጉ ሰዎች ግዙፍ ቢሆኑ እንኳን በባህሉ ምሰሶውን እንዲነኩ አይፈቀድላቸውም።ያልተገረዙ ወንዶች ቆመው ይጠብቃሉ፤እጅ ያጨበጭባሉ እንጂ ምሰሶው ላይ እጃቸውን አያሳርፉም(ቃለ መጠይቅ፣ ወልደ ማርያም ልሳኑ፣03/10/2015ዓ.ም)

ፎቶ 18፡- ምሰሶውን የማቆም ሂደትን የሚያሳይ



ምንጭ፡- በወላይታ ዞን፣ በኦፋ ወረዳ፣ግንቦት/10/2014 ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ

በወላይታ ባህል ምሰሶ ትልቅ ክብር የሚሰጠው ነው ፡፡ ምሰሶ ለብዙ ነገሮች በውክልና የሚቆም ሲሆን ብዙ ፍቺዎችን በስሩ ይይዛል ፡፡ ይህንኑ በተመለከተ የኦፋ ነዋሪ የሆኑት አቶ ታደሰ ኮይራ ሲገልጹ ምሰሶ የሚቀረጠው የቤቱ ግድግዳ ስራ በሚጠናቀቅበት እለት ሲሆን ቤቱ ከመቆሙ በፊት አይቆረጥም ፡፡ ምክንያቱም ምሰሶ ክብር ስለሆነ ተቆርጦ ከቆየ ውሻና ሌሎች ምሰሶውን የሚያረክሱ ነገሮች ምሰሶውን አቋርጠው ያልፋሉ ተብሎ ስለሚገመት ነው ፡፡ የወላይታ ህዝብ ከጥንት ጀምሮ ብሳና እና ብርብራ የእንጨት አይነቶች ለምሰሶ ቢቆሙ መቅሰፍት ይመጣል ብለው ስለሚያስቡ (ስለሚፈሩ) እነዚህን እንጨቶች አይጠቀሙባቸውም ፡፡ ለምሰሶ ቢቆሙ ተስማሚ ተብለው የሚታመኑት ዋንዛ፣ጥቁር እንጨት፣ከበረሃ የሚገኙ Guuganttaa የተባሉ እንጨቶች እንደሆኑ ገልጸዋል ፡፡[36]

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በብሔረሰቡ በወላይታ ባህል መሰረት ምሰሶ ትልቅ ክብር አለው ፡፡ ምሰሶ ቤትን ይሸከማል ስለዚህም ሲቆረጥም ሆነ ወደ ቤት ሲመጣ ከውሻና ሌሎች ነገሮች ጥንቃቄ ይደረጋል ፡፡ ሌላው በህዝቡ ለምሰሶ ተስማሚ የሆኑ ተብለው

36 . ቃለ መጠይቅ፣ታደሰ ኮይራ፣20/10/2015 ዓ.ም ፡፡

የሚታመንባቸው ዋንዛ፣ጥቁር እንጨት፣ከበረሃ የሚገኙ ጉጉንታ (Guuganttaa) የተባሉ ሲሆኑ ብሳና እና ብርብራ የተባሉ የእንጨት አይነቶች ደግሞ መቅሰፍት ያመጣሉ ተብሎ ይታመናል

በሌላ መልኩ አቶ አድማሱ ቱማቶ ለምሰሶ ተስማሚ ስለሆኑት እና ለምሰሶ አይሆኑም ስለተባሉት እንጨቶች ሲገልጹ በባህሉ ባህላዊ ቤት ሲሰራ ዋላሴኖ የሚባለውን የእንጨት አይነት ለምሰሶ አይጠቀሙም ። ምክንያቱም ይህ እንጨት ለምሰሶ ከቆመ አብዛኛውን ጊዜ ሰው ይጣላል፤በቤተሰቡ ውስጥ ፍቅር ይጠፋል ተብሎ ስለሚታመን ነው ። ሌላው የብሳና እንጨት እርኩስ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ለምሰሶ አይሆንም ። በባህሉ ለምሰሶ ቢሆኑ በቤት ውስጥ ፍቅርና በረከት ያመጣሉ ንጹህ ናቸው ተብለው የሚታሰቡት የእንጨት አይነቶች ጥቁር እንጨት፣ዋንዛና እድሜ ጠገብ ዛፍ ናቸው [37]።

በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ሲሰራ ለምሰሶ ከሚሆኑ የእንጨት አይነቶች ተመርጦ ይደረጋል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በባህሉ ምሰሶ የተከበረና ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ ቀደም ሲል ተስማሚ ናቸው ከተባሉት እንደ ዋንዛና ጥቁር እንጨት…ውጪ እርኩስ ናቸው በረከት ያጠፋሉ፤ሰው ያጣላሉ ስለሚባሉ ለምሰሶ አይሆኑም ።

ምሰሶ ማለት ተሸካሚ ማለት ነው ። በብሔረሰቡ ትላልቅ ሰዎችን ይወክላል ። ንጉስ ፣ ባል፣ ወንድ ልጅ፣ በምሰሶ ይመሰላል ። በባህሉ ምሰሶ ማንኛውንም ማህበራዊ፣ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚሸከም ተደርጎ የሚወሰድ ስለሆነ በትላልቅ ስራ በተለይ ጀብድ የሰሩ ሰዎች ካና ባይዚያ፣ ዱቡሻ ፎጊያ፣ ዳናባ አይሲያ፣ ተብለው በሚጠሩ ሰዎች ዝግጅት ላይ በዓመት አንዴ የተሰበሰበ ግዳይ ለንጉስ ተሰጥቶ እዛ ላይ ካዎ ዛናቃ በሚባለውና በዓመት አንዴ በሚደረገው በዘመን መለወጫ በዓል በንጉሱ ቤት በሚዘጋጀው የግብር ሥርዓት ላይ ከሚሰጡ ምርቃቶች መካከል አንዱ "ምሰሶ ሁን "ይባላል ። በጣም ትልቅ የህዝብ መሪ ፤የአገር መሪ ፤የቤተሰብ መሪ ሁሉ መሪ ሁን ተብሎ ምርቃት ይደረጋል ። ሁሉንም ነገር አንተ ቻይ ሆነህ፣ታጋሽ ሆነህ፤በትከሻህ ይዘህ ሁሉም ነገር ባንተ ይሁን አንተ ሁሉን ነገር ተሸክመህ አሻግራቸው ተብሎ ምርቃት የሚሰጥበት ነው ። ይሄ ምሳሌ ተይዞ ምሰሶ ይመረጣል ።[38]

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ብሔር ምሰሶ ማለት ሁሉን ነገር የሚሸከም፣ትልልቅ ውክልናዎችን የያዘ፣ማህበራዊና ፖለቲካዊ ጉዳዮችን የሚሸከም፣እንደ ሀገር

---

[37] .ቃለመጠይቅ፣አድማሱ ቱማቶ፣ሶዶ ዙሪያ፣04/12/2015 ዓ.ም ።

[38].ቃለ መጠይቅ፣ወልደ ማርያም፣ሶዶ ዙሪያ፣05/10/2015 ዓ.ም ።

መሪ፣የቤተሰብ መሪ ሁሉ የሚወክልና ትልቅ ትርጉም ያለው ነው ። በዚህም ንጉስ በምሰሶ ይወከላል፤አባወራ በምሰሶ ይወከላል፣ወንድ ልጅ ሲወለድ በምሰሶ ይወከላል ።

በሌላ በኩል በወላይታ ብሔረሰብ ምሰሶ ከሀዘን ጋር በተገናኘ ይገለጻል ። ስለዚህ ጉዳይ አቶ መለሰ ያያ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

**ለ.ምሰሶና ሀዘን ፡-** በወላይታ ብሔረሰብ ምሰሶ ከሀዘን ጋር ይገናኛል ። የቤቱ ባለቤት ሲሞት ምሰሶ ወድቋል (ቱሳይ ወዲስ) ይላሉ፣ንጉስ ሲሞት ምሰሶ ወድቋል (ቱሳይ ወዲስ) ይላሉ፤ወዲስ ማለት ምሰሶ ወድቋል (ዘንበል) ብሏል ማለት ሲሆን የዚህም ትርጓሜ የብሔረሰቡን ጥቅም የሚያስጠብቅ መሪ ህዝቡን፣ሊያሻግር ይችላል ተብሎ ተስፋ የተደረገበት ሰው ባልተጠበቀ ሁኔታ ሲሞት ምሰሶው ወድቋል በሚል ለሀዘን ተምሳሌትነት ይገለገሉበታል[39]

በወላይታ ባህል ምሰሶ ከብዙ ነገሮች ጋር ተገናኝቶ ይገለጻል ወይም ትርጓሜ ይሰጠዋል ። ለአብነት ምሰሶውን ከሞት ጋር በማገናኘት ትርጉም የሚሰጡ ሲሆን በዚህም በብሔረሰቡ ህዝብን ወይም ቤተሰብን የሚያስተዳድር መሪ፣አባት ሲሞት ምሰሶው ወደቀ ይላሉ ። ይህም ምሰሶ ሁሉንም ነገር የሚሸከምና በባህሉ ትልቅ ቦታ የሚሰጠው በመሆኑ መሪ ወይም አባት ሲሞት ብዙ ነገሮች ስለሚበላሹ ምሰሶው ወደቀ ይላሉ (መጋቢት፣ዲዳዬ ቃልቶሬ፣2016ዓ.ም)

ከላይ የቀረበው የጽሁፍ ይዘት እንደሚያስረዳው በወላይታ ብሔረሰብ ምሰሶ ከሚሰጠው ክብር ባሻገር ከተለያዩ ነገሮች ጋር የሚገናኝ ሲሆን ከነዚህም አንዱ ሀዘንና ሞት ነው ። ይህም በህዝቡ ዘንድ ትልቅ ክብር የሚሰጣቸው ሰዎች ለአብነት አስተዳዳሪ ወይም አባወራ ሲሞት ምሰሶው ወድቋል በማለት ይገልጻሉ ።

**መ.ምሰሶ እና መንጻት** ፡- ምሰሶ ከውክልናው ጋር ተያይዞ የትውፊታዊ እምነት አካልም ነው ። በወላይታ ምሰሶ ሲቆም ህዝቡ ላይ በደል ያደረሱ ሰዎች ወደ ምሰሶው የሚቀርቡ ከሆነ ምሰሶው አልቆም ብሎ ያስቸግራል ተብሎ ይታመናል ። ስለዚህ ሁኔታ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አየለች ተ/ማርያም ሲገልጹ በባህሉ ምሰሶ ሲያቆሙ ምሰሶው አልቆም ብሎና እየዋለለ ካስቸገረ ምሰሶውን ከያዙት ሰዎች መካከል ሀጥያት የሰራ፣የዋሸ ወይም ሰውን ክፉኛ የበደለ ሰው አለ ተብሎ ስለሚታሰብ መመሪያ እየሰጡ ቤቱን የሚያሰሩት አባቶች፤የተጠቀሱትን እኩይ ምግባሮች የሰራ ሰው ካለ እራሱን እንዲያጋልጥ ይጠይቃሉ? ከነሱ ጥየቃ በኂላ ስህተት የሰራው ግለሰብ ፍርሀት ስለሚይዘው አብረውት ምሰሶውን ለሚያቆሙ ሰዎች ያደረገውን ነገር ይናገርና እኔ ነኝ

[39]. ቃለ መጠይቅ፣20/11/2015 ዓ.ም ።

በደለኛው ብሎ እራሱን በማጋለጥ ይቅርታ ጠይቆ ትቶ ሲወጣ ምሰሶው ይቆማል (ቃለ መጠይቅ፣አየለች ተ/ማርያም፣ ሶዶ ዙሪያ፣13/12/2015 ዓ.ም) ።

በወላይታ ባህል በቤት ስራ ውስጥ ከምሰሶ ጋር ተያይዞ ጥንቃቄ የሚፈልጉ ጉዳዮች በርካታ ሲሆኑ ከነዚህም መካከል መዋሸትና ሰውን መበደል ይጠቀሳሉ ። ምሰሶውን ሲያቆሙ ወደዚያና ወደዚህ እየዋለለ አልቆም ብሎ ካስቸገረ ወዳጁን ያለአግባብ በድሎ የመጣ ሰው አለ ተብሎ ስለሚታሰብ መመሪያ እየሰጡ ቤቱን የሚያሰሩ ሽማግሌዎች ከናንተ መካከል ከሰው ጋር ተጣልቶ ወይም በድሎ የመጣ ሰው ካለ እራሱን ይግለጽ በማለት ጥያቄ  አዘል ትእዛዝ ይሰጣሉ?! ግለሰቡም የሰራውን ስህተት አውርቶ በደለኛ ነኝ በማለት ይቅርታ ጠይቆ ምሰሶውን ከሚያቆሙት ሰዎች ተነጥሎ ሲወጣ ምሰሶው ይቆማል (ቃለ መጠይቅ፣ ወልደማርያም፣2016)

ከላይ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ምሰሶ የሚያቆሙ ሰዎች እራሳቸውን ከበደልና ከሀሰት ያራቁ መሆን አለባቸው ። ይሁንና ሰዎች ላይ ክፉ ነገር አድርገው የመጡ ሰዎች ምሰሶውን ቢይዙ ምሰሶውን ለማቆም አስቸጋሪ እንደሆነና በደል የፈጸሙት ሰዎች እራሳቸውን እስከሚያጋልጡ ድረስ ስራው በአግባቡ እንደማይከናወን ነው ።

***ሠ.ምሰሶና ትውፊታዊ እምነት*** ፡- የተወለደ ልጅ ከሞተ፣ ከብት ከሞተ፣ ማታ ውርጃ ካጋጠመ (ኦማርሲ ቦሻይ ዴኢኮ)፤ኪቶሳ (kittoosa) ማይዛ ካዮቲ፤ አልባናዋ ጃልቦሶ ዶይ፣ጊዲቾ ሶይ፣ሞቼ ሶይ[40] የተባሉ ጠንቋዮች ያሉ ሲሆን እነዚህ ጠንቋዮች ጋር ሄደው እኔን የቸገረኝ ነገር አለና በምሰሶው ስር ያለውን ንገሩኝ ይላል ። በዚህም ምሰሶው ይቆፈራል፤ በምሰሶ ጉድጓድ ስር ከሚገቡ ነገሮች  አንዱ ከጎደለ ከብት አርደው አንጀቱን እያነበቡና የጥንቆላ ጠጠር እየለቀሙ በምሰሶው ውስጥ የነበረውን (ቀደም ሲል የገባውን እወቅ ይባላል)  ምሰሶው ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች የጎደለ ነገር ካለ ከኑሮው ይጎላል ተብሎ ስለሚታሰብ በግና ኮርማ ታርደው የበጉን ደም ከአስርና በላይ ዓመታት የቆመውን ምሰሶ አፈር በመቆፈር የበጉ ደም፤የበጉ በጠጥ ምሰሶው ውስጥ ይጨመራል ። እነዚህ ከተደረጉ በኋላ የተወለዱ ልጆች፣ከብቶች አይሞቱም ተብሎ ይታመናል በዚህም ሞትን መልሶታል ምሰሶውን በደምብ ነው የሚጠብቀው ተብሎ ይታሰባል [41]።

---

[40]. በወላይታ ውስጥ ከሚገኙት ጎሳዎች መካከል አንዳንዶቹ የሀገረሰባዊ አምልኮ ተከታዮች የነበሩ ናቸው የሀገረሰባዊ  አምልኮ ስያሜዎችና እምነቶች ዘብዲዮስ(2012፣ገ.25)።

[41].ቃለ መጠይቅ፣ታደሰ ኮይራ፣11/12/2015 ዓ.ም ።

.

በምዕራፍ አራት እንደተገለጸው “በጥንታዊው የአሪት ዘመንና ከዚያም በፊት የነበረው የእምነት አይነት በወላይታ ነበር፤የዚያ አይነት እምነት አሁንም ራቅ ራቅ በሚሉ ዘመናዊ ሥልጣኔ ባልተዳረሰበት አካባቢ ይንጸባረቃል በወላይታ ውስጥ ከሚገኙት ጎሳዎች መካከል አንዳንዶቹ የሀገረሰባዊ አምልኮ ተከታዮች የነበሩ ሲሆን ለአብነት ወምግራ የተባለው ጎሳ ሀምዛ ፤ቡቡላ ጎሳ ሙሉ ጉሾ፤ ፤ወሺሻ ኢንጊላላ የሚባል ሀገረሰባዊ አምልኮ ይከተላሉ” (ዘብዴዮስ፣2012፣ገ.427) ፡፡

ከላይ የቀረበው የጽሁፍ ይዘት እንደሚያስረዳው በወላይታ ልጅ ከሞተ፣ከብት ከሞተ፣ድንገተኛ ውርጃ የሚያጋጥም ከሆነ ባህላዊ ቤቱ ሲሰራ በምሰሶ ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች ከጎደሉ አልባናኖ ጃልቦሶና ኪቶሳ(kittoosa) ወደ ተባሉ ጠንቋይ ቤቶች በመሄድ ከብት አርደው አንጀቱን እያነበቡና የጥንቆላ ጠጠር እየለቀሙ ቀደም ሲል በምሰሶ ውስጥ ያለውን እወቅ ይላሉ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ምሰሶው ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች የጎደለ ነገር ካለ ኑሮው ይጎላል ክፉ ነገር ይደርሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ለዚህም ማርከሻ እንዲሆን ምሰሶውን በመቆፈር የበግ ደምና የበግ በጠጥ ይጨመራል፤እነዚህ ነገሮች ከተጨመሩ በኋላ የተወለዱ ልጆች አይሞቱም፤ከብቶች አይሞቱም ተብሎ ይታሰባል ፡፡

**ረ.ምሰሶና የብሔረሰቡ ሀላፊነት ፦** በሶዶ ዙሪያ የወይራ መንደር ነዋሪ የሆኑት አቶ አድማሱ ቱማቶ በቤት ስራው ውስጥ በተለይ ከምሰሶ ጉተታ ጋር በተያያዘ የብሔረሰቡን ሀላፊነት በተመለከተ ሲገልጹ ሁል ጊዜ በምሰሶ ጉተታ ላይ የቤቱ ባለቤት የጎረቤት፣የዘመድ (የሌላ) ሰው ቤት ሲሰራ በምሰሶ ስራ ላይ መገኘትና በአግባቡ የሚሳተፍ መሆን አለበት ፡፡ ለዚህም ተሳትፎው ሲባል በንጹህ ልብ ምሰሶውን ሳያጉላሉ በአግባቡ ጎትተው ያመጣሉ ፡፡ ይህ ካልሆነና ከጎረቤትና ከአካባቢው ሰዎች ጋር በምሰሶ ስራ የማይሳተፍ ከሆነ ህዝቡ አስተማሪ ቅጣት ይቀጣዋል ፡፡ ለምሳሌ ነጋዴ ከሆነ በጎረቤቱ ወይም በአካባቢው ምሰሶ በሚቆምበት ቀን ወደተለያዩ የዞኑ ወረዳዎች ለአብነት በሌ የሚባል ወረዳ ንግድ አለብኝ፤ጉኑኖ የሚባል ወረዳ ንግድ አለብኝ በማለት ከምሰሶው ስራ የሚቀርና ወደተጠቀሱት ቦታዎች ለግል ጉዳዩ የሚሄድ ከሆነ ይሄው ሰውዬ ቤት ሲሰራ ምሰሶ በሚያቆምበት ቀን የአካባቢው ሰዎች ምሰሶውን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ በመጎተት እያጉላሉ ግለሰቡን ያስተምራሉ ፡፡ ብሔረሰቡ የሰውዬው የቀደመ ስራ ልክ አለመሆኑን ለማሳየት ምሰሶውን ያመጣሉ ፡፡ በዚህም ግለሰቡ እሄድባቸዋለሁ ያላቸውን ቦታዎች (ወረዳዎች) በመጥራት ምሰሶውን በስርአት አያመጡም ፡፡ ከሚጎትቱት ግማሹ ኦሆሆ ወደ ዳውሮ ወረዳ ጎትት ይልና ወደ ሌላ አቅጣጫ ይጎትታል፤ግማሹ ደግሞ ኦሆሆ ወደ ሶዶ ከተማ ጎትት ይላል፤ እሱ እሄዳለው ወዳለባቸው

ቦታዎች እየጎተቱ ምሰሶውን ያጉላላሉ ፡፡ ቀጥለውም ምሰሶውን ወደ አንድ ቦታ አድርገው አያነሱም፤ብዙም አይጎትቱም፤ከጎተቱም ወደ ሌላ አቅጣጫ እያደረጉ በአግባቡ አለማምጣታቸውን የቤቱ ባለቤት ሲመለከት በሌሎች ሰዎች የምሰሶ ስራ ላይ ስላልተሳተፈ እንደሆነ ይገባውና በጣም ይደነግጣል ፡፡ በዚህም ድምጹን ከፍ(ጮክ) አድርጎ ህዝቤ ማረኝ፤ማረኝ (ዴሬ ወጊ ወጊ) ባህሉን አላከበርኩም ብሎ ይንበረከካል ፡፡ አጥፍችያለሁ መሳተፍ የነበረብኝንም ሳልሳተፍ ቀርችያለሁ ፡፡ ሁል ጊዜ ከህዝብ (ዴሬ) በታች ማለፍ ነበረብኝ ከናንተ በታች ነው የማልፈው ለናንተ በሬ አርዳለሁ ይላል ፡፡ ህዝቡ ቢበላም ባይበላም በሬውን ጎትቶ ለህዝቡ ያስረክባል ፡፡ ከህዝቡ ሽምገል ያለ ሰው እጁን በሬው ላይ ያስቀምጣል ፡፡ ከዚህ በኋላ ምሰሶውን በአግባቡ ወደ ቤት መስሪያው ቦታ ጎትተው ይወስዳሉ(ቃለ መጠይቅ፣7/12/2015 ዓ.ም) ፡፡

የኪንዶ ዲዳዬ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ እንደነገሩኝ በወላይታ ብሔረሰብ ከአንድ ሰው አቅም በላይ የሆነ ስራ ሲሰራ ህዝቡ ተባብሮ የመስራት ባህል አለው ፡፡ በዚህም ቀደም ሲል በምዕራፍ አምስት እንደተገለጸው ቤት በሚሰራበት ወቅት የብሔረሰቡ ተጠሪዎች የሚባሉት ምሰሶ የሚቆምበትን ቀን ቀደም ብለው ያሳውቃሉ ፡፡ ህዝቡም ቀኑን ጠብቆ መጥቶ በስራው ይሳተፋል ይሁንና ከህዝቡ ተነጥሎ ቦዲቲ፣ሁምቦ... ሄጄ ነው በማለት የተለያዩ ምክንያቶችን በማቅረብ ወደራሱ ጉዳይ በመሄድ የማይሳተፍ ግለሰብን ብሔረሰቡ አስተማሪ ቅጣት ይቀጣዋል ፡፡ ይህ ግለሰብ ቤት ሲሰራ ምሰሶ በሚያቆምበት ቀን የአካባቢው ሰዎች ምሰሶውን ወዳልተፈለገ አቅጣጫ በመጎተት የሚያጉላሉ ሲሆን ከሚጎትቱትም ግማሾቹ ኦሆሆ ወደ ቦዲቲ ወረዳ ጎትቱ ይሉና ወደ ሌላ አቅጣጫ ይጎትታሉ፤ግማሾቹ ደግሞ ኦሆሆ ወደ ሁምቦ ጎትት እያሉ እሱ እሄዳለው ያለባቸውን ቦታዎች በመጥራት ምሰሶውን ያጉላላሉ ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ምሰሶውን አንድ ቦታ አድርገው አያነሱም፤ በዝግታ ወደማይሆን ወደ ሌላ አቅጣጫ ይጎትታሉ ፡፡ ባለቤቱ የሰዎቹን ሁኔታ ሲመለከት በሌሎች ሰዎች የምሰሶ ማቆም ስራ ላይ አለመሳተፉ ጥፋት እንደሆነ ይገባውና ድምጹን ጮክ አድርጎ ተንበርክኮ አጥፍችያለሁ ህዝቤ ማሩኝ ደንባችንን ባለማክበሬ በሬ አርድላችኋለሁ በማለት በሬውን ጎትቶ ያመጣል ፡፡ ሽምገል ያሉ አባቶች በሬው ላይ እጃቸውን ጭነው ይቅርታ ካደረጉለት በኋላ ምሰሶውን በአግባቡ በማቆም የተባብሮ መስራትን አስፈላጊነት ያስተምራሉ (ቃለ መጠይቅ 2015 ዓ.ም ) ፡፡

ከላይ የቀረቡት መረጃዎች በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኙ በወላይታ ባህል በተለያዩ ስራዎች ሰዎች እርስ በርስ ይረዳዳሉ ፡፡ ብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ወቅት ባህሉን ተከትለው እየተጋገዙ ይሰራሉ ፡፡

በወላይታ ለእርሻም ሆነ ለሌሎች ስራዎች በባህሉ ሦስት አይነት የመረዳዳት ባህሎች አሉ፤ቤት ሲሰራ ግብአቶቹን የመሰብሰብ እና የመረዳዳት ባህል ያለ ሲሆን እነዚህ ሦስት የመረዳዳት ባህሎች ሀሺያ ፣ ዘይያና ዳጓ ተብለው ይጠራሉ ፡፡

***ሀሺያ፡-*** የሚባለው ከ2-5 ሰዎች በጋራ በመሆን የመተጋገዝ ባህልን ይገልጻል፤ይህም በሬ በማረስ፣ ስኳር ድንችና ድቡልቡል ድንች ሲተከል፣እንሰት ሲተከል ሀሺያ የሚባል ሲሆን በዚህም ዛሬ በአንዱ ጓሮ ከተከሉ ነገ በሌላዋ ጓሮ ይተክላሉ ይህ በየተራ የመስራት ባህል ሀሺያ ተብሎ ይጠራል ፡፡

**ዘይያ፡-** የሚባለው ከ5-10 ሰዎች የሚሳተፉበት ሆኖ እንደ ስራው ስፋትና መጠን የሚወሰን ሆኖ እንጨት በሚሰበሰብበትና ሰንበሌጥ በሚታጨድበት ጊዜ በዘይያ መልክ ይሰራሉ

***ዳጓ፡-*** የሚባለው ደግሞ አጠቃላይ የቤቱ ስራ ህዝቡ በሙሉ ስለሚነሳ ዳጓ ጠቅላላ ህዝብን አነሳስቶ መስራት ማለት ነው (ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ 01/04/2015 ዓ.ም.) ፡፡

### 6.6. ምሰሶ የሚቆምበት ጉድጓድ ውስጥ የሚጨመሩ ነገሮች ትዕምርት

በድሮ ጊዜ ምሰሶ በሚቆምበት ጉድጓድ ውስጥ ወላጆቹ፣ ወንድምና እህት ያልሞተበት ሰው የተለያዩ ነገሮችን ምሰሶው ውስጥ ይጨምራሉ ፡፡ ይህንንም ሁኔታ የኦፋ ወረዳ ነዋሪዎች የሆኑት አቶ ኢያሱ ቃለ መጠይቅ 03/04/2015/ እና አቶ ታደሰ ቃለ መጠይቅ፣19/04/2015/ አቶ ጥላሁን ቃለ መጠይቅ 11/05/2015/ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

ምሰሶውን ወደ ተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ከመክተታቸው በፊት አባት፣እናት ፣ታላቅ ወንድም (እህት)፤ያልሞተበት ወንድ ልጅ እንዲመጣ ይደረግና ለምሰሶው በተቆፈረ ጉድጓድ አጠገብ ቆሞ አንድ ቅል ቦርዴ እንዲጨምር ይደረጋል ፡፡ የቅል ቦርዴ የሚጨመርበት ምክንያት ቤቱ ባልና ሚስቱ ፍቅር ይኖራቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ይህ የቅል ቦርዴ የሚጠጣው በጋራ ነው ይህም በብሔረሰቡ የፍቅር መገለጫ ነው ፡፡ ጎርጣ የሚባል ሳር የሚጨመር ሲሆን የዚህ ምክንያት ደግሞ ቤቱ የማይደርቅ ኢኮኖሚ ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታመን ነው ፡፡ ቤቱ ከብት ይዋለድበታል ተብሎና ብዙ ልጆች ይወለዳሉ ተብሎ ስለሚታመን የጥጃ አዛባ ይጨመራል፡፡ ጥሬ ገብስ እህል ስለሚያበረክትና በማሳ ላይ የሚበቅል እህል ምርታማ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ በምሰሶ ጉድጓድ ውስጥ ይጨመራል ፡፡ ኑሯቸው ጣፋጭ ይሆናል ተብሎ ስለሚታሰብ ትንሽ ጨው ይጨመራል ፡፡ ብቅልና ጠላ የሚጨመሩት ለመሬቱ በረከት ያመጣሉ

ተብለው ስለሚታሰቡና የተወለዱ ልጆች ጦርነት ያሸንፋሉ፤ጠንካራ ይሆናሉ፤ዳኛ ይሆናሉ፤ ትልቅ ስልጣንና ኑሮ ያገኛሉ ተብሎ ስለሚታመን ነው ።

በወላይታ ባህል ለምሰሶ በተቆፈረው ጉድጓድ ስር የተለያዩ ነገሮች የሚጨመሩ ሲሆን ጎርጣ ሳር ቤቱ በኢኮኖሚ እያደገ እንዲሄድና ችግር እንዳይገባ ፤የጥጃ አዛባ ብዙ ልጆች እንዲወለዱ እንዲሁም ጨው ደግሞ ቤት ውስጥ ፍቅር እንዲበዛ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታመን ነው (አቶ አየለ፣ሁምቦ 2015 ዓ.ም) ።

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያሳየው በባህሉ ቤት ሲሰራ ለምሰሶ በተቆፈረ ጉድጓድ ውስጥ ምሰሶው ከመቆሙ ቀድሞ ወንድም፣እህት፣እናትና አባት ያልሞቱበት ወንድ ልጅ አንድ የቅል ቦርዴ ወደ ጉድጓዱ ይጨምራል፤ይህም በባልና በሚስት መካከል ፍቅር ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ሌላው በብሔረሰቡ ዘንድ የመዋደድና የአንድነት መገለጫ ይባላል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ። ቀጥሎ ጎርጣ የተባለ የሳር አይነት ቤቱ የማይደርቅ ኢኮኖሚ ይኖረዋል ተብሎ ስለሚታመን ይከተታል ሌላው የጥጃ አዛባ በቤቱ ከብት ይዋለድበታል ተብሎ ስለሚታሰብ ይጨመራል ። ጥሬ ገብስ እህል ያበረክታል ተብሎ ስለሚታሰብ የሚጨመር ሲሆን ኑሯቸው ጣፋጭ እንዲሆን ደግሞ ጨው ይጨመራል ።

ከላይ ከተጠቀሱት በተጨማሪ በምሰሶ ጉድጓድ ስር የበግ፣የበሬና የኮርማ ደም ይጨመራል ስለዚህ ሁኔታ አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ ጥንት በወላይታ ብሔረሰብ ጥሩ መልክ ያለው ኮርማ ተመርጦ የብሔረሰብ ተጠሪዎች እንዲያርዱት ይደረጋል ። ቀጥሎ የኮርማውን ደም የቤቱ ባለቤት ለምሰሶ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይጨምራል ። አክለውም የብሔረሰቡ መሪዎች ቡራኬና ምርቃት ይሰጣሉ ። ደም የሚጨመርበት ምክንያት ቤቱ እርጥብ እንዲሆን እና በባህሉ የቃል ኪዳን ምልክት ከሚባሉት ነገሮች አንዱ ስለሆነ ነው ። በተጨማሪም የመሀላ፤ የመልካም ነገር መገለጫ፤የህይወት ቀጣይነት ማመላከቻ ተደርጎ ስለሚታመን ነው [42]

በሌላ ጎኑ አቶ ዲዲዮ ቃልቶሬ የምሰሶው ጉድጓድ ውስጥ የሚገቡ ነገሮችን በተመለከተ የተለየ መረጃ እንደነገሩኝ በባህሉ ለምሰሶ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ የተለያዩ ነገሮች የሚጨመሩ ሲሆን እነዚህም የሚከናወኑት ጎሳቸውን መሰረት አድርገው የሚያምኑት አምላክ በሚፈልገው መስዋእት ነው ። ሌላው እነዚህ ነገሮች የሚከናወኑት ድብቅ ናቸው ከጎሳቸው ውጪ ማንም

---

[42].ቃለ መጠይቅ፣ወልደ ማርያም፣ሶዶ ዙሪያ፣21/09/2016 ። .

አያውቅም ፡፡በህዝብ ፊት ለምሰሶ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ቦርዶ የሚጨምሩ ሲሆን ምክንያቱ ደግሞ ፍቅርና መዋደድ ይሁን፤ ሰላም ይሁን ለማለት ነው ፡፡[43]

ከላይ ለምሰሶ በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ስለሚጨመሩ ነገሮች በአቶ ዲዳዬ ቃልቶሬ የተገለጸው ሀሳብ በምዕራፍ አራት ስለብሔረሰቡ እምነት በቀረበው መረጃ ሲቃኝ ጥንት በወላይታ የተወሰኑ ጎሳዎች የሀገረሰባዊ እምነትን ይከተላሉ ፡፡ ለአብነት የወምግራ ጎሳ የሚባለው የሀምዛ እምነት ፤ የቡቡላ ጎሳ የሙሉ ጉሾ እምነት፤ የዛምባቻ ጎሳ የሀውዝሎ እምነት ፤የወሺሻ ጎሳ የኢንግላላ፤የዛቷ ጎሳ የአቦርዶ እምነት፤የቃልቻ ጎሳ የሳጋኖ እምነት ተከታዮች ነበሩ (ዘብዲዮስ፣ 2012፣ገ.25) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ሲሰራ ምሰሶው ከመቆሙ አስቀድሞ ወደ ተቆፈረው ጉድጓድ የሚጨመሩ ነገሮች የጎሳዎቹን የአምልኮ ስርዓት ተከትለው በሚስጢር እንደሚከናወኑ የሚያስረዳ ነው ፡፡

**ሰ. የምሰሶና የሥርዓተ ጾታ ግንኙነት ፡-** በወላይታ ባህል ከጥንት ጀምሮ ምሰሶ ከወንድ ጾታ ጋር የሚያያዝ ትርጉም አለው ፡፡ ወንድ ልጅ ሲወለድ ምሰሶ ወልደሃል ይባላል፤አቤት አባወራው ሲሞት ምሰሶው ወደቀ ይላሉ፤በባህሉ ሴትን ወክሎ ምሰሶው አጠገብ የሚቆሙት ቱቂያ ተብለው የሚጠሩና ለድጋፍ የሚያገለግሉ እንጨቶች ሲሆኑ እነዚህ ቱቂያ የተባሉት እንጨቶች ቤቱ በአንድ በኩል አርጅቶ እንዳይወድቅ የሚደግፉ ናቸው ፡፡ ትርጉሙም ሴት ከወንድ ጎን ቆማ የቤቱን አጠቃላይ ነገር በመስራት ስለምትደግፍ ሲሆን ወንድ ደግሞ ምሰሶው ቆሞ ጣሪያውን ሰንጥቆ ማለፉን በተፈጥሮ የሴትና ወንድ ጾታዊ ግንኙነትን የሚያመለክት ነው[44]፡፡

በወላይታ ባህል ምሰሶ ከወንድ ልጅ፣ከአባት ጋር የሚገናኝ ትርጉም ያለው ሲሆን ሴት ልጅ ደግሞ ቤቱን ደግፌው በሚይዙ እንጨቶች (ቱቂያ) ይወከላሉ ፡፡ ሌላው ምሰሶው ጣሪያውን ሰንጥቆ ማለፉ የሴትና የወንድ ጾታዊ ግንኙነትን የሚገልጽ ሆኖ ምሰሶው ወንድን ወካይ ሲሆን ጣሪያው ደግሞ ሴትን ይወክላል [45]፡፡ ጣሪያውን አምጥተው ምሰሶውን ለማስገባት ሲታገሉ የሚከተለውን ዘፈን ይዘፍናሉ ፡፡

Hey ne machchiyo ekka !

---

43. ቃለ መጠይቅ፣20/06/2015ዓ.ም ፡፡

44. ቃለ መጠይቅ፣ ኢያሱ ገጃቦ፣ጥላሁን ኡኩሌ ፣አፋ፣18/09/2015 ዓ.ም ፡፡

45. ቃለ መጠይቅ፣ አድማሱ፣አየለች፣ሶዶ ዙሪያ 17/10/2016 ዓ.ም ፡፡

Hey ne machchiyo ekka!

ምሰሶውን ጣሪያው ስር ካስገቡ በኋላ ቀጥሎ ያለውን ዘፈን በቡድን እየተቀባበሉ ይዘፍናሉ ፡፡

Keettaaway machchoohoo!

Keettaaway machchoohoo!

ከላይ ከቀረበው የጽሁፍ ይዘት መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ምሰሶ ከወንድ ጾታ ጋር የሚገናኝ ሲሆን በብሔረሰቡ ወንድ ልጅ ሲወለድ ምሰሶ ወልደሃል ይባላል፤አባት ሲሞትም ምሰሶው ወደቀ ይባላል ፡፡ በባህሉ ሴት ደግሞ ቱቂያ ተብሎ በሚጠራውና ምሰሶውን ደግፎ በሚቆመው እንጨት ስትመሰል ምሰሶው ጣሪያውን በስቶ ማለፉ ደግሞ የሴትና ወንድ ጾታዊ ግንኙነትን የሚገልጽ እንደሆነ ነው የተገለጸው ፡፡

ከቀረበው መረጃ ጋር ተመሳሳይ በሆነ መልኩ የኪንዶ ዲዳዬ ነዋሪ የሆኑት አቶ ጳውሎስ አላሮ ሲገልጹ እማወራዋ በድጋፍ እንጨት (ቱቂ) ትመሰላለች ፡፡ እማወራዋና አባወራው ተደጋግፈው ነው የሚሰሩት ፡፡ አባወራው ብዙ ስራዎች እሱን የሚመለከቱ ቢሆንም በመተባበርና በመተጋገዝ ነው የሚኖሩት ፡፡ ይህም ብዙ የስራ ክፍሎች ባለቤቱን የሚመለከት ቢሆንም ከሴቷ ጋር ተደጋግፈው እንደሚሰሩ ለመግለጽ ነው [46]፡፡

ከላይ ከቀረበው ጽሁፍ መረዳት እንደተቻለው በባህላዊ ቤት ሥራ ውስጥ ሴት ከምሰሶ ስር በሚቆመው ቱቂ የምትመሰል ሲሆን ወንድ በምሰሶ ይመሰላል፤አባወራው ብዙ ስራዎችን የሚያከናውን ቢሆንም ሴቷም ከእሱ ጋር በትብብር እንደምትኖር ለመግለጽ ነው ፡፡

የሰው ልጅ ሀሳቡን፣ስሜቱን በተለያየ መንገድ ለመግለጽ ይፈልጋል ፡፡ ለምሳሌ:- ከባህላዊ ቤት ምሰሶ እና ከድጋፍ እንጨቶቹ ጋር በተያያዘ ብሔረሰቡ ወደሚፈልገው ተፈጥሯዊና ማህበራዊ ሀሳቦች ጋር ለማዛመድ ትልቅ ድርሻ አላቸው ፡፡ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ በባህላዊ ቤት ስራ ወቅት ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ከምሰሶና ከድጋፍ እንጨቶች ጋር የተገናኙ ፊት ለፊት የማይነገሩ ጾታዊ ጉዳዮችን በመመርመርና በመፈከር በብሔረሰቡ ድብቅ የአዕምሮ ክፍል ውስጥ ያሉ ሀሳቦችን ለመረዳት ያስችላል ፡፡

ቀደም ሲል ሴት ልጅ ለምሰሶ ድጋፍ በሚሆኑ እንጨቶች እንደምትመሰል የሚገልጹ መረጃዎች ቀርበዋል ፡፡ ይሁንና ከተሰጠው ሀሳብ በተለየ መልኩ የተለያዩ ሀሳቦች ቀርበዋል ፡፡

---

[46]. ቃለ መጠይቅ፣22/10/2015 ዓ.ም ፡፡

በወላይታ ባህል መሰረት ሴት ልጅ ተቆርጦ መሬት ላይ ያለ የምሰሶ እንጨትን አልፋ ወይም በላዩ ላይ አቋርጣ እንድታልፍ አይፈቀድም ፡፡ ድንገት እንኳን አቋርጣ ብታልፍ ይረክሳል ተብሎ ስለሚታሰብ ያቋረጠችው ይጣልና ሌላ ይቆረጣል ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ምናልባት የወር አበባ ላይ ካለች በሚልና እንደ ልማድ ስለሚታይ ነው ፡፡[47]

ከላይ ከቀረበው መረጃ መገንዘብ እንደሚቻለው በቤት ስራ ወቅት የተለያዩ እገዛዎችን የሚያደርጉ ሴቶች በተመለከተ ብሔረሰቡ ከምሰሶ ጋር ተያይዞ የተለያዩ ሀሳቦችን የሚያስቀምጡ ሲሆን ይህም ሴቶች ምሰሶ አቋርጠው የሚያልፉ ከሆነ ምሰሶው ይረክሳል ተብሎ ስለሚታመን ያቋረጡት የምሰሶ እንጨት ተቆርጦ ይጣልና በምትኩ ሌላ አዲስ የምሰሶ እንጨት ይተካል ይላሉ ፡፡

ሴትና ውሻ ምሰሶን አቋርጠው ካለፉ ምሰሶው ይረክሳል ተብሎ የሚታመን ሲሆን ይህም በባህሉ እንደ ልማድ የሚወሰድ ነው ፡፡ [48]

በባህሉ ሴት ልጅ ምሰሶ ካቋረጠች ይረክሳል ተብሎ ይታመናል ፡፡ በዚህም ምሰሶ ከሴት መጠበቅ አለበት በሚለው ሀሳብ መረጃ ሰጪዎች የተለያየ መረጃ ሰጥተዋል ፡፡ ቀደም ሲል ከተሰጠው ሀሳብ በተለየ መልኩ በወላይታ ሴት ልጅ ምሰሶ ማቋረጥ የሌለባት ከክብር ጋር በተያያዘ እንደሆነ የቡድን ተኮር ውይይት ተሳታፊ የነበሩት አቶ ወልደ ማርያም ሲገልጹ

ወላይታ ውስጥ ሴት ምሰሶን አቋርጣ ማለፍ የለባትም የሚለው አባባል ሴት ምሰሶን ታረክሳለች ተብሎ ሳይሆን ክብሯን ታጣለች ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ወላይታ ላይ ሴቶች እንዳይሰሩ የሚከለከሉ ነገሮች አሉ፤ምክንያቱም ክብራቸውን ያዋርዳል ተብሎ ስለሚታሰብ ሲሆን ለምሳሌ ሴት በሬ እንድታርስ፤ሴት እንድትኮተኩት፣ሴት ከባድ ነገር እንድትሸከም የማይፈቀደው ሴት በመሆኗ ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቡ ክብር ተደርጎ ጭምር ስለሚወሰድ ነው ፡፡ ለምሳሌ አንዷት ሴት ባሏ ቢሞት፤ልጅ ባይኖራት፤ወጥታ ስትኮተኩት ከተገኘች የትኛውም መንገደኛ እያለፈ ይህንን ካየ ልብሱን አውልቆ ይሄ ለአካባቢው መርገም ነው ብሎ ከእጇ የያዘችውን ነገር ነጥቆ እሷ የምትሰራውን ሰርቶ ሰጥቶ ነው የሚያልፈው ይሄ የብሔረሰቡ ግዴታ ነው፤ምክንያቱም ትልቅ መርገም ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው ፡፡ የብሔረሰቡን ክብር ያዋርዳል ተብሎ ይታመናል ፡፡ ወንድ ሰው በሌለበት ሴት ስትሰራ ከታየ፤ብሔረሰቡ ሞቶ አልቆ ነው እንደዚህ

---

[47]. ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣አፋ፣19/11/2015 ዓ.ም ፡፡

[48]. አማኑኤል አይዴ፣ ቃለ መጠይቅ፣25/12/2016/ዓ.ም ፡፡

አይነት ስራ የሚሰራው ተብሎ በጣም ከባድ መርገም ተደርጎ ስለሚወሰድ ሴት እየሰራች ሰው አጥታ ምን እበላለሁ ብላ በአጋጣሚ ዝም ብላ ብድግ አድርጋ የሆነ ነገር ይዛ ወጥታ ስራ ትጀምር ይሆናል፤እያየ ያለፈ ሰው ግን በብሔረሰቡ ውስጥ የተረገመ ነው፤አይፈቀድም፤ሴት ውሃ ብትቀዳ፣ሳር ብታጭድ፣ቤት ልጆችን ብታሳድግ፣ምግብ ብትሰራ፣እነዚህ ነገሮች ምናልባት ልጅ ተሸክሞ የመውለድ ነገር ተፈጥሯዊ ሊሆን ይችላል፤ከዚህ ውጪ ግን በብሔረሰቡውስጥ የሥራ ክፍፍል ውስጥ ሴቶች ከበድ ያለ ስራ እንዳይሰሩ ይከለከላል ። ምሰሶው ትልቅ ነው ሴት ደግሞ ያንን እንድትሻገር መደረግ የለበትም (ቃለ መጠይቅ፣2014 ዓ.ም) ።

በቡድን ተኮር ውይይት የቡድን አንድ ተሳታፊ የሆኑት አቶ ኢያሱ ሲገልጹ በወላይታ ባህል ሴት ምሰሶን አቋርጣ ማለፍ የለባትም የሚለው አባባል ሴት ምሰሶን ታረክሳለች ተብሎ ሳይሆን ጉዳት ይደርስባታል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ። ሴት በሬ እንድታርስ፤ሴት እንድትኮተኩት፣ሴት ከባድ ነገር እንድትሸከም የማይፈቀደው ሴት በመሆኗ ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቡ ክብር ተደርጎ ስለሚወሰድ ጭምር ነው ። ሌላው ለምሳሌ አንዲት ሴት የሚያግዟት ወንዶች ልጆች በጎኗ ከሌሉና እርሻ ስትኮተኩት ከተገኘች መንገደኛ እያለፈ ከተመለከተ ከሚሄድበት ተመልሶ የምትሰራውን ከእጇ ተቀብሎ ሰርቶ አግዟት ይሄዳል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ሴት ልጅ ከበድ ያለ ነገር እየሰራች ወንዶች እያዩ የሚያልፉ ከሆነ ለአካባቢው ሰዎች ክፉ ነገር ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ። ስለዚህም በስራ ክፍፍል ውስጥ ሴቶች ከበድ ያለ ስራ እንዳይሰሩ ስለሚከለከልና ምሰሶ ትልቅ በመሆኑ ሴት ደግሞ ያንን እንድትሻገር ስለማይፈቀድ ነው ። ሌላው ሴት ልጅ ውሃ ብትቀዳ፣ሳር ብታጭድ፣ቤት ልጆችን ብታሳድግ፣ምግብ ብትሰራ፣እነዚህ ነገሮች የሚፈቀዱ ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣2016/ዓ.ም) ።

ቀደም ባሉት አንቀጾች በወላይታ ባህል ሴት ምሰሶን አቋርጣ ማለፍ የለባትም የሚለው ሴት ምሰሶውን ታረክሳለች ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ነበር የተገለጸው ከዚህ ገለጻ በላይ የቀረበው ይዘት ደግሞ ቀደም ብሎ ከቀረቡት ሀሳቦች በተቃራኒው የቀረበ ሲሆን ይህም ሴት ምሰሶን አቋርጣ ማለፍ የለባትም የሚለው ሴት ምሰሶውን ታረክሳለች ተብሎ ስለሚታሰብ ሳይሆን ክብሯን ታጣለች ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ። ሌላው በወላይታ ባህል ሴቶች እንዳይሰሩ የሚከለከሉ ነገሮች ያሉ ሲሆን ለዚህም ምክንያቱ ክብራቸውን ያዋርዳል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ለምሳሌ ሴት በበሬ እንድታርስ፤ሴት እንድትኮተኩት፣ሴት ከባድ ነገር እንድትሸከም አይፈቀድም፤ለዚህ ምክንያቱና የማይፈቀደው ሴት በመሆኗ ብቻ ሳይሆን የብሔረሰቡ ክብር

ጭምር ተደርጎ  ስለሚወሰድና እነዚህን ስራዎች ከሰራች ለህዝቡ መርገም ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ፡፡

ቀደም ባሉት አንቀጾች በወላይታ ባህል ሴቶች ልጆች ለምሰሶ ደጋፊዎች (ቱቂያ) በተባሉ እንጨቶች እንደሚመስሉ ተገልጿል ፡፡ ይሁንና ከዚሁ ሀሳብ በተቃራኒው ደግሞ ሴቶች ምሰሶን አቋርጠው ማለፍ የለባቸውም የሚል መረጃ ቀርቧል ፡፡ በዚሁ ሀሳብ ላይም የተለያዩ መረጃዎች የቀረቡ ሲሆን ይህም ምሰሶን አቋርጠው ካለፉ ይረክሳል የሚልና ምሰሶውን እንዳያቋርጡ የሚከለከለው ለሴቶች ከባድ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ነው ፡፡ በሁለት የቡድን ተኮር ውይይቶች እንደተገለጸው በባህሉ ሴቶች ከባድ ስራዎችን እንዲሰሩ አይፈቀድም ፡፡ ለአብነት አንድ ሴት እርሻ ስታርስ፣ ስትኮተኩት፣ስትዘራ ብትታይ ለአካባቢው ሰዎች መርገም ወይም ክፉ ነገር ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ፡፡ ስለዚህም ምሰሶን አቋርጣ ማለፍ የለባትም የሚለው ለሴቷ በማሰብ ሲሆን ይህም ምሰሶውን አቋርጣ ስታልፍ ጉዳት እንዳይደርስባት ተብሎ ስለሚታሰብ እንደሆነ ነው ፡፡ ሌላው ሴቶች ከባድ ስራ ሲሰሩ ከታዩ የብሔረሰቡ ክብር ይጎላል ስለሚባል ነው ፡፡

### 6.7. የበር መቃን ሥራ

የበር መቃን ስራ ከምሰሶ ስራ በኋላ የሚመጣ ነው ፡፡ የቤት መስሪያ ቦታው ከተደለደለ በኋላ ግድግዳ የሚቆምበት ከ60-70 ሳ.ሜ በጥልቀት ይቆፈራል፣ቁፋሮው እንዳለቀ የወይራ እንጨት ግድግዳው ዙሪያውን ይቆማል ፡፡ የግድግዳው እንጨት ቆሞ እንዳለቀ አፈር ይመለስበታል ፡፡ ቀጥሎ ከላይ በአናቱ ዙሪያ ሶስት ዙር ማገር በኋላ ላይ ተቆርጦ የሚወድቅ ይማገርለታል ፡፡ ምሰሶው በሚቆምበት ሰዓት ግድግዳውን እንዳያፈርሰው ከቤቱ ውስጥና ውጭ አራት ባላ እንጨቶች ተተክለው በአናቱ ላይ አግዳሚ እንጨት ይደረጋል፣የሚቆመው ጉበን(ቆስሌቲያ) ይባላል ፡፡ ቆሪያ ከላይ ያለው ሲሆን ጉበንና መቃን አብሮ መምጣቱን እንደውም ከጎኑ ጉበን(ቆስሌቲያ) ያለ ሲሆን ማገሩ እንዳይጎዳ ማቻሚያ የሚባል እንጨት አለ ፡፡ ይህም በሚማገርበት ወቅት ማገሩ እንዲታይ ያደርጋል፣ በሩ ኢፌታ (ሳንቃ)የሚባል ሲሆን  ሀማካ ከሚባል እንጨት ተዘጋጅቶ ይሰራል፣ እንጨቶቹ ማሰሪያዎች አሉት፣እነዚህም በዛጎሎች ከውስጥ ይቆማሉ፣በሩ በእነዚያ ላይ እንዲንከባለል ተደርጎ  ውሃ ልኩን ጠብቆ ስለሚሰራ እንደተፈለገ እያንከባለሉ መክፈት ይችላሉ (አየለ፣24/12/2016/ዓ.ም) ፡፡

ፎቶ 19፡- በአግድም መዝጊያውን ለመቆለፍ የሚያገለግለው ኮልቢያ (Kolbbiyaa)




ምንጭ፡- በኦፋ ባህላዊ የወላይታ ቤት የበር መዝጊያ እንጨቶች ሰኔ06/10/2014 ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ

ፎቶ 20፡- ቋሚና አግዳሚ መዝጊያ እንጨቶችን ማስገቢያ ሂራቁዋ (Hiraquwaa)




ምንጭ፡- በኦፋ ባህላዊ የወላይታ ቤት የበር መዝጊያ እንጨቶች ሰኔ06/10/2014 ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ

**ፎቶ 21፡- የበር መቃን ሥራ**




**ምንጭ፡- ኦፋ ወረዳ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣ 2014ዓ.ም**

በመግቢያ በር ፊት ለፊት ጉበን /ቆስሌታ/ Qosilettaa/ መቃን /Qoriyaa/ ከጎጮኗ ጋር ተያይዞ ይሠራል፡፡ ለመዝጊያ ከቀርከሃ ወይም ከሃሜካ የተዘጋጀ መዝጊያ /Ifittaa/ ይጠቀማሉ፡፡

የቤት ክዳን ሥራ የሚጀመረው ቤቱ ተሠርቶ ለሣር ክዳን ሲደርስ ሲሆን በመጀመሪያ ሰንበሌጥ ታጭዶ ከመጣው ግምድ ሣር /Konddaa/ ይዘጋጃል ፡፡ ግምዱን /Konddaa/ ለመሥራት አራት አጠና እንጨት ይቆምና ምርጥ የክዳን ሣር ተለቅሞ በውኃ ይርስና ጭብጥ እየያዙ በቋሚ

አጠና እየተጠመዘዘ ይሠራል። ቀጥሎ ቤት ሲከደን የታችኛዉ ክዳን /Daddaha/ ከመሬት እስከ ግድግዳው ጫፍ 11 ዙር ያህል በክርክም ይከደናል ። የላይኛዉን ለመክደን /Kamaa/ የሰንበሌጡን ታችኛ ክፍል ወደ ላይ በመገልበጥ በማገር እየታሰረ ቤቱ አናት ድረስ ይከደናል ። ቤቱ ተከድኖ ሲጠናቀቅ ከዋንዛ ተጠርቦ የተዘጋጀ ጉልላት (Gumbbuwaa) በምሰሶ አናት ላይ ይደረጋል ። ከጉልላቱ በታች ወይዛሪያ (Woyizariyaa) የተባለው የሣር ክዳን ይደረግለታል ። ወይዛሪያ (Woyizariyaa) ወይም ዳሼታ (Dashettaa) በቤቱ አናት የሚደረግበት ጥቅሙ የቤቱ ክዳን ሣር ሳይረግፍና ሳያረጅ እንዲሰነብት ስለሚረዳ ነው ።

ፎቶ 22፡- ባለሙያዎች በመቃንና በጉበን ሥራ ላይ




ምንጭ፡- አፋ ፤በአጥኚዋ የተነሳ፤2015/ ዓ.ም

## 6.8. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት የክዳን ሥራ

የወላይታ ባህላዊ ቤት በሚሠራበት ጊዜ የቤት ክዳን ሥራ ግድግዳው፤ ጣሪያው፤ ምሶሶ ሁሉም ከተጠናቀቀ በኋላ የሚሠራ ሥራ ነው ። ክዳኑ የሚሠራው ከተለየ የሣር ዓይነት ነው ። ይህም ቤት ለመሥራት አባወራው ገና ዕቅድ ካወጣበት ጊዜ ጀምሮ ከብቶች እንዳይግጡት ታጥሮና ተከልሎ በጣም ያደገ ሣር ሲሆን በብሔረሰቡ ቋንቋ "ጋታ " ይባላል ። ይህ ለቤት ክዳን የሚሆን ሣር ከ3-5 ወራት ያህል በጣም ማደጉን በግምት ካዩ በኋላ ይታጨዳል ። በመልክ በመልኩም ተደርጎ ሳይዘበራረቅ እንዲደርቅ ይደረጋል ። ለባህላዊ ቤት ክዳን ሣሩ ደርቆ ከተዘጋጀ በኋላ ሁሉም ሰው በዘፈቀደ አይከድነውም ። የቤት ክዳን የሚከናወነው ቀደም ሲል ሳር ይከድኑ በነበሩ ባለሙያዎች አማካይነት በከፍተኛ ጥንቃቄ ነው ። ይህም የሚሆነው እንደ ቤቱ ዓይነት ዲዛይንና (ከዛው ከሣሩ) ወጥቶለት ውበቱ ተጠብቆ ይከደናል ። ባለሙያዎች የቤቱን ክዳን በረቀቀ ጥበብ በሚያከናውኑበት ጊዜ አስፈላጊውን ቁሳቁስ በማቀበል በሙያም ሌሎች ደጋፊ ባለሙያዎችን መርጠው ይጠቀማሉ። ዋናዎቹ ባለሙያዎች ከአራት እስከ ስድስት ሊሆኑ ይችላሉ ። ሥራው ልዩ ጥበብ እና ጥንቃቄ የሚያሻው በመሆኑ ነው

(ቃለ መጠይቅ፣አየለች፣ሶዶ ዙሪያ ህዳር13/2015) ።

ሳሩ ከውጪ ስለሚከደን ሳር የሚከድኑ ባለሙያ የሆኑ ሰዎች እንዲመጡ የሚደረግ ሲሆን መጀመሪያ አጫጭር ሳር ይከደናል ። ቀጥሎ ረጃጅም ሳር ይከደናል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አጫጭር ሳሮች ክፍተት ያለበትን ቦታ ለመድፈን ስለሚያገለግል ነው ። ማገር የታሰረባቸው ሁሉም ከውጭና ከውስጥ በስርዓት በሳር ይከደናሉ ። ይህንንም እስከ ላይ ድረስ ያደርሱና ከግማሽ በላይ ካለፉ በኋላ ከታችና ከላይ በማድረግ ሳሩን ማልበስ ይጀምራሉ ። ሌላው ዝናብ ሲዘንብ ቤቱ እንዳያፈስ አድርገው ሳሩን የሚከደኑ ሲሆን ቀጥሎም እስከታች ድረስ ያመጡና ከላይ ካደረጉ በኋላ የክዳን ስራው ይጠናቀቃል (ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዴ፣13/10/2016 ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው ሳር የሚከድኑ ባለሙያ የሆኑ ሰዎች ሲሆኑ መጀመሪያ አጫጭር ሳር ቀጥለው ደግሞ ረጃጅም ሳር ይከድናሉ ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አጫጭሩ ሳር የቤቱን ክፍተት ለመክደን ስለሚያገለግል ነው ። ማገር የታሰረባቸው ሁሉ ከውጭና ከውስጥ በስርዓት በሳር እንደሚከድኑ የሚገልጽ ነው ።

ሌላው ሲሳይ ኩማ ቃለመጠይቅ፣ ህዳር12/2015ዓ.ም እና ኢያሱ፣ቃለመጠይቅ፣ 14/11/2015/ዓ.ም፣የቤት አሰራሩን ትእምርቶች በተመለከተ ሲገልጹ የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ከብሔረሰቡ ጋር ጥብቅ ቁርኝት አለው ። ይህም ለቤት መስሪያ የሚውሉ ግብአቶች እንደ ማገር፣የግድግዳ እንጨት፣ወፍቾና የመሳሰሉት ጥብቅ ተደርጎ መሰራትና ጠንካራ መሆን፤እንጨቶቹ ከግርግዳው ጋር ተቀራርበው በወፍቾ ታስረው መገኘታቸው የቤቱ አሰራር የህዝቡን ጥንካሬና ህብረትን ያመለክታል ። በበሰለና በጠበቀ ሁኔታ የተገናኘና የተዋደደ ህዝብ አይለያይም ። ከላይ የቀረበው ጽሁፍ እንደሚያስረዳው የወላይታ ብሔር ባህላዊ ቤት አሰራሩ የማገሩ ጠንካራና ጥብቅ ብሎ መሰራት የህዝቡን ጥንካሬና ህብረትን የሚገልጽ እንደሆነ ነው ።

### 6.9. በወላይታ ብሔረሰብ ቤት የሚሰራባቸው እለታትና ወራት ትርጓሜዎች

በወላይታ ባህል በሳምንቱ ውስጥ ያሉት ቀናት ገዳምና ገደቢስ ተብለው በሁለት እንደሚከፈሉ ከመስክ የተገኘው መረጃ ያመለክታል ።

- **ቤት የሚሰራባቸው ቀናት ፦** በወላይታ ብሔረሰብ በሳምንት ውስጥ ከሚገኙ ቀናት መካከል ቅዳሜ እለትን ቤት ለመስራት ያውሉታል ።

በወላይታ በሳምንት ውስጥ ያሉ ቀናት በሁለት ምድብ የሚከፈሉ ሲሆን አንደኛው ምድብ ማክሰኞ፣ሀሙስና ቅዳሜ ሶስት ቀናትን የሚይዝ ሲሆን እነዚህም ገዳም ወይም ሴቴ (Shaagaa woyikko Maccaa gallassaa) እለታት ይባላሉ ። በሁለተኛው ምድብ የሚጠቀሱት ሰኞ፣ረቡዕ፣አርብና እሁድ አራት ቀናትን የሚይዝ ሲሆን እነዚህም ገደ ቢስ እለት (Eqa Gallassa) ወይም ወንዴ እለት (Attumaa Gallassa) ይባላሉ ። በዚህም መሰረት በወላይታ ገዳም እለታት በተባሉት የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ ይባረካሉ ተብሎ ታሳቢ ይደረጋል፤ከዚህም የተነሳ ቅዳሜ ምሰሶ ይቆማል፤ግርዛትና ምሰሶ ቅዳሜ ነው የሚከናወነው ። በወላይታ ምሰሶ ማክሰኞ እለት አያቆሙም፤ ማክሰኞ የሴት ቀን ይባላል፤ ወንዶች ሚስት የሚያጩት ማክሰኞ እለት ነው ። ሴት ለመጠየቅ ለሽምግልና የሚኬደው ማክሰኞ እለት ነው (ቃለመጠይቅ፣ አቶ ታደሰ ኮይራ፣2016ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ባህል በአንድ ሳምንት ውስጥ የሚገኙ ቀናት የራሳቸው ትርጓሜ አላቸው ። እነዚህም ቀናት ከቤት ስራ ጋር ይገናኛሉ፤ማክሰኞ፣ ሀሙስና ቅዳሜ ገዳም ወይም ሴቴ (Shaagaa woyikko Maccaa gallassaa) እለታት የሚባሉ

ሲሆን ሰኞ፣ረቡዕ፣አርብና እሁድ ገደ ቢስ እለት (Eqa Gallassa) ወይም ወንዴ እለት (Attumaa Gallassa) ይባላሉ ። ከዚህ የተነሳ ገዳም ቀናት በተባሉት የሚከናወኑ ነገሮች ሁሉ ይባረካሉ ተብሎ የሚታሰብ ሲሆን በዚህም ከነዚህ ቀናት መካከል ቅዳሜ ምሰሶ የሚቆምበት ቀን ሲሆን በዚህም ምሰሶው ይባረካል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ።

ከቡድን አንድ ተሳታፊዎች መካከል አቶ ታደሰ ኮይራ፤ሸዋዬ ፎልታሞ የቤት መስሪያ ቀናትን በተመለከተ በተለየ ሁኔታ የሚከተለውን ሀሳብ ሰጥተዋል፡-

እያንዳንዱ ቀናት የየራሳቸው የሆነ ከሌላው የተለየ ትርጓሜ እና ፋይዳ አላቸው ። ይህም ከላይ ከተጠቀሱት ቀናት ውጪ የምሰሶ እንጨት እንዳይቆርጡ ግብአቶችን እንዳይሰበስቡ ባህላዊ ክልከላዎች አሉ ። ከእነዚህ ቀናት ውጪ የምሰሶ እንጨት ቢቆረጥ እንጨቱ በምስጥ እንደሚበላና እንደሚበሰብስ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል (ቡድን አንድ 27/11/2016) ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደሚቻለው በወላይታ ባህል እያንዳንዱ ቀናት የየራሳቸው የተለየ ትርጓሜ ያላቸው ሲሆን በእነዚህ ቀናትም የብሔረሰቡ አባላት የተለያዩ ስራዎችን በመስራት ያሳልፋሉ ። ይህን ሀሳብ በተመለከተ በመዋቅራዊ ተግባራዊ ንድፈ ሀሳብ በገጽ 29 እንደ Durkheim የስራ ክፍፍል በሁሉም ብሔረሰቦች ላይ በግልጽ የሚታይ ሆኖ ይህም በ"አንድነት" እሳቤ ውስጥ ሊገኝ የሚችል ነው ። በጥንት ዘመን ቀደምት የጥንት ብሔረሰቦች ትብብር ሁሉንም ሰው በአንድነት እንዲይዝ አድርጓል ። Durkheim የጋራ እሴቶች፣ የጋራ ምልክቶች እና የልውውጥ ሥርዓቶች ሲሆኑ በእነዚህ ማህበረሰቦች ውስጥ የመተሳሰሪያ መሳሪያዎች ሆነው ይሠሩ እንደነበር አስቀምጧል ። ተቋማት እና ማህበራዊ ሚናዎች አንድ ላይ ተጣምረው ንድፍ ያላቸው ማህበራዊ ዝግጅቶችን ይመሰርታሉ ብለው ማህበረሰቦች የማህበራዊ እኩልነት እና የመተሳሰር ዝንባሌን የሚያሳዩባቸውን መንገዶች መርምረዋል ። በተጨማሪም ማኅበራዊ ተቋማት የተረጋጋ ማኅበራዊ ሥርዓቶችን ለመመሥረት እርስ በርስ በመደጋገፍ ይሰራሉ (Sean P. Hier, 2005) ።

**ቤት የሚሰራባቸው ወራት ፡-** በባህሉ ቤት ለመስራት የሚመረጠው በበጋ (Boniyaa) ወራቶች ሲሆን ። ይህም ከጥር እስከ የካቲት ባሉት ጊዜያት ይከናወናል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በጋ የእርሻ ጊዜ እና ለመምህራንና ለተማሪዎች የእረፍት ጊዜያት በመሆናቸው የሚያግዙ ሰዎችም ይገኙበታል (ቃለ መጠይቅ፣ ኢሳያስ፣23/11/2014 ዓ.ም) ።

ቤት የሚሰራው በጋ(Boniyaa) ወራት ላይ ሲሆን በጋ የሚባለው ከታህሳስ ወር በኋላ ያሉ ጊዜያቶች ሲሆኑ ቤትም የሚሰራው በነዚሁ ወራት ማለትም ከታህሳስ እስከ መጋቢት ድረስ

ሆኖ በተለይ ጥርና የካቲት የቤት መስሪያ ጊዜ ነው ። በጋ ላይ የተመረጠው የእርሻ ጊዜ ስላልሆነ ነው ። እነዚህን  አልፎ ከሄደ መጋቢት ላይ ይሰራል ። ከላይ የተጠቀሱት ወራቶች ካለፉ ቤት መስራት አይቻልም ። ምክንያቱም ሰባተኛ ወር ላይ ዝናብ ስለሚዘንብና የእርሻ ጊዜ በመሆኑ ሰው ወደ እርሻ ስራውና ወደ ዘር መዝራት ይገባል እንጂ ቤት አይሰራም ። ሌላው ድንገት ቤት የፈረሰበት ወይም የተቃጠለበት በማንኛውም ሰዓት ይሰራል (ቃለ መጠይቅ፣ ኢሳያስ፣23/11/2014 ዓ.ም) ።

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚገልጸው በወላይታ ቤት የሚሰራው በበጋ ሲሆን በዚህም ከጥር እስከ መጋቢት ባሉ ወራት ውስጥ ለመስራት የሚመረጡ ሲሆን በተለየ ሁኔታ የካቲትና ጥር ተመራጭ ናቸው ።

ከቡድን አንድ ተወያዮች መካከል አቶ ዲዳዬ ቃልቶሬ የተባሉ የኪንዶ ዲዳዬ ነዋሪ ቤት ስለሚሰራባቸው ወራት ሲገልጹ የወላይታ ህዝብ ቤት ለመስራት ከህዳር እስከ ጥር ድረስ ያሉትን ወራት የሚመርጥ ሲሆን ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ህዳር ‹‹ባራታ›› (Baraataa) ማለት በረከተ፣በረከተ፣ብርካቴ፣ህዝቡ በዋናነት ለእህል ብርካቴ የሚጠቀምበት ነው።ህዳር የተለያዩ ምርቶች የሚደርሱበት ወር በመሆኑ ችግር የሌለበት የጥጋብ ወር ነው ። ከዚህም የተነሳ በህዳር ደሃ የለም (Hidaariyan hiyyeesi baa) ተብሎ ተረት እስከ መተረት የተደረሰበት ወር ስለሆነ ሲሆን ጥር በወላይታ ‹‹ኢቻሺያ›› (Ichchashiyaa) ይባላል ። ኢቻሻ (አምስት) ከሚል የወላይትኛ ቃል የተወሰደ ቃል ሲሆን ትርጉሙም አምስት ማለት ነው ። ከዚህ በመነሳት ጥር አምስተኛ ወር መሆኑን ለመግለጽ ነው ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በባህሉ አንድ ሰው ቤት ሲሰራ ለብቻው አይሰራም፣እኔ ለሚቀጥለው ዓመት ቤት እሰራለሁ እያሉ እጅ የሰጠው( ኩሺያ ኢሚዶጌ ) አለ፤ወይም ለዘሩ የሚነግረው አለ ወደዚህ የሚመጣ ሰው በፊት ሄደን ያገዝነውን ፋንታ ለማገዝ በጎሮው እህል አለው፣ገንዘብ አለው እያለ ለሁሉም ሰው ጥሩው ወር ለአንተ እህል ያለህ ጊዜ ፣ዝናብም የሌለበት ጊዜ መቼ ነው የሚለውን ከተነጋገሩ በኋላ ህዳር ላይ ደሀ የለም ይባላል ። በወላይታ ባህል በህዳር ለሁሉም ሰው ገንዘብ አለው ። በዚህ ወር ሁሉም ሰው ከጎሮው የሚወስደው አለው፣ገንዘብ አጥቶ አያውቅም፤ ብቻውን አይሰራም (ቃለ መጠይቅ፣23/10/2016/ዓ.ም.) ።

### 6.10. የወላይታ ባህላዊ ቤት አሰራርና የጨረቃ ኡደት

የወላይታ ብሔረሰብ በጨረቃ እንቅስቃሴ ላይ ተመስርተው ስለዘመን አቆጣጠር፣ በወራቱ ውስጥ ስለሚከናወኑ ጉዳዮች ጨጌና (cegenna)ን መሰረት ያደርጋሉ ። ይህን በተመለከተ አቶ ኢያሱ፣አቶ አየለና ኤርሚያስ ጎባና እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

በወላይታ ብሔረሰብ የቤት ማገር ሲቆረጥ፣ግድግዳ ሲቆም፣ማንኛውም ነገር ሲሰራ የጨረቃ እንቅስቃሴን መሰረት በማድረግ ነው። በወላይታ ባህል ጩጌና (cegenna) ማለት አውዳሚ(የሚሰሩ ነገሮች ሁሉ በአግባቡ እንዳይከናወኑ የሚያደርግ) ማለት ነው። ጨረቃ ከታየች ከ1ኛ እስከ 3ኛ ያሉት ቀናት ጤሮ ጩጌና የሚባሉ ሲሆን በሁለተኛው ደግሞ ጨረቃዋ ከወጣች ከ15ኛ ቀን ጀምሮ ያሉት ሦስት ተከታታይ ቀናት ጎባና ጩጌና ይባላሉ። በእነዚህ ስድስት ቀናት ለምሰሶ፣ለግርግዳ የሚሆኑ እንጨቶች አይቆረጡም። ቤቱን ለመከፋፈል የሚያገለግለው ሳጠራ በጩጌና ወቅት አይቆረጥም። በባህሉ ለእንግዳ መቀመጫ የሚሆን ክብና አግዳሚ ከእንሰት የሚዘጋጀው ማቶት(ሸድአ)የተባለውን መቀመጫ መስሪያ ግብአትም የሚቆረጠው ከነዚህ ቀናት ውጪ ነው። በባህሉ አውዳሚ በሚባሉ (ጩጌና) ወቅት ቤት ቢሰራ፣ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ቢቆረጡ፣ቢሰበሰቡ፣ቢታጨዱ፣እንሰት ቢፋቅ፣ምስጥ ይበላቸዋል ተብሎ ይታሰባል። ከዚህ የተነሳ በባህሉ ከቤት ስራ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ለመስራት ጩጌና (cegenna) የሚባሉት አውዳሚ (የሚሰሩ ነገሮች ሁሉ በአግባቡ እንዳይከናወኑ የሚያደርግ) ቀናት ስለሆኑ ቤት ሲሰራ እነዚህን ቀናት ግንዛቤ ውስጥ ማስገባትና ተጠንቅቆ መጠቀም ከሚደርስ ጉዳት ይከላከላል ተብሎ ይታሰባል (ቃለመጠይቅ፣2015/ዓ.ም )።

የቤት ማገር ሲቆረጥ፣ግድግዳ ሲቆም፣ማንኛውም ነገር ሲሰራ የጨረቃ እንቅስቃሴን መሰረት በማድረግ (ባህላዊ አስትሮኖሚን) በመከተል ነው ። በዚህም ወራትን ይቆጥራሉ ። ጨረቃ ምድርን ለመዞር 29 ቀን ሲቀራት በነዛ በ29 ቀናት ውስጥ የተለያዩ ነገሮችን ታሳያለች ። ጩጌና ጤሮ፣ ጩጌና ጎባና ጩጌና ብርሀን(ፖኡዋ)፣ ጨለማ(ጡማ) የሚባሉ ሲሆን ይህም ጨረቃ ከታየች ከ1ኛ እስከ 3ኛ ባሉት ቀናት ውስጥ ጨረቃ ከወጣች ጤሮ ጩጌና የሚባል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ጨረቃ ከወጣች ከ15ኛ ቀን ጀምሮ ያሉት ሦስት ቀናት ጎባና ጩጌና ይባላሉ ። ለቤቱ መከፋፈያ የሚያገለግለው ሳጠራ ጩጌና በሌለበት ነው የሚቆረጠው፤ በር ላይ ለእንግዳ መቀመጫ የሚሆን ክብና አግዳሚ ከእንሰት የሚዘጋጀው ሸድአ የተባለው መቀመጫ መስሪያ ግብአትም የሚቆረጠው ከነዚህ ቀናት ውጪ ነው ። ሌላው በጩጌና ወቅት ቤት

ቢሰራ፣ምሰሶ ቢቆረጥ ምስጥ ይበላዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው ። ስለዚህም ከቤት ስራ ጋር የተያያዙ ነገሮችን ከጩጌና ተጠንቅቆ መጠቀም በጥንጣን ከሚደርስ ጉዳት ይከላከላል (ቃለ መጠይቅ፣ኤርሚያስ ጎባና 20/09/2014 ዓ.ም) ።

ከላይ ከቀረበው የጽሁፍ ይዘት መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ባህል ለባህላዊ ቤት ለመስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ከመቆረጣቸው በፊት መታወቅና መተግበር ያለበት ከጨረቃ ኡደት ጋር የተያያዘ ደንብ አለ ። ይህም ጨረቃ ከወጣችበት ከ1-3ኛ ቀናትና ጨረቃ ከወጣች ከ15ኛ ቀን ጀምሮ ባሉ ተከታታይ ቀናት ውስጥ ለቤት መስሪያ የሚሆኑ እንጨቶች ቢቆረጡ በምስጥ ይበላሉ ተብሎ ይታሰባል ። ሌላው ከ1-3ቀን ያሉት ጤሮ ጩጌና ሲባሉ ከ15ቀን ጀምሮ ለሶስት ቀን ሲቆይ ጎበና ጩጌና ይባላል ። ስለዚህም በእነዚህ ቀናት እንጨትም ሆነ ሌሎች ግብአቶችን ለቤት መስሪያ ቆርጠው ማዘጋጀትም ሆነ ቤቱን መስራት በባህሉ አይፈቀድም ።

ከቡድን አንድ የውይይት ተሳታፊዎች መካከል አቶ ሀይሌ ሀርጎ ጨጌናን በተመለከተ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

ከጩጌና ጋር ተያይዞ ያለ ነገር ለወላይታ በጣም ወሳኝ ነገር ነው ። ጩጌና ማለት ጨረቃ ከወጣች ቀን ጀምሮ እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ያለው ጊዜ ጤሮ ጩጌና ይባላል፤በጨረቃና በመሬት መካከል ያለ የግንኙነት ጉዳይ ነው ። ጨረቃ ወጥታ እስከ 15ኛው ቀን ድረስ ትሄዳለች፤ ወደ ታች ትታያለች፤ወደ ምስራቁ ጫፍ ትታያለች፤በዛ አካባቢ ደግሞ ፀሀይዋ ሙሉ ሆና ሙሉ አካሏ እየታየ በሚወጣበት ሰዓት ጎባና ጩጌና ይባላል፤በዚህም የምትቆየው እስከ ሦስተኛው ቀን ድረስ ነው፤ልክ እንደ ጤሮ ጩጌና በዚህ ጊዜም ዛፍ አይቆረጥም፤እንሰት አይፋቅም የምሰሶ እንጨት በነዚህ በሁለቱ ጊዚያት የሚቆረጥ ከሆነ ጥንጣን ይበላዋል፤ለቤት መስሪያ የሚሆኑ እንጨቶች ይበሰብሳሉ ተብሎ ይታመናል፤በባህሉ የቤት መስሪያ እንጨቶች ከመቆረጣቸው በፊት እነዚህ ቀናት ግንዛቤ ውስጥ መግባት አለባቸው፤አንድ ሰው ቀናቱን የሚያውቅ ከሆነ ያንን አውቆ ይሰራል፤የማያውቅ ከሆነ አዋቂዎችን ማለትም በአካባቢው ያሉ ሽማግሌዎችን ይጠይቃል? እንጨት ልቆርጥ ነበር ጩጌናው አልፏል ወይ ተብሎ ይጠየቃል?፤ ጨረቃዋን አይተው ነው የሚቆጥሩት ያውቃሉ፤ ወር በገባ ሳይሆን የወላይታ ወር የሚቆጠረው በጨረቃ ነው ። በኛ በኢትዮጵያ ካላንደር አይደለም፤በጨረቃ ነው፤ወሩን የሚመራው ጨረቃ ስለሆነ ነው፤ጨረቃ ወጣች አዲስ ወር ገባ ማለት ነው ። ጨረቃ አልፋ መጥታ ደግሞ ሌላ እስክትታይ ወሩ አልቆ ሌላኛው ወር ተጀመረ ማለት ነው ። በዛ መልኩ ነው የሚቆጠረው፤ልክ ጨረቃ ስትወጣ በቃ ጩጌና ነው በነዚህ ሦስት ቀናት ውስጥ እንጨት አትቁረጡ ፤እንሰት

አትፋቁ ይባላል ፡፡ እነዚህ የጩጌና ወቅቶች ቤት ሲሰራ ከሚታሰቡ ነገሮች አንዱና ዋንኛው የቤቱን ግብአት ከመሰብሰቡ በፊት መቼ መሰብሰብ እንዳለበት ጊዜው መታወቅ አለበት፤በሁለቱም ጩጌናዎች አይሰራም፤ ቤት ሰሪው ሰው ግብአት አይሰበስብም፤ይታቀባል ፡፡ ይሄንን እውቀት የሚያገኘው ከሽማግሌዎች እነሱን በማማከር ነው (ቃለመጠይቅ/2015/ዓ.ም)

በሌላ በኩል ደግሞ የቡድን አንድ የውይይት ተሳታፊ የሆኑት አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ ለቤት መስሪያ የሚቆረጡ እንጨቶች ጩጌና እንዳይነካቸው ጊዜ ተጠብቆ የሚቆረጡ ናቸው ፡፡ ጩጌና የሚባለው በወር ሁለት ጊዜ መዘዋወር የሚያደርግ ጎባና ጩጌናና ጤሮ ጩጌና የሚባሉ ሲሆኑ የጨረቃ ኡደትን ተከትሎ ጤሮ ጩጌና የሚባለው ልክ ጨረቃ የሚወጣበት ጊዜ ተቆጥሮ መግቢያው ላይ ለሦስት ተከታታይ ቀናት የሚቆዩ ሲሆን በዚህ ሰዓት የተቆረጠ ማንኛውም ነገር ይበሰብሳል ፡፡ እሱ የተቆረጠበት ቦታ ላይ የሚያቆጠቁጠው ነገርም ሆነ በህይወት የሌለው የተቆረጠው ክፍልም በምስጥ ተበልቶ ያልቃል ፡፡ የተቆረጠበት ጉቶ የሚያቆጠቁጠው ክፍልም ይበሰብሳል ፡፡ በባህሉ ጩጌና በጣም ወሳኝ ጉዳይ ነው ፡፡ ሁለተኛው ጎባና ጩጌና የሚባለው ሙሉ ጨረቃ ከሰራ በኋላ ወደ መጥለቅ በሚሄድበት ጊዜ የሚያሳያቸው ጎበና ጩጌና ምልክቶች አሉት፤ለሦስት ቀኖች የሚቆይ ነው ፡፡ እነዚህ ስድስት ቀናት መርዛማ ቀናት ናቸው፤ በወላይታ ባህል በጩጌና ወቅቶች የሚቆረጡ፣የሚነቀሉና የሚፈለጡ ነገሮች ሁሉ ደርቀው ይጠፋሉ (ቡድን ሁለት/2015) ፡፡

የቡድን አንድ ተወያይ የሆኑት አቶ አድማሱ ቱማቶ እንደነገሩኝ በአንድ ወር ውስጥ ጨረቃ ከታየችበት የመጀመሪያ ቀን እስከ 3ኛው ቀን ያለው ጊዜ " ጤሮ ጨጌና"(Xeero Ceggennaa) ተብሎ ሲጠራ ከ16ኛው -19ኛው ቀናት የሚሸፍነው ጊዜ ደግሞ "ጎባና ጨጌና" (Goo bana Ceggennaa) በመባል ይታወቃል :: በጨጌና ጊዜያት ዛፎች ቢቆረጡ በጥንጣን ይጠቃሉ፤ እህል ቢዘራና ቢኮተኮት በነቀዝ ይወድማል፤ የንፋስንም ሀይል መቋቋም አይችልም ተብሎ ሲታሰብ ቤት የሚሰሩ ሰዎች እነዚህን ቀናት ግንዛቤ ውስጥ መክተት አለባቸው (ቡድን አንድ፣27/11/2014 ዓ.ም) ፡፡

"ቤቱ ለመኖር ምቹ የሚያደርገው ቤቱ በክረምት ወቅት ሙቀት አለው ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ከብቶቹ እቤት በጓዳ ውስጥ ስለሚኖሩ እና ምግብ የሚዘጋጀውና እሳት የሚነደው ጓዳ ውስጥ በመሆኑ ሲሆን ይህም ለቤቱ ሙቀት ይሰጣል ፡፡ ሌላው የቤቱ አሰራርም በበጋ ወቅት ቀዝቀዝ በክረምት ደግሞ ሙቀት እንዲኖረው ተደርጎ ነው" (ቃለ መጠይቅ፣አድማሱ15/09/2016/ዓ.ም)

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው የወላይታ ባህላዊ ቤት ለመኖር ምቹ እንዲሆን ካደረጉት ምክንያቶች አንዱ ከብቶች እቤቱ ውስጥ ስለሚኖሩና ምግብ የሚበስለው እቤት ውስጥ በመሆኑ እሳት የሚነደውም እዛው ነው ይህ ደግሞ ቤቱ ሙቀት እንዲኖረው ያግዛል ። ሌላው ቤቱ ሲሰራ ከአሰራሩ ጀምሮ በበጋ ቀዝቀዝ እንዲል በክረምት ሙቀት እንዲኖረው ተደርጎ ይሰራል ።

- **የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አቅጣጫ**

የወላይታ ባህላዊ ቤት ሲሰራ የቤቱ አቅጣጫን በተመለከተ የተለያዩ ሀሳቦች መጠቀማቸውን ከመስክ በምልከታ፣በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ተችሏል ።

የወላይታ ባህላዊ ቤት ሲሰራ ንፋስ ወደሌለበት አቅጣጫ በአብዛኛው ወደግራ አቅጣጫ ተደርጎ ነው። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ አውሎ ንፋስ ከመጣ ቤቱን ያፈርሰዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው።

"ቤታቸውን ሲሰሩ አቅጣጫውን ወላይታ ላይ ወደሚገኘው ዳሞት ተራራ አድርገው አይሰሩም። ለዚህ ምክንያቱ ከተራራው የሚመጣው ሀይለኛ ንፋስ ቤቱን ያፈርሰዋል ብለው ስለሚሰጉ ሲሆን በብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ጊዜ የንፋስ አቅጣጫን በሚገባ ጠብቀው ነው ። የወላይታ ባህላዊ ቤቶች የአየር ንብረትን መሰረት አድርገው ይሰራሉ (ቃለ መጠይቅ፣አማኑኤል፣ 17/08/2015 ዓ.ም) ።

የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው የቤቱ አቅጣጫ በአብዛኛው ንፋስ አያገኘውም ተብሎ ወደሚታሰብ አቅጣጫ ተደርጎ የሚሰራ ሲሆን በዚህም በአብዛኛው ወደ ግራ ተመልሶ ይሰራል ከዚህ በተጨማሪ ቤቶቹ የአየር ንብረትን መሰረት አድርገውና ለመኖር ምቹ እንዲሆኑ ተደርገው ይሰራሉ ።

ቤት ሲሰራ የበሩን ሁኔታ የሚወስነው የመሬቱ አቀማመጥ ነው ። በአብዛኛው ንፋስ ቤቱን በማይገፋበት አቅጣጫ ተደርጎ ይሰራል ። የወላይታ ህዝብ ቤቱን በሁለት ቦታ ሳሎንና ጓዳና ብለው ይከፍላሉ ። ከብቶች በወላይታ ባህል ከሰዎች ጋር ቤት ውስጥ ይኖራሉ ። ከብቶቹ የራሳቸው የአቋቋም ቅደም ተከተል አላቸው ። ይህም በመጀመሪያ ፈረስ፣ቀጥሎ በቅሎ፣በሬ፣የወተት ላም ጊደር፣ወይፈን፣ጥጃዎችና በመቀጠል ደግሞ በግ እና ፍየል በተጠቀሰው መንገድ እንዲቆሙ ይደረጋል ። የእንስሳቶቹ በቅደም ተከተል መቆም ወይም መኖር በብሔረሰቡ ያለው ትርጓሜ መጀመሪያ ላይ ፈረስ እንዲቆም የሚደረግበት ምክንያት

በባህሉ ፈረስ ትልቅ ክብር ስለሚሰጠው የወላይታ ሰው የወለደው ልጅ እያለ በፈረስ የሚጠራ ሲሆን በዚህም ፋሳሞ ጎዳ፣ሶርሳ ጎዳ፣ዳማ ጎዳ፣ኢሊሊዋ ጎዳ እያለ በራሱ ፈረስ ነው የሚጠራው ። ሌላው ፈረስ ከሰው ጋር አገር ለማቅናትና ለመጠበቅ ጦር ሜዳ ስለሚውል ነው ። በቅሎ ባለቤቱን ይዛ ስለምትወጣ በሬ ደግሞ እቤት ውስጥ በእርሻ ስራ ስለሚያገለግል ነው ። የወተት ላም ደግሞ እቤት ልጆችን የምታሳድግና ቤተሰብን የምትቀልብ በመሆኗ ክብር ስለሚሰጣት ነው ። የግለሰቡ ሁኔታና የቦታው አመቺነት አቅጣጫ ለመወሰን አስፈላጊ ነው ። ይህም ወደ ምስራቅ አቅጣጫ አዙረው ሲሰሩ ደስተኛ የሚሆኑ አሉ ። ሌላው የግለሰቡን ፍላጎት መሰረት ያደረገ ሆኖ ይሄ ይመቸኛል፤ይሄ አይመቸኝም በማለትም ነው (ቃለ መጠይቅ፣ጳውሎስ፣ኪንዶ፣22/09/2015) ።

ከላይ ከቀረበው የጽሁፍ ይዘት መረዳት እንደተቻለው በባህሉ ቤት ሲሰራ በሩን በአብዛኛው ንፋስ ቤቱን በማይገፋበት አቅጣጫ አድርገው ይሰራሉ ። በቤቱ ውስጥ የእንስሳት ቦታ አያያዝ በቅደም ተከተል ነው ። ከላይ ከቀረበው በተጨማሪ በሌላ መልኩ የወላይታ ህዝብ ለሁለት ነገር በጣም ይጨነቃል፤አንደኛው ለሰርጉ ወይም ለደስታ ዝግጅቱ ይጨነቃል፤ሁለተኛው ለሞቱ ይጨነቃል፤ወላይታ ላይ አንድ አባወራ ቢሞት የሱ ማንነት የሚታወቀው በሞቱ እለት ሲሆን ባሊያ በሚባለው በውሎ ለቅሶ ደጁ ለፈረስ መጋለቢያ እንዲሆን ሰው የሚውልበት እንዲሆን ተደርጎ ይዘጋጃል፤በዚህም የተነሳ ቤቱን ሲሰራ አቅጣጫውን በተመለከተ ወደ ሰፊ ጎዳና አዙሮ ይሰራል ።

የወላይታ ቤት ሲሰራ ቤቱ ወደ ትልቅ ጎዳና ተደርጎ ነው[49] ። አቅጣጫው ደቡብ፣ ምስራቅም፣ምዕራብ፣ሊሆን ይችላል ። ብቻ ቤቱ ፊቱን የሚያዞረው ወደ ትልቅ ጎዳና(መንገድ) ነው፤ለዚህ ምክንያቱ መንገዱ የቤቱ መለያ ስለሆነ ሲሆን ሌላው ከጥንት ጀምሮ የወላይታ ሰው ብቻውን ምግብ አይበላም ። በዚህም ምግብ አቅርቦ ጎዳና ላይ የሚያልፍ ሰው ካገኘሁ በሚል ይመለከት ነበር ። ይህም ከመንፈሳዊ ህይወት ጋር የተያያዘ ሆኖ ከአብርሐም ታሪክ ጋር የተገናኘ እንደሆነ የሚነገር ሲሆን በመጽሐፍ ቅዱስ አብርሐም ቤቱን የሰራው መስቀለኛ ጎዳና ላይ እንደሆነ ኦሪት ዘፍጥረት ምዕራፍ18፡ከቁጥር 1ጀምሮ ተጠቅሷል፤በዚህም መስቀለኛ ጎዳና ላይ ሆኖ እንግዳ ሳይመጣ እህሉን አይበላም፤ይህም በወላይታ የነበረ ባህል ስለሆነ ከረጅም ጊዜ

---

[49]. አቶ ሲሳይ ኩማ፣ቃለ መጠይቅ፣ህዳር12/2015ዓ.ም፣ሶዶ ዙሪያ እና ወ/ሮ ባሎሜ አንጁሎ፣ ቃለ መጠይቅ፣28/12/15 ዓ.ም ።

ጀምሮ አባቶቻችን በር ላይ ቆመው ገበያ፣ለቅሶ፣ የሚሄደውንም ብቻ በደጃቸው የሚያቋርጥን ሰው ጠርተው እህል ያበላሉ፤ለዚህ እንዲመቻቸው ቤታቸውን ወደ ሰፊ ጎዳና አዙረው ይሰራሉ

ከላይ የቀረበውን ጽሁፍ በሁለት መንገድ መረዳት ይቻላል ፡፡ የመጀመሪያው በወላይታ ብሔረሰብ ቤት ሲሰራ አቅጣጫው ወደ ምስራቅ፣ሰሜን፣ደቡብና ምዕራብ ተደርጎ ሊሰራ ይችላል፡፡ ዋናው የቤቱ አቅጣጫ ወደ ትልቅ ጎዳና ተደርጎ መሰራቱ ነው ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ጥንት በባህሉ ህዝቡ ብቻውን መብላት፤መጠጣት ስለማይወድ በሩ ላይ ቆሞ በተለያየ ምክንያት አልፈው የሚሄዱ ሰዎችን ቤቱ በማስገባት ያበላል፤ ያጠጣል ፡፡ ይህም በመጽሐፍ ቅዱስ ከአብርሐም እንግዳ መቀበል ጋር የተገናኘ እንደሆነ ነው ፡፡

## 6.11. በወላይታ የቤት አሰራር ውስጥ የህዝቡ የሥራ ድርሻዎች

በዚህ ክፍል በወላይታ ባህላዊ ቤት ስራ ተሳታፊ የሚሆኑ የብሔረሰቡ ክፍሎችና የስራ ድርሻቸው ቀርቧል ፡፡ በብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ወቅት የብሔረሰቡ ተጠሪዎች፣አባቶች፣ እናቶች፣ ወጣቶች፣ የቤተሰቡ አባላት፣ ጎረቤቶች፣ ዘመዶችና የአካባቢው ህዝብ የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የቤቱን ባለቤቶች የማገዝ ተግባር የተለመደ ነው ፡፡ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (ድቡሻ ፎጊያ አሳታ) የሥራ ድርሻ በወላይታ በማንኛውም ስራ ላይ ስራውን የሚያስጀምሩ፣የሚመሩ በብሔረሰቡ  የተመረጡ ድቡሻ ፎጊዮጋ (Debbushshafogiya asati) የሚባሉ ሲሆኑ እነሱም የመምራት፣የመባረክ፤የመመረቅ፣ስልጣን የተሰጣቸውና መንፈሱን እውን ያደርጋሉ የሚባሉ ሲሆኑ ብሔረሰቡን የሚመሩ እነሱ ናቸው ፡፡

(Debbushsha fogiya asati) ዱቡሻ ፎጊያ አሳታ ስለተባሉት  ሰዎች የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ወልደ ማርያም ልሳኑ ሲገልጹ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (Debbushsha fogiya asati) ዱቡሻ ፎጊያ አሳቲ የሚባሉት የብሔረሰቡ ታላቆች ናቸው ፡፡ የብሔረሰብ ተጠሪዎች የትኛውም የብሔረሰቡ ስራዎች ውስጥ ቅድሚያ የሚሰጣቸው ስለሆኑ ያለእነሱ ምክር ማንም ሰው ደስ ያለውን ነገር መስራት አይችልም ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ብሔረሰቡ  በእነዚህ ተጠሪዎች (መሪዎች) አመራር ውስጥ ለመኖር አምኖ የሾማቸው ሰዎች በመሆናቸው ነው ፡፡ እነዚህ ሰዎች ሲሞቱ ወዲያው የሚተኩ በመሆናቸው በእነዚህ ሰዎች ምትክ ሌላ ሰው አይቀየርም ፡፡ ምክንያቱም የቤቱ ታላቅ ሳይሆን የብሔረሰቡ ታላቅ ሰው ስለሆነ በሞት ይተካል

የብሔረሰቡ ተጠሪዎች ጎሳ ውስጥ የጎሳ መሪ እንደ ማለት ሀሳብ ያለው ሆኖ ልዩነቱ አንድ ታላቅ ጎሳ ይመረጥና ከተመረጠው ጎሳ ውስጥ ደግሞ ለዚህ ተግባር የሚሆን ሰው ይመረጣል፡፡ ለምሳሌ ንግስና ከማላ የሚወጣ ከሆነ ከነሱ ውስጥ ይመረጣል ፡፡ የብሔረሰብ ተጠሪዎች (Debbushsha fogiya asati) መርቀው የማድረስ ስልጣን አላቸው ፡፡ ንግስና የሚወጣው ከወላይታ ማላዎች ነው ፡፡ ማላ የሚባለው 12 ክፍሎች አሉት ከ12ቱ ይሻላል ብለው የመረጡትን ለምሳሌ ወላይታ ውስጥ አሩጂያ የማላ ዘር ነበር፤ ትግሬ የማላ ዘር ነበር፤ በማላ የሚነገሩ ሁለት ጎሳዎች ዝርጎ ማላና ዶጎ ማላ ይባላሉ ፡፡ ሌሎቹ ወደ 78 የሚሆኑ የዶጋላ ጎሳዎች ጦማ ጎሳ በሚል በተለይ በእደ ጥበቡ ሞያ የሚገለጹ ናቸው ፡፡

አቶ ወልደማርያም ከላይ ካቀረቡት ሃሳብ በተጨማሪ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች ዶጎላ አያና ዶጎና እና ካታ ዶጎና ከሚባሉት ይመረጣሉ ፡፡ አያና ዶጎና የሚባለው መንፈሱ ያላቸው በብሔረሰቡ ውስጥ መርቀው የማሳደግ፤ረግመው የማቀጨጭ በብሔረሰቡ ተቀባይነት ያላቸው ወደ ስምንት የሚሆኑ ጎሳዎች አሉ ከእነዚህ ጎሳዎች መካከል አንዱ ይመረጥና የብሔረሰቡ መሪ እንዲሆን ይደረጋል ፡፡ ይሄ አንድ ማህበረሰብን ይመራል፤ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች የመባረክ፣የመመረቅ፣የመምራት፣ መንፈሱን እውን የሚያደርጉ ናቸው ፡፡ የብሔረሰቡ ተጠሪዎች የሚባሉት ለምሳሌ ከዎሚጊራ (womigira) ከሚባል ጎሳ ከተመረጡ በእነዚህ ጎሳ የሚያመልኩት አምላክ አምባዛ የሚባል ሲሆን ይህም የመለኮታዊ ስልጣን አለው ብለው ስለሚያምኑ ይማጸኑታል ፡፡ ቡቡላ (Bubulaa) የሚባለው ሌላኛው የሚያምኑበት የተለየ አምልኮ አላቸው ፡፡ ሙሉጉሻ (mulugusha)የሚባለው የሚያምኑበት የቤተሰብ አምላክ አላቸው ፡፡ ከነዚህ ጎሳዎች ውስጥ የተገኙት የብሔረሰቡ ተጠሪዎች የቤተሰባቸውን አምላክ ቡራኬና ምርቃት ወደ ብሔረሰቡ ያስተላልፋሉ ተብሎ ይታመናል ፡፡ በዚህ አይነት ወደ 12 የሚያህሉ በታወቁ በአባቶቻቸው አማልክት ህዝቡን መርቀው የማድረስ ስልጣን አላቸው (ቃለመጠይቅ፣ወልደማርያም፣2015፣ዓ.ም) ፡፡

የብሔረሰቡ ተጠሪዎችን በተመለከተ አቶ ወልደማርያም አክለው የሚከተለውን ሀሳብ አስቀምጠዋል፡-

የብሔረሰቡ ተጠሪዎች ሲመርቁ አሜን ብሎ ሲረግሙ ይቅርታ ጠይቆ የሚሰጡትን መመሪያ ተከትሎ ይኖራል ፡፡ እነዚህ ሰዎች ተጠሪነታቸው ለነገስታቱና ለህዝቡ ነው ፡፡ ስለሆነም በወቅቱ የነገስታቱን ትዕዛዝ በቀጥታ አድርሶ መንፈሳዊ ማድረግ ፤የብሔረሰቡን ጥያቄ ቀጥታ ወደ ንጉስ የማቅረብና ምላሽ የማግኘት( የአማላጅነትም አገልግሎት) ጭምር የሚሰጡ ሰዎች ናቸው ፡፡

ሁሉም ሥራ ላይ የመወሰን ስልጣን ስላላቸው ከስራው ጋር የተያያዙ ነገሮች ይመለከታቸዋል ፡ በዚህም ቤት በሚሰራ ሰዓት ከቀናቱ፣ከወራቱና ከጨረቃና አቆጣጠሩ ጋር በተያያዘ ለህዝቡ በባህላዊ ቤት አሰራር ላይ እውቀት ላላቸው ሽማግሌዎች መመሪያ የሚሰጡ እነሱ ናቸው፤ በነሱ ቡራኬ ስር ሆኖ ነው ሁሉም ነገር የሚሰራው ስራው እስከሚጠናቀቅ ህዝቡ በእነዚህ ሰዎች እየተመራ ነው ስራውን የሚያከናውነው(ቃለመጠይቅ፣2014 ዓ.ም) ፡፡

አቶ ጳውሎስ፣ቃለ መጠይቅ፣15/09/2015/ዓ.ም ከላይ ከቀረበው ሀሳብ ጋር በተያያዘ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል፡- ጥቅል ስራው የሚሰራው በደቦ (በህብረት ስራ) ነው ፡፡ ደቦ ደግሞ ሀላፊ አለው ፡፡ ሀላፊ ማለት ዋናው የሚያዘው ህጻኑንም አዋቂውንም እላይ ጣሪያው ላይ ወጥተው የሚሰሩትን የሚያሳይና የሚያዝ ማለት ነው ፡፡ ምሰሶውን ለመነተት፤ ካለበት አምጥተው ለመስራት፤ሌሎች ስራዎችን ለመስራት ሀላፊው ደቦው ሲሆን እሱም ያዛል፤ከተቀመጡ ተነሱ ይላል፤ከደከሙ ደግሞ አስቀምጦ ተጋግዘው እንዲሰሩ፤እንደገናም ስራውን እንዲቀጥሉ እያደረገ ስራው በአግባቡ እንዲሰራ ያደርጋል ፡፡

- **የሴቶች፣የወጣቶች፣ ጎልማሶች፣የቤት ቁሶችን የሚሰሩ ሰዎች የሥራ ድርሻ**

ምሰሶ በሚቆምበት እለት ሴቶች የተለያዩ ስራዎችን በጋራ ይሰራሉ ፡፡ በዚህም እናቶች ምግብ ያዘጋጃሉ፤መጠጥ ያዘጋጃሉ፤ንፍሮ ይቀቅላሉ፤ቂጣ ይጋግራሉ፤የተለያየ ነገር ይሰራሉ ፡፡ ወጣት ሴት ልጆች ደግሞ ቤት ለሚሰሩት ሰዎች የሚሄደውን ምግብ ተሸክመው በማገዝ እንዴት እንደሚሰራና እንደሚስተናገድ ከእናታቸው ያያሉ፤ይማራሉ ፡፡ ይህንንም ከቤቱ ባለቤት ውጪ ሁሉም ሰው ከየቤቱ የሚጠጣ፣የሚበላ ምግብ አዘጋጅቶ ያመጣል፤ይህም ያጋኖ ይባላል፤የቤቱ ባለቤትም በቤቱ ምግብ፣መጠጥ እንዲዘጋጅ ያደርጋል፤ሌላው ቦርዴ የሚቀመጥበት ትልቅ ጋን ይቀመጣል፤እዛ ጋን ውስጥ ከየቤቱ የመጣ መጠጥ ይገለበጣል፤ ይህም መጨረሻ ላይ ይጠጣል፤ከዚህ በተጨማሪ ልክ ምሰሶው ወደ ሰፈር ሲደርስ ሴቶች መጥተው እልልታቸውን ያቀልጣሉ፤ያጨበጭባሉ፤እልል ይላሉ ደስታቸውን ይገልጻሉ (ቃለ መጠይቅ፣አየለ፣አድማሱ፣ወል ደማርያም 2016፣ዓ.ም) ፡፡

ሌላው ወጣቶችና ጎልማሶች ደግሞ ምሰሶውን ከህዝቡ ጋር ተሸክመው በማምጣት እንዲሁም ወጣቶች ቀለል ያሉ ነገሮችን በማቀበል ይተባበራሉ ፡፡

“በአካባቢው የተለያዩ የቤት ቁሶችን የሚሰሩ ባለሙያዎች ቤት ሲሰራ ከባለቤቱ የሚሰጣቸው የሥራ ድርሻ ምሰሶ በሚቆም ቀን ለቦርዴ መጠጫ የሚያገለግል ጽዋ የሚባል ከሸክላ የሚሰራ መጠጫን እንዲሰሩ ትእዛዝ ይሰጣችዋል ፡፡ የሸክላ ባለሙያዎቹም በተነገራቸው መሰረት ሁለት

ሰዎች በአንድነት እንዲጠጡበት የሚያገለግል ጽዋ ይሰራሉ” (ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዴ፣14/10/2015 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው በባህሉ በቤት ስራ ወቅት ምሰሶ በሚቆምበት ሁሉም ሰዎች የራሳቸው የሆነ የሥራ ድርሻ አላቸው ፡፡ እናቶች ምግብና መጠጥ በማዘጋጀት፣ወጣት ሴቶች ምግቡን ቤት ወደሚሰራበት ቦታ በማጓጓዝና በመስተንግዶው ከእናታቸው ጎን በመሆን የሥራ ድርሻቸውን ይወጣሉ ፡፡ “ህዝቡ ምሰሶውን እየጎተቱ ያመጣሉ፡፡ ህጻናት፣ወጣቶችና ጎልማሶች ሳይቀሩ ቀለል ያሉ ነገሮችን በማቀበል ይተባበራሉ፡፡ ምሰሶውን ያመጣሉ፤ ወደ ቤት ያስገባሉ፤ያቆማሉ፤የተዘጋጁ ምግቦችን ቤቱን ለሰሩት ሰዎች በማስተናገድ እናቶችን ይረዳሉ ፡፡ ሽማግሌዎች ይመርቃሉ፤ምሰሶውን ያቆማሉ” (ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዴ፣14/10/2015፣ዓ.ም) የቀረበው መረጃ በንድፈ ሀሳብ ሲቃኝ በማህበራዊ አስተምህሮ ንድፈ ሃሳብ (Social Learning theory) እንደተገለጸው የፆታዊ ልዩነት ምንጩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ፆታ ለይ ተግባራትና ህገ ደንቦች ናቸው ብሎ ያምናል (Bandura 2006). ስለዚህም የሥራ ክፍፍላቸውም ጾታን መሰረት ያደረጉ ናቸው ፡፡

- **የቤቱ ባለቤት የሥራ ድርሻ**

የአካባቢው ነዋሪዎች በብሔረሰቡ ተጠሪዎች፤በሽማግሌዎች አማካይነት ቤቱን ሰርተው ከጨረሱ በኋላ የቤቱ ባለቤት የቀሩ ስራዎችን በተመለከተ ውሳኔ ይሰጣል ፡፡ ይህም ቤቱን ሌላ ቀን ለመጨረስ ቀጠሮ ማስያዝ ሲሆን ይህም እንደባለቤቱ ዝግጅት ይወሰናል (ቃለመጠይቅ፣ኢያሱ ገጃቦ፣ኦፋ፣14/11/2014 ዓ.ም) ፡፡

በአጠቃላይ ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ባህል ቤት ሲሰራ የብሔረሰቡ አባላት በሙሉ የየራሳቸው የስራ ድርሻ ያላቸው ሲሆን እነዚህም የብሔረሰቡ ተጠሪዎች (ድቡሻ ፎጊያ አሳታ) የሴቶች ሥራ፣የአካባቢው ሽማግሌዎች፣የቤቱ ባለቤት፣የአካባቢው ወጣቶችና ጎልማሶች፣በአካባቢው የቤት ቁሶችን የሚሰሩ ሰዎች የራሳቸው የሥራ ድርሻ አላቸው ፡፡ በባህሉ ቤት በሚሰራበት ወቅት የቤተሰቡ አባላት፣ጎረቤቶች፣ዘመዶችና የአካባቢው ህዝብ የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የቤቱን ባለቤቶች የማገዝ ተግባር የተለመደ ነው ፡፡

የብሔረሰቡ የስራ ድርሻ በመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ ሲቃኝ ግለሰቡ በማህበራዊ ሥርዓቱ ውስጥ የሚሳተፈው በስርአቱ ውስጥ ባለው ልዩ ልዩ ሚናዎች እና የስራ ቦታዎች መሰረት ከሌሎች ጋር በመገናኘት ሲሆን ቤተሰብ ደግሞ ትልቅ ሚና አለው ፡፡ Parsons ወንድ

እና ሴት ልጆችን በመለየት ከስርዓተ-ፆታ ጋር የተያያዘ ተግባር-ተኮር ሚናዎች የወንዶች እና የሴቶች ተለይተው ይታወቃሉ። እነዚህ ጾታ-ተኮር ተደጋጋፊ ሚናዎች የቤተሰብን ስርዓት እንዲሁም ደግሞ የህብረተሰቡን አጠቃላይ ስርዓት ሚዛን ይጠብቃሉ (Parsons and Bales 1955)

በወላይታ ምሰሶ በሚቆምበት ዕለት ሴቶች በጣም ስራ ይበዛባቸዋል፤ጎረቤቱ፣ዘመድ አዝማዱ ሁሉ ዝግጅት ያደርጋሉ ። ለቤተ ሰሪው ምግብ አዘጋጅተው ይዘው ይሄዳሉ፤ቤት ሰሪውም በቤቱ የሚያዘጋጃቸው ምግቦችና መጠጦች አሉ ። እነዚህም ንፍሮ ምሰሶ ለማቆም ለሚሰበሰብ ህዝብ እንዲበቃ በሚል በበርሜል ይቀቀላል ። ቆጮ እና ቂጣ ይዘጋጃል፤ቦዬ፣ቦይና(ጎዳሬ) ተቀቅሎ ይዘጋጃል። ከምግብ ዝግጅት አካል የሆነው ሌላው ባህላዊ መጠጥ ነው። በቤቱ ስራ ወቅት ቦርዴ የተባለ መጠጥ የሚዘጋጅ ሲሆን አሰራሩም በደንብ ሳይልም(ሳይደቅ) ከተፈጨ የቦቆሎ ዱቄት እና የገብስ ብቅል ሲሆን መጀመሪያ የተዘጋጀው የቦቆሎ ሽርክት(ዱቄት) ተዘፍዝፎ ያድራል፤ይነከራል፤እንክሮ ገባ ሳይል በነጩ ይነኮራል ። ከዚያም ወጥቶ እንዲቀዘቅዝ ይደረጋል ። እንደገና ይህ የተነኮረው እንኩሮ ታሽቶ በወፍራሙ እየተድበለበለ በእንፋሎት ይቀቀላል ። ይህም “Sulaa” ይባላል ። መጀመሪያ እንደ ጥንስስ ተበጥብጦ ካደረ በኋላ የብቅል ዱቄት ጋር በደንብ እስከሚዋሃድ ውሀ ተመጥኖ እየተጨመረ ይታሻል ። ተደፍድፎ ያድርና በማግስቱ ሆፔ በሚባል ወንፊት በመሰለ ማጣሪያ ተጨምቆ ይጣራና ለመጠጥነት ይውላል ። ይህም ምሰሶ በሚቆምበት ጊዜ በትልቅ ጋን ተዘጋጅቶ በቅል እየተደረገ ይጠጣል (ጳውሎስ አላሮ፣ቃለ መጠይቅ፣ኪንዶ፣2015ዓ.ም) ።

- **የወላይታ ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት የሚቀርቡ ምግቦች**

ባህላዊ ቤት በሚሰራበት ወቅት የተለያዩ ምግቦች ይቀርባሉ ። የምሰሶውን ጫፍ የሚጠርቡ ባለሙያዎች፤የበር ጉበንና መግቢያውን የሚያስውቡ የዛ ሙያ ያላቸው ሰዎች ናቸው ። ለእነሱ የሚሰራውና ለእንግድነት ተጋብዘው ትንሽ ራቅ ካለ ቦታ ለሚመጡ ዘመድ አዝማዶችም የሚሰራው የተለየ ምግብ ነው ።

ይህንኑ በተመለከተ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት ወ/ሮ አየለች ተ/ማርያም 03/12/2016/ዓ.ም ወ/ሮ ሽዋዬ ፎልታሞ 10/12/2016/ ዓ.ም በቃለመጠይቅ የሚከተለውን መረጃ ሰጥተዋል ፡-

የግድግዳ እንጨት ሲዘጋጅ ከአደንጓሬና ከበቆሎ ንፍሮ ይዘጋጃል፣ፍሬ ቡና ይፈላል፤ቅጠል ቡና በደምብ ተቀምሞ ይፈላል ። ግድግዳ በሚቆምበት ወቅት ከአደንጓሬና ከበቆሎ ንፍሮ ይቀቀላል፤ፍሬ ቡና እና ቅጠል ቡና ተቀምሞ ይፈላል ።

- **የቅጠል ቡና(haytta tukkiya) አፈላል**

በመጀመሪያ ቡናውን ከጓሮ ይለቀማል፣ ቀጥሎ ይወቀጣል፤ውሃተመጥኖ የተወቀጠው የቅጠል ቡና(haytta tukkiya)እሳት ላይ ከለሩን እስከሚቀይር በደንብ ከተንተከተከ በኋላ ከእሳት ላይ ይወርዳል ፡፡ ቀጥሎ በማጣርያ ይጣራል፡፡ በመጨረሻም የተለያዩ ቅመማ ቅመሞችን እንደ ጤናዳም፣ነጭ ሽንኩርት፣ ዝንጅብል፣ድንብላል፣አጉፍያና የዛፍ ፍሬ, ተወቅጠው ይጨመራሉ

**የቅጠል ቡና ጥቅሞች**

1. ለሆድ ሕመም እና ሴቶች ሲወልዱ ሆዳቸው ውስጥ አላስፈላጊ ደም እንዳይቀመጥ ከለጋ ቅቤ ጋር የተፈላ የቅጠል ቡና እንዲጠጡ ይደረጋል ይህም ሆዳቸውን አጥቦ ቆሻሻ ያወጣል ይባላል፡፡

**Wolayttan haytta tukkiya essiyo maaraa mankkaanne go"aa.**

Kasetidi tukkiya maxidi, udalan caddidi guuttaa wodiya caddidoogee zo"ana mala udulan wottishshheettees. Hegaappe simmidi haattaa taman wottidoogaa bollan yeggeettees. Hegee loyttidi poridaagaa kessettees. Ha tukkee taman poriiddi de'ishshin, assi koshshiya tukke xaliya leem, naatiraa, xalotiya, aguppiya, tukkiyan yeggiyo zaafiya ayfiyanne hayttaa, tuummuwa, yenjjeeluwa, deebbuwa, katikkallaa/shillariya, keppuwa, h.h.m ubbabaa issippe gattidi caddidoogaa caala oyssaara gattidi/ oyssaa yeggikke giikko ha xaleta Jabanan yeggidoogaa bolli xilissidi taman guyye wottidoogee zaari zaari poridi ha yeggido xalee ka'idoogaa siiniyan tigidi ganxxidi be'idi kesseettees. Ha tukkiya kokkaara, shaashshaara, dumma dumma boyyiya, shukkaariya malatiyabatuurakka uyettees.

Wolayttan haytta tukkiyassi de'iya go"ay

- Uloy sakkikko uyikko xallees.

- Qassi macca asay yeli simmiyo wode yelo suuttay uluwan dagattenna woykko attenna mala yelaga oyssaanne naatiraa darissido haytta tukkiya uyikko keehippe maaddees woykko uluwan koshshenna.suuttay uttenna mala meeccidi kessiichchees/ geeshshees.

Xaaxi waaxin ulo giddon sakkiya ay harggiyassikka haytta tukke keehippe maaddees/xallees.

Dunuye taassi erettiyageeta ubbaakka xaafaas. Ane xeellada taappe attidabata gujjada go'etta. Ta michcheessi injjeto!

ከዚህ በተጨማሪ ቂጣና ንፍሮ ይቀርባል ፡፡ በጣሪያ ሥራ ወቅት ከትኩስ ወተትና ባጭራ ከሚባል የእንስት ተዋጽኦ ከሚገኘው ቆጮ የሚዘጋጅ ባህላዊ ምግብ ይቀርብላቸዋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ አይብ ከሥጋ፣ ከእንቁላል እንዲሁም ከሥጋና ከጎመን ጋር ይዘጋጅላቸዋል ፡፡ እነዚህ ለየት ያሉ ምግቦች የሚቀርብላቸው ምክንያት ጣሪያ የሚሰሩ ሰዎች በሙያው እውቀት (ልምድ) የገበዩ ሰዎች ስለሆኑ እና ቤቱን የሚያሳምረው ዋናው የጣሪያ ስራ ስለሆነ ጣሪያውን በሚገባ ጠቅጥቆ የመስራት ስራ እነሱን ስለሚመለከት ነው ፡፡ አሰራሩም በመጀመሪያ አይቡ ውሃ እንዳይኖረው ተደርጎ በንጹህ ጨርቅ በደንብ ይጨመቃል ፡፡ ቀጥሎ ቅቤ ይነጠራል፤ቀይ ሥጋ ገንተር ተደርጎ በደቃቁ ይከተፋል፤ አይብና ሥጋው ውስጥ ነጭ አዝሙድ ጥቁር አዝሙድ፣ አብሽና ኮሮሪማ ተመጥኖ ይጨመርበታል፤ደቃቅ ጨው ይነሰነሳል፤ከተነጠረው ቅቤ ጋር ይዋሃድና በቆጮ እና በማሽላ ወይም በበቆሎ ቂጣ ይቀርብላቸዋል ፡፡ ጣሪያ የሚሰሩት ሰዎች ከህዝቡ ጋር ሳይሆን ለብቻ ይስተናገዳሉ ፡፡ ይህን ከተመገቡ በኋላ ትኩስ ወተት ይቀርብላቸዋል በባህሉ ጣሪያውንና ሌላውን የቤቱን ክፍል ለሚሰሩ የሚቀርቡ ምግቦች የተለያዩ ናቸው ፡፡ ህዝቡ በደጎ በሚነሳበት ወቅት ለህዝቡ ንፍሮ(Kokkaa)፣ቂጣ (oyttaa) ቦርዴ (Parssuwaa) የሚባል ባህላዊ መጠጥ ይዘጋጃል ፡፡ ደጎው በንፍሮ(ኮካ)፣ ቂጣና ቦርዴ (ኦይታኔ ፓርሱዋ) ይስተናገዳል ፡፡

ከላይ ከቀረበው በተጨማሪ ጳውሎስ አሳሮ፣ቃለ መጠይቅ፣ኪንዶ፣2015ዓ.ም ጣሪያ ለሚሰሩ ሰዎች የሚቀርቡ ምግቦች ሲገልጹ ቀይ ስጋ በጣም ሳይደቅ ጎረድ ጎረድ ተደርጎ ይከተፍና በቅመም እና በቅቤ በደንብ ተለውሶ በቆጮ እና በቂጣ ይቀርብላቸዋል ፡፡ ቅቤ ቡና ቡናው በቀይ ይቆላና ቅመማ ቅመም ተጨምሮበት ይወቀጣል፤ጀበናው ውስጥ ቅቤ ተጨምሮ ውሃ በትንሹ ተደርጎ የቡናው ዱቄት ተጨምሮበት ይፈላል ፡፡ ቀጥሎም ከገብስ፣ ከባቄላ፣ ከሽንብራ፣ወይም ከአተር ቆሎ ጋር ይቀርብላቸዋል ፡፡ ቡናውን ከጠጡ በኋላ ትኩስ ወተት ይቀርብላቸዋል ፡፡ ቡልአ ከሚባል የእንስት ተዋጽኦ ይሰራል ፡፡ የአዘገጃጀት ሂደቱም እንስት ይፋቅና ሳይውል ሳያድር የተፋቀው ይጨመቃል፤ይህም በሰታቴ ድስት ይደረግና ውሃው ቀስ በቀስ ይቀነሳል ከስር ዘቅጦ የቀረው ቡልአ ፀሐይ ላይ ተደርጎ እንዲደርቅ የሚደረግ ሲሆን ይህም በኮባና በወፍቾ አየር እንዳይገባበትና እንዳይነፍስ በደንብ ታስሮ ይቀመጣል ፡፡ በመጀመሪያ ለማዘጋጀት ታስሮ ከተቀመጠው ቡልአ በመውሰድ በቆጮ ወንፊት ተነፍቶ በሸክላ ምጣድ ይነኮራል ፡፡ ቀጥሎ የተነኮረው ቡልአ ውሃ ሳይነካው በእንፋሎት ይቀቀላል ፡፡ በመጨረሻም የተነጠረ ቅቤ፣ቅመም እና ጨው ተጨምሮበት ይዋሃድና ይቀርባል ፡፡

ፎቶ 23፡- ሙቾ (Muchchuwa) ባህላዊ ምግብ



ከቅመም ይዘጋጃል፤አሰራሩም ቦዬው በደምብ ተፍቆ ከታጠበ በኂላ ይቀቀላል ፡፡ ከበሰለ በኂላ ወጥቶ በመክተፊያ ተደርጎ ወፍራም እና አጭር ዱላ ወይም ለሱ ተብሎ በተዘጋጀ አጥንት(ካቲሴ) በደንብ ብትን ብሎ ዱቄት እስከሚሆን ይቀጠቀጣል፤ከዛም የተነጠረ ቅቤ በድስት ተዘጋጅቶ ያየተቀጠቀጠው ቦዬ በድስቱ ይጨመራል፤ቅመም እና ጨው ተነስንሶበት በደንብ ይታሽና ይቀርባል፡፡

**መ. ቦይና ጫዲያ (Boynaa cadhdhiya) :-** ቦይና ከሚባል ሥራ ሥር፣ከቅቤና ከቅመም ይዘጋጃል፤ቦይናው ተፍቆ ከታጠበ በኂላ ይቀቀላል፤ከበሰለ በኂላ ወጥቶ መክተፊያ ላይ ተደርጎ ይቀጠቀጣል፡፡ የተነጠረ ቅቤ ይደረግበትና በቅቤና በቅመም በደንብ ይታሽና በዳታ በርበሬ ይቀርብላቸዋል፡፡

**ፎቶ 24፡- ተቀቅለው የቀረቡ ቦዬ፣ስኳር ድንችናድቡልቡል ድንች**
**(Doysettida boyyiya,shukkaariyanne donuwa)**




**ምንጭ፡- ሶዶ ዙሪያ ፣ በፎቶ አንሺና በአጥኚዋ የተነሳ 2015ዓ.ም**

ፎቶ 25፡- ለመስተንግዶ የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጥ







ከእንሰት ቡልአ
የሚዘጋጅ(ሙቾ)

ከአደንጓሬና ቆጮ
የሚሰራ (ብላንዶ)
bilandduwa.

**ምንጭ፡- ኦፋ ወረዳ፣በአጥኚዋ የተነሳ 2015ዓ.ም**

**ሠ. የአመጋገብና የአጠጣጥ ስርዓቶች**

የአመጋገብና የአጠጣጥ ሥርዓቶች በወላይታ ብሔረሰብ ትርጓሜ አላቸው ፡፡ ከላይ እንደተገለጸው በቤቱ ስራ ወቅት የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ከተዘጋጁ በኋላ በቤቱ ስራ ወቅት የተሳተፉ ሰዎች በሙሉ የሚመገቡበት የራሱ ሥርዓት አለው ፡፡ ምግቡ ሁሉ ተሰናድቶ ከመጣ በኋላ ሰው የሚበላው የሚጠጣው በተሰራው አዲሱ ቤት ውስጥ ነው ፡፡ አቀማመጣቸው እቤቱ ውስጥ ዙሪያውን ክብ ሰርተው ሲሆን መጀመሪያ ወንዶችና በእድሜ ጠና ያሉ ሽማግሌዎች በሙሉ ይቀመጣሉ፤የነዚህም አቀማመጥ በቤቱ ዙሪያ ክብ በመስራት ሲሆን ይህም አንድነትንና ህብረትን ለመግለጽ ነው፤ምግብ ሲመገቡም በጋራ ነው፤የመጣውን መጠጥ እዛው በጋራ ይጠጣሉ ፡፡

ለሁለት ሰው በአንድ ጽዋ መጠጫ እንጂ ለአንድ ሰው አይሰጥም ፡፡ ይህም በባህሉ ፍቅርንና ወንድማማችነትን ለመግለጽ ሲባል የሚደረግ ነው ፡፡ በተጨማሪም ቂጭ ብለው ቂጣ፣ንፍሮና የተለያዩ ነገሮችን ይበላሉ፤መጠጣት ሲያስፈልግ በጋራ ይጠጣሉ፤ ለምግቡ ማቅረቢያ አንድ

ወጥ የሆነ ኮባ በቤቱ ዙሪያ ሰው ከተቀመጠ በኂላ ይነጠፋል፤ ምግቡ የሚቀርበው ኮባው ላይ ነው ፡፡ ኮባው እርጥብ ሲሆን ትርጓሜውም ነገር ሁሉ መልካም ይሁን፤ሁሉም እርጥብ ይሁን፤ ቤቱ እርጥብ ይሁን፤ዘመኑ እርጥብ ይሁን የሚል ነው ፡፡

ሌላው የኮባው ወጥ መሆን የህዝቡን አንድነትና እርስ በርስ ተደጋግፈውና ተያይዘው መኖራቸውን ለመግለጽ ነው ፡፡ እዛው አዲሱ ቤት ውስጥ ይቀመጣሉ፤ ምግቡም አዲሱ ቤት ውስጥ ኮባ ላይ ይቀመጣል፤የሰፈሩ ልጆች ከአባቶቻቸው ፊት ለፊት ተያይዘው ይቀመጣሉ ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በባህሉ ልጆቹ የአባቶቻቸውን ፈለግ ተከትለው እነሱ የሚያደርጉትን እያዩ ፤ደንቡን ተከትለው ባህላቸውን አክብረውና ወደው እንዲያድጉና እንዲያስቀጥሉ ነው ፡፡

ልጆቹ ይበላሉ፤ የሚጠጣው ነገር ለልጆች የማያሰክርና ከእድሜአቸው ጋር የሚሄድ ከገብስና ስኳር ወይም ማር ብቻ የሚሰራ ኪኔቶ የሚባል መጠጥ ወይም ከሸንኮራ አገዳ የሚዘጋጅ ቃሬቦ ይቀርብላቸዋል ፡፡ ምክንያቱም ልጆች በልጅነታቸው የአዋቂዎችን መጠጥ መጠጣት ከጀመሩ በጤንነታቸው ላይ ችግር ከማድረሱም ባሻገር ስነምግባራቸው ጥሩ እንዳይሆን አስተዋጽኦ ያደርጋል ፡፡ ስለሆነም ከእቅም ጋር የሚሄድ ነገር ከሆነ እንዲጠጡ ይደረጋል ፡፡ ከዚያ በኂላ ለቦርዴ መጠጫ የተባለውን ጽዋ የሰሩት የሸክላ ባለሙያዎች ደግሞ ሰው ሲበላ የተረፈውን የበሬ ስጋም ሆነ ሌላ ምግብ ሁሉ መጨረሻ ላይ ሰብስበው ይዘው ይሄዳሉ ፡፡ ለእለቱ ዝግጅት የቀረበው ምግብ ወደቤት ተመልሶ አይወሰድም ፡፡ ወደ ቤተሰሪው/የቤቱ ባለቤት/ ቤት አይገባም ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በባህሉ ደንብ ነው ፡፡ ምግቡን ወደ ቤት መመለስ እንደ ነውር ይቆጠራል ፡፡[50]

ከላይ የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያለከቱት በወላይታ ብሔረሰብ ቤት በሚሰራበት ወቅት ለሚሰሩት ባለሙያዎች፤በቤቱ ስራ ለተሳተፉ ለአካባቢው ሰዎች የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ይዘጋጃሉ ፡፡ ለዝግጅቱም በባህሉ መሰረት ቤት ለሚሰራው ሰው ከጎረቤት፣ከዘመድና ጓደኛ እንደቅርበታቸው መጠን የተለያዩ ምግቦችና መጠጦች ይመጣሉ ፡፡ ሌላው የቤቱ ባለቤት በሥራው ለደከሙ ጎረቤት፣ጓደኛ፣ዘመድና ለአካባቢው ህዝብ የሚያዘጋጀው ነው ፡፡ ስለዚህም በወላይታ ባህል ምግብና መጠጦች የሚቀርቡት ከቤት ስራው ጋር በተያያዘ ነው ፡፡

---

[50] . ጳውሎስ አላሮ፣ቃለ መጠይቅ፣ኪንዶ፣2016ዓ.ም ፡፡

## 6.12. ከቤት ጋር ተያይዘው የሚነገሩ ምርቃቶች፤ባህላዊ ዘፈኖችናምሳሌያዊ አነጋገሮች፤

በዚህ ንዑስ ርዕስ ስር ባህላዊ ቤት ሲሰራ፤አልቆ ወደ አዲሱ ቤት ሲገቡ የተለያዩ ምርቃቶችና ዘፈኖች በስራው ላይ የተሳተፉትን ለማበረታታትና ቶሎ እንዲጨርሱ እንዲሁም ባለቤቱን ለማወደስ ይቀርባሉ ፡፡ እነዚህም በአማርኛና በወላይትኛ ቋንቋ ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡

- **ለግድግዳ የሚሆን እንጨት ሲፈልጡ**

ለግድግዳ የሚሆን እንጨት የሚፈልጡ ሰዎችን ለማገዝ የሚመጡና በመንገድ አልፈው የሚሄዱ ሰዎች ጉልበት ይስጣችሁ ፤ በማለት ይመርቃሉ ፡፡ ‘wolqqaa immo! Goday meeshuwa keexetto!’ giidi anjjiyogee ይህም ማለት የግድግዳ እንጨት መፍለጥ አድካሚ ስለሆነ ኃይል ይስጣችሁ በማለት ያበረታታሉ ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ በድካም ስራው ሳይጠናቀቅ እንዳያቆሙ ፈጣሪ ጉልበት ሰጥቷቸው በተሳካ ሁኔታ እንዲጨርሱ የሚገልጽ ነው

‘wolqqaa immo’ giyogee ha qoo’iyo oosoy keehi deexo ooso gidiyo gishshaw godaa qoo’iya asay elle daafiridi izaawaa oosuwa ogiyan olenna mala gujo wolqqaa woykko gida qolqqaa madhdhida Goday immana mala amottiyogaa qonccissees. Ha anjjo qaalaa birshshettaa naa’’u ogiyan be’anaw danddayettees. Koyroy oottiya asay daafuridi harggennaadan woykko qohettennaadan etassi lo’’o amotaa nne qaretaa qonccissiyogaa

- **ግድግዳ ሲፈለጥ**

በባህሉ ግድግዳ ሲፈለጥ ብቻ ሳይሆን ግድግዳ ሲቆምም የምርቃት ሥርአት አለ ፡፡

‘‘keettan mehee kumo!’’ giidi anjjiyogee ubba allaanaappekka shiishshido naqaashshan boxooxiis. Ha keettan mehee kumo giyogee woygiyogee? Giidi shiiqida oyshaw naa’’u ogiyan birshshettay imettiis. Koyruwan keettan mehee kumo giyogaw sitta birshshettay, wuygeppe qol’’o gakkanaashin mehee- booray, mirggoy, maatta miizzay ussay hegaadankka paraynne baquly sippi giidi keetta kumidi de’o giyogaa. Keettan mehee kumo giyogaw ciimma birshettay qassi ha koyro sitta birshshettan qonccida mehee, marccuwa maxoy, shakkuwan baattan kattay, saaxiniyan ordde bullukkoy, ordde irppanee xaaxi waaxin aadhdhida duretettay he kaatta asaassi de’o giyo lo’’o amuwa gidiyogee ubba allaanatuppekka shiishshido naqaashshan qoncciis. ቤቱ በክብት የተሞላ ይሁን ብለው ይመርቃሉ ፡፡ በባህሉ የቤት እንስሳት ከሰው ጋር አብረው ጓዳ ውስጥ ይኖራሉ፡፡ የዚህ ቀጥታ ጥርጉም በቤቱ ጋጣ በሬ፣ወይፈን፣ላም፣ጊደር፣ጥጃ፣በግ፣ፍየል፣ፈረስ፣በቅሎ ይሙላ ማለት ሲሆን ፍካሪያዊ ትርጉሙ የተከማቸ ወይም የተትረፈረፈ ሀብት ንብረት ይስጣችሁ ማለት ነው ፡፡

ከዚህ ጋር ተያይዞ በወላይታ ባህል ቤት ውስጥ ለአባት በሬዎች፣ፈረስና በቅሎ ለእናት ደግሞ የወተት ላሞች መኖር እንዳለባቸው ይታመናል ። ለዚህ ምክንያቱ በሬዎቹ ለእርሻ ስራ በቅሎ ደግሞ ለመጓጓዣ ስለሚያገለግሉ ሲሆን የወተት ላሞቹ ደግሞ ለቤተሰቡ ወተትና የወተት ተዋጽኦ ስለሚያቀርቡ ነው ።

Wolayttan asay miizzaa qachchiyo zazzaluwa essiya asaa ‘‘zazzaluwan maattay ussay komo!’’ giidi anjjees. Maattay ussay kumo giidi anjjiyo gaasoy woykko he anjjuwassi birshshettay Wolaytta wogan zazzaluwan eqqiyay woykko qashettiyay maatta miizzaanne ussaa gidiyo gishshaw maatta miizzaynne ussay kumo giidi anjjees. Hara baggaara qassi wolaytta asay gaaxaataa gaaxaatiya woykko essiya asaa ‘‘keeday, mirggoy, qolchcha paray, ordde baquloy qashetto!’’ giidi anjjiyogee ‘‘keeday, mirggoy, qolchcha paray, ordde baquloy qashetto!’’ giyogee‘‘Wolaytta wogan pengge baggaara keeda booraa, qassi A kaallidi boora kiyanaw biya mirgguwa, keettaaway toggiyo paraa, keettaaway caaniyo baquluwa awdenne wuyge baggaara qacchchyiogee mayzzaa ma’’iya kaallidi yiida wolaytta mayzza woga gidiyo gishshaw gaaxaataa gaaxaatishin yiida ooninne wolytta wogaa erikko keeday, mirggoy, qolchcha paray, ordde baquloy qashetto! gidi anjjees.’’

- **የቤቱ መሰረት ሲቆፈር**

4. ኃይል ይስጣችሁ፤ ብለው ይመርቃሉ ይህም ጉልበት የሚጠይቅ አድካሚ ስራ በመሆኑ በምርቃቱ ጉልበት አግኝተው ስራውን ቶሎ ቶሎ ብለው እንዲጨርሱ ያግዛቸዋል ። ሌላው ከዚሁ ስራ ጋር በተያያዘ የቤቱን ባለቤት በዘፈን ያወድሳሉ ። ha baasuwa baasiya asay banttaw bollay ho’’in oosoy sugettana mala dumma dumma yettata yexxiyogee ha pilggettaa naqaashshaa shiishshiyo wode qoncciis. Yexxiyo yettay he yettaa kessiya izzaw eraadaaninne qaalaa shonggaadan dumma dumma gidanaw danddayiyogeekka qoncciis.

**ለምሳሌ፡-** Hanxxaalo Mana Dalkke

Asaabaa bochchenna xoossa suure

I qassi meeshuwa keexxa minno

Ameeshuwan walxxi giida maxo.

እያሉ ያዜማሉ ። ትርጉሙም የሐንገሎ የመና ልጅ ዳልኬ የሰውን ነገር የማይነካ የመልካም ሰው ተምሳሌት እሱ የተከበረ ባህላዊ ቤት የሰራ ጀግና ነው ። በቤቱ ብዙ ጥሪት ያፈራ ባለ ሀብት ማለት ነው ።

- **ምሰሶ ሲጎተት**

5. **ምሰሶው በትከሻችሁ ይቅለል፤ ብለው ይመርቃሉ ፡፡ ለወላይታ ባህላዊ ቤት የሚሆነው የምሰሶ እንጨት ወፍራም፣ትልቅና ጠንካራ ስለሆነ ከብዷቸው መንገድ ላይ እንዳያቆሙ ይረዳቸዋል ፡፡ ሌላው ከዚህ ጋር ተያይዞ ባህላዊ ዘፈን የሚቀርብ ሲሆን**

Xoossay wolqqa immaana

Immiyo wolqqaa ekkaana

**ይህም ማለት ፈጣሪ ጉልበት ይሰጠናል እኛም የሚሰጠንን እንቀበላለን ማለት ሲሆን ይህንንም ግማሾቹ ፈጣሪ ጉልበት ይሰጠናል ሲሉ ገሚሱ ደግሞ እኛም የሚሰጠንን እንቀበላለን በማለት በቅብብሎሽ እንዲያገኙ ይረዳቸዋል ፡፡** Wolaytta asay darotoo keettaw essiyo tuussaa orddiya dooridi dere asay bolliiddinee kaa''iiddi goochchiyo tuussaa doorees. Hegaa xalaala gidenna wolayyttan ordde tuussaa essiyogee he keettaawaa minotettaa nne qassi I gamma gakkida asa gidiyogaa bessiya wolaytta woga gidiyo gishshataassa. ''tuussay hashiyan deexxoppo!'' giyogee wolayttan tuussay hachchi qanxxettidi hachchi kare gakkidi eqqidi aqanaw bessees giya deretettaa ammanoy de'iyo gishshaw ha tuussay goochchiya asaa hashiyan deexxidi soo gakkennan ogiyan aqqenna mala giidi lo''o amuwa amottiyogan asay ''tuussay hashiyan deexxoppo''! Giidi anjjees. Gidoppe attin wolaytta asay tuussaa goochchidi daroppe amottiyonne yexxiyo qaalay ''xoossay wolqqaa immaana! Immiyo wolqqaa ekkaana! Giya naa''u issoy issuwaara maayettiya qofata gidiyogee naqaashsha immidi ubba kombbe cimatunkka boxooxiis. Xeeraappe dulliya gakkanaashin tuussaa goochchiya asay giddo ginan doommidi sinttawnne guyye naa''aw shaahettidi issi citay ha woosa yettaa (''xoossay wolqqaa immaana!'') denttiyo wode hankoy qassi ha immiyo woosa yettaa (immiyo wolqqaa ekkaana!'') ekkiyogan maayettidi yexxiyo yetta woykko medhdhida godaa woossiyo woosa gaanaw danddayettees.

- **ቤቱ ሳር ሲከደን ደግሞ**

6. **ቤቱ አርጅቶ ፤ሌላ ግንባታ ሲታሰብ ይፍረስ** (Kettay gaariqidi qoletto) **ይህ ምርቃት ሰላምንና ደህንነትን በመመኘት የሚመረቅ ምርቃት ነው ፡፡ በባህሉ እሳት የሚነደውና ምግብ የሚሰናዳው ሳር ቤቱ ውስጥ በመሆኑ አደጋ እንዳያጋጥም በመመኘት ነው ፡፡ሌላው ጥንት በአካባቢው ጠላት ሳር ቤቶችን እሳት በመለኮስ ስለሚያወድም ከእንደዚህ አይነት አደጋ ይሰውራችሁ ወይም ይጠብቃችሁ በማለት መልካም ምኞታቸውን የሚገልጹበት ነው ፡፡ በተጨማሪም ባለቤቶቹ ረጅም እድሜ እንዲኖሩ መመኘትንም ያካትታል ፡፡** gaariqidi baacan

qoletto giyogee daro wode keettay dumma dumma gaasuwan keexxi simmin gam’’ennan taman meetettiyo gaasoy merettidi daafurid nne halchchidi keexido keettaa mela ashshyio gishshaw ‘‘gaariqidi qoletto!’’ giidi anjjiyogee ‘‘baacan qoletto!’’ giyogee tami moopp! Giyogaa qonccissanaassa

- **የእህል ቆጥ ሲሰራ ደግሞ**

7. **የእህል ክምር ይስበረው፤ ብለው ይመርቃሉ ፡፡ ቆጡ ተሰብሮ እንደገና መስራት አድካሚ ቢሆንም የእገሌ ቤት ቆጥ በእህል ተጨናንቆ ተሰበረ ከተባለ የግለሰቡን ታታሪነት የሚያመለክት ሆኖ በአካባቢው እንደ ዝና ስለሚቆጠርም ነው ፡፡ ሌላው እህል በደንብ ይመረትልህ፤የበረከት ቤት(ቤትህ) ይሁንልህ እንደ ማለት ነው ፡፡** Wolaytta asay shakkuwa shakkiya asaa be’ikko ‘‘shakuwa mirqqee mentto!’’ giidi anjjiyogaa naqaashshaa immida ubba kombbe cimatunkka qoncciis. Hegee garaw gezziyawkka haniya anjjo gidiyogaa akeekanaw danddayettees. Wolayttan aaraa asay maldduwa, gaashiya malatiya kattata shakkuwan wottiyo wode gezziya asay qassi banqqaa, gisttiya, gaashiya maltiya kattata mirqqiyara mirqqiyara shakkuwan wottiyo gishshaw ‘‘shakkuwa mirqqee mentto!’’ giyogee gaden zerido kattay keehin daro ayfiya ayfidi shakkuwan mirqqiyara mirqqiyara ehiidi wottiyo wode shakkuwa ‘‘kumidaagaa gido’’ woykko ‘‘shakkuwa deexxidaagaa gido’’ giyo birshshettaa immiyogaa akeekanaw danddayettees. Hara baggaara qassi ‘shakkuwa mirqqee mentto!’’ giyo wode me’’o! Mooretto! Laaletto! Giyogaa gidennaagaa akkeekanw bessees. Ayssi giikko wolaytta wogan asay issoy issuwassi lo’’obaa amotteesppe attin iitabaa amottiyo zuge woykko qanaate haasaya gidennaagee qoncciis. [51]

8. Keettan galoy buraaqo (**ኬታን ጋሎይ ቡራቆ**)፤ Naati mehee kumo(**ናቲ ሜሄ ኩሞ**) Ketta Baacay qolo ፤ Kettay ayyaannoo ፤ Bariya adusso **በወላይታ ባህል ቤቱ ተሰርቶ አልቆ ሰዎቹ እቤት ከገቡ በኋላ ከውጭ የሚመጣ ሰው ይመርቃል ፡፡**

**እያሉ ይመጣሉ፤ሌላው የአካባቢው ሽማግሌዎች በወላይታ ቤቱ ሲሰራም ሆነ አልቆ ወደ ቤቱ በሚገባበት የአካባቢው ሽማግሌዎች ለወጣቶቹ በቤቱ አሰራር ላይ መመሪያ በመስጠት ከማሰራት ባሻገር የምሰሶው እንጨት ወደ ጉድጓድ ሲገባ የምርቃት ስርዓት ያካሂዳሉ ፡፡ ቤቱ አልቆ ሲገቡም ምርቃት ያደርጋሉ ፡፡**

---

[51].ቃለ መጠይቅ፣ደገፉ፣አድማሱ፣ወልደማርያም፣ኢያሱ፣ኢሳያስ እና ባሎሜ ሚያዝያ 2016 ዓ.ም) ፡፡

Ketta Baacay qolo ቤቱ የእሳት አደጋ ወይም ሌላ ነገር(ችግር) አያግኘው፤ አርጅቶ ይፍረስ ፤እሳት አይብላው አርጅቶ በእጅ ይነቀል፤ማለት ነው ፡፡ Kettay ayyaanaa keho-ቤቱ በረከትና ሲሳይ የሞላበት ቤት ይሁን ማለት ነው ፡፡ Shemppuwan qoraphpho- ቤተሰቡ ረጅም እድሜ ይኑረው ማለት ነው፤Keettan galoy buraaqo- ቤት ለእምቦሳ፤Naati mehee kumoቤቱ በሀብትና በልጆች የተሞላ ይሁን ፤Natti daimmo- ማለት ልጆች ይደጉበት፤Kettay ayyaannoo ቤቱ መንፈስ ቅዱስ ይደርበት፤Bariya adusso የቤቱ ባለቤት ረጅም እድሜ ይኑር ማለት ነው (ቃለ መጠይቅ፣አማኑኤል፣07/12/2015ዓ.ም) ፡፡

9. Woraay gasiyo ketta gido ማለት አባትየው አደን ሄዶ የአደን መረጃን ይዞ ይመጣል፡፡ እቤት ውስጥ የአደን፣የጦርነት ውጤቶች የሚቀመጡበት ቤት ይሁን ብለው ይመርቃሉ፡፡ ዎንታን Wonttan doyettiyo ketta gido ከነጋ በኋላ በሰላም የሚከፈት ቤት ይሁን ለሊት ከተከፈተ ሰው በሚያስደነግጥ ወሬ ይዞ መጥቶ ሰው ሞቷል ፡፡ እንዲህ ይላል በማለት የሚነገርበት ሳይሆን ጥሩ ወሬ በቀን የሚነገርበት ቤት ይሁን እንደ ማለት ነው ፡፡

ቤቱ ተሰርቶ ሲጠናቀቅ አባወራው ቤቱ መጠናቀቁን ያረጋግጣል፤የአካባቢው ነዋሪዎችም ያረጋግጣሉ ፡፡ ከዛ በኋላ ቤቴ ልገባ ነው ብሎ ለሚቀርባቸው ሰዎች ይነግራቸዋል፤እቤት መጠነኛ የሆነ ዝግጅት ይደረጋል፤ከዛ በኋላ እቤት ሊሟሉ የሚችሉ መጀመሪያ በእጃቸው የተገኙትን ወይንም በርቀት በሰው ቤት ያሉ ከብቶች(እንስሳት)ይሁኑ ሌሎች ነገሮችን በሙሉ ወደ ቤት አካባቢ ያቀርባሉ፤ ለሚጠራ ህዝብ የሚሆን ጠላ(ፓርሶ) የተባለ ባህላዊ መጠጥ እና ቃሬቦ ይዘጋጃል ፡፡ እንዲሁም የብሔረሰቡ የባህል ምግቦች በሚገባ ይዘጋጃሉ፤ለቤተ ዘመድ ሁሉ ይነገራል ፡፡ ከአይብ፣ከሥጋና ከቅቤ የሚዘጋጅ ሆኖ ከሸክላ የሚሰራ የራሱ ማቅረቢያ እቃ ያለው ሲሆን ሎጎሞ ይባላል ፡፡ ይህም የባህልና የአክብሮት መገለጫ የሆነ ምግብ በመሆኑ እንዲያመጡ ይነገራቸዋል ፡፡ ያመጡትን ምግብ ለሚስትየው ይሰጥዋታል ፡፡ ከዚያ በኋላ ይበላል፤ይጠጣል፤ይዘፈናል (ቃለመጠይቅ፣ኤርሚያስ ጎባና 18/10/2015 ዓ.ም) ፡፡

ቀደም ሲል ቤቱ ማለቁ የተነገራቸው ሰዎች ወደ አዲሱ ቤት በመምጣት ከባለቤቱ ጋር ወደ አዲሱ ቤት እየገቡ «ልጆች ይጫወቱበት፣በረከት ይሙላበት» በማለት የተለያዩ ምርቃቶችን ይመርቃሉ ፡፡ አቅም ያላቸው ደስታቸውን ለመግለጽ ከብት በማረድ መጠነኛ የሆነ መስተንግዶ ያደርጋሉ ወይም ደግሞ የባህል ምግቦች አዘጋጅተው ከኔ ጋር አመስግኑ ይላሉ ፡፡ ከብት አርደው ደም የሚያፈሱት ከአምልኮ ጋር በተገናኘ ሲሆን ይህንንም ሥርአት ከወደፊት ደህንነታቸው ጋር ያገናኙታል፤ ያን ደም ካደረጉ በኋላ እያንዳንዳቸው በግንባራቸው ላይ

ይቀባሉ፤ይህን ስርዓት አንዳንዶቹ በምስጢር የሚያደርጉበት ሁኔታ አለ ፡፡ በመጨረሻም ቅርብ የሆኑ ሰዎች እየበሉ፤ እየጠጡ፤እየጨፈሩ ያድራሉ ፡፡ ከዚያ በነጋታው ወደየቤታቸው ይሄዳሉ

ቤቱ ረጅም እድሜ እንዲኖረው ሲፈለግ ምርቃቱ ጤቱ(መቶ) ፤መቶ ዓመት ኑር (ጤቱ ላይታ ዱአ) ይባላል፤ መቶ ዓመት ኑር የሚለው መቶ ቁጥርን ለመግለጽ ሳይሆን ዘላለማዊ ህይወትን እንደ መመኘት፤ ወሰን የሌለው የሆነ ነገር እንዲያገኙ ያለውን ምኞት መግለጫ ነው፤ጤቶ የሚለው ትልቅ ምርቃት ነው ፡፡ ከብት በጋጥ ላይ ቆሞ የሆነ ድምጽ ሲያሰማ ጤታ ይላል፤መቶ የሚለው ፍጹም አገላለጽ ተደርጎ ይወስዳል ፡፡ በሬ የሚጮህ ከሆነ ድምጽ ሲያሰማ ጤታ ይለዋል ፡፡ ይህም ተባረክ እንደማለት ነው፤በባህሉ ጤታ የሚለው ቃል እንደ ትልቅ ቡራኬ ተደርጎ ነው የሚወሰደው (ቃለመጠይቅ፣ወልደማርያም፣03/10/2015ዓ.ም) ፡፡

ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት በወላይታ ባህል አንድ ሰው ረጅም አመት ኑር ተብሎ ሲመረቅ ጤቱ(መቶ) ዓመት ኑር ይባላል፤መቶ ቁጥርን ለመግለጽ ሳይሆን ዘላለማዊ ህይወትን እንደ መመኘት ሲሆን ጤቶ የሚለው ከሙሉነት ጋር የተያያዘ ነው ፡፡ ጤታ የሚለውን ምርቃት ህዝቡ እንደ ትልቅ በረከት ይቆጥረዋል ፡፡

በወላይታ ባህል ከቤት ጋርና ከቤቱ ስራ ጋር ተያይዘው የሚቀርቡ ምሳሌያዊ አነጋገሮች የሚገኙ ሲሆን እነዚህም በወላይትኛ እና በአማርኛ ቋንቋ እንደሚከተለው ቀርበዋል፡-

1. Pengekoinne santtiyakonne gakiyode hokises

Miishshi kiissen xaykko oossikka wolqqi baawa giyogaa. Hara baggaara qassikka penggiya geliya uray hokkana xaykko pengge goccan Dom"ettees. Hegeekka qassi yootiyobay hookkana xaykko iita wodiyaka pinnanawu deexxees giyogaa.

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚነግረን ኪሳችን ባዶ ሲሆን ስለ ማንኛውም ጉዳይ ብናወራ ተቀባይነትን ስለማናገኝ በራስ መተማመናችንን እናጣለን በሌላ በኩል ደግሞ በሩ ጋር ሲደረስ ወደ ቤት አጎንብሶ ካልተገባ ማንም መገጨቱ አይቀርም ፡፡ ሌላው በር ክብር ስለሆነ እጅ እንነሳለን፤ በር መግቢያ ነው፤ በር ተስፋ ነው ፡፡ ይሁንና አጎንብሶ የማይንቀሳቀስ ሁሉ ወደ ተስፋው መግባትም ሆነ መሻገር የማይችል መሆኑን የሚገልጽ ሲሆን ካላጎነበስን ክፉውን ጊዜ አንሻገርም፤ በር አከባቢ ስንደርስም ዝቅ ካላልን መግባት እንደማይቻል የሚያስረዳ ነው "Penggiyakonne santtiyakonne gakkiyode hokissees" geetettees! በበር ስገባ የማያጎነብስ ሰው የለም ፤ ስለገንዘብ ሲነሳ እጅ የማይሰጥ ሰው የለም እንደ ማለት ነው ፡፡

5. Karri baynay kana ፡ kawoy baynay kayso.

Kanay ossoo biikokka di aggiyo gishawu kanawu kaarri baawa. Hara baggaara qassi kaysoykka taani ha biitta asa woykko hini biitta asa giidi caaqqenna gishawu kaysuwawu kawoy baawa geettees.

ከዚህ የወላይታ ምሳሌያዊ ንግግር የምንረዳው ነገር  ውሻ በየሄደበት ሲመቸው ዝም ብሎ ጠግቦ በበላበት ስለሚኖር የባለቤቱን ቤት ይረሳል ፤ "እከሌ አሳድጎኛል ብሎ ወደ ኋላ አይመለስም ፤ በዚህም ምክንያት"Kaarri baynnay kana" ይባላል ፤ በሌላ በኩል ደግሞ ሌባ የትም ሄዶ ቢሰርቅና ቢያዝ በራሱ የግዛት ወሰን ስለማይመካ  ሲመታ "እኔ የዚህ ወይም የዚያ ሀገር ዜጋ ነኝ" ብሎ ስለማይምል ሌባ ንጉሥ የለውም ይባላል ፡፡

6. Ketta bachaweka hoollaa kettaw kafuwaa kettaweka hoollaa.

Wolayttan keettawu keehi gita birshshettay diyogaa yootees. Datta baachchaykka awaappe, iraappe, meeguwaappe, danuwappe woykko iitaappe qottidi ashshi ekkees. Hegaa gishawu keetti darobaa oyqiis. Kafo keettaykka darobaappe kafota ashshiyo gishawu kari erettenna giyogaa.

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በወላይታ ባህል ውስጥ ቤት ብዙ ትርጉም እንዳለው የሚያሳይ ነው ፡፡ የሸማኔ ጎጆ ራሱ ከፀሐይ፣ ከዝናብ ፣ ከብርድ፣ ከአደጋ ወይም ከክፉ ነገር ሸፍኖ ያተርፋል ፡፡ ሌላው ቤት የወፍ ጎጆ ራሱ ወፎችን ጋርዶ ከብዙ ነገር  የሚጠብቃቸው ቤት ነውና "Keettan baachchawuka hoola; Keettan kafuwaa keettawukka hoola geettees." ይላሉ፡፡የሰው  ልጆች መኖሪያ የሆነው ቤትም ከፍ ያለ ጠቀሜታ ያለው ሆኖ ሰዎችን ከተፈጥሮና ሌሎች አደጋዎች ይጋርዳል በማለት ቤት ሰፋ ያለ ትርጓሜ መያዙን ያሳያል ፡፡

7. Keettaa Xooiyaa soo gelida asi demmees.

Haakki eqqin aybikka erettenna gishawu ayne shiiqi xeelliko lo"o giyogaa. Haahuwan eqqin pirddawu ushshachchenna gaanaasa.

የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር መልእክት ማንኛውንም ጉዳይ ቀረብ ብሎ መመልከት ለብዙ ነገሮች ጥቅም አለው ማለት ሲሆን ሩቅ ቆመው ቢፈርዱ ለየትኛውም ነገር የሚሰጠው ትርጉም አሉታዊ ጎን እንዳለው የሚያሳይ እንደሆነ ነው ፡፡ ሌላው ቤትንም ከውጪ አይቶ ከመፍረድ ቤት ውስጥ ገብቶ ማየቱ የተሻለ እንደሆነ የሚገልጽ ሆኖ ሰውንም ከውጭ ሆኖ በእይታ ብቻ መፍረድ አላስፈላጊ እንደሆነም ያመላክታል ፡፡

8. O keettee giissiyay uuttaa, O nae giissiyay maayuwa.

Aybikka bawu bessiyaba kunttin puulattees giyogaa. Uutti lo"idi tokkettido keettaa asay eqqidi xeellees. He keettaawaakka hayyannaa giidi nashsheessinne xoqqu oottees. Ubba

keettaaway hayqqinkka a duufuwaara ubbaa sabissees giyogaa. Hara baggaara qassi loytti maayikko ay assikka ayyiyo gishawu maayettaa giigissana bessees gaanaasa.

**የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክት የትኛውም ነገር የራሱን መስፈርት አሟልቶ ሲገኝ ያምራል ለማለት ሲሆን በደጁ በጥሩ ሁኔታ እንሰት የተተከለበትን ቤት ሰው ተመልክቶ "ይህ የማን ቤት ነው?" ይላል ። በዚህም ለባለቤቱ ክብርና ከፍ ያለ ቦታ ይሰጠዋል ። ሌላው ጠንካራ አርሶ አደር እንደሆነ የሚነገርለት ሰው በህይወት ባይኖርም እንኳን ስሙ ይታወሳል ። ከዚህ በተጨማሪ አለባበሳችን ያማረ ከሆነ "እሱ የማ ልጅ ነው? እሷስ የማን ነች?" ይባላል ፤ ልብስ ሰውን በጣም ይቀይራል የሚል መልእክት አለው ።**

9. Keettaa karaa gallassi daddeettees, yohuwaa karaa qammi daddettees.
   Keettaa kaaraa gallassi daddiyogee ha dadettiidi diya kaaraa ogiyawaykka aadhdhidi bari kushshiya wotto giyogaa gidishi yohuwaa qammi daddiyogee xuuray daridi kare laalettoppo giyogaa.

**አዲስ ቤት የሚሠራው በኅብረትና በቀን ስለሆነ ለደቦ የተጋበዘ እና መንገደኛውም** "Keettan mehee kumo!" **ብሎ መንፈሳዊ ትርጉም አዘል ምርቃት ይመርቃል ። በዚህም በረከት አንድነት፣ሲሳይ ብሎም የወደፊት መልካም ተስፋ ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ የወላይታ ባህላዊ ቤት ጣሪያ ቀን ቀን የሚሰራ ሲሆን** "Yohuwaa kaaraa qammi daddeettees" **ይህም ማለት በቤተሰብ ብሎም በማንኛውም ቡድን መካከል አለመግባባት ወይም ቅራኔ ካለ ቀን ሳይሆን ማታ ማታ ሽማግሌዎች፤በአካባቢው የተከበሩ ሰዎች በተፈጠረው ችግር ከፍ ወዳለ ደረጃ ደርሶ ለሰዎች መሳለቂያ እንዳያደርጋቸው ማታ ከ12 ሰአት በኋላ ተሰብስበው አለመግባባቶችን ይፈታሉ ።ሰው ሳይሰማችሁ ቶሎ ብላችሁ ታረቁ ማለት ነው ።**

10. Keettawu penggee attumaa asawu siiree xeelettees.
    Keettawu penggee keehi sitta gidikonne puula gidikko geliya ordde kaccaama boorawu, parawunne gamma gakkida asawukka bonchcho giyogaa. "Pengge giidi" yettan yeggiyogeekka issi gufana penggiya gidiina gidenna. Hara xeelan qassikka attuma asawu siiree eqa gidiko machchiya gelanawunne appe naata yelanawu dossawusu. Attuma asawu siiree tinbbicciicca gidikko garssaykka tillena giidi oonne bari kahan qoppennan aggenna. Yaatiyo gishawu "Keettawu penggee attuma asawu siiree xeelettees" yaagoos.

አንድ ሰው የወላይታን ባህላዊ ቤት በር በማይረቡ ቁሶች ሰካክቶ የተዛነፈ በር ከሠራ በሩን ቀጥ አድርገህ በአግባቡ አልሰራህም ተብሎ በብሔረሰቡ ይሰደባል፤ ይናቃል። ቤት ሠራሁ ወይም ገነባሁ ብሎም አያወራም ። ስለሆነም ግርማ-ሞገስ ያለው በር ሲበጅ ለፈረስ፣ ለድልብ ከብት፣ ለጥቁር እንግዳ፣ ለዕድር ብሎም ለተለያዩ ጉዳዮች ሰፊ መግቢያ ክብርም ስለሆነ"Keettawu penggee xeelettees" ይላሉ ። " በሌላ በኩል ደግሞ ወንድ ልጅ አፍንጫው ቀጥ ያለ ከሆነ ሚስት ለማግባት አይቸገርም፤ የወንድ ልጅ አፍንጫ ጎራዳ ከሆነ ውስጣዊ ማንነቱም አይረባም ብለው ስለሚያምኑ የቤቱ በርም ሆነ የወንድ አፍንጫ ቀጥ ያለ ያልተንጋደደ መሆኑ ፋይዳውን ከፍ ያደርጋል ።

11. Keetti maccaasi baynnan zazaloy miizzi baynnan loenna.

Macca asay issi keettaa puulatettawu keehi koyettoosona. Hegaa gidiyo gishawu keettay sonkka karen qitattiyode "Ha keettan macca assi baaweeyye?" geetettees. Macca asay ubbabawukka keehippe lo"o. Hara baggaara qassi zaddaloy miizzi xaykko dara malatees. He miizzi baynna zaddaloy qanggetta malatidi keettaa asaa ubbankka pokkodan xeelettees.

በዚህ ምሳሌያዊ ንግግር የሚተላለፈው ቁልፍ መልዕክት ሚስቶች ወይም ሴቶች ለአንድ ቤት ውበት ወሳኝ መሆናቸውን ለማሳየት ሲሆን ቤቱ ከውስጥም ሆነ ከውጪ ሲቆሽሽ "እዚህ ቤት ሴት ልጅ የለችም እንዴ?" ይባላል ። በባህሉ ሴቶች ለብዙ ነገሮች ግንባር ቀደም ሆነው ይታያሉ ። በሌላ ምሳሌያዊ ንግግር "Macci maqqin maati mokkenna!" ይላሉ። በዚህ የተላለፈው መልዕክት ሴት ልጅ ለመነሳትም ሆነ ለመውደቅ ምክንያት ልትሆን ትችላለች ለማለት ሲሆን በሌላ በኩል ደግሞ ቤት ውስጥ ከብት ከሌለ የከብቶች በረት ብቻውን መኖሩ ጥሩ እንዳልሆነ በዚህም በረት ያለ ከብት እንደ እርግማንና ነውር ይቆጠራል ለማለት ነው ። ሌላው በጸሎት ጊዜ ራሱ "miizzay gaaxaatan adabo" ከብቶች በበረት ይብዛላችሁ ካሉ ትልቅ ጸሎት ነው ።

12. Keettay kehiin santtay aattees.

Lo"iichchikko ubba yaa bin ha yin duussi oyssa kiyyi aggees. Miyobi uyyiyobi kummi uttidaba gidikko gadden santtay aattees. Hara baggaara qassi mettin ubba bosan yosan meto gididi "ha duussaappe tana shodda!" giissees.

ይህ ምሳሌያዊ ንግግር በወላይታዎች ዘንድ ዘወትር የሚነገር ሲሆን ይህም፤ የሆነ ጊዜ መልካም የሆነ አንድ ነገር ከተሳካ ሁሉም ነገር መልካም ይሆናል የሚል መልዕክት ይዟል ፡፡ ሌላው እቤት ውስጥ ጥሩ እራት ከተዘጋጀ አባት ከገበያ የሚያምር ጮማ ሥጋ ይዞ ይመጣል፤ በጓሮ ደግሞ ድንች ከተኮተኮተ ጎመን ይጎመራል ፣ማሽላ፣ ስንዴና ገብስ ይሞላል በደንብ ያፈራል ይላሉ ፡፡ ነገር ግን አንድ ጊዜ በአንድ በኩል ክፉ ዕጣ ፈንታ ካጋጠመ ሌሎች ነገሮችም ተያይዘው ይበላሻሉ፤ይተረማመሳሉ አይሳኩም የሚል ትርጉም ይዟል ፡፡ ድንገት ምጣድ ቢሰበር ቦርዴው የያዘው ጋን ይሰበራል "iitin iitees aayyiyo aawaa worees, kehidi kehees giyan qoccan wodhdhees" ይላሉ ፡፡

13. Cimay baynna deree, kuway baynna karee.

Cimay baynna deree issi cabboy kiyikko issoy issuwaa koxxiyan gaallokkiidi gonni gaaman eqqees. Cimay xaykko machchiya azzinaara duukku. Shooroy shooruwaara deenna. Hegaadankka kuwi baynna karen cimi uttenna. Ubbabayka ha kuwi bayna kereeni woppenna ya-ya haakkees. He kuwi baynna keettaa metuwaa pagalanawuka cimay shoorossoo biidi kuwi diyosan uttees. Hagee ubbaykka anjjuwaara gaytti uttiis.

የዚህ ምሳሌያዊ ንግግር መልዕክት የአንድ ሀገር ሕዝብ ሽማግሌ ከሌለው እርስ በእርሱ ግጭት ውስጥ በመግባት ወደ መጠፋፋት ሊያመራ ይችላል ፡፡ ስለዚህም መክሮና ገስጾ ተው ተመለስ ለማለትም ሽማግሌ በጣም አስፈላጊ እንደሆነ በዚህም ሽማግሌ ከሌለ ባል ከሚስቱ ጋር ግጭት ውስጥ ቢገባ አማካሪ የለውም ፡፡ በሌላ ጎኑ ደግሞ ጥላ የሌለበት ቤት ወይም ደጃፍ የሆነ ችግር ቢከሰት ያንን ፀብ ለማብረድ ቁጭ ብለው ለመወያየት የሚሆን ጥላ አስፈላጊ ስለሆነ "kuway baynna karee" ተብሎ ይተቻል ፡፡ ጥላ የሌለበት ቤት እንደ እርግማን ምልክት ወይም በረከት የሌለው ፤ እረፍት የሌለው ቤት እንደሆነ ተደርጎ ስለሚታይ ለጥላ የሚሆን ተክል የሌለው ቤት በባህሉ ትዝብት ውስጥ ይገባል ከዚህ የተነሳ ጥላ በሌለው ቤት ችግር(ክፍተት) ከተፈጠረ ሽማግሌዎች ጎረቤት ሄደው ይቀመጣሉ ፡፡ ስለሆነም በደጃፉ የጥላ አለመኖር የግለሰቡን የውስጥ ገመና(ሚስጥር) ሌሎች የውጭ ሰዎች እንዲያውቁ ያደርጋል፡፡ ሌላው ምሳሌያዊ ንግግሩ በሙሉ ከበረከት ጋር ተያይዞ ስለሚነገር ወላይታዎች "Cimay baynna deree, kuway baynna karee" ካሉ "ሽማግሌ የሌለው ሕዝብ ፤ ጥላ የሌለው ደጃፍ" በውስጡ ብዙ ነገር ይዟል (ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ ገጃቦ፣04/11/2016ዓ.ም) ፡፡

## 6.13. የወላይታ ብሔረሰብ የባህላዊ ቤት ሙያተኞች እና የቤት አሰራር እውቀት ተስተላልፎ

ባህላዊ ቤትን የሚሰሩ ባለሙያዎች በህዝቡ የተከበሩ ናቸው ። በወላይታ ባህል ቤት ሲሰራ ሁሉም የራሳቸው ሙያ አላቸው፤ሳሩን እንጨቱን የማይነኩ ጠና ያሉ አባቶች(ካይማ) የሚባሉ አሉ የሚያጠፋውን የሚገስጹ፤መመሪያ የሚሰጡና እውቀቱ በአግባቡ እንዲተላለፍ የሚያደርጉ ናቸው ። እነዚህ አባቶችም ክብር ይሰጣቸዋል፤ሁሉም እንደሙያቸው የተከበሩና እንክብካቤ የሚደረግላቸው ናቸው ። ለአብነት ቤት ሲሰራ ጣሪያ የሚሰሩት ሰዎች ሙያዊና ውድ ስለሆኑ ይከበራሉ፤የተለየ እንክብካቤም ይደረግላቸዋል ። ወላይታ ውስጥ በፍስክ የሚበሉ(ማልኡዋ) በአዘቦት የሚበሉ(ማሱካ) የሚባሉ ምግቦች አሉ፤ ጣሪያ ለሚሰሩ ሰዎች እነዚህ ለየት ያሉ ምግቦች ይዘጋጅላቸዋል።[52]

እንደ ማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ እዉነታ ከሆነ ሰዎች እርስ በርሳቸው በምልከታ እና በማስመሰል ሊማሩ ይችላሉ ። የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳባዊያን እንደሚናገሩት ሰዎች በመመልከት ብቻ መማር ይችላሉ (Bandura,1965) በወላይታ ብሔረሰብ የቤት አሰራር እውቀቱ አባቶች ወንዶች ልጆችን አስከትለው በመሄድ ቀለል ያሉ ስራዎችን እንዲሰሩ በማድረግና በማሳየት እንዲለምዱ ያደርጓቸዋል ። አባወራው ለቤቱ ስራ ሲሄድ ትንንሽ ወንዶች ልጆችን አስከትሎ ይሄዳል፤ ወንዶች ብቻ እንዲለምዱ የተፈለገበት ምክንያት በባህሉ ሴቶች ቤት እንዲሰሩ ስለማይፈቀድ ነው ። ተከትለው የሄዱት ልጆችም ዝም ብለው አይቀመጡም ይህ ሀሳብ በንድፈ ሀሳብ ሲቃኝ በማህበራዊ ግንባታ ንድፈሃሳብ እንደተገለጸው ሥርዓተ-ፆታዊ ግንዛቤ ከስነህይወታዊ ይልቅ ማህበራዊ ፍችና ስምምነቶች ላይ ስለሚያተኩር ማህበራዊ ህገ ደንብ አለው። እናም ሰዎች ወንድነትንና ሴትነትን ሲማሩና ሲቀበሉ በዛ ህግ እየታረሙ እንደሆነ ተገልጿል። እንደዚሁ ሁሉ የማህበራዊ አስተምህሮ ንድፈ ሃሳብ /Social Learning theory/ም የፆታዊ ልዩነት ምንጩ በማህበረሰቡ ውስጥ ያሉ ፆታ ለይ ተግባራትና ህገደንቦች ናቸው ብሎ ያምናል ። ይኸውም ማበረታቻዎችና ቅጣቶች ልጆችን ወደ ሚመስላቸው ፆታዊ ምድብ እንዲሄዱ ይገፋፏቸዋል ። ከዚህም ባለፈ እያዩትና እየተገበሩት የሚማሩበት ወኪል/ሞዴልም ይቀርብላቸዋል (Bandura, 2006) ፡፡

---

[52].ቃለ መጠይቅ፣ አቶ ታደሰና አቶ ኢያሱ፣11/10/2016 ዓ.ም ።

ልጆች ለቤቱ ማሰሪያ የሚሆን ውሃ ውስጥ ተጨምሮ የተቀመጠውን ወፍቾ በማምጣት የሚያግዙ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም መለስተኛ ማገሮችን ማምጣትም የእነሱ ድርሻ ነው ፡፡ ህጻናት ወላጆቻቸውን ተከትለው ሄደው ወፍቾ ከማምጣት ባሻገር ቤቱ እንዴት እንደሚሰራ ያያሉ ፡፡ እነዚህ ቀደም ብለው ከተጠቀሱት ልጆች የተለዩ ናቸው ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወላጆችን ተከትለው የሚመጡ ህጻናት ያሉ ሲሆን እነዚህም ማሱዋ (Masuwa) ይባላሉ፡፡

ማሱዋ የሚባሉት ህጻናት ቤት ወደሚሰራበት ወላጆችን ተከትለው በመሄድ የሚመገቡ ለማለት ሲሆን ማሱዋ የተባሉት ሳይጠሩ መጥተው በማገዝ ይበላሉ፤ ይጠጣሉ ፡፡ ህጻናት ለአካለ መጠን እስከሚደርሱ ድረስ ወላጆቻቸውን ተከትለው በመምጣት በሰንበሌጥ አጨዳ፣በግድግዳ ቆረጣ ወቅት ሰው እንዴት እንደሚሰራ ያያሉ፤ይለምዳሉ ፡፡ ወላጆችም ሆኑ ወጣቶች ቤት እንዴት እንደሚሰራ፤እንዲያዩ እያደረጉ የቤት አሰራር ጥበቡን ለትውልድ ያስተላልፋሉ ማለት ነው ፡፡ አባት ወደ ቤቱ ስራ ሲሄድ ልጆችን አስከትሎ ይሄዳል ፡፡ ልጆችም ወፍቾና አነስ ያሉ ማገሮችን በማምጣት የሚያግዙ ሲሆን በዚህም የቤት አሰራሩን ይለምዳሉ ፡፡

የቤት ስራ እውቀቱ መተላለፊያ መንገዶችን በተመለከተ አቶ አማኑኤል አይዴ ሲገልጹ እውቀቱ ከህዝቡ(ከሽማግሌዎች) ወደ ወጣቶች ይተላለፋል፤ሽማግሌዎች መሪ ሆነው ያሰራሉ፤ጣሪያው ሲሰራም እንዲህ አድርጉ እያሉ ለወጣቶቹ መመሪያ ይሰጣሉ ፡፡ በዚህ ሁኔታ ነው የእውቀት ሽግግሩ የሚደረገው ፤ባለሙያዎቹ ውስን ናቸው ፡፡ ለምሳሌ ጣሪያውን የሚሰሩ ባለሙያዎች ስራውን የሚችሉ ሆነው ጣሪያውን በጣም አስጊጠው የሚሰሩ ናቸው ፡፡ ቀደም ሲል ከሌሎች አካባቢዎች ከርቀትም ቢሆን ሙያውን የተማሩና የተካኑ መሆናቸው ሲሆን ሌላው ቀርቶ ምሰሶውን ቆርጠውና አስተካክለው ጉበን ወይም መቃን ለማዘጋጀት ፤መዝጊያ ለማዘጋጀት አስቀድመው ከሌላ ቦታ ከጥንቶቹ ሽማግሌ ሰዎች በማየት እውቀት ያዳበሩ ሰዎች ናቸው፡፡

ሌላው ሙያውንም ቢሆን አንዱ ከሌላው ይማራል፤እንዲህ አድርገህ ስራ ተብሎ በአንድ ሽማግሌ ወይም በአንድ አዋቂ ሰው ከተነገረው ሌላኛው ይቀበላል ፡፡ ስለዚህ በዚህ መልክ ሙያውም ከጥንቶቹ ለአሁኖቹ፤ከአሁኖቹ ለወደፊቶቹ እንዲተላለፍ እየተደረገ የቆየው በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ነው፡፡ አባት ለልጅ እነዚህ ግብአቶች እንደዚህ ናቸው እነዚህን ደግሞ ተንከባክበህ ያዛቸው፤ ከዚህ ቦታ ይገኛሉ፤ በማለት ግብአቶቹ የሚገኙበትን ቦታ ይጠቁማል ፡፡ እውቀቱ ያለው አባቱ ለልጁ እያሳየ በእንደዚህ አይነት መንገድ እያስተላለፈ ልጆች እንደዚህ ነው በዚህ አይነት ድካም ነው ያፈራሁት ተንከባከቡ፤ እውቀቱም እንደዚህ ነው እያሉ ደሞ በዚህ ስራ እውቀት ያላቸው ግለሰቦች እነዚህ ናቸው ብለው እከሌን ከዚህ አካባቢ ሄጄ አምጥቼ

አሰርችያለሁ፤ እኔም ደግሞ ካለኝ እውቀት ጋር አጣምሬ እንደዚህ አድርግያለሁ በማለት ለልጃቸው፤ለልጅ ልጃቸው ፤እውቀቱን ያስተላልፋሉ ፡፡[53]

የቀረቡት መረጃዎች በማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሐሳብ ሲቃኙ ሶስት ፅንሰ-ሀሳቦች አሉ ፡፡ በመጀመሪያ ሰዎች በመመልከት መማር ይችላሉ ፡፡ ይህም የእይታ ትምህርት በመባል ይታወቃል፤በሁለተኛ ደረጃ የአዕምሮ ሁኔታዎች ለመማር አስፈላጊ ነገሮች ሲሆኑ እሱም እንደ ውስጣዊ ማጠናከሪያ ተብሎም ይጠራል ብለዋል ፡፡

ከላይ ከቀረበው ይዘት መረዳት እንደተቻለው የወላይታ ባህላዊ ቤት አሰራር እውቀት ከሽማግሌዎች ወደ ወጣቶች ይተላለፋል፤ የመተላለፊያ መንገዱም ሽማግሌዎች መሪ ሆነው እንዲህ አድርጉ ብለው ለወጣቶቹ መመሪያ ይሰጣሉ፤በዚህ ሁኔታ ከአንዱ ወደ አንዱ የሚተላለፍ ሲሆን ባህላዊ ቤትን የሚሰሩ ባለሙያዎቹ በቁጥር ውስን ናቸው ፡፡ ይሁንና በአንድ አዋቂ ሰው እንዲህ ስራ ተብሎ ከተነገረው ሌላኛው ተቀብሎ ይተገብራል፤የሚተገብር ሲሆን ሙያውም በዚህ መልክ ከአባት ወደ ልጅ እነዚህ ግብአቶች እንደዚህ ናቸው ፡፡ እነዚህን ደግሞ ተንከባክበህ ያዛቸው ፡፡ ከዚህ ቦታ ይገኛሉ በማለት ግብአቶቹ የሚገኙበትን ቦታ እየጠቆመ አባት ለልጁ ያስተላልፋል ፡፡

የኪንዶ ዲዳዬ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኦልኬ ታንቱ የቤት አሰራርን የለመዱበትን መንገድ ሲገልጹ ቤት መስራት የለመድኩት ልጅ ሆኜ አባቴ ቤት በሚሰራበት ቦታ ይዞኝ በመሄድ ቤቱ ሲሰራ ያሳየኝ ስለነበር ሲሆን ከዚህ በተጨማሪ እሱም ብዙ ነገሮችን እየነገረኝ ስላሳደገኝ ነው ፡፡ ሌላው በአካባቢው ቤት በመስራት በጉብዝናቸው የሚታወቁ ሰዎችን አስተዋውቆኝ ስለነበር ከነሱም ብዙ ነገሮችን ተምርያለሁ፤እኔም አባቴ ያስተማረኝን ሁሉ ለልጆቼ አስተላልፍያለሁ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ይሄ ባህላዊ ቤት ከማንነታቸው ጋር የተገናኘ በመሆኑ እነሱም ባህሉን ጠብቀው ለልጆቻቸው በማስተላለፍ ባህሉ እንዲቀጥል ስለሚፈልጉ ነው ፡፡[54]

ከላይ የቀረበው መረጃ ከማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ እሳቤ አንጻር ሲቃኝ ሰዎች እርስ በርሳቸው በምልከታ የመማር ወይም የመልመድ ትምህርት በማንኛውም የዕድሜ ክልል ውስጥ ሊከናወን የሚችል ሆኖ በዚሁ ውስጥም የእውቀት ሽግግር እንደሚካሄድ ተገልጿል (Bandura 1965)፡፡

[53].ቃለ መጠይቅ፣ጳውሎስ፣15/09/2014ዓ.ም ፡፡
[54] ቃለ መጠይቅ፣ህዳር 10/2015ዓ.ም ፡፡

### 6.14. ድህረ ቤት ሥራ ክዋኔዎች

በወላይታ ባህል ቤቱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የተለያዩ የአጥርና የጓሮ አትክልቶች ይተከላሉ፡፡

ድህረ ቤት ክንዋኔ በየትኛውም የወላይታ ህዝብ ዘንድ በትኩረት የሚደረግ በመሆኑ ልክ እንደ ቤቱ "የእከሌ ቤት እንሰትን አያችሁት" ይባላል፡፡ ቤቱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የጓሮ አትክልቶች ይተከላሉ፤አጥር ይታጠራል፡፡ አንድ ሰው ቤት አለው ሲባል ጓሮ አለው ማለት ነው፤የተለያዩ አትክልትና አዝዕርት መትከያ ከቤቱ ጀርባ ትልልቅ ዛፎች፤እንሰቶች ይተከላሉ፡፡ በተጨማሪ የጓሮ አትክልት በወላይታ ባህል መሰረት ሴቶች የሚተክሏቸው ተክሎች አሉ፤ወንዶች የሚተክሏቸው ተክሎች አሉ፤በጋራም የሚተክሏቸው ተክሎች አሉ፤ለምሳሌ እንሰት የጋራ ነው፤እንሰትን በመትከል ትልቁን ድርሻ የሚወስዱት ወንዶች ናቸው፤ እንሰቱን በመንከባከብ ፤መጨረሻ ላይ እንሰቱን ለምግብነት የሚያዘጋጁት ሴቶች ናቸው፤የቡና ቅጠል መድሐኒትን የሚተክሉትና የሚንከባከቡት ሴቶች ናቸው (ቃለ መጠይቅ፣ሲሳይ፣ሶዶ ዙሪያ፣ህዳር12/2015 ዓ.ም)፡፡

**ፎቶ 26፡- የቡና ቅጠል መድሐኒት**




**ምንጭ፡-ህዳር3/2015ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ**

ፎቶ 27፡- በቤቱ ጓሮ፣ከጎንና ከፊት ለፊት የሚተከሉ አትክልቶች












**ምንጭ፡- ሶዶ ዙሪያ፣ግንቦት/10/2015ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ**

**የወላይታ ባህላዊ ቤት አጥር መስሪያ ግብአቶችና ትዕምርቶች በተመለከተ ኢያሱ ገጃቦና ታደሰ ኮይራ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-**

**የወላይታ ባህላዊ ቤት አጥር ቋሚዎች በኮርች ይሰራሉ፤አጥሩ እንደ ጥላ በመሆንና ጎርፍን ለመከላከል ያግዛል፤ ክፍተቱ የሚሞላው ከማሽላና ከቀርከሃ አገዳ ነው፡፡ ዋናው የአጥሩ መግቢያ ላይ ጎልጊያ የሚባል ይዘጋጃል እነዚህ እንጨቶች የተመረጡበት ምክንያት ጸዳቂ በመሆናቸው ሲሆን ይህም የባለቤቱን እድሜ ያበረክታል ተብሎ ይታመናል፤ልጆች በብዛት እንዲወለዱ ያደርጋል፤ለቤተሰብ ጥሩ ገድ ያመጣል ተብሎ ስለሚታመን ነው ፡፡ ሌላው አጥሩ እድሜ እንዲኖረውና ለቤቱ ውበት ስለሚሰጥ ነው (ቃለመጠይቅ፣ሲሳይ፣ሶዶ ዙሪያ፣ህዳር12/2015 ዓ.ም) ፡፡**

**ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያስረዳው የወላይታ ባህላዊ ቤት አጥር ከኮርች፣ከማሽላና ከቀርከሃ አገዳ የሚሰራ ሲሆን እነዚህ እንጨቶች የተመረጡበት ምክንያት ለቤተሰቡ ጥሩ ገድ ያመጣልናል ብዙ ልጆች እንዲወለዱ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታሰብ ነው፡፡**

**በባህሉ በባህላዊ ቤቱ ዙሪያ የሚተከሉና የማይተከሉ ተክሎች ተለይተው ይታወቃሉ፡፡ በወላይታ ባህል በቤት ዙሪያ የተለያዩ ተክሎች ይተከላሉ፡፡ ለምሳሌ ቡና ከቤት የማይርቅ ተክል ነው፤በቤት ዙሪያ ይተከላል፤እንሰት በቤት ዙሪያ ይተከላል፤በወላይታ ከሚታወቁ የጓሮ አትክልቶች የመጀመሪያው ለቅጠል ቡና አገልግሎት የሚውሉ የቅጠል ቡና መድሐኒት**

ተብለው የሚጠሩ ከቅጠል ቡናው ጋር አብረው የሚፈሉ እጽዋት ፤አሪቲ፣ጤናአዳም፣ጠጅሳር፣ እንስላል፣ ድምብላል፣ በሶብላ፣ ጦስኝ ሲሆኑ እነዚህ በወላይትኛና በአማርኛ የሚታወቁ ሲሆኑ በአማርኛ ስማቸው የማይታወቁት ደግሞ ሺለሪያ፣ጉፒያ፣ሀሹንቻ፣የሚባሉ በቤት ዙሪያ የሚተከሉ ሆነው ለእለት እለት አገልግሎት ለምግብነት ይፈለጋሉ፤አንደኛ የቅጠል ቡናው ቅመም ሆነው ያገለግላሉ፤ሁለተኛ ለቅቤ ማንጠሪያነት ያገለግላሉ፤ ሦስተኛ ለእለት ህመም መድሀኒትነት ጥቅም ላይ ይውላሉ፤ለምሳሌ ለሆድ ህመም ሀሪቲ፣ጤናአዳም፣ እነዚህ ከቤቱ አጠገብ የሚገኙ፤ ቤቱን ከበው ይተከላሉ፤ሰውም ሆነ ከብት ቢታመም ለመድሀኒትነት ይውላሉ፤ጤናአዳም ሰው ሲሞት ለማጠብ ያገለግላል (ቃለ መጠይቅ፣ሲሳይ፣ሶዶ ዙሪያ፣ህዳር12/2015ዓ.ም) ።

**ፎቶ 28፡- ቡና እና እንሰት**



***ምንጭ፡-ታህሳስ3/2015ዓ.ም፣በአጥኚዋ የተነሳ***

- ***በወላይታ ባህል በቤቱ ዙሪያ የማይተከሉ ተክሎች***

በወላይታ ባህል ቅንጭብ ቤት አጠገብ አይተከልም፤ ለዚህ ምክንያቱ ሲቀነጠስ ውስጡ ያለው ፈሳሽ አይን ያጠፋል ተብሎ ስለሚታመን ነው። እሾሃማ የሆኑ ዛፎች ወይም ተክሎች ጉዳት ያደርሳሉ ተብለው ስለሚታሰቡ በቤቱ ዙሪያ አይተከሉም። በወላይታ አደገኛ ከሚባሉ እጽዋቶች ዳምቢያ የሚባል ዛፍ አለ፤ይህም ግምብ ሰንጥቆ የመግባት አቅም ያለው ነው፤ይሄ የዛፍ አይነት የትኛውም ሌላ ዛፍ ላይ ከወጣ ያንን ዛፍ ያመነምናል፤ በባህሉ ይህን ዛፍ በተመለከተ ‹‹ደምቤ ዛሬ አሳድረኝ ብሎ ለእንግድነት መጥቶ ጠዋት ውረድ ሲባል ስር ሰዶ ያድራል›› ይላሉ። ሌላው አጥብቀህ ያዝ ለማለት እንደ ደምብ ያዝ ይባላል። ለማገዶነት ሲውልም ሴቶችን ይጎዳል፤ የጤና እክል ያመጣል ተብሎ ስለሚታሰብ በቅርብ እንዲኖር አይደረግም (ቃለ መጠይቅ፣ባሎሜ አንጁሎ፣ህዳር 14/2015 ዓ.ም) ።

የቀረቡት መረጃዎች እንደሚያመለክቱት  በወላይታ ባህል በቤት ዙሪያ የሚተከሉ አትክልቶች ከቤት ስራው ጋር ይገናኛሉ። እነዚህ ከቤቱ አጠገብ የሚገኙ፤ ቤቱን ከበው የሚተከሉት የተለያዩ አትክልቶች ለሰውም ሆነ ከብት  ለመድሀኒትነት ይውላሉ። በተጨማሪም ጎርፍን ለመከላከል ይረዳሉ።

# ምዕራፍ ሰባት

# የወላይታ ባህላዊ ቤት ቅርጽና ተምሳሌታዊ ትርጓሜ የውጭና የውስጥ ገጽታዎች

## 7.1. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ቅርጽ

በዚህ ምዕራፍ የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውጫዊ እና ውስጣዊ ቅርጽ ትርጓሜዎች ቀርበዋል ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ የቤቱ ክብነትና ትርጓሜ፤የክብና የሙሉ ቁጥር እሳቤ በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ውስጥ ፤የባህላዊ ቤት መገንቢያ ግብአቶች፤የቤት አሰራሩ ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ ተገልጸዋል ፡፡ ሌላው የቤት ማስዋቢያ ግብአቶች፤ የባህላዊ ቤት ጉልላት(ጉምቦ) እና የቀለም ምርጫ ትርጓሜዎች ቀጥለው ቀርበዋል ፡፡ እነዚህም ዓላማዎችን መሰረት አድርገው በጽንሰ ሀሳብና በተጠቀሱት ንድፈ ሀሳቦች እንዲሁም ሞዴሎች ተግባራዊ ሆነው መረጃዎች ተተንትነው ቀርበዋል ፡፡

የወላይታ ባህላዊ ቤት ቅርጽን በተመለከተ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ አየለ ሲገልጹ የወላይታ ብሔረሰብ የቤት ቅርጽ ክብ ነው ፡፡ ቤቱ ከውጭ በኩል ሲታይ ሁለት አይነት የሳር አከዳደን አለው ፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ ከላይ እስከ ታች ወጥ በሆነ መልኩ በሳር የተከደነና ከበሩ መግቢያ ጀምሮ ጎን ዙሪያው ድረስ የተከረከመ አከዳደን ያለው ነው ፡፡ ከውጭ ሲታይ እንደ ፀጉር በስርዓት ተከርክሞ የተሰራ ይመስላል (ቃለ መጠይቅ፣13/10/2014ዓ.ም) ፡፡

ከቡድን ሁለት ተወያይ አባላት መካከል አቶ ኢያሱ፣አቶ ወልደማርያምና አቶ አየለ አይዴ የወላይታ ባህላዊ ቤትን ቅርጽ በተመለከተ እንደሚከተለው ያስረዳሉ፡-

የወላይታ ባህላዊ ቤት ክብ ቅርጽ ያለው ሆኖ አከዳደኑ ከምሰሶ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሳር የሚለብስና ከግማሽ ጀምሮ የሚለብስ ነው (ቃለ መጠይቅ፣21/11/2014 ዓ.ም) ፡፡

ፎቶ 29፡- በመሰራት ላይ ያለ የወላይታ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ቅርጽ



ፎቶ 30፡-ያለቀ የወላይታ ባህላዊ ቤት ውጫዊ ገጽታ በምስል




ምንጭ፡-በአጥኚዋና ባህላዊ ቤቱን ባሰራው ባለሙያ አማካይነት ጳጉሜ2/2015ዓ.ም የተዘጋጀ

1.Gumbbuwa -ጉልላት
2.Shidhdhaa-ዋልታ
3.Zaruwa-ቋሚማገ ር
4.Zandidda-ቀጫጬጫ ማገ ር
5.Quruxuwaa-ሳሎንና ጓዳ ማካያ

### 7.2. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ቅርጽና ትርጓሜ

የቤቱ ውስጣዊ ቅርጽ ቤትን ለመለየት(ለመክፈል) በሚያገለግለው Quruxuwaa (ቁሩጡዋ) አማካይነት ሳሎንና ጓዳ በሚል ለሁለት ይለያል ። Quruxuwaa (ቁሩጡዋ) ቤቱን ከመክፈል ባሻገር ለውበት አገልግሎት ይውላል ። ቅርጮው ላይ የተሰቀሉ የዳታ ማቅረቢያ ሻቴ የሚባሉ ትናንሽ ከሸክላ የተሰሩ ክብ ቁሶች፤የተለያዩ ቅሎች፤የምግብ ማቅረቢያ መሶቦች፤የስፌድ እና የወንፊት አይነቶች ወደ ውስጥ ገብቶ ለሚመለከት ሰው ለአይን የሚማርኩ ሲሆን ከዚህ በተጨማሪም ቤቱ ውስጥ የጎደለ ነገር እንደሌለ የሚገልጹ መሆናቸውን (ቃለ መጠይቅ፣ 10/10/14፣ሀይሌ ሀርጎ) ።

የቀረበው መረጃ በስነፍቺ ንድፈ ሀሳብ ሲቃኝ በቁስ አካል፣ በአዕምሮ እና በባህል መሃል በሚካሄድ የእርስ በእርስ መስተጋብር ውስጥ ነው። ቁስ አካል የተለያዩ ትዕምርቶች የሚመነጩበት ተጨባጩ አካል ነው። አዕምሮ ደግሞ የሰው ልጅ ውጪያዊ ዓለምን ከውስጣዊ እሳቤ ጋር በማገናኘት አካባቢውንና ዓለምን ይገነዘባል። የፎክሎር ባለሙያዎችም በማህበረሰቡ የተወከሉ ባህላዊ ተግባራትንና ቁሶችን በማጤን የትዕምርቶችን ምንነት፣ትርጓሜ እና ፍካሬ እንደሚመረምሩ ተጠቁሟል (Danesi, 2004: P.18) ። ሌላው ከዚህ በተጨማሪ ከSchlereth የመተንተኛ ሞዴሎች ሲቃኝ በታሪካዊ ጥበብ አመልካች ቁሶች በሚጠኑበት ጊዜ የሚሰጡት ጠቀሜታ ላይ ትኩረት ማድረግ ሳይሆን በቁሶቹ ላይ ያለውን ጥበባዊነት የምናሳይበት ነው ። ስለዚህም ጥበባዊ ውጤቶች ግንዛቤ ውስጥ ገብተው ቅርጽ፣ቀለምና ጥንካሬ በአግባቡ መግለጽ ታሪካዊ ጥበብ አመልካችነታቸውን ያሳያል ። ተምሳሌታዊ በቁሳዊ ባህል ጥናት ውስጥ ቁሶቹ ዕለት ዕለት በማህበረሰቡ ከሚኖራቸው ተግባር ባሻገር ያለውን ጥበብ መመርመር እንደሚያስፈልግ ነው ። ቁሶቹ ከማህበረሰቡ ጋር ያላቸውን ዝምድና እንዲሁም ደግሞ ምን ለመግለጽ እንደመጡ መመርመርና ተምሳሌታዊ ፋይዳቸው ምንድነው? ቁሶቹ የሚያሳዩት የህይወት ፍልስፍና ምንድነው? የሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ ምላሽ ያገኙ ሲሆን የቀረበው መረጃ በነዚህ ሞዴሎች እሳቤ መሰረት ተተንትኖ የቀረበ ነው ።

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ በመጀመሪያ ቤቱ ከቀርከሃ በሚሰራ ሳጠራ ለሁለት ተከፍሎ ከፊት በኩል ያለው ሳሎን ሲሆን በስር በኩል ያለው ጓዳ በመባል ይታወቃል ። በዚህም ጓዳው የከብቶች ማደሪያን ጨምሮ ለተለያዩ አገልግሎቶች ይውላል ።

ፎቶ 31፡- የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ገጽታ ምስል




| መግለጫ | |
|---|---|
| A | መኝታ |
| B | መቀመጫ |
| C | ጓዳና ሳሎን መከፈያ |
| D | ምሰሶ |
| E | ሳሎን |
| F | ጓዳ |
| G | የእሳት ምድጃ |

| መግለጫ | |
|---|---|
| H | .የከብቶች በረት |
| J | የፈረስ በረት |
| K | መሽሎኪያ |
| L | ጉበኑን ከታች የሚያዩዝ |
| M | መዝጊያ በር |
| N | መቃን |
| O | መርገጫ |

ምንጭ፡-በአጥኚዋና ባህላዊ ቤቱን ባሰራው ባለሙያ አማካይነት ጳጉሜ2/2014ዓ.ም የተዘጋጀ

የቤቱ ውጫዊ ክፍል ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኂላ የውስጥ ክፍፍሉ ‹‹ቁርጡዋ›› ከሚባል ከማሽላ አገዳ ወይም ሸምበቆ ተሰርቶ ከምሰሶ አካባቢ ጀምሮ እስከ ግድግዳው ድረስ ከለላ በመስራት ሳሎን (Wuyigiiyaa) እና ጓዳ (Qoliuwaa) የሚለይ ሲሆን ጓዳ (Qoliuwaa) ውስጥ ደግሞ ጋጣታ (Gaxaattaa) የፈረስ ማደሪያ፣የከብት ማደሪያ (Zazaluwaa) እና የእህል መከመሪያ (Shakkuwaa) ወደጣሪያው በተወሰነ ጠጋ በማድረግ ይሰራለታል (ቃለ መጠይቅ፣ታደሰ፣10/10/2015ዓ.ም)፡፡

ከላይ ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊው ክፍል ሳሎን እና ጓዳ ተብሎ ለሁለት ከተከፈለ በኂላ ጓዳው የከብቶች ማደሪያ (Zazaluwaa) እና የእህል ማጠራቀሚያ (Shakkuwaa) የያዘ እንደሆነ የሚገልጽ ነው ፡፡

የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ በባህሉ ያሉት ትርጓሜዎች ቀጥሎ ቀርቧል፡- የመጀመሪያው ትልቁ ክፍፍል ምሰሶን መሰረት አድርጎ ሳሎንና ጓዳ በሚል ለሁለት ይከፈላል፤ ጓዳ (Qoliuwaa) የሴቶች ሲሆን ሳሎን (Wuyigiiyaa) ደግሞ የወንዶች ነው ፡፡ ጓዳ (Qoliuwaa) የሚስት፤ሳሎን (Wuyigiiyaa) የባል ነው፤መሃል ላይ የሳሎንና የጓዳ መግቢያ አለ ፡፡ ከምሰሶው በታች (ጓዳ) ውስጥ ከከብቶች ማደሪያ ጋር ተያይዞ የልጆች መኝታ የሚዘጋጅ ሲሆን እንደ ቆጥ አይነት ሆኖ የትኛውንም ቁሳቁስ ለማስቀመጥ የሚጠቀሙት ሻኩዋም የሚገኘው ጓዳ ውስጥ ነው ፡፡ ሌላው ጓዳ ውስጥ ሴቶች የተለያዩ እቃዎችን የሚያስቀምጡበት ሴፋ፤የምግብ መስሪያ ጮጬ(ምድጃ) ይገኛል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሙሽራ ስትመጣ የምትሞሽረው፤የሙሽራዋ ስርዓት፤ የሙሽራዋ መኝታ፤የምትቀለብበትና ለሶስት ወራት የምትቆየው እዛው ጓዳ ውስጥ ነው፡፡ የሙሽራ መውጫ የጓዳ ውስጥ በሮች ሲሆኑ የኂላ በር በጓዳ በኩል ሆኖ ይህም በር በአብዛኛው በፊት ለፊት የማይገቡ ነገሮች የሚገቡበትና ክፉ ቀን ሲመጣ የሚወጡበት ሆኖ የሴቶች ዘወትር መጠቀሚያ በር ሲሆን ክፉ ቀን ካልመጣ በስተቀር በዚህኛው በር ላይ ባል አይወጣም (ወልደ ማርያም፣03/10/2015ዓ.ም) ፡፡

በቀረበው መረጃ መሰረት የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጣዊ ቅርጽ ሳሎንና ጓዳ በሚል በቅርጮ ሁለት ቦታ ይከፈላል ፡፡ ጓዳ የሴቶች ሲሆን ሳሎን ደግሞ የወንዶች ነው ፡፡ ጓዳ ውስጥ የከብቶች ማደሪያ፤ የልጆች ማደሪያ፤ ሻኩዋ የተባለ የቁሳቁስ ማስቀመጫ፤ ሴፋ ሴት የተለያዩ እቃዎችን የምታኖርበት ሙሽራ የምትሞሽርበት፤ጓዳ ውስጥ ሆኖ የሙሽራዋ መኝታ ይገኛል ፡፡ የኂላ በር በጓዳ በኩል ያለ ሲሆን ይህ በሩም በአብዛኛው በፊት ለፊት የማይገቡ ነገሮች የሚገቡበትና ክፉ ቀን ሲመጣ የሚወጡበት ሆኖ በአብዛኛው የሴቶችና የሙሽራ መውጫ በር ነው ፡፡

ምልክቶች ጠቃሚ የሆነ ታሪካዊ እና ባህላዊ ትርጉሞች ያላቸው ነገሮች ናቸው። የዳዊት ኮከብ ለአይሁዶች ፤የአሜሪካ ባንዲራ ከአሜሪካውያን ጋር የሚገናኙ ሲሆኑ እነዚህ ምልክቶች ከታሪክ እና ከባህል ጋር የተሳሰሩ ናቸው ። በእያንዳንዱ ማህበረሰብ ውስጥ ጠቃሚ ሚናዎች አላቸው (Clifford1973: P.45) ። «በወላይታ ባህል ባልና ሚስት ሲጣሉ ባል ሚስቱን ሊደበድባት ዱላ ቢያነሳ ጓዳ ከገባች አልፎ መንካት አይችልም ። በባህሉ ነውር ነው ተብሎ ስለሚታሰብ ወንድ ወደ ጓዳ አይገባም ። ሴት ልጅ ባሏ ሲቆጣት እሮጣ ወደ ጓዳ (Qoluwa) ከገባች አትነካም፤እንኳን ሸሽታ ተከትሎ ገብቶ ይቅርና ብትሰድበው፤ያለአግባብ ብትናገረው ጓዳ ገብቶ አይነካትም፤ጓዳ ገብቶ ከመታት ጉዱን እዩ ጓዳ ገብቶ ነው ጎትቶ ያወጣኝና የመታኝ በማለት አቤቱታ ታሰማለች ። ሴት ጓዳ ከገባች አትገሰጥም፤አትነካም፤ባል ወደ ጓዳ ገብቶ ሚስቱን ከመታ ህዝቡ እሱን እንደ ሚስት እሷን እንደ ባል ስለሚያይ ክብሩን ያወርድበታል ተብሎ ይታሰባል፤እሷም ክብሯ ጓዳ ውስጥ ነው ተብሎ ይታመናል ። ይህም የሚደረገው ለሴቷ ክብር ለመስጠት ሲባል ሲሆን በባህሉ ወንዶች ጓዳ የሚገቡት እባብ ከገባ ለመግደል ነው ። ሴት ልጅ ጓዳዋ ገመናዋ ነው ያላትን ጥሪት እንደ ቅቤ፣ወተትና አይብ ጓዳ ውስጥ አጠራቅማ የቅቤ እቁብ በመግባት ጥሪት ታከማቻለች» (ቃለ መጠይቅ፣ሲሳይ ኩማ፣ህዳር 12/2015ዓ.ም) ።

በአጋጣሚ በባልና ሚስቱ መካከል የከረረ ጠብ ቢፈጠርና ተናዶ የሆነ ነገር አንስቶ ሊመታት ቢነሳ ወደ ጓዳ (ቆልኡዋ)ከገባች መንካት አይችልም ። ቢነካና በብሔረሰቡ ውስጥ ይሄ ወሬ ቢወጣ ደካማና የወደቀ ሰው ተደርጎ ይወሰዳል፤በህዝቡ ዘንድም እንደ ዝቅተኛ ሰው ነው የሚታየው ። ግን በአጋጣሚ ሳሎን (ውይጊያ) ላይ አግኝቷት ጉዳት ቢያደርስባትና ተነስታ ወጥታ ህዝብ ብትሰበስብ ጥፋተኛ የምትሆነው እራሷ ናት፤አንቺ ሴት አይደለሽ፤እናት አይደለሽ፤ የራስሽ ድንበር እያለ ለምን እሱ ድንበር ጋር ሄድሽ እንዲህ የተደበደብሽውና ጉዳት የደረሰብሽ ያለቦታሽ ስለተገኘሽ ነው ተብሎ ጥፋተኛ የምትባለው እሷ ናት ። የፈለገ ጥፋት ቢኖርባት እንኳን አልፎ ሄዶ ጓዳ ገብቶ ጥቃት ቢያደርስ አንተ እንዴት እንደዚህ አይነት ነገር ታደርጋለህ የሷን ድንበር አልፈህ ጉዳት ስላደረስክ አንተ የዚህ ቤት ሚስት እንጂ ባል አይደለህም በማለት የማህበራዊ ክብሩ ተምሳሌት የሚነጠቅበት አይነት ድርሻ እስኪኖር ድረስ ያደርሳል (ቡድን አንድ፤ወልደማርያም፣ሶዶ ዙሪያ፣ 2015ዓ.ም)

በሠላማዊ ግንኙነት ካልሆነ በስተቀር ባልና ሚስት ቢጣሉና ባል ወደ ጓዳ (Qoliuwaa) ገብቶ ሚስቱን ሲደበድብ ቢገኝ “አንተ ባል ሳትሆን ሚስት ነህ ድንበርህን ዘለህ ለምን በደል

ታደርሳለህ" በሚል በባህሉ እንደ ዝቅተኛና ማህበራዊ ክብሩን እንደጣለ ሰው ይቆጠርና በህዝቡ ዘንድ የተናቀና ተሰሚነት እንደሌለው ተደርጎ ማህበራዊ ክብሩ ይወሰድበታል ፡፡

## 7.3. የወላይታ ብሔረሰብ የቤት ቅርጽ ክብነትና ትርጓሜ

በወላይታ ባህል ክብ ነገር ከብዙ ነገሮች ጋር የሚገናኝ ሆኖ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉት ፡፡

በባህሉ ክብ ነገር ሙሉ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የቤቱም ክብነት ከሙሉነት ጋር የተያያዘ ነው በቤቱ ውስጥ ለመገልገያነት የሚውሉ ቁሶች ክብ መሆናቸው ከቤቱ ቅርጽና ከሙሉነት ጋር የተገናኘ ነው ፡፡ በባህሉ ክብ ወይም ሙሉ ቁጥር ያልሆነ በረከት የለውም የመጥፎ ነገር ምሳሌ ነው ተብሎ ይወሰዳል ፡፡ ለምሳሌ  ልጅ ሲወለድ በተቻለ መጠን ሙሉ ቁጥር ያለው ልጅ እንዲወለድ ይፈለጋል፤ጥንድ ጥንድ ሆኖ ካልተቆጠረ ጎዶሎ ተብሎ ይወሰዳል ፡፡ አንድ ልጅ ከተወለደ ቢዛ ነው ይባላል፤ቢዛ ማለት መንፈሱ ጠንካራና ሃይለኛ ሰው ሊሆን ይችላል ተብሎ ይታመናል (ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣ታህሳስ16፣2015 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲታኝ ቤት የባህል አንዱ ክፍል ሆኖ በቅርጹ እና በቦታው አቀማመጥ ባህላዊ እምነቶችን እና ልማዶችን የሚያንፀባርቅ ነው (Al-Homoud, 2009) የማንኛውም ቤት ቅርጽ እንደየተገነባው አካባቢ፤የሰውን ልጅ ባህሪ የባህል እና ትውፊታዊ እምነቶችን ያንጸባርቃል፤ሌላው የቤት ቅርጽ እና ባህል ሁልጊዜ እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው (Samadi, 2013) ፡፡ የወላይታ ባህላዊ ቤት ቅርጽ ክብ ሲሆን ይህም ከሙሉነትና ከበረከት ጋር የተያያዘ ነው ፡፡

የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ ሲሳይ ኩማ (ቃለ መጠይቅ፣ታህሳስ 20፣2016 ዓ.ም) ከላይ ከሙሉነትና ክብነት ጋር ተያይዞ በቀረበው ሀሳብ ላይ የሚከተለውን ተጨማሪ መረጃ ሰጥተዋል፡-

የወላይታ ህዝብ ሙሉ የሚለውን ነገር የሚያስቡት ከክብነት ጋር በመሆኑ የቤቱ ክብነት ሙሉ መሆኑን ይገልጻል፤በባህሉ የቤቱ ቅርጽ ክብ መሆን ከቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች ጋር የተገናኘ ነው፡፡ ለአብነት ዳታ የሚዳጥበት መለንቀጫ መጅ (ሞይላ) አይነት ነገሮች የሸክላ ስራ የሆኑት የቤት ቁሶች ፤የባህል ጭፈራቸው ሁሉም ክብ ናቸው ፡፡ ክብ ሙሉ ነው ተብሎ ይታሰባል፤ሙሉ የሚባለው ጉዳይ ሁል ጊዜ የሚገለጸው በማዕዘን አይደለም፤ማዕዘን ያለው ነገር ሙሉ አይደለም ተብሎ ይታሰባል፤ሁሉም ነገር ሰው ላይም ሆነ በየትኛውም ፍጥረት ላይ

ምልክት የሚደረገው ነገር ሁሉ ክብ ነው ። ስለዚህም ክብ ነገር ከብሔረሰቡ ማንነትና እምነት ጋር የተገናኘና ሙሉ ነው ብለው ያስባሉ ።

በቡድን ሁለት በሶዶ ዙሪያ በተካሄደው ውይይት ውስጥ ከተሳተፉ አባላት መካከል የወላይታ ባህላዊ ቤት ቅርጽ ፍቺ ከብሔረሰቡ ጋር ያለውን ዝምድና ፤በብሔረሰቡ ያለውን ትርጉም በተመለከተ የቡድኑ አባላት በተመሳሳይ ሁኔታ የገለጹ ሲሆን ለአብነት ያህል የቡድኑ አባል የሆኑት አቶ ወልደ ማርያም ይህንኑ ጉዳይ ሲገልጹ የወላይታ ቤት መሰረት (ባሷ) ሲቆፈር ሙሉ ክብ ነው ። የቤቱ ዙሪያ (ዳርኩዋ )የሚሰራው ሙሉውን ከመሰረት ጋር ትይዩ በሆነ መልኩ ሙሉ ጨረቃ ነው ። ለምሳሌ ያህል በክብ ጉልቻ እና በክብ የሸክላ ምጣድ ላይ ክብ ቂጣ ይጋገራል፤ ይህም ቂጣ በባህሉ ክብነቱን እንደጠበቀ በትልቅ ሰው ፊት ሙሉው ይቀርብና ሰብረው ይበሉታል ። ጎዶሎ የሆነ ነገር በሰው ህይወት ውስጥ የትኛውም የጎደለ ነገር የተሻለ ነገር እንኳን ቢሆን እሱ አይበላም ። መንፈሳዊ ግንኙነት አለው ተብሎ ይታሰባል ።

ክብ ነገር ከሰው ህይወት ከሁሉም ነገር ጋር የሚገናኝ ሲሆን ሙሉ የሚባለው ክብ ነገርን ለመግለጽ ነው ተብሎ ይታመናል ። በወላይታ ብሔረሰብ የሚገኙ ነገሮች እንደ መመገቢያ ቁሶች፤መስሪያ ቁሶች ምግብ የሚሰራበት ጉልቻ፤የአመጋገብ ስርአታቸው፤የምርቃትና የእርግማን ስርአታቸው፤የጭፈራ ስርአታቸው በአብዛኛው ክብ ናቸው ። በተጨማሪም ቤት ብቻ ሳይሆን በአካባቢው የሚገኙ ዋሻዎችም ጭምር ክብ ናቸው ። በወላይታ ውስጥ የሚገኘው ሀሩሪና የተባለው ዋሻ ሙሉ ክብ ሲሆን በጨረቃ ቅርጽ የተሰሩ ወደ ስድስት ክፍሎች አሉት(ዘብዲዎስ፣2012) ። እነዚህም ሙሉ ክብ ሲሆኑ እንዲህ የሆኑበት ምክንያት አንደኛው ክፍል ግማሹ የሚታየውን ዓለም፤ግማሹ የማይታየውን ከስር ያለውን ዓለም ይወክላል ተብሎ ስለሚታሰብ ቤቶቹ ክብ ሆነው ይሰራሉ ።

የቤቱ ቅርጽ ክብነትና ቤት ውስጥ የሚገኙት ቁሶች ክብ መሆናቸው የትክክለኛነት (ፍጹምነት)ተምሳሌት ነው ። ምክንያቱም ክብ ነገር ፍጹምነት አለው ብለው ስለሚያምኑ ነው

ቤት ውስጥ ያሉ ማናቸውም የመገልገያ ቁሶች ክብ ሆነው ነው የሚሰሩት፤ለምሳሌ የፈረስና የበሬ ጋጥ አርክ ነው የክቡ1/2ኛውን ይዞ ነው የሚሰራው፤ምድጃ(ጮጪያ) እሳት የሚነድበት የሚቆፈረው ክብ ነው፤የከብቶች ጋጥ ውስጥ ያለው አዘባ የሚወድቅበት አርክ ነው ። በባህሉ ሙሉ ክብ እንኳን ባይሆን የተጀመረ ክብ ሳይቀር ሙሉ የሚባለውን ሀሳብ ይይዛል ።

የወላይታ ህዝብ በራሱ ሙሉ ነን ብሎ ያምናል ። እንደ ሀገር ሙሉ ነን ፤እንደ ህዝብ ሙሉ ነን ፤እንደ መንግስት ሙሉ ነን ብለው ያስባሉ ። ይሁንና ይህን ሙሉነት ሸርሽረው ጉድለት ሊያመጡ የሚችሉ ነገሮች ሲከሰቱ(ሲፈጠሩ) ይህን ለማስተካከል ደግሞ በባህሉ የመሀላ (ጫቁዋ)[55]የሚባል ሥርዓት ይደረጋል ። በዚህም ይሄ መሃላ (ጫቁዋ) ሲፈጸም የጎደለው ይሞላል ተብሎ ይታመናል ።

በምልከታ ፣በቃለ መጠይቅና ቡድን ተኮር ውይይት ከተገኘው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ብሔረሰብ ዘንድ ሙሉነት የሚታሰበው ከክብ ጋር ተያይዞ ነው ። በመሆኑም በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤቱ ብቻ ሳይሆን የቤት ውስጥ መገልገያ ቁሶች፤ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች ሁሉ ክብ ናቸው ። በባህሉ ክብ ነገር ከሰው ህይወት ጋር የተያያዘ ሆኖ ሙሉ የሚባለው ክብ ሲሆን ነው ተብሎ ስለሚታመን እንደሆነ ነው ።

አቶ ዲዳዬ ቃልቶሬ፣ቃለ መጠይቅ፣ታህሳስ 24/2016ዓ.ም. የባህላዊ ቤቱ ክብነትና ትርጓሜ ላይ እንደነገሩኝ ክቡን የሚሰነጥቀው መግቢያ በር ከታች የሚደረገው ጎጭላ ሲሆን መውጫያ ቦታውም እንደ አርክ አይነት ቅርጽ ያለው ነው ። ቆሪያ ማለት ከላይ በኩል በበሩ መግቢያ ላይ ያለው ልክ ሻሽ እንዳሰረች ሴት ሙሉ የክብ ዲዛይን እንዲኖረው ተደርጎ የሚሰራው ሲሆን የቤቱ መግቢያው ቅርጹ እንደ ኮፍያ አርክ ነው ። ጉልላቱ ሙሉ ክብ ቅርጽ እንዲኖረው ተደርጎ ይሰራል ። እነዚህ በክብ ቅርጽ የተገለጹት በሙሉ የማይሰነጠቁና የማይከፈሉ ጥብቅ ያሉ የሚጨበጥ ነገር የሚገለጽባቸው ናቸው ። ሌላው መሃላ የሚደረግበት ድንጋይ ኡማ ሹቻ የሚባል ሲሆን ይህም ምንም አይነት ቀዳዳ(የተሰነጠቀ) ነገር የሌለበት ሲሆን መሀላ የሚፈጸመውም እሱ ላይ ተቆሞ ነው ። በባህሉ ክብ የሚለው ከቅርጽ ያለፈ ትርጓሜ አለው ።

[55] . ከጥንት ጀምሮ ፊቲያ፣አምባቢሳ ጉቺያ፣ካላቻ፣ውይጢያ፣ማዞሊያ የሚባሉ ስድስት መሀላዎች አሉ። ህዝብ ከመንግስት ጋር ከመሬት አለቆች ጋር መሀላ የሚፈጽሙበት፤የጎደሉ ነገሮች አሉ ተብለው ሲታሰቡ ሙሉ ለማድረግ ወዲያው በመለከት ድምጽ ህዝብ ተሰብስቦ እምነት ጎሏል፤ድንበር ጎሏል፣ከተባለ በኋላ ሙሉ ለማድረግ መሀላ ያደርጋል። በዚህም በመሃላ ስርዓቱ ሰዎች ክብ ሰርተው ተሸፋፍነው ይቀመጣሉ፤ እምነት ያጎደለው ሰው እስኪ በዙሪያችን ዙር ይባልና በመሀሉ እንዲያልፍ ይደረጋል፤ ይሄ ደግሞ በባህሉ ከባድ መሃላ ስለሆነ ድፍን ሆነው ሙሉውን ተሸፋፍነው የተቀመጡትን ሰዎች ዙሪያቸውን የዞረ ሰው መሀሉን ሰንጥቆ ሲያልፍ ወዲያው ይሞታል። ምክንያቱም ያን መንፈስ መቋቋም ስለማይችል ይሞታል ተብሎ ይታመናል። ይህም ከቤቱ ክብነት ጋር ይያያዛል

ፎቶ 32፡- ለክብነት አሰረጂ የሆኑ የወላይታ ባህላዊ የቤት ቁሶች




ምንጭ፡- ከኦፋ ወረዳና ከሶዶ ዙሪያ ወረዳ በአጥኚዋ ጳጉሜ2፣2014ዓ.ም የተነሳ

ምንም እንኳን በሀገራችን በተለያዩ ቦታዎች ክብ ቤቶች የተለመዱ ቢሆንም የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤቶቹ ብቻ ሳይሆኑ መገልገያ ቁሶቹም ክብ መሆናቸውን ከመስክ መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ሌላው ክብነት ከብሔረሰቡ ማንነት፣እምነትና ፍልስፍና ተዛምዶ አለው ፡፡ ሌላው ከፍጹምነት ጋር የሚያያዝ ፍቺ እንዳለው መረዳት ተችሏል፡፡

**ፎቶ 33 ፦ ባህላዊ የሙዚቃ መሳሪያዎች፣መቀመጫዎችና ባህላዊ የገበጣ መጫወቻዎች ቅርጽ ከቤቱ ክብነት ጋር ያላቸውን ተመሳስሎ ለማሳየት አስረጂ**




| መግለጫ | |
|---|---|
| 1 | ድምጻ ቀጭን አታሞ (ኢንዴ ካሪቢያ) |
| 2 | ካምባ-ለለቅሶና ለዘፈን ጊዜ የሚያገለግል |
| 3 | ከእንሰት ወፍቾ የሚሰራ ባህላዊ ክብ ወንበር |
| 4 | ነጋሪት(ናጋሪታ) |
| 5 | ድምጻ ጎርናና አታሞ(አዴ ካሪቢያ) |
| 6 | ገበጣ መጫወቺያ(ሳዲቃ) |

**ምንጭ፦ ከሶዶ ዙሪያና ኦፋ ወረዳዎች በአጥኚዋ ጳጉሜ 2፣2015ዓ.ም የተነሳ**

በፎቶ 32 የቀረቡት የሙዚቃ መሳሪያዎች፤ከእንሰት ወፍቾ የተሰሩ ባህላዊ ወንበሮች እና ገበጣ መጫወቺያ (ሳዲቃ) የተባሉት ክብ ናቸው ። ስለዚህም ክብ ነገሮች ከብሔረሰቡ ጋር ያላቸውን ጥብቅ ቁርኝት ከማሳየት ባሻገር ከቤቱ ውጪ ቤቱ ውስጥ የሚገኙ ቁሶች ክብ እንደሆኑ የሚያሳይ ነው ።

- **የክብና የሙሉ ቁጥር ትእምርቶች በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ውስጥ**

በየሀገሩ ለቁጥሮች የሚሰጠው ትርጓሜ በሀገሩ ከሰው ልጅ ጋር በቆዩ ባህሎች እና ልማዶች ምክንያት ይለያያል ። የተወሰኑ ቁጥሮች ደግሞ ከሰው ልጅ ሃይማኖታዊ አስተምህሮ ጋር ይገናኛሉ ። በዚህም ምክንያት ብዙ ቁጥሮች ያላቸው ጠቀሜታ ከሐይማኖታዊ እይታ ውጭ ብዙ ፍቺ የያዙ ስለሆነ በሰው ልጅ ባህላዊ እይታ ላይ ምን ዓይነት ተጽእኖ እንደሚያሳድሩ ማወቅ ተገቢ ነው ። በተጨማሪም ቁጥሮች በተፈጥሯቸው ስለአንድ ነገር መለኪያ ወይም

ምልክት በመሆናቸው በሂሳባዊ ቀመሮችና ቆጠራ ላይ ጉልህ ሚና አላቸው፡፡ በቅደም ተከተላቸው ቁጥሮች አቅጣጫን ወይም መጠንን ሊጠቁሙ ይችላሉ፤ በሌላም ጎን ሂሳባዊ ማለት ከቁጥር ይለያል ምክንያቱም ሂሳባዊ ማለት ቁጥሮችን የምንሰይምበት መንገድ ነው፡፡ ግብጻዊያን የቁጥሮችን ቀመር ሠርተዋል (Radeloff,1990).

በዚህ ርዕሰ ጉዳይ ስር ከላይ ከቀረቡት ሀሳቦች በተጨማሪ የክብ እና የሙሉ ቁጥር እሳቤ ቀጥሎ ቀርቧል፡-

በባህሉ ለቤቱ የሚቆፈረው ጉድጓድ ክብ ሲሆን ለቤቱ መስሪያ የሚውሉት ወራጅ እንጨቶችና ማገሮች ቁጥራቸው ሙሉ እንዲሆን ይደረጋል ፡፡ ቁጥሮቹ በራሳቸው ብዙ ፋይዳ አላቸው፤በወላይታ ባህል ብዙውን ጊዜ ሙሉ ተደርጎ የሚታየው መቶ (ጤታ) ነው፤መቶ ተስማሚ ቁጥር ነው ተብሎ ይታሰባል ፡፡ አንድ አገር ላይ ብዙ ሚሊየን ህዝብ ሊኖር ይችላል በባህሉ ይሄ ህዝብ መቶ(ጤታ) በሚል ይገልጻል፤ጤቲስ ይላል እንጂ ሚሊየን ሆን  አይልም ፡፡ ጤቲስ ማለት ሞላ ወይም ሙሉ ማለት ነው ፡፡ ህዝቡ ሁሉን ነገር ሲመርቅ ጤታ ሙሉ ሁን ይላል ፡፡ ለምሳሌ አስር ሺህ የሚወስደውን ፈረስ ጤታ ይላል፤ጤታ ማለት ዋጋውን አይደለም፤ጤታ ማለት መቶ ማለት አይደለም፤ሙሉ ማለት ጤቲስ ብሎ የሚገለጸው አንድ ያልታወቀ ነገር ከቁጥሩ ባሻገር እንደ ማለት ነው፤በተግባር ጤታ መቶ ቁጥርን ይወክላል፣ግን አሁን መቶ(ጤታ) ሲሞላ ከብቶችን ዳላ ብሎ የቆጠራ ስርዓት ይደረጋል፤የግድ ከብቶቹ መቶ ያልሞሉ 80 ወይም ከመቶ በላይ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ ለምሳሌ፡- አራት መቶ፣አምስት መቶ ሊሆኑ ይችላሉ ፡፡ ሺህ ሲሞላ ሊቃ እስኪደርስ ድረስ ያለውን ሁሉ ጤቲስ ብሎ ይተዋል እንጂ ከዛ ያለፈውን ቁጥር አይገልጽም፤ሙሉ(ጤታ) በአዕምሮው ለሙሉነት የተሰጠ ተምሳሌት ነው ዝቅ ያለ ነገርንም ጤቲስ ብሎ ይገልጻል፤ለምሳሌ አሁን አንድ ሰው በርከት ያለ ልጅ ከወለደ 11፣13፣15 ሊሆን ይችላል፤ለእገሌ ልጁ መቶ(ጤቲስ) ይላል፤ሞልቷል በቂ ማለት ነው ቤተሰቡ በጣም ሰፊ የሆነ ህብረተሰብ ሆኗል የሚለውን ለመግለጽ ነውና ከዚህ ውጪ  ሙሉ የሚለው ሀሳብ ህዝቡ ቤቱን ሙሉ አድርጎ እንዲያይ ያደርገዋል (ቃለ መጠይቅ፣ታደሰ ኮይራ፣ታህሳስ30/2016 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ባህል መቶ ቁጥር (ጤታ)ሙሉ ተደርጎ ይታሰባል፡፡ ሙሉ(ጤታ) በአዕምሮ ውስጥ ለሙሉነት የተሰጠ ተምሳሌት ነው፡፡ በብሔረሰቡ መቶ ተስማሚ ቁጥር ነው ተብሎ ስለሚታሰብ በእያንዳንዱ ባህላዊ ክዋኔያቸው ውስጥ ይገለጻል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በብሔረሰቡ የቤት አሰራር እውቀት ውስጥ ከግብአት ምርጫና

ከቤቱ ፍጻሜ ጋር በተያያዘ በሚደረግ ስርአተ ክዋኔ ውስጥ መቶ ቁጥር የተለየ እንድምታ እንዳለው የመስክ መረጃዎች አመላክተዋል፡፡ ይኸውም ለቤት መስሪያ የሚውሉ ወራጅ እንጨቶች፣ቀጫጭን ማገሮች(ሀማካ)፣የግድግዳ እንጨቶች፤የማገሮቹ ማሰሪያ ወፍኞ ሙሉ ቁጥር እንዲኖረው ስለሚፈለግ የትኛውም የቁጥር መጠን ቢኖራቸውም መቶ(ጤቲስ) ተብሎ ይገለጻል፡፡ ምክንያቱም  መቶ(ጤቲስ) ማለት በባህሉ ሞላ ወይም ሙሉ ሆነ ማለት ስለሆነ ይህንንም የሙሉነት እሳቤ ከቤት አሰራር ጋር ስለሚያያይዙት ብሎም ህዝቡ ቤቱን ሙሉ አድርጎ እንዲያይ የሚያሳዩ እንደሆነ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡ ከግብአቶች ባለፈ ቤቱ አልቆ የቤቱ ባለቤት ወደ ቤት ሲገባ በአካባቢው የሚገኙ በእድሜ የገፉ ሰዎች በአዲሱ ቤት ውስጥ ሆነው መቶ (ጤታ) ሁኑ በማለት ባለቤቱንና ቤቱን ይመርቃሉ፡፡ ይህም ቤቱ ረጅም እድሜ እንዲኖረው ጤታ(መቶ) ሁን በማለት ሲመርቁ ባለቤቱን ደግሞ መቶ ዓመት ኑር (ጤቱ ላይታ ዴአ) በማለት መቶ ሁን  ብለው ይመርቃሉ፡፡ ይህ ማለት በባህሉ መቶ ቁጥርን ከመግለጽ ባለፈ ለባለቤቱ ዘላለማዊ ህይወትን ሙሉ በሆነ ቤት ውስጥ እንዲኖር ከመመኘት ጋር የሚገናኝ ትርጉም አለው፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ባህል ብዙውን ጊዜ ሙሉ ተደርጎ የሚታየው መቶ ቁጥር (ጤታ) ነው ፡፡ ለብሔረሰቡ መቶ ተስማሚ ቁጥር ነው ተብሎ ይታሰባል አንድ አገር ላይ ብዙ ሚሊየን ህዝብ ሊኖር ይችላል፤ያንን እንኳን ህዝቡ መቶ(ጤታ) በሚል ይገልጻል፤ጤቲስ ይላል እንጂ ሚሊዬን ሆነ  አይልም ፡፡ ጤቲስ ማለት በወላይታ ባህል የሙሉነት ተምሳሌት ነው፡፡ የወላይታ ህዝብ ሁሉን ነገር ሲመርቅ ጤታ ሙሉ ሁን ይላል ፡፡ መቶ(ጤታ) ማለት ዋጋውን ለመግለጽ አይደለም ፡፡ ጤታ ማለት መቶ የሚለውን ከመግለጽ ያለፈ ትርጉም አለው ፡፡ ሙሉ ማለት ጤቲስ ተብሎ የሚገልጽ ሲሆን መቶ (ጤታ) ማለት ነው በብሔረሰቡ ከቁጥሩ ያለፈ ሙሉነትን የሚገልጽ ትርጉም አለው ፡፡ ይህም ብሔረሰቡ እራሱን እንከን አልባ አድርጎ ከማሰብ ባሻገር የመንፈሳዊ አስተምሮ ተምሳሌት ነው (ቃለ መጠይቅ፣አቶ ወልደማርያም ፣አቶ ኢያሱ፣አቶ ኢሳያስ፣2016 ዓ.ም ) ፡፡

የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ የሰው ልጅ ከጥንት ጀምሮ ከቁጥሮች ጋር የፍቅር እና የጥላቻ ግንኙነት ነበረው ። የባህል ማህበራት፣ ሃይማኖታዊ ጉዳዮች፣ፍልስፍና እና ውበትን ጨምሮ ከተለያዩ ቁጥሮች ጋር ምናልባት ከ30,000 ዓመታት በፊት የነበሩ አጥንቶች የጨረቃ ደረጃዎችን የሚወክሉ የጭረት ምልክቶችን ያሳያሉ ። የጥንቶቹ ባቢሎናውያን የፕላኔቶችን

እንቅስቃሴ ተመልክተው በቁጥራቸው ተመዝግበው ግርዶሾችን እና ሌሎች የስነ ፈለክ ክስተቶችን ለመተንበይ ይጠቀሙባቸው ነበር (Matheus, 2018)፡፡

በኤዥያ ባህል ማንኛውም ትልቅ ቁጥር እንደ ዕድለኝነት ወይም እድለብስነት የሚታዩት በውስጣቸው በያዙት ነገር ልክ ነው ፡፡ በአንዳንድ ኤዥያ ቋንቋዎች 8 ቁጥር ከዕድለኝነት፤ ከመልካም አጋጣሚዎች ወይም ከገንዘብ ጋር ሲገናኙ በሌላ ጎን ደግሞ 4 ቁጥር ልክ እንደ ሞት ዜና ተደርጎ ይታያል ፡፡ ስለዚህ 8 ቁጥር ዕድለኛ ሲሆን 4 ዕድለ ቢስ ነው ፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ቁጥሮች ትርጉማቸው ከዕድል እና ከዕድለ ቢስነት አልፈው ይተረጎማሉ ፡፡ በተጨማሪም ማንኛውም ቁጥር 4ን ከያዘ ለምሳሌ፡- 14 እና 41 ከሆነ ከዕድለቢስነት ጋር ይቆራኛል ነገር ግን በውስጣቸው 8 ቁጥር ካለ ለምሳሌ፡- 18 እና 81 ሲሆን ዕድለኝነት ተደርጎ ይወሰዳል ፡፡ እንደ 88 ያሉ ቁጥሮች የበለጠ ዕድለኝነት ተደርገው ይወሰዳሉ ፡፡ አንድ ቁጥር በውስጡ 4 እና 8 ቁጥር ከያዘ ዕድለቢ ስነት፣ መጥፎ ዕድል፣ ጋጠ-ወጥነት፣ ከመልካም አጋጣሚ ያፈነገጠ ብሎም 8848 ዕድለኝነትን ከሚያመለክተው በላይ የከፋ መልክ አለው (Greene, 1995)፡፡

### 7.4.የወላይታ ባህላዊ ቤት መገንቢያ ግብዓቶች

በዚህ ምዕራፍ ስር የወላይታ ባህላዊ የቤት መገንቢያ ግብዓቶችናማህበረ ባህላዊ ፋይዳቸው እንደሚከተለው ቀርቧል ፡፡

በወላይታ ለቤት መስሪያ የሚውሉ ግብዓቶች የተለያዩ ሲሆኑ ይህንኑ ጉዳይ አቶ አየለ አይዴ ሲገልጹ የወላይታ ባህላዊ ቤት ለመስራት እስከ ሁለት መቶ የሚደርሱ የግድግዳ እንጨቶች ማገር እስከ ሁለት መቶ ሀምሳ ድረስ ያስፈልጋል ፡፡ ለማገር የሚሆኑ እንጨቶች፤ ለበር መቃን መስሪያ፣ ለበር ጉበን መስሪያ፣ የበር መግቢያ፤የበሩ መርገጪያ፤የበርእንጨቶች፤ጎርዴሚታ፣(በርመዝጊያ) ፤ የምሰሶ እንጨት፣ ወፍቾ፣ ፎሹዋ የሚባል ሀረግ የሚወጣበት (ቃለ መጠይቅ፣ጥር/2016ዓ.ም) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ሀሳብ መረዳት እንደተቻለው በወላይታ ቤት ለመስራት ለማገር የሚሆኑ እንጨቶች፣የምሰሶ እንጨት፣ወፍቾ፣ለበር መስሪያ የሚሆኑ እንጨቶች የሚያስፈልጉ ሲሆን እነዚህም የምሰሶ፤ እንደ ቤቱ መጠን ለማገር የሚሆኑ፤ለግድግዳ የሚሆኑ እንጨቶች እንዲሁም ለበር ጉበንና የማሰሪያ ወፍፎ እንደሚያስፈልግ የሚገልጽ ነው ፡፡

የቤት መስሪያ ግብአቶች መገኛ ቦታቸውን በተመለከተ የሶዶ ዙሪያ ነዋሪ የሆኑት አቶ አድማሱ እንደነገሩኝ በወላይታ ለቤት መስሪያ የሚውሉ ግብአቶች ከባለቤቱ ከማሳ እና ከጫካ ይገኛሉ ፡፡ ይህንን በተመለከተ የኦፋ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢያሱ ሲገልጹ የወላይታ ሰው ማሳውን የቤት መስሪያ ቦታ፣የእህልመዝሪያቦታ፣ የሳር ቦታ፣ የእንጨት ቦታ እያለ ለየብቻ ከፋፍሎ ያስቀምጣል፡፡ ከጫካ ለማገርና ለተለያዩ አገልግሎቶች የሚሆን እንጨት ቆርጠው ያመጣሉ፡፡ ሌላው የሰንበሌጥ፤የግርግዳና የማገር እንጨት እያለ ያሰባስባል፡፡ ከጫካ ለቤት መስሪያ ነው ብሎ እንጨት በሚቆርጥበት ጊዜ ከልካይ ባይኖረውም ደንን በማይጎዳ ሁኔታ ይከናወናል ፡፡ ይህም ኦቾሎ የሚባል የደን መዋቅር አለ ፤ በዚህ ውስጥ የደን ሀብት ሀላፊ አለ ፡፡ ይህም ለወላይታ ዘመን መለወጫ በዓል(ጊፋታ) ለቤት መስሪያ የሚሆን እንጨት በሚቆረጥበት ጊዜ ደን እንዳይጎዳ ክትትል የሚያደርግ ነው ፡፡ ለማገር ለግድግዳ ተብሎ ተቆርጦ የተቀመጠውን ጓደኞቹን ይዞ ሄዶ እስከሚያነሳ ድረስ የሚነካው የለም (ቃለመጠይቅ፣2016ዓ.ም) ፡፡

በባህሉ ቤት የሚሰራው ግለሰብ ግብአቶችን ከጫካ ወይም ከራሱ የእንጨት መሬት ሊሰበስብ ይችላል ፡፡ ሰንበሌጥ ፤ ለማሰሪያ የሚሆን ወፍቾን ከጓደኞቹ እና ከራሱ የሳር መሬት ሊያሰባስብ ይችላል ፡፡ በቤቱ ስራ ወቅት የአካባቢው ሰዎች በሙሉ ይሳተፋሉ ፡፡ በባህሉ በእርሻም ሆነ በቤት ስራ የመረዳዳት ባህል አለ፤የመረዳዳት ባህሉ በሦስት የሚከፈል ሲሆን እነዚህም ሀሺያ ከ2-5 ሰው በመሆን የሚረዳዱበት ሲሆን በዚህ ውስጥ ኩትኳቶና በበሬ ማረስ ይካተታሉ ይህም እንሰት፣ስኳር ድንች ለመትከል ሲሆን ይህም ዛሬ የአንዱ ሰው ከተተከለ ነገ የሌላኛው ቤት ይተከላል፡፡፣ዘይያ የተባለው ከ5-10 ሰው ሆኖ የሚሰሩበት ነው፣ ደጎ ደግሞ ከ10 ሰው በላይ የሚሰሩበት ነው፡፡ እንጨት ሲሰበሰብ፣ሰንበሌጥ ሲታጨድ በሀሺያ ያሰራሉ፡፡ አጠቃላይ የቤቱ ስራ ከሆነ ግን ደጓ ያነሳሉ ፡፡ እነዚህ የመረዳዳት ልማዶችን መሰረት ተደርገው የቤት መስሪያ ግብአቶች ይሰበሰባል ቤት ይሰራል (አቶ ኡኩሌ፣ቃለመጠይቅ፣2015ዓ.ም) ፡፡

ከላይ ከቀረበው ይዘት መረዳት እንደተቻለው የቤት መስሪያ ግብአቶችን በተመለከተ በወል መሬቶች ላይ ለሳር ፣ለምሰሶ የሚሆን እንጨት የሚተከልበት እራሱን ችሎ ለየብቻ ያለ ሲሆን ማሳው ላይ የሌሉትን ደግሞ ከጫካ ቆርጠው ያመጣሉ ፡፡ ሌላው በባህሉ ኦቾሎ የሚባል መዋቅር ያለ ሲሆን ይህም እንጨቶቹ ሲቆረጡ ደኑ እንዳይጎዳ የሚከላከል ነው ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በወላይታ ሰዎች በቤት ስራ ወቅትም ሆነ በእርሻ ስራ ወቅት በመተጋገዝ ይሰራሉ ፡፡ ይህንንም የመረዳዳት ባህሎች ሀሺያ፣ ዘይያ እና ደጎ ይባላሉ እነዚህን እንጨት

ሲሰበሰብ፣ሰንበሌጥ ሲታጨድ በሀሺያ ሲያሰሩ አጠቃላይ የቤቱ ስራ ከሆነ ደን በማስነሳት ቤት ይሰራሉ ፡፡ በባህሉ እነዚህ የመረዳዳት ባህሎች የቤት መስሪያ ግብአቶችን ለመሰብሰብ ይረዳሉ፡፡

የቡድን አንድ ተወያይ የነበሩት አቶ ሀይሌ ሀርጎ ስለ ወላይታ ባህላዊ ቤት መስሪያ ግብአቶች ሲገልጹ ግብአቶቹ ከባለቤቱ ማሳ ወይም ከጫካ የሚገኙ ሲሆን መጀመሪያ የሚሰበሰበው የግድግዳ እንጨት ነው ፡፡ ለግድግዳ የሚሆኑ ግራርና ሌሎች እንጨቶች ከቆላና ከበረሃ አካባቢ ይገኛሉ ፡፡ ግርግዳን በደቦ መልክ ሰዎች ቀን ተቀጥሮ ግድግዳውን ቆርጠውና ፈልጠው እንዲያመጡ ይደረጋል፤ ሌሎች እረጃጅም እንጨቶች ለማገር ወይም ለወራጅ የሚሆኑ እንደ ሀማካ ያሉ እዛው አካባቢ ከሚገኝ ጫካ ውስጥ ይገኛሉ ፡፡ ህዝቡ ለቤት መስሪያ የሚሆኑትን ግብአቶች በሙሉ ከማሳው ወይም አካባቢው ጫካ ውስጥ ይሰበስባሉ ፡፡ ለምሳሌ ለምሰሶ የሚሆነው ጠንካራ እንጨት ሲሆን ይህንንም ከራሱ፣ከጎረቤት ወይም ራቅ ካለ ጫካ ሊያገኝ ይችላል ፡፡ የተገኘው ትንሽ እራቅ ያለ ቦታ ላይ ቢሆን እንኳን እየጠበቀ ይቆያል፤ሰው አያስነካም እንደ አዋጅ በአካባቢው ያስነግራል (ቡድን አንድ፣ኪንዶ ዲዳዬ፣2016 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ በቀረቡት መረጃዎች ላይ አክለው የቡድን አንድ ተወያይ የነበሩት አቶ ኢሳያስ ስለ ወላይታ ባህላዊ ቤት መስሪያ ግብአቶች እንደነገሩኝ ለማሰሪያ የሚሆን ወፍቾ ጡዙማ ከተባለው የእንሰት ዝርያ የሚገኝ ሲሆን ይህ እንሰት በጓሮው ከሌለ ከጎረቤት ወይም ከዘመድ ያስመጣል በወላይታ ከሚገኙት የእንሰት ዝርያዎች መካከል ጡዙማ በጥንካሬው የታወቀ በመሆኑ ለቤት ማሰሪያ የሚያገለግለው ከዚሁ የእንሰት ዝርያ ነው ፡፡ ጡዙማ ደጋና ወይናደጋ አካባቢ ላይ የሚያድግ ሲሆን ቆላ ላይ አይበቅልም፤ ቆላ ላይ ቤት የሚሰራ ሰው ይህንን ወፍቾ ከደጋና ከወይን አደጋ አካባቢ ጠይቆ አምጥቶ አስሮ ያስቀምጣል ፡፡ ስራው በሚጀመርበት ጊዜ ኩሬ ውሃ ውስጥ ወይም እቤት አካባቢ አስቀምጦ ውሃ በሱ ላይ በማርከፍከፍ ይጠቀማል ፡፡ ሌላው የግራር ቅርፊት ሀይለኛ ጥንካሬ ያለው በመሆኑ ቶሎ ስለማይበጠስ ለማሰሪያነት ያገለግላል ፡፡ በተጨማሪ ቦርቶ አልካሻ የሚባል የቃጫ ዝሪያ ሆኖ እሾሃማ ሲሆን የሚበቅለውም ቆላማ አካባቢ ላይ ነው ፡፡ ደጋ ላይ አይገኝም ፡፡ ልክ እንደ ቃንጫ ማገርን እና ዘንዲዳውን ለማሰር የሚያገለግል ነው (ቡድን አንድ፣ኪንዶ ዲዳዬ፣2016 ዓ.ም) ፡፡

ከበሩ ፊት በቀኝና በግራ በኩል እንደ ጉበን የሚቆሙት ቆስሌታ የሚባሉ ሲሆኑ ሁለቱም ሰፊ ናቸው ፡፡ ከሀምሳ እስከ ስልሳ ሳንቲ ሜትር ስፋት ያላቸው ሲሆን ቁመታቸው ወደ ሁለት ሜትር የሚጠጋ ነው ፡፡ ከድሮ ጊዜ ጀምሮ ቆስሌታ በብዛት ከዋንዛና ከዶቅማ እንጨት በአዋቂ ባለሙያ ተጠርቦ ይሰራል፤ከላይ እነዚህ ሁለቱን የሚያያይዘው ቆሪያ የሚባል ሲሆን በጣም

እረጅም ሆኖ ውበት አለው ። ሌላው ግድግዳ ሲሆን በግድግዳ ላይ ተሰክቶ እስከ ጣሪያ የሚዘልቅ ማገር(ሆታ) አለ ። ማገሩን ለማጥበቅ ደግሞ ዘምባባ (ቱራ ወይም ጢሄ) እንደ ሀረግ አይነት አለ ፤ በደቦ ከጫካ ተቆርጦ መጥቶ ማገሩን ለማጥበቅ ያገለግላል ። በተጨማሪ ፖሹዋ እሱም ከእንጨት ተሽልቅቆ የሚወጣ ሲሆን ለማሰሪያነት ጥቅም ላይ ይውላል ። ወፍቾን ደግሞ ዘንዲዳዎችን ከዋናው ምሰሶ ጋር ለማገናኘትና ለማያያዝ ይጠቀሙበታል ። (ቃለ መጠይቅ፣ጳውሎስ፣16/09/2016ዓ.ም) ።

በወላይታ ለባህላዊ ቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች ከባለቤቱ ማሳ፣ከጎረቤት፣ከጫካና ከአካባቢው የሚገኙ ሲሆን እነዚህም ለበር መቃን መስሪያ የሚሆኑ፣ለበር መዝጊያ የሚሆኑ፣ወፍቾ፣የማገር እንጨቶች ወዘተ የሚገኙ እንደሆነ መረጃው አመላክቷል ።

**ፎቶ 34 ፦ ለአጨዳ የደረሰ ሰንበሌጥ**





ፎቶ 35፡- ከውጭ በኩል ለጌጥ የሚደረግ




ምንጭ፡- ኦፋ ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣2014 ዓ.ም

ፎቶ 36፡- የወላይታ ባህላዊ ቤቶች መገንቢያ ሆማካ በፎቶ



ምንጭ፡- ኦፋ፣ግንቦት/ 2015.ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ

ፎቶ 37፡- የማገሮቹ ማሰሪያዎች ወፍቾ በፎቶ



ምንጭ፡- ኦፋ፣ግንቦት/2015 ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ

ፎቶ38፡- ተገምዶ ቀለም የተነከረ ቃጫ



ምንጭ፡- ሶዶ ዙሪያ፣ግንቦት/10/2014/ በአጥኚዋ የተነሳ

የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤቶች በብሔረሰቡ እውቀት ላይ ተመስርተው ፤በአካባቢው በሚገኙ ግብአቶች በአካባቢው በሚገኙ ባህላዊ የመስሪያ መሳሪያዎች ፤ ይሰራሉ ። በገሱባ፣ኪንዶ ዲዳዬና ዞዶ ዙሪያ የተመለከትኳቸው መሳሪያዎች በአጥኚዋና በረዳት ፎቶ አንሺ የተነሱ ሆነው እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ።

ፎቶ 39፡- ለቤት ሥራ የሚውሉ መሣሪያዎች




(ምልከታ ጥር፣2016 ዓ.ም) ፡፡







ምንጭ፡- ገሱባ፣ኪንዶ ዲዳዬና ሶዶ ዙሪያ፣በአጥኚዋና በረዳት ፎቶ አንሺ የተነሳ፤ምልከታ ጥር፣2016 ዓ.ም ።







የቤት መስሪያ ቁሶችም ከአካባቢው የሚገኙ ግብአቶች ሲሆኑ ፎቶዎች በገሱባና በሶዶ ዙሪያ ወረዳ በአጥኚዋ የተነሱ ናቸው (ምልከታ፣ጥር2016 ዓ.ም) ፡፡

**ፎቶ 40፡- ለቤት መስሪያ የሚውሉ ቁሳቁሶች**




### 7.5. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ

በዚህ ንዑስ ምእራፍ  የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት አሰራር ማህበረ ባህላዊ ፋይዳ የቀረበ ሲሆን በባህሉ ሁሉም ሰው እንደ ገቢ ምንጩ ቤት ይሰራል ፡፡ ይህም በኢኮኖሚ ደረጃ ሻል ያለ ገቢ ያላቸው ጥሩ ቤት ይሰራሉ ፡፡ ስለዚህ ሁኔታ አቶ ኦልኬ ታንቱ እንደሚከተለው ገልጸዋል « በወላይታ ቤት የገቢ ምንጭን መሰረት አድርጎ የሚሰራ ሲሆን ይህም ከቤቱ ስፋትና ከቤቱ ግብአት አንጻር ሊሆን ይችላል ፡፡ ለምሳሌ ቡራሪያ ተወታትፎ ዝቅ ባለ የአቅም ደረጃ የሚሰራ ቤት ሲሆን ሜሾ  የሚባለው ደግሞ ከፍ ያለ የገቢ ምንጭ የሚፈልግ ቤት ነው ፡፡ በባህሉ ቤት ሲሰራ የቤቱ አይነት የሚወሰነው በኢኮኖሚ፤በማህበራዊ አደረጃጀት፤በሀብት መጠን፤ በስልጣን በመከበር ነው ፡፡ ሌላው መሪ ግድግዳ የሚባሉትም እንደየሰው አቅም በሃያ አራት፣በአሰራ ስምንት፤በአስራ ሁለት ሊሰራ ይችላል» (ቃለ መጠይቅ፣ ኪንዶ፣17/10/2014 ዓ.ም) ፡፡

በወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ሲሰራ የሚዘጋጁ ምግቦች የባለቤቱን የሀብት መጠን መሰረት ያደርጋሉ ስለዚህ ሁኔታ አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ በወላይታ ቤት ሲሰራ ምሰሶ በሚቆምበት ቀን በአብዛኛው የቤቱ ባለቤቶች ቂጣ፣ንፍሮ፣ቦርዴ የሚያዘጋጁ ሲሆን ጥሩ ኢኮኖሚ ካላቸው ተጨማሪ የተለያዩ ባህላዊ ምግቦች እንዲዘጋጁ ያደርጋሉ ፡፡ ሌላው እነዚህ የምግብና መጠጥ ዝግጅቶች በቤቱ ባለቤት ብቻ ሳይሆን በዛ አካባቢ ከሚኖሩ ጎረቤቶቹ፣ዘመዶቹ፣አማቾቹ ቤት የተዘጋጀ ምግብ ይመጣል ይህም ያጋኖ ይባላል (ቃለ መጠይቅ፣ኢሳያስ፣2015 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚገልጸው በባህሉ ቤት ሲሰራ ምሰሶ በሚቆምበት ቀን  የሚዘጋጁ ምግቦችና መጠቶች የባለቤቱን የኢኮኖሚ ደረጃ መሰረት ያደረጉ ናቸው ። ሌላው የአካባቢው ሰዎችም  ምግብና መጠጥ አዘጋጅተው በመምጣት ባለቤቱን ያግዛሉ ።

የቡድን ሁለት ተወያይ የነበሩት አቶ ኢያሱ ገጃቦ ስለዚህ ጉዳይ እንደነገሩኝ በወላይታ ቤት የሚሰራው በመተጋገዝ ሲሆን ይህም በተለመዱት የመረዳጃ ባህሎች አማካይነት ነው ። ከዚህ በተጨማሪ እድር ፣ደቦ ፣ ዘመድ አዝማዶች ፣አማች በጋብቻ የተሳሰሩ ሰዎችም በጉልበት ስራ ያግዛሉ፤ቤተዘመዶች፣ ጎረቤቶች፣ መጠጥና እህል በአካባቢው ከሚገኙ የእህል አይነቶች አዘጋጅተው ያቀርባሉ ። ሌላው ለመስተንግዶ በህብረትና በመተጋገዝ የገቢ መጠናቸውን መነሻ አድርገው የሚሰሩ ሲሆን ቀደም ብለው ልክ እንደ ግብአቶቹ ለሚቀርቡ ምግብና መጠጦች በገንዘብ ዝግጅት ያደርጋሉ (ቡድን ሁለት ሶዶ ዙሪያ፣26/11/2016/ዓ.ም) ።

በባህሉ የባህላዊ ቤቱ አሰራር እንደ ግለሰቡ ኢኮኖሚ ደረጃ ይወሰናል ። ይህም ውጫዊና ውስጣዊ አደረጃጀት ያለው ሲሆን ያንን ለማዘጋጀት መጀመሪያ ላይ ቤት የሚሰራው ግለሰብ ገና ወጣት ከሆነ ከአቅሙ ጋር የሚመጣጠን ቤት ይሰራል፤ ለምሳሌ መጀመሪያ አራት ክንድ ቤት ሰርቶ ከሆነ ቀስ እያለ ኢኮኖሚው ከፍ እያለ ሲሄድ ሰባት ክንድ ድረስ ሊሰራ ይችላል (ቃለ መጠይቅ፣አየለ አይዴ፣14/10/2014ዓ.ም) ።

### 7.6. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ማስዋቢያ ግብአቶች

የቤት ማስዋቢያዎች ቤቱ ሲሰራ አብሮ የሚሰራና ቤቱ ሲጠናቀቅ አገልግሎት የሚሰጥ ተብለው በሁለት መንገድ ሊዘጋጁ ይችላሉ ። በወላይታ ለቤት ውበት የሚሆኑ ግብአቶች የሚገኙት ከአካባቢው ነው ስለዚህ ጉዳይ በሶዶ ዙሪያ የግሼ መንደር ነዋሪ የሆኑት አቶ አየለ አይዴ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

“በወላይታ ለቤት ማሳመሪያ ባራ የሚባል የአፈር አይነት ያለ ሲሆን ባራ የተባለው ቀይ አፈር ስለሆነ ነው ። ቤቱ ተሰርቶ ሲያልቅ ያንን አፈር አምጥተው በውሃ አቡክተው የበር ዙሪያ እንጨቶችን፤የበር መግቢያው ፤የምሰሶ ጫፉ ጉልላት የሚደረግበት ይቀባል፤የምሰሶ ጫፍ ከቤቱ ወደ ላይ የሚወጣው ይቀባል” (ቃለ መጠይቅ፣2015 ዓ.ም) ።

መረጃው እንደሚያመለክተው በወላይታ ባህል ቤቱን ለማሳመር ባራ የተባለ ቀይ አፈር ጥቅም ላይ የሚውል ሲሆን ይህም ቤቱ ተሰርቶ ካለቀ በኋላ በውሃ አቡክተው የበሩን ዙሪያ እንጨቶች፣የበር መግቢያ፣የምሰሶውን ጫፍ ጉልላት የሚደረግበትን ይቀባሉ ።

አቶ ኢያሱ ገጃቦ ደግሞ የወላይታ ባህላዊ ቤትን ለማሳመር ጠቀሜታ ያላቸውን ነገሮች ሲገልጹ ጉንቦ ወይም ጉልላት ለቤት ውበት ለመስጠት ያገለግላል ፡፡ ጉልላት በምሰሶው አናት በሚሰካበት ጊዜ ሁለት ጥቅም አለው ፡፡ ይህም አንደኛ ለቤቱ ውበት መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ ምሰሶውን ዝናብ እንዳያበሰብሰው ይረዳል ፡፡

ሌላው በቤቱ የውስጠኛው ክፍል ለቤቱ ውበት የሚሰጡ ነገሮች አሉ ፡፡ እነዚህም ወደ ቤት ሲገባ መጀመሪያ ላይ የሰው አይን የሚያርፈው በመሃል ሳሎንና ጓዳ የሚለይበት ሳጠራ ላይ በተሰቀሉ የቤት ውስጥ ቁሶች ላይ ነው ፡፡ በባህሉ ሳጠራው ባዶውን ስለማይቆም በሳጠራው አናት ላይ የተለያዩ እንደ ለቦርዴ መጠጫ ከቅልና ከሸክላ አፈር የተዘጋጁ መጠጫዎች ፤የእንጀራ መጋገሪያ ቅል፣የውሃ መቅጂያ ቅል፣ቢላዋ፣የባህል ማንኪያዎች፣ባህላዊ ፎጣ (ዛንዛ)፣መሶብ፣ወንፊት፣እንዲቀመጡ ይደረጋል (ቃለመጠይቅ፣አድማሱ፣ታህሳስ፣2016 ዓ.ም) ፡፡

በመረጃው መሰረት በቤቱ የውስጠኛው ክፍል የሚገኙ ለቤቱ ውበት የሚሰጡ ነገሮች ሲሆኑ ከነዚህም አንዱ ወደ ቤት ሲገባ በመጀመሪያ የሰው አይን የሚያርፍበትና ሳሎንና ጓዳ ለመለየት የሚያገለግል ሳጠራ ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በሳጠራው አናት ላይ የሚቀመጡ የተለያዩ ለቦርዴ መጠጫ የተዘጋጁ ሸክናዎች፣የእንጀራ መጋገሪያ ቅል፣የውሃመቅጂያቅል፣ቢላዋ፣የባህል ማንኪያዎች ባህላዊ ፎጣ (ዛንዛ) መሶብ፣ወንፊት፣የሰፌድ አይነቶች ከቤት ቁስነት ባሻገር ለውበት አገልግሎት ላይ ይውላሉ ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ ለቤቱ ውበት ኮጫ የተባለ ሁለት መንታ ቅርንጫፎች(ባላ) ያሉት እንጨት አለ ፡፡ ይህም በዓመት በዓል ወቅት አባት ፊት የሚቀመጥ ሺንጫ የተባለ ሥጋ ከተበላ በኋላ ቀሪው አባት ፊት ላይ ኮጫ በተባለው ባለ ባላ እንጨት ላይ ይሰቀላል፡፡ ጦርም ከኮጫው ጋር እዛው አልጋው አጠገብ ተሰቅሎ ይቀመጣል ፡፡ ይህም የሆነበት ከአልጋው እንደተነሳ ወዲያው ይዞት ለመሄድ እንዲያመቸው ተብሎ ነው ፡፡ ሌላኛው ባለ ባላ እንጨት  ኮጫ ደግሞ ከምሰሶው ትንሽ ራቅ ብሎ ይቆማል በዛ ላይ ደግሞ ዘር ይሰቀልበታል (ቃለ መጠይቅ፣15/06/2016 ዓ.ም)

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደሚቻለው ባህላዊ ቤቱን ለማሳመር ጠቀሜታ ካላቸው ነገሮች አንዱ ጉልላት (ጉንቦ) ነው ፡፡ ጉልላት በምሰሶው አናት በሚሰካበት ጊዜ ሁለት ጥቅም አለው ፡፡ ይህም አንደኛው ለቤቱ ውበት መስጠት ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ በቤት አናት በሚሰካበት ጊዜ ምሰሶውን ዝናብ እንዳያበሰብሰው መከላከል ነው ፡፡

የቡድን አንድ ተወያይ የነበሩት አቶ ጳውሎስ ስለ ቤት ማስዋቢያ ግብአቶች በተመለከተ ሲገልጹ

ለቤት ውስጥ ማስዋቢያ የሚመረጡ ጎይዲያ የተባሉ እንጨቶች አሉ፡፡ መጀመሪያ ከጣሪያ ጀምሮ ጎይዲያ የሚባሉ እንጨቶች ቤቱ ሲሰራ ሰላሳ ሳ.ሜ ክፍተት እየተደረገ ይሰራል፤ ቤቱን ሲዞርም ሰላሳ ሳ.ሜ ክፍተት ይፈጠራል ፡፡ ቤቱ ውበት እንዲኖረው □ሜሾ ቤት ሲሰራ አስራ አንድ ወይም አስራ ሁለት ክንድ ቤት ላይ ክፍተት የሚደረገው ለቤቱ ውበት ሲባል ነው ፡፡ እነዚህ ለውበት የሚሆኑት እንጨቶች ደግሞ የተመረጡ ናቸው ፡፡ ሀማካው ለማገር ሆኖ ከሀማካው ቀጨጭ የሚለው ለጎይዴ ይመረጣል ፡፡ ሌላው በድሮ ጊዜ ቁርቃ የሚባል እንጨት አለ ይህም ለቤት ማጠናከሪያና ለውበት ይጠቅማል፤ከዚህ በተጨማሪ ሀማካ የሚባል ችፍ ብሎ የሚበቅል እንጨት አለ፤ቀጥ ብሎ የሚያድግ ሆኖ ወደ ጫፍ አካባቢ ቅርንጫፎች ያሉት ሆኖ ከስር ልሙጥ ነው፤ ይህም በጣም ውበት ስላለው ለቤት መስሪያነት ይጠቀሙበታል፤ከላይ እንጨት ተጠርቦ ጉልላት ይደረጋል ይህም ለቤቱ ውበት ይሰጣል፤እቤት ውስጥ ደግሞ ለማስዋቢያ ጋጣታ የሚባል ለጋማ ከብቶችና ለበሬዎች ተለይቶ የሚሰራ ክፍል የከብቶች በረት አለ ይህም ለቤቱ ውበት አሰተዋጽኦ አለው ፡፡ ሌላው ቁርጧ ከቀርከሃ የሚሰራ ሆኖ ቤቶቹን ለመከፋፈልና ለውበት ያገለግላል ፡፡

ወለሉ ለአይን ማራኪ ሆኖ ውበት እንዲሰጥ ደግሞ ጉማሪያ የሚባል ጥምጥም እንጨት ተቀጥቅጦ ተጨምቆ የቤቱ ወለል ይለቀለቃል፤ይህም የቤቱ ወለል በጣም እንዲያብረቀርቅና ውበት እንዲኖረው ያደርጋል፤ በባህሉ ቤቱን በጣም ለማድነቅ ሲፈለግ ጉማሪያ የተለቀለቀ ይመስላል ይላሉ ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ እንደሚያመለክተው ለቤት ውበት የሚሰጡ ጎይዲያ የተባሉ እንጨቶች ቤቱ ሲሰራ ከጣሪያ ጀምሮ  ሰላሳ ሳንቲ ሜትር ክፍተት እየተደረገ ይሰራል፤ ቤቱን ሲዞርም ሰላሳ ሳ.ሜ ክፍተት ይፈጠራል ፡፡ ቤቱ ውበት እንዲኖረው ጋሾ ቤት ሲሰራ ለቤቱ ውበት ሲባል አስራ አንድ ወይም አስራ ሁለት ክንድ ቤት ላይ ክፍተት ይደረጋል፤ ሌላው ቁርቃ የሚባል እንጨት ሲሆን ይህም ለቤት ማጠናከሪያና ለውበት አገልግሎት የሚውል ሲሆን ሀማካ የሚባለው እንጨት በተፈጥሮው በጣም ውበት ስላለው ለቤት መስሪያነት ጠቀሜታ አለው ፡፡

ከዚህ በተጨማሪ  ጋጣታ የሚባል ለጋማ ከብቶችና ለበሬዎች ተለይቶ የሚሰራ የከብቶች በረት ለቤቱ ውበት አሰተዋጽኦ አለው ፡፡ ቁርጧ ደግሞ ከቀርከሃ የሚሰራ ሆኖ ቤቶቹን ለመለየትና ለውበት የሚያገለግል ነው ፡፡

ከላይ ከውበት ጋር ተያይዞ በቤቱ የውስጠኛው ክፍል ለቤቱ ውበት የሚሰጡ ነገሮች ያሉ ሲሆን ይህም ወደ ቤት ሲገባ መጀመሪያ ላይ የሰውን አይን የሚስበው በመሀል ሳሎንና ጓዳ

የሚለይበት ሳጠራ ሲሆን ይህም በባህሉ ባዶውን አይቆምም በሳጠራው አናት ላይ ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶች የሚሰቀሉበት ሲሆን እነዚህም ከሚሰጡት ጠቀሜታ ባሻገር ለውበት ትልቅ ፋይዳ አላቸው ።

**ፎቶ41፡- ሳሎንና ጓዳ የሚለይበት ሳጠራው ጥግና በሳጠራው አናት ላይ ለውበትና ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶች የሚያሳይ**



**ምንጭ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፣በአጥኚዋ ጳጉሜ2፣2014ዓ.ም የተነሳ**

ከላይ በፎቶው ላይ እንደሚታየው ቤቱ የተከፈለበት ቁርጡዋና በላዩ ላይ የተሰቀሉ የተለያዩ ባህላዊ ቁሶች ለውበት የሚሰጡት አስተዋጽኦ ከፍ ያለ ነው ።

ሌላው ከቤት ውበት ጋር ተያይዞ የሚነሳው የከብቶች ማደሪያ ነው ። ይህም ለከብቶች ማደሪያነት ከመዋል ባሻገር ለቤቱ ውበት ከፍ ያለ አስተዋጽኦ አለው ።

ፎቶ42፡- የፈረሶችና የበቅሎዎች ማደሪያ ሲሆን ለቤቱ ውበት አስረጂነት የቀረበ



ምንጭ፡- ወላይታ ዩኒቨርሲቲ ከሚገኘው ባህላዊ ቤት በአጥኚዋ ጳጉሜ2፣2014ዓ.ም የተነሳ


Zanzzaa
(ዛንዛ)
Miizzay eqqiyosa
(የላሞች መቆሚያ)
Para gaaxxaataa
(የፈረስ መቆሚያ)
Gaaxxaataa
(ጋጣ)

ፎቶ 43፡- የፈረሶችና የበቅሎዎች ማደሪያ ሲሆን ለቤቱ ውበት አስረጂነት የቀረበ



### 7.7. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ጉልላት(ጉምቦ) ሥራና ትርጓሜው

ጉልላት(ጉምቦ) ከሸክላና ከእንጨት ተቦርብሮ ከተሰራ በኂላ በቤቱ አናት ላይ ይሰቀላል ፡፡ ጉልላት ቤት በሚሰራ ሰዓት እንደ መለያ የሚያገለግል ሲሆን ትልቅ ቤት ሰርተው ቤቱ አናት ላይ ጉልላት የሚሰቅሉ ሰዎች በማህበራዊ ክብር የተፈቀደላቸው ሰዎች ናቸው ፡፡ ከጌጥነቱ በላይ ሰው አይቶ አይኑ የሚያርፍበት ጉልላት(ጉምቦ) ላይ ስለሆነ ከውበት በላይ ትርጉም አለው፤ የማህበራዊ ክብር ደረጃ መገለጫ ተደርጎም ስለሚወሰድ ነው ፡፡

በወላይታ ባህላዊ ቤት ላይ የሚደረገው ጉልላት(ጉምቧ) በቤቱ አይነት የሚወሰን ሲሆን ሁሉም ሰው ቤቱ ላይ አያደርግም፤ሜሹዋ ላይ፤ዙፋ ላይ፤ጉላንታ ላይ የሚደረጉ አይነት ነገሮች ቡራሪያ ላይ አይደረጉም ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቡራሪያ ለወጣት የሚሆን የመጀመሪያ ቤት ስለሆነ ቤቱ ይሰራና ይተዋል፤ ወጣቱም አቅም ሲያገኝ የጉልላት አምሳል ያሰራና ምሰሶ ጫፍ ላይ ያደርገዋል ፡፡ ሌላው በብሔረሰቡ ዎራቴ የሚባሉ ሰዎች ያሉ ሲሆን ዎራቴ ማለት በጦርነት ጠላት ገለው፤ትላልቅ አውሬዎችን በተለይ ጎሽ፣ዝሆን፣ነብርና ቀጭኔ ገለው የመጡ ሰዎች የገደሏቸውን አውሬዎች የሰውነት ክፍሎች እንደ የነብር ቆዳ እና የዝሆን ጥርስ የመሳሰሉ የግዳይ ምልክቶችን ጉልላት (ጉምቦ) አናት ላይ ያደርጋሉ፤ይህን የሚያደርጉት ለምስክርነትና ለጌጥ አገልግሎት እንዲውል ነው ፡፡

የቡድን ሁለት ተወያይ የነበሩት አቶ ወልደ ማርያም ከምሰሶ በላይ በቤቱ አናት ላይ የሚሰቀለው ጉምቦ (ጉልላት)ሁለት አይነት ሲሆን የራሱ ትርጉም አለው ፡፡ ጉልላት(ጉምቦ) የማህበራዊ ክብር ልዩነትን መሰረት አድርጎ ይሰራል ፡፡ አንደኛው ከሸክላ የተሰራ የእሳት ማንደጃ (እንክሪት) ሲሆን ከታች በኩል ሰፊና እንደ ክብ አይነት ሆኖ ሙሉ የጉምቦ(ጉልላት) ቅርጽ ጠብቆ የሚሰራ ሆኖ ሁለተኛው ደግሞ ከእንጨት ተቦርብሮ የሚሰራ ነው ፡፡

በወላይታ ባህላዊ ቤት አናት ላይ የሚደረገውን ጉልላት(ጉምቦ) ሁሉም ሰው አያደርግም፤ይህም የሚወሰነው ወላይታ ውስጥ በሚሰሩት የቤት አይነቶች ሲሆን፤ የሚደረጉት የጌጥ አይነቶችም ልክ አሁን ሰው እንደ አቅሙ የሚሰራው አይነት ቤትን መሰረት የሚያደርግ ሲሆን ለአብነት ያህል ሜሹዋ ቤት ላይ፤ዙፋ ቤት ላይ፤ጉላንታ ቤት ላይ የሚደረጉ የጌጥ አይነቶች ቡራሪያ ቤት ላይ አይደረግም ፡፡ ለወጣት የሚሆን የመጀመሪያ ቤት ይሰራና ይተዋል፤ወጣቱም አቅም ሲያገኝ በጉምቦ አምሳል ያሰራና ባለው ምሰሶ ጫፍ ላይ ሰክቶ ጉምቧ ቤት እንዲኖረው ያደርጋል (ቃለ መጠይቅ፣08/12/2014 ዓ.ም) ፡፡

አቶ ወልደ ማርያም ከላይ በቀረበው ሀሳብ ላይ የሚከተለውን ተጨማሪ መረጃ ሰጥተዋል፡-

ዎራቴ የሚባሉ ሰዎች አሉ፤ዎራቴ ማለት በጦርነት ጠላት ገለው፤ትላልቅ አውሬዎችን በተለይ ጎሽ፣ዝሆን፣አውራሪስ፣አንበሳ፣ነብርና ቀጭኔ ገለው የመጡ ሰዎች እነዚህን የግዳይ ምልክቶችን ጉልላት(ጉምቦ) አናት ላይ ያደርጋሉ ። ይህን የሚያደርጉበት ምክንያት ለምስክርነት ሲሆን ብዙ ግዳይ የጣለ ሰው እዛ ቦታ ላይ ማድረግ በማይችልበት ሰዓት ዙቃኑዋ የሚባል የዚህ የግዳዩን ምልክት ቤቶችን የሚያቆዩባቸው መሳሪያዎች አሉ፤ያንን መሳሪያ ልክ ሰውዬው በሞተ ጊዜ ነው ወጥቶ የሚሰቀለው እንደዚህ አይነቱን በአብዛኛው ለጌጥ ይሆናሉ ብለው የሚያስቀምጡ ሲሆን የዝሆን ጥርስ(ዛሊያ)፣ እሱን በተለየ ቅርጽ አሰርተው አንደኛ ለጌጥ አገልግሎት ሁለተኛ ተምሳሌቱ ግዳይ መጣሉን ዎራቴ መሆኑን በሚገልጽ ደረጃ መሆኑን ለመግለጽ ሲሆን ሦስተኛው ማህበራዊ ክብር ነው ቤት በሚሰራ ሰዓት አንዱ መለያ ትልቅ ቤት ሰርተው ቤቱ አናት ላይ ጉልላት የሚሰቅሉ ሰዎች በማህበራዊ ክብር የተፈቀደላቸው ሰዎች ሲሆኑ ከዚህ በተጨማሪ ከጌጥነቱ በላይ ማንኛውም ሰው ያንን ቤት ሰርቶ የቤቱ ትልቁ ውበት የሚታየው ከውስጥ በኩል ሲሆን ከውጪ በኩል ማህበራዊ ክብሩን አድርጎ ሰው መጀመሪያ ቤቱን ሲያይ አይኑ የሚያርፍበት ጉልላት(ጉምቦ) ላይ ስለሆነ ጉልላት ከውበት በላይ ትርጉም ያለውና የማህበራዊ ክብር ደረጃ መገለጫም ስለሆነ ነው (ቃለ መጠይቅ፣15/12/2014 ዓ.ም) ።

ከላይ የቀረበው ይዘት እንደሚያስረዳው ጉምቦ ሁለት አይነት ሲሆን አንደኛው ከሸክላ ተሰርቶ በጉምቧ ቅርጽ የሚደፈን ሆኖ ልክ እንደ እንክሪት(የሸክላ ማንደጃ) አይነት ሆኖ ሙሉ የጉምቧ(ጉልላት) ቅርጽ ጠብቆ የሚሰራ ሲሆን ሁለተኛው ከእንጨት ተቦርብሮ የሚሰራ ነው ። በወላይታ ባህላዊ ቤት ላይ የሚደረገውን ጉልላት(ጉምቧ) ሁሉም ሰው አያደርግም፤ይሄ ደግሞ በቤቱ አይነቶች ይወስናል፤ሜሹዋ ላይ፤ዙፋ ላይ፤ጉላንታ ላይ የሚደረጉ አይነት ነገሮች ቡራሪያ ላይ አይደረግም ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቡራሪያ ለወጣት የሚሆን የመጀመሪያ ቤት ስለሆነ ቤቱ ይሰራና ይተዋል፤ ወጣቱም አቅም ሲያገኝ በጉምቦ አምሳል ያሰራና ምሰሶ ጫፍ ላይ ያደርገዋል፤ ሌላው በብሔሩ ዎራቴ የሚባሉ ሰዎች ያሉ ሲሆን ዎራቴ ማለት በጦርነት ጠላት ገለው፤ትላልቅ አውሬዎችን በተለይ ጎሽ፣ዝሆን፣አውራሪስ፣አምበሳ፣ነብርና ቀጭኔ ገለው የመጡ ሰዎች ሲሆኑ እነዚህን የግዳይ ምልክቶችን ጉምቦ አናት ላይ ያደርጋሉ፤ይህን የሚያደርጉት ለምስክርነት ነው ። ከዚህ ጋር በተያያዘ መልኩ የዝሆን ጥርስ(ዛሊያ) የተባለውን በተለየ ቅርጽ አሰርተው ለጌጥ አገልግሎት እንዲውል የሚያደርጉ ሲሆን በተጨማሪም ተምሳሌቱ ግዳይ መጣሉን ዎራቴ መሆኑን ለመግለጽ ነው ። ሌላው ቤት በሚሰራ ሰዓት እንደ መለያ የሚያገለግል ሲሆን ይህም ትልቅ ቤት ሰርተው ቤቱ አናት ላይ ጉምቧ የሚሰቅሉ ሰዎች በማህበራዊ ክብር የተፈቀደላቸው ሰዎች ሲሆኑ ከጌጥነቱ በላይ የሰሪውን በማህበራዊ ክብር ከፍ ማለት የሚያሳይ ነው ።

ሰው አይቶ አይኑ የሚያርፍበት ጉምቦ ላይ ስለሆነ ከውበት በላይ ትርጉም አለው ።

**ፎቶ 44፡-ከእንጨት ተጠርቦ የተሰራ ጉልላት ፎቶ**



**ምንጭ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፣በአጥኚዋ የተነሳ፣2014ዓ.ም**

የቡድን ሁለት ተወያይ የነበሩት አቶ ኢሳያስ ኡሻቾ ከወላይታ ባህላዊ ቤት ውበት ጋር በተያያዘ የሚከተለውን ሀሳብ አስቀምጠዋል፡-

በወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጥ ውበት የሚሰጡ ነገሮች ይገኛሉ። በመጀመሪያ ወደ ቤት ሲገባ የሰው አይን የሚያርፍበት በመሀል ሳሎንና ጓዳ የሚለይበት ሳጠራ አለ፣ሳጠራው ብቻውን የራሱ ውበት ቢኖረውም ባዶውን አይቆምም፤በሳጠራው አናት ላይ የተለያዩ የባህል እቃዎች እንደ ሸክና፣እንጀራ መጋገሪያ ቅል፣የውሃ መቅጂያ ቅሎች፣ቢላዋ፣የባህል ማንኪያዎች፣ባህላዊ ፎጣ (ዛንዛ) ይቀመጣል። በሳጠራው ላይ መሶብ፣ወንፊት፣የሰፌድ መስፊያ ሳታ የሚባልም እንዲቀመጥ ይደረጋል (ኢሳያስ፣23/11/2014 ዓ.ም) ።

ኮጫ የተባለ ባለ ባላ እንጨት ለቤቱ ውበት ከመስጠት ባሻገር በበዓል ወቅት ሺንጫ የተባለ ሥጋ ከተበላ በኋላ የቀረው ሥጋ በቤቱ አባወራ (አባት) ፊት ለፊት በኮጫ ላይ ይሰቀላል ። ሌላው ጦርም ከኮጫው ጋር እዛው ተሰቅሎ ይቀመጣል ። ይህም የሆነበት ከአልጋው እንደተነሳ ወዲያው ይዞት ለመሄድ እንዲያመቸው ተብሎ ነው ። ሌላው ኮጫ ደግሞ ከምሰሶው ትንሽ ራቅ ብሎ ይቆማል በዛ ላይ ዘር ይሰቀልበታል ። እቤት ውስጥ የገበታ መጫዎቻዎች ቡና እስከሚደርስ እየተዝናና እንዲቆይ ይረዳል ። ሌሎች እቤት ውስጥ የሰውዬው አልጋ ሰው ሲመጣ በጥሩ ቦታ እንዲቀመጥ ፣ውበት ያላቸው መቀመጫዎች እንዲኖረው ይረዳል ። ወደ ጓዳ በሚገባበት ጊዜ የተለያዩ ከሸክላ የተሰሩ የቤት ቁሶች ይገኛሉ ። ሌላው ሳሎን ውስጥ ኢንኪራቲያ የተባለ ምድጃ ይቀመጣል ። የተለያዩ የባህል ባርጩማዎች ባለሦስት እግር፣ባለድጋፍ ባርጬማ ይቀመጣል ። ቤቱ እራሱ ውበት እንዲኖረው ተደርጎ ነው የሚሰራው(ኢሳያስ፣23/11/2014 ዓ.ም)።

የወላይታ ጉላንታ ቤት ዘጠኝ ቦታ ክፍተት እንዲኖረው ተደርጎ ይሰራል ፡፡ ይህ ደግሞ በባህሉ በዓለም ላይ ካሉ ፕላኔቶች ቁጥር ጋር ግንኙነት አለው ተብሎ የሚታሰብ ቢሆንም ወደፊት በስፋት ሊጠና የሚገባ ጉዳይ ነው? ከዘጠኝ ክፍተቶች በላይ መሀል ላይ ያለው እንደ ፀሐይ ነው የሚሰራውም በነጭ ኮባ ነው ይህም እንደ ፀሀይ ያንጸባርቃል ይህም ጉዳይ ከባህላዊ አስትሮኖሚ ጋር ተያይዞ መጠናት ያለበት ነው (ኢሳያስ፣ጥር/2016 ዓ.ም) ፡፡

### 7.8. የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት የቀለም ምርጫና ትርጓሜ

ቀለም በጥንት ጊዜ በሰው ልጅ ባህላዊ አኗኗር ላይ እንደመሰረታዊ ፍላጎት ሆኖ አገልግሏል ፡፡ ቀለም በሰው ልጅ አእምሮ እና ስሜት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ያለው ሆኖ ቁርኝቱም ከነሱ ጋር ነው ፡፡ ቀለም ለያዘው ስዕላዊ መልክ የመጀመሪያ ምንጩም ተፈጥሮ ነው ፡፡ ስለሆነም አረንጓዴ በእስልምና ሃይማኖት አስተምህሮ እንደ ቅዱስ ነገር ሲታይ የነበረ ሲሆን ወጣ ባሉ አከባቢዎች እንደ ጥንካሬ ይመለከቱት ነበር ሰማያዊ ቀለም ደግሞ መንፈስ፣ እውነት እና ሰማይ ነው ፡፡ ነገር ግን የቀለም ስዕላዊ ምልከታው ከባህል ባህል ሊለያይ ይችላል ፡፡ በሌላ ጎን ደግሞ በግልጽ እንደሚታወቀው ከሆነ ጥቁርና ነጭ ቀለም መንታ ሀሳብ ወይም ተቃርኖ ተደርጎ ይታያሉ ፡፡ በሌላ አገላለጽ በአንዳንድ ባህሎች ነጭ እንደ ጭቆና እና መታፈን ተደርጎ ሲወሰድ በሌሎች ደግሞ ጥቁርም በዚህ መንገድ ይወሰዳል (Jung, 2016)፡፡

የወላይታ ቤት ሲሰራ ካረጀ ቤት የወጣ ጥቁር ቀለም ያለው ሳር እና ለቤቱ መስሪያነት ከመጣው አዲሱ ሳር የተወሰነውን በበሩ መግቢያ አካባቢ ማሰር የተለመደ ነው ፡፡ ጥቁር ቀለም የወላይታ ህዝብ ቁጡና ጠንካራ መሆኑን ለማሳየት ነው፡፡ ቀዩ የወላይታ ህዝብ መስዋዕትነት ከፍሏል የሚለውን ለማመልከት ሲሆን ከድሮ ጀምሮ ወላይታ አገሩን ለማስፋት ከብዙዎች ጋር ተዋግቶ ብዙ መስዋዕትነት ከፍሏል ፡፡ ሌላው ባራ የሚባል ቀይ አፈር ሲሆን ይህም ቀይ አፈር ተበጥብጦ የበሩ መዝጊያውና መቃኑ ይቀባል፤ህዝቡ በአካባቢው የሚገኙ ግብአቶችን በመጠቀም ቤቱን ያሳምረል (አየለ አይዴ፣ ቡድን አንድ፣ሶዶ ዙሪያ፣2015ዓ.ም) ፡፡

ቀለም በሥነ ሕንፃ የውጭ እና የውስጥ ንድፍ ውስጥ ጠቀሜታው የጎላ መሳሪያ በመሆኑ ስሜትን በማነሳሳትና በማስተካከል የማይረሱ ቦታዎችን መፍጠር ይችላል ፡፡ በቤት አሰራርውስጥ የቀለም አጠቃቀም የቤቱን ክፍል ከመለወጥ ባሻገር ተግባሩን ሊያሳድግ ይችላል (Lewis,1930) ፡፡

በቀረበው መረጃ መነሻነት ጥቁር ብሔረሰቡ ደማችን ጥቁር ነው በማለት እራሳቸውን የሚገልጹበት ሆኖ ጥቁር መልክን ሳይሆን በወላይታ ባህል የህዝቡ ቁጡነትና የጀግንነት ምልክት ተደርጎ ይገለጻል ፡፡ ቀዩ ቀለም የወላይታ ህዝብ መስዋዕትነት ከፍሏል የሚለውን ለማመልከትና የጦረኝነት መገለጫ ሲሆን ቢጫ

ቀለም ደግሞ የመስፋፋት ተምሳሌት ነው ፡፡ ህዝቡ እነዚህን ቀለማት በራሱ እውቀትና ጥበብ ከአካባቢው በሚያገኛቸው ግብአቶች የሚሰራቸው ናቸው ፡፡ ጥቁር ቀለም የወይራ ፍሬን ከጥቀርሻና ከቅቤ ጋር በማፍላት ጥቁር ቀለም ይፈጥራሉ ፡፡ ቢጫ ቀለም ለመስራት ጎይዲያና ጎሌ የተባሉ የእንጨት ዝርያዎችን ፍቀው ከወቀጡ በኋላ በጥብጠው ሁለት ቀናት በማሳደር ያዘጋጃሉ ፡፡ ቀዩ ቀለም ደግሞ እንሶስላ(ዎሶሉዋ)፣ዲልጬዋ ከተባለ የሀረግ ፍሬ፤ባራ ከሚባል ቀይ አፈር ተዘጋጅቶ የበሩ መዝጊያ ይቀባል (ቃለ መጠይቅ፣ኡኩሌ ጥላሁን፣ኦፋ፣2015ዓ.ም) ፡፡

የተጠቀሱት ቀለሞች በመግቢያ በር በግራና በቀኝ በኩል በሚቆሙ እንጨቶች (ቆስሌታ)፣የበሩ ድምድማት በሚገኝበት የላይኛው ክፍል (ቆሪያ)፤ከታች ተረግጦ የሚገባበት (ጎጪሊያ)፤ተብለው በሚጠሩት ላይ ይቀባሉ ፡፡ እነዚህ ቀለሞች ከብሔረሰቡ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህዝቡ ቤቶቹን ለማሳመር ከአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት ባህላዊ ቤቶቹን ይቀባል ፡፡ ቀለሞቹ በባህላዊ ልብሶች፣በሰንደቅ ዓላማና ሌሎች ባህላዊ ክዋኔዎች ሲኖሩ ተግባር ላይ ይውላሉ (ቃለ መጠይቅ፣ታደሰ ኮይራ፣15/10/2015ዓ.ም) ፡፡

የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ የቀለም አተረጓጎም ከሰው ወደ ሰው ቢለያይም በጥንት ጊዜ ሥልጣኔ ሰዎች ብዝሃነትን ለመሰየም ባደረጉት ትግል በጋራ የሚያስማማንን የቀለም ምንነትን ሰርተው አስቀምጠዋል፡፡ ስለሆነም የመጀመሪያዎቹ ቀለማት የሚተሳሰሩት ከሀይማኖታዊ አስተምህሮዎች መስተጋብርና አቅጣጫዎች ጋር ነው፡፡ በጥንት ጊዜ በማዕከላዊ አሜሪካ ውስጥ በነበሩ በማያዎች እይታ የምስራቃዊ፣ የሰሜናዊ ፣የምዕራባዊ እና የደቡባዊ አቅጣጫ ትርጉም የምናገኘው በቀይ፣ በነጭ፣ በጥቁርና ቢጫ ቀለማት ጋር ሲሆን በጥንት ቻይናዎች እይታ ደግሞ ምስራቅ፣ ደቡብ፣ ምዕራብ፣ ሰሜን እና ማዕከላዊ ሀገራት የሚተሳሰሩት ከሰማያዊ፣ ከቀይ፣ ከነጭ፣ ከጥቁር እና ከቢጫ ቀለማት ጋር ነበር፡፡ አልፎ አልፎ ሃይማኖታዊ እይታው ደግሞ ከፍተኛውን ጠቀሜታ ይሰጠዋል፡፡ በሌላም ጎን ለቡዲስቶች ቢጫ ቀለም ከየዋህነት ጋር ተገናኝቶ ጥቅም ላይ ሲውል የነበረውም በመነኮሳት መኖሪያ ሰፈር ነበር፡፡ ለክርስቲያኖች ደግሞ ነጭ ቀለም የሚያመለክተው ንጹህ ልቦናና የጸዳ ማንነት ሲሆን ይህ የሆነውም ነጭ ቀለም ከሁሉም ንጹህ ተደርጎ ስለሚታይ ነበር ( Hui-Chih Yu፣ 2014) ፡፡

በወላይታ ቤት ለማስዋብ የሚሆኑ የቀለም አይነቶች ከላይ በዝርዝር የተገለጹ ሲሆን ለዚህም አሰረጂ እንዲሆን ከስር ቀለሞቹ በፎቶ ቀርበዋል ፡፡

**ፎቶ 45፡- የወላይታ ህዝብ የሚጠቀማቸው ቀለሞች**



**ምንጭ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ፣2015ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ**

እንደ አቶ ኢያሱ ገለጻ ወላይታ ውስጥ ከሚገኙ ባህላዊ ልብሶች መካከል ሀዴ[56] ተብሎ የሚጠራው ባህላዊ ልብስ ቀለማት ጥቁር፣ቀይና ቢጫ እንደሆኑ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች አሳይተዋል ፡፡ እነዚህ ቀለሞች ከብሔረሰቡ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህዝቡ ቤቶቹን ለማሳመር ከአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት ባህላዊ ቤቶቹ ላይ የሚቀባው የቀለም አይነቶች ከባህላዊ ልብሶቹ ጋር ተመሳሳይ ቀለሞች ነው ፡፡ ስለሆነም ከላይ ለመግለጽ እንደተሞከረው ወላይታ በቅርበት ከሚገኙና ጎረቤት ከሆኑ ብሔረሰቦች ጋር ባህላቸው ተወራራሽ ነው ፡፡ ስለዚህም ባህላዊ ልብሶቻቸው ጥቁር፣ቢጫና ቀይ ቀለማት ሲሆኑ እነዚህ ቀለማት የመመሳሰል ሁኔታ እንደሚታይባቸው ይነገራል (የቡድን ውይይት፣አፋ)

ብሔረሰቡ እነዚህን ቀለማት ከተለያዩ ግብአቶች የሚያዘጋጁ ሲሆን ጥቁር ቀለምን ለማዘጋጀት የወይራ ፍሬን ከጥቀርሻና ከቅቤ ጋር በማፍላት ጥቁር ቀለም ይፈጥራሉ ፡፡ ቢጫ ቀለምን ደግሞ ጎይዲያና ጎሌ የተባሉ የእንጨት ዝርያዎችን ፍቀው ከወቀጡ በኋላ በጥብጠው ለሁለት ቀናት በማሳደር ሲሰሩ ቀዩን

---

56 . ድንጉዛ ሀዲያ፣ሴሪ ሀዲያ፣ጉመራ ሀዲያ እና ፓታላ ሀዲያ የተባሉ አራት ባህላዊ የልብስ አይነቶች የጥለታቸው ቀለሞች ጥቁር፣ቀይና ቢጫ ናቸው ፡፡ ቢጫ ቀለም ጮዲያ ከሚባል ሳር እና ወይቤታ ከሚባል ቅርፊት ተዘጋጅቶ ቁሊያ (ማሰሮ) ውስጥ ይጨመራል ፡፡ ቢጫ ቀለም የብሔረሰቡ ተስፋ ነው ፡፡ ጥቁር ቀለም ደግሞ የወይራ ፍሬን ከጥቀርሻና ከቅቤ ጋር በማፍላት ይሰራሉ ፡፡ መልካቸው አሁን ያለው አይነት ጠይም ቢሆንም ጥቁር ወላይታ በሚል ነው የሚገልጸው ፡፡ በተፈጥሮ የደም ከለር ቀይ ነው፤የወላይታ ህዝብ ደማችን ጥቁር ነው ብለው ያምናሉ ፡፡ ሌላው ቀይ ቀለም ለማዘጋጀት ምሶሉዋ(እንሶስላ)፤ዲልጩዋ የተባለ የሀረግ ፍሬ ፤ዙምቤ ሱታ የሚባል( የመዥገር ደም ) ቀላቅለው ቀይ ቀለም ይፈጥራሉ ፡፡ በመጨረሻም እነዚህን ቀለሞች የቤቱ መግቢያ ቆሪያ ላይ፤ ቆስሌታ ላይ ይቀባሉ ፡፡ ሌላው ሳጠራ (ቃርጣ) ቤቱን ለመክፈል በሚያገለግለው አናት ላይ ይቀባል (ቡድን ሁለት፣ሶደ ዙሪያ፣2015 ዓ.ም) ፡፡

ቀለም ደግሞ እንሶስላ (ምሶሉዋ) ፣ ዲልጬዋ ከተባለ የሀረግ ፍሬ እና ባራ ከሚባል ቀይ አፈር ያዘጋጃሉ(ቡድን ውይይት፣ጥላሁን፣ኦፋ፣2015 ዓ.ም) ፡፡

ከጥንት ጀምሮ ህዝቡ እራሱን የሚገልጽባቸው ጥቁር፣ቀይና ቢጫ ቀለሞችን ከአካባቢው በሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት በቀለሞቹ በግራና በቀኝ መግቢያ በር ላይ በሚቆሙ እንጨቶች (ቆስሌታ)፤የበሩ ድምድማት የሚኖርበት የላይኛው ክፍል (ቆሪያ)፤ከታች ተረግጦ የሚገባበት(ጎጪሊያ)፤ተብለው በሚጠሩት ላይ በመቀባት ቤቱን ያሳምራሉ እነዚህ ቀለሞች ከብሔረሰቡ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህዝቡ ቤቶቹን ለማሳመር ከአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት ባህላዊ ቤቶቹን ይቀባል ፡፡ ቀለሞቹ በወላይታና አጎራባች በሆኑት እንደ ጋሞ ባሉ ብሔረሰቦች በባህላዊ ልብሶችና ሌሎች ባህላዊ ክዋኔዎች ሲኖሩ ተግባር ላይ ይውላሉ(ቃለ መጠይቅ፣ኢያሱ፣ወልደማርያም፣2015ዓ.ም) ፡፡

ቀለም በኪነ-ጥበብ፣ በሥነ-ጽሑፍ እና ስለሰው ዘር አመጣጥና ዕድገት ዘርፍ የሚያጠና ሳይንሳዊ ስዕል ሆኖ የተለያዩ ባህሎችንና ትረካዎችን ለመግለጽ የሚቆም ምልክት ነው ፡፡ ቀለማት ዘርፈ-ብዙ ጥቅም ያላቸው ሲሆን ትስስራቸውም ባህልን ከሌላ ባህል ጋር ለማስተሳሰር ብሎም አንድ ባህል ከጊዜ ወደ ጊዜ ሳይጣረስ በውስጡ ለራሱ ባለው ቅቡልነት ተሳስሮ እንዲዘልቅ ይረዳል ፡፡ አንድ ተመሳሳይ ቀለም በውስጡ ከብዙ ነገሮች ጋር ግንኙነት ሊኖረው የሚችል ሆኖ ሊቆም ይችላል ፡፡ የቀለም ትርጉም ዘርፈ-ብዙ እይታ እና ትስስር ሲኖረው ይህም አንድ ቀለም የሚቆምለት የራሱ ግላዊ፣ ባህላዊ እና አጠቃላይ መሰረት ያለው ምስል ነው፡፡ የቀለም ትርጉም ደግሞ እንደየ ሁኔታዎች ሲለያይ በየጊዜው ሊቀያየር ይችላል ፡፡ ቀለም ሃይማኖታዊ ሀሳቦችን ወይም አንቀጾችን የሚይዝ ሆኖ በውስጡ ለአንድ ነገር ብቻ የተሰጠ ትርጉም ያለው ምልከታ ሊሆን ይችላል (Matheus,2018) ፡፡

ስለቀለማት የሚያትቱ ምልከታዎች ቢኖሩም የቀለማቱ ትርጉም እንደየአካባቢው ይለያያል፡፡ በዚህም መሰረት ከቦታ ወደ ቦታ ከሰው ልጅ ብዝሃነትና ሃይማኖት ጋር የተቆራኙ የተለያዩ ትርጉሞችን ይሰጣሉ

በቡድን አንድ ተወያይ ከነበሩት መካከል አቶ ወልደ ማርያም በ2015ዓ.ም የብሔረሰቡን የቀለም ምርጫ እንደሚከተለው ገልጸዋል፡-

ጥቁር፣ቀይና ቢጫ ቀለሞች ወላይታ ውስጥ ከብሔሩ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ ናቸው፤አንደኛው በቀይና ቢጫ መካከል የሚያልፍ ጥቁር ዝግዛግ ሀዲድ ያለው ሆኖ የሚሰራው ከቀይ፣ቢጫና ጥቁር ቀለሞች ነው ፡፡ እነዚህን ቀለሞች ህዝቡ በራሱ እውቀትና ጥበብ የሚሰራቸው ሲሆኑ ከነዚህ ቀለማት የመጀመሪያውን ቦታ የሚይዘው ጥቁር ነው ፡፡ ጥቁር ብሔረሰቡ እራሱን የሚያይበት ደማችን ጥቁር (ሱታይ ካሬታ) ጥቁር ወላይታ በማለት እራሱን የሚገልጽበት ሆኖ ጥቁር መልክ ሳይሆን በወላይታ ባህል የህዝቡን ቁጡነት፣ደመ መራራነቱን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት ነው ፡፡ ሌላው ጥቁርነቱ

የጀግንነት ምልክት ተደርጎ ይገለጻል ። ቀዩ የብሔረሰቡ የጀግንነት፣የጦረኝነት፣የወራሪነት መገለጫ ሲሆን ቢጫው ቀለም ደግሞ የመስፋፋት ተምሳሌት ነው ።

የወላይታ የባህል ልብስ ሀዴ ተብሎ የሚጠራ ሲሆን የሀዴ ቀለም አይነቶችም ጥቁር፣ቀይና ቢጫ እንደሆኑ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች ጠቁመዋል። እነዚህ ቀለሞች ከወላይታ ብሔረሰብ ህይወት፣ማንነትና ታሪክ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህዝቡ ቤቶቹን ለማሳመር ከአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት ባህላዊ ቤቶቹን የሚቀባው የቀለም አይነቶች ከባህላዊ ልብሶቹ ጋር ተመሳሳይ ቀለሞች ነው ።

በቤት አሰራርውስጥ የቀለም አጠቃቀም የቤቱን ክፍል ከመለወጥ ባሻገር ተግባሩን ሊያሳድግ ይችላል ስለሆነም እነዚህ ቀለሞች ከብሔረሰቡ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ በመሆናቸው ህዝቡ ቤቶቹን ለማሳመር ከአካባቢው ከሚገኙ ግብአቶች በማዘጋጀት ባህላዊ ቤቶቹን ይቀባል ። ቀለሞቹ በወላይታና አጎራባች በሆኑት እንደ ጋሞ ባሉ ብሔረሰቦች በባህላዊ ልብሶችና ሌሎች ባህላዊ ክዋኔዎች ሲኖሩ ተግባር ላይ ይውላሉ።

የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ በቅድመ-ታሪክ ጊዜ ውስጥ ሰዎች በሚኖሩበት በዋሻዎች ግድግዳዎች ላይ በአካባቢያቸው የሚገኙ ነገሮችን እንደ ጥቁር ማንጋኒዝ ከሰልን ከቀይ ጠመኔ ጋር ይጠቀሙ ነበር። እየቆዩ ሲሄዱ የቤቱን ግድግዳ ኖራ ለመቀባት የኖራ ወተትን ይጠቀሙ ነበር (Matheus፡ 2018).

ፎቶ 46፡-ወላይታ የሀዴ አይነቶች




ምንጭ፡-ከወላይታ ዩኒቨርሲቲ እና ከሶዶ ዙሪያ ጳጉሜ2/2014ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ

መግለጫ

1.ድንጉዛ ሀዲያ፡- ንጉስና ሹማምንቶች የሚለብሱት ሲሆን የወንዶች ልብስ ነው፡፡

2.ሴሪ ሀዲያ፡- የጦር ሜዳና የአደን ሰዎች የሚለብሱት ሆኖ ከሌሎቹ የሚለየው በዘርፉ ነው፡፡

3.ጉመራ ሀዲያ፡-ወጣቶች ማህበራዊ ሽግግር ሲያደርጉ (ከግርዛት ሲወጡ አገልድመው የሚለብሱት ነው፡፡

4.ፓታላ ሀዲያ ፡- በጊሞ (በሀብት ማከማቸት) ስርዓት ሴቶች የሚለብሱት ሆኖ ቀሚሱ ወቲያ ተብሎ ሲጠራ አላባሹ ቆቶቲያ ይባላል፡፡

## ምዕራፍ ስምንት

## በወላይታ ባህላዊ የቤት አሰራር ውስጥ የታዩ የለውጥና የቀጣይነት ገጽታዎች

በዚህ ምእራፍ ስር የተለወጡና የቀጠሉ ነገሮች ምንድናቸው ?ለለውጡ ምክንያት የሆኑ ነገሮች እንዲሁም ለውጡ ከመቼ ጀምሮ እንደተከሰተ የሚገልጽ ሲሆን ይህም ጥናቱ በተካሄደባቸው ወረዳዎች በምልከታ፣በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት የተገኙ መረጃዎች ቀርበዋል ፡፡

ስለወላይታ ባህላዊ ቤት ለውጥና ቀጣይነት ለመመርመር መነሻ የሆኑት የምሁራንና ሥራዎቻቸው መሰረታዊ መርሆች ፤መመዘኛዎች እና ማጣቀሻዎች ሲሆኑ እነዚህም ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡

አንድ የባህል መገለጫ (ለምሳሌ የቤት አሰራር) እንዴት አንዳንድ ገጽታዎቹን ለዘመናት ሳያስለቅቅ እንደያዘ (continuity) በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ሌሎች ገጽታዎቹን ከማኅበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ቴክኖሎጂያዊ ለውጦች ጋር እያጣጣመ እንደሚቀይር (change) መተንተን ላይ ነው ፡፡

- **ቀጣይነት (Continuity)** አንድ ብሔረሰብ ለማንነቱ፣ ለእምነቱና ለአለም አተያዩ መሰረታዊ የሆኑ እሴቶችን፣ ቅርጾችንና ትርጉሞችን ከትውልድ ወደ ትውልድ የሚያስተላልፍበት ሂደት ነው፡፡ በቤት አሰራር ረገድ ይህ የሚገለጸው በቤቱ መሰረታዊ ቅርጽ፣ በምሰሶዎች ትርጓሜ፣ በክፍሎች አደረጃጀትና ከሥርዓተ-ጾታ ወይም ከማኅበራዊ መደብ ጋር በተያያዙ የቦታ አጠቃቀሞች ነው፡፡
- **ለውጥ (Change):** በብሔረሰቡ ውስጥ በሚፈጠሩ ውስጣዊና ውጫዊ ግፊቶች ምክንያት የባህል መገለጫዎች የሚቀየሩበት ሂደት ነው፡፡ ለውጥ በአዳዲስ የግንባታ ቁሶች፣ በዘመናዊ ቴክኖሎጂ፣ በግሎባላይዜሽን፣ በትምህርትና በአዲስ የአኗኗር ዘይቤ ግፊት ሊከሰት ይችላል፡፡

ይህ ንድፈ ሐሳብ "ባህል እየጠፋ ነው" ከሚለው ጥንታዊና ተስፋ አስቆራጭ ንድፈ ሐሳብ ይልቅ ባህል ራሱን የሚያድስበትንና የሚቀጥልበትን መንገድ በአዎንታዊ እይታ ይመለከታል (Dundes, 1969) ፡፡

Henry Glassie "Folk Housing in Middle Virginia" በሚል በ1975 ባቀረበው ስራው ላይ፣ ባህላዊ ቤቶችን እንደ ቀላል የግንባታ ውጤት ሳይሆን፣ እንደ "የቀዘቀዘ የሰው ልጅ ባህሪ" (frozen human behavior) ይመለከታቸዋል ፡፡ ቤቶች የሰሪዎቻቸውን የአእምሮ ካርታ (mental template)፣ ማኅበራዊ መዋቅርና የአለም እይታ እንደሚያንጸባርቁ ይከራከራል ፡፡ Glassie, የቤቶችን ቅርጽ፣ የግንባታ ቴክኒክና አጠቃቀም በመተንተን ከጀርባቸው ያለውን ባህላዊ ሰዋሰው ማግኘት እንደሚቻል ያሳያል ፡፡ ይህ አካሄድ አንድ ተመራማሪ በወላይታ ቤት ላይ የሚታየውን ቀጣይነት እና ለውጥ እንዲመረምር ያስችለዋል ፡፡ ሌላው

Smith, J. A. (2020) **የለውጥና ቀጣይነት መመዘኛዎች በማለት ቀጥሎ የገለጻቸው መሰረት ተደርገው የባህላዊ ቤቶቹ ለውጥና ቀጣይነታቸው ተፈትሾ ቀርቧል ፡፡**

1.ታሪካዊ አውድ

2.ባህላዊ ልምዶች እና ወጎች

3. የስነ-ህንፃ እና የቦታ አጠቃቀም

4.እሴቶች እና እምነቶች

5. የቋንቋ እና የቃል ወጎች

6.አርቲስቲክ አገላለጽ

7. የአስተዳደር እና የአመራር መዋቅሮች

8.ማህበራዊ አወቃቀሮች እና ሚናዎች መሆናቸው ይጠቀሳል ፡፡

የምሁራን ሥራዎችና መመዘኛዎች መሰረት የሚከተሉት ውጤቶች ተገኝተዋል ፡፡

- **ለውጥ የታየባቸው ገጽታዎች** (Aspects of Change)

ከዘመኑ ጋር ተያይዞ በሚመጡ ተጽዕኖዎች ምክንያት ቤቱ በተለያዩ መንገዶች ለውጥን ያስተናግዳል፡፡

- **የግንባታ ቁሶች** (Construction Materials)፡- ከባህላዊው ሳርና እንጨት ይልቅ ቆርቆሮ ለክዳን፣ ሲሚንቶና ብሎኬት ለግድግዳ መጠቀም የቴክኖሎጂና የኢኮኖሚ ለውጥ ውጤት ነው፡፡ ይህ ለውጥ የቤቱን ጥንካሬና የአገልግሎት ዘመን ሊያሻሽል ይችላል፡፡
- **የአገልግሎት ለውጥ** (Functional Change)፡- ባህላዊ ቤቶች ለመኖሪያነት ብቻ ሳይሆን ለቱሪስት መስህብነት፣ለሙዚየምነት ወይም ለማኅበራዊ መሰባሰቢያነት ማገልገል ሲጀምሩ ተግባራዊ ለውጥ እንዳሳዩ ያሳያል (ለምሳሌ የዶ/ር ዘብዲዎስ ሙዚየም)፡፡
- **ውበትና ማስጌጫ** (Aesthetics and Decoration)፡- ባህላዊ ቀለማት በዘመናዊ የፋብሪካ ምርት ቀለሞች ሊተኩ ይችላሉ፡፡ እንዲሁም የውስጥ ማስጌጫዎች ከባህላዊ ቁሶች በተጨማሪ ዘመናዊ እቃዎችን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡

- **የባለሙያ እጥረት ፦** ቀደም ሲል ባህላዊ ቤትን ይሰሩ የነበሩና በቤቱ ስራ ወቅት በተለያዩ ሙያዎች የሚታወቁ ሰዎች በዘመናዊነት ተጽዕኖ የተነሳ ቆርቆሮ ቤት መስራት በመጀመራቸው ቀደም ሲል ከነበረው ቁጥራቸው አንሷል።

ከላይ በዝርዝር የቀረቡት ጽንሰ ሀሳቦች ለለውጡ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች በጥቅሉ እንደሚከተለው ቀርበዋል ።

(1) **ተፈጥሯዊ**

- ✓ የአየር ንብረት / የአካባቢ ለውጦች
- ✓ የሳር መሬት የነበረው ቦታ ወደ እርሻ መሬትነት መቀየር፤
- ✓ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የሳር ማሳ ማነስ ፤

(2) ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጉዳዮች

- ✓ ቤቱን ለመገንባት የሚያስፈልገው ወጪ ከፍተኛ መሆን ፤
- ✓ የህዝብ እድገት እና የመሬት እጥረት

(3) **የ Mass culture' መስፋፋት**

- ✓ የዘመናዊ ቁሳቁሶች ወደ ሀገር ውስጥ መግባት
- ✓ ዘመናዊነትና ቴክኖሎጂ ባሳደረው ተጽእኖ ፤
- ✓ ለዓለምአቀፍ/ለምዕራባውያን አርክቴክቸር መጋለጥ

(4) **የማዕከላዊ መንግስት ፖሊሲዎችና ማህበረባህላዊ እሴት ተጠርሶ**

- ✓ የመንግስት ፖሊሲዎች እና የእቅድ ደንቦች
- ✓ የከተማ ልማት እና ዘመናዊ የአኗኗር ዘይቤዎች

**ቀጣይነት የታየባቸው ገጽታዎች** (Aspects of Continuity)

ባህላዊው ቤት የብሔረሰቡን መሰረታዊ እምነትና ማንነት የያዘ በመሆኑ አንዳንድ ገጽታዎቹ ሳይለወጡ ቀጥለዋል ።

- **ቅርጽና ትዕምርታዊ ትርጉም** (Form and Symbolic Meaning): የቤቱ ክብ ቅርጽ፣ ወደ ላይ የሚሾለው አናት፣ እንዲሁም የማዕከላዊ ምሰሶ (ቱሳ) የሚሰጣቸው ትርጓሜዎች የብሔረሰቡን ኮስሞሎጂ (የዓለም አፈጣጠር ግንዛቤ) እና ፍልስፍና ያንጸባርቃሉ። እነዚህ በቀላሉ አይለወጡም ምክንያቱም ከማንነቱ ጋር የተሳሰሩ ናቸው።

- **የውስጥ አደረጃጀትና ማኅበራዊ ሥርዓት** (Internal Layout and Social Order): በቤት ውስጥ ለወንድ፣ ለሴት፣ ለእንግዳና ለቁሳቁስ የሚመደቡ ቦታዎች የማኅበረሰቡን የሥራ ክፍፍል፣ የሥርዓተ-ጾታ ሚና እና የእንግዳ አቀባበል ሥርዓት ያሳያሉ፡፡ ይህ አደረጃጀት የብሔረሰቡን ሥርዓት የሚያንጸባርቅ በመሆኑ በቀላሉ አይቀየርም፡፡
- **የግንባታ ሥርዓትና እምነት** (Construction Rituals and Beliefs): ቤት ሲሰራ የሚከናወኑ ሥርዓቶች (ለምሳሌ ቦታ ምርጫ፣ የምሰሶ ተከላ፣ የምረቃ ሥነ-ሥርዓት) ከብሔረሰቡ እምነትና መንፈሳዊ ህይወት ጋር የተቆራኙ በመሆናቸው ቀጣይነት ይኖራቸዋል፡፡

ከላይ ከቀረቡት በተጨማሪ ለቀጣይነት ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች የሚከተሉት ናቸው ፦

- ✓ ቃላዊ አገላለፆችና ድርጊታዊ ባህላዊ ክንውኖች
- ✓ የባህሉ ከዋኞች ማህበራዊ ስፍራ (ቦታ)
- ✓ የቤቱ መጠሪያ ቦታዎችና ባህላዊ ድርሻቸው
- ✓ ማንነትና ገላጭ ባህላዊ ሀብቶች

በባህሉ በአሁኑ ሰዓት ሳር ቤቶቹ ቁጥራቸው እየቀነሰ ወደ ቆርቆሮ ቤቶች እየተቀየሩ ነው፡፡ እነዚህ ቤቶችም ለውጣቸው በከፊል ነው ፡፡

የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ አገር በቀል የቤት አሰራር ጥበብ በየወቅቱ ነባር የአሰራር ልምዶችን በማስቀጠል፤ከተለያዩ ማህበረሰባዊ እና ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦችን በመቀበል፣ ሽግግሮሽን በመቀበል እንዲሁም ልምምድን በማካተት የማህበረሰቡን ወቅታዊ ፍላጎት ከግምት ውስጥ በማስገባት በእድገት ውስጥ ይገኛል Rapoport (1969) and Rudofsky (1964) ፡፡ ሌላው ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብ ቀጣይነት ከቦታ፣ከጊዜ እና ቁሳዊ ሁኔታ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለው ሲሆን ከቅርጽ፣ከአገልግሎት፣ከማህበረሰባዊ ጉዳዮች አንጻር የተለያየ ትርጉም ሊሰጠው ይችላል (Philokyprou, 2015) ፡፡

ይህም ቆርቆሮ ቤቶቹ ሳር ቤቶቹ ውስጥ ያሉ ቁሶችን ይዘው ቀጥለዋል (ቃለመጠይቅ፣ሲሳይ፣ህዳር12/2015ዓ.ም ይህ መረጃ በለውጥና ቀጣይነት እሳቤ ሲቃኝ ለውጥ በጊዜ ሂደት ውስጥ ቀጣይነት ባለው ማንነት ውስጥ ያለ ልዩነት ሲሆን ለውጥ ሲከሰት የሚታይ ልዩነት አለ፤ ከሚታየው ልዩነት ጋር በለውጥ ውስጥ ያለው ጉዳይ ይቀጥላል ፡፡ ሆኖም ቀጣይነት እና ለውጥ በባህላዊ ሽግግር አውድ ውስጥ የሚተገበሩ ተለዋዋጭ ጥንዶች እንደሆኑ በ (Nisbet P.197) ተገልጿል፡፡

በተጨማሪም በጽንሰ ሀሳብ ክፍል እንደቀረበው ለውጥ ማንነትን እየጠበቀ በጊዜ ውስጥ የሚፈጠር ልዩነት ነው ፡፡ ለውጥ ሲከሰት የሚታይ ልዩነት ያለ ሲሆን ይህም ልዩነት የሚታይበት የጊዜ ቆይታ አለ፡፡ የለውጡ ርዕሰ ጉዳይ ማንነት እንደቀጠለ ነው ፡፡ ሌላው የቀጣይነት እና የለውጥ ጽንሰ ሀሳቦች

**ተለዋዋጭና ጥንድ ሆነው በባህላዊ ሽግግር አውድ ውስጥ በተደጋጋሚ የሚተገበሩና በማህበረ-ባህላዊ ስርዓቶች ለውጦችን የሚያሳዩ ናቸው** (Galvin 2009; Catley et al. 2013, in Berkes et al. 2016:2).**ለዚህም በባህላዊ ቤት ውስጥ የምናገኘው የላሞች ማደሪያ በቆርቆሮ ቤት ውስጥ መኖሩን የሚገልጽ አስረጂ በፎቶ ቀርቧል ፡፡**

**ፎቶ47፡- ቆርቆሮ ቤት ሆኖ በከፊል ባህላዊ ቁሶችን ያያዘ**





**በጽንሰ ሀሳብ ክፍል እንደተገለጸው የቀጣይነት ፅንሰ-ሀሳብ ያለፈውን፣ የአሁኑን እና የወደፊቱን ማዋሃድን የሚያካትት ሆኖ ቀጣይነት ትውፊትን በማላመድ እና በመለወጥ ዘላቂ ጠቀሜታው የሚጠበቅበትን ውህደት ይወክላል** (Smith 1982:127). **ከዚህ በተጨማሪ ይህ እሳቤ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ ቀጣይነት በባህላዊ ቤት አሰራር ውስጥ በሚለው እሳቤ ስር ሦስት ነጥቦች ቀጥሎ ቀርበዋል ፡፡**

- ባህላዊ ማንነት፡- ባህላዊ ቤቶች የማህበረሰቡን ባህላዊ ወግ ፣ እሴት እና ልማድ በመግለጽ አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ ። ይህንንም ብዙ የማህበረሰብ አባላት ጠብቀው እያኖሩት ያለ ክዋኔ ነው ።
- የቤት መስሪያ ቁሳቁስና የአሰራር ዘዴዎች፡- በተወሰኑ አካባቢዎች አገር በቀን (ባህላዊ) የግንባታ ቁሳቁስ እንዲሁም ባህላዊ የቤት አሰራር ዘዴዎች ተጠብቀው ጥቅም ላይ እየዋሉ ነው።
- ወካይነት፡- እንደ የቤት መሰረት አጣጣል ፤የግድግዳ ጠረዝ እና ክበብ አሰራር እንዲሁም ቀለም አመራረጥ ያሉ ጉዳዮች ማህበረሰባዊና ሀይማኖታዊ ትርጉም እንዲሰጡ ተደርጎ የመስራቱ ሁኔታ እንደቀጠለ ነው (Oliver ,2006)፡፡

በለውጥ ንዑስ ርእሰ ጉዳይ ስር ሦስት ጉዳዮች ቀጥሎ ቀርበዋል ።

ዘመናዊ ተጽእኖ ፡- የዓለም በአንድ መንደር ስር መሆን፤የውጪው ዓለም የቤት አሰራር እንዲሁም የከተማ ልማት እንቅስቃሴዎች አባህላዊ ቤት አሰራር ቅርጽ እና መሰረት አጣጣል ላይ አይነተኛ ተጽእኖ ፈጥረዋል።

ቴክኖሎጂና መሳሪያዎች ፡- በአሁን ወቅት ባህላዊ ቤቶች እንደ ኤሌትሪክ ዝርጋታ፣ የውሃና ፍሳሽ እንዲሁም የኢንተርኔት ዝርጋታዎች አካተው እየተገነቡ ነው።

አገልግሎት ፡-የማህበረሰቡ የአኗኗር ዘዴ ከመለወጡ አንጻር ባህላዊ ቤቶች ዘመናዊ ክፍሎችን እና የተለያዩ አገልግሎት የሚሰጡ ስፍራዎችን አካተው አእየተገነቡ ነው (Rapoport, 1969)፡፡

**ፎቶ 48፡- የወላይታ ዙፋ ቤት ውጫዊ ገጽታ**



ምንጭ፡- ሶዶ ዙሪያ፣በክቡር ዶ/ር ዘብዲዮስ ጫሞ የተገነቡ ባህላዊ ቤቶች የተገኘ፤ በአጥኚዋ የተነሳ፣11/11/2014ዓ.ም) ።

እንደ (Qian, 2021), ለገጠር አካባቢ ልማት የማህበረሰባዊና ምጣኔ ሀብታዊ ለውጦች ፤ የተቀናጀ የገጠርና ከተማ ልማት መኖር አይነተኛ ምክንያቶች ናቸው፡፡ይህም ለመኖሪያ ቤቶች ቅርጽና አቀማመጥ ለውጥ መኖር፤ የአኗኗር ዘይቤ መቀየር፤እንዲሁም የከተማና የገጠር ትስስር ሂደት አይነተኛ ማሳያ ናቸው፡፡በተጨማሪም እንደ Qian (ibid) ሀሳብ የዘመኑ የዘርፉ ተመራማሪዎች እንዳስቀመጡት በኢትዮጵያ ዘመናዊነት ከመስረጹ በፊት በርካታ ባህላዊ የቤት አሰራር ስልቶች እንደነበሩ ያስቀምጣሉ ፡፡ ይህም ባህላዊ ቤቶች ተምሳሌነታቸው ከትውልድ ትውልድ ቀጣይነት እንዳይኖረው ተጽእኖ ፈጥሯል፡፡ቢሆንም የአለም የቤት አሰራር ስልት በብዙ የእድገት እርከን ውስጥ ማለፉ እሙን ነው፡፡ በተጨማሪም ይህ እሳቤ በጥናቱ ዳራ ሲቃኝ Sherif and Sabry (2000) እንደገለጹት ጥንታዊ ሰዎች በዛፍ ስር ፤በዋሻ እና የተለያየ ቅርጽ ባላቸው አለቶች ውስጥ ይኖሩ ነበር ፡፡ እንዲሁም Sherif and Sabry (ibid) ስለ ግብጾች፣ጀርመኖች፣እስካንዲኒቪያኖች እንዲሁም አጠቃላይ ስለ አውሮፓ የቤት አሰራር ስልት አስቀምጠዋል፡፡ ጎንለጎን የአንድ ቦታ ወይም አካባቢ የቤት አሰራር ስልት ቀጣይነት ከቦታ እና ከጊዜ ጋር ፣ከአሰራር ቅርጽ ጋር፣ ቤቶችን ከአገር በቀልነትና ባህላዊነት አንጻር ከመመደብ አንጻር፤ ከሚሰጡት አገልግሎትእንዲሁም ከማህበረሰብ ማንነት ጋር ትስስር እንዳለውም ገልጸዋል ፡፡ ጉዳዩ ሰፊ ንባብ እና ትርጉምም እንደሚያስፈልገው ምልከታውን አስቀምጧል (Philokyprou, 2015)፡፡

በመስክ በተደረገው ምልከታና በቃለመጠይቅ በተገኘው መረጃ ከላይ በፎቶ የቀረበው የዙፋ ባህላዊ ቤት ሲሆን አሰራሩም ባህላዊውንና ዘመናዊውን ስልት ተከትሎ የተሰራ መሆኑን በመስክ መረጃዎች ሊረጋገጥ ችሏል፡፡ እነዚህ ዘመናዊ የተባሉ እንደ በር፣ ሲሚንቶ የመሳሰሉት ግብአቶች ለባህላዊ ቤቱ ጥቅም ላይ እንዲውሉ የተደረገው ቤቱ ረጅም ጊዜ እንዲቆይ ታሳቢ ተደርጎ የተሰራ እንደሆነ ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት ተችሏል ፡፡

አጠቃላይ በጊዜ ሂደት ውስጥ ወደ ቆርቆሮ የተለወጠው የወላይታ ባህላዊ ቤት ውስጥ ቀደም ሲል ከሳር ቤቱ ቀጥለው የመጡ ቁሶች አሉ ፡፡

ኮጫ በባህላዊ ቤት ውስጥ የሚገኝ ሆኖ በበዓል ወቅት ጮማ ስጋ ተሰቅሎበት አባት አጠገብ የሚቀመጥ ቁስ ነው ፡፡ ይሁንና በመስክ የተገኘው መረጃ እንደሚያመለክተው በአሁኑ ሰዓት የተጠቀሰው ቁስ በቆርቆሮ ቤት ውስጥ ይገኛል ፡፡

Barre Toelken "The Dynamics of Folklore" (1996) በሥራው ላይ ባህል በ"ቀጣይነት" እና በ"ተለዋዋጭነት" (continuity and variation) መካከል ባለው ውጥረት ውስጥ እንደሚኖር ያስረዳል፡፡ አንድ የባህል መገለጫ ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፍ ዋናው ጭብጡ (continuity) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ እያንዳንዱ ተራኪ ወይም ፈጻሚ የራሱን አሻራ (variation/change) እንደሚያሳርፍበት ያብራራል፡፡

ይህንን በቤት አሰራር ላይ ስንተገብረው፣ የወላይታ ቤት መሰረታዊ ቅርጽና ትርጓሜ እንደተጠበቀ ሆኖ እያንዳንዱ ገንቢ እንደየአቅሙና ፍላጎቱ ጥቃቅን ለውጦችን ሊያደርግ እንደሚችል ለመረዳት ያስችላል፡፡

ሌላው Alan Dundes በፎክሎር ጥናት ውስጥ የነበረውን "ባህል እየጠፋና እየተበላሸ ይሄዳል" የሚለውን አስተሳሰብ የተቃወመ ምሁር ነው፡፡ በጽሑፉ "The Devolutionary Premise in Folklore Theory" (1969) ላይ፣ ፎክሎር በአዲስ መልክ እየተፈጠረና ከዘመኑ ጋር እየተጣጣመ እንደሚቀጥል ይሞግታል፡፡ ይህ ሃሳብ፣ በወላይታ ቤት አሰራር ላይ የሚታየው ለውጥ የባህሉ መጥፋት ሳይሆን፣ ህያው ሆኖ ለመቀጠል የሚያደርገው መንገድም መሆኑን ለመረዳት ያግዛል፡፡

**ፎቶ 49፡-ባህላዊ የስጋ መስቀያ ኮጫ**




ከስር በፎቶ የተቀመጠው ሳር ቤት ባህላዊውን አሰራር ተከትሎ የተሰራ ቢሆንም ባህላዊ ቤቱ ውስጥ መካተት የሌለበትን የጭቃ ምርግ ይዟል ፡፡ ይህ ደግሞ የሳር ቤቱን ለውጥ ያመለክታል፡፡

ፎቶ 50፡- የጭቃ ምርግ የተደረገበት ባህላዊ ቤት




አቶ አየለ አይዴ እንደነገሩኝ ከስር በፎቶ የቀረበው የወላይታ ጉላንታ ቤት በባህላዊና በዘመናዊ ግብአቶች የተሰራ መሆኑን በመስክ በምልከታና በቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል፡፡ ቤቱ ተጨማሪ ዘመናዊ ግብአት እንዲኖረው ያደረገው ምክንያት ቤቱ በሳር የሚሰራ በመሆኑ ድንገተኛ የእሳት አደጋ ሊያጋጥም ይችላል ከሚል ፍርሀት የተነሳና ከግብአት እጥረት መሆኑን ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል (ቃለ መጠይቅ፣2014 ዓ.ም) ፡፡

ሌላው የጉላንታ ባህላዊ ቤት በር መዝጊያው በባህላዊ ጥበብ የሚዘጋጅ ነው ፡፡ ይሁንና ከላይ ቀርቦ እንደነበረው አሰራሩም ሆነ ግብአቶቹም ዘመናዊውንና ባህላዊውን መንገድ ተከትለው የተሰሩ ናቸው ፡፡

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው በሩ ከላሜራ ቆርቆሮ የተሰራ ቢሆንም የበሩ መዝጊያ ከብረት የተዘጋጀ ሆኖ በሩን ለመዝጋት የሚያገለግሉት ግብአቶች ባህላዊ ናቸው ፡፡

ፎቶ 51፡- ለዚህም አስረጂ የጉላታ ባህላዊ ቤት ቀጥሎ ቀርቧል ፡፡



ምንጭ፡- ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ ፣ዋናው ጊቢ የካቲት/2015ዓ.ም በአጥኚዋ የተነሳ

አቶ ኢያሱ ሲገልጹ በወላይታ ዩኒቨርሲቲ በዋናው ጊቢ የሚገኘው ባህላዊ ቤት ለሙዚየም አገልግሎት በመሰራቱ በስሩ በርካታ ባህላዊ ቅርሶችን ይዟል ፡፡ ይህ ቤት አጀማመሩ የባህላዊውን ስልትና ግብአቶችን በመጠቀም የተሰራ ነው ፡፡ ከቦታ መረጣ ጀምሮ የግድግዳ እንጨት፣የምሰሶ እንጨት፣የጣሪያ ስራ፣የቤት ክዳን ወይም ሳር ማልበስ ድረስ ባህላዊውን ግብአትና አሰራር ተከትለው የተከናወኑ ሲሆን ከሳር ክዳን በኋላ ከስር ቀጫጭን የፌሮ ብረት፣አርማታና ቆርቆሮ ተደርጎባቸዋል ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቤቱ የወላይታ ባህላዊ ቁሶች የሚገኙበት ሙዚየም በመሆኑ በሳር ብቻ ከተሰራ ድንገት ቤቱ በእሳት ቢቃጠል ውስጥ የሚገኙት ቅርሶች ተጎድተው ይጠፋሉ ከሚል ስጋት የተነሳ ዘመናዊ ግብአቶች ተጨምሮበታል

ከላይ ከቀረበው በተጨማሪ በወላይታ ባህልና ቱሪዝም ጊቢ የሚገኘው ባህላዊ ቤት ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ የባህላዊውን አሰራር ተከትሎ የተሰራ ነው ፡፡ ይሁንና መጨረሻ ላይ ቤቱን ለማሳመር በሚል የወላይታ ባህላዊ ቤትን ባህላዊ ልብስ ቀለም የያዘ መጋረጃ በሩ ላይ ማድረጋቸው ዘመናዊ ግብአቶችን እንደመጠቀም ነው ፡፡ ይህ ደግሞ ቤቱ ላይ ቀደም ሲል የነበሩ መቀጠላቸውንና ለውጥ መኖሩን በምልከታና በቃለመጠይቅ ከተገኘው መረጃ መረዳት ተችሏል ፡፡

### I, የቆርቆሮ ቤት

በዚህ ንዑስ ርእስ ስር የቆርቆሮ ቤት በወላይታ ብሔረሰብ እንዴት ይታያል እንዲሁም ደግሞ ሳር ቤቱ ከቆርቆሮ ቤቱ ጋር ያለውን ልዩነት የሚመለከቱ መረጃዎች ቀርበዋል፡፡

የቆርቆሮ ቤት በብሔረሰቡ ያለውን እይታ እንዲሁም ባህላዊ ሳር ቤት ከቆርቆሮ ቤት ጋር ያለውን ልዩነት አስመልክተው የዴሪ ነዋሪ የሆኑት አቶ መቶሳል ሲገልጹ የቆርቆሮ ቤት ከዘመናዊነትና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው ፡፡ ባህላዊ ቤቱ ከቆርቆሮ የሚለየው አንደኛ በክረምት ወራት ሙቀትን የመያዝ ሀይል አለው ፡፡ ለምሳሌ ቤት ውስጥ እሳት ከነደደ ሙቀቱን አምቆ ይይዛል ፡፡ በበጋ ወራት ደግሞ እርጥበትን ወደ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ቤቱ እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል (ቃለመጠይቅ፣ኢያሱ፣06/05/2014 ዓ.ም) ፡፡

አቶ አድማሱ እንደነገሩኝ የወላይታ ባህላዊ ቤት ሙቀትንና ቅዝቃዜን አመጣጥኖ ይይዛል (ቃለመጠይቅ፣05/06/2015 ዓ.ም) ፡፡

ከቀረቡት መረጃዎች መረዳት እንደተቻለው የቆርቆሮ ቤት ከዘመናዊነትና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን በህዝቡ ዘንድ የሚወደደው ግን ባህላዊው ሳር ቤት ነው ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ባህላዊ ቤቱ በክረምት ሙቀትን የመያዝ ሀይል ሲኖረው በበጋ ወራት ደግሞ እርጥበት ወደ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ቤቱ እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ሳር ቤቱ ውስጥ ከሚነደው እሳት የሚወጣው ጪስ ጓሮ ውስጥ ላሉ ተክሎች ጠቀሜታ እንዳለው ነው የተገለጸው ፡፡

ከላይ የቀረበው መረጃ በጽንሰ ሀሳብ ሲቃኝ አጠር ባለ ምልከታ በ Iron Age and the Etruscan period ወቅት በግንባታ ቁሳቁሶች እና በቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ይሰጥ የነበረው አጽንኦት  በቅሪት አካል ጥናት ግኝት አተረጓገም ላይ አይነተኛ ተጽእኖ አድርጓል ፡፡ እንዲሁም በባህላዊ የቤት አሰራር ልምምድ ቀጣይነት ላይ ጥላውን አጥልቷል ፡፡ ይህም በቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ከታየው ለውጥ ይልቅ በቤት መስሪያ ግብአቶች ላይ የታየው ለውጥ በቤት ግንባታ ጥበብ ላይ  እንዲኖር ያረገው አይነተኛ ለውጥ ዋና ምክንያት ሆኖ ተጠቅሷል፡፡ እንደ ግድግን ያለ ምንም ማጠናከሪያ እራሱን  ችሎ እንዲቆም የማድረግ ዘዴ እና በተጠረበ ድንጋይ ቤትን  የመስራት ዘዴ የሚገመገሙት ወይም የሚዳኙት በሚሰጡት አገልግሎት ሳይሆን ቁሶችን በማነጻጸርና በማበላለጥ ነው Pallottino (1975) ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ነገር ግን የግንባታ ስልት ቀጣይነትን ከተለያዩ የግንባታ ግብአቶች አንጻር ማየት በቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ላይ የሚኖረውን አረዳድ  ያጠነክራል ፡፡ እንዲሁም በሂስቶሪቻል ፔሬድ ያለውን እይታ ከመገዳደር አንጻር ተቀሚታ አለው ፡፡

ከመነሻው እንደ Pallottino (1975) ያሉ ምሁራን የ Etruscan የቤት አሰራር ስልት ወይም ጥበብ ሽግግር የግሪክና የምስራቃዊያን ተጽእኖ ውጤት እንደሆነ አሳይተዋል፡፡ አክለውም የዘመናዊ የቤት መስሪያ ቁስ በእነዚህ አገራት መመረት Etruscan የቤት አሰራር ስልት ላይ ለውጥ አምጥቷል ፡፡

ከአስር ዓመታት በኋላ Torelli (1985) የተለየ ምልከታ አስቀምጦ ነበር፡፡ይህም ተጽእኖው ከሌሎች አገሮች ተጽእኖ ይልቅ በአገሪቱ ውስጥ በነበሩት ተጽእኖ ፈጣሪ ማህበረሰብ ተጽእኖ ምክንያት የመጣ ለውጥ መሆኑን ገልጿል፡፡ በአገሪቱ ውስጥ የነበሩት ተጽእኖ ፈጣሪ ማህበረሰቦች ያላቸውን ሀብት ለማሳየት ከነዚያ አገራት የሚገቡትን የቤት መስሪያ ቁሳቁስ ይጠቀሙ እንደነበርም እንደ ማሳያ አቅርቧል ፡፡

በተቃራኒው ቅርብ በሆነ የ Izzet (2007) እና Rohner (1996), ምልከታ አዳዲስ የሆኑ የግንባታ ቁሶችን መጠቀምን ከከተማዊነት ጋር አያይዞ አቅርቧል ፡፡ ይህም በግንባታ ቁሶች እና በግንባታ ስልት ላይ የሚታዩ ለውጦች አዳዲስ የከተማ አሰራር ልምዶችን ወደራስ ለማምጣት ከመነጨ የማህበረሰቡ ፍላጎት አንጻር እንደሆነ አትቷል ፡፡ ይህም ምልከታውን የለውጡ ምክንያት የግንባታ ቁሶች ለውጥና የቴክኖሎጂ ለውጥ ይልቅ የአገነባብ ስልት ላይ አጽንኦት መሰጠት እንዳለበት አስምሮበት አልፏል ፡፡ ስለሆነም ምሁራኖች ለውጡ በማህበረሰቡ የባህርይ ለውጥ ማምጣትና ባህልን ከማደስ አንጻር እንደሆነ ትኩረት እንዲያረጉ አድርገል፡፡ ይህም የአመለካከት ለውጥ የቴክኖሎጂ ሽግግር ላይ ትኩረት ከመስጠት ይልቅ የቤት አሰራር ጠባያት መለያየት ላይ ትኩረት እንዲሰጥ ጠቆመቀ ሰቶ አልፏል ፡፡

የኪንዶ ዲዳዬ ነዋሪ የሆኑት አቶ ኢሳያስ እንደ ነገሩኝ ዘመናዊነት ተጽእኖ እየፈጠረበት ቆርቆሮ መስራት ተጀመረ እንጂ አሁንም አባቶቻችን ልጄ ለኔ የሚመቸኝ ይሄ ሳር ቤቱ (ባህላዊ ቤቱ) ነው በማለት ወደ ቆርቆሮ ቤት ለመግባት ፍቃደኛ አይደሉም (ቃለመጠይቅ፣05/08/2014 ዓ.ም)

ሌላው ወ/ሮ ሸዋዬ ሲገልጹ ሳር ቤት ውስጥ የከብቶች ትንፋሽ ለቤቱ ሙቀት ይሰጣል ፡፡ እሳት ሳር ቤት ጓዳ ውስጥ የሚነድ ሲሆን ቆርቆሮ ቤት ደግሞ ውጪ ወይም ማዕድ(ኩሺና) ቤት ይነዳል ፡፡ ስለሆነም ከሳር ቤቱ ውስጥ የሚወጣው ጪስ ጓሮ ውስጥ ያሉ የእንሰት፣የቡና ተክሎችና ጓሮ አትክልቶች ቶሎ እንዲያድጉ ያግዛል ፡፡ የወላይታ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች አማራጭ አጥቶ የዘመናዊነት ተጽእኖ እየተፈጠረበት ወደ ቆርቆሮ ቤት መግባት ጀመረ እንጂ የሚመርጠው ባህላዊ የሳር ቤትን ነው (ቃለመጠይቅ፣04/04/2016 ዓ.ም) ፡፡

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው ዘመናዊነት በሳር ቤት ላይ ተጽእኖ በማሳረፉ ሰው ግድ ሆኖበት ቆርቆሮ ቤት መስራት ጀመረ እንጂ ቆርቆሮ ቤትን አይመርጠውም ፡፡ ሳር ቤት ብዙ ጥቅም አለው ፡፡ ለምሳሌ፡- ከብቶቻቸውን ሌባ እንዳያጠቃ አብረው እንዲያዩ፣እንዲቀመጡ ያደርጋቸዋል ፡፡ ሌላው ቤቱ ተመጣጣኝ የሆነ የአየር ንብረት አለው፤ በበጋ የተመጣጠነ ሙቀት ያለው ሲሆን በክረምት ላይ ደግሞ

የብርድ ስጋት፣የበሽታ ስጋት የለም ፡፡ በተጨማሪም ከሳር ቤት የሚወጣው ጪስ ደግሞ ለተክሎች አስፈላጊ በመሆኑ ህዝቡ ለኑሮ የሚመርጠው ባህላዊ ሳር ቤቱን ነው ፡፡

## II. የሳር ቤቶች ቁጥር ዝቅተኛ የሆኑበት ምክንያቶች

በዚህ ንዑስ ምእራፍ ስር የወላይታ ባህላዊ ቤቶች ቁጥር እየቀነሱ የመጡበት ምክንያቶች ቀርበዋል ፡፡ ስለዚህ ጉዳይ አቶ አድማሱ ሲገልጹ ባህላዊ ቤቶች እየተመናመኑ ለመሄዳቸው ብዙ ምክንያቶች አሉ ፡፡ የህዝብ ቁጥር በመጨመሩ ምክንያት የመሬት ጥበት መከሰት ፤ የሳር መሬቶች እየጠበቡ መምጣት፤የሳር መሬቶች ከሌሉ ሳር ስለማይኖር የወላይታ ባህላዊ ቤትን መስራት አይቻልም ፡፡ ዋናው የሳር መሬት እየጠፋ ሲሄድ ሰው ሌላ አማራጭ የለውም ሳር ከሌለ ደግሞ ያ ቤት ዋጋ አይኖረውም፤እድሜም የለውም፤በየዓመቱ ሳሩ እየተፈተሸ በስርዓት መከደን አለበት ፡፡ ያ ካልሆነ ቤቱ ይበላሻል፤ማፍሰስ ይጀምራል ፡፡ ማፍሰስ ከጀመረ ደግሞ ውስጥ ላለው ሰው ምቾት አይሰጥም ፡፡ ከዚህ የተነሳ ጊዜውን እየጠበቀ ቤቱ ሳይበላሽ ክዳኑ ይፈተሻል ፡፡ ይህ ደግሞ መለወጥ አለበት፤ ፡፡ በዚህም ቆርቆሮ ቤት ምንም አማራጭ የሌለው ጉዳይ ሆነ፤ማንም ሰው እንደምንም ተጣጥሮ ቆርቆሮ ቤት እንዲኖረው ይገባል፤ ቆርቆሮ ቤት መስራት ይጀምራል፤በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ቆርቆሮ ቤት የግድ ይወደዳል፤በአሁኑ ሰዓት ሰው ሳር ቤት አይሰራም፤ከኢኮኖሚ አንጻር ኢኮኖሚው በእርሻ ምክንያት እነዚህ የሳር መሬቶች ለእርሻ ስለዋሉ ሳር የሚባል ነገር አይገኝም (ቃለመጠይቅ፣05/06/2015ዓ.ም) ፡፡

በቀረበው መረጃ መሰረት የወላይታ አባቶች ከቆርቆሮ ቤት ይልቅ ባህላዊ ሳር ቤትን ይመርጣሉ፤ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ የሳር ቤት አየሩን እንደ ሁኔታው ማመጣጠን ስለሚችል ነው ፡፡ አሁን ላይ የሳር ቤቶች ቁጥር እየተመናመነ ይገኛል ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ የህዝብ ቁጥር መጨመርና የሳር ማሳ ማነስ ነው ፡፡ ሌላው ከኢኮኖሚ አንጻር ሲሆን ይህም ቀደም ሲል የሳር መሬት የነበረው ቦታ ወደ እርሻ መሬትነት በመቀየሩ ነው ፡፡

የቡድን ሁለት ተወያይ የሆኑት አቶ አማኑኤል አይዴ እንደነገሩኝ የወላይታ ባህላዊ የቤት አሰራር ለምቾት ተመራጭ ነው ፡፡ ሽማግሌዎቹ የሚተኙት ጓዳ ውስጥ ነው ፡፡ እድሜ እየጨመረ ሲመጣ ሰውነት ብርድ ስለማይችል እሳት ይነዳል፤ገጠር አካባቢ ደግሞ እሳት እየነደደ ሲመጣ ይሞቃል፤ቆርቆሮ ቤት ውስጥ እሳት ማእድ (ኩሺና) ውስጥ ይነዳል ፡፡

የቡድን አንድ ተወያይ የሆኑት አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ የወላይታ አባቶች ለኑሮ የሚመርጡት ባህላዊ ቤቱን ነው ፡፡ ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ከህዝቡ ጋር በትብብር በባህሉ የተሰራ ስለሆነ ከብርድ ይከላከልልኛል (ቃለመጠይቅ፣05/05/2016 ዓ.ም) ፡፡

ሌላው « አቶ መቶሳል እንደነገሩኝ የአባቴ አይን አባት አለ እድሜው ከ90 ዓመት በላይ የሆነ ሽማግሌ ብዙውን ጊዜ ይታመማል፤እርጅናውም ተጫጭኖታል፤ ገጠር ስሄድ እጠይቀዋለሁ፤ የነበረበትን ሳር ቤት አረጀ ዘመናዊ ቤት ውስጥ መኖር አለብህ ብለው ልጆቼ ናቸው የሰሩልኝ፤እዚህ ቆርቆሮ ቤት ውስጥ መኖር ከጀመርኩበት ቀን ጀምሮ ልጄ በጣም እየደከምኩ ነው፤ብርድም እያስጨነቀኝ ነው ብለው በምሬት የነገሩኝን አጋጣሚ አልረሳም » (ቃለመጠይቅ፣2016ዓ.ም) ፡፡

ከቆርቆሮ ቤት ይልቅ ተመራጭ የሚሆነው የወላይታ ቤት ነው  የወላይታ ሽማግሌዎች የሚመርጡት የወላይታ የባህል ቤትን ነው፤የአሁኑ አይመቻቸውም ፡፡

የቡድን ሁለት ተወያይ የሆኑት አቶ ኢያሱ ገኛበ እንደገለጹት የቆርቆሮ ቤት ከዘመናዊነትና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የመጣ ነው ፡፡ ባህላዊ ቤቱ ከቆርቆሮ የሚለየው አንደኛ በክረምት ወራት ሙቀትን የመያዝ ሀይል አለው ለምሳሌ ቤት ውስጥ እሳት ከነደደ ሙቀቱን አምቆ ይይዛል፤በበጋ ወራት ደግሞ እርጥበትን ወደ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ቤቱ እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል ፡፡

የቡድን አንድ ተወያይ የሆኑት አቶ ወልደማርያም ሲገልጹ ዘመናዊነት ተጽእኖ እየፈጠረበት ቆርቆሮ መስራት ተጀመረ እንጂ በህዝቡ በተለይ በእድሜ በገፉ አባቶች የሚመረጠው ሳር ቤት ነው፤ሳር ቤት ውስጥ ከብቶች ስለሚኖሩ የከብቶች ትንፋሽ ለቤቱ ሙቀት ይሰጣል ፡፡ እሳት ሳር ቤት ውስጥ የሚነድ ሲሆን ቆርቆሮ ቤት እሳት የሚነደው ውጪ ነው ፡፡ የወላይታ ሰው በተለያዩ ምክንያቶች አማራጭ አጥቶ ዘመናዊነት ተጽእኖ እየፈጠረባቸው ወደ ቆርቆሮ ቤት ገቡ እንጂ የሚመርጡት ባህላዊ ቤትን ነው ፡፡

በምልከታ፣ በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት እንደተረጋገጠው በአሁኑ ሰዓት የሚሰሩ ባህላዊ ቤቶች ዘመናዊ ግብአቶችን እንደ ብረት፣ሚስማርና ቆርቆሮ የመሳሰሉትን በማካተት ይሰራሉ ፡፡ ሌላው ባህላዊ የወላይታ ቤቶች ቀደም ሲል ከነበረው የአሰራር መንገድ የተወሰነውን በመለወጥ እንዲሁም ቀሪውን በአዲስ መንገድ መስራታቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል ፡፡ ለዚህ አስረጂ የሆነውና በቅርቡ በኦፋ የተሰራው ባህላዊ ቤት አስረጂዎች እንደሚከተለው ቀርበዋል፡፡

ፎቶ 52፡- የመሰረት ስራ እና በጅምር ያለ ቤት



ምንጭ፡- ኦፋ፣2016ዓ.ም

ከዚህ በታች በፎቶ የቀረበው የጉላንታ ቤት ውጫዊ ገጽታ ከርቀት ሲታይ በሰንሰለት የተከደነ ሆኖ በቅርበት ደርሰው ሲዳስሱት ግን ከድንጋይ መሆኑ የሚረጋገጥበት ነው ፡፡ ይህም የሆነበት ምክንያት ቤቱ ለረጅም ጊዜ ቆይቶ ለትውልድ እንዲተላለፍና ለሙዚየም አገልግሎት እንዲውል ታስቦ የተሰራ እንደሆነ ከመስክ መረጃዎች መረዳት ተችሏል ፡፡

ቤቱ ከስር ባህላዊ ደረጃውን ጠብቆ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ  ክዳኑ በሳርና በሰንበሌጥ ምትክ በድንጋይ የሳር ክዳን መልክ እንዲይዝ የተደረገ ሲሆን ባለቀው ውጫዊው የቤቱ አካል ከላይ ከጉልላቱ ጀምሮ እስከ መሬት ድረስ ፌሮ እንዲዞር ተደርጎ በፌሮው  ዙሪያ ሌላ ቀጭን ፌሮ በየ50ሳ.ሜ ስፋት እየተማገረ ከጉልላቱ ጀምሮ እስከ ግድግዳው ጫፍ የሚደርስ ጠንካራ ወንፊት ሽቦ ተዘረጋ ፡፡ ከሽቦው ወንፊት በታች ከመሬት እስከ ጫፉ ድረስ ብሎኬት ተደርጎበት ከላይ ያለውን የቤቱን ውጫዊ ክፍል ደግሞ ኮንክሪት በማልበስ የቤቱ ስራ ተጠናቋል (ቃለመጠይቅ፣ኢያሱገዳቦ፣መጋቢት/2016ዓ.ም) ፡፡

ከቀረበው መረጃ መረዳት እንደተቻለው የተጠቀሰው ቤት ምንም እንኳን ዘመናዊና ባህላዊውን ተከትሎ የተሰራ ቢሆንም የጥናቱ የትኩረት አቅጣጫ ግን ባህላዊው ቤት ነው ፡፡ ይህ ቤት በዚህ ጥናት

የተካተተው የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤቶች ያሉበትን ደረጃ ለማወቅና ቤቱ ላይ የታዩ ለውጦችንና ቀጥለው የመጡ ነገሮችን ለመግለጽ ነው ።

**ፎቶ53፡- ያለቀ የጉላንታ ቤት ፎቶ ውጫዊ**




ገጽታ

**ፎቶ54፡-በባህላዊና በዘመናዊ ግብዓቶች የተሰራ ቤት**









ምንጭ፡- አፋ፣2014 ዓ.ም

ከላይ ከቀረቡት ፎቶዎች መረዳት እንደተቻለው እነዚህ ቤቶች ባህላዊውንና ዘመናዊውን የቤት አሰራር ተከትለው የተሰሩ ሲሆን ለዚህም ምክንያታቸው ቤቶቹ ጨርሰው እንዳይጠፉና ከትውልድ ትውልድ ሳይሸራረፉ እንዲተላለፉ ታሳቢ ተደርጎ ነው ። ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል የነበረውን

የአሰራር መንገድ፣የመስሪያ ግብአቶች ተከትሎ መሰራቱ ቀጣይነቱን የሚያመለክት ሲሆን ለውጡ ደግሞ ዘመናዊ ግብአቶችን ጥቅም ላይ መዋላቸው እንደሆነ በኦፋ(ገሱባ) በቤቱ ስራ ወቅት በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል ፡፡

የወላይታ ባህላዊ ቤቶች የብሔረሰቡን አካባቢያዊ ምንነት፣ እሴት እና ባህል የሚገልጹ ቢሆንም በጊዜ ሂደት የተወሰኑት የአሰራር ሁኔታዎች ቀጣይነት ሲኖራቸው አንዳንድ ሁኔታዎች ደግሞ በመተው ላይ ናቸው፡፡

**ቀጣይነት፡-** ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት  የብሔረሰቡን ባህል እና እምነት የሚያንጸባርቁ ተምሳሌታዊ የሆኑ የማስዋብ ስራዎች በመስራት፤ የቤት አቀማመጥ ምርጫ ሁኔታ ፤ እንዲሁም አገር እና አካባቢያዊ በቀል የሆኑ ቁሳቁሶችን በመጠቀም ቀጣይነትን እያረጋገጠ ነው፡፡

**ለውጥ፡-** ምንም እንኳን በቤት አሰራር ሂደት ላይ ባህሉን እንዲጠብቅ ጥረት ቢደረግም  የዓለም አንድ መንደር መሆን፤ ዘመናዊነት እንዲሁም ከተማ በአሰራር ሂደት ላይ ተጽእኖ ፈጥረዋል፡፡ ስለሆነም አብዛኛዎቹ ባህላዊ ቤቶች ዘመናዊ የቤት መስሪያ ቁሳቁስ፣ቴክኖሎጂዎችን(ምሳሌ የኤሌትሪክ  እና የውሃና ፍሳሽ ዝርጋታዎች) እንዲሁም የውጪው አለም የቤት አሰራር እየተተገበረ ይገኛል፡፡ ይህም የማህበረሰቡን የአኗኗር ዘይቤ እና የምጣኔ አብት ለውጦች ውጤት መሆኑን ያመለክታል፡፡

በምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት በተገኙ መረጃዎች መሰረት ለለውጡ ምክንያት የሆኑ ጉዳዮች ቀጥለው ቀርበዋል ፡-

I. የህዝብ ቁጥር መጨመርና የሳር ማሳ ማነስ ፤
II. የሳር መሬት የነበረው ቦታ ወደ እርሻ መሬትነት በመቀየሩ፤
III. ዘመናዊነትና ቴክኖሎጂ ባሳደረው ተጽእኖ ፤
IV. ቤቱን ለመገንባት የሚያስፈልገው ወጪ ከፍተኛ መሆን ፤

በምልከታ፣በቃለ መጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት በተገኙ መረጃዎች መሰረት በባህላዊና በዘመናዊ ግብአቶች የተሰሩ ቤቶች ለውጣቸው በከፊል ሲሆን  እነዚህ ቤቶች በሶዶ ዙሪያ፣በሁምቦና ኦፋ ወረዳዎች ይገኛሉ ፡፡ ለውጡ የተጀመረው በ2012 ዓ.ም  ሲሆን ይህም ቤቱ በእሳት አደጋ ቢጎዳ ውስጥ ያሉት ባህላዊ ቁሶች ይጎዳሉ ከሚል ነው (ቃለ መጠይቅ፣ኢሳያስ ፣2014 ዓ.ም) ፡፡

ከላይ በቀረበው መረጃ መሰረት ላይ አቶ ኢያሱ እንደነገሩኝ አሁን ባለው የገበያ ሁኔታ  ሲሚንቶ፣ፌሮና ቆርቆሮ ዋጋቸው በጣም በመጨመሩ የተነሳ ዘመናዊ ግብአቶችን ቤቱ ላይ መጨመሩ አዋጪ ካለመሆኑም ባሻገር ከህዝቡ ኢኮኖሚ ጋር አይመጣጠንም  (ቃለ መጠይቅ፣2015 ዓ.ም) ።

ሌላው የወላይታ ባህላዊ ቤት ተሰርቶ ካለቀ በኋላ የአመጋገብ ስርአቱ ባህሉን ተከትሎ ይከናወናል ። ይሁንና በመስክ ጉብኝት በምልከታ በተገኘው መረጃ መሰረት ከአመጋገብ ስርአቱ ከፊሉ የነበረውን ይዞ የቀጠለ ሲሆን ቀሪው ደግሞ በከፊል ተለውጧል ። ቀጥሎ የቀረቡት ፎቶዎች አስረጂ ናቸው

**ፎቶ 55-ባህላዊ ቤቱ ተሰርቶ ከተጠናቀቀ በኋላ መምህራንና የአስተዳደር ሠራተኞች በጋራ ሲመገቡ**



**ምንጭ፡-** ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 2014ዓ.ም.

**ፎቶ፡-56የምረቃ ስነስርዓት ላይ የሀገር ሽማግሌዎች ባህላዊ ልብስ ሀዴ ለብሰው ንፍሮ በመመገብ ባህላዊ መጠጥ በጋራ ቦርዴ እየጠጡ**



**ምንጭ፡-** ወላይታ ሶዶ ዩኒቨርሲቲ 2014ዓ.ም.

በፎቶ 67 በወላይታ ዩኒቨርሲቲ የተሰራው ባህላዊ ቤት ማለቁን አስመልክቶ በተደረገ የምረቃ ስነስርዓት ላይ የሀገር ሽማግሌዎች ባህላዊ ልብስ ሀዴ ለብሰው ንፍሮ በመመገብና ባህላዊ መጠጥ ቦርዴ እየጠጡ የሚያሳየው ፎቶ በተወሰነ መልኩ ማለትም አለባበሱ፣ ምግቡ፣ባህላዊ መጠጡና የአጠጣጥ ስርአቱ ብቻ ባህሉን ተከትሎ የተከናወነ ቢሆንም ቀሪዎቹ ግን ባህሉን መሰረት አለማድረጋቸውን ያሳያል ፡፡

በአጠቃላይ የለውጥና ቀጣይነት ንድፈ ሐሳብ፣ የወላይታን ባህላዊ ቤት እንደ አንድ ጊዜ ተሰርቶ የተቀመጠ የማይንቀሳቀስ ቁስ ሳይሆን፣ የብሔረሰቡን ታሪክ፣ ማንነት፣ እምነትና ከሌላው አለም ጋር ያለውን መስተጋብር በውስጡ ይዞ የሚጓዝ ህያው ሰነድ አድርጎ ለመተንተን የሚያስችል ጠንካራ የንድፈ ሐሳብ ማዕቀፍ ይሰጣል፡፡

# ምእራፍ ዘጠኝ

# ማጠቃለያ ግኝትና ይሁንታ

## 9.1. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት «የወላይታ ብሔረሰብ ቁሳዊ ባህል ጥናት በባህላዊ የቤት አሰራር ተተኳሪነት» በሚል ርእስ ላይ የተመሰረተ ነው ። በዚህ ርእስ ለመስራት ካነሳሱኝ ምክንያቶች የመጀመሪያው የግል ገጠመኝ፤ሁለተኛው አካዳሚያዊ፤ሦስተኛው በፒኤችዲ ፕሮግራም የወሰድኳቸው ኮርሶችን መነሻ በማድረግ ነው ። የወላይታን ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሂደት መተንተን የሚል ዋና ዓላማ አለው ። የቤት ምንነትን፣ውክልናውን እና የቤት አይነቶችን መግለጽ፤የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት የአሰራር ሥርዓትና ተግባርን ማሳየት፤የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጽን መተርጎም፤የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ጥበብን ለውጥና ቀጣይነት መፈተሽ የሚሉ ዝርዝር ዓላማዎችን በውስጡ ይዟል ። ቤት ምንነቱ፣ ውክልናውና በወላይታ ህዝብ ዘንድ የታወቁ ባህላዊ ቤቶች የትኞቹ ናቸው ? የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ሥርዓትና ተግባር ምን ይመስላል ? የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ውስጣዊና ውጫዊ ቅርጾች ምንን ይወክላሉ? የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ የቤት አሰራር ለውጥና ቀጣይነት ደረጃና መገለጫዎች ምንድናቸው? የሚሉ ጥያቄዎች በጥናቱ ምላሽ አግኝተዋል ።

መረጃ ሰጪዎች በዓላማ ተኮር ናሙና (Purposive sampling) እና ጠቋሚ ናሙና (Snow ball sampling) የናሙና አመራረጥ ስልት ተመርጠዋል።

በጥናቱ ሂደትም ሰላሳ (30) በዕድሜ የገፉ ወንዶች፤ሃያ (20) በዕድሜ የገፉ ሴቶች እና ሃያ 20) ወጣቶችና በመካከለኛ እድሜ ላይ የሚገኙ በድምሩ ሰባ (70) ሰዎች በመረጃ ሰጪነት ተመርጠው ተሳትፈዋል ።

ጥናቱ የተካሄደባቸው ቦታዎች በወላይታ ዞን በኪንዶ ዲዳዬ፣ ሶዶ ዙሪያ፣አፋ፣ሁምቦና ካዎ ኮይሻ በተባሉ አምስት ወረዳዎች እና በስራቸው በሚገኙ አሥር ቀበሌዎች ነው ። እነዚህ ወረዳዎች የተመረጡበት ምክንያት የጥናቱን ዓላማ መሰረት በማድረግ ከሌሎቹ አካባቢዎች በተሻለ ባህላዊ ቤቶቹ እና የባህላዊ ቤት ባለሙያዎች ስለሚገኙባቸው ነው ። ሌላው መልክአምድራዊ አቀማመጣቸውና የአየር ንብረታቸው የተለያየ በመሆኑ ። በተጨማሪም በርዕሰ ጉዳዩ ዙሪያ በእውቀት መረጃ ሊሰጡ የሚችሉ የሀገር

ሽማግሌዎች በአካባቢው እንደሚገኙ በጥቆማ ባገኘሁት መረጃ መሰረት ሲሆን ይህንንም በተለያዩ ጊዜያት በአካባቢዎቹ በነበረኝ የመስክ ቆይታ ማረጋገጥ ችያለሁ ፡፡

ጥናቱ አይነታዊ የምርምር ዘዴን ተከትሎ ተግባራዊ የሆነ ሲሆን የማህበራዊ ትምህርት ንድፈ ሀሳብ የመዋቅራዊ ተግባራዊነት ንድፈ ሀሳብ፤ የሥነ ትዕምርት ንድፈ ሀሳብና የማህበራዊ ግንባታ ንድፈ ሀሳብ ለትንተና ተግባራዊ ሆነዋል፡፡

ጥናቱም በመስክ ላይ ትኩረት ያደረገ በመሆኑ በዋናነት መረጃዎች በምልከታ፣በቃለመጠይቅና በቡድን ተኮር ውይይት እና በንጥል መሰብሰቢያ ዘዴዎች ተሰብስበውና ተተንትነው ቀርበዋል፡፡

ከመስክ በመቅረጸ ድምፅ በቃል የተቀዱት መረጃዎች ከመተርጎማቸው በፊት ወደ ጽሁፍ ተቀይረዋል ፡፡ ጽሁፉ ደግሞ መረጃ ከተሰበሰበበት ወላይትኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ቋንቋ የተቀየረ ሲሆን ይህም በድምጽ የተገለጹት መረጃዎች መልእክታቸው በትክክል እንዲተላለፍ በጥንቃቄ ደጋግሞ በማዳመጥ ለመግለጽ ጥረት ተደርጓል ፡፡

መረጃዎች ከባህሉ ባለቤቶች በአማርኛና በወላይትኛ ቋንቋዎች በተለያዩ ዘዴዎች ተሰብስበዋል ፡፡ ይህም በኪንዶ ዲዳዬ፣ካዎ ኮይሻ፣ኦፋና ሁምቦ ከሚገኙ ሰዎች መረጃዎች በወላይትኛ ቋንቋ የተሰበሰቡ ሲሆን በሶዶ ዙሪያ ከሚኖሩ መረጃ ሰጪዎች ደግሞ በአማርኛ ቋንቋ ተሰብስቧል ፡፡ የትርጉም ሥራው እንደ መረጃዎቹ አይነት ቀጥታ ትርጉምና አውዳዊ ትርጉም ስራ ላይ ውለዋል ፡፡ የትርጉሙ ትክክለኛነት በቋንቋው ባለሙያዎች ታይቷል ፡፡ በሂደቱም መረጃው የተሰበሰበበት የወላይትኛ ቋንቋ ሀሳብ ሳይሸራረፍ ቀርቧል ፡፡ ይሁንና አንዳንድ በአማርኛ አቻ ትርጉም የሌላቸው የወላይትኛ ቃላት በጥናቱ እንደነበረ ተቀምጠዋል ፡፡

### 9.2.ግኝቶች

ጥናቱ ከቦታ ምርጫ፣ ከጨረቃ ዑደት ጋር ካለው ቁርኝት፣ ከብሔረሰቡ ተሳትፎ፣ ከምሰሶ ተከላ ሥርዓት፣ ከግንባታ ቅደም-ተከተል እስከ ቤት ምርቃት ድረስ ያለውን ሂደት በሙሉ በዝርዝር አቅርቧል፡፡

ቤት በወላይታ ባህል "የኑሮ መገለጫ" እና "የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ" መሆኑን፣ እንዲሁም የዙፋ፣ ሚሹዋ፣ ቡራሪያና ጉላንታ የተባሉ አራት የቤት አይነቶች እንዳሉ ከነልዩነታቸው በግልጽ አስቀምጧል፡፡

የብሔረሰቡ ተሳትፎ (ደቦ)፣ በሥራ ወቅት የሚቀርቡ ምግቦችና መጠጦች፣ ባህላዊ ዘፈኖችና ምርቃቶች ማህበራዊ አንድነትን፣ መተጋገዝንና ፍቅርን እንደሚያመለክቱ በሰፊው አብራርቷል ፡፡

የቤቱ ክብ ቅርጽ "ሙሉነትን"፣ የምሰሶው "ወንድነትን"፣ የቱቂያ "ሴትነትን"፣ የውስጥ ክፍፍሉ (ጓዳና ሳሎን) ማህበራዊና ጾታዊ ደንቦችን፣ የቀለማት (ጥቁር፣ ቀይ፣ ቢጫ) ምልክታዊ ትርጉምን በጥልቀት ተርጉሟል ።

የጥናቱን ዝርዝር ዓላማዎችና ትንታኔ መነሻ በማድረግ ከሚከተሉት ዝርዝር ግኝቶች ላይ ለመድረስ ተችሏል ።

በወላይታ ባህል ቤትና ህይወት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ሲሆኑ ህዝቡ ቤትን እንደ ሁሉ ነገሩ ያየዋል ። መጀመሪያ የሚሰሩት ቤት ነው፤ ሁሉም ነገር ከቤት ቀጥሎ ነው ብለው ያምናሉ ። ወንዶች ቤት ሳይሰሩ ለትዳር ሚስት አያጩም ። ኑሮ የሚመሰረተው ቤት ሲኖር ነው ። አንድ ሰው ኑሮ አለው ሲባል ቤት አለው ማለት ነው ። በመሆኑም በወላይታ ቤት በኑሮ ይመሰላል ። ከመስክ የተገኙ መረጃዎች እንዳመለከቱት የወላይታ ባህላዊ ቤቶች አራት አይነት ሲሆኑ እነሱም ዙፋ፣ሚሹዋ፣ቡራሪያና ጉላንታ ሆነው ቤቶቹ ከውጪ ሲታዩ ተመሳሳይ ቢሆኑም በውስጣዊ አሰራራቸው በተለይ ደግሞ የሚጠቀሙት ግብአቶች ፤አመጋገራቸው እንዲሁም ደግሞ የሚሰሩበት ቦታ የአየር ንብረት የተለያየ ነው ። ይህም ሁኔታ ቀጥሎ ቀርቧል ።

የዙፋ ቤት (Zuufa keettaa) በቆላ አካባቢ የሚሰራ ሆኖ ውስጣዊ አሰራሩ በግማሽ ጨረቃ ቅርጽ ነው ። ከታች ከወለሉ ጀምሮ እስከ ላይ ጣሪያ ማዋቀሪያ ድረስ በተመሳሳይ ሁኔታ ይማገራል። የዙፋ ቤት በአብዛኛው የማገሩ ማሰሪያ ሀረግ ነው ። ሁለተኛው ባህላዊ ቤት ሚሹዋ ቤት (Meeshsho keettaa) የሚባለው ሲሆን በቆላና በደጋ አካባቢ ሊሰራ የሚችል ሆኖ ከጣሪያ ወረድ ብሎ አንድ ክፍተት አለው ። አመጋገሩም ከታች እስከ ላይ ጣሪያው (kaaraa) ውቅር ድረስ ጥቅጥቅ ተደርጎ የሚሠራ ነው ። ሦስተኛው የቤት አይነት ቡራሪያ (Buraariyaa keettaa) የሚባለው ሲሆን የውስጥ አመጋገሩ ከወለሉ እስከ ግድግዳው ጫፍ ድረስ በሸምበቆ ወይም ቀጫጭን ማገር (Hamakkaa) ሽብ ሽብ ተደርጎ የሚሰራ ሆኖ ከግድግዳው በላይ እስከጣሪያው ድረስ በዛንዲዳ (zanddidaa) ዘርዘር ተደርጎ ይታሠራል ። የጉላንታ ቤት (Gulanttaa Keettaa) ከውስጥ በኩል አመጋገሩ ከላይ እስከ ታች በ9 ዙር ክፍተት እና በ12 ክንድ ልኬት የሚሠራ ነው ። ውስጣዊ ቅርጹ ዘጠኝ ረድፍ ያለው ሆኖ አሰራሩ የፕላኔት አቀማመጥ ተምሳሌትን መሰረት ያደረገ ነው ።

ቤት ለመስራት በመጀመሪያ አዕምሮአዊ ዝግጅት ይደረጋል ። ሁለተኛው ቤት ልሰራ ነውና አግዙኝ በማለት ለዘመድና ለጓደኛ ይነገራል ። ሦስተኛው ከቦታ መረጣና ሌሎች ጉዳዮች ጋር ተያይዞ ደግሞ ግለሰቡ ቤት ልሰራ ነው በማለት የብሔረሰብ መሪዎች (Debbushsha fogiyageta) የተባሉትን ሰዎች ፍቃድ ይጠይቃል ። ሌላው የወላይታ ባህላዊ ቤት ከጨረቃ ዑደት ጋር ቁርኝት ስላለው በቅድሚያ ጨረቃ

የምትወጣበት ቀን መታወቅ አለበት ። ይህ ካልሆነ በባህሉ እንጨት መቁረጥና ሌሎች ግብአቶችን መሰብሰብ አይፈቀድም ። ምክንያቱም የጨረቃ ጉዳይ በባህሉ ቤት ለመስራት ከባህላዊ ግዴታዎች መካከል አንዱ መስፈርት ነው ።

በባህሉ ደንብ መሰረት በእነዚህ ስድስት ቀናት ውስጥ ለቤት መስሪያ የሚሆኑ የዛፍ እንጨቶችና ሌሎች ግብአቶች ቢቆረጡ በጥንጣን ይበላሉ፤ይበሰብሳሉ ተብሎ ስለሚታመን በእነዚህ ቀናት ለቤት መስሪያ የሚሆኑ ግብአቶች መቁረጥ፤ማዘጋጀትና ቤት መስራት በባህሉ አይፈቀድም ።

በወላይታ የባህላዊ ቤት አሰራር ቅደም ተከተልን በተመለከተ ቦታ መረጣ፣ቦታ ድልደላ የጣሪያ ሥራ፣ምሰሶ ማቆም፣በር ወይም መቃን ማዋቀር፣የቤት ክዳን ስራ ያሉ መሰረታዊ ቅደም ተከተሎች አሉት ። ምሰሶ በባህሉትልቅ ክብር ይሰጠዋል ። ከዚህም የተነሳ በቤት ሰሪው ባለቤት ጓሮ ለምሰሶ የሚሆን እንጨት ከሌለ ከጎረቤት ወይም ከዘመድ ማሳ በነጻ መውሰድ ይችላል ። እንጨቱን ከጎረቤቱ ጓሮ ካገኘ ልብስ ያለብሰዋል ። ጎረቤቱም ‹‹በንጉስ ቤት ልብስ ልበስ፤ ልጅህም ይልበስ››በማለት ይመርቀዋል ። በባህሉ ለምሰሶ የሚሆን እንጨት የሰጠውም ሆነ የተቀበለው በህዝቡ ዘንድ ክብርና ሙገሳን የሚያገኙ ሲሆን አንዱ በአንዱ ላይ ክፉ ነገር አያደርጉም ። ምክንያቱም ምሰሶ ስለተቀባበሉ ግፍ ከተሰራ ይደርሳል ተብሎ ይታመናል ።
በባህሉ ለምሰሶ የሚመረጡ እንጨቶች ጥቁር እንጨት፤ዋንዛና ከበረሃ የሚገኙ ጉጉንታ (Guuganttaa) የተባሉት ናቸው ። እነዚህ እንጨቶች የተመረጡበት ምክንያት ተስማሚና ንጹህ ስለሆኑ ነው ። በተጨማሪ በቤት ውስጥ ፍቅርና በረከት ያመጣሉ ተብለው ስለሚታመንባቸው ነው ። ሌላው ብሳና እና ብርብራ የተባሉ የእንጨት አይነቶች ደግሞ መቅሰፍት ያመጣሉ ተብሎ ስለሚታመን ለምሰሶ አይመረጡም ። በተጨማሪ ዋላሴኖ የሚባለው የእንጨት አይነት ደግሞ ለምሰሶ ከቆመ አብዛኛውን ጊዜ ሰው ይጣላል ተብሎ ስለሚታሰብ አይመረጥም ።

በወላይታ ባህል በመጀመሪያ ወንድም፣እህት፣እናትና አባት ያልሞቱበት ወንድ ልጅ ለምሰሶው በተቆፈረው ጉርጓድ አጠገብ እንዲቆም ይደረግና አንድ ቅል ቦርዴ ይጨመራል። የዚህ ምክንያት በባልና ሚስቱ መካከል ፍቅር እንዲኖራቸው ታስቦ ሲሆን በባህሉ ቤቱ አልቆ የቅል ቦርዴ በጋራ ይጠጣል። ይህ በብሔረሰቡ የፍቅር መግለጫ ነው ተብሎ ይታሰባል። ቤቱ የማይደርቅ ኢኮኖሚ እንዲኖረው ደግሞ ጎርጣ የተባለ የሳር አይነት ይጨመራል። በቤቱ ከብት እንዲዋለድበት የጥጃ አዛባ ይጨመራል። ገብሱ እህል የሚያበረክት እንዲሆን፤በማሳ ላይ የሚበቅሉ የእህል ዘሮች ምርታማ ይሆናሉ ተብሎ ስለሚታሰብ ጥሬ ገብስ ይጨመራል። ኑሯቸውን ጣፋጭ ያደርጋል ተብሎ ስለሚታሰብ ጨው ይገባል። ከነዚህ በተጨማሪ የኮርማ ደም፣የጠቦትደም ፣የበግናየበሬ ኮርማ ደም በባህሉ የቃልኪዳን የመሀላ

የመልካምነገርመገለጫና የህይወት ቀጣይነት ማመላከቻ ተደርጎ ስለሚወሰድና ቤቱእርጥብ እንዲሆን በተቆፈረው ጉድጓድ ውስጥ ይጨመራል ፡፡

በወላይታ ባህል ምሰሶ ከማህበራዊ ክብር ፣ከመንጻት ጋር ፣ከትውፊታዊ እምነት እና ከሥርዓተጾታ ጋር የሚገናኝ ሲሆን ይህም ቀጥሎ ቀርቧል ፡፡

በወላይታ ባህል ምሰሶ ከማህበራዊ ክብር ጋር ይገናኛል፣ምሰሶን ማንም ሰው አይነትተውም፣ ምሰሶ እንዲነትቱ የሚፈቀድላቸው ለማህበራዊ ክብር የበቁ ወንዶች ናቸው ፡፡ በባህሉ ከማህበራዊ ክብር መገለጫዎች አንዱ ግርዛት በመሆኑ ያልተገረዙ ወንዶች የምሰሶውን እንጨት እንዲነትቱ በባህሉ አይፈቀድላቸውም ፡፡

ምሰሶ ከመንጻት ጋር የተያያዘ ሲሆን ይህም በባህሉ ምሰሶ የትውፊታዊ እምነት ማሳያ ተደርጎ ስለሚታሰብ ምሰሶ የሚያቆሙ ሰዎች ቀደም ብለው ክፉ ነገር አድርገው ምሰሶውን ለማገዝ በሚሞክሩበት ጊዜ ምሰሶው ለማቆም አስቸጋሪ ይሆናል ፡፡ በዚህም ሰዎቹ ሌላ ቦታ የፈጸሙትን በደል አጠገባቸው ለሚገኙ ሰዎች ተናግረው እራሳቸውን ያጋልጣሉ፡፡ ከዚህ በኋላ ያለችግር ምሰሶውን ያቆማሉ፡፡

ምሰሶ ከትውፊታዊ እምነት ጋር የተያያዘ ስለሆነ ልጅ ከሞተ፣ከብት ከሞተ፣ድንገተኛውርጃ የሚያጋጥም ከሆነ ባህላዊ ቤቱ ሲሰራ በምሰሶው ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች ኀይል ተብሎ ስለሚታሰብ አልባናኖ፣ ጃልቦሶና ኪቶሳ ወደ ተባሉ ጠንቋይ ቤቶች በመሄድ ከብት አርደው አንጀቱን እያነበቡና የጥንቆላ ጠጠር እየለቀሙ ምሰሶው ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች መጉደላቸውን ያረጋግጣሉ፡፡ በጎደሉት ነገሮች የተነሳ ኑሯቸው ይጎላል፣ክፉ ነገር ይደርስባቸዋል ተብሎ ስለሚታሰብ ለዚህ ማርከሻ እንዲሆን ምሰሶውን በጎን በመቆፈር የበግ ደምና የበግ በጠጥ ይጨመራሉ፡፡ ከዚህ በኋላ የተወለዱ ልጆች አይሞቱም፣ከብቶችአይሞቱምተብሎይታሰባል፡፡

ምሰሶ ከሥርዓተጾታ ጋር የሚገናኝ ሆኖ ከወንድ ጾታጋር በባህሉ ወንድ ልጅ ሲወለድ ምሰሶ ወልደሃል፣አባት ሲሞት ምሰሶው ወደቀ የሚባል ሲሆን ሴት ደግሞ ቱቂያ ተብሎ በሚጠራውና ምሰሶውን ደግፎ በሚቆመው እንጨት ትመሰላለች፡፡ከዚህ በተጨማሪ ምሰሶው ጣሪያውን በስቶ ማለፉ ደግሞ የሴትና ወንድ ጾታዊ ግንኙነትን የሚገልጽ እንደሆነ ነው የተገለጸው፡፡

በአጠቃላይ በወላይታ ብሔረሰብ የምሰሶ ስራ ከማህበራዊ ክብር፣ ከትውፊታዊ እምነት ከሥርዓተ ጾታ ጋር፣ መቆሚያው ጉርጓድ ውስጥ ከሚገቡ ነገሮች ጋር የሚገናኝ ሲሆን በዚህም የተለያዩ ፍቺዎች እንዳሉት ከመስክ ከተገኙት መረጃዎች መረዳት ተችሏል፡፡

በብሔረሰቡ ቤት በሚሰራበት ወቅት የህብረተሰብ ተጠሪዎች፣አባቶች፣እናቶች፣ ወጣቶች፣የቤተሰቡ አባላት፣ ጎረቤቶች፣ዘመዶችና የአካባቢው ህዝብ ቀደም ሲል ባላቸው ድርሻ የተለያዩ ስራዎችን በመስራት የቤቱን ባለቤቶች ያግዛሉ።

በወላይታ ባህል ባህላዊ ቤት ሲሰራ የተለያዩ ምግቦች ይዘጋጃል ፡፡ እነዚህም እንደስራው አይነት የሚሰሩ ሲሆን ለምሳሌ የምሰሶውን ጫፍ ለሚጠርቡ ባለሙያዎች ፤ የበር ጉበንና መግቢያውን ለሚያስውቡ ፤ ግድግዳ ለሚሰሩ፣ጣሪያ ለሚሰሩ ባለሙያዎች ባጭራ፣ አይብ በሥጋ ሙቾ፣ቡልአ፣ፋጫታ የተባሉ የባህል ምግቦች ይዘጋጃሉ ፡፡ ግድግዳ ለሚሰሩ ደግሞ ከአደንጓሬና ከበቆሎ ንፍሮ ቂጣ፣ይዘጋጃል ፡፡ እንዲሁም ፍሬ ቡና፤ ቅጠል ቡና ይፈላል ፡፡ እነዚህን ምግቦች የሚያሰናዳው ባለቤቱ ሲሆን ጎረቤቶችም እንደቅርበታቸው መጠን ምግብ ሰርተው ያመጣሉ ፡፡ ምግቡ አንድ ወጥ በሆነ እርጥብ ኮባ ላይ ይቀርባል የኮባው እርጥብ መሆን ሁሉ መልካም ይሁን፣ቤቱ እርጥብ ይሁን፤ዘመኑ እርጥብ ይሁን የሚል ትርጉም አላቸው ፡፡ የኮባው ወጥ መሆን የህዝቡን አንድነትና እርስ በርስ ተደጋግፎ መኖርን ይገልጻል ፡፡ ሌላው ክብ ሰርተው መቀመጣቸው ፤ በጋራ መመገባቸው ፤ በጋራ በአንድ ጽዋ መጠጫ ለሁለት መጠጣታቸው ፍቅርን፤ ወንድማማችነትን፤ አንድነትንና ህብረትን  የሚገልጽ ነው፡፡

በወላይታ ባህል መሰረቱ ሲቆፈር፤ ለግድግዳ የሚሆን እንጨት ሲፈለጥ፤ግድግዳው ሲሰራ፤በጣሪያ ስራ ወቅት፤ምሰሶ ተቆርጦ ሲመጣ፤ምሰሶ ሲቆም ፤ቤቱ አልቆ ሲገቡ፤ ምሳሌያዊ አነጋገሮች ፤ባህላዊ ዘፈኖችና ምርቃቶች ይቀርባሉ ፡፡ እነዚህም ህዝቡ ቶሎ ቶሎ ሰርተው እንዲጨርሱ ከማድረግ ባሻገር ኃይልና ብርታት እንዲያገኙ ያግዛቸዋል ፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል ለብሔረሰቡ በተለያዩ ነገሮች ውለታ የዋሉላቸውን ሰዎች በዘፈኖቹ ያስታውሳሉ፤ ያወድሳሉ ፡፡ ለምሳሌ ቤትን ከበረከትና ከቅርስ ጋር አያይዘው Keettan kehay deiyaga naw፤ goban minjay deiyaga naw ይላሉ ፡፡ ትርጓሜውም፣ ማለት በቤት ውስጥ ትልቅ በረከት ያለው ሰው የወለደህ goban minjay deiyaga naw ማለት ደግሞ በዕቃ ማስቀመጫ (መደበቂያ) ውስጥ የተለያዩ ቅርሶች ያሉህ እንደ ማለት ነው Keettan kehay deiyaga naw

በወላይታ ብሔረሰብ የቤት አሰራር እውቀቱ አባቶች ልጆችን አስከትለው በመሄድ ቀለል ያሉ ስራዎችን እንደ ወፍቾና መለስተኛ ማገሮችን እንዲያመጡ በማድረግ ድርሻቸውን እየሰሩ እንዲለምዱ ያደርጓቸዋል በተጨማሪም ተከትለው ሄደው ወፍቾ ከማምጣት ባሻገር ቤቱ እንዴት እንደሚሰራ ያያሉ ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ወላጆችን ተከትለው የሚመጡ ህጻናት ያሉ ሲሆን እነዚህም ማሱዋ (Masuwa) ይባላሉ ፡፡ ህጻናት ለአካለ መጠን እስከሚደርሱ ድረስ ወላጆቻቸውን ተከትለው በመሄድ ቤት እንዴት እንደሚሰራ ያያሉ፤ይለምዳሉ ፡፡ ወላጆች ወጣቶች ቤት እንዴት እንደሚሰራ እንዲያዩ እያደረጉ የቤት አሰራር ጥበቡን ለትውልድ ያስተላልፋሉ ማለት ነው ፡፡ አባት ወደ ቤቱ ስራ ሲሄድ ልጆችን አስከትሎ ይሄዳል ፡፡

ውጫዊ ቅርጹን በተመለከተ ቤቶቹ ከሞላ ጎደል ተመሳሳይ ናቸው ፡፡ የወላይታ ብሔረሰብ ባህላዊ ቤት ቅርጽ ክብ ሲሆን ከውጭ በኩል ሲታይ ሁለት አይነት የሳር አከዳደን አለው ፡፡ ይህም ሙሉ በሙሉ ከላይ እስከ ታች ወጥ በሆነ መልኩ በሳር የተከደነና ከበሩ መግቢያ ጀምሮ ጎን ዙሪያው ድረስ የተከረከመ አከዳደን ያለው ነው፡፡

የወላይታ ባህላዊ ቤት አቀማመጥን በተመለከተ ባህላዊ ቤቱ ክብ ቅርጽ ያለው ሲሆን ሁለት አይነት የአከዳደን ስልት አለው ይህም ከምሰሶ ጀምሮ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ ሳር የለበሰና ከግማሽ ጀምሮ የሚለብስ ማለት ነው ፡፡

ውስጣዊ ቅርጹን በተመለከተ የመጀመሪያው ትልቁ ክፍፍል ሳሎንና ጓዳ በቅርጮ(ሳጠራ) ለሁለት የሚከፈል ሲሆን ጓዳ (Qoliuwaa) የሴቶች ሲሆን ሳሎን (Wuyigiiyaa) ደግሞ የወንዶች ነው ፡፡ ከምሰሶ በታች ያለው የከብቶች ነው ፡፡ ከከብቶች ማደሪያ ጋር ተያይዞ የልጆች መኝታ ይገኛል ፡፡ ከከብቶች በላይ እንደ ፎቅ ቅርጽ አይነት ያለው የትኛውንም ቁሳቁስ ለማስቀመጥ የሚጠቀሙበት ሻኩዋ አለው ፡፡ ሌላው ጓዳ ውስጥ የምግብ መስሪያ ጮጬ ይተከላል ፡፡ በጓዳ በኩል ሙሽራዋ ከሰርግ በፊት የምትቆየው ጓዳ ውስጥ ነው ፡፡ የሙሽራ የመውጪያ መግቢያ በር ያለው ጓዳ ውስጥ ነው ፡፡

በተጨማሪ በባህሉ በአጋጣሚ በባልና ሚስት መካከል ፀብ ቢፈጠር ባል ወደ ሚስት ክፍል አይገባም ገብቶ ሚስቱን ከመታ እንደ ነውር ስለሚቆጠር ደካማ ተደርጎ ይወሰዳል፤ በህዝቡ ዘንድም እንደ ዝቅተኛ ሰው ይታያል ፡፡

የወላይታ ባህላዊ ቤት ክብ ነው ፡፡ በባህሉ ክብ ነገር ከብዙ ነገሮች ጋር የሚገናኝ ሆኖ የተለያዩ ትርጓሜዎች አሉት ፡፡ ባባህሉ ክብ ነገር ሙሉ ነው ተብሎ ስለሚታሰብ የቤቱም ክብነት ከሙሉነት ጋር የተያያዘ ነው በቤቱ ውስጥ ለመገልገያነት የሚውሉ ቁሶች ክብ መሆናቸው ከቤቱ ቅርጽና ከሙሉነት ጋር የተገናኘ ነው ፡፡ በባህሉ ክብ ወይም ሙሉ ቁጥር ያልሆነ በረከት የለውም የመጥፎ ነገር ምሳሌ ነው ተብሎ እንደሚወሰድ ከመስክ የተገኙ መረጃዎች አመላክተዋል ፡፡

ባህላዊ ቤቶችን ለማስዋብ እና ለማሳመር ቀለማት ጉልህ ሚና እንዳላቸው ከመረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል ከቀለማትም ጎልተው የሚታዩት ጥቁር፣ ቢጫና ቀይ መሆናቸውን በምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል ፡፡ ይህንንም በአካባቢው የሚገኙ ግብአቶችን በመጠቀም ያዘጋጃሉ፡፡ በነዚህ ቀለሞች የባህላዊ ቤቱ ግራና ቀኝ መግቢያ በር ላይ የሚቆሙ እንጨቶችና የበሩ ድምድማትን በመቀባት የቤቱን ውበት ያሳምራሉ፡፡

እነዚህ ቀለሞች ከብሔሩ ህይወት፣ከማንነቱና ከታሪኩ ጋር የተያያዙ ሆነው ህዝቡ በራሱ እውቀትና ጥበብ የሚሰራቸው ናቸው ፡፡ ከነዚህ ቀለማት የመጀመሪያውን ቦታ የሚይዘው ጥቁር ሲሆን ይህም ብሔረሰቡ

እራሱን የሚያይበት ደማችን ጥቁር ነው(ሱታይ ካሬታ) ጥቁር ወላይታ በማለት እራሱን የሚገልጽበት ነው ። ሌላው በባህሉ ጥቁር መልክን ብቻ ሳይሆን የህዝቡን ቁጡነት፣ደመ መራራነቱን ለመግለጽ የሚውል ሲሆን ቀዩ ቀለም ደግሞ የጀግንነት፣የጠረኝነትና የወራሪነት መገለጫ ነው ። ቢጫው ቀለም ደግሞ የመስፋፋት ተምሳሌት ተደርጎ ይወሰዳል ።

ከውበት ጋር ተያይዞ በቤቱ የውስጠኛው ክፍል ለቤቱ ውበት ከሚሰጡ ነገሮች መካከል ሳሎንና ጓዳ በሚለይበት ሳጠራ አናት ላይ ለተለያየ አገልግሎት የሚውሉ ባህላዊ የቤት ውስጥ ቁሶች ይሰቀላሉ ። እነዚህ የተለያዩ ቁሶች ለቤቱ ውበት ይሰጣሉ ። በዚህም ወደ ቤት ሲገባ መጀመሪያ ላይ የሰውን አይን ከመሳብ ባሻገር ቤቱን ያሳምራሉ ። ሌላው በባህሉ ሳሎንና ጓዳው የሚከፈልበት ሳጠራ ባዶውን አይቆምም

በባህሉ በአሁኑ ሰዓት ሳር ቤቶቹ ቁጥራቸው እየቀነሰ ወደ ቆርቆሮ ቤቶች እየተቀየሩ ነው። ይሁንና ቆርቆሮ ቤቶቹ ሳር ቤቶቹ ውስጥ ያሉ ቁሶችን ይዘው እንደቀጠሉ ከመስክ ከተገኙ መረጃዎች ማረጋገጥ ተችሏል ። ሳር ቤት ባህላዊውን አሰራር ተከትሎ የተሰራ ቢሆንም ባህላዊ ቤቱ ውስጥ መካተት የሌለበትን የጭቃ ምርግ ይዟል። ይህ ደግሞ የሳር ቤቱን ለውጥ ያመለክታል ።

የቆርቆሮ ቤት ከዘመናዊነትና ከቴክኖሎጂ ጋር ተያይዞ የመጣ ሲሆን በህዝቡ ዘንድ የሚወደደው ግን ባህላዊው ሳር ቤት ነው ። ለዚህ ምክንያቱ ባህላዊ ቤቱ በክረምት ሙቀትን የመያዝ ሀይል ሲኖረው በበጋ ወራት ደግሞ እርጥበት ወደ ውስጥ እንዲገባ በማድረግ ቤቱ እንዲቀዘቅዝ ያደርጋል ። ከዚህ በተጨማሪ ሳር ቤቱ ውስጥ ከሚነደው እሳት የሚወጣው ጪስ ጓሮ ውስጥ ላሉ ተክሎች ጠቀሜታ እንዳለው ነው የተገለጸው ።

ሌላው የቤቱ አጀማመር የባህላዊውን ስልትና ግብአቶችን በመጠቀም የተሰራ ነው ። ከቦታ መረጣ ጀምሮ የግድግዳ እንጨት፣የምሰሶ እንጨት፣የጣሪያ ስራ፣የቤት ክዳን ወይም ሳር ማልበስ ድረስ ባህላዊውን ግብአትና አሰራር ተከትለው የተከናወኑ ሲሆን ከሳር ክዳን በኋላ ከስር ቀጫጭን የፌሮ ብረት፣አርማታና ቆርቆሮ ተደርጎባቸዋል ። ለዚህ ምክንያቱ ደግሞ ቤቱ የወላይታ ባህላዊ ቁሶች የሚገኙበት ሙዚየም በመሆኑ በሳር ብቻ ከተሰራ ድንገት ቤቱ በእሳት ቢቃጠል ውስጥ የሚገኙት ቅርሶች ተጎድተው ይጠፋሉ ከሚል ስጋት የተነሳ ዘመናዊ ግብአቶች አገልግሎት ላይ ውለዋል ።

ለጥናት በተመረጡት አካባቢዎች ከተገኙት ቤቶች መካከል የተወሰኑት ባህላዊውንና ዘመናዊውን የቤት አሰራር ተከትለው የተሰሩ ሲሆን ለዚህም ምክንያታቸው ቤቶቹ ጨርሰው እንዳይጠፉና ከትውልድ ትውልድ ሳይሸራረፉ እንዲተላለፉ ታሳቢ ተደርጎ እንደሆነ መረጃ ሰጪዎች ይገልጻሉ ።

ከዚህ በተጨማሪ ቀደም ሲል የነበረውን የአሰራር መንገድ፣የመስሪያ ግብአቶች ተከትሎ መሰራቱ ቀጣይነቱን የሚያመለክት ሲሆን ለውጡ ደግሞ ዘመናዊ ግብአቶችን ጥቅም ላይ መደረጉ እንደሆነ በኦፋ(ገሱባ) በቤቱ ስራ ወቅት በተደረገው ምልከታ ማረጋገጥ ተችሏል፡፡

➢ ከላይ የቀረቡት ግኝቶች ጠቅለል ተደርገው እንደሚከተለው ቀርበዋል ፡፡

- በአጠቃላይ በወላይታ ባህል ቤትና ህይወት/ ማንነት የማይነጣጠሉ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታዎች ናቸው ፡፡

